ከተማሩት ከተማርን

A Suffer from Intelligence

የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ!!!

MODERNITY THE MODERN DISEASE

በናትናኤል ኃይሌ

ህዳር 2010/2017

Contact: 0934265129
Email address: nathimanhailekab@gmai.com

ማውጫ

ምዕራፍ አንድ 6

በውሸት የተሞላ ሕይወት 6

ማሳሰቢያ 7

ቅድመ ምዕራፍ አንድ 8

ማርና ወተቴ 9

ደረጃው፡ ወደ ላይ ወይስ ወደ ታች? 20

አዲሱ እኔ 25

ስምረት 36

ሌላኛው የሕይወቴ ምዕራፍ፡ ጭንቀት፣ ውድቀት፣ እንግልት፣ ሞት፣... ቃላት ያጣሁለት፣ መከራ፡፡ 45

ምዕራፍ ሁለት 88

አስተማሪ የታሪክ ክፍሎች 88

ቅድመ ምዕራፍ ሁለት 89

ስልጣኔ መቼ ጀመረ? 89

ቅድመ ስልጣኔ 89

ከክርስቶስ ልደት ወዲህ 93

የክርስትያን ቲዮሎጂ 95

የማርቲን ሉተር ሪፎርሜሽን ትሩፋቶች 97

ህይወት በሬኔሳንስና በሪፎርሜሽን ዘመን 104

ምዕራፍ ሶስት 110

እውነተኛው እውነት 110

ቅድመ ምዕራፍ ሶስት 112

እውነቱ ከመሰረቱ 114

የዘመናችን ነቢያትና አስተማሪዎች 118

የዚህ ዘመን ክርስትያን እንደገና ሊያጤናቸውና ሊያስተውላቸው ከሚገባው እውነትና ህያው፣ ህይወት ከሆነው የእግዚአብሔር ቃል ጥቅሶች መካከል፡ 120

ክርስትናና ታሪክ 139

ከድጡ ወደ ማጡ 141

ድንገት ያነበብኩት/WHO IS THE REAL CHRIST (እውነተኛው ክርስቶስ ማን ነው?) 148

በእውነት ስልጣኔ ምንድነው? 151

የጥላሁን ጉግሳ ስህተት በአዲስ አመት 158
ምሳሌና መክብብ 162
ማጠቃለያ 178

ምዕራፍ አንድ

በውሸት የተሞላ ሕይወት

CHAPTER ONE

A LIFE FULL OF LIES

ማሳሰቢያ

ሁላችንም በደግታቸው የምናስታውሳቸው፣ በክፋታቸው የማንረሳቸው፣ ከክፉነት ወደ መልካምነት፣ ከጓደኝነት ወደ ጠላትነት የተቀየሩብን ሰዎች እኛነታችንን በተሸከመው አዕምሮአችን ውስጥ አዝለን እንገኛለን፡፡ በደግነታችን የሚያስታውሱን፣ በክፋታችን የማይረሱን፣ በተሞላላጭ ባህርያችን ስንቱን ግራ እንዲጋባን ምን ያህሎቻችን ራሳችንን እንደምንገመግም እኔ አላውቅም፡፡ በርግጥ ከመልካምነት ባለፈ፡፡ ሁሉም መልካም እንደ ሆነ ያስባል፡፡ ቀይ ክፋት ሰርቶ እንኳን ክፉነቱን ከመቀበል ለምን እንደ ሰራው ካለም ምክንያት በማቅረብ፣ ከሌለም በመፍጠር ክፉ እንዳልሆነ ራሱን ለማሳመን ይሞክራል፡፡ እንሞክራለን፡፡ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በህይወቴ ውስጥ ያለፉ ብዙ ሰዎችን እጠቅሳለሁ፡፡ ከተጠቀሱት ሰዎች የሚደሰቱ፣ የሚያዝኑ፣ የሚናደዱ፣ እንደሚኖሩ እርግጠኛ ነኝ፡፡

ውድ አንባቢ፡ እኔ ግን ይሄን መጽሐፍ የጻፍኩት የማንም ማስታወሻ እንዲሆን ወይም ለማንም ያለኝን ፍቅር ለመግለጽ ወይም ለማንም ያለኝን ጥላቻ ለመግለጽ ወይም ማንንም ለማሞገስ ወይም ማንንም ለማዋረድ ወይም ማንንም ለማዳነቅ ወይም ማንንም ለማናናቅ ወይም ማንንም ለመሳደብ ወይም ማንንም ለመበቀል ወይም እራሴን ለማጋነን ወይም ያስከፋኋቸው ወይም ያስቀየምኳቸው ወይም ያናደድኳቸው ሰዎች ይሄን መጽሐፍ አንብበው ይቅርታ እንዲያረጉልኝ አስቤ...ሰውን ለማስከፋትና ለማስደሰት ሳይሆን አንባቢ የሚማረው ነገር እንደሚኖር ስላመንኩ ነው የጻፍኩት፡፡

በህይወቴ ውስጥ ያለፉትን ሰዎች በዚህ መጽሐፍ ምክንያት ሊገኙ የሚችሉትን ስለነርሱ መልካም ነገር በመጻፌ የሚሰማቸውን ደስታም ሆነ ስለነርሱ መጥፎ ነገር በመጻፌ የሚሰማቸውን ንዴት፣ ወይም የተለያዩ በዚህ መጽሐፍ ምክንያት ሊመጡ የሚችሉትን የተሳታፊ ሰዎችን ግብረ መልሶችን ጨርሼ ማጥፋት ባልችልም ለመቀነስ ስል በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያካተትኳቸውን የህይወቴና የዚህ መጽሐፍ ክፍል የሆኑትን ጓደኞቼን፣ ጎረቤቶቼን፣ የትኞቹንም እዚህ መጽሐፍ ላይ ያካተትኳቸውን ሰዎች በእውነተኛ ስማቸው ሳይሆን በተተኪ ስም እንደ ገጸ-ባህርያት እንዲሆኑ አድርጌያቸዋለሁ፡፡ አዎ እንደ ልቦለድ ገጸ-ባህርያት፡፡ ገጸ-ባህርያት ደራሲው ማስተላለፍ የፈለገውን ሀሳብ ሊያስተላልፍባቸውና ትርጉም በሚሰጥ መልኩ እውነተኛውን አለም ለማንጸባረቅ የሚፈጥራቸው በእውነት የሌሉ ምናባውያን ፈጠራዎች ናቸው፡፡ ይሄን መጽሐፍ የሚያነብ ማንኛውም ሰውም እኔን ባለታሪኩን ጨምሮ ሌሎቹን ሰዎች እንደ ልቦለድ ገጸ-ባህርያት እንጂ በእውነተኛው አለም ሊያገኛቸው እንደሚችል እንደ እውነተኛ ሰዎች ወይም እንደ ፊልም ተዋናዮች እንኳን አይያቸው፡፡ ይሄን ስል ግን ታሪኩ ልቦለድ ወይም ፈጠራ ነው ለማለት አይደለም፡፡

ውድ አንባቢ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተጻፈ የትኛውም ነገር በጊዜው ሳስበው ስለነበረ እንጂ ይሄን ጽሁፍ በምጽፍበት ጊዜ ያለኝ አቋሜ ስለሆነ አይደለም፡፡ ለምሳሌ 9ኛ ክፍል ላይ “ከፊልም በላይ የሚያዝናና ምን ነገር አለ?” ስል ያኔ ሳስበው የነበረ ነገር ስለሆነና “ያኔ ከፊልም በላይ የሚያዝናና ምን ነገር አለ ብዬ አስብኩኝ” ብዬ መጻፍ ስለደበረኝ እንጂ የዚያ ጊዜ ሀሳቤ ብቻ ነው፡፡ ይሄ ማለት ግን ዛሬን የዘለቀ የድሮ አስተሳሰብ የለኝም ማለትም አይደለም፡፡

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ያሉ ሀሳቦች ደግሞ የእኔና የራሴ አረዳድና አመለካከቶች እንጂ የማንም የሁለተኛ ወይም የሶስተኛ ሰው አይደሉም፡፡ እኔ እንደተረዳሁት ብቻ፡፡ ከአንድ ሰው ጋር ስናወራ ሰውየው እየሳቀ ቢሆን፣ እያስመሰለ ሊሆን ይችላል፣ እውነቱንም ሊሆን ይችላል፣ የተንኮል ሳቅም ሊሆን ይችላል... ታዲያ አንተ የምትረዳው በአንድ መንገድ ነው፡፡ ሰውየው ስሜቱን የሚረዳበት መንገድ ይኖራል፣ አንተ የምትረዳበት ሌላ መንገድ ይኖራል፡፡ ስለዚህ የኔ አረዳድ ትክክል ሆነም አልሆነ እኔ እንደተረዳሁት ከራሴ አቅጣጫ የተጻፈ ነው፡፡

ቅድመ ምዕራፍ አንድ

ይሄ ምዕራፍ የኔ ታሪክ ነው፡፡ ለኔ ጥቅም የጻፍኩት ግን አይደለም፡፡ ለትውልድ ጥቅም እንጂ፡፡ እኔ እንደሆንኩ፣ ብጎዳበት እንጂ አልጠቀምበትም፡፡

ሰው አንተን መሆን እንደሚፈልግ ነግሮህ ያውቃል? ማንም እገሌን በሆንኩ የማይል ሰው የለም፡፡ አንተን በሆንኩ ብሎ ለሰውየው ለራሱ መንገር ግን በጣም የተለመደ ነገር አይደለም፡፡ በጣም ከፍተኛ አድናቆት ነውና፡፡ እንኳንም አንተን አልሆንኩ ተብለህስ ታውቃለህ? እገሌን ከመሆን መሞት ይሻላል ማለት ያለ ነገር ነው፡፡ እገሌን ራሱን ግን እንኳንም አንተን አልሆንኩ ማለት የተለመደ ነገር አይደለም፡፡ ምን ቢሆን ነው እንደዚያ የምትለው?

ሁሌም እናስባለን፡፡ አዕምሮአችን ጤናማ ባይሆን እንኳን እናስባለን፡፡ ሰው አዕምሮውን ሲታመም አስተሳሰቡ ተዛባ ማለት እንጂ ማሰብ አቆመ የሚያስብል የአዕምሮ በሽታ የለም፡፡ አንድ ጓደኛዬ በግርምት እንዳለው ከተወለድንበት ቀን ጀምሮ ማሰብ ማቆም አንችልም፡፡ ነጩ ወረቀት ይጻፍበት ይጀምራል፡፡ ሲጻፍበት ይኖርናም ከተጻፈበት፣ ከተጻፈበት በኋላ፣ እስከ እለተ ሞታችን ይጻፍበታል፡፡ ተኝተን እንኳ ይጻፍበታል፡፡ ህልም፣ ደስ ብሎህ ስትተኛና ተከፍተህ ስትተኛ የሚኖርህ የእንቅልፍ ጣዕም አንድ አለመሆናቸው እንቅልፍ ከዚህ የ"የማሰብ" ጉዳይ ውጪ እንዳልሆነ ያስረዳናል፡፡
ታድያ ከምናስባቸው ጉዳዮች አብዛኞቹ ያለፉ ነገሮች፣ ትዝታዎች ናቸው፡፡ በርግጥ ሰው ስለ ወደፊቱም ሲያስብ ያለፈው ላይ፣ በፊት ባየው፣ በሰማው፣ በሚያውቀው፣ በለመደው ነገር ላይ ተመርኩዞ ነው፡፡
ሁሌም ያሳለፍናቸውን ነገሮች ወደድንም ጠላንም እናስባለን፡፡ አንዴ ያሳለፍነው ነገር እስከ መጨረሻው አብሮን በትዝታ መልክ ሊዘልቅ ይችላል፣ እስካልረሳነው፡፡ ደጉን እያሰብን ፈገግ ስንል "ምንድነው የሚያስቅህ?" ይሉናል፣ ማስታወስ የማንፈልጋቸው አጋጣሚዎች፣ በዳስተር ብናጠፋቸው የምንወዳቸው፣ የትዝታ ሰሌዳዎች፡፡ መርጦ ማስታወስ ቢቻል የሚያስብሉ፣ መርጦ መርሳት መቻልን የሚያስመኙ፡፡
እኔም እንዳንተው፣ እንደ ሁሉም ሰው፣ ስላሳለፍኳቸው የህይወቴ ክፍሎች ወድጄ ሳይሆን በግድ አስባለሁ፡፡ ሁኔታዎች ያስገድዳሉ፡፡ ከአስገዳጅ ሁኔታዎች መሀል ለምሳሌ፣ በህይወት መኖር፡፡ ከአሁን(ከደቂቃ በፊት) እስከማስታውሰው፣ ህልም እስከሚመስለኝ የህጻንነት ጊዜ፣ እንዳንተው ሳልወድ በግድ አስባለሁ፡፡ ደጉን እያሰብኩ ፈገግ እላለሁ፣...
በህይወቴ በጣም ትዝ! የሚለኝ አንድ አጋጣሚ ግን ስለ ህይወቴ፣ ከተወለድኩ ጀምሮ ስላለው ማንነቴ ዞሬ እንደማላውቅ ሁሉ ዞር ብዬ እንዳስብ አደረገኝ፡፡ በግዴታ ሳይሆን አስቤበት፣ አቅጄበት፣ ትዝ እያለኝ እንድስቅ ሳይሆን፣ ትዝ ብሎኝ እንድከፋ ሳይሆን፣ ትዝ ብሎኝ እንድተክዝ ሳይሆን፣ ከየት ወደ የት ነኝ ብዬ ራሴን እንድጠይቅ ነበር ያደረገኝ፡፡

ስንኖር ከመገመት የዘለለ መጨረሻችንን ማወቅ ከባድ ነው፡፡ ወዴት የሚለው ግልጽ ላይሆን ይችላል፡፡ ከየት የሚለው ግን ከየት ነው፡፡ ሊቀየር አይችልም፡፡ ሊረሳ እንጂ፡፡ ከየት ለሚለው ጥያቄ የማይቀየረውን መልስ እያስታወስን በሄድን ቁጥር ወዴታችንን ቢያንስ መገመት እንችላለን፡፡

ከወትሮው፣ ሳልወድ ከማስበው በበለጠ ስላሳለፍኳት አጭር ህይወት ማሰብ ነበረብኝ፡፡ ከድሮ እስከ ዘንድሮ ያለኝን የማስታወስ አቅም አንጠፍጥፌ መጠቀም ነበረብኝ፡፡ ቦርሳ ውስጥ ያለ ከረሜላ እንደሚፈልግ ህጻን ልጅ አዕምሮዬን አራግፌ መበርበር ነበረብኝ፡፡ የተረሳ መታወስ ነበረበት፡፡ በጊዜው ያልተሰበ ከአመታት በኋላም ቢሆን መታወስ ነበረበት፡፡ የደበዘዙ፣ ድንገት የሰማኋቸው ወሬዎችን፣ አይን ስላለኝ ብቻ ያየኋቸውን እንኳን ከቆየ በኋላ ማስታወስ በቀኑ አይቻለሁ ሰምቻለሁ ለማለት የሚያዳግቱ ሙታን ትዝታዎች ላይ ትውስታን መዝራት ነበረብኝ፡፡ አንድ አጋጣሚ በውዴታ ድሮን እንዳሰላስላት አነሳሳኝ፡፡ አንዳንዶች ራስን መፈለግ ይሉታል፡፡ መልካም እኔን መፈለግ፡፡

በዚህ ምዕራፍ ስር ስለ ራሴ ብዙ ነገር አወራለሁ፡፡ ማውራት ከሌለብኝ፣ "ይሄን ተራ ነገር አሁን ምን ይሁን ብሎ ነው የጻፈው?" እስከሚያስብለኝ፡፡ ነገር ግን እያንዳንዷ ቀን፣ እያንዳንዷ አዋዋል፣ እያንዳንዷ ትዝታ ስለኛ ወይም ስለ ሆነ ነገር የምትናገረው ቢያንስ አንድ ነገር ይኖራታል፡፡ በዚያ አምናለሁ፡፡

ማርና ወተቴ

መቱ፣ ተወልጄ ያደግኩባት ከፉና ደጉን ያየሁባት ከተማ ነች፡፡ የሚገርሙ የልጅነት ጊዜያት፣ የሚያስፈሩ የጭንቀት ዓመታት…

በ97ቱ ምርጫ ጊዜ አዲሳባ ስትተረማመስ ከ600 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ ሆነን ተጨንቀናል፡፡ 2003 ዓባይ ሊገደብ እንደሆነ ስንሰማ "እንደ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ" አይደል የሚባለው? የህዳሴ ግድቡ(the Renaissance dam) መሰረት ሲጣል እንደ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ተደስተናል፣ ፈንድቀናል፣ ታድሰናል፣ አልቆ ሲመረቅ ተኝተን አልመናል፣ መጨረሻውን ለማየት ተቁነጥንጠናል፡፡ እኔ በበኩሌ ግድቡ ሲያልቅ ለሀገሪቱ የመብራት ሃይል የሚያመነጭላት ብቻ ሳይሆን ረጃጅም ፎቆችን የሚያበቅልላት ነበር የመሰለኝ፡፡ ትክክል ነበርኩ ሊሆን ይችላል፡፡ ሰው ሞተ በተባለ ቁጥር ደግሞ "ወይኔ የህዳሴ ግድቡ አልቆ ሳያይ" ብዬ በውስጤ አግባብ ያልሆነ ሀዘን ኣዝን ነበር፡፡ አወይ ግድቡ አልቆ ሳላይ አትግደለኝ ያልንበት ያ ጊዜ…
የግድቡን መሰረት የጣለው ጠቅላይ ሚኒስትራችን መለስ በአመቱ፣ 2004 መጨረሻ ላይ ሲሞት ብሄራዊውን ሀዘን ተካፍለነናል፤ እስቴድየም በተደረገው ሰልፍ ላይም በነቂስ ወጥተን "ዓባይን የደፈረ ጀግና"፣ "ጀግና አይሞትም" እያልን ፎክረናል፡፡
2008 መንግስት ላይ ታምጾ ባጭሩ፣ ብዙ ወጣቶች ሲጨፈጨፉ ከባባድ ስሜቶችን አስተናግደናል፡፡ ጀዋር መሀመድ የሀገሪቱን ፖለቲካ መቆጣጠሩ፣ ፌስቡክ ላይ "ኢትዮጵያን በዚህ ሰዓት እያስተዳደረ ያለው፡ A. ሐ/ማርያም ደሳለኝ B. ዓባይ ጸሃዬ C. በረከት ስምኦን D. ጀዋር መሃመድ" ተብሎ መቀለዱና መንግስት ሰዓት እላፊንና ኢንተርኔት መዝጋትን የሚያካትት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አውጥቶ የደርግ ሲዝን 2 መሆኑን ማረጋገጡ፣ ማትሪክ ከተፈተነ በኋላ በአመጹ ምክንያት ተገሎ፣ ውጤቱ ሲመጣ ስትሬት A አምጥቶ ስንት እንዳመጣ ሳያውቅ የተቀጨው ልጅ አሳዛኝ ክስተት፣ ይሄን መፅሐፍ መፃፍ የጀመርኩ ሰሞን ትዝታዎች ናቸው፡፡
ባጠቃላይ መቱ ከፉና ደጉን ያየሁባት ከተማ ነች ስል ሀገራዊና አለማዊ ሁነቶችን፣ ክስተቶችን፣ ከፋቶችንና ደግነቶችንም መቱ እንዳለሁ ታድሜያለሁ ማለቴ እንደሆነ ከወዲሁ አንባቢዬን ለማስገንዘብ እወዳለሁ፡፡ ሀገርና ዓለም የእያንዳንዱ ሰው የዕለት ተዕለት ኑሮ አካል የሆኑበት ዘመን ሰዎች ነንና፡፡

በአሜሪካ ሁለት ሰማይ ጠቀስ ህንፃዎች በአጥፍቶ-ጠፊዎች ሲከሰከሱ፣ ያየሁት ፍንዳታ በህይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ ያየሁት ፍንዳታ መሆኑን ማሰታወሴ ይገርመኛል፡፡ 3 አመቴ ነበር:: በታሪክ ከፍተኛው የሽብር ጥቃት ፍንዳታ ለመጀመሪያ ጊዜ ያየኹው ፍንዳታ(bombing) ሲሆን አይገርምም? ያኔ በጣም ትንሽ ስለነበርኩ ህልም ይመስለኛል፡፡ ያኔ ቲቪ አልነበረንም፡፡ ከጎረቤታችን እነእቴቴ ቤት ነበር ያየሁት፡፡ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ፣ የመጀመሪያውን ህንፃ ያፈነዳቸው ጄት ራሱዋ በቀኝ እንደ ገባች በግራ ወጥታ፣ አሁንም እንደገና በሌላ መንገድ ዞራ መጥታ ሁለተኛውን ህንፃ አፈንድታ፣ በዚያው ጠፍታ ያመለጠች ነበር የሚመስለኝ፡፡ ያኔ ቲቪ አልነበረንም፡፡ በነእቴቴ ቲቪ ነበር ያየሁት፡፡

ያኔ ድሮ በህፃንነቴ ቲቪያችን ሬድዮናችን ነበረች፡፡ የጠዋት ጠዋቱ የገቢ ምንጫችን ቡና ቡናን፣ መማር ያስከብራል ሀገርን ያኮራል፣ እቴሜቴ የሎሚ ሽታን የመሳሰሉ ድሮ በሬድዮ ተደጋግመው ሲቀርቡ የነበሩ ዜማዎች በልጅነት አዕምሮዬ ላይ እንደታተሙ ይኸው ዛሬ አስታውሳቸዋለሁ፡፡ በርግጥ እነዚህን ዜማዎች ከዚያ ወዲህ አለፎ አልፎ ባልሰማቸው ከናካቴው እረሳቸው ይሆን ይሆናል፡፡ አሁን ለምሳሌ እቴሜቴ የሎሚ ሽታ በሬድዮ የልጆች ፕሮግራም ላይ ይቅረብ እንጂ ብዙዎቻችን በጊዜያችን ተጫውተን ያሳለፍነው ጨዋታ ነው፡፡ሌሎቹም እንዲሁ ተደጋገመው ስለሚሰሙ ለመርሳት እንጂ ለማስታወስ አይከብዱም፡፡

የቅዳሜና የእሁድ ጠዋት ጠዋቱን የልጆች ጊዜ እኔና ታላቅ ወንድሜ በጉጉት ነበር የምንጠብቀው፡፡ በተለይ ተረቶቹን፡፡ የማውቀውን ተረትም ቢሆን በሬድዮ ማዳመጥ የሚሰጠው የሆነ ልዩ ስሜት ነበረው፡፡ ልጅነት ነው ልበል?

ከጊዜ ርዝመት የተነሳ እነኛን የሬድዮ ዝግጅቶች ልረሳቸው እችል ይሆናል፡፡ ግን ያቺን ድንቅ ቀይ መካከለኛ ባለሁለት ስፒከር ቴፕ ለመርሳት፣ እውነቴን ነው፣ የአዕምሮ በሽተኛ መሆን ይጠይቃል፡፡

በአራት አመቴ ቲቪ ገዛን፡፡ 14 inch SONY:: ከዚያ በፊት ከነእቴቴ ቤት ተሰብስበን ቲቪ ስናይ፣ በተለይ የዚያኔው 120፣ የአሁኑ እሁድ መዝናኛ ላይ ሲተላለፉ የነበሩትን ድራማዎች ማየት በጣም እፈራ ነበር፡፡ ሲስቁ እፈራለሁ፣ ሲያወሩ እፈራለሁ፣ በተለይ ፊታቸው ትንሽ ከተቋጠረ በቃ ለኔ የመጨረሻ ሆረር ነው፡፡ ገጸ-ባህርያቱ ከተናደዱ፣ እየጮኹ የሚያወሩ ከሆነ፣ ድብድብ፣ ለቅሶ፣ የሆነ የሚለቅቁብኝ ነገር አላቸው፡፡ ሽጉጥ ካየሁ ወይም ድምፁን ከሰማሁ ደግሞ ያው ድራማውን አቋርጬ እወጣለሁ፡፡

ያኔ ከነእቴቴ ቤት ድራማ ስናይ አዕምሮዬ ላይ ታትሞ የቀረና ዛሬ ድረስ የማስታውሰው አንድ የሆነ ሌላ ነገሩን የማላስታውሰው ድራማ ላይ ያየሁት ትዕይንት አለ፡፡ ሰውየው ሴትየዋን በመኪና ከከተማ ወጣ ወዳለ ቦታ ይዟት ይሄድና በፌስታል ነገር አፍኖ ይገላታል፡፡ ያን ክፍል ለምን እንደማስታውሰው ይገረመኛል፤ በጣም ስላጨናነቀኝ ሊሆን ይችላል፡፡ ያቺን ቦታ ብቻኮ ነው ደግሞ የማስታውሰው፡፡ በእንዲህ አይነት ድራማ ተመስጦ፣ ድራማው ውስጥ ሰምጦ ጠፍቶ፣ ሲያልቅ መንቃትና “ውይ እነእቴቴ ቤት ነው እንዴ ያለሁት?” ማለት፣ ከፍርሃቱ የሚልቅ ደስ የሚል፣ ስሜት ነበረው፡፡ ሌላ አለምን ጎብኝቶ እንደ መመለስ አይነት፡፡ የልጆች ጊዜና አባባ ተስፋዬም አይረሱም፡፡ ልጆች፣ የዛሬ አበባዎች የነገ ፍሬዎች... ቲቪ ከገዛን ወዲህ ጉዲፈቻን፣ ያይኔን የመሳሰሉ ድራማዎችን ሳይ እንደነበረ ትዝ ይለኛል፡፡

አንድ በኢትዮጵያ የቴሌቪዥን ታሪክ ትልቅ ነገር፣ ታላቅ ፊልም! ቅዳሜ ምሽት ከ4 ሰዓት ጀምሮ ነበር የሚታየው፡፡ በርግጥ እኔ ታላቅ ፊልምን ያየሁት ሶስት ወይ አራት ጊዜ ብቻ ነው፡፡ እኔ ለአቅመ ምሽት እስከ 4 ሰዓት ሳያንቀላፉ መቀመጥ መቻል ሳልደርስ ኢቲቪ ታላቅ ፊልምን ማስተላለፍ አቆመ፡፡ በርግጥ ይሄ የኔ ችግር ነው፣ ብዙ እኩዮቼ ብዙ ፊልሞችን በታላቅ ፊልም አይተዋል፡፡ እኔ እንቅልፋም ስለነበርኩ ነው፡፡ መሰለኝ፡፡ የጃኪ ቻን “The good guy” ፊልም በታላቅ ፊልም ላይ እንቅልፌን ውጬ ካየኋቸው፣ በአንድ እጅ ጣቶች ከሚቆጠሩ ፊልሞች መሃል አንዱ ነው፡፡ ብዙ ጓደኞቼ ስለ ታላቅ ፊልም ሲነሳ ትዝ የሚላቸው ይሄ ጃኪ ሼፍ ሆኖ ለሽፍታው ቃሪያ ወርውሮ የሚያጎርስበት ፊልም ነው፡፡ ፊልሙ አስቂኝና አክሽን ስለሆነ ብቻ ሳይሆን በታላቅ ፊልም ቅዳሜ ምሽት ተደጋግሞ ስለታየ ሊሆን ይችላል፡፡

በህይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ ያየሁት ፊልም ታይታኒክ (TITANIC) ነው ብል ማን ያምነኛል? ቀድሜ እንደ ገለጽኩት በአራት አመቴ ይቅርና በአስርና በአስራ አንድ አመቴ እንኳን እስከ አራት ሰዓት ጠብቄ ለማየት እንቅልፍ ስለሚይዘኝ በአራት አመት የሚበልጠኝ ወንድሜ ብቻ ነበር እኛ ቤት ታላቅ ፊልምን የሚያየው፡፡ እኔ የአራት አመት እድሜ ህፃን እያለሁ በሰፈራችን አንዱንና ብቸኛውን ዴክ የነበራቸውን ሰዎች(ቤተሰብ) ነበሩ፡፡ ታይታኒክን ከነሱ ቤት የማየት እድል ገጠመኝ፡፡ በአለማችን ምርጥ ከሚባሉት ፊልሞች መሃል የሚጠቀሰው TITANIC በህይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ ያየሁት ፊልም ሆነ፡፡ ይሄኛውም አጋጣሚ ከፊልሙ ተወዳጅነትና አስደማሚነት የተነሳ ሊሆን ይችላል፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ታይታኒክንና ፊልም የተባለን ነገር ሳይ በጣም ከመፍራቴና ከመመሰጤ ባለፈ የማስታውሰው ነገር አለ ማለት ይከብደኛል፡፡ የምትሰምጥ መርከብ፣ ሰዎች ሲተረማመሱ፣ በጣም የሚዋደዱ ፍቅረኛሞች እንደነበሩ አስታውሳለሁ? የጃክና የሮዝ ምስሎች ባሉባቸው TITANIC ካርታዎች እየተጫወትኩ ስላደግኩ ሊሆን ይችላል፣ የማስታውስ የመሰለኝ፡፡

ህፃን ስለነበርኩ ሊሆን ይችላል፣ ቲቪ ስንገዛ ከመደሰት በዘለለ እንዲገዛልን መጎትጎቴ ወይም በጣም ቲቪ እንዲኖረን መፈለጌ ትዝ አይለኝም፡፡ ህፃን ስለነበርኩ መሆን አለበት እንጂ ቲቪ ብርቅ በነበረበት ጊዜ ቲቪ እንዲኖረው የማይፈልግ ማን ነበረ? በርግጥ ብርቅ ያልሆነን፣ ሁሉም ሰው ያለውን ነገር ማጣቱ ይከፋል፡፡

አምስተኛ አመቴ ኬጂ ትምህርት የጀመርኩበትና ቤት የቀየርንበት ነበር፡፡ በቀድሞው ቤት፣ ከነአልማዝና አብርሽ ጋር፣ ከነእቴቴ፣ ማሬ፣ ራሄልና ማቲ ጋር የሚገርም ጉርብትና ነበረን፡፡ እናቴ ስለዚያ ጊዜ ባወራች ቁጥር “ወይ ያ ዘመን...” ትላለች፡፡ ቤት መቀየር ቀላል ነገር አይደለም፡፡ ቤት ወደ ቁጠባ ነበር የቀየርነው፡፡ ሁለት ቤቶች በግርግዳ ብቻ ወደሚለያዩበት፣ የቁጠባ ቤት፡፡ ይኸኔ A B C D፣ 1 2 3 ማለት ጀምሬአለሁ፡፡ አዲሱ ቤት ከጓደኛዬ ከሳሙኤል ጋር አጎራበተኝ፡፡ በአጥር ነበር የምንለያየው፡፡ ቁጠባ ቤት እስከ ሰባተኛ ክፍል ካልተለያየነው ጓደኛዬ ጋር ብቻ አይደለም ያቀራረበኝ፣ መአት ጓደኞች፣ ብዙ ጎረቤቶች፣ ከብዙ ሰዎች ጋር የተቀራረብኩበትም ነበር፡፡ ከአመታት በኋላ ስለዚያ ጊዜ ሳስበው ባለታሪኩ እኔ እንዳልሆንኩ ሁሉ “እንዴት ሊሆን ቻለ? How was that possible?” ብዬ ራሴን እጠይቃለሁ፡፡” አሁንስ ቢሆን ለምን አልቻልኩም?”፡፡ በጓደኝነት፡ እኔ አለሁ፣ ሳሚ አለ፣ እኔና ሳሚ በሁለት አመት የምንበልጠው አቢቲ አለ፡፡ በጉርብትና ደረጃ ከኛ ጋር በግርግዳ የምንለያየው እነአስተማሪ ተሰማ፣ እስከዳር፣ ስንቴ፣ ዳግምና ኢየሩስ ትልቁን ስፍራ ይይዛሉ፡፡ ከዚህ ቤተሰብ ጋር የነበረን ቅርርብ ከምር ግርግዳ

ብቻ የለየው ነበር፡፡ በተለይ እኔ ከሁላቸውም ጋር፣ ከኣባትና እናታቸው ጋር፣ ከስንቴ ጋር፣ ከዳጊ ጋርም የጓደኝነት ነገር ነበረኝ፡፡ የዛ ቤት ቤተኛ ነበርኩ፡፡ ኢየሩስ ደግሞ እኩያዬ ነች፡፡ ከሷ ጋር ደግሞ ምርጥ ጓደኞች ነበርን፡፡

በተረፈ ከነለሚ፣ ሳራ፣ አቢቲ፣ ሚጡና ኦዳ ጋር፣ ከነስዩም፣ አበባ፣ ሳሚ፣ ያዕቆብ ጋር፣ ከነተስፋዬ፣ እመቤት፣ ማሙሽ፣ ሰላሜ ጋር፣ ከነፊሮምሳ፣ ወርቄ፣ ስጦታ፣ እሙቲ፣ አቡቲ ጋር፣ ከነጸሀይ፣ ቲኪ፣ መቅዲ ጋር፣ ከነናኦል ጋር፣ ከነአቤ ጋር የሚገርም ጉርብትናና ግንኙነት ነበረን፡፡ ከነዚህ ቤት ልጆች ጋር ጓደኛ ብቻ አልነበርንም፡፡ ቡድን ነበርን፡፡ አቤት ትንሽ ነህ ትልቅ ነህ ብሎ መናናቅ ያልነበረበት ያ ዘመን፡፡ እኔን የሚገርመኝ እሱ ብቻ አይደለም፡፡ አጥር በቅጡ ባልተሰራላቸው በነኛ ቤቶች ውስጥ ስንኖር፣ አንዳችን ባንዳችን ቤት ሳሎን ገብተን በጓሮ ስንወጣ፣ ብዙ ለጥል የሚጋብዙ አጋጣሚዎች የነበሩ ቢሆንም ያን ያህል የተጋነነ ግጭት በመሀላችን ያልነበረ መሆኑ ነው፡፡ በቃ የሚያጣሉ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር ሰው አልነበረም፡፡ የኛ ሰፈር ሰው ደግ ነው ማለቴ አይደለም፡፡ ግን በቃ የሆነ ክፉ ነገር እንዳናስብ የጋረደን ነገር ነበር ልበል? በሰላም ነበር የተበታተንነው፡፡ ለየወላጆቻችን የነበረን ክብር፣ እርስ በራስ የነበረን ፍቅር ከአዕምሮ በላይ ነበረ፡፡

የጸሀይ ልጅ መቅዲ በጣም አልቃሻ ነበረች፡፡ ስታለቅስ በቀጭን ጨኸት የሰፈሩን ጆሮ ነው የምትበሳው፡፡ ያኔ 3 ወይ 4 አመት ቢሆናት ነው፡፡ ሰው የሆነ ነገር ካላት ዋይ ትላለች፡፡ እንደዛ የምትጮኸው እናቷ እንድትሰማ ነው እንዳልል፣ ከቤት ስትመታ(ስትነካ)ም እንደዛው ነው አለቃቀሷ፡፡ የሆነ ሰው ነኳት ወይ ሰድቧት ስትጮህ እናቷ ድምጽዋን ትሰማና እየሮጠች መጥታ “ምን ሆንሽ” ትላታለች፡፡ “ቤቢ መታኝ፡፡” “ለምንድነው ልጄን የምትመታት” ብላ ሰውን ታስደነግጥና ልጅቷን ደብቃ ከንፈሯን እየነከሰች ሰውን ትቆነጥጣለች፡፡ የውሸት ልጅቷ እንድታቆም ማለት ነው፡፡ ሌላ ቀን ደግሞ ታለቅሳለች መቅዲ፡፡ ዋአአአይ..ዋአአይ፡፡ እናትየው ትመጣለች፡፡ “ምን ሆንሽ?” “ሳሚ መታኝ፡፡” “ለምንድነው ልጄን ምትመታት?” እያለች ስትመጣ እኛ ነቅተን የለ? እንደበፊቱ ሳንሸበር በፈገግታ ቁጣውንም፣ ቁንጥጫውንም ለመቀበል ስንዘጋጅ እሷ የምሯን አምርራ ቁጣዋን አዝንባብን ትሄዳለች፡፡ ቀጥላ ደግሞ ቁጣ ስንጠብቅ መጥታ ትቀልዳለች፡፡ ስለዚህ የነበረን አማራጭ ሁሌ ቁጣ መጠበቅ፣ ከቀለደች ጥሩ፣ ከተቆጣች ደግሞ ያው “እንደ ጠበቅኩት” ማለት ነበረ፡፡

በቲቪ ከልጆች ጊዜ፣ የማታ ማታ በተለይ ሮብ ማታ ድራማዎች፣ 120ና ቅዳሜና እሁድ ከሚተላለፉ አንዳንድ ፕሮግራሞች በዘለለ ቀልብ የሚይዙ ፕሮግራሞች አልነበሩም፡፡ የስርጭት ጊዜውም በጣም አጭር ነበረ፡፡ ETV የ24 ሰዓት ስርጭት የጀመረው ከሚሊኒየሙ ወዲህ ይመስለኛል፡፡ ያኔ ቁጠባ ቤት ስንኖር ኢቲቪ ይቆራረጥ ነበር፡፡ ጠዋት ጠዋት 12 ሰዓት ላይ በኤሮቢክስ፣ ይጀምርና ጠዋት ተነስተን ት/ቤት የምንሄደውም፣ ቢሮ የሚሄዱትም ቁርሳችንን በአንድ ሰዓት ዜና እናወራርዳለን፡፡ በየጊዜው የሚቀያየሩ ፕሮግራሞች፣ ከዛ ከ5 ሰዓት እስከ 6 የእንግሊዘኛ ዜናና ፕሮግራም፡፡ እያለ እያለ 7 ሰዓት ላይ “እንደ ምን ዋላችሁ፣ በእስቱዲዮ አቆጣጠር 7 ሰዓት ሆኗል ከኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የሰዓቱን ዜና ይዤ ቀርቤአለሁ ከዜናዎቹ ጋር አማረ ማሞ ነኝ፡፡” ይላል፡፡ ትንሽ ቆይቶ እነተመስገን በየነ ይመጣሉ፡፡ ከዜና በኋላ የታዩ ፕሮግራሞች ይደገሙና ስምንት ሰዓት ላይ ያልቃል፡፡ ፕሮግራሞቹ 8 ሰዓት ላይ ሲያልቁ የኛ ሶኒ ቲቪ በቀስተ-ደመና ቀለሞች ጡጥ በሚል ድምፅ ታጅቦ የመዝጊያ ስነ-ስርአት ይፈፅማል፡፡ ትንሽ ቆይቶ ደግሞ የሆኑ ነጭና ጥቁር ጥቃቅን ነገሮች ብሽሽሽሽ በሚል ድምፅ ታጅበው በቴሌቪዥኑ ላይ ይሮጣሉ፡፡ ያ የሚያናድድ ድምፅ፣ “የሚታይ ነገር የለም ቲቪውን ዝጉት” የሚል ይመስላል፡፡ ይሄን የሚያስጠላ የሶኒ ቲቪ no transmission ማስታወቅያ በአንድ የገጠር ወረዳ ልጆች “የሚሮጡ ህፃናት” እያሉ ስራችን ብለው ያዩ ነበር አሉ፡፡

ወደ ማታ የሚኖረው ፕሮግራም ቶሎ ቶሎ ይቀያየር የነበረ ይመስለኛል፡፡ የሆነ ጊዜ፣ 10 ሰዓት ላይ ጠብቀን የምናየው Jim and Jam የተሰኘ ካርቱን ፊልም ይተላለፍ እንደ ነበረ ኣስታውሳለሁ፡፡ የሆነ ሌላ የማይጥም የቢጫ ካርቱኖች፣   ደግሞ ነበር፡፡ ወደ ማታ የትግርኛና የኦሮምኛ ፕሮግራሞች ተከታትለው ይቀርባሉ፡፡ ዕንባባታትና Qophii Ijoollee ላይ ሲቀርቡ የነበሩ ፊልሞችን በጣም በናፍቆት ነበር የምናየው፡፡ የአንድ ወይም የሁለት ሰዓት ፊልም በየሳምንቱ አስር ደቂቃ ለማትሞላ ጊዜ ሲያሳዩ፣ እሷንም ያለፈውን ሳምንት ካሳዩት ከግማሹ ነው ሚጀምሩት፡፡ ቢሆንም ግን በጉጉት፣ በጣም በጉጉት ነበር ፊልሞቹን የምንጠብቀው፡፡ ዕንባባታት ላይ ያየሁት፣ ልጆቹ በሆነ ማሽን ትንሽ ሆነው፣ ከጉንዳን በታች አንሰው የቤታቸው ግቢ ሳር ውስጥ የሚንገላቱበት፣ ከትናንሽ ነፍሳት ጋር የሚገጥሙበት ፊልም አይረሳኝም፡፡ ትዝ ይለኛል፣እናቴ እህቴ ሚጣን እንደተገላገለች ከሆስፒታል ተደውሎ ሲነገረን፣ ዓርብ ማታ ከአንድ ሰዓት በኋላ “Qophii Ijoollee”ን እያየን ነበረ፡፡

ከዚያ ሁለት ሰዓት ላይ የአማርኛ ዜና ይቀርብና የተለያዩ ፕሮግራሞች እስከ አምስት ሰዓት ተከታትለው ታይተው፣ “የዜግነት ክብር” እያለ ብሄራዊ መዝሙራችን ማረጊያ ይሆናል፡፡ በኢቲቪ አንድ የተለመደ ነገር ነበር፣ አንድ ዝግጅት አልቆ ሌላው ከመጀመሩ በፊት አልፎ አልፎ በተደጋጋሚ ለአንድ ወይ ለሁለት ደቂቃ ወንዞች፣ተራራዎች፣ ፓርኮች፣ ያዲሳባ ፎቆች፣ መንገዶች ምናምን ሲታዩ፣ ከጀርባ የሚያጅበው ሙዚቃ መስጦኝ ሆነ አላውቅም፣ ሁሌ ስራዬ ብዬ አያቸው ነበር፡፡ ጅልነቴም ሊሆን ይችላል፡፡ ሰው ሁለቴ አይቶ አይተውም? እሺ አስሬ አይቶ አይተውም? እኔ አንዴ ያየሁትን ዝም ብዬ ደጋግሜ በታየ ቁጥር አየው ነበር፡፡ በተለይ የሁለት ሰዓት ዜና ሊጀምር ሲል፡፡ የሚሮጡትን ህጻናት እንደሚያዩት የገጠር ህጻናት ማለት ነው፡፡ ይኸኔ ያዝናናቸው ነበርኮ፡፡
ማታ እስከ 5 ሰዓት የመቀመጥና ብሄራዊ መዝሙራችን በቲቪ ሲዘመር የመስማት ከፍተኛ ጉጉት ነበረኝ፡፡ ጉጉቴን አንድ ቀን አሳክቼዋለሁ፡፡ አንድ ቀን ብቻ! እኔ እስከ 5 ሰዓት ቀርቶ እስከ ጠዋት 12 ሰዓት ሳልተኛ መቀመጥ በምችልበት እድሜና ደረጃ ላይ ስደርስ፣

ብሄራዊ መዝሙራችን ሰው በሚተኛበትና ማንም ጆሮውን ሊሰጠው ፈቃደኛ በማይሆንበት ሰዓት የመንቆርቆር እገዳው ተነስቶለት ኢቲቪ ከ5 ሰዓት ወዲህ ስረጭቱን እስከ (8 ሰዓት) አስፍቶት ነበር፡፡
በተለያዩ እድሜዎቻችን፣ በተለያዩ ቦታዎች፣ በተለያዩ ጊዜያትና አጋጣሚዎች ማድረግ አለብኝ፣ ሊኖረኝ ይገባል፣ ያለሱ መኖር አልችልም፣ በጣም ያስፈልገኛል፣ important, too important የምንላቸው ነገሮች በማናስተውለው እና/ወይም በምናስተውለው ሁኔታ ግን ብናስባቸው በሚገርም ሁኔታ እየተቀያየሩ፣ በሚገርም ሁኔታ ሳይቀየሩ፣ ለኛ ግራ በሚገባን ሁኔታ "ይሄን ነበር ያስፈልገኛል ስል የነበረው?" አስብለው በአዕምሮአችን ላይ የተለያዩ ስሜቶችን ይፈጥራሉ፡፡ "እኤማ መቼም እንደዛ አልለብስም፡፡ ምን የሚሉት አለባበስ ነው?" ብለን ከአመት በኋላ የዚያ አለባበስ አቀንቃኝ ሆነን ስንገኝ ስንቶቻችን ራሳችንን እንታዘባለን? ስንቶቻችን ተገርመንስ እናውቃለን፡፡ ለምሳሌ እኔ የሆነ ጊዜ እንኳን ከአፌ ማውጣትና መጠቀም፣ ሰው ሲል ስሰማቸው፣ ያን ቃል ከሚናገረው ሰውዬ በተቻለኝ መጠን ለመራቅ ጥረት ሳረግ የነበርኩበትን ቃል ካመታት በኋላ ሳላቅማማ የምልበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበረ፡፡

በቲቪ፣ ታላቅ ፊልምንና 5 ሰአት ላይ የዜግነት ክብር ሲዘመር ማየት በለጋ አዕምሮዬ ለረጅም ጊዜ ስመኛቸው የነበሩ ነገሮች ናቸው፡፡ በጊዜው እስከ አምስት ሰአት መቆየት አለብኝ ብዬ ስላሰብኩ ለኔ አስፈላጊ ነበረ፡፡ አስፈላጊነት(importance) የምንለው ነገርም እንዲህ ነው፡፡ አስፈላጊነት የእምነት ጉዳይ ነው፡፡ ያስፈልገናል ብለን ያመንነው ነገር ያስፈልገናል፡፡ የማያስፈልገን ነገር መስሎ ያልተሰማን ነገር አያስፈልገንም፡፡ አንባቢ ሆይ ስለማስፈለግ ወይም ስለ አስፈላጊነት ሳነሳ ስለ መፈለግ(want)ና ስለማስፈለግ(need) በማሰብ ወደ ኤሌሜንተሪ የእንግሊዘኛ ት/ት ወደ ኋላ እንድትመለስ አልፈልግም፡፡ ወንትና ኒድ ልዩነታቸው የዲግሪ ነው፡፡ እኔ እያወራሁ ያለሁት ስለ ኢምፖርታንስ ነው፡፡ ሁለቱንም ያጠቃልላል፡፡ በጣም አስፈላጊ ሲመስለን ኒድ እንለዋለን፡፡ ሌስ ኢምፖርታንት ሲሆን ደግሞ ወንት እንለዋለን፡፡

I need to stay awake until 5pm. (why?)
I need some food, I'm starving.
I want shoes. (Is it really important right now?)
I need money for food.
I want to have an ice cream. (No you don't.)

እንግዲህ ያስፈልገናል ብለን ያመንበት(ያሰብነው) ነገር እውነት ሊያስፈልገን የሚገባ ነገር ነው ወይ? እውነት ምኞታችንና ፍላጎታችን ለተገቢውና ለአስፈላጊው ነገር ነው ወይ? የሚሉት ጥያቄዎች እንዳልተመለሱ ይቆያሉ፡፡
አንዳንዴ ህይወታችንን በሙሉ ያስፈልገኛል፣ ማድረግ አለብኝ... እያልን የኖርናቸው ብዙ ነገሮች ይኖራሉ፡፡ በርግጥ እድሜ ዘመናችንን ያንን ነገር እየሻትን መኖር ነበረብን ወይ? ደግሞ ማንነው ፍላጎታችን ትክክል ነው ወይም አይደለም የሚለው? ክፉ ብለን ስናስብ የነበረውን ነገር ከጊዜ በኋላ መልካም፣ መልካም ስንል የነበረውን ደግሞ ክፉ ብለን እንድንቀበልና እንድንከራከር የሚያደርገንስ ምንድነው? በቀዳሚነት የሚነሳው ማህበረሰቡ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ላይ ሰው ሲሞት ለቅሶ ይኬዳል፡፡ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ ውጪ ሀገር ብዙ ሰው አይሄድም፣ የሚኬደውም የቀብር ቀን ነው እንጂ በቀጣይ ቀናት ለቅሶ ብሎ የሚሄድ ሰውም፣ ሰው የሚጠብቅ ሀዘንተኛም የለም፡፡
እንግዲህ ጥያቄው "ማህበረሰቡ የሚያሳስቡት፣ ሊያሳስቡት የሚገቡ ነገሮች ናቸው ወይ?" የሚለው ነው፡፡ ማህበረሰቡ የሚቀበላቸውና የሚያወግዛቸው ነገሮች እውነት ሊቀበላቸው ወይም ሊያወግዛቸው የሚገቡ ነገሮች ናቸው?

በዚያኔው ኢቲቪ እኛን ልጆችን የሚስቡ ፕሮግራሞች በጣም ጥቂት ነበሩ፡፡ ከጥቀቱ ደግሞ በአማርኛው የልጆች ጊዜ ላይ፣ በኦሮምኛው Qophii Ijoollee ላይ፣ በትግርኛው ዕምባባታት ላይ ይታዩ ለነበሩ ፊልሞችና ድራማዎች የነበረን ጉጉት ከፍተኛ ነበር፡፡ ለሩጫና ለኳስስ? ኦሎምፒክ አለ ከተባለ መጠበቅ የምንጀምረው ከኦሎምፒኩ አንድ ወር ቀድመን ነበር፡፡ አቤት የዚያ ወር ርዝመት!
የአቴንስና የቤጂንግ ኦሎምኮች፣ ቀነኒሳና ጥሩነሽ፣ አቴንስ ኦሎምፒክ ቀነኒሳ፣ ሀይሌና ስለሺ ተከታትለው ሲገቡ የነበረን ስሜት፣ አቤት!
ሌላ ጊዜ ደግሞ ያንን አረንጓዴ ጎርፍ ይደግሙታል ብለን ስንጠብቅ ሀይሌ ተጎድቶ ቀነኒሳ ወደ ኋላ እየዞረ ሀይሌን ሲፈልግ...

ድርር ደርር ደርር...
መርቆ ሸኝቶን ሀገር አስይዞ ሰንደቅ አላማ
መርዶ ነው ለወገናችን ማሸነፍ ካቃተንማ
ኤይ ኤይ ኤይ ኤይ
ልሰለፍ ህመሜን ችዬ፣ እሮጨ ላሯሩጣቸው
ትልቁን እምነት በናንተ ጥለናል እንግዲህ አይዟችሁ፡፡
ከበደኝ ትቼህ ለመግባት ከበደኝ የወኔ አባቴ
ከበደኝ ባይኔ ፈለግኩህ ከበደኝ አዞሬ ፊቴን
በል ፍጠን ድሉ ናፍቆታል በል ፍጠን ዳጉቷል ወገኔ፣
በል ፍጠን እንዳትቀደም በል ፍጠን አትይ ወደኔ
አልሆንልህ አለኝ እኔን አልሆንልህ አለኝ ዬሄ
አንተን ጥሎ መግባት ሀይሌ
አልሆንልህ አለኝ፡፡
አንበሳ ቀነኒሳ

አንበሳ ታሪክ ሰራ
አንበሳ የማይረሳ... ብሎ ቴዲ ሲዘፍን ስሜት የሚነካ ነበር፡፡

ቴሌቪዥን በአንድ ሰው አስተሳሰብ ላይ ከፍተኛ ተጽእኖን ያሳድራል፡፡ ተጽእኖውን ለመፍጠር ግን የግድ ተጽእኖ የሚደረግበት አዕምሮ የግድ ፕሮግራሞቹን በጉጉት እየጠበቀ ማየት የለበትም፡፡ በዚያ ጊዜ የነበረን ብቸኛ ጣቢያ ኢቲቪ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የኢቲቪ ወሬዎች በተለይ በዛ የልጅነት አዕምሮ ላይ ተጽእኖ የማድረግ አቅማቸው ለመካድ የሚያዳግት እውነታ ነው፡፡ የሩጫ ሰሞን፣ ሰፈር ውስጥ አሩጫ መወዳደር፣ የአለም ዋንጫ ሰሞን፣ ቆርኪ ቀጥቅጦ ዋንጫ ሰርቶ፣ በጨርቅ ኳስ መጋጠም...
ሁሌ ልማትን፣ እድገትን፣ ለውጥን ሲሰብኩ ኢትዮጵያ ደሀ ሀገር አትመስለኝም ነበር፡፡ ኢትዮጵያ የኛ መመኪያ ሲባል፣ ወንዞችን፣ ተራራችን፣ ደናችን፣ ቱሪዝማችን፣ እያሉ ሲያደናንቁ፣ እንደ ኢትዮጵያ በተፈጥሮ ሀብት የታደለች ሀገር ያለች አይመስለኝም ነበር፡፡ የሌላ ሀገራትን ተፈጥሮ፣ አድጌ ሳይ ለካስ ሌላ ሀገርም እኛ ጋር ያለው አለ ማለት ጀመረኩኝ፡፡ እንዲያውም ከኛ የበለጠ የሚያምሩት ሞልተው የለ? አሁን አሜሪካ ሲባል ፎቅና ብረት ብቻ ይመስለኝ ነበር፡፡ ግን እነሱም ደን፣ የሚያማምሩ ፏፏቴዎች፣ ትላልቅ የቱሪስት መዳረሻዎች አሏቸው፡፡
ከሁሉም ስለ መሰረተ-ልማትና ስለ እድገት እየተሰበኩ አድገው፣ "ኢትዮጵያ በድህነት አንደኛ ነች፣ ከሁሉም ያነሰች ደሀ ነች" መባል በጣም ግራ የሚያጋባ ዜና ነው፡፡ አሁን በአንድ ቻናል ላይ ላይቭ ቀነኒሳ እሩጫ ሲያሸንፍ አይተው ተደስተው ወዲያው ወደ ሌላ ቻናል ሲቀይሩት የብዙ ሪከርዶችና የብዙ የኦሎምፒክ ወርቆች ባለቤቱን ከሁለት ሰከንድ በፊት ውድድር ሲያሸንፍ ያዩት፣ የአትሌት ቀነኒሳ የቀብር ስነ-ስርአት ሲካሄድ እንደ ማየት ነው፡፡ "ምን?!" ያስብላል፡፡

ያኔ በኢቲቪ ስለ ፖለቲካ የነበረው ሁኔታ "እከክህን እኔ አክልሀለሁ፣ አንተ አርፈህ ተዝናና" አይነት ነበር፡፡ የመንግስቱ ትሩፋቶችና የልማት ውጤቶች፣ ስፖርት፣ መዝናኛ፡፡ ስለ መንግስት ክፉ ነገር ሳት ብሎት የሚያወራ የለም፡፡ ለነገሩ አንደበት ስለባለቤቱ ክፋት ያወራ ዘንድ አይጠበቅም፡፡ በተለይ መናገሩ ባለቤቱን የሚጎዳ ወይም ለጉዳት የሚያጋልጥ ወይም ሚስጥር የሚያወጣ ከሆነ፡፡ እውነት ነው፡፡ ኢቲቪ የተናገረውን ነው የምናስተጋባው፡፡ ኢቲቪ በሰፈረልን ልክ ነው የምናስበው፡፡ ስለ ኢህአዲግ ክፉ ነገር ማሰብ በጣም ከባድ ነበር፡፡
የምርጫ 97 ሰሞን አዲሳባ ስትተራመስ ሳይ በጣም ነበር ግራ የተጋባሁት፡፡ ለምን ብጥብጥ? ምን ለማትረፍ ነው? መልሱ ኢቲቪ እንድንሰማ በፈለገው መንገድ ይቀርብልናል፡፡ በብርቅዬው የቴሌቪዥን ጣቢያችን፡፡ ተቃዋሚዎች የሚቃወሙት፣ መንግስትን ብቻ ሳይሆን ልማትን፣ እድገትንና ብልጽግናን፣ ሀገሪቱንም ጭምር ይመስለኝ ነበር፡፡ እና ምን ጎደላቸውና ነው መንግስትን የሚቃወሙት፡፡ ምርጫ ተጭበረበረ የሚለን አልነበረም፡፡ የሰማሁት ጸረ ልማት ሃይሎች ሲባል ነዋ! እንደ ኢቲቪ ኢህአዲግን የጠቀመ ግን ምን አለ?

አንድ ቀን ትዝ ይለኛል፡፡ የነኢየሩስ(ጎረቤታችን) ቤት ከስንታየሁ ጋር ተቀምጥን ነበር፡፡ ምንም የለም፡፡ ረፋድ ነው፡፡ ፓርላማ ላይ መለስ ሲያወራ በቀጥታ ስርጭት እየተላለፈ ነበር፡፡ እሱም ተመስጦ እያዳመጠ ነው፡፡ እኔ ደግሞ ደብሮኝ እነሳሚ ቤት ሄጄ ለመጫወት ጠየቅኩት፡፡ ለምን ተቀምጠህ ይሄን አታይም አለኝ፡፡ ምን ያረግልኛል? አልኩት፡፡ ስለሀገርህ ነውኮ አለኝ፡፡ መቼም ልጅ ነበርኩና ስለ ሀገሬ ስለነበረ፣ ተቀምጬ ለማዳመጥ አልፈለግኩም፡፡
ከስንቴ ጋር የሚገርም ቅርርብ ነበረን፡፡ እሱ ያኔ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ነበረና ክረምት ለእረፍት ቤት ሲመጣ ነበር አብረን የምንውለው፡፡ አቡነ ጴጥሮስ ት/ቤት አንደኛ ወይ ሁለተኛ ክፍል ስማር ስጋ ወጥ ለራሱ ሰርቶ አብልቶ ልኮኝ ያውቃል፡፡

በ97 የሠፈራችን ሰዎች ዲቪዲ ማጫወቻ መግዛት ጀመሩ፡፡ እነማሙሽ፣ እነአዳ፣ እነሳሚ፣ ተከታትለው ገዙ፡፡ አዲስ የፊልም ዘመን፡፡ ዘማሪዎች ሲዘምሩ መስማት ብቻ ሳይሆን ሲዘምሩ ማየት ጀመርን፡፡ የሳሚ አባት የመሰረተ ክርስቶስ ቸርች ወንጌላዊ ስለነበረ መንፈሳዊ ፊልሞችን ያመጣ ነበርና እነሱ ቤት ብዙ መንፈሳዊ ፊልሞችን አይቻለሁ፡፡ መንፈሳዊ ድራማዎችን፡፡
ያኔ ፊልም እንደ ልብ አይገኝም ነበር፡፡ አንድ ቀን ከሌላኛው ጎረቤታችን ከወንድሜ ጓደኛ ከማሙሽ ጋር ከሁለገብ አዳራሽ አካባቢ ሄደን ፊልም ስንከራይ ትዝ ይለኛል፡፡
እኛ ቤት እንዲህ አይነት አዲስ ነገር በመግዛት በጣም ኋላ ቀር ነበሩ፡፡ እንዲህ አይነት ነገር ለምን ስሜት እንደማይሰጣቸው አላውቅም፡፡ ሌላው ለምን ከሰው አንሳለሁ ብሎ ከሰው ተበድሮ ይገዛል፣ የኛዎቹ እንዲህ አይነት ነገር ምንም አይመስላቸውም፡፡ ለኔ ግን በዚያ ሁሉም ጓደኞቻችን ቤት ዲቪዲ ኖሮ እኛ ቤት ያልነበረ ጊዜ ከዲቪዲ የሚልቅ ምንም ነገር አልነበረም፡፡ እውነቱን ነው፡፡ እኔና ወንድሜ ዲቪዲ እንዲገዛልን ጨቅጭቀን ጨቅጭቀን፣ ጓጉተን ጓጉተን ጉጉታችንን ከተለማመድነው በኋላ ነበር የተገዛልን፡፡ ጓደኞችህ ስላላቸው፣ አንተ ግን ስለሌለህ ነገር ከማሰብ የበለጠ ምን የሚያስጠላ ስሜት አለ፡፡ ለዛ ነው ሁሉም የበለጠ እንዲኖረው የሚፈልገው፣ ከሁሉም በላይ ሀብታም መሆን የሚፈልገው፡፡ ሌላውን ለመብለጥ፡፡
Planet Of The Apes የተሰኘውን ፊልም እንዴት እንዳየነው ትዝ ይለኛል፡፡ የሆነች ዲቪዲ ከምምጣቱ በፊት የነበረች ማጫወቻ ነበረች፡፡ እና የሆነ ከጋምቤላ የመጣ ጓደኛችን ባመጣት በዚያች ትንሽ ማጫወቻ ነበር እነዳጊ(ጎረቤታችን) ቤት ተሰብስበን ያየነው፡፡ ግን እንደ ፊልም የሚያዝናና ነገር ምን ነበር እሱ? ቀስ በቀስ ፊልም መቀያየር፣ አንዱ ያላየውን ለሌላው ማስተላለፍ፣ እየመጣ ፊልም ማየት የሚዘወተር ነገር እየሆነ መጣ፡፡ በዚያ ላይ የዲቪዲ ጌም አለ፡፡ ኮንትራ ምናምን፡፡ እሱንም ተጫውተን ነው ያደግነው፡፡

1999 የካቲት 16 እህቴ ተወለደች፡፡ ለወላጆቻችን 3 ልጆች ሆንን፡፡ ሚጣን ማሳደጉን እናታችን የመንግስት ሰራተኛ የነበረች ከመሆኑ ጋር ተያይዞ አስቸጋሪ ነበር፡፡ ሰራተኛ ከመቅጠር ጀምሮ ብዙ ተሞክሯል፡፡ ወንድሜ "እኔ ትምህርት አንድ አመት አቋርጬ ልጠብቃት" እስኪል ድረስ፡፡ ያኔ እንደዚያ በሚልበት ጊዜ 14 አመት ቢሞላው ነው፡፡ በክፍል 7 ወይም 8፡፡ እዚህ ጋር ማንሳት የፈለግኩት የጎረቤቶቻችንን እርዳታ ነው፡፡ ከጎረቤትም በላይ ነበርን ስል ማጋነኔ አልነበረም፡፡ በተለይ የሲስተር እመቤት ልጅ፣ የማሙሽ ታላቅ እህት የሰላሜን፡፡ ገላገለችን፡፡ ባለውለታችን ናት በእውነቱ፡፡ እናቴ ሚጣን እሷ ጋር አስቀምጣ ነበር ቢሮ የምትሄደው፡፡

የቀድሞ ጎረቤቶቻችን እነአልማዝና እነእቴቴ ጋር በተለይ ቤት በቀየርን የመጀመሪያ አመታት እኔም ወንድሜም እንሄድ ነበር፡፡ የእቴቴ ልጅ ድሮ ታጫውተን የነበረችው ማሬ እኛ ከዚያ ሳንለቅ ነው አዲሳባ የሄደችው፡፡ ትንሽ ቆይቶ እነእቴቴም ሰፈር ቀየሩ፡፡ የድሮ ጉርብትናችን የድሮ ጉርብትና ብቻ ሆነ፡፡ ትዝታ፡፡
ወንድሜ ከነአልማዝና ከነአብርሽ ጋር ያለውን ወዳጅነት ቀጠለ፤ እኔ ደግሞ ከነራሄልና ከነእቴቴ ጋር፡፡ እስከ አስረኛ ክፍል ድረስ፡፡ አስረኛ ክፍል እስከገባ ድረስ እነእቴቴ ቤት በየሳምንቱ የምሄድበት ጊዜም ነበር፡፡

ትምህርት፣ ከአቡነ-ጴጥሮስ ወጥቼ አዲስ ወደተከፈተው ቤተሰብ(የእንደሻው) ት/ቤት ገባሁ፡፡ያኔ በርግጥ ብዙ የሰፈራችን ልጆች እዚያ ት/ቤት ስለገቡ አንድም የማህበረሰቡ ተጽዕኖ ነው ማለት ይቻላል፡፡ አቡነ-ጴጥሮስ የመንግስት ት/ቤት ሲሆን እንደሻው ደግሞ የግል ነው፡፡ ለመማር የሚከፈልበት፡፡ ለመማር!
በኤሌሜንተሪ የመጀመሪያ አመታት ትዝ የሚለኝ ክርክር ነበረ፡፡ ከገንዘብና ከእውቀት የቱ ይሻላል የሚል፡፡ አንዱ ቡድን ገንዘብ ይሻላል፡ ገንዘብ ካለህ ነው፣ ምትማረው፣ ገንዘብ ካለህ፣ የተማረ ሰው ቀጥረህ ማሰራት ትችላለህ ይላል፡፡ እውቀት ይበልጣል የሚለው ደግሞ እውቀት ካለ ነው፣ ገንዘብ ማግኘት የሚቻለው፣ ገንዘብ በስርአቱ መያዝ የሚቻለው ይላል፡፡ ይሄን ክርክር በጣም ከባድ የሚያደርገው፣ ሁለቱም ቡድን ገንዘብም፣ እውቀትም በጣም አስፈላጊ የሆኑና የሁሉም ሰው የህይወት ግቦች እንደሆኑ እየታወቀ ለአንዱ ማድላት የግድ ማስፈለጉ ነው፡፡
የእንደሻው ት/ቤት ት/ት በጣም ይከብዳል ሲባል ስለሰማሁ መጀመሪያ በጣም ፈርቼ ነበር፡፡ የምወድቅ የምወድቅ ይመስለኝ ነበር፡፡ በጣም ፈርቼ ስለነበር በጣም አጠና ነበር፡፡ 2ኛ ክፍል አንደኛ ወጣሁ፡፡ እንደዚያ እያልኩ አንደኝነቴን እንዳስጠበቅኩኝ ቀጠልኩ፡፡
እስከ አምስተኛ ክፍል እንደሻው ት/ቤት ስማር ብዙም ትዝ የሚለኝ ከልጆች ጋር የነበረኝ ግንኙነት አልነበረኝም፡፡ ህይወቴ ሰፈር ውስጥ ነበር፡፡
ት/ቤት ሁላችንም የምንታወቅበት ጸባይ ይኖረናል፡፡ በአንድ ክፍል ውስጥ ደግሞ የተለያዩ እርከኖች ይኖራሉ፡፡ ታዲያ እስከ 5ኛ ክፍል የነበረኝን የት/ቤት(የክፍል) ማንነቴን ሳስበው ጎበዝ፣ መምህራን የሚወዱኝ፣ ጸባየኛ፣ አለቃ፣ ተማሪ የማይቀርበኝ፣ የሚጠላኝ አይነት ተማሪ እንደነበርኩኝ ማሰብ የጀመርኩት ከ10ኛ ክፍል ወዲህ ነው፡፡ ሳስበው መምህራኖቼን የሚያስደስት ከመሰለኝ ተማሪዎችን ተኩሼ የምገድል አይነት ተማሪ እንደነበርኩ ይሰማኛል፡፡ እውነት ነው፣ ተማሪዎች ሲረብሹ ሄጄ ለአስተማሪዎች ስማቸውን አሳልፌ እሰጥ ነበር፡፡ የእንደሻው ት/ቤት መምህራን ቅጣት ደግሞ አያድርስ ነው፡፡ እንደ አህያ ነው ተማሪ የሚጋረፉት፡፡ በዚያ ላይ ልጆች የፈተና ቀርቶ የቤት ስራ መልስ ሲጠይቁኝ እከለክላቸው ነበር፡፡ ለምን እንደማልሰጣቸው ሲጠይቁኝ ሃጢአት እንደሆነ እነግራቸዋለሁ፡፡ የቱ ነው ሃጢአት?
የወጋ ቢረሳ... ሳይሆን አይቀርም፣ ከአምስተኛ ክፍል በፊት ስለነበረኝ የት/ቤት ህይወት ብዙም አላስብም ነበር፡፡ ግን 10ኛ፣ 11ኛ ክፍል ከደረስን በኋላ፣ የድሮ የዚያኔ ጓደኞቼ "ድሮኮ ታስገርፈን ነበር"፣ "አቤት ምቀኝነትህ? መልስ አትሰጥም ነበር" እያሉ ሲያሸማቅቁኝ ነው ወደኋላ ማጠንጠን የጀመርኩት፡፡

የኔን ወላጆች ጨምሮ ብዙ ወላጆች የሚያዘወትሯት አንድ ሀረግ አለች፣ "የዚህ ዘመን ልጆች"፡፡

> የዚህ ዘመን ልጆች እንደሁ
> ምን ይሻላችኋል?
> ስንፍና ይለቅባችኋል፡፡

እናትና አባቴ "የዚህ ዘመን ልጆች እንደሁ እንዴት ትቀብጣላችሁ? እኛ ድሮ ያሳለፍነውን ብታውቁኮ እንዲህ አትሆኑም ነበር፡፡ በዝናብ ውስጥ ቆፍረን፣ በዝናብ ውስጥ አርመን፣ ይሄን ተሸክመን፣ ያንን ፈልጠን..." ከቧንቧ ውሃ መቅዳት ሲደብረን "እኛኮ ከየትና የት ነበር ለእናታችን ውሃ ቀድተን የምናመጣው፣ አንተ ከበር ላይ ወደ ቤት ውስጥ ማስገባት አቃተህ፣ ወይ ጊዜ!" ይላሉ፡፡ "እናንተማ የተመቻቸ ጊዜ ላይ ተወልዳችሁ ነው እንዲህ የምትቀብጡት፡፡ ድሮኮ ካባታችን ጎን ተቀምጠን ምግብ አንበላም ነበር፣ አሁን አጉል ዲሞክራሲ፣ ይኸው ዛሬ ልጆች... "፡፡ እኛ ቤት ታዲያ እንዲህ ሲሉ እኔና ወንድሜ እንናደዳለን፡፡ "ታዲያ እኛ ምን እናርግ? ጊዜው ነውኮ፣ ከጊዜው ጋር አብሮ መሄድ ነው" እንላቸዋለን፡፡ "ድሮኮ..." ሲሉ "ጊዜው ነውኮ..." እንላቸዋለን፡፡
እውነት ነው ያልተለወጠ ነገር የለም፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ፣ ከአመት ወደ አመት ከቀን ወደ ቀን የሰው አኗኗር እየተለወጠ ነው፡፡ እየተለወጠ የሌለ ነገር የለም፡፡ ከአለባበሱ እስከ አመጋገቡ፣ ካነጋገሩ እስከ አስተሳሰቡ፣ ከሚወደደው እስከሚጠላው፣ ከባህሉ እስከ እምነቱ በየጊዜው እየተቀየረ ነው፡፡ ይሄ የቀን ተቀን ወይም የአመት አመት ለውጥ በትወልድ ደረጃ ሲታይ ነው፣ ወላጆች ልጆቻቸውን "አቤት የዚህ ዘመን ልጆች!" ብለው የሚያማርሩት፡፡ የተቀየረውን ጊዜ አይተውም ከራሳቸው ጋር እያነጻጸሩ እንደ እድለኞች የሚቆጥሩን፡፡
በልጅነቴ በቲቪ አንድ የሚዘወተር፣ ተደጋግሞ የሚነሳ ሀሳብ ነበረ፡፡ ስለ ባህል፡፡ "ወጣቱ የራሱን ባህል ትቶ ወደ ነጮቹ እያዘነበለ ነው፡፡ የሀገሩን ልብስ፣ አመጋገቡን፣ የሀገሩን ባህል እየናቀ ነው" አይነት ወሬ ይበዛ ነበር፡፡ "ባህላችንን ማሳደግ፣ ዘፈኖቻችንን በአለም አቀፍ ደረጃ ተሰሚ ማድረግ፣ በጥበብ ስራዎቻችን ሀገራችንን ማስተዋወቅ፣ ገጽታ ግንባታ..." ይባል ነበር፡፡ ከዚያ እያወሩ ይውሉና "አሁን ደግሞ የማይክል ጃክሰንን እንዲህ እንዲህ የሚለውን ዘፈን እንጋብዛችኋለን፣ መልካም ጊዜ" ይላሉ፡፡

በኔ የልጅነት ጊዜ በማህበረሰቡ ውስጥ የሴቶች አለባበስ የሚገርም ለውጥ ያሳይ ጀመር፡፡ በሙቱ ሴቶች ጂንስ ሱሪ የማይለብሱበትን ጊዜ አስታውሳለሁ፡፡ ቀስ በቀስ ሱሪ መጣ፣ ቀሚስ ማሳጠር፣ የሱሪ ስፋት መጥበብ፣ መገላለጥ እያለ መጣ፡፡ በሌላ በኩል ፊልም ላይ አጫጭር ቀሚስ፣ ፓንትና ጡት ማስያዣ ብቻ አርገው ሲሄዱ ስናይ፣ "እነዚህ ፈረንጆች ትንሽ ቆይተው እራቁታቸውን መሄድ መጀመራቸው አይቀርም" እንል ነበር፡፡
ድሮ እንግሊዘኛ ፊልም ስናይ በጣም እንቆቅልሽ ይሆንብን ነበር፡፡ ተኩሱ፣ ደሙ፣ ውጊያው፣ ሁሉም እውነት የሚመስለው ነገር፡፡ ቆይቶ ቆይቶ ነው በቲቪ ፊልም እንዴት እንደሚሰራ፣ ሲሰራ ምን እንደሚመስል ማየት የጀመርነው፡፡ ሌላ ስለ ፊልም የሚያስገርመን ነገርም ነበረ፡፡ ያ የሚሳሳሙት ነገር፡፡ "ትንሽ አያፍሩም እንዴ ፊልም ላይ ሲሳሳሙ?" እንል ነበር፡፡ "ባል፣ ሚስት የላቸውም እንዴ?"

ስለ ፈረንጅ ሳነሳ ድሮ ፈረንጅ ማየት ብርቅ ነበረ፡፡ አልፎ አልፎ ባመት አንዴ ስናያቸው ዩ ዩ መኒ መኒ እንላቸው ነበር፡፡ “አይ ላቭ ዩ” ምናምን፡፡ ከዚያ ስናድግ ያው ፈረንጅ ሲያዩ ማካበድ ፋራነት ይሆናል፡፡ ባጠገባችን ሲያልፉ ላለማፍጠጥ መታገል ነው፡፡
ስለ ፈረንጆች እየሰማን ያደግነው ነገር ይኖራል፡፡ የምናወራው፡፡ “ፈረንጆችኮ ሀብታም ናቸው”፣ ”አሜሪካ ብወለድ በና፣ አይስ ክሬሜን እንደፈለግኩ እየበላሁ፣ ቸኮሌት፣ ሁሉም ነገር አለኮ እዛ”፣ “አሜሪካ ብትወለድኮ በና መመታት የለም”፣ “በና በቤት መኪናህ እንደፈለግክ ነውኮ የምትሽከረከረው”፣ “እዛኮ በና ጭቃ የለም፣ አስፓልት ብቻ ነው፣ ስትተኛ ጫማ ማውለቅ የለም”፣ “መጫወቻ ነፍ ነው”፣ “በና አሜሪካ ሄድክ ማለትኮ ገነት ገባህ ማለት ነው” እያልን ስለ ነጩ አለም ተመስጠን እንጓጓለን፡፡ ስለጊዜ አጠቃቀማቸው ምናምንም እንዲሁ ይወራል፡፡

ቶም አንድ ጄሪ ከዲቪዲ መምጣት በኋላ ትንሽ ቆይቶ በጣም የምናየው ካርቱን ፊልም ነበረ፡፡ ቶም(ድመቱና) ጄሪ(አይጧ) የሚሰራሩት ተንኮል ያው እንደሚታወቀው በጣም አስቂኝ ነው፡፡ በተለይ ያኔ፡፡ በዲስክ እየተሻማን፣ በልጆች ጊዜ ላይ ደግሞ በጉጉት ነበር ጠብቀን የምናየው፡፡ከአንድ አመት ህጻን እስከ ሽማግሌ የማዝናናት አቅም ያለው በጣም አስቂኝ ሆሊውድ ስራት ነው፡፡ ታዲያ ቶም ኤንድ ጄሪ ሁሌም በሚያስቅ ተንኮል ጀምሮ በሚያስቅ ተንኮል ነው የሚያልቀውና፣ እኔ በልጅነት አዕምሮዬ በተለይ በኢቲቪ የልጆች ጊዜ ላይ ሲያመጡት “እንዴ፣ ይሄ ነገር ተንኮል አይደለም እንዴ? ልጆችን ተንኮል አያስተምርም? ለምንድነው በልጆች ጊዜ ላይ የሚያሳዩት?” ብዬ ራሴን እጠይቅ ነበር፡፡ እንዲህ የምለው “ልጆች እንደ ነጭ ወረቀት ናቸው” የምትለዋን አባባል የሰማሁ ሰሞን ሳይሆን አይቀርም፡፡ ወይም ልጆች የሚያዩአቸውን ፊልሞች ወላጆች ሊመርጡላቸው ይገባል የምትለዋን የሰማሁ ሰሞን፡፡

እንዳለ በተማርኩባቸው በተለይ በመጀመሪያዎቹ አመታት አሪፍ የእንግሊዘኛ መምህራን ነበሩን፡፡ እሮብን “English day of the week” ብለው የሰየሙት ማለት ነው፡፡ እሮብ እሮብ እንግሊዘኛ ዲያሎግ ሸምድደን እናቀርብ ነበር፡፡ እንግሊዘኛ የመቻል ፍላጎታችን ምን ያህል እንደነበረ በማስረዳት አንባቢዬን ማሰላቸት አልፈልግም፡፡ በሁላችንም ልብ ውስጥ እኩል ተሰራጭቶ ስላለ፡፡ አላምንም የሚል ቢኖር እንኳን ብዙ የአማርኛ ፊልሞችን በማስረጃነት ማቅረብ እችላለሁ፡፡ ቶም ኤንድ ጄሪ በተንኮል ጀምሮ በተንኮል እንደሚያልቅ፣ በእንግሊዘኛ አነጋገር ለማሳቅ በመሞከር ጀምረው፣ እንግሊዘኛ ባለመቻል ለማሳቅ በመሞከር የሚያልቁ ብዙ decomedy ፊልሞች አሉን፡፡
እንደ ት/ቤት እንዳለ በከተማው ከሁሉም በተለይ በእንግሊዘኛ የተሻለ ስለነበር ከሌላ ት/ቤት ተማሪዎች የተሻለ እንግሊዘኛ የመቻል እድል ይኖራል፡፡ ከክፍሉ ቁንጮ ተማሪ ሲኮን ደግሞ ከት/ቤቱም የተሻለ የመሆን እድል ሰፊ ይሆናል፡፡
እንዳለ ከተማርናቸው እንግሊዘኛ መዝሙሮች መሀል፡

Sometimes I feel good
Sometimes I feel bad.
Learning is aha aha good tea
Singing is aha aha good tea...

=//=

I am a boy she is a girl
We are equal in nature
But only the gender
I can do what she does
She can do what I do
Girls lack opportunity
But they have ability....

አንደኛ ሀለተኛ ክፍል ስማር ስንቴ ቤታቸው የነበሩ የድሮ የኦሮምኛ ተረቶችን ያነብልኝ ነበር፡፡ ይመስጡ ነበር፡፡ እንደሻው 3ኛ ከፍል ስማር ላይብረሪ ውስጥ ምትሀተኛው ተራራ የሚል አንድ የተረት መጽሐፍ አገኘሁ፡፡ አማርኛ ፊደል መቁጠር ጀምሬ ነበርና አማርኛ ለማንበብ እሞክር ነበር፡፡ በተረት መጽሐፉ ላይ የነበሩ ታሪኮች፣ በተለይ የመጀመሪያው፣ ርእሱ “ምትሀተኛው ተራራ” የሆነው ተረት ምንም አልገባኝም ነበር፡፡ በግድ ነው ራሱ አንብቤ የጨረስኩት፡፡ ንባቡ ሳያስቸግረኝ አልቀረም፡፡ ግን እየቀጠልኩ...”ምትሃተኛው ተራራ”... “አውራ ጣት”...”ሶስቱ ወታደሮች” እያልኩ ስሄድ ታሪኮቹ እየገቡኝ፣ እየተገለጡልኝ መጡ፡፡ በተለይ መጨረሻ ላይ ያለውን የሶስቱን ወታደሮች ታሪክ አሁንም አልረሳሁትም፡፡ ምትሀተኛው ተራራን አንብቤ ስጨርስ አማርኛ በትክክል ማንበብ ችዬ ነበር፡፡
የት/ቤት ላይብረሪ እየተመላለስኩ ያነበብኩት የታዳጊዎች የተረት መጽሐፍ በጣም ስለተመቸኝ የክፍሌን ልጆች፣ የማገኘውን ሰው ሁሉ የተረት መጽሐፍ እንዳለው መጠየቅ ጀመርኩ፡፡ ጎረቤታችን ሚጡ እንደ ምህታተኛው ተራራ አይነት ሌላ “ምስጢራዊው መንደር” የተሰኘ መጽሐፍ ሰጠችኝ፡፡ “የሰው ነው፣ ነገ እመልሰዋለሁ ለዛሬ ብቻ ነው የምሰጥህ” ብላ ስለሰጠችኝ ከት/ቤት ስገባ እንደ ወትሮው ከነሳሚ፣ ከነኢየሩስ ጋር ወጥቼ መጫወት ትቼ ጊዜ ሳላባክን ከት/ቤት እንደገባሁ ማንም ጠርቶ የማይረብሽኝ ቦታ፣ ማለት ቤት ሆኜ፣ ቤት እንዳለሁ እንዳይነቃ፣ ተደብቄ ግማሽ ያህሉን አነበብኩት፡፡ በነጋታው ሳልጨርሰው መለስኩላት፡፡ ይሄኛው ደግሞ ከዚያኛው ይበልጥ ነበር፡፡ “ጮሌው ዮሀንስ” ለምሳሌ በጣም ደስ የሚል ተረት ነው፡፡ ከዚያ ቀጥዬ አስማተኛዋ አሮጊትን፣ 3ቱን የልጆች አለም የተረት መጽሐፍትን አነበብኩ፡፡ ይጣፍጣሉ፡፡ አንድ መጽሐፍ እንግዲህ ወደ አስር ተረቶች ይኖሩታል፡፡ ራፑንዘል፣ ስኖው ውሃይት፣ ሲንደሬላ፣ ካነበብኳቸው ውስጥ፣ ፊልም ከተሰራባቸው መካከል ናቸው፡፡ `Maleficent` የተሰኘው የአንጀሊና ጆሊ ፊልም መሰረት ተደርጎ የተሰራበትን ተረትም አንብቤዋለሁ፡፡

አራተኛ ክፍል አንድ የክፍሌ ልጅ አምጥቶልኝ ክፍል ውስጥ “Godaannisa” የተሰኘ ልቦለድ መጽሐፍ አነበብኩኝ፡፡ ታሪኩ ረጅም ስለ ነበረ ምንም አልገባኝም፡፡ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች...ጫማውን ሲያስጠርግ...ሀረማያ ዩኒቨርሲቲ...ድሬደዋ....ጭሮ ከተማ...ብቻ ምንም አልገባኝም፡፡ ግን ለመጀመሪያ ጊዜ ያነበብኩት ሙሉ ልቦለድ ነበር፡፡

አምስተኛ ክፍል 96 አምጥቼ አንደኛ ብወጣም፣ ክፍሉ 5A የነበረው (እኔ B ነበርኩ) በቅርቡ(ያኔ) ሰፈራችን የገባው ሱራፌል ፈረደ በነጥብ በልጦኝ ከአል አንደኛ ወጣ፡፡ አዲስ ተፎካካሪ፡፡ ሂሳብ በጣም ይችላል፡፡

ከሚሊኒየሙ ወዲህ የኢትዮጵያ የፊልም እንደስትሪ እያደገ መጣ፡፡ እውነቱን ለመናገር የተወለደውም ከሚሊኒየሙ ወዲህ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በፊት ፊልም በጣም አልፎ አልፎ ስለሚሰራ፡፡ በርግጥ የቲቪ ድራማዎች ነበሩ፡፡ከጥራት አንጻር ሲታይ ከነስርየትና ከነየወንዶች ጉዳይ ወዲህ የተሰሩ ፊልሞችን ፊልም ማለት ስለሚከብድ “የኢትዮጵያ የፊልም ኢንደስትሪ ተወልዶ ማደግ ተሳነው፣ ተወልዶ፣ መራባት ጀመረ” ማለት ይቀላል፡፡ በርግጥ ከዚያ ወዲህ የአማርኛ ፊልሞች እንደ ጎርፍ ነበር መጉረፍ የጀመሩት፡፡ በመጠኑ ታድያ እናይ ነበር፡፡ ሀገርኛ እንደ መሆናቸው ይመረጡ ነበር፡፡ በተለይ አማርኛ እንደ መሆናቸው፡፡ ያው የምንሰማው ቋንቋ ስለሆነ ከማንሰማው እንግሊዘኛ ማስበለጣችን የሚገርም ነገር የለውም፡፡ቀስ በቀስ ሰው ትኩረቱን ወደ ሀገሩ ፊልሞች መመለስ ጀመረ፡፡ እንግሊዘኛ ፊልም 3 ብር ነበር የሚከራየው፡፡ አማርኛ 5 ብር ሆኖ እንግሊዘኛ ወደ 2 ብር ሲወርድ በእድሜዬ ታዝቤአለሁ፡፡

ዘፈንን ክርስትያን ከሚባሉት እንደኛ እንደ ጴንጤዎች የሚያወግዝ የለም፡፡ አንድ አባባል አለ፡፡ እኔ አየሁ አንጂ አላደረግኩም፡፡ እኔ ሰማሁ እንጂ አልዘፈንኩም፡፡ ብዙ ጴንጤዎች አልዘፍንም፣ ዘፈን አላዳምጥም ይላሉ፡፡ በርግጥ ሀሳባቸው ስራዬ ብለው የዘፈን ካሴት እንደማይገዙ፣ ወይም ስራዬ ብለው ስልካቸው ላይ ዘፈን እንደማያስጭኑ ለመግለጽ ነው፡፡ እኔም ከማያዳምጡት ሳይሆን ከማይዘፍኑት መካከል ነበርኩ፡፡ ማዳመጥማ ቲቪ ወይም ሬድዮ ኖሮት ዘፈን የማያዳምጥ ሰው የለም፡፡ በርግጥ አንድ ቀን እነኢየሩስ ጎረቤታችን፣ ገና እንደገቡ አባታቸው ጋሽ ተሰማ በቲቪ ዘፈን ሲመጣ ሚዩት አድርገው ድምጹን ሲያጠፉ አይቼ ተገርሜአለሁ፡፡
 መዝፈኑንም ቢሆን ተደብቀን እንዘፍን ነበር፡፡ መርካቶ ሰፈሬ ችላ ችል አትበይ አይተሽ መቸገሬን፣ አንቺ ቢራቢሮ፣...ኦማሂሬ...፣ ቼ በል ጋሜ...ምሽት የእግር ጉዞ ባዳማ ከተማ...ኤሰ ጂርቲ ኢንተልቲ...፣ ዲምቢ ለዲምቢ...ቅዳሜ ገበያ ልሄድ አሰብኩና...yaa damaallaseetoo yaa damaallaseetoo... በቲቪና በተለያዩ አጋጣሚዎች በልጅነቴ ስሰማቸው ከነበሩ ዘፈኖች መሃል ናቸው፡፡
ዘፈን ከማዳመጥና ከመዝፈንም በላይ ግን ዘፈንን በጣም እንኮንን ነበር፡፡ በተለይ መዝፈኑን፡፡ “መስማት ችግር የለውም እስካልዘፈንክ” የሚል ነበር ለመስማቱ የነበረን የኩነኔ ልስላሴ፡፡

እንግሊዘኛ ዘፈን ምንም ስሜት አይሰጠንም ነበር፡፡ እንግዲህ ድሮ እንግሊዘኛ ዘፈን ከተባለ ማይክል ጃክሰንን ብቻ ነው የማውቀው፡፡ አንድ ኢቲቪ ላይ የማይክል ጃክሰንን ዘፈን ሲያመጡ ግራ የሚገባኝ ነገር ነበረ፡፡ ኮንሰርት ላይ እሱ ሲዘፍን ሰዎች ያለቅሳሉ፣ ይጮሀሉ፣ ራሳቸውን ይስታሉ፣ በስትሬቸር ይወሰዳሉ፡፡ መአት ህዝብ እንደ እብድ ያረገዋል፡፡ ምንድነው እንደዚህ የሚያረጋቸው ብዬ ይገርመኝ ነበር፡፡

በልጅነታችን ተጫውተናል፡፡ ኳስ፣ እጅ ቦንብ፣ እሩጫ...ከቁማር፡ ብይ፣ ቆርኪ፣ ፖስተር፣ የሞባይል ካርድ፡፡ ቡሄ፣ ሆያ ሆዬ መሄድ...

 ቸርች እንደማንኛውም ህጻን ነበርኩ፡፡ መካነ ኢየሱስ ሰንበት ት/ት እማር ነበር፡፡ ሌላው ኮንፈረንስ እወድ ነበር፡፡ ከነሳሚ ጋር የማይረሱ የኮንፍረንስ ትዝታዎች አሉን፡፡ ኮንፍረንስ ሲኖር አቤት ደስታችን? አንቀርም ነበር፡፡ የምንወደው ደግሞ ለዝማሬውና ለአምልኮው ነው፡፡ እነሳሚ እነአቢቲ እነኢየሩስ፣ ብዙ ሆነን ነበር የምንሄደው፡፡ ኮንፍረንስ ሲኖር ሁሉም ነገር ሞቅ ይላል፡፡ ቢሊሴ አንዴ መቱ አርነት ቸርች የመጣች ጊዜ ድንቅ ነበር፡፡

Amman gubaa garaa diina koo
Nan bobeessaa garaa masaanuu koo
Darabee dhaan ahaahaa darabee dhaan
Dinni koo utuu eeguu baduuf salphachuu koo...

መሰረተ-ክርስቶስ ቸርች መድረኩ በጣም ከፍ ያለ ነው፡፡ ቦታ ስለማይበቃ ህጻናት ፊት ለፊት ሰሌን ተነጥፎልን መሬት እንቀመጣለን፡፡ አሁንም ሰው ሲበዛ አስናጋጆቹ ያስነሱንና ሰሌናችን ለትልቅ ሰዎች ይሰጣል፡፡ ከዚያ ቦታ ሲጠፋ መድረኩ ላይ ወጥተን ጠርዙ ላይ ወደ ህዝቡ ዞረን እንቀመጣለን፡፡ አስበከዋል? ወይ የልጅነት ነጻነት!
የመዝሙር ጊዜ እንግዲህ ይዘለላል፡፡ የመዝሙር ጊዜ መድረክ ላይ ወጥቼ የዘለልኩባቸው ሁለት አጋጣሚዎች ትዝ ይሉኛል፡፡

1. መሰረተ-ክርስቶስ መገርሳ መጥቶ Leenca Qaraaniyooን የዘመረ ጊዜ፣
2. ሁለገብ አዳራሽ አንድ ስሙን የማላውቀው ሰውዬ መጥቶ በቃለ ህይወት ኮንፈረንስ ላይ ያስመለከ ጊዜ፡፡

የኛ ቸርች(መካነ-ኢየሱስ) መዝለል፣ መጨፈር አይቻልም፡፡ ቀዝቀዝ ያለ ነው፡፡ ብዙ ሰዎች ቅዝቃዜውን አይወዱትም፡፡

ድሮ ለዱሪዬነት ያለን አስተሳሰብ አለ፡፡አስጸያፊ ቃላትን የሚጠቀም፣ አቅመኛ ነኝ ባይና በቃ የሆነ ዱሪዬ የሆኑ ልጆችን "ዱሪዬ ነው" እያልን እንሸሻቸው ነበረ፡፡

እንደሻው ት/ቤት ስማር የC ክፍል ተማሪዎች በጣም ይመቹኝ ነበር፡፡ ቀርቤአቸው አላውቅም ግን በሩቁ ይመቹኝ ነበር፡፡

አምስተኛ ክፍል ስንገባ saayinsii naannoo(አካባቢ ሳይንስ) ወደ saayinsii bu'uuraa(መሰረታዊ ሳይንስ) ተቀየረ፣ ሲቪክ(የዜግነትና ስነ-ምግባር ት/ት)፣ ሙዚቃ፣ ጥበባት፡፡ ሲቪክ ላይ መጀመሪያ ያለው ስለ ዲሞክራሲ ነው፡፡ "ዲሞክራሲ የህዝብ፣ በህዝብ፣ ለህዝብ የሚሰራ አስተዳደር ነው" በአብረሃም ሊንከን፣ የምትለዋ አባባል ትዝ ትለኛለች፡፡ ትመቸኝ ነበር፡፡

አንደኛ ወይም ሁለተኛ ክፍል ስንማር ጓደኛዬ ሳሚ ከቤታቸው ውስጥ አንድ ነጭ መጽሐፍ አውጥቶ አሳየኝ፡፡ ሽፋኑ ላይ 666 ምናምን ተብሎ ተጽፎበታል፡፡ ሳሚ እንደነገረኝ "በመጨረሻው ዘመን፣ ሰይጣን መጥቶ ከኔና ከእግዚአብሔር ምረጥ ይለናል፣ እሱን ከመረጥን 666 የሚለውን ምልክት ግንባራችን ላይ ይለጥፍልናል፣ እግዚአብሔርን ካልን አንገታችንን በሰይፍ ይቀላዋል፡፡" ያስፈራል፡፡
መቱ ውስጥ አንድ ህጻናትን የማረድ ወሬ አለ፡፡ድሮ ማታ በኛ ሰፈርና በሶር ወንዝ አርጎ ወደ አዲሳባ በሚወስደው መንገድ ላይ አብዲቦሪን አልፈን መሄድ በጣም ነበር የምንፈራው፡፡ ምክንያት፡ "ህጻናትን የሚያርድ ሰው ያገኛችኋል" ይባላል፡፡ ህጻናትን ይዞ የሚያርድ ሰው፡፡ ቤቱም እዚያው ሶር አካባቢ ያለ ጫካ ውስጥ ነው ይባል ነበር፡፡ ለምንድነው ልጆችን የሚያርደው ብለን ስንጠይቅ፣ "ለባለ ወፍጮ ቤቶችና ለነጋዴዎች ደማቸውን ይሸጣል"፡፡ አዲስ ወፍጮ ቤት ሲተከል፣ ወፍጮው በሚተከልበት መሬት ላይ የህጻን ልጅ ደም ያፈሳሉ የሚባለውን ወሬ መስማት ከጀመርኩ ቆየሁ፡፡ እንዴት? ለምን? ምን ያረግላቸዋል? ግራ ያጋባል፡፡ ጥቂት ቆይቶ 2ኛ ክፍል ምናምን ስማር የዘንዶ ወሬ፣ "ዘንዶ እየቀለቡ ነው ሀብታም የሆኑት..."፡፡ እኛው ሰፈር ራሱ ደግሞ ዘንዶ ሲቀልቡ ኖረው ዘንዶው ከጉድጓዱ ወጣና ሰው ገድሎት ወዲያውኑ ቤታቸውን ለቅቀው ከከተማ የጠፉ ሰዎች ነበሩ፡፡ "አይደረግም አይባልምኮ"፡፡

ትዝ ይለኛል ቀኑ፡፡ የመጀመሪያው ገመና ድራማ ላይ መሰረት መብራቴ ሰራተኛ ሆና፣ ሳምሶን ታደሰ(ቤቢ) ሰአሊ ሆኖ የሠው ቤት እየኖሩ፣ በጥፊ የምታጮለው ትእይት ላይ፣ በጥፊ ጯ እንዳደረገችው መብራት ድርግም አለ፡፡ ያን ቀን ሌላ የማስታውሰው ሽንት ቤት ተደርምሶበት በሞተው አስተማሪ ነው፡፡ ያን እሁድ ነበር በሱ ላይ ሽንት ቤት በቤተሰቡ ላይ አለም የተደረመሱት፡፡ ትዝ ይለኛል ቀኑ፡፡ ያን ቀን ውሃ ጠፍታ ሶስት ቀን ሆኗታል፡፡ አስተማሪው መብራት ሲጠፋ ወደ ሽንት ቤት ሄደ፡፡ እኛ ደግሞ ወደ ወንዝ፡፡ ከነሳሚ ጋር ድራማው እንዳለቀ ውሃ ለመቅዳት ለመሄድ ተመካክረን ነበር፡፡ በ6 ሊትር ትንሽ ጄሪካን ውሃ ለመቅዳት ልሄድ ስል የአክስቴ ልጅ ትዕግስት፣ "አትሂድ በቂ ውሃ አለ፣ ደግሞ በዚህች ጄሪካን አምጥተህ ምን ይጠቅማል" እያለችኝ ነበር፡፡ እኔም ውሃ መጥፋቱ አሳስቦኝ አልበረም ። ሰአት ካለፈ 6 ሊትር ጄሪካኔን ይጌ ወንዝ ለመሄድ ጓደኞቼን ፍለጋ የወጣሁት፡፡ ወንዝ መሄድ ብርቅ ሆኖብኝ እንጂ፡፡ "ለአድቬንቸር" ነው የሚሉት? ሳሚን ፍለጋ ቤታቸው ስሄድ፣ ቤት አለነበረም፡፡ አቢቲም አልነበረም፡፡ ጥለውኝ ሄደው ይሆናል ብዬ ብቻዬን ሄድኩኝ፡፡

ከኛ ሰፈር ዋናውን መንገድ ተሻግሮ፣ በአቡነ-ጴጥሮስ ት/ቤት መጨረሻ ላይ ቦሶቃ የተባለች ምንጭ አለች፡፡ እኔ ከአስፋልቱ ላይ፣ "እዚያ ጫካ ውስጥ ነው" ከመባል የዘለለ፣ ከመንገድ ወርጄ ውሃይቱን አይቼያት አላውቅም፡፡ ዝም ብዬ ወረድ ወረድ ብዬ ስሄድ፣ እነሳሚ ይኖራሉ ብዬ የጠበቅኩትን፣ ማንም አልነበረም፡፡ ምንጯ ራሷ አልነበረችም፡፡ በጋ ስለነበር ደርቃ ሊሆን ይችላል፡፡ የማረገው ሲቸግረኝ፣ ትንሽ ወደታች ወርዶ እኔ የማውቃት የውሃ ጉድጓድ ነበረችና ወይ እዚያ ካገኘኋቸው፣ ካላገኘኋቸውም ቀድቼ ብቻዬን ልመለስ ብዬ ሄድኩኝ፡፡ ስሄድ እነሱ አልነበሩም፡፡ በነሱ ፋንታ እየቀዳሁ እያለሁ ሌላው ጎረቤታችን ስጦታ መጣ፡፡ እስኪቀዳ ጠብቄው፣ አብረን እየተመለስን "ስድስት መቶ" መንገዱ ላይ የአቢቲ አባት ጋሽ ለሚና ሌላ ሶስት ትላልቅ ሰዎች ወደ ታች እየወረዱ መጡብን፡፡ ጋሽ ለሚ "እነማሙሽኮ አሁን ገና ነው ሶር የሄዱት፣ አላያችዋቸውም?" አሉን፡፡ እሳቸውን ሰምተን እየተመለስን አቢቲና ሳሚ ከ6 አመቱ የሳሚ ወንድም ከያዕቆብ ጋር እየሮጡ መጡብን፡፡ የት እየሄዳችሁ ነው? አልኳቸው፡፡ ውሃ ለመቅዳት አሉኝ፡፡እኔና ስጦታ ከቀዳንበት ለመቅዳት ነበር አመጣጣቸው፡፡ "ኑ ሶር እንሂድ" አልኳቸው፡፡ "ጋሽ ለሚኮ አሁን አሁን ነው፣ እነማሙሽ ከሶር ውሃ ለመቅዳት ሄዱ ያሉኝ" አልኳቸው፡፡ ሶር ወንዝ ሄጄ አላውቅም ነበር፡፡ በ6 ሊትር ጄሪካን የቀዳሁትን ውሃ በአዲሱ ገና ሬንጁ ተጨምሮበት ያልደረቀው አስፓልት ላይ ደፍቼና ስጦታን ተሰናብቼ ከነሳሚ ጋር ወደ ኋላ ወደ ሶር መሽምጠጥ ጀመርን፡፡ ሶርን ከኛ መሀል አይቶ የሚያውቅ አልነበረም፡፡ ሶር እሩቅ እንደሆነ ሰምተናል፣ አቋራጭ መንገድ እንዳለውም እናውቃለን፡፡ አቋራጩ መንገድ ግን ጫካ ከመሆኑና ከማስፈራቱም በላይ አናውቀውም፣ ልንጠፋ እንችላለን፡፡ በአስፓልት ግን፣ ቀጥ ብለን ድልድዩ ጋር እስከንደርስ መሄድ ብቻ ነው፡፡ እነጋሽ ለሚም በቅርቡ ባጠገቤ እንዳለፉና እንደምናገኛቸው እየነገርኩ፣ የፈሩትን ጓደኞቼን አበረታታኋቸው፡፡ ሄድን ሄድን፣ ካሰብነው በላይ ይርቃል፡፡ ኩርባዎቹ አያልቁም፡፡ ምንድነው ድልድዩ ጋር አንደርስም እንዴ? አልን፡፡ እነለሚ የት አሉ አለ አቢቲ፡፡ ችግሩ የአቋራጯን መንገድ፣ መግቢያዋን እንጂ ውስጧን አለማወቃችንና በዚያ መሄድ መፍራታችን ነበር፡፡ ሶር ድልድዩ ጋር ደርሰን ወደ ውሃው ስንሄድ ወላ ማሙሽ፣ ወላ ኤደን፣ ወላ ማንም አልነበረም፡፡ እነጋሽ ለሚም የት እንደገቡ አናውቅም አልመጡብንም፡፡ ግራ ገባን፡፡ በአቋራጯ መንገድ ገብተዋል ማለት ነው፡፡ ውሃው፡ እንደዚያ የሚተልቅ ወንዝ አይተን የማናውቅ ሰዎችና ጊዜው መሸት ያለ ሆኖ በጣም ያምር ነበር፡፡ ለማዳነቅ ጊዜ አልነበረንም፡፡ ቶሎ ውሃችንን ቀዳድተን መመለስ ነበረብን፡፡ ቀዳድተን እግራችንን ውሃው ውስጥ ነክረን፣ ወደቤታችን ለመመለስ ተዘጋጀን፡፡ እነሱም ትናንሽ ጄሪካኖችን ነበር የያዙት፡፡ መመለሻችን የግድ በመጣንበት መሆን ነበረበት፡፡ እዚያ ደግሞ የአቋራጯ መንገድ መግቢያ በየት እንደሆነ ራሱ አላወቅንም፡፡ እየጨለመ ነበር፡፡ ቶሎ መመለስ ጀመርን፡፡ ከወንዙ ወደ አስፋልቱ ተመለስን፡፡ መመለሻው ግን እንደ መምጫችን አልነበረም፡፡ ውሃ ይዘን ብዙም መሄድ አልቻልንም፡፡ መሸብን፡፡ ብዙም ሳንሄድ ምሽትሽት አለብን፡፡ ፈራን፡፡ ከቤት ምን ይሉናል? እየሄድን እየሄድን አንድ ደብል ጋቢና ፒክ አፕ መኪና እኛ ጋር ደርሳ አቀዘቀዘችና ሾፌሩ ምልክት ነግሮን የሆነ ልጅ አይተን እንደሆነ ጠየቀን፡፡ እንዳላየነው ነገርነውና አልፎን ሄደ፡፡ ይኸኔ ነበር ለቅሶ የተጀመረው፡፡ ሳሚ "ወይኔ አበባ ትገለኛለች፣ ስዩም እንኳን የለም" እያለ ማልቀስ ሲጀምር ወንድምየው ተከተለው፡፡ ትንሹ ያዕቆብ፡፡ "እሱንም ያቁቤን ይጌ በዚህ ሰአት፣ አለቀልኝ" እያለ ያለቅሳል፡፡ አቢቲ ደግሞ ጀመረ፡፡ እያለቀሱ መሄድ ጀመሩ፡፡"ወዮ ጉዴ" እያሉ ለቅሶ ቅዳ ለቅሶ መልስ ሆነ፡፡ እኔ ደግሞ በነሱ ለቅሶ እስቃለሁ፡፡ ግን እኔ አልፈራሁም ማለት አይደለም፡፡ እነሱ እያለቀሱ ሄደን ሄደን፣ በተለምዶ ስድስት መቶ

የሚባለው ቦታ ኩርባ ጋር ደረስን፡፡ መንገዱ ገና ተሰርቶ አላለቀም ነበርና ከመንገዱ ዳር ቦዩ ተቆፍሮ፣ ግን ገና አልተሰራም ነበር፡፡ ያን ጊዜ በጣም ጨልሞ ነበር፡፡ በግራ መስመር ላይ እየሄድን ኩርባውን እየተጠማዘዝን እንዳለን አንድ ሲኖትራክ ገልባጭ መኪና ከየት መጣ ሳይባል ዥው ብሎ አጠገባችን ሲያልፍ ሁላችንም በድንጋጤ ዘለን ቦይው ውስጥ ገባን፡፡ አጠገባችን ያልኩት ወደ ጎን ስለዘለልን ብቻ ነው፡፡ ለጥቂት ነበር የተረፍነው፡፡ ያ ድንጋጤ ለቅሶአቸውን አስረሳቸው፡፡ አሁን ደግሞ ስለ ድንጋጤውና ስለመዝለሉ በግርምት ማውራት ተጀመረ፡፡
ስንመለስ፣ መንገዱ ስንሄድ ከነበረው ሶስት እጥፍ ይሆናል የረዘመው፡፡ "አንደርስም እንዴ?" ብለው ሲያለቅሱ ነበር፡፡ አንድ ስንሄድ በየመሀሉ እየሮጥን ነበር፡፡ ስንመለስ፣ ውሃ ስለያዝን መሮጥ አንችልም፡፡ ሁለተኛ እንዳልኩት ስንሄድ ቁልቁለታማ ስንመለስ ደግሞ ያው ዳገታማ ነበረ መንገዱ፡፡ ሶስተኛውና ዋነኛው በጣም ቶሎ ቤት መግባት ፈልገን ነበረ፡፡ ስድስት መቶ ከደረስን ወዲህ ውሃችንን እያፈሰስን መቀነስ ጀመርን፡፡ ስድስት መቶ አካባቢ ማለት የደህናውን ጊዜ ውሃ ደፍቼ፣ ስጦታን ተሰናብቼ እነሳሚን ሶር እንድንሄድ ያገፋፋሁበት ቦታ ነው፡፡ ታዲያ የዚያ ቀን ትዝታችን ጊዜው ከራቀ፣ 10ኛ ክፍል ከገባሁ በኋላ ስለዚያች አጋጣሚ ሳስብ ይዘን የነበረውን ውሃ ደፍተን ቶሎ ቶሎ መሄድ ስንችል ጻበል ይመስል ተሸክመን መጓተታችን ያስገርመኝ ነበር፡፡ እኔ አትሂድ እየተባልኩ ነበር የሄድኩት፡፡ የእነሱንም ውሃ የፈለገ ሰው እንዳልነበረ እርግጠኛ ነኝ፡፡ ግን ውሃችንን እየጎተትን ቤት ስንደርስ ሁላችንም ራሳችንን ለግርፊያ አዘጋጅተን ነበር፡፡ ከትንሹ ያዕቆብ በስተቀር፡፡ በተለይ ትንሹን ልጅ ያመጣው ሳሚ፡፡ ያን ምሽት ቤት ስንደርስ ሁለት ሰአት አልፎ ነበር፡፡ የረሳሁት ነገር፣ እናቴ እሁድ እሁድ ማታ የሴቶች የጸሎት ፕሮግራም ነበረባትና ቤት አልነበረችም፡፡ አባቴ ደግሞ ብዙም አላካበደም፡፡ ብቻ ከጠበቅኩት በተቃራኒው ነበር የጠበቀኝ፡፡ ውሃውን ለካስ ከምሽቱ ከሁለት ሰአት በኋላ ውሃ ቀድተን መጣን፣ እሱንም ከሶር ውሃ ቀድተን መጣን ስንል በማስረጃነት ለማቅረብ ነው ሳንደፋ እስከ ቤት ድረስ ይዘን የገባነው፡፡ አስበን ተነጋግረንበት ባይሆንም ማለት ነው፡፡ ትንሽ ቆይቶ ሳሚ ትንሹን ወንድሙን ያዕቆብን ይዞ እኛ ቤት መጣ፡፡ ለካስ አበባ እኛ ቤትና እነማሙሽ ቤት አጥታቸው እነሱን ፍለጋ ወጥታለች፡፡ ተፈልጋ ልጆቹ ቤት እንደደረሱ ተነገራት፡፡ ሳሚ አለቀለት በቃ፡፡ ያን ማታ ሳሚ በዚያ ምሽት ህጻኑን ልጅ ከኛ ጋር በማንከራተቱ፣ትንሽ ማሰብ ስላቃተው "ትንሽ እንኳን አታስብም?" እየተባለ ስለሚቀጣው ቅጣት እያሰብኩ ተኛሁ፡፡ አቢቲስ ምን ተብሎ ይሆን? በነጋታው ሳሚ ተገድሎም ቢሆን ለመቅበር ወደ ቤታቸው ፈጠን ፈጠን እያልኩኝ ሄድኩ፡፡ ስሄድ ያልጠበቅኩት ነገር ነበር የጠበቀኝ፡፡ ከአበባ ጋር እያወሩ ነበር፡፡ ይባስ ብሎ ምንም አልተቀጣም፡፡ ተቆጥታዋለች ራሱ? "የሆነ ነገር ገንዳ ላይ እያጠበች ነበር፡፡ ስታየኝ እየሳቀች "ቆይ እናንተ ምን ይሁን ብላችሁ ነው በዚያ ሰአት ሄዳችሁ ከማታውቁበት ከሶር ድረስ ውሃ ለመቅዳት የሄዳችሁት?" አለችኝ፡፡
እኛ ሰፈር ያኔ ደስ የሚለው ይሄ ነበር፡፡ ምርጥ ሰፈር ነበር፡፡ እገሌ ልጄን አበላሸብኝ፣ የእገሌ ልጅ ልጄን አበላሸብኝ የሚባል ነገር አልነበረም፡፡ ሁላችንም ተመጣጣኝ የጸባየኛነትና የዱሪዬነት ባህርይ ስለነበረን ነው መሰለኝ፡፡ እንደዚህ አይነት ነገር ቢኖር ኖሮ ለዚህ ሁሉ ተጠያቂው እኔ ስለነበርኩኝ ጽጌ ሳሚን "ሁለተኛ ከዚያ ቤቢ ከሚሉት ልጅ ጋር እንዳላይህ፣ አዚህ ቤትም ድርሽ እንዳይል " ልትለው በተገባ ነበር፡፡ ሲኖትራኩ ገጭቶን ቢሆንስ?
ሳሚ እንደነገረኝ ከሆነ እናቱ አበባ ያን ምሽት፣ በሁለቱ ልጆቿ መጥፋት በጣም ደንግጣና ተናዳ ስለነበር ምንም አላለችውም፡፡

ስድስት መቶ አንድ በመቱ የሚታወቅበት ነገር አለ፡፡ የመቱ ሰው ወከ ያረግበታል፡፡ ከ11፡30 ጀምሮ በተለይ ወጣቶች ከጓደኞቻቸው ጋር፣ ከፍቅረኞቻቸው ጋር ይመጣሉ፡፡ ይመጣሉ የምለው ስድስት መቶ ሚኬደው የኛን ሰፈር ተሻግሮ ስለሆነና እኛው ሰፈር ስለሆነ ነው፡፡ ታድያ ወጣትነት ተሰማን መሰለኝ እኔ አራተኛ ክፍል በምማርበት የገና ቀን ከነሳሚ ጋር ከቀናት በፊት ወደ ስድስት መቶ ወከ ለመውረድ እቅድ አወጣን፡፡ የገና በአል ቀን ደረሰ፡፡ ያን ቀን ወደ 8 ሰአት ተገናኝተን መምከር ጀመርን፡፡ እኔ፣ ሳሚ፣ አቢቲና የነሳሚ ጎረቤት ናኦል፡፡
እኔ እነእቴቴ ቤት ደርሼ እንደምመጣና እስከዚያው ጥለውኝ እንዳይሄዱ ነገርኳቸው፡፡ እነእቴቴ ቤት ሄጄ እንኳን አደረሳችሁ ብያቸው፣ የሚበላውን በልቼ፣ የሚጠጣውን ጠጥቼ በሩጫ ተመለስኩ፡፡ ትቻቸው ወደ ሄድኩበት የነሳሚ ቤት ሄጄ ሳያቸው፣ የሉም፡፡ ያዕቆብና አበባ ብቻ ነበሩ፡፡ ስጠይቃቸው ትንሹ ያዕቆብ "ወከም ነው፣ ምናምን ብለው አሁን ገና ወጡ" አለኝና አሳቀኝ፡፡ ወዲያው በጉጉትና በሩጫ በአብዲቦሪ አርጌ ልደርስባቸው የሽምጥ ጋለብኩ፡፡ እውነትም አሁን ገና፡፡ በአብዲቦሪ ህጻናት ማሳደጊያ አድርጌ ወደ መንገዱ ስወጣ አገኘኋቸው፡፡ ያዕቆብ ወከም ያለኝን ነግሬ ከሳቁ አካፈልኳቸው፡፡ ያኔ መንገዱ ገና ተቆፍሮ አብዋራ በአብዋራ ነበረ፡፡ መንገዱን ተሻግሮ በአንድ በኩል ወደታች ገደልና ጫካ ነው፡፡ በሌላ(በአብዲ ቦሪ) በኩል ደግሞ ወደ ላይ በጣም ከፍ ያለ ነውና መንገዱ አብዲ ቦሪ ስር ነው ተኝቶ ያለው፡፡ አብዲ ቦሪና መንገዱ መሀል ያለው ዳገት መንገዱን በሚሰሩት ቻይኖች ተጠርጎ ግርግዳ(ቨርቲካል) ለመሆን ምንም አልቀረውም ነበር፡፡ ዳገቱ አሁን እንደሚታየው አፈሩ እንዳይሸረሸር ቬቲቫሪ ሳር ሳይተከልበት በፊት ያኔ ገና እንደተጠረገ፣ ጠጠር አይነት፣ ቀይ አፈር ብቻ ለብሶ ነበር፡፡ ሄድንና ታድያ እዚያ ሰው ሰራሽ ዳገት ላይ ወጣን፡፡ ከዳገቱ በላይ ሶስት ሰው የሚያስተላልፍ ቀጭን መንገድ አለው፡፡ ቶሎ ላይ የሚወጣ ስንወዳደር ነበር፡፡ በግድ እየወጣን እየወጣን ጫፍ ከደረስን በኋላ ወደታች ያንሸራትተናል፡፡ እንንታተታለን ምናምን፡፡ ያኔ ትዝ ይለኛል፣ አዲስ ጫማ ተገዝታልኝ ነበርና ያን ቀን አፈር ገብቶባት አዲስ ጫማ ሊያገኝ የሚገባውን እንክብካቤ አላገኘችም፡፡ ብቻ ያን ቀን ደስ ይል ነበር፡፡ በህይወቴ ምርጡ አመት በአል ነበረ፡፡ The best holiday ever.

እንደሻው ት/ቤት 4ኛ፣ 5ኛ ክፍል ስማር አካባቢ ጋሽ ታረቀኝ የተባሉ ወደ 70 የሚጠጉ ሽማግሌ ተቀጠሩ፡፡ የሥራ ድርሻቸው ምን እንደሆነ ለተማሪው ግልጽ አልነበረም፡፡ ተቆጣጣሪ ነገር ነበሩ ግን፡፡
ጋሽ ታሬ በግቢያችን ያች የድሮ አይነት ክብ መነጽራቸው፣ ጎርናና፣ ለምክርና ለተግሳጽ የተፈጠረ የሚመስለው ድምጻቸውና ስማቸው መለያቸው ነበሩ፡፡
አምስተኛ ክፍል ስማር አንድ ፍሪ በነበርንበት ጎደሎ ፔሬድ አራት ወይም አምስት ሆነን ክፍል ውስጥ በትንሽ ኳስ፣ ኳስ እየተጫወትን፣ ጋሽ ታሬ ከች፣ ከተፍ አሉ፡፡ ክፍሉ በርም መስኮትም ገና አልተገጠመለትም ነበር፡፡ ጋሽ ታሬ ቁጥጥርም መለያቸው ነበር፡፡ "ምን እየሰራህ ነው?" አሉን፣ በዚያ ጎርናና ድምጽ አራት ነው አምስታችንን አንድ ላይ ጨፍልቀውን፡፡ በጣም ነበር የተናደዱት፡፡ "ቤትህ ውስጥ ትጫወታለህ? ነገረኝ! ኑ ውጡ አሁን" እያሉ እየተቆጡን ቢሮአቸው አደረሱን፡፡ "አሁን ወላጆቻችሁን ታመጡና የሰራችሁት ተነግሮዋቸው ትባረራላችሁ "አሉን፡፡ "አንመስበትም፣ ይቅርታ ይደረግልን" እያልን መለማመን ጀመርን፡፡ "ኧረ ቲቸር አይደገመንም፣ ይቅርታ ያርጉልን" አልናቸው፡፡ አልሰማም አሉ፡፡ "ቤትህ ውስጥ ትጫወታለህ? ቤትህ ውስጥ ትራገጣለህ? ይሄምኮ ቤትህ ነው፣ ትምህርት ቤትህምኮ ቤትህ ማለት ነው" ብቻ፡፡ ለምነናቸው ለምነናቸው አልሰማ ሲሉ አብረውኝ የነበሩ ልጆች ማልቀስ ጀመሩ፡፡ እያለቀሱ መለመን፡፡ እኔ ምኑም እውነት

አልመሰለኝም፣ በዚያ ላይ የክፍል ጓደኞች እንዲህ እያለቀሱ ሲለማመጡ ማየት በጣም ያስቃልና ሳቄን ለማፈን መታገል ጀመርኩ፡፡ ጉንጩን አነክሳለሁ፣ ምን እላለሁ፡፡ እሳቸው እዚያው ጥለውን ከቢሮው ወጣ ሲሉ እኔ የታፈነ ሳቄን ለቀቅኩት፡፡ ሲመለሱ ከባድ ስራ መስራት ነበረብኝ፡፡ ሳቄን ለቅሶ ማስመሰል፡፡ ምገባበት ነበር ያጣሁት፡፡ እኔ እየሳቅኩ እንደሆነ ከነቁ በርግጠኝነት፣ እነሱን ያለ ይቅርታ ወደ ክፍል እኔንም ያለ ይቅርታ ወደ ቤት ይሸኙን ነበር፡፡ ሳቄን ለቅሶ ማስመሰሉ ተሳካልኝ፡፡ ጋሽ ታሬም አስለቅሰው አስለቅሰው በይቅርታና በምክር ወደ ክፍል መለሱን፡፡ ተባረን ነበርኮ! ቅጣታችን ምን ነበረ? ፍርሃትና ለቅሶ፡፡ የጋሽ ታሬ የስራ ድርሻ ምን ነበረ? የት/ቤት አባታችን ነበሩ፡፡ ለሁሉም ተማሪ፡፡

የአባቴ እናት የሞቱ ጊዜና የእናቴ እህት የሞተች ጊዜ እኛ ቤት ለቅሶ ነበረ፡፡ የአባቴ እናት የሞቱት ነቀምቴ ሲሆን፣ የእናቴ እህት ደግሞ ደምቢዶሎ ነው፡፡ ሁለቱም በየሀገራቸው ነበር የሞቱትና የተቀበሩት፡፡ እናትና አባቴም ለቅሶ ሄደው ተቀምጠዋል፡፡ ወላጆቼ አዚህ መቱ ሲመለሱ የነበረው ለቅሶ ግን፣ የሞቱት ሌላ ቦታ ሳይሆን ከኛ ቤት ወጥተው የተቀበሩ ነበር የሚመስለው፡፡ እያወራሁ ያለሁት ስለ ማህበራዊ ህይወት ነው፡፡
ጎረቤታችን የነኢየሩስ ቤትም የእናታቸው ወንድም ከቡሬ ሞቶ ለቅሶ ነበረ፡፡ ወደ አስራ ሁለት ሰአት ተኩል ከኢየሩስ ጋር ሱቅ ለመሄድ ወጣን፡፡ የውጪው በር አጠገብ እንደ ደረስን ነጭ ነጠላ የለበሱ ሴቶች አንድ በአንድ ይገቡ ጀመር፡፡ መንገዱ ጠባብ ነበረች፡፡ገብተው እስኪያልቁ ጠበቅን፡፡ ጠበቅን፣ ጠበቅን፣ ገብተው አያልቁም፡፡ እኔና እሷ እዚያው ቆመን መምሸት ጀመረ፡፡ አለቀ አለቀ ስንል ሰአቱ ሄደ፡፡ የሚገርም ማህበራዊ ሰንሰለት፡፡ ሰዎቹ ገብተው አላልቅ ብለው ሲመሽ፣ እኔና ኢየሩስ ስለ ጨለመ ሱቁን መሄድ ፈራን፡፡
በአራት አመቴ አራታችንም፣ ወላጆቼ፣ ወንድሜና እኔ የአባቴ ቤተሰቦች ጋር ነቀምቴ ሄድን፡፡ ስንመለስ እቴቴና አልማዝ ለራሳቸው ስጋ ወጥ ሰርተው ምናምን ቤታችንን አሰማምረው ነበር የጠበቁን፡፡

እኛ ቤት አባትና እናቴ ደጋግመው የሚሉት አንድ አባባል አላቸው፡፡ “የዚህ ምድር ሀብት ጥቅም የለውም፣ ሀብታሞች ገንዘብ ቢኖራቸውና ምርጥ ምርጡን አልጋ ቢኖራቸውም የሰላም እንቅልፍ የሚተኛው ግን ደሀው ነው፣ ሀብታም ስለ ሀብቱ ይጨነቃል፣ እንዳይሰረቅ ይሰጋል፣ ደሀ ግን ምንም ስለሌለው ሀሳቡን ጥሎ ይተኛል”

አርብ አርብ ማታ የቤተሰብ ጸሎት ጀመርን፡፡ሁሌ እንዳንቀላፋሁ ነበር እኔ፡፡ እንቅልፍ ይይዘኛል፡፡ ሄዶ መተኛት ደግሞ አባቴ አይፈቅድልኝም፡፡ ሌላ ጊዜ እስከ አራት ሰአት፣ አስከፈለግኩ የምቀመጠውን፣ አርብ አርብ የጸሎት ጊዜ ጸሎት አንድ ሰአት ላይ እንኳን ከጀመረ እኔ አንቀላፋለሁ፡፡ እየተጸለየ፣ ቃል እየተካፈለ ስተኛ ታድያ “ተነስተህ ቁም” እባላለሁ፡፡ እንቅልፉ እንዲሄድልኝ ነው፡፡ አንዳንዴ ታድያ ቆሜም እንቅልፍ ያስቸግረኛል፡፡ እየተጸለየ ምናምን በቆምኩበት አሽልብና ልወድቅ እነሳለሁ፡፡ እየተጸለየ ወደፊት ልወድቅ ስል አንድ እግሬን ታኮ ሳስገባ “ጉዋ!” ይልና ሁሉንም አስደነግጣለሁ፡፡ “ሰይጣን ነው እንዲህ የጸሎት ጊዜ እንቅልፍ የሚጥልብህ፣ ጸልይበት” ይሉኛል፡፡ ይጸልዩልኝማል፡፡
4ኛ 5ኛ ክፍል ስማር ጥሩ መንፈሳዊ ህይወት ነበረኝ ማለት እችላለሁ፡፡ ሰንበት ት/ት በከፍተኛ ተነሳሽነት ነበር የምማረው፡፡ ቤት ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ አነባለሁ፣ እጸልያለሁ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ በቀን 4 ምዕራፍ የማነብበት ጊዜ ነበረ፡፡ ብሉይ ኪዳን ከዘፍጥረት ጀምሬ እስከ ኢያሱ ወልደ ነዌ፣ አዲስ ኪዳን ከማቴዎስ ወንጌል እስከ ሐዋርያት ስራ መጨረሻ አንብቤአለሁ፡፡ ያኔ ሳነብ ታድያ ታሪክ ያለው ክፍል ነበር ደስ የሚለኝ፡፡ እያነበብኩ ሌላ ሀሳብ ውስጥ የምገባባቸው አጋጣሚዎች ግን ብዙ ነበሩ፡፡ ያኔ በግሌ እጸልይም ነበር፡፡ በማገኘው የት/ት ውጤት ደስተኛ ነበርኩና እግዚአብሔርን አመሰግነው ነበር፡፡ ፋይናል ፈተና ሲኖር ጸልዩ ነበር የምሄደው፡፡ ፈተናውን ልሰራ ስል እንኳን እጸልይ ነበር፡፡ ያኔ ብዙ ፈተናዎችን እደፍን ነበረና ፈተናው ታርሞ ሲመጣ “እግዚአብሔር ሆይ የኔ አይደለም ያንተ ስራ ነው” እያልኩ “ተመስገን” ብዬ እግዚአብሔርን አመሰግነው ነበር፡፡

ድሮ በህጻንነቴ ያ ካለት/ቱ ምንም የማያውቀው ጎበዝ ተማሪ ነበርኩኝ፡፡ መምህራን ለኔ ያላቸው አመለካከት ከምንም በላይ ቅድሚያ የምሰጠው ጉዳይ ነበር፡፡ የማይረብሽ፣ ጎበዝ፣ ት/ቱን ብቻ የሆነ ተማሪ ነበርኩ፡፡ ለዚያ ነበር መምህራን ይወዱኝ የነበሩትና ሁሌ አለቃ ሆኜ እመረጥ የነበረው፡፡

My 3 sisters 5ኛና 6ኛ ክፍል ስማር በኢተቪ ይተላለፍ ነበር፡፡ ብዙም የሚከታተለው ሰው ግን አልነበረም፡፡ ማን እንግሊዘኛቸውን ይሰማል? እንግሊዘኛ ችዬ የሚያወሩትን ለመስማት የነበረኝ ጉጉት ትዝ ይለኛል፡፡

የሆነ ጊዜ ከፍተኛ የኮፒ ራይት እንቅስቃሴ ነበረ፡፡ በቲቪ መአት ዲስክ ሲያቃጥሉ ይታይ ነበር፡፡ “ጥበብ እንዴት ትደግ?”፣ “የኮፒ ራይት ህግ ካልወጣ ጥበብ ማደግ አትችልም”፣ ”አርቲስቱ ምን በልቶ ይኑር?”፣ “አሁን ያለው ሁኔታ ተስፋ አስቆራጭ ነው” የሚሉ ዜናዎች ተበራክተው ነበር የሆነ ሰሞን፡፡ የአርቲስት ድህነት ከድሮ ስሰማው የነበረ ነው፡፡ በተለይ ድሮ እንዲህ እንዲህ የነበረው ሰውዬ እንዲህ እንዲህ ሆነ ሲባል መስማት የተለመደ ነው፡፡ “ጎዳና ላይ ወጣ”፣ “ጣርያው በሚያፈስ ቤት ውስጥ ነው የሚኖረው፡፡ ውጪኮ አክተርና ዘፋኝን ያህል የሚከፈለው የለም፣ እነሱ እንዴት ሰው እንደሚያከብሩ ያውቁበታል” ይባላል፡፡ ባለጉዳዩ አርቲስቱ ደግሞ “ያው የኛ ገንዘብ የህዝቡ ፍቅር ነው” ይላል፡፡ አንድ ቀን ሀና ዮሀንስ ሰው ለሰው ላይ በመተወኗ ስላገኘችው ጥቅም ተጠይቃ ስትመልስ በቲቪ “የቲቪ ድራማ እንግዲህ ጥቅሙ ከምንም በላይ የህዝብ ፍቅር የሚገኝበት ነው” ምናምን ስትል ሰማሁ፡፡ የህዝብ ፍቅር የሚሉት ዝነኝነትን ነው፡፡ ግራ ሲገባኝ የነበረው ደግሞ፣ ለምን “ዝና” አይሉም? ለምን “ያው ለዝና ነው እንጂ ያን ያህል ገንዘቡ እንኳን ኪስ የሚገባ አይደለም” አይሉም? ለምን “የቲቪ ተከታታይ ድራማ ዝናን ያከናንባል” አትልም? ዝና የምትለዋን ቃል ለምን ይፈሯታል? አሜሪካዊቷ የቴሌቪዥን ሾው ባለቤትና አቅራቢ የሆነችው ኤለን ዲጄነረስ በሾውዋ አንደ ሽልማት አሸንፋ ንግግር ስታደርግ “ እኔ ይሄን ሾው ስጀምር ሰዎችን ለማዝናናት፣ ለማስተማር፣ ገንዘብ ለመሰብሰብ እና ዝነኛ

ለመሆን እንጂ እንዲህ አይነት ሽልማቶችን አሸንፋለሁ ብዬ አስቤ አላውቅም" ነበር ያለችው፡፡ በርግጥ ዝና ማለት ያው በብዙ ሰው መታወቅ፣ መወደድ ማት ነው፡፡ የህዝብ ፍቅር ጸባየኛ የዝና ትርጉም ነው፡፡
ለማንኛውም ይሄ የኮፒ ነገር አርቲስቶችን በጣም የጎዳቸው ይመስላል፡፡ አንዳንዴ ቴክኖሎጂ ባልነበረ ያስብላልኮ፡፡ አሁን ይሄን መጽሐፍ በምጽፍበት ጊዜ ፊልም በፍላሽ ዲስክና በፍላሽ ሼር እየተቀባበልን ነው የምናየው፡፡ ከኢንተርኔት ማውረድም ተጀመረ፡፡

ደረጃው፡ ወደ ላይ ወይስ ወደ ታች?

እባካችሁ ልጆች እንጫወት በጣም፣
ከንግዲህ ልጅነት ተመልሶ አይመጣም
ልጅነቴ ልጅነቴ ማርና ወተቴ፡፡

2002 ዓመተ-ምህረት ወረሃ ግንቦት ቀነ መጀመሪያ በቤታችን ትልቅ ለውጥ ተደረገ፡፡ የቤት ለውጥ፡፡ ቤት ቀየርን፡፡በኪራይ ከምንኖርባት፣ ጠባብ ከጎረቤታችን ጋር ግርግዳ ከምንጋራባት የቁጠባ ቤት ወደ ሰፊ፣ የራሳችን የሆነ፣ ብዙ ክፍሎች ወዳሉትና ወዳሰራነው ቤታችን ስንገባ ከሁሉም በላይ ሚጣ፣ በተለይ የኮሪደሩ ስፋት በጣም ነበር የተመቻት፡፡ ዲዲዲ ብላ ከጫፍ እስከ ጫፍ ትሮጥበታለች፡፡ እሁድ እለት ከሰአት ቤት መቀየር ጀመርን፡፡ ብዙ ጎረቤቶቻችን እቃ በማጋዝ አገዙን፡፡ በቀጣይ ሁለት ቀናት በአይሱዙና በሰፈር ሰዎች እርዳታ ታግዘን ወደ አዲሱ ቤታችን ተጠቃለን ገባን፡፡
ማክሰኞ ቀን ምሽት እኔና ወንድሜ እንደወትሮው ለእህታችን ሚጣ ጡጦ የሚሆን ወተት ማምጣት ነበረብንና ምሽት እንድ ሰአት ተኩል አካባቢ ሹጊያችንን ይዘን እያወራን እየሄድን ነው፡፡ ስለቤት ቅያሪያችን ነው የምናወራው፡፡ ከጓደኞቼ ራቅኩኝ አልኩት፡፡ እኔ ግን እንዲያውም ጓደኞቼ እዚያ ነው ያሉት አለ፡፡ በቤታችን(በድሮው) አጠገብ እያለፍን ነበረ፡፡ እውነቱን ነበረ፡፡ ከት/ቤት ጓደኞቹ ጋር አቀራርቦታል፡፡ የድሮ ቤታችን እኔን ከሳሚ ጋር እንዳቀራረበኝ፡፡ የድሮ ቤታችን ጋር ስንደርስ ምን እንደሆንኩ አላውቅም፣ እንደዚያ አይነት ስሜት ተሰምቶኝ አያውቅም፣ ሆዴ ባባ፡፡ ሆዴ አለቀሰ፡፡ "ህህ"፣ አንድ ዘለላ እምባ ከአይኔ፡፡ ድብርብር ብሎኝ ነበረ ያን ጊዜ፣ እንደዚያን ጊዜ ላለቅስ እንደሆነ ሳላውቅ ያለቀስኩበት ቀን በርግጠኝነት የለም፡፡ ጨለማ ነበር፡፡ ወንድሜ ማልቀሴን አውቆ እንደሆነ አላውቅም፡፡
የድሮ ቤታችንና አዲሱ ቤታችን ምንም እንኳን ብዙ ባይራራቁና ሰፈር ቀየርን ባይባል፣ አዲስ ቤት ነው፣ አዲስ ጎረቤት፣ አዳዲስ ብዙ ነገሮች ስለነበሩት አዲስ ህይወት ነበረ፡፡
እኛ ቤት ስንቀይር፣ የመራቂ መአት፡፡ ካባቴ ቢሮ፣ከእናቴ ቢሮ፣ የድሮ ሰፈር ሰው፣ የአዲሱ ሰፈር ሰው፣ የሚያውቀን ሁሉ መጥቶ ቤታችንን መመረቅ ጀመረ፡፡ ጋጋታ ነበረ፡፡
ቤታችን ሳንገባ በፊት ቀለም እየተቀባ የነበረ ጊዜ ኣሊ የሚባል 5ኛA የሚማር ጓደኛዬ ያልሆነን ልጅ ቤታችን አድርሼ አሳይቼው ነበር፡፡ ቅርብ ጊዜ ነበር እኛ ሰፈር የገቡት፡፡
ከአዲሱ ሰፈራችን ጋር ጥሩ ወዳጅነት ፈጠርን፡፡ ከጎረቤቶቻችን ጋር፡፡ ቢሆንም ከበፊቱ ሰፈር ጋር መለያየት ከባድ ነበረ፡፡ ከድሮ ሰፈር ልጆች፣ ከነሳሚ ጋር እየሄድኩ እንደቀድሞው እጫወት ነበር፡፡

ነሐሴ መጨረሻ ላይ መሆን አለበት፡፡ ቁማር መሆን አለበት፡፡ አዲሱ ሰፈራችን ገብተን ተለማምደናል፡፡ ወደ 4 ሰአት አካባቢ ነው፡፡ ብዙ ልጆች ከቤታችን መውጫ በሆነው መንገድ ላይ ነበሩ፡፡ የሆኑ ልጆች ብይ እየተጫወቱ ነው፡፡ እኛ ደግሞ ቆመን እያየን ነው፡፡ ልጆቹ በጨዋታው በጣም ተመስጠዋል፡፡ እኛ ቆመን እያወራን እያለ እዚያው እኛ ሰፈር የሆነ ወጣት የሆነ ሰውዬ ወደኛ መጣ፡፡ ብይ እየተጫወቱ ከነበሩት መሀል የቴዎድሮስ አጎት ነው፡፡ አብረው ነው የሚኖሩትና አጎትየው ወጣት ነው፡፡ "አንተ ተነስና ሄደህ ት/ቤት ተመዝገብ" አለው አጎትየው በጨዋታ ልቡ የጠፋችውን ቴዲን፡፡ አተዛዘዙ ሲያዝ ውሎ እንዳደረ ሰው ነው፡፡ "እቺ የመጨረሻ ነች፣ እስከ አሁን እንቢ ብለሃል፣ አሁን ግን በግድ ነው ማንቁርትህን ይገፔ ነው የማስመዘግብህ" አይነት፡፡
"እሺ" ይለዋል ቴዲ፡፡ "ተነስ አሁን ምዝገባ እያለቀ ነው"፡፡ ለ2ኛ ወይም ለ3ኛ ክፍል ምዝገባ መሆን አለበት፡፡ ቴዲ ጨዋታው መስጦታል፡፡ "እሺ እቺን ልጨርስ" ቢለው አጎቱ አሰፋ አልሰማ አለ፡፡ "አሁኑኑ ና" እንጂ፡፡ ቴዲ በሽቀ፡፡ ወንድሜና እነቶለሳ፣ ብዙ ልጆች ነበሩ፡፡ ወደኛ ዞሮ "ትናንትም ሂድ ተመዝገብ ስለው እሺ ብሎኝ ቀረ፣ ከትናንት ወዲያም፣ ይኸው ምዝገባ ዛሬ ነው ሚያልቀው" ምናምን ብሎ ነገሩን ሊያብራራልን ሞከረ፡፡ ቴዲ ድምጹ በጣም ይጮሃል፡፡ "ተነስ" ሲለው "በቃ አልመዘገብም፣ አልመዘገብም በቃ፡፡ በግድ ነው እንዴ? አለመማር መብቴ ነው፣ አልማርም በቃ!" አለ ደጋግሞ፡፡ "ተው አንተ ልጅ ይሄ ልጅኮ ተበላሸ በቃ" ይለናል እኛን አጎቱ፡፡ "በቃ አለመማር መብቴ ነው አለ ቴዎድሮስ፡፡ አንድ ባለ ጎርናና ድምጽ የሰፈራችን ልጅ፣ "ኧረ ዲሞክራሲ ቴዎድሮስ?" አለው፡፡ አስቂኝ ክስተት ነበረ፡፡ በዚያ ቦታ ላይ የነበሩና ይሄን የቴዲንና የአጎቱን እንኪያ ሰላንትያ የሰሙ ልጆች፣ ቴዲንና አጎቱን ጨምሮ ስለዛች አጋጣሚ ነግሬያቸው፣ ላስታውሳቸው ብሞክር እንኳን የሚያስታውስ አንድ ሰው አንደሚኖር እጠራጠራለሁ፡፡ "ያለመማር መብት አለኝ"..."ኧረ ዲሞክራሲ" መታወስ ያለበትና የሌለበት ነገር እንደሆነ አንባቢ ሆይ ፍረድ፡፡

ያኔ ቤት ስንቀይር እህቴ ሚጣ ገና 3 አመቷ ነበረ፡፡ ታድያ ላይ ሰፈር ይገኘት እሄድ ነበረ፡፡ አንዳንዴ እሷን አስቀምጬ ኳስ እጫወታለሁ፡፡ እሷን አስቀምጬ ምትትሮሽ ምናምን እየተጫወትን፣ ትንሽ ቆይቼ ዞር ስል እሷ የለችም፡፡ ወይኔ ጉዴ፣ አለቀልኝ፡፡ እህቴ ጠፋች፡፡ ሄጄ ሳፈላልጋት ለካስ አንድ ሰው ቤት ገብታ ከልጆች ጋር እየተጫወተች እኔን ራሱ ረስታኛለች፡፡
ቤት ከቀየርን ወዲህ ጊዜው እየገፋ ሲሄድ፣ ሚጣ ያልነበራትን አመል አመጣች፡፡ ያለምክንያት እያለቀሰች መዋል፣ መነጫነጭ ጀመረች፡፡ ትታ የነበረውን፣ እናታችን የሆነ ቦታ ስትሄድ እንዳዲስ እያለቀሰች መዋል ጀመረች፡፡ እንዲያው ከበፊቱ የበለጠ፡፡ በፊት ትንሽ አልቅሳ ትረሳ ነበረ፡፡ አሁን ምንም ብትባል አታቆምም፡፡ በጣም ትጮሀለች፣ ምርር ብላ ታለቅሳለች፡፡
አንድ ቀን እናታችን ምሳዋን በልታ ወደ ቢሮ ስትመለስ፣ ሚጣ ማልቀስ ጀመረች፡፡ ጀምራ ልታቆም ነው ታድያ? ማልቀሷ አንሶ ከቤት ልትወጣና ልትሮጥ፡፡ ያዝኳት፡፡ እያለቀሰች ትንፈራገጣለች፡፡ የማረገው ሳጣ እለቃታለሁ፡፡ ባዶ እግሯን ነበረች፣ በጣም ትሮጣለች፡፡ እየሮጥኩ እከተላታለሁ፡፡ እይዛታለሁ፡፡ ለጉድ ታለቅሳለች፡፡ ማንም የሚያቆማት ያለ አይመስልም ነበር፡፡ እጇን ስይዝ እጇን እኔ ጋር ትታ ዝም ብላ ለመሮጥ የቆረጠች ትመስል ነበር፡፡ እጄ ላይ የሆነ ነገር የምትሆን መስሎኝ ዝም ብዬ እከተላት ጀመርኩ፡፡ እናታችንን የት አገኛታለሁ ብላ ነው? ግራ ገባኝ፡፡ ወደ ድሮ ሰፈራችን በሚያደርሰው መታጠፊያ ታጠፈች፡፡ ስትሮጥ የ3 አመት ህጻን አትመስልም፡፡ ያዝኳት፡፡ እሪ አለች፡፡ ለቀቅኳት፡፡ የወተት ጥርሶች፣ በእምባ የታረሰ ቀይ ድምቡሽቡሽ የህጻን ፊት፣ ማሳዘን ብቻ ሳይሆን ግራ ያጋባል፡፡ ሮጠች፣ ተከተልኳት፡፡ ደሜን የት አገኛት ብላ እየሮጠች እንደሆነ ለማወቅ ጓጓሁ፡፡ የድሮ ቤታችን ይሆን? የድሮ ቤታችን ጋር እየደረሰች ነበር፡፡ ከቤታችን ቀድሞ ከነበረው የነሳሚ ቤት ጋር ስትደርስ ቆመች፡፡ ቆማ ማልቀስ ጀመረች፡፡ ደሜኮ እዚህ የለችም አልኳት፡፡ ምንም አላለችኝም፡፡ ተሸክሜአት በመጣችበት መንገድ ስመልሳት ምንም እሪታ፣ መንፈራገጥ፣ እንቢ ባይነት አልነበረም፡፡ የዚያ ቀን አጋጣሚ ከዚያ በኋላ ተመላልሶ ወደ አዕምሮዬ ይመጣ ነበር፡፡ የሆነ ያልገባኝ ነገር ነበረ፡፡

የሚጣ የዚያን ቀን ትክክለኛ ስሜት ከአመታት በኋላ 10ኛ ክፍል ላይ ነበር የገባኝ፡፡ እኔ እንዳሰብኩት ቢሮ እንደሄደች የምታውቀውን እናቷን ለመፈለግ አልነበረም ወደ ድሮ ሰፈራችን እያለቀሰች የሮጠችው፡፡ የድሮ ሰፈሯ ናፍቋት እንጂ፡፡ መነጫነጭ ስለጀመረች በእናቷ መሄድ የጀመረችውን ለቅሶ ሳታውቅ ለወደደችው፣ በጣም ለናፈቃት ሰፈር ተጠቀመችው፡፡ ባዶ እግሯን ሮጠች፣ ሮጠች፣ የሮጠችለትን፣ እሪ ያለችለትን፣ ናፍቆቱ በ3 አመት እድሜዋ የ23 አመት ወጣት ጉልበት የሰጣትን የድሮ ሰፈሯን እንደገና የምታገኝ መስሏት፡፡ ባትችልም ከድሮ ሰፈሯ ጋር መሆን ፈለገች፡፡ የህጻን አዕምሮ፣ የእህቴ የሚጣ የ3 አመት ልብ በጣም ወደምትወደው ሰፈር መመለስ አንደማትችል ሲገባት፣ የተስፋ መቁረጥ እምባዋን አውጥታ፣ ተሸክሜ ወደ ቤት ልመልሳት ስል ተቃውሞዋና ያ ሀይለኛነቷ ከእምባው ጋር ከውስጧ ወጥቶ ነበር፡፡ ወደ ጎረቤታችን ወደነሳሚ ቤት ግቢ ውስጥ አንገቷን አስግጋ አይታ እንደነበር ትዝ ይለኛል፡፡ ግቢው ጭር ብሎ ነበር፡፡

እኛ ቤት ከመቀየራችን በፊት የሳሚ አባት ተዛውሮ ወንጂ ይኖር ጀምሮ ነበር፡፡ እነሳሚ ወደዚያ መዛወራቸውም የጊዜ ጉዳይ ሆነ፡፡ የአጭር ጊዜ ጉዳይ፡፡

አዳማ የሚኖር አጎት አለኝ፡፡ በልጅነቴ (በ4ና 6 አመቴ) ነቀምቴና ደምቢዶሎ ዘመድ ጥየቃ ከመሄድ ባለፈ ክረምት ምናምን የትም ሄጄ አለማወቄ ሁሌ ያናድደኝ ነበር፡፡
እኔ አዳማ አጎቴ ጋር ስሄድ ሀምሌ ተጋምሶ ነበር፡፡ የአጎቴ ሰፈር ዱቄት ነበር፡፡ ከባጃጅ ወርደን ውስጥ ለውስጥ ወደ ቤቱ በእግር እየሄድን ገርሞኝ በኦሮምኛ ነውና የምናወራው “maanni safara kana ijoolleen hin jiranuuyii?”(ምንድነው እዚህ ሰፈር ልጆች የሉም እንዴ?) አልኩት፡፡ “maaliif jette?”(ለምን አልክ?) አለኝ፡፡ “biyya keenya ijoolleen karaarra taphachaa ooluu”(እኛ ሀገር ልጆች መንገድ ላይ ሲጫወቱ ነው የሚውሉት) አልኩት፡፡ “biyya keenya maaliif jettaa? Asiis achiis biyyuma tokkohootii?”(ለምን እኛ ሀገር ትላለህ? እዚህም እዚያም አንድ ሀገር አይደለም እንዴ?) አለኝ፡፡ “anis inni naannoo naannoo dhaan qoodanii biyya jedhan na dhiba ture, gaafa namni hundi akka sana akka jedhu baruun anis itti fufee”(እኔም ሰዎች በቦታ ተከፋፍለው ሀገሬ፣ ሀገራችን ሲሉ ይገርመኝ ነበረ፣ ሁሉም እንደዚያ እንደሚል ስረዳ ነው እኔም የቀጠልኩበት) አልኩት፡፡ ከዚያ በኋላ እኔ እንደዚያ ማለቴን በግርምት ለብዙ ሰዎች መንገሩ ትዝ ይለኛል፡፡ አጎቴ እንደኔው ለማድነቅ ቅርብ የሆነ ሰው ነው፡፡
ያኔ የአጎቴ ቤት ስሄድ ብዙ ነበርን፡፡ የቤቱ ተመዝጋቢ አባላት ከሰራተኟቷ ጋር 4፣ ሌላ እንደኔ የነሱ የአጎቴና የሚስቱ ዘመዶች የነበሩ 5 ልጆች፡፡እነአጎቴ ዲሽ ነበራቸው፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ዲሽ አየሁ፡፡ ያኔ መቱ ዲሽ እንደቀልድ አይገኝም ነበር፡፡ በጣም ጥቂት ሰዎች ነበሩ ዲሽ የነበራቸው፡፡ አዳማ ደግሞ ያልነበረው ሰው ራሱ አልነበረም፡፡ በቀጣዩ አመት በ2003 ነው በመቱ ውስጥ ዲሽ እንደተዛማች በሽታ መሰራጨት የጀመረው፡፡
መቱ የልጆች ጊዜን እየጠበቅንና በዲስኩ የምናየው ቶም ኤንድ ጄሪ በMBC3 በገፍ ጠዋትና ማታ ይታይ ነበረ፡፡ ሪስሊንግስ? ከልጆች ጋር ሪስሊንግ እውነት ነው፣ ፌክ ነው? ብለን እንከራከር ነበር፡፡ እኔ ሁሌም ውሸት እንደሆነ ነበር የምከራከረው፡፡ 2007 ላይ ኢቢኤስ ላይ የቴከከቶኩ ሰውዬ ሪስሊንግ ውሸት እንደሆነ እስኪገልጽ ድረስ፡፡ የእውነት፣ የውሸት መሆኑ የሚያወዛግበው ባለቤቶቹ እውነት እንደሆነ እንድናምን ስለሚፈልጉ እንደሆነም ተናግሯል፡፡ እኔም በርግጥ ሪስሊንግ እንኳን በኢትዮጵያ በሚሰራበት ሀገር ራሱ የእውነት የውሸትነቱ እንደሚያወዛግብ አንዴ ከአንድ ፊልም ላይ ማስተዋል ችያለሁ፡፡ አባትየው “wrestling is fake” ሲለው በሪስሊንግ ፍቅር ያበደው ወጣት ልጅ “wrestling is not fake Dad” ብሎ አባቱን ይቃወመዋል፡፡

ቴክቶክ የተለያዩ በጣም አዳዲስና አስገራሚ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን የሚያስተዋውቅ ፕሮግራም ነው፡፡ ሰውየው አሜሪካ ሆኖ ነው ፕሮግራሙን የሚያዘጋጀውና፣ አንድ ጊዜ ኢትዮጵያ ሲመጣ ሰይፉ ሾው ላይ ተጋብዞ ነበር፡፡ ሰይፉ ሰለሞንን ከጠየቃቸው ጥያቄዎች መካከል አንዱ የኔም ጥያቄና እንቆቅልሽ ነበር፡፡ “በቀን ሶስቴ መብላት ከባድ በሆነበት ሀገር እንዲህ አይነት አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ማሳየት ፋይዳ ቢስ ነው ብለህ አታስብም?” ብሎ ጠየቀው፡፡
ሰለሞን ደግሞ ሲመልስ “አይመስለኝም፣ ለሚመጣው የቴክኖሎጂ ዘመን ህዝቡን ማዘጋጀት ነው” አለ፡፡(ሀሳብ በሀሳብ እንጂ ቃል በቃል አይደለም ያለውን የጻፍኩት)

አዳማ ጥሩ ጊዜ እያሳለፍኩ ነበር፡፡ ብዙ ነበርን፣ ደስ ይል ነበር፡፡ ለሁለት ሳምንት፡፡ ከሁለት ሳምንት በኋላ ዘመድ ሆነን የአጎቴ ቤት ለክረምት እረፍት ከሄድነው፣ ከአምስታችን 4ቱ ሌላ ዘመዶቻቸውን ለማካለል አዲሳባ ሄዱ፡፡ እኔ ብቻ ቀረሁ፡፡ ሁሉም አዝኖልኝ ነበር፡፡ እኔ ብቻ ነኝ ነገሩ ያልገባኝና ለራሴ ያላዘንኩት፡፡
የአጎቴ ሚስት እህት አንባቢ ቢጤ ነበረች፡፡ እሷ ጋር የነበሩ ቃል ኪዳንና ጥቁር ደም የተሰኙ ልቦለድ መጽሐፍቶችን አነበብኩ፡፡ ጥቁር ደም የሚሉት በጣም አስፈራኝና ድሮ የቲቪ ድራማ ሳይ የነበረው ስሜት ውስጥ ነበር የከተተኝ፡፡ በጣም አስፈሪ ነበረ፡፡ የበቀል ታሪክ ያለው መጽሐፍ ነው፡፡ ቃል ኪዳን ደግሞ እንዲያውም በሽመልስ አበራና በሚስቱ ፊልም ተሰርቶበታል፡፡
ሁለቱንም ሳነብ በጣም እየገባኝ አልነበረም፡፡ ስማቸው ብቻውን ይምታታብኝ ነበር፡፡ ማን ምን እንደሆነ የሚያዝልኝ መጽሐፉን ካጋመስኩ በኋላ ነው፡፡
ጥቁር ደም የሚለው መጽሐፍ የዘር ግንድ እየቆጠሩ እየተገዳደሉ የሚበቀሉትን የገጠር ክፉ ባህል ይዳስሳል፡፡ ያ መጽሐፍ ደመላሽ ስለሚባለው የሰው ስም ያሉኝን ጥያቄዎች መልሶልኛል፡፡ ሁለቱም መጽሐፍት ብዙም አልገቡኝም ሳነባቸው፡፡ የገባኝ ነገር ቢኖር መጽሐፍ ማንበብ እንደምቀጥል ነበር፡፡

አዳማ ልጆቹ ሲሄዱ ዝም ብዬ ቤት ውስጥ መጎለት ሆነ ስራዬ፡፡ እነሱ የነበሩ ጊዜ ሲሰራ የነበረው ዲሽም ተበላሸ፡፡ ያኔ ከመበላሸቱ በፊት ካየኋቸው ፊልሞች አንድ ትዝ የሚለኝ ረጅም ፊልም አለ፡፡ “Pearl harbor” ጃፓኖች በአውሮፕላን የአሜሪካን መርከቦች ሲደበድቡ፡፡ ፍቅረኛሞቹ፣ የሚመስጥ ታሪክ፡፡

እያደረ እያደረ ሲሄድ ቤት ይናፍቀኝ ጀመረ፡፡ ሁሉም የመቱ ነገር ይናፍቀኝ ጀመረ፡፡ ቀኑ እየገፋ ሲሄድ ማልቀስ ማልቀስ ብቻ እየሆንኩኝ መጣሁ፡፡ አልጋዬ ላይ ሆኜ አለቅሳለሁ፡፡ የምግብ አፒታይቴ ቀነሰ፡፡ ድሮ ሁለት ሶስት ቁርጥ እንጀራ እበላ የነበርኩ ሰውዬ አንድ ቁርጥ በግድ መጨረስ ጀመርኩ፡፡
አንዴ አዳማ የአጎቴ ቤት ዶሮ ወጥ ተሰራ፡፡ እኔ ምኑም ዶሮ ወጥ አልመስልህ አለኝ፡፡ ይመርረኝ ነበር፡፡ ሽንኩርቱን አቃጥለውት መሰለኝ፡፡ በግድ ነበር የምበላው፡፡ እኔ እነሱም ካስጠላቸው ብዬ ፊታቸውን ደጋግሜ ባይ፣ እነሱ ለካስ ጣፍጦአቸው በጣም ደስ ብሏቸዋል፡፡
አጎቴ ምሳ ሰአት ቤት አይገባም ነበርና ምሳ ይዞ ነበር ስራ ቦታ የሚሄደው፡፡ ዶሮ ወጡን ለካስ ከሌላ ሰው ጋር በልቶ ኖሯል፡፡ ሚስቱን ምን ይላታል? “ከእገሌ ጋር ነው ምሳዬን የበላሁት፣ በጣም ይጣፍጣል አለ” ብሎ ለሚስቱ በኩራት ይነግራታል፡፡ እኔ እንቆቅልሽ ሆነብኝ፡፡ “ከሀገሩ ነው ማለት ነው? ይሄ የሚጣፍጥ ከሆነ እኛ ቤት የሚሰራውን ዶሮ ወጥ ቢቀምሱ ደግሞ ምን ሊሉ ነው?” አልኩኝ ባሳቤ፡፡ ልክ ነበርኩ፡፡ ወደ መቱ ከተመለስኩና ከቆየ በኋላ እንኳን ስለዚያ እኔ በግድ፣ ሌላው በፍቅር ስለበላው ዶሮ ወጥ ሳስብ በጣም ግራ እጋባና ጥያቄ ይሆንብኝ ነበር፡፡ ለካስ እውነትም ከሀገሩ እንደ ነበር የገባኝ 10ኛ ክፍል ስገባ ነው፡፡ ያለመድኩትን ከቤተሰቤ፣ ከምኔ ከምኔ ተለይቼ፣ ባዕድ በሆነብኝ ሀገር ውስጥ ስለበላሁት ነው ያ ጣት የተቆረጠመለት ወጥ እኔን ያቅለሸለሸኝ፡፡ ናፍቆት፡፡ ከባድ ናፍቆት ነበር፡፡

አንዴ አጎቴ ከተማ ይዞኝ ወጥቶ ከጓደኛው ጋር ተገናኘን፡፡ እግረ መንገዴን የአዳማን መንገድ ከመቱ መንገድ ጋር ሳነጻጽር ነበር፡፡ መቱ፣ ዋናው፣ ከተማውን አቋርጦ የሚያልፈው መንገድ የተሰራው ራሱ በዚያው አመት ነበረ፡፡
ኮብል ስቶን ለኔ አዲስ ነገር ነበር፡፡ ኮብል ስቶን የሚገርም ነገር የለውም፡፡ ቴሌቪዥን ግን ድንጋይ ሳይሆን የሚበላ ነገር እንደሆነ አድርገን እንድናስብ ነበር ያደረገን፡፡ በቲቪ ብቻ ለምናይ ልጆች ያጓጓ ነበር፡፡
የአጎቴ ጓደኛ የነበረበት ሆቴል ደረስን፡፡ ሰውየው ተጫዋች ነው፡፡ “ትማራለህ?” ብሎ ጠየቀኝ፡፡ ”አይ” አልኩት፡፡ “ምንድነው የምትሰራው ታድያ?” ምን ብለው ጥሩ ነው? “ኮብል ስቶን”፡፡ ሳቅ፡፡ “የዚህ ዘመንን ልጅ ስንተኛ ነው የምትማረው ነው እንጂ ትማራለህ ወይ ተብሎ አይጠየቅም” አልኩት፡፡ የተባባልነውን ለአጎቴ ነገረው፡፡ አጎቴም ሳቀ፡፡ ያንኑ ቀን መቱ ደውሎ ነገሩን ለቤት ነገራቸው፡፡ እነሱ ደግሞ ለጎረቤት አዳረሱ፡፡ እኔ በ2002 ክረምት ነበር አዳማ የሄድኩት፡፡ መቱ ላይ 11ኛ ክፍል ስማር በ2008 ከስድስት አመት በኋላ ያቺን አባባል ያስታወሰኝ ሰው አለ፡፡ ወይ ኮብል ስቶን፡፡

ከሁለት ሳምንት ደስ የሚል ጊዜና ደባሪ፣ በናፍቆት የተሞሉ 3 ሳምንታት፣ ባጠቃላይ ከአንድ ወር ከሳምንት በኋላ ወደ መቱ ተመለስኩ፡፡ ምንም እንኳን መቱ ዶሮ ወጥ እስኪዘጋኝ ብትናፍቀኝ ከዚያች ነፋሻማና ጸሀያማ የምታምር ከመቱ አንድ እርምጃ ወደፊት ከሆነች ከተማና ከአጎቴ ጋር መለያየትም ቀላል አልነበረም፡፡
መቱ ቤት ስገባ ስጋ ወጥ ተሰርቶ ነበር፡፡ አንድ ቁርጥ ብቻ እንደምበላ አይተው “ለምን በትክክል አትበላም?” አሉኝ፡፡ “ብዙ መብላት ጥቅም የለውም” አልኳቸው፡፡ ከሶስት ቀን በኋላ 3 ቁርጥ ራሱ አያጠግበኝም ነበር፡፡ የዶሮ ወጡ ትንግርት የተፈታልኝ ግን ከአመታት በኋላ፣ 10ኛ ክፍል ስደርስ ነው፡፡ ለካስ ናፍቆት ዶሮ ወጥ ያስመርራል፡፡

እንደሻው ት/ቤት ዋጋ ሲጨምር ብዙ ልጆች ከዚያ ወጥተን ሰንሻይን ገባን፡፡

ከአዳማ ከተመለስኩ ወዲህ አባቴ ድሮ ሲያነባቸው የነበሩ መጽሐፍትን መበርበር ጀመርኩ፡፡ ሳፈላልግ አመዳፋሽ የተባለ የድሮ ልቦለድ መጽሐፍ አገኘሁ፡፡ መጽሐፉ የአንደኛው ወይም የሁለተኛው የአለም ጦርነት የስለላ ስራ ዙሪያ ያጠነጥናል፡፡ ትርጉም ነው፣ ዋና ገጸ-ባህርያቱ ትዝ ይሉኛል፡ ካትሪንና ጳውሎስ፡፡ ታሪኩ ግን በትክክል አልገባኝም፡፡ ወደ አራት መቶ ገጽ ነበረው፡፡ እኔ አንብቤው ሳልጨርስ ትምህርት ጀመረ፡፡ አባቴ፣ ደግሞ እንዳቆም እየነገረኝ ነበረ፡፡ እንደምንም ብዬ ጨረስኩት፡፡ ቀጥዬ ከቤት ያገኘሁት ደግሞ ዕንባና ሳቅ የተባለ የሀገር ውስጥ ልቦለድ ሲሆን፣ ይሄኛውን መጽሐፍ ሳነብ የተረዳሁት አንድ ነገር፡ የአማርኛ ልቦለዶች አላስፈላጊ ማብራሪያዎችን በመስጠት እንደሚያሰለቹ ነው፡፡ ከታሪኩ ማብራሪያው ይረዝማል፡፡ እንዲህ እንዲህ ትመስላለች፣ ቤቷ፣ ጸሀይዋ… ባንጻሩ የውጪ መጽሐፍት በጣም ደስ ይላሉ፡፡ በፊት በፊት የማይንዛዙት ተርጓሚዎቹ ስለሚያሳጥሯቸው ይመስለኝ ነበር፡፡

ሰንሻይን አዲስ ት/ቤት ነበረ፡፡ ብዙ ተማሪዎችና አስተማሪዎች ነበሩ ከእንደሻው ወጥተው ወደ አዲሱ ሰንሻይን የገቡት፡፡ ሰንሻይን ለኔ እስከአምስት እንደ ተማርኩበት እንደ እንደሻው አልነበረም፡፡

የምንማረው ጠዋትም ከሰአትም ነበረ፡፡ ጠዋት ስድስት፣ ከሰአት ሁለት ፔሬድ፡፡ ቤታቸው ሩቅ የሆነ ልጆች ምሳቸውን ይዘው ሄደው እዚያው ት/ቤት ይበላሉ፡፡ እንደኛ አይነቱ ቤቱ ቅርብ የሆነ ደግሞ ቤት ገብቶ ምሳውን በልቶ ይመለሳል፡፡ ታድያ እዚያው የሚበሉ ልጆች ቤት ገብተን ከምንበላው ልጆች ጋር ተቀላቅለው ከትምህርት ቤት ግቢ ወጥተው ሌላ ቦታ እንዳይሄዱ፣ ለምሳ ለሚወጡት ልጆች፣ ለዘበኛ አሳይተን የምንወጣው ካርድ ይሰጠን ነበር፡፡ ካርዱን ቤት ረስተን የሄድን ጊዜና ሲጠፋብን እንግዲህ ከዘበኞች ጋር ጭቅጭቅ ነው፡፡
7ኛ ክፍል ላይ አሊ ካርዱ ሲጠፋበት የሚወጣበትን መንገድ ዘየድኩለት፡፡ እኔ ካርዴን ለዘበኛው ሳሳይ እሱ ይከተለኛል፡፡ እኔ አሳይና ወዲያው እጄን ወደ ኋላ አርጌ ካርዴን ለሱ አቀብለዋለሁ፡፡ ወዲያው ተቀብሎኝ፣ እሱም ካርዴን ያሳይና እሱም ይወጣል፡፡ ዘበኛ ማታለል ደስ ይል ነበር፡፡ መያዝ አይቀርም(ድሮ ፖሊስና ህብረተሰብ ላይ ወንጀል ተሰርቶ ከህግ ማምለጥ አይቻልም ሲሉ እውነትም ወንጀል ከሰሩ መታሰር የማይቀር፣ እውነትም ሰው ወንጀል የሚሰራው እንደሚታሰር እያወቀ ይመስለኝ ነበር) ተያዝን፡፡ ከብዙ ቀናት ማታለሎች በኋላ አንድ ቀን አንዱ ዘበኛ ያዘን፡፡ "ማንን ነው ምታታልሉት? እዚሁ በዚሁ?" አለን፡፡ የአማርኛ አስተማሪያችንን ጠራብን፡፡ ጮኸች፡፡ "አንተ ልጅ ምን ላርግህ?" አለችኝ፡፡ "አባትና እናትህን ነው የምጠራልህ" አለችኝ፡፡ አስደነገጠችኝ፡፡ አሊንም እንዲሁ፡፡

ሰንሻይን 6ኛ ክፍል ስማር፣ የ8ኛ ክፍል ተማሪ ስላጣ እስከ 7ኛ ክፍል ብቻ ነበር፡፡ 7ኛ ክፍል እነገነት፣ እነሚጡ፣ ነበሩ የሚማሩት፡፡ ገነት የምትባለዋን ልጅ የት/ቤቱ ተማሪ በጠቅላላ ነበር የሚፈራት፡፡ ለምኗ እንደሆነ በጣም ግራ ይገባኝ ነበር፡፡ አስተማሪዎች እንኳን ይፈሯት ነበር፡፡ የት/ቤቱ ምክትል ዳይሬክተር ነበረች ማለት እችላለሁ፡፡

ሰንሻይን እንደ እንደሻው ውስጥ ለውስጥ አልነበረም፡፡ ዋናው መንገድ ላይ ከጎን ነበረ፡፡ ሰንሻይን መግባት ከጠቀመኝ አንዱ በቅርቡ ፊልም ማከራያ ቤቶች ነበሩ፡፡ ፊልም ለራሴ መከራየት ጀመርኩ፡፡

ሁሉም የሚጀምረው ሰው የሚያየው ልብስ ነው፣ ስዘንጥ ሁሉም ሰላም ይለኛል፣ ሳልዘንጥ አልታያቸውም ከማለት ነው፡፡ ደረጃ አንድ፡፡

ኦሊ(የት/ቤትና የሰፈር ጓደኛዬ) ብዙ መጽሐፍት ነበረው፡፡ ዴርቶጋዳ የሚባል መጽሐፍ ነበረውና ወስጄ አነበው ጀመርኩ፡፡ ላስቀምጠው አልቻልኩም፡፡ እንዴ ማነው ይሄን የጻፈው? በጣም የሚገርም መጽሐፍ፡፡ ስለሀገሬ ማሰብ እንድጀምር ያደረገኝ መጽሐፍ ነበረ፡፡ ልቦለድ ማንበብ ምን ያህል እንደሚያዝናና፣ እንዴት እንደሚያስደስት? እንደ ዴርቶጋዳ እኔን ሊያዝናኑ የሚችሉ ስንትና ስንት መጽሐፍት ሊኖሩ እንደሚችሉ አሰብኩ፡፡ መገመት አልችልም፡፡ በአጭሩ ብዙ፡፡ ደስ አለኝ፡፡ ዴርቶጋዳ፣ "መጽሐፍ አዳኝ" እንድሆን ያደረገኝ መጽሐፍ ነው፡፡ ዴርቶጋዳ እንደ ትርጉም መጽሐፍትም አልነበረም፡፡ እንደ ሀገር ውስጥ መጽሐፍትም አልነበረም፡፡ ዴርቶጋዳ እንደ የይስማዕከ ወርቁ አይነት መጽሐፍ ነበረ፡፡ ሚራዥ፣ ሻጊዝ፣ ዣንጊዳ፣ ሜሮዳ፣ ሲጻራ፣ አናንያ… ዴርቶጋዳን ከዚያ ወዲህ ሁለቴ እንብቤዋለሁ፡፡ ለልጆች፡፡ እሱንም እየለመንኳቸው፡፡ 7ኛ ክፍልና 10ኛ ክፍል ስማር፡፡
ቀጥዬ ከኦሊ ፍቅር እስከ መቃብርን ተቀብዬው ማንበብ ጀመርኩ፡፡ "The legend ፍቅር እስከ መቃብር!"፡፡ ፍቅር እስከ መቃብርን ከዴርቶጋዳ ቀጥዬ ማንበብ አልነበረብኝም፡፡
ቤት፣ እንዳነብ ነጻነት አይሰጡኝም ነበር፡፡ በርግጥ "ማንበብ ጥሩ ነው፣ አዕምሮን ያሰፋል" ይላሉ፡፡ ግን እኔ እያነበብኩ ሲያዩኝ ደስ አይላቸውም፡፡ "ምንድነው እነዚህ ሰዎች እኔን የሚያስደስተኝ ነገር ያናድዳቸዋል ማለት ነው?" እል ነበር፡፡ ፍቅር እስከ መቃብርን ማንበብ ስጀምር የ6ኛ ክፍል ተማሪ ነበርኩ፡፡ ቤት በት/ት መጽሐፍ ሸፍኜው ሳነብ፣ ያው መጽሐፉ በጣም ትልቅ አይደል? ለመደበቅ አይመችም፡፡ እናቴ መጣችና "እስኪ ምን እያነበብክ ነው? "አለችኝ፡፡ መጥታ ስታይ፣ "ፍቅር እስከ መቃብር"፡፡ "ማንን ማታለልህ ነው? በት/ት ሰአት ነው ምታነበው? ሄጄ ነው ሽንት ቤት ውስጥ የምጥልልህ" አለችኝ፡፡ ትዝ ይለኛል ገጽ 10 ላይ ነበርኩኝ፡፡ "ኧረ የሰው ነው" አልኳት፡፡ "እና እኔን ምን አገባኝ?"አለችና አስፈራራችኝ፡፡ "እሺ አሁን ቶሎ ወዳመጣህበት መልሰው" አለችኝ፡፡ ሮጥ ብዬ መጽሐፉን ለኦሊ መለስኩኝና የሆነውን ነገርኩት፡፡

6ኛ ክፍል የእንግሊዘኛ አስተማሪያችን አንዴ ምን መሆን እንደምንፈልግ ሁሉንም የክፍሉን ተማሪ ጠየቀን፡፡ የመጠየቁ ተራ እኔ ጋር ሲደርስ፣ መሆን የምፈልገውን የተናገርኩት፣ ያኔ ቃሉን በቅርቡ ስለሰማሁትና ብዙ ልጆች ያኔ ቃሉን ስለማያውቁት "እሱ ደግሞ ምንድነው?" ብለው እንዲጠይቁ ብቻ ሳይሆን እውነትም ሰዎች ስለሚያስቡት ነገር መመርመር ስለምወድ ነበር "ሳይኪያትሪስት" (psychiatrist) ያልኩት፡፡
በዚያ አመት አንዴ አንድ አስተማሪ፣ ያው እንግዲህ አስተማሪዎች አስተምረው ሲጨርሱ "ጥያቄ ካላችሁ መጠየቅ ትችላላችሁ" አይሉም? አስተማሪውም ድምጹን ከፍ አድርጎ "gaaffii?"ጥያቄ? ብሎ ሊወጣ ሲል እኔም ድምጼን ከፍ አድርጌ "deebii"(መልስ) አልኩኝ፡፡ አስተማሪው ሰማ፡፡ እየወጣ የነበረውን ተመልሶ መጣ፡፡ ማን እንዳለ አወቀ፡፡ "እኔ ላይ ነው ምትቀልደው?" ብሎ ቢሮ አድርሶኝ በእርጥብ የጥድ እንጨት አርጩሜ፣ እጄ ላይ ለጥልጦ ሸኘኝ፡፡ አውቄ አስተማሪውን ለማናደድ አስቤ ሳይሆን አምልጦኝ ቢሆንም ያቺ ቀን የመጀመሪያዋ አስተማሪን የተሳፈጥኩባት ቀን ነበረች፡፡

ቲቪ፡ "ግማሹን ህዝብ ሳንጠቀም ያሰብነውን አላማ ልናሳካ አንችልም" ይባል የነበረበት፣ ፓርላማ የሴት አባላቱን ብዛት ግማሽ ያህል ለማድረስ የሚሰራበት ጊዜ፣ ሴቶች ከወንድ እኩል መሆናቸውን ያመኑበት፣ ወንዶች ስለሴቶች እኩልነት የሚከራከሩበትም ጊዜ ነበር፡፡
2003 በኔ ህይወት የፊልም አብዮት የተነሳበት ጊዜ ነበረ፡፡ ሆራይዘን መግባቴ ፊልም ለራሴ አማርጬ እንድከራይ እድሉን ከፈተልኝ፡፡ ብዙ ፊልሞችን ማየት ቻልኩኝ፡፡ የትርጉም ፊልሞች፡፡ ዴቦራ ሪከርድስ ትርጉም በስለሺ፣ ዋሴ ሪከርስ ትርጉም በስለሺ፣ ዋቢ ቪዲዮ ሴንተር

ትርጉም በስለሺ፡፡ “ሁሉም የስለሺ ነው እንዴ?” እል ነበር፡፡ 2008 ላይ ሰይፉ ሾው ላይ ቀርቦ ለቪዲዮ ቤቶቹ እየዞረ እንደሚተሮጉም እስከሰማ ድረስ፡፡ እኔ የስለሺ አድናቂ ነበርኩኝ፡፡ እነትርጉም በቶፊቅ፣ ትርጉም በቃሲም፣...አይመቹኝም ነበር፡፡

የማይደርስ ክፉ ነገር የለም የ2003 የሴሚስቴር እረፍት ጊዜ ደረሰ፡፡ ከነዚያ የሁለት ሳምንት የእረፍት ቀናት መሃል በአንዱ ቀን ጠዋት እነአዳ(የአቢቲ ወንድም) ቤት ተሰይሜአለሁ፡፡ ከአዳ ጋር ሠካራሙ ፖስታን እያየሁ፡፡ ሠካራሙ ፖስታ በጣም የተወራለት ፊልም ስለሆነ በጣም በጉጉት ነበር ያየሁት፡፡ እውነትም አሪፍ ነበር፡፡ ግን ፊልሙ ላይ አንድ አልዋጥልህ ያለኝ ነገር ነበረ፡፡ ያኔ አልመጣልኝም ነበረ፡፡ 10ኛ ክፍል ላይ ታድያ ስለዚያ ፊልም ሳሰላስል ያ ያልተዋጠልኝ ነገር ተገለጠልኝ፡፡

ባለ ፖስታዋ የተኛችው ሰውዬ የኤች አይ ቪ ተሸካሚ ነው፡፡ እና እሷም ቫይረሱ ደሟ ውስጥ እንዳለ እርግጠኛ ነች፡፡ የሰለሞን ቦጋለ ጓደኛ ታሪኩን ሲጠይቃት ድንግል እንደነበረችና ያኔ በኮንዶም እንደተኙ ትነግረዋለች፡፡ ታድያ ይሄ ንግግር ቫይረሱ ከፍቅረኛዬ ወደኔ አልተላለፈም ብሎ ለማመን እንጂ ተላልፎብኛል እራሴን አጠፋለሁ ምናምን ለማለት ነው እንዴ መዋል የሚችለው? አያሳምንም፡፡ መሃይም ነች እንዳትባል ደግሞ አይደለችም፡፡ ታሪኩ ባጠቃላይ አያሳምንም ማለት ይሆናል፡፡

ሰካራሙ ፖስታን አይቼ ስጨርስ እነሳሚ ቤት ሄድኩኝ፡፡ ሳሚ ዝውውራቸው ከክረምት (ከ5 ወር በኋላ) ወደ ዛሬ ማታ(ያን ቀን ማታ) ወይ ነገ ጠዋት እንደተቀየረ ነገረኝ፡፡ I was like “what?!” ከዚያ የሰካራሙ ፖስታን ታሪክ ነገርኩት፡፡ ድሮ ያየነውን ፊልም ታሪክ መነጋገር እንወድ ነበር፡፡ ግን ብዙ ጊዜ ይሰለቻል፣ ለሚሰማው፡፡ የሚናገረውማ በጣም ነው ደስ የሚለው፡፡
ያን ቀን ቤት ስገባ ወንድሜ አንድ ተከታታይ ፊልም ይዞ መጥቶ ነበር፡፡ ከሰአት እኔ፣ ወንድሜና ጎረቤታችን የነበረው ቦሻ ጀመርነው፡፡ The Vampire Diariesን፡፡ አቢቲ(ሌላኛው ጓደኛችን) ት/ቤት ነበረ፤ እኔ ፊልም እያየሁ፡፡ እነሳሚ ቤት መኖር እንደነበረብኝ አውቀዋለሁ፡፡ ሁለት ፓርት ነበረ ያየነው፡፡ አንድ ኤፒሶድ 40 ደቂቃ፣ አራቱ 2 ሰአት ከ 40 ደቂቃ፡፡ ፊልሙን አይተን እንደጨረስን ወደ ላይ ሰፈር ሳሚ ጋር ልሄድ ስል የአክስቴ ልጅ የሆነችውና እኛ ጋር ትማር የነበረችው ፍሬ፣ “ገና እኔ ከግቢያችን ሳልወጣ መጥታ እነሳሚ ሄዱኮ” አለችኝ፡፡ “አሁን ገና ነው የሄዱት፣ ሳሚ ደግሞ ሲጠይቅህ ነበር”፡፡ ጓደኛዬን ሳልሸኘው ቀረሁ፡፡ ወደ 10 አመት ለሚጠጋ ጊዜ ጓደኛዬ የነበረውን ጓደኛዬን ሳልሸኘው ሄደ፡፡ ከዚያ በኋላ እንገናኝ እንደሆነ አላውቅም፡፡ እኔ የማውቀው ያቺ ቀን መገናኘት እንዳለብኝ በማውቅበት ቦታ አለመገኘት የጀመርኩባት ቀን መሆኗን ነው፡፡ አሳሳቢው ጉዳይ እንደገና መገናኘታችን አይደለም፡፡ አሳሳቢው ጉዳይ እኔ ሳሚ የመቱን ምድር ለቆ ሲሄድ አለመሸኘቴ ነው፡፡ ጓደኛዬን ሳልሸኘው ቀረሁ፡፡ ለምን? ፊልም ለማየት፡፡ The Vampire Diaries የተሰኘ ተከታታይ ፊልም፡፡ ሳሚ “ቤቢስ?” ብሎ ሲጠይቀኝ ነበረ፡፡ ተላቅሰን ነበር መሄድ የነበረበት፡፡ ያ ፊልም አንድ በህይወቴ ትልቁን ትዝታ ነጠቀኝ፡፡ ብዙ ፊልሞች ብዙ ትዝታዎችን ሊነጥቁኝ...
በአካል መለያየት ይኸው እንዲሁ ጠዋት ሲያወሩ ውለው ከሰአት የመለያየት ያህል ቀላል ነው፡፡ ጓደኛዬን መርሳት ግን ቀላል አልሆነልኝም፡፡ እያደረ ይናፍቀኝ ነበር፡፡ በህልሜ አብረን ስንጫወት አይ ነበር፡፡ ያለቀስኩበት ጊዜም ነበረ፡፡
የማይቆረጥ ነገር የለም ከጊዜ ብዛት እኔና ሳሚ ተቆራረጥን፡፡

እኛ ቁጠባ ቤታችንን ቀየርን፡፡ እነሳሚ ሀገር ለቀው ወንጂ ገቡ፡፡ እነጸሀይ ተከትለው ቤት ቀየሩ፡፡ እነስጦታ ቀጠሉ፣ እነኢየሩስም፣ እነናኦልም፡፡ የማይረሱ ትዝታዎችን ያሳለፍንበት ሰፈራችን በሁላችንም የድሮ ሰፈራችን ለመባል ተገደደ፡፡ አስተማሪ ተሰማ ፊልድ ሲሄዱ ለዳግምና ለኢየሩስ ብቻ አልነበረም የወጪ የሚሰጡት፡፡ ለኔ፣ ለወንድሜም ጭምር ነበር፡፡ እኛ ቤትም እንዲሁ፡፡ ያ ጉርብትናም የድሮ ጉርብትና ሆኖ ቀረ፡፡ በዚያ የቀሩት እነማሙሽ፣ እነአቢቲና እነአቤ ብቻ ነበሩ፡፡

ቫምፓየር ዳያሪስን መውደድ ብቻ ሳይሆን አበድንለት ማለት ይቻላል፡፡ 6ኛ ክፍል ምሳ ሰአት ይሄን ፊልም ሳይ ቆይቼ አርፍጄ አስተማሪ ከገባ በኋላ ክላስ የምገባበት ጊዜ ነበረ፡፡ ቀስ በቀስ ዘቫምፓየር ዳያሪስ በክፍላችን ዋና የመወያያ ርዕስ ሆኖ ብቅ አለ፡፡ ሁሌ ስለዚያ ፊልም ነበረ የምናወራው፡፡ ቀድሞ ብዙ ፓርት ያየ ላላየው ታሪኩን ይነግረዋል፡፡

ሰንሻይን ከብዙ ልጆች ጋር መቀራረብ ቻልኩ፡፡ በተለይ ከኦሊ ጋር፡፡ እንደሻው ስንማር እሱ ኤ እኔ ቢ ነበርን፡፡ አሁን ግን አንድ ክፍል አንድ ሰፈር አብረን ነበር የምንውለው፡፡ ከኦሊ ጋር በጣም እየተቀራረብን ከመምጣታችን በተረፈ በጣም ያናድደኝ ነበር፡፡ በጣም አናዳጅ፣ ጓደኛው ልሆን የማልችል አይነት ልጅ ነበር ኦሊ፡፡ እሱ ስለ አንድ ስለሚያናድድ ነገር ሲያወራ ዝም ብዬ ነበር የማዳምጠው፡፡ ዝም ብዬ ያልተናደድኩ ለመምሰል እሞክራለሁ፡፡ ከዚያ “እንዴ እሱ እንደፈለገ ሲያናድደኝ እኔ ዝም ብዬ ላዳምጠው አይገባም” ብዬ እኔም እሱን ለማናደድ መሞከር ጀመርኩ፡፡ ከዚያ ኦሊን አፉን መክፈት እንዲፈራ ነበር ያረግኩት፡፡ ኦሊ እኔን ማናደድ አቆመና በግልባጩ እኔ አናዳጁ ሆንኩኝ፡፡ ከኦሊ ጋር ፊልም አብረን እናይና እንዋዋስ ነበርና ከት/ቤት አብረን ስንገባ ትናንቱን ያየሁትን ፊልም እንዴት እንደሚጸዳ ብዬ እየነገርኩት እያለ “ስጠኝ” አለኝ፡፡ “አልሰጥም” አልኩት፡፡ “ለምን?” “አሁን እንደገባሁ ነው የምመልሰው እኔ ጋር ቆየ” አልኩት፡፡ “አልሰጥም ስትልኮ መስጠት ያልፈለግክ ነው የሚመስለው፡፡ እኔ ጋር በጣም ቆይቷል አሁን ነው የምመልሰው፣ ልሰጥህ አልችልም ነው የሚባለው” አለኝ፡፡ ሳቅኩና “ትክክል ነህ” አልኩት፡፡

ስድስተኛ ክፍል ስማር ሁሴን የሚባል አስተማሪ ነበረን፡፡ ስም ጠሪያችንም ነበር፡፡   ህብረተሰብ ነበረ የሚያስተምረን፡፡ ከሚያስተምርበት፣ የሚቀልድበት፣ ከትምህርት ጋር የማይያያዙ ነገሮችን የሚያወራበት ጊዜ ይበልጣል፡፡ስለፍልስፍና፣ ስለፈላስፎች ታሪክ፣ ስለዲዮጋን ምናምን፡፡ ወጣቱ ሁሴን አስተማሪ ሳይሆን ኮሜዲያን ነበር የሚመስለው፡፡ አስተማሪው ት/ቤታችንን ሊለቅ እንደሆነ ስንሰማ የክፍላችን ልጆች ብር አዋጥተን ሽኝት አዘጋጅተንለታል፡፡   የጥበብ ፈለግ የሚባል ሰማያዊ መጽሐፍ በስጦታ መልክ አበረከትንለት፡፡ መጽሐፉን እንደነበረው አሁን(ከ10ኛ ክፍል ወዲህ) እጠረጥራለሁ፡፡ ያን የሽኝት ቀን ፕሮግራም መሪያችን ማን ቢሆን ጥሩ ነው? ከየት መጣች ሳትባል የ7ኛ ክፍሏ ገነት! እኛ ስድስተኛ ነን፡፡ “ምንድነች? ምን ትሰራለች ከዚህ?” ብዬ ጠየቅኋቸው የኛ ክፍል ጓደኞቿን፡፡ “ከፍላለች” አሉኝ፡፡ ጥያቄዬ ስለመክፈሏ አልነበረም፡፡ ስለመምጣቷ እንጂ፡፡ የማታፍርና የማያፍሩ ልጆች! ፕሮግራማችን መማሪያ ክፍል ውስጥ ነበረና፣ ገነት እንዲህ

አሳምራ በእንግሊዘኛ ሰሌዳ ላይ የሆነ ነገር ስለበአሉ ጻፈች፡፡ “cermony” ይላል፡፡ “ceremony” ተብሎ ነው የሚጻፈው አልኳት፡፡ አላመነችኝምና አላስተካከለችውም፡፡
ይሄ እኛ ላስተማሪው ስጦታ የሰጠነው አይነት የፍልስፍና መጽሐፍ ማንበብ፣ ያሳብዳል ይባላል፡፡ እገሌ አሾ አንብቦ አበደ፡፡ እገሌ ራምፓን አምብቦ አበደ፣ የፍልስፍና መጽሐፍ ማንበብ ያሳብዳል... ምንም አላምነውም ነበር፡፡ It’s just a book, right? ትዝ ይለኛል ቀኑ ቅዳሜ ነበር፡፡ ቤት ስገባ ወንድሜ “ይሄን ነው ለብሰህ ሽኝት የሄድከው?” አለኝ፡፡ “አዎ” አልኩት፡፡ እኔ ምንም አልመሰለኝም ነበር፡፡

ሰኔ ሰላሳ በአመቱ የት/ት መዝጊያ ስነስርአት የወላጆች ቀን ኬነሳ ቀልደኛ ነበረና ቀልድ አቅርብ ይባላል፡፡ በፊት አልተነገረውም አልተዘጋጀበትም ነበር፡፡ ልጁም ስላልፈለገና በወላጅ ፊት መቅረብ ስለፈራ እምቢ አሻፈረኝ አለ፡፡ ሲበረቱበት መስማማት አይቀርም ተስማማ፡፡ ሄደና ማይክራፎኑን ጨበጠ፡፡ ያን ቀን የተናገረውን ቀልድ እኛ በፊትም እናውቀዋለን፡፡ ግን ብዙ ቀልዱን የማያውቁና ወላጅ በዚህ ቀልድ ይስቅ ሆነ ይናደድ፣ ለመለየት ሲሉ ቀልዱን እንደገና ቢሰሙ የማይከፋቸው ተማሪዎች ብዙ ነበርን፡፡ ቀልዱ እንዲህ ነው፡
የሆኑ ሴትዮ ቤት ቁርስ ሁሌ ገንፎ ነው፡፡ ታድያ ከአንድ ልጃቸው ጋር ነው የሚኖሩትና ልጁ ገንፎ መብላት ይሰለቸዋል፡፡ ስለዚህም ቁርስ የሚያስቀይርበትን መላ ይዘይዳል፡፡ “እማ ገንፎ HIV ማስያዝ ጀመረ አሉኮ” ይላቸዋል፡፡ እናትየውም ተቀብለው፣ “ታድያ ምን ችግር አለው? በኮንዶም እንበላለና” ይሉታል ይባላል፡፡ ሰውዉ ኬነሳ ቀልዱን ሲናገር በሳቅ ፈረሰ፡፡ በርግጥ የሚያሳፍር ቀልድ ነው፡፡ ለዚህ ነው አንዱ ወላጅ “ልጆቹን እንዲህ አይነት ነገር ነው የምታስተምሯቸው ማለት ነው?” ብሎ ልጁን ይዞ ያኔው ውልቅ ብሎ በመጣበት በንዴት የተመለሰው፡፡

አዲሱ እኔ (A whole brand new me)

በ2003 ክረምት እቅዴ መጽሐፍ ማንበብ ነበረ፡፡ ልቦለድ መጽሐፍት፡፡ መጀመሪያ ጀምሬ እናቴ የከለከለችኝን ፍቅር እስከ መቃብርን ዛሬ ነገ ሳልል ከአሊ ተቀብዬ አነበብኩት፡፡ ፍቅር እስከመቃብር አሪፍ ታሪክ አለው፡፡ በየመሀሉ የሚገቡት የተንዛዙ ፍለስፍናዎች ግን ያሰለቻሉ፡፡ አልፎ አልፎ፣ እየዘለልኳቸው ነበር መጽሐፉን አንብቤ የጨረስኩት፡፡ ከዚያ ወዲህ የማነበውን መጽሐፍ ከማን ከየት ብዬ እንደማገኝ አጣሁኝ፡፡ ከአንድ አዲስ የተከፈተ ላይብረሪ ለመዋስ አባል መሆን እንደሚያስፈልግ ሰማሁኝ፡፡ አሊ ነበር የነገረኝ፡፡ ከአሊ ጋር ቤተሰብ መምሪያ ላይብራሪ አባል ሆነን መታወቂያችንን ወሰድን፡፡ የቤተሰብ መምሪያ ላይብረሪ እኔ እንደምፈልገው ብዙ ልቦለድ መጽሐፍትን ያለው ብቻ ሳይሆን ለቤት ቅርብ ነበረ፡፡ እኛው ሰፈር፡፡ ወዲያው ነበር እኔና አሊ መጽሐፍ መዋስ የጀመርነው፡፡ ከመምሪያ ለመጀመሪያ ጊዜ ተውሼ ያነበብኩት መጽሐፍ ትዝ ይለኛል፡፡ ሰውየው አንዴ ፒተር፣ አንዴ የፒተር ሮቦት፣ ፖል ነኝ እያለ ሴትየዋን የሚፎግርበት በዳኤላ ስቲል የተጻፈ ትርጉም መጽሐፍ ነው፡፡ ዳኤላ ስቲል ማለት የብርቅርታ ደራሲ ነች፡፡ እናም በብዛት ከዚያ ላይብረሪ ተውሼ ያነበብኳቸው መጽሐፍት የትርጉም ስራዎች ነበሩ፡፡
ልቦለድ መጽሐፍት ማንበብ በጣም ደስ የሚል ሲበዛ በጣም የሚደንቅ ልምድ ነበረ፡፡ ታሪኩን ትጀምራለህ፣ እያነበብከው ስትሄድ ውስጡ ትገባለህ፡፡ በቃ ተው ከዚያ ወዲያ ሌላ አለም ውስጥ ነህ፡፡ ክረምት ልቦለድ ሳነብ፣ቀኑን ሙሉ እንደመተኛት ነበረ ስሜቱ፡፡ የት እንዳለህ አታውቅም፣ ባካባቢህ ስላሉት ነገሮች አታስብም፣ብቻ አንዱ ደራሲ አዕምሮውን ጨምቆ የፈጠረውን እንደማር የሚጣፍጥ ታሪክ በአይኖችህ መኖር ነው፡፡ የማነባቸውን መጽሐፍት መጨረሻቸውን ለማወቅ ስለምጓጓ ከሁለት ቀን በላይ ሳልጨርሳቸው እጄ ላይ እንዲቆዩ አልፈልግም ነበር፡፡ ይሄን መጽሐፍ ሳልጨርስ አልተኛም በሚል ከሌሊቱ እስከ 8 ሰአት ተቀምጬ የማነብበት ጊዜ ነበረ፡፡
መጽሐፍ ማንበብ በጣም ነበር የተመቸኝ፡፡ ታዲያ እንዴት አይመቸኝ? የማስበው ነገር የለ፣ የምጨነቅበት ነገር የለ፣ የሚያናድደኝ ሰው የለ፣ ቢኖር እንኳን ስለዚያ ለማሰብ አዕምሮዬ ቦታ አልነበረውም፡፡ የሆኑ ሰዎች ህይወት ውስጥ መስመጥ ነው፡፡ እነሰይጣናዊ በቀል፣ ስርየት የለሽ ጸጸት፣ የታፈነ ዕንባን የመሳሰሉት መጽሐፍት ጓደኞቼ ሆኑ፡፡ ቀንና ማታ አከታትዬ አነባቸው ነበር፡፡ ቤት ውስጥ፣ እኔ እራት ከተበላ እኔ ወደ መጽሐፌ፡፡ እነሱ ወሬ ሲይዙ እኔ ቤት የለውም፡፡ እነሱ ሲያወሩ ጆሮዬም፣ ምኔም፣ ሁለነገሬ አይን ሆኖ መጽሐፍ ውስጥ ነው፡፡ ሁለት ገጽ መገልበጥህን ሳታውቅ 15 ገጽ ላይ መድረስ ደስ ይላል ነው የሚባለው? ይጥማል፡፡

ፊልም ስናይ ከቤት እኛ በማየታችን ሳይከፉ ቀርተው አያውቁም፡፡ የአማርኛ ፊልም እንኳን ቢሆን በአንድም ሆነ በሌላ ምክንያት እኛ ፊልም ማየታችንን ካወቁ ይቆጣሉ፡፡ አንደኛው፣ ማጥናት ትተህ፣ ሁለተኛው የታዘዝከውን ሰርተህ ሳትጨርስ፣ ሶስተኛዋና የአባቴ ብቻ የሆነችው መቆጫ፡ “ፈረንጅ የደረሰበት ደርሶ የሚሰራውን ሲያጣ ይቀልዳል፣ አንተ ተቀምጠህ ትጃጃላለህ”፡፡ እኛ በልባችን “Come on Dad, you know nothing about movies. They are very entertaining, making movies is just one type of industry, it provides job opportunities for many people.” አና እንደኔ ስትሆን “አርት ነውኮ ሀይል፣ ጥበብ፡፡ ፊልምኮ ጥበብ ነው፡፡ አንተ ፊልም ሳታይ ስላደግክ ነው እንጂ ፊልም በጣም አሪፍ ነገር ነው” ትላለህ፡፡ ብቻ “እነሱ የሚላላሱትን ለማየት ስታፈጥ ውለህ፣ ምን ትጠቀማለህ?” ያለ ቀን ጋማ ትገባና አንገትህን ትደፋለህ፡፡ ሰው ለሰው እኛ ቤት ሁሉም ሲያየው የነበረ ድራማ ነበር፡፡
ቤት፣ ከቲቪ ሰምተው ነው መሰለኝ ከሆነ ጊዜ ወዲህ “ብታዩምኮ ጠቃሚውን ከጎጂው ለይታችሁ መሆን አለበት” ማለት ጀመሩ፡፡

ብዙ የአማርኛ ፊልሞች መሰራት ጀመሩ፡፡ ነጻነት ወርቅነህ የሚሰራቸው ፊልሞች ተወዳጅ ሆኑ፡፡ በተለይ ኤፍቢአይ፡፡ እኔ ኤፍቢአይን ካየሁ በኋላ እንደሱ ቀልደኛ፣ ሴት የማይፈራ፣ የሚያስቅ ጀንጃኝ ለመሆን እፈልግ ነበር፡፡ በፊት በፊት ሲሰሩ የነበሩ ጥቂትም ቢሆኑ ፊልሞች እንደነአላዳንኩሽም አሳዛኝ ሲሆኑ የወንዶች ጉዳይን፣ ብሎም ኤፍቢአይን ተከትለው የመጡት ግን በብዛት ኮሜዲ ናቸው፡፡ በተለይ የነጻነት ወርቅነህን ፈለግ ይከተላሉ፡፡ ሴቶችን እያሳቁ፣ ከዛ እንዲወዷቸው ማድረግ፡፡ በተለይ የነጻነት ወርቅነህ ኤፍቢአይ ብዙ ከሱ ወዲህ የመጡ የአማርኛ ፊልሞችና ልጆች ላይ ተጽዕኖ አድርጓል፡፡ ብዙ ልጆች እሱና ከሱ በኋላ መጡ ካራክተሮች የሚናገሩበት የንግግር ስልትና አቀላለድ ተጋብቶባቸው ታዝቤያለሁ፡፡
ብዙ ሰዎች የአማርኛ ፊልሞች ላይ ሂስ ሲሰጡ የአማርኛ ፊልም መጨረሻው ይታወቃል ይላሉ፡፡ እኔ አይዋጥልኝም ነበር ታዲያ፡፡ እንግሊዘኛ ፊልምምኮ አክተሩ(ነበር የምንለው)(ዋና ተዋናዩ) መጨረሻ ላይ እንደሚያሸንፍ ይታወቃል አይደል እንዴ? ሰውዉ እንደዚያ የሚለው በሀገራችን የሚሰሩ ፊልሞች በብዛት የፍቅር ዘውግ ስላላቸው ነው፡፡ እኔም የእንግሊዘኛ ፊልሞች መጨረሻቸው ይታወቃል ያልኩት ድሮ የምናየው የአክሽን ፊልሞችን ስለነበረ ነው፡፡ ያኔ ካለ አክሽን ፊልም አናይም፡፡ ጭፍጭፍ፣ከሽከሽ፣ ጥፍጥፍ የሌለበት ፊልም ፊልም አይመስለንም ነበር፡፡ የሽዋዚንገር ፊልሞች፣ የጃኪ ቻን፣ ጄት ሊ፣ ቫን ዳም፣ ጄሰን ስታተን፣ ሬንቦ ምናምን፡፡ በቃ ኤክስፔንደብልስ ላይ ያሉ አክተሮች ፊልሞች ናቸው ፊልም ራሱ የሚመስሉን፡፡ ይተዋወቃሉ፣ ያስቃታል፣ ይዋደዳሉ፣ የዋሻት ወይም የደበቃት ነገር ይኖራል፣ ይጣላሉ፣ አብረው ያሳለፉትን ጊዜ ያስታውሳሉ፣ ይታረቃሉ፡፡ አክተሩ አለ፣ ጠላት አለው፣ ይጣላሉ፣ ይደባደባሉ፣ መጨረሻ ላይ አክተሩ ያሸንፋል፡፡ ነገር ግን ተመሳሳይ ነው ብሎ ማየቱን የሚተው ሰው የለም፡፡ ነገሩ እንደዚያ አይደለማ፡፡ በተጨማሪ የቻይና ፊልሞችንና የህንድ ፊልሞችንም እናያለን፡፡አሳዛኝና ሆድ የሚያባቡ የነሳልማንና የነሻሩክ ረጃጅም ፊልሞች፡፡ የትኛውም ፊልም፣ እንግሊዘኛውም፣ አማርኛውም፣ ህንድኛውም፣ የቻይናውም፣ ሁሉም የማዝናናት ሀይል አላቸው፡፡ ወይ ፊልም ያኔ!

ስለ ሴቶች ማውራት፣ ሴክስ እያሉ መቀባጠር እኔ ዘንድ ከቶውን ያልነበሩ ከፍተኛ ጥንቃቄ የማረግባቸው ጉዳዮች ነበሩ፡፡ ስለንደዚህ አይነት ነገሮች የሚያወራ ሰው እኔ ጋር እንደ ዱሪዬ ነበር የሚቆጠረው፡፡

ጎረቤት ከልጆች ጋር ፊልም እያየን ተቀምጠው ከነበሩ ነገሮች አንድ ነገር አየሁ፡፡ ተበታትነው ተቀምጠው ከነበሩ መጽሐፍት መሃል አንድ በነጭ ሽፋን የተሸነፈነ መጽሐፍ አየሁ፡፡ ርዕሱ ጥበብ 1 ይላል፡፡ ከስር ደግሞ "ከጺላጦስ" ይላል፡፡ ውስጡን ከፍቼ ሳየው እንደገመትኩት የፍልስፍና መጽሐፍ ነው፡፡ ከጎረቤት መጽሐፉን ተውሼ ማንበብ ጀመርኩኝ፡፡ አንድ ሌላ ጥበብ 3ም ነበራቸው፡፡ እስከ አስር ነው መጽሐፍቱ ተከታትለው የሚዘልቁት፡፡ መጽሐፎቹ የአለም ታዋቂ ፈላስፎች ፍልስፍና ተተርጉሞና ተቀነጫጭቦ የቀረበበት ሲሆን ጥበብ 1 የነፐሌቶን የነሶቅራጥስን፣ የነአሪስቶተልን፣ የነኮንፊሺየስን፣... በሀይማኖት ደረጃ ደግሞ የቡድሂዝምን፣ የዜናውያንንና የሌሎቹንም ፍልስፍናዎች፣ ታሪኮች፣ አባባሎችና ቀልዶችን የያዘ ነው፡፡ አነበብኩት፡፡ "እኔ ማውቀው አለማወቄን ነው"፣ በዚህች አለም ያለው እውቀት እውቅያኖስ ቢሆን የኔ እውቀት አንዲት ጠብታ ያህል ነች፡፡ ጥበብ 3ንና ጥበብ 7ንም አግኝቼ አነበብኩ፡፡ ጥበብ 7 የኦሾ መጽሐፍት ብቻ የተቀነጫጨቡበት ነው፡፡ በመጽሐፉ መጨረሻ ላይ ኦሾ 93 መኪኖች እንደነበሩትና በአስምና በተለያዩ በሽታዎች ለብዙ አመታት ተሰቃይቶ እንደሞተ ያትታል፡፡ በእግዚአብሔር ላይ ለሰነዘራቸው ሀሳቦች ቅጣቱን ተቀብሎ እንደሆነ አሰብኩኝ፡፡ መቱ ውስጥ ኦሾን አንብቦ እንዲህ ሆነ፣ አበደ፣ ኦሾ፣ ኦሾ ይባላል፡፡ እኔ ግን እኚህን መጽሐፍት ሳነብ የሳበኝ ፍሬድሪክ ኒቼ የሚሉት ፈላስፋ ነው፡፡ እነኚህን መጽሐፍት ሳነብ አንድ የገባኝ ነገር ፍልስፍና በቂ ምክንያት በማቅረብ ሰውን ማሳመን ብቻ እንዳልሆነ ነው፡፡ ከሞት በኋላ ህይወት የለም ይላሉ፡፡ እኔም ከህይወት በኋላ ያለውን ህይወት ሞቼ አላየሁም፣ እሱም አለመኖሩን ሞቶ አላየም፣ እኔ ከሞት በኋላ ህይወት እንዳለ የሞተ ሰው አልነገረኝም፣ እሱም አለመኖሩን የሞተ ሰው አልነገረውም፡፡ ከሞት በኋላ ህይወት እንዳለ በምን አወቅክ ብሎ ሰውን መፈተን እሺ ይሁን፣ ከህይወት በኋላ ህይወት የለም ብሎ በጭፍን መከራከር ግን ምንድነው? ፍልስፍናነቱ የቱ ጋር ነው? እኔስ እሺ "ከተፈጸሙ ትንቢቶች፣ እግዚአብሔር የተናገረው ነገር ከተፈጸመ፣ እግዚአብሔር አለ ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር ካለና የእግዚአብሔር ትንቢት ደግሞ ከተፈጸመ፣ እግዚአብሔር "ከሞት በኋላ ህይወት አለ" ካለ፣ አለ ማለት ነው" ብዬ ትንሽ ምክንያታዊ ልሆን እችላለሁ፡፡ አንዳንዴ የሚገርም ፍልስፍና ይይዙሉ፣ አንዳንዴ ደግሞ የሚያስንቅ ቀላል ነገር ላይ በደረቁ ሲሙዋገቱ ይስተዋላሉ፡፡ ኦሾኮ "ኤድስን ለማጥፋት ከፈለግን ሰውዉን ዝም ብለን መረን እንልቀቅና ተይዞ ተይዞ ሲሰለቸው ያቆማል፣ ኤችአይቪም በዚያው ይጠፋል" የሚል ፈላስፋ ነው፡፡

ኦሾ ምናምን እየተባለ ይካበድ የለ፣ ጥበብ 3ን ት/ቤት ይዤ ሄድኩኝ፡፡ ለጓደኞቼ የሚያስቁትን ክፍሎች መርጬ፣ ስለ አብረሃም ሊንከን ምናምን ላነብላቸው ስል፣ እነሱ እኔ ላነብላቸው የፈለግኩትን ያህል፣ ለመስማት ፍላጎት አልነበራቸውም፡፡ ያን ቀን እረፍት ላይ መጽሐፉን ላይብረሪ ገብቼ ማንበብ ጀመርኩ፡፡ ላይብረሪው ውስጥ ከላይብረሪያንዋ ሌላ ማንም አልነበረም፡፡ ልጆች ከውጪ እየተጫወቱ ነበር፡፡ የኔ ክፍል ልጆች እዚያ አብዋራ እግር በሚያሰምጥበት ሜዳ ላይ ከሌላ ክፍል ልጆች ጋር ኳስ ሲጫወቱ፣ ጸጉራቸውና የአይናቸው ሽፋሽፍት ከለራቸውን ይቀይሩ ነበር፡፡ እኔና ላይብረሪያኗ ብቻ ነበርን ቤተ-መጽሐፍቱ ውስጥ፡፡ እኔ የፍልስፍና መጽሐፌን ካቆምኩበት ቀጥዬ እያነበብኩ ነው፡፡ ከዚያ የአማርኛ አስተማሪዬ ቲቸር ስሜነሽ፣ ላይብረሪያኗ ጋር መጣችና ትንሽ አውርተው አውርተው፣ ቲቸር ስሜነሽ "ናቲ ምን እያነበብክ ነው"ብላ መጥታ እያነበብኩ የነበርኩትን መጽሐፍ ርዕሱን፣ ሽፋኑን፣ አይታ ገልበጥ፣ ገልበጥ አርጋው ማንበብ ጥሩ ነው ምናምን ብላኝ መጽሐፉን ትታልኝ ሄደች፡፡ እንደ አጋጣሚ ከእረፍት ስንመለስ አማርኛ ነበረን፡፡ ያን ቀን የተማርነው ስለእብደት ነበረ፡፡ ስሜን አልጠራችም፡፡ ግን አበደች፡፡ "እኔ ብዙ ፍልፍና መጽሐፍ አንብበው ያበዱ ሰዎች አውቃለሁ..." ብላ ክፍሉን አመሰች፡፡ በዚያ አላበቃችም፣ እያነበብኩ የነበርኩትን መጽሐፍ ይዘት ለት/ቤታችን ዳይሬክተር ነገረችው፡፡ እንደሚያስቀምኝ ነገር፡፡ እርሱ ደግሞ አባቴን ደውሎ ጠርቶ ጉዳዩን ነገረው፡፡ ያን ቀን ቤት ተ.ቆ.ጡ.ኝ፡፡ ማበድ ፈልጌ እንደሆነ ጠየቁኝ፡፡ እግዚአብሔር የለም የሚል መጽሐፍ ማንበብ ለምን

እንዳስፈለገኝ ጠየቁኝ፡፡ እኔ ግን ያኔ ወላጆቹ ሲቆጡት የሚመልስ አይነት ልጅ አልሆንኩም፡፡ አባቴ ከዚህ በኋላ እንዲህ አይነት ነገር አነበበ ሲባል ልስማና መግቢያህን ፈልግ አለኝ፡፡ መጽሐፉን ወዳመጣህበት መልስ ተባልኩኝ፡፡ መጽሐፍ እንዴት ነው ሰውን የሚያሳብደው? ጥያቄዬ ነበረ፡፡ በዚያ ላይ መጽሐፍ ማንበብ ማለት ሁሉንም እንዳለ መቀበል ማለት አይደለም፡፡ መጽሐፍቶቹ ላይም ይሄ የሰዎቹ እንጂ የተርጓሚው ሀሳብ አይደለም ይላል፡፡ የሚጠቅምህን ትቀበላለህ፣ የማይጠቅምህን ታቆየዋለህ፣ የሚጎዳህን ትጥለዋለህ፡፡ ለማንኛውም አታንብብ ተብዬ የነበረውን መጽሐፍ ደብቄ አንብቤ ጨረስኩት፡፡ አሁን ላይ ሆኜ ሳስበው ኃይለጊዮርጊስ ማሞ እንደዚያ አይነት አደገኛ መጽሐፍት ለምን መተርጎም እንዳስፈለገው ብጠይቀው ደስ ይለኛል፡፡ ብር ነው? ዝና ነው? የሀገሩ ነገር አሳስቦት ነው? ነው ብርና ዝና ብቻ? ወይስ ሁሉም? 7ኛ ክፍል(2004) ለኔ ከድሮው እኔ ወደ አዲሱ እኔነቴ የተለወጥኩበት ነበር፡፡ ሳነብ መያዜ የአንባቢነት መለያ ምሳሌ ነበር ያደረገኝ፡፡ ከክፍሌ ልጆች ጋር በጣም ተቀራረብኩኝ፡፡ እንዳዋቂ እየቆጠሩኝ ሲመጡና ለኔ ያላቸው አመለካከት ከፍ እያለ ሲሄድ ይታወቀኝ ነበር፡፡ ንባቡ ብቻ አይደለም፡፡ የማወራቸው ነገሮችም ጭምር፡፡ እየበሰልኩ መጣሁ ልበል?

ሰንሻይን እንደ እንደሻው ትምህርት ቤት አልነበረም፡፡ ለቀቅ ያለ እንደ እንደሻው ጥብቅ ያልሆነ ት/ቤት ሲሆን ፣ሳንማር የምናሳልፋቸው የሚቃጠሉ ክፍለ-ጊዜያት ብዙ ነበሩ፡፡ ከሰአት ከሰአት በጠራራ ጸሀይ ክፍል ውስጥ ታጉሮ ካስተማሪ ጋር ከመነታረክ፣ ውጪ ጥላ ስር ተቀምጦ ከልጆች ጋር ማውራት በጣም እንደሚጥም ባውቅም የትምህርት ቤቱ ስርአት አልበኝነት ግን በጣም ያናድደኝ ነበር፡፡ ወጥ የሆነ አሰራር ሊኖር ይገባ እንደነበረ ይሰማኝ ነበር፡፡ አንዳንዴ እንደሻው ት/ቤት ይናፍቀኛል፡፡ እዚያኮ እንዲህ በየቀኑ የትምህርት ጊዜ ማቃጠል፣ እንደፈለጉ ግቢ ውስጥ መዞር የሚባል ነገር የለም፡፡ እንደሻው ት/ቤት አስተማሪዎች ተማሪውን ልክ ያስገባሉ፡፡ ተማሪውን ጨምሮ የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ በጠቅላላ ደግሞ እንደሻው ልክ ያስገባል፡፡

እኔ 7ኛ ክፍል ስማር 8ኛ የነበረችው ገነት በትምህርት ቤታችን ማህበረሰብ በጣም የምትፈራ ተማሪ ነበረች ብያለሁ፡፡ እኔ እንደ ሌላው ተማሪ አልፈራትም፡፡ ይልቅ ሌሎች ለምን እንደሚፈሯት እጠይቃቸዋለሁ፡፡ አትወደኝም አልወዳትም ነበር፡፡ ቀኑ የክበባት ቀን ማክሰኞ ነበር፡፡ ስፖርት፣ ሚኒሚዲያ.... ማለት ነው፡፡ የመጨረሻው ፔሬድ ላይ ነበር የክበባት ፕሮግራም የሚካሄደው፡፡ የኛ ት/ቤት ክበባት ለስሙ እንጂ የሚሰራበት ፕሮግራም አልነበረምና ያናድደኝ ነበር፡፡ በዚያ የክበባት ፔሬድ ሁሉም ተማሪ ውጪ ነበር ያን ቀን፡፡ በዚያ ፔሬድ የስፖርት አስተማሪ የነበረው ወጣት መምህር፣ መረብ ኳስ ሊያጫውት እየተዘጋጀ ነበርና ብዙ ልጆች ሜዳው ላይ ውርውር እያሉ ነበር፡፡ ሲጀመር ይሄ አስተማሪ ለሴቶች እንደሚያዳላ አውቃለሁ፡፡ "ገነት ልጆች ምረጪ" ሲል ሰማሁ፡፡ ለጨዋታው ነበር፡፡ እኔ ደግሞ ይሄን ስሰማ አስተማሪው ሳይሰማ "ለምን? ገነት ምን ስለሆነች ነው?" አልኩኝ፡፡ አስተማሪው እንዲሰማኝ ፈልጌ ሳይሆን እንዲሁ ልጅቷን ለምን ያካብዷታል ብዬ ተናድጄ ተቃሞዬን መግለጼ ነበር፡፡ ለማን? ለማንም፡፡ ለራሴው፡፡ "Gannatiin maal caalteetu? Boo!" እንዳልኩኝ ከአናቴ ላይ ጓ የሚል ድምጽ ሰማሁኝ፡፡ እኔ ማንም እንዲሰማ አልነበረም እንደዚያ ያልኩት ሰው እንዲሰማ ቢሆንም እንዲሰማ የምፈልገው የመጨረሻዋ ሰው... የት ሆና እንደሰማችኝም ሆነ፣ ከምኔው አጠገቤ እንደደረሰች አላውቅም፣ ወደ ኋላ ዞር ስል ገነት ነበረች በኋላ በኩል ጭንቅላቴን በጥፊ ያለችኝ፡፡ ምን ሆንሽ? አልኳት በንዴት፡፡ "ናቲ ይኸው ነገሬን አትፈልግ አለችኝ"፡፡ "ምን የምፈራሽ ይመስልሻል እንዴ?" አልኳት፣ ድንጋጤ ልቤን እያፈነው፡፡ "ተው ይኸው ናቲ" እየሰደበችኝ ወደኔ ትመጣ ጀመር፡፡ እኔ ወደ ኋላ፡፡ እጇን እየሰነዘረች ነበር፡፡ ልጆች ይጯጯሁ ጀመር፡፡ አፈግፍጌ አፈግፍጌ ደሜ ሞቅ እያለ ሲሄድና ልጅቷ አላቆም ስትል አንድ ቡጢ ወደ ፊቷ ሰነዘርኩ፡፡ አፍንጫዋን አገኘሁ፡፡ አፍንጫዋን በእጇ ጠረግ ስታረግ ደም በእጇ ላይ፣ አፍንጫዋን አደማሁት፡፡ ደነገጥኩኝ፡፡ "እውነት አስቤ አይደለም አፍንጫሽን የመታሁሽ" ልላት ነበር፡፡ ህዝቤ ተጯጯኸ፡፡ "ደሜን አፍስሰህማ አልለቅህም" አለችኝ፡፡ ደግነቱ ዳይሬክተሩ መጣ፡፡ ቢሮው ይዞን ሄዶ ምን ላይ እንደተጣላን ከጠየቀን በኋላ ወደየቤታችን ተሸኘን፡፡ የምትከታተለኝ መስሎኝ ነበረ፡፡ ወደ ቤት ስገባ ወደ 10 ሰአት ነበር፡፡ ወደ 11 ሰአት ወንድሜ መጣ፡፡ የሆነውን ነገርኩት፡፡ "አንተ እንዴት ሴት ልጅ ትመታለህ?" አለኝ፡፡ ትክክል ነው፡፡ የትምህርት ቤታችን ልጆች ግን እንደዚያ አልነበረም ያዩት፡፡ ማንም ቀና ብሎ የማያያትን ልጅ አፍንጫ ነበር ያደማሁት፡፡ በነጋታው ጠዋት ትምህርት ቤት ስሄድ የክፍሌ ልጆች ጀግና እያሉ አዳነቁኝ፡፡ የትምህርት ቤታችን ልጆች ጀብዱ እንደሰራሁ ነበር የቆጠሩት፡፡

ምህረት የለሽ እንደሆንኩ እያወቁ ተማሪዎች ለምን እኔን ለአለቃነት እንደሚመርጡኝ አላውቅም፡፡ 7ኛ ክፍልም እንደሌሎች ታችኞቹ ክፍሎች እኔው ነበርኩ የተመረጥኩት፡፡ የ7ኛ ክፍል አልቅናዬ ግን የተለየ ነበር፡፡ ከመምህራን ይልቅ ለረጅም ጊዜ አብረውኝ የሚዘልቁት ተማሪዎች እንደሚበልጡብኝ እየገባኝ ነበር፡፡ በፊት የሚረብሹ ተማሪዎችን ስም በደስታ፣ አንዳንዴም በራሴው ተነሳሽነት ለአስተማሪዎች አደርስ ነበር፡፡ ተማሪዎች ይጠሉኝ ነበር፡፡ እኔ ግን ምንም አይመስለኝም ነበር፡፡ የአስተማሪ ፍቅር ይበቃኛላ! 7ኛ ክፍል ላይ ግን ዋና አመጻኛ ሆኜ አረፍኩት፡፡ ተማሪዎች ሊደባደቡ ሲሉ የአለቅነት ግዴታዬን እወጣለሁ፡፡ አስተባብራለሁ፡፡ በፊት ክፍል እንዳይረበሽ፣ 7ኛ ክፍል ላይ ደግሞ ክፍል ውስጥ ልጆች ሲደባደቡ ተጩሆ አስተማሪዎች መጥተው ቶሎ እንዳያገላግሉ ተማሪዎች እንዳይጮሁ አስጠነቅቃለሁ፡፡

ፎራፊ ሲባል መፎረፍ የዱሪዬነትና የመጥፎ ባህርይ ጣሪያ ይመስለኝ ነበር፡፡ አስበው፣ ተማሪው እየተማረ አንተ ውጪ መንቀዋለል ማለት ምን ማለት ነው? ይሄኮ አዕምሮ የሌለው ሰው ስራ ነው፡፡

ሰንሻይን ትምህርት ቤታችን በፊት ኮሌጅ ነበረ፡፡ ትምህርት ቤት ሲሆን ኮሌጁ በሁለት ብሎክ ተወስኖ በኮሌጁና በትምህርት ቤቱ መሃል የቆርቆሮ አጥር ተሰራ፡፡ ታዲያ ያልታጠረ ጎን ነበረውና በኮሌጁ በኩል ለመፎረፍ ይመች ነበር፡፡ 7ኛ ክፍል የተለየ አመት ነበረ፡፡ ምን እንደነካኝ አላውቅም፡፡ ራሴን ከክፍል ጓደኞቼ ጋር ለመፎረፍ ስመካከር አገኘሁት፡፡ ደግሞ የሚገርመው እኔ ከሌሎቹ የበለጠ ደፋር መሆኔ ነበር፡፡ ሌሎቹ ፈርተው ሲመለሱ ብቻዬን ወጥቼም አውቃለሁ፡፡ አንድ ቀን ልንፎርፍ ቁጥራቸውን ከማላስታውሰው የክፍሌ ልጆች ጋር ወደ

ት/ቤታችን ጓሮ(ሰንሻይን ኮሌጅ) በር ተደብቀን ለመውጣት ስንሄድ፣ ከበሩ ትንሽ ራቅ ብሎ ዘበኛው ቆሞ ወደ ሌላ አቅጣጫ ዞሮ አለ፡፡ እንሂድ ብላቸው ታዲያ ዘበኛው ያየናል ብለው ፈሩ፡፡ እምቢ ሲሉ ታድያ እኔ ፊቴን በዩኒፎርሜ ሸሚዝ ሸፍኜ ሮጬ ወጣሁኝ፡፡ እነሱ ቀሩ ታዲያ ከክፍል ኅበዙ ተማሪ ነበርኩኝ፡፡ ታዲያ የምሄደው ፊልም ለመከራየት ወይም ቤት ገብቼ ለማየት ነበር፡፡

7ኛ ክፍል ሁለተኛ ወጣሁ፡፡ ክረምት ገባ፡፡ እኔም ሙሉ ሀይሌን ተጠቅሜ ልቦለዴን ማንበቤን ቀጠልኩ፡፡ አሁንም የማነበው በብዛት የትርጉም መጽሐፍትን ነው፡፡ አሁንም ከቤተሰብ መምሪያ ላይብረሪ፡፡ እዚያ መጽሐፍት-ቤት ውስጥ የነበሩትን ልቦለዶች እያካለልኩ ነበር፡፡ መጽሐፍቶቹ አሁንም ይጣፍጣሉ፡፡ ግን አንዳንዴ አንድ መጽሐፍ አንብቤ ስጨርስ ጭንቅ ይለኛል፡፡ አንድ ቦታ ሳልንቀሳቀስ ረጅም ሰአት የምቆየው ነገር ሊሆን ይችላል፡፡ ከጨረስኩ በኋላ የሆነ ባዶነት ይወረኛል፡፡ አንድ ስርየት የለሽ ጸጸት የሚል ትልቅ መጽሐፍ አለ፡፡ ትርጉም ነው፡፡ በጣም ከተመቹኝ መጽሐፍት መሃል አንዱ ነው ግን መጽሐፉ ከውልደት ጀምሮ አርጅቶ እስከሞት ያለውን ታሪክ ነው በሚመስጥ መንገድ ክሽን አርጎ የሚያቀርበው፡፡ ታዲያ እንደዚህ የአንድ ሰው የ60ና 70 አመት ታሪክ በሁለት ወይም በሶስት ቀን አንብቤ ስጨርስ፣ እኔም እንደዚያው በ3 ቀን ፍጥነት አርጅቼ የምሞት ይመስለኛልና በጣም ነበር ውስጤ የሚታወከው፡፡
እንደ ድሮ ውጪ ውጪ ማለት ቀነስኩ፡፡ ቤት ተቀምጬ ማንበብ፣ ፊልም ካለ ማየት፡፡ ከወጣሁ መጽሐፍ ለመውሰድ ወይም ፊልም ለመከራየት፣ አንዳንዴ ደግሞ አሊ ጋር ለመሄድ፡፡ በዚያ ክረምት አሊ ዘመድ ጥየቃ ሀገሩ ሄዶ እኔ የምሄድበት ቦታ አጥቼ ማልቀሴ ትዝ ይለኛል፡፡ "በቃ እኔ ጓደኛ የለኝም ማለት ነው?" አልኩኝ፡፡ ደግነቱ መጽሐፍቶቼን ማንበብ ስጀምር ሀሳቤ ሁሉ ታሪኩ ይሆንና ወዲያው እረሳዋለሁ፡፡

የመለስ ደሞዝ 6400 እንደሆነ ሰማን፡፡ትንሽ ቆይቶ መለስ አንድ የኢኮኖሚ ፎረም ላይ ከጉባኤተኛው መሃል "Meles is a dictator" ብሎ መለስን በኦባማና በታላላቅ ሰዎች ፊት አንገቱን ሲያስደፋው በስልክ አየን፡፡ ይሄ የተቃዋሚዎች ነገር ግራ እየገባኝ ነበር፡፡

ያን ክረምት የአና ማስታወሻን አነበብኩኝ፡፡ በጣም ልብ የሚነካ ታሪክ ነበር፡፡ ከዚህ ስወጣ አምስተርዳም ውስጥ ያሉ ላይብረሪዎችን አካልላለሁ ትላለች፡፡ የአና ማስታወሻ መጽሐፍ ስለ አንደኛውና ሁለተኛው የአለም ጦርነቶች ብዙ የማወቅ ጉጉት ፈጠረብኝ፡፡ ስለጦርነቶቹ አነፍንፌ፣ ዘርግፌ ማንበብ አማረኝ፡፡ ያኔ የአና ህይወት እንዴት እንደ ነበረ እንዳወቅኩኝ የሌላውንም፣ ለማወቅ፣ አትሞስፌሩን ለመረዳት፡፡ ፖለቲካውን ምናምን፡፡

2004 ነሀሴ ገባ፡፡ ነሀሴ 1፣ 2፣ 3...10፣ 11፣ 12፣ 13....ነሀሴ 14 ጠዋት ወደ አንድ ሰአት ከእንቅልፌ ስነሳ እናቴ "መለስ ሞተ" አለችኝ፡፡ የቱ መለስ እንዳልል፣ ከመለስ ሌላ የማውቀው መለስ አልነበረም፡፡ ተመስገን በየነ ጠቅላይ ሚኒስትራችን ከምሽቱ (5፡40) ላይ ከዚህ አለም በሞት እንደተለዩ መርዶውን እያሰማ ነበር፡፡ ሳይታመም አልቀረም ሲባል ነበር፡፡ ከዚያ መዘዘኛ ፎረም በኋላ መለስ ከቲቪ ላይ ጠፍቶ፣ ሀይለማርያም ደሳለኝ ነበር ቴሌቪዥኑን የሞላው፡፡ ግን ሞቱ ዱብ እዳ ነበረ፡፡ ትንሽ ቆይቶ ለቁርስ ሂድና ዳቦ ግዛ ተባልኩኝ፡፡ ሱቅ እየሄድኩ መንገድ ላይ አንድ የሰፈር ልጅ ሲመጣብኝ "መለስ ሞተኮ" አልኩት፡፡ "ሂድ!" አለኝ፡፡ አላመነኝም ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ ለሁለት ሳምንት ኢቲቪ ሳያቋርጥ ስለ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ሲያወራ ሰነበተ፡፡ ሳሊዩት ሚስተር ፕራይሚኒስትር፡፡ ስወለድ ጀምሮ ያላወቅኩትን መሪ ሲሞት ተዋወቅኩት፡፡ የመለስን ታሪክ ጠጣን፡፡ ከትግል ጊዜ ጀምሮ ያደረጋቸው ንግግሮችና ቃለ-መጠይቆች፣ አንባቢነቱ፣ ኢህአዴግ፣ ያለ መለስ ምሶሶ የሌለው ጎጆ ቤት እንደ ሆነ ሰማሁ፡፡ ኢትዮጵያ ከዳር እስከ ዳር በእምባ ተራጨች፡፡ ኢትዮጵያ መለስን ብላ ሰላማዊ ሰልፍ ወጣች፡፡ አባይን የደፈረ ጀግና ተባለ፣ ጀግና አይሞትም አልን፡፡ በየቀበሌው ድንኳን ተተከለ፡፡ ያኔ ስለ 77 ድርቅ በእንግሊዘኛ ሲያወራ "This is the saddest time of my life..." ከታምራት ላይኔ ጋር መለስ ሰማያዊ ጃኬት ለብሶ አርሶ አደሮችን ሲያወያዩ፣ የሚገርሙ ትውስታዎች፡፡ የሰውዉ ለቅሶስ? አንዷ እስካሁን ትዝ ትለኛለች፣ ባይሞት ጥሩ ነበር እያለች ማውራት አቅቷት ስታለቅስ፡፡

ምነው ሞት ክፉ ተመኘ
ምነው ሞት ዛሬ ተሞኘ
ተተኪ እንዳለ ባወቀ
ሞት እንዲህ ባልተጨነቀ
ተተኪ እንዳለ ባወቀ
ሞት እንዲህ ባልተጨነቀ

ለኢትዮጵያችን ነጻነት
አፍላ እድሜውን የከፈለ
የድህነትን ፀር ትውልድ
ነበልባል ያቀጣጠለ
የሞተው በአካል እንጂ
መንፈሱ ከኛ አልተለየ

ከሁሉም ሰው የእምባ ጠብታ ውስጥ የሚንፀባረቅ ጥያቄ ነበረ፡፡ አሁን ማን ነው የሚመራን? ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ሐይለማርያም ደሳለኝ ቀጣዩ የኢትዮጵያ መሪ ሆነው ሲሾሙ ለመጀመሪያ ጊዜ በሀገሪቱ ታሪክ ስልጣን በሰላማዊ መንገድ ተሸጋገረ ተባለ፡፡

የጠቅላይ ሚኒስትሩን ሞት ተከትሎ ያን ሰሞን የነበረው የሚዲያ ድባብ ብዙ ኢትዮጵያውያን ወጣቶችና ህጻናት ላይ ተጽእኖ እንዳደረገ በርግጠኝነት መናገር እችላለሁ፡፡ የዚያ ሁሉ ህዝብ ለቅሶ፣ ንግግሮቹ፣ ድሎቹ... ያን ሰሞን ብዙ ህጻናት የወደፊት ምኞታቸውን ከዶክተርነት ወደ ጠቅላይሚኒስትርነት እንደቀየሩ መናገር ይቻላል፡፡ እንደኔ ፖለቲካን ድንቄም ያሉና እንደሚመለከታቸው የማያስቡ ታዳጊ ወጣቶች በፖለቲካ ተስበዋል፡፡ አዎ ስለ ፖለቲካ ማሰብ ጀመርኩ፡፡ ያኔ መለስ ከመሞቱ በፊት የሚገርም ንግግር እያደረገ ደንታ የማይሰጠኝ ሰውዬ ሐይለማርያም ደሳለኝን ማዳመጥ ጀመርኩ፡፡ የመለስ ንግግሮች አዝናኝነትና ምጡቅነት የታወቀኝ፣ ከሞተ በኋላ በቲቪ እንደዥረት ሲያንቆረቁት ነው፡፡ አንድ እሱ ከመሞቱ በፊት፣ ሲያወራ የሳበኝ ንግግር ቢኖር ፓርላማ ላይ ድንበር ሲጥስ ተይዞ በአሸባሪነት ስለተጠረጠረው ነጭ ጋዜጠኛ፣ ስልክ አናገረ እንጂ ምንም አላረገም ሲባል መለስ “በስልክ ምን ሲያወራ ነበር? ስለ አየር ሁኔታ?” ብሎ የሰጠው፣ “ገመድ ይዤ ነበር፣ ገመዱ ከምን ጋር ተያይዞ ነበር፣ ከፈረስ ጋር፣ ፈረሱ ምን ይዞ ነበር፣ ጋሪ፣ ጋሪው ምን ይዞ ነበር፣ ወርቅ” ምሳሌ ነበር፡፡ “ይሄ ጋዜጠኛ በሜክሲኮ አርጎ የአሜሪካን ድንበር ሲጥስ ቢያዝ የሚከራከርለት አንድ የጋዜጠኞች መብት ተሚጋች አለ? ሁሉም አላውቀውም ነው ሚለው፡፡” “የነጭ ደም ቀይ ነው፣ የጥቁርም ደም ቀይ ነው”፡፡ እኔ ደግሞ አስረኛ ክፍል ራሴን እንደ አዋቂ መቁጠር ስጀምር፣ የመለስን የዚያን ቀን የፓርላማ ንግግር አስታወስኩና “የነጭ ደም ቀይ ነው፣ የጥቁርም ደም ቀይ ነው...የእንስሳም ደም ቀይ ነው” አልኩኝ፡፡ በተረፈ በፊት በፊት ፖለቲካ የሆነ አሰልቺ ነገር ይመስለኝ ነበር፡፡

ከዚያ በኋላ እንዲህ ማሰብ ጀመርኩ፡፡ “አሁን የሚያዝናኑኝን የልቦለድ መጽሐፍቶች የቻልኩትን ያህል አነባለሁ፡፡ ከዚያ ከፍ ስል ደግሞ ትምህርት ያላቸውን የፖለቲካና የታሪክ መጽሐፍት አነባለሁ፡፡” አሁን የወጣትነትና ተዝናንቼ ማሳለፍ ያለብኝን ጊዜ ባግባቡ መጠቀም አለብኝ ብዬ ማሰቤ ነበር፡፡ በዚህን ጊዜ የቤት ልጅ በመሆን እየታወቅኩ ነበር፡፡ ቢሆንም ግን እኔ እኮራበት ነበር፡፡ ማንም የሚያናድደኝ የለም፣ የማይረባ ወሬ እያወራ የሚያሰለቸኝ የለም፣ አንዱ ከባህር ማዶ ቀምሞ አጣፍጦ ያቀረበልኝን ታሪክ ብቻ እንደ ጅረት ወደ አዕምሮዬ ማፍሰስ፡፡ እንዲዚያ ብዙ ልቦለዶችን ሳነብ አንድ ራሴን ደጋግሜ የምጠይቀው ጥያቄ፣ እነዚህን ሁሉ መጽሐፍት ሳነብ እየተማርኩ ያለሁት ነገር አለ ወይ? እሺ የማነበው የአማርኛ ልቦለድ ቢሆን፣ ፍልስፍናቸውንና አስተሳሰባቸውን በየመሃሉ ስለሚሰነቅሩበት ተማርኩ እላለሁ፡፡ ምሳሌ ፍቅር እስከ መቃብር ላይ ጉዱ ካሳ ከሚያወራቸው ነገሮች ትምህርት አገኘሁ ማለት ይቻላል፡፡ እኔ የማነባቸው ልቦለዶች ባብዛኛው ትርጉም ስለነበሩ እንዲህ አይነት ነገር የላቸውም፡፡ ስለዚህ መደምደሚያዬ፣ “መልዕክት የለም፣ መማር የለም፣ መዝናናት ብቻ” ነበር፡፡

የፍቅር እስከ መቃብር ደራሲን የሀዲስ አለማየሁን “የልምዣት”ን ሳነብ ስለዚያ ዘመን የማወቅ ጉጉት ፈጠረብኝ፡፡ የሀይለስላሴን ዘመን፡፡ የሃይስኩልተ ተማሪዎቹ ፓርቲ ምናምን ያዘጋጁ ነበር፡፡ “በርበሬ በርንስ ማይ ታንግ” እያሉ የ1960ዎቹ ልጆች እንደኛው ዘመን ይቀባጡ እንደነበረ ሳነብ ገረመኝ፡፡ ብቻ የድሮና ዘንድሮን ልዩነት የማወቅ ጉጉት አለብኝ፡፡ ድሮ ሲባል ጨለማ፣ ሁሉም ነገር እንደ ጥቁርና ነጭ ቲቪ ጨለማ ይመስለኝ ነበር፡፡ ይሄን መጽሐፍ ሳነብ ግን እውነታውና የምሰማው የተለያዩ መሰሉኝ፡፡
ግጥም ምንም ስሜት አይሰጠኝም ነበር፡፡ የበዕውቀቱ ስዩምን የግጥም ስብስብ የምትል ባለ ነጭ ሽፋን ትንሽ የግጥም መድብል ሳነብ ነው የግጥም ሀይልና መሳጭነት የታወቀኝ፡፡ በተለይ በቀጣዩ አመት የበዕውቀቱን መግባትና መውጣት የተሰኘ ልቦለድ ሳነብ፣ በፖለቲካ እንደ መለስ፣ በጥበብ እንደ በዕውቀቱ ስዩም ያለ፣ አረ ማናለ! ነበር ያልኩት፡፡

የሰንሻይን ት/ቤት ባለ ቤት የትምህርት ቤቱን አድራሻ ስትቀይር ሰንሻይን ገብተን የነበርን ብዙ ልጆች ወደ እንደሻው ስንመለስ እኔ በጣም ነበር ያሳፈረኝ፡፡ እሱ ግን ጥሩ አቀባበል ነበር ያደረገልን፡፡ “ልጆቼ ናቸው” ነበር ያለው፡፡
ከሁለት አመት በፊት አብረናቸው የተማርነው የእንደሻው ት/ቤት ተማሪዎች በተለይ ሴቶቹ በጣም አደጉ፡፡ እኔ ደግሞ “ናቲ ድምጹ ወፈረ” ተባለልኝ፡፡ በዚያ ላይ ቁመቴ በጣም እየጨመረ ነበረ፡፡
የ8ኛ ክፍል የአፋን ኦሮሞ አስተማሪያችን ቲቸር አለሚቱ ስም ጠሪያችን ሆነች፡፡ መጀመሪያ ስታወራልን በጣም ነበር የተመቸችኝ፡፡ የመማር ማስተማር ሂደቱ እንዴት እንደሚሆን፣ በትህትና ነበር የገለጸችልን፡፡ ለኔ ደግሞ ጥሩ አመለካከት ነበራት፡፡ ጎበዝ ነው፣ የሱራፌል ተፎካካሪ ነው ብለዋት ነው መሰለኝ፡፡ ከሰንሻይን አብሮኝ ት/ቤት ከቀየረው ከአሊ ጋርም ስናወራ እንደተመቸው ነግሮኝ ነበር፡፡ ከዚያ ቀን ቀንን እየተካ ሲሄድ ምርጥ አስተማሪ ያልኳት ሴትዮ በህይወቴ አይቼ የማላውቀው አይነት ደባሪ አስተማሪ ሆና አረፈችው፡፡ ለካስ በቀድሞ አመታት ያስተማረቻቸው የክፍላችን ልጆች ሲነግሩን፣ ወንዶቹን ስሊፐር ለምን አርጋችሁ መጣችሁ ብላ ትገርፋቸዋለች፡፡ ለካስ መጽሐፍን በገጽ ሽፋኑ አትገምት የሚሉት አባባል፣ ለሰውም ይሰራል፡፡ ሰውን በመግቢያ ንግግሩ አትገምተው፡፡
ሰንሻይን ሳደርጋቸው የነበሩትን ነገሮች እንደሻው ት/ቤት ድሮ አብረውን ሲማሩ የነበሩትና ከሁለት አመት በኋላ ሲነግሩኝ፣ ያ ያልጠበቅኩት ነገር ነበር፡፡ አንባቢነቴ፣ ክፍል ውስጥ አስተማሪ እያስተማረ እንደማነብ ምናምን ሲነግሩኝ ይገርመኝ ነበር፡፡ ገነትን ያደማኋትን እንደ ሰሙ ሲነግሩኝ አድናቆት ይነበብባቸው ነበር፡፡ ባለፉት አመታት ስለኔ ብዙ ያወሩ ነበር ማለት ነው፡፡

ክረምት ወደ መጨረሻ እኔና አሊ ከመምሪያ መፅሐፍ እንደተዋስን በጣም አቆየን፡፡ ወደ ሁለት ወር፡፡ እኔ በሁለት ወሬ ስመልስ ላይብራርያኑ ተናድዶ ነበር፡፡ ለምኜውና ሁለተኛ እንደማይደገመኝ ቃል ገብቼ 8ኛ ክፍል ስማር እንደገና መፅሐፍ መዋሴንና ንባቤን ቀጠልኩ፡፡ አሊ መሄድ ሰለፈራ በጣም ያቆየውን መፅሐፍ እኔ መለስኩለት፡፡ ቤተሰብ መምሪያ ላይብራሪ ውስጥ የነበሩ ልቦለድ መፅሐፍትን አንብቤ ጨርሼ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ የሳይኮሎጂ መፅሐፍት ነበሩ፣ ቺክ መጥበሻ መንገዶችን የሚዘረዝሩና ምክር የሚለግሱ፣ ልጅን በምን አይነት ሁኔታ ማሳደግ እንዳለብን፣ ሀብታም እንዴት እንደሚኮን የሚያስረዱ፣ ስለ ጊዜ አጠቃቀም ወዘተ፡፡ እንደነዚህ አይነት መፅሐፎችን አለመውደድ ብቻ ሳይሆን እፈራቸው ነበር፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ በጣም የማሰብ፣ በተለይ የሰዎችን ሳይኮሎጂ፣ መመርመር፣ ምን ማለት ፈልጎ ነው? ለምን? ማለት እያበዛሁ ስለመጣሁ “እንኳንስ ዘንቦብኝ ድሮውንም ጤዛ ነኝ” ብዬ እንዲህ አይነት መፅሐፍት፣ ያንን ችግር ያባብሱብኛል እያልኩ እፈራ ነበር፡፡ በሌላ በኩል እንዲህ አይነት መፅሐፍትን በጣም እንቅ ነበር፡፡ ከንደነዚህ አይነት መፅሐፍት አዲስ ነገር የማገኝ አይመስለኝም ነበር፡፡ ለምሳሌ ስላጠባበስ የሚያወራ መፅሐፍ ሳይ፣ ሴቶች ሀብታም፣ ኩሩ፣ ዘናጭ አለ አይደል የሚፈልጉት አይነት ወንድ የታወቀ ነው፤ ወንዱም ቆንጆ ሴት...፣ የሚፈልጋት አይነት ሴት ትታወቃለች፡፡ ሌላው ደግሞ ሁሉም ሰው ተመሳሳይ አይደለም፣ አንዱ ቁጡ ከሆነ ሌላው ተጫዋች ነው፣

አንዷ የምትጠላውን ሌላዋ ልትወድ ትችላለች፣ እንደዚህ አይነት መፅሐፍት ምንም አይጠቅሙም ብዬ ስለማስብ የሚያነቡትን እንደሞኝ ነበር የምቆጥረው፡፡ ፊልም ላይ እንኳን ያነበበውን፣ ሴቶች ላይ ለመተግበር እንደሚሞክረው አይነቶቹን ማለት ነው፡፡ በተለይ መምሪያ ልጅ ማሳደግ ምናምን የሚል መፅሐፍ አይቼ በጣም ነበር የገረመኝ፣ ልጄን እንዴት ማሳደግ እንዳለብኝ ለማወቅ መፅሐፍ ሳነብ ታይቶኝ፡፡ መፅሐፍ ማንበቤን ቀጠልኩ፡፡ በተለይ ሚኒስትሪ ተፈታኝ ስለነበርኩ ከቤት እንዳላነብ አስጠንቅቀውኝ ነበር፡፡ ስለዚህ እንዳልያዝ በጣም መጠንቀቅ ነበረብኝ፡፡ በብዛት የማነብበው ክፍል ውስጥ መምህር እያስተማረ ነበር፡፡

ላይብራሪው ጥቂት አዳዲስ መፅሐፍት ገብተው ነበር፡፡ ዴርቶጋዳ ቀጣይ ክፍል እንዳለው ከሰማሁ ጀምሮ ስፈልገው የነበረውን፣ ዣንቶዣራን አገኘዋለሁ ብዬ ግን አልጠበቅኩም ነበር፡፡ ከሱ በፊት ራማቶሐራ ነበረ፡፡ ታድያ ራማቶሐራን እስካገኝ ብዬ ልተወው? ተሽቀዳድሜ አነበብኩት፡፡ ሜሮዳ እጇ በምን ምክንያት እንደተቆረጠ አላወቅኩም፡፡ ዣንቶዣራም በሚገርም የአፃፃፍ ስልት የተፃፈ መሆኑ የደራሲው የፅሁፍ ጥበብ የማይዋዥቅ እንደሆነ ያስተዋልኩበት ነበር፡፡ የፃፋቸውን መፅሃፍት ሁሉ አግኝቼ ለማንበብ ተመኘሁ፡፡ በርግጥ ተልሚድን ባለፈው የ2003 ክረምት አንብቤው ነበር፡፡ ከሱ ላይ ነው ይስማዕከ ብዙ መፅሐፍት እንደፃፈ ያየሁት፡፡

ደራሲው ይስማዕከ ወርቁ አንዳንዶች አሜሪካ ሜዲካል ሳይንስ እያጠና ነው ይላሉ፡፡ አንዳንዶች እንደዚህ የሚባል ሰው የለም በአሉ ግርማ ነው ገዳም ተደብቆ በብዕር ስም እየፃፈልን ያለው ይላሉ፡፡ በአሉ አልሞተም በህይወት አለ ሲባል አልነበር? ብዙ ብሰማም ያለፈው አመት 2008 ፌስቡክ ላይ ይስማዕከ ወርቁ ከሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ማስተርሱን ተቀበለ የሚል መረጃ በፎቶ ተደግፎ አየሁ፡፡ መልኩን ስለማላውቅ እሱ መሆኑን ማረጋገጥ አልቻልኩም፡፡ ዊኪፒዲያ ደግሞ ስለሱ ጽፎ፣ ስለሱ ማረጋገጥ አልተቻለም፣ በሚል አጥፍቶታል፡፡ ይስማዕከ ወርቁ የመጀመሪያው ዊኪፒዲያ ላይ የታተመ ኢትዮጵያዊ ደራሲ ይመስለኛል፡፡

ሰውየው ዴርቶጋዳ ላይ ስለመለስ ጥቂት፣ በጣም ጥቂት ፅፏል፡፡ ዣንቶዣራ ላይ ግን መፃፍ ሳይሆን ስለመለስ ከበድ ያለ ጉዳይ ነበር ያነሳው፡፡ መለስ ሰይጣንን ከሚያመልኩ ምስጢራዊ ማህበራት ጋር ግንኙነት እንዳለውና አባላቸውም እንደሆነ ብቻ ሳይሆን ባንዲራችን ላይ ያለው የብሄር ብሄረሰቦችን እኩልነትና ትስስር የሚያሳየው ኮከብ የነሱ ነው፣ ምስጢራዊ ተልዕኮ አለው ይላል፡፡ ያ የፌዴራል መንግስታችን አርማ የሆነው ኮከብ እራሱ፣ ፍየልም ሰይጣንም የሚመስል ቀንዳም አውሬ ግንባር ላይ ተስሎ እንዳለና የዚህ ሁሉ የባንዲራ አርማ ትርጉም ዝባዝኪ ጠንሳሽ መለስ እንደ ሆነ በምስል በማስደገፍ ያሳያልና መለስ በምስጢር ኢትዮጵያን ለኢሉሚናቲ ስርአት እያበጃጀ እንደሆነ የኢትዮጵያን ህዝብ ሊያስረዳ ይሞክራል፡፡ የማህበሩ አመሰራረት፣ በአለም ላይ ያለው ተፅእኖ፣ አሁን ስላለበት ሁኔታ መፅሐፉ ላይ ተቀምጦ ነበር፡፡ ኢሉሚናቲ(Illuminati) የሚለውን ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ የሰማሁበት አጋጣሚ፡፡ እንዲህ አይነት ተረት ተረት የሚመስል ወሬ የሚሰማ ጆሮ አልነበረኝም፡፡ እንዲያውም ስለ ኢሉሚናቲ የተፃፈውን ክፍል ትንሽ አንብቤ አልጥም ብሎኝ ቀጣዩን ታሪክ ሳፈላልግ የመለስን ስም አይቼ ነው፣ መለስ ከማህበሩ ጋር ያለውን ግንኙነት ለማወቅ እንደገና ከመጀመሪያው ስለማህበሩ የተፃፈውን ያነበብኩት፡፡

አንድ ያነበብኩት እውነተኛ ታሪክ ትዝ ይለኛል፡፡ የማይደርቅ ቁስል ነው ርዕሱ? ስላንዲት ህፃናት አምባ ውስጥ ትኖር የነበረች ወላጅ አልባ ልጅ የህይወት ውጣ ውረድ ነበር መፅሐፉ፡፡ በደርግ ዘመን የነበሩ ህፃናት እንደኛው ናቸው ማለት ነው? ስለ ደርግ ስወለድ ጀምሮ መጥፎ ነገሮችን እየሰማሁ ነው ያደግኩት፡፡ ባለ ታሪኳ መንግስቱ ሐ/ማርያምን እንደምትወደውና አዲሱ መንግስት ምን እንዳደረጋቸው ስትናገር በጣም ነበር የተወዛገብኩት፡፡ መንግስቱ ጥሩ፣ እህአዲግ መጥፎ? ኢህአዴጎች ያኔ ገና ስላልተደራጁ ነው ብዬ አሰብኩ፡፡ ግን የምሰማው ስለደርግ የሚወራው ምን ያህል እውነት እንደሆነ ማወቅ ፈለግኩ፡፡ ስለ ድሮ፣ ስለ ታሪክ፣ ስለ ቀይ ሽብር፣ ያ ወጣት በትልቅ ወረቀት ለምን ቀይ ሽብር ተብሎ ተጠቅልሎበት እንደ ነበረ...

ፌስቡክ፣ ትላልቅ ሰዎች የሚከፍቱት፣ የሆነ ከባድ ነገር ይመስለን ነበር፡፡ ስምንተኛ ክፍል ስገባ ልጆች ፌስቡክ መክፈት ጀመሩ፡፡ ሲያወሩ እንዴት እንደሚያስቀና? “ፎቶ ትለቅና፣ ከፈረንጅ ጋር ምናምን ማውራት ራሱ ትችላለህ፣ ኮሜንት ታረጋለህ፣ እንዲህ እንዲህ አረግኩ ሲሉ ጉጉቱ ጉጉት እንዳይመስልህ፡፡ ይህቺን ይወዳል! እኔ ላልከፍት? እንዴት እንደሚከፈት ስጠይቃቸው ተወሳሰበብኝ፡፡ ያኔ ስልክ የነበረውም አልነበረም፤ ስልክ ይዞ ት/ቤት መሄድም አይቻልም ነበር፡፡ ጉጉቴን ውጬ ስቀመጥ ወንድሜ ለሴሚስቴር እረፍት መጣ፡፡አንደኛ አመት ዩኒቨርሲቲ ተማሪ ነበረ፡፡ ፌስቡክ ከከፈተ ካንድ አመት በላይ ነበረና እንዴት እንደሚከፈት ጠየቅኩት፡፡ ቀላል ነው አለኝና ቅደም ተከተሉን ነገረኝ፡፡ ወንድሜ ቀላል ነው ካለ ቀላል ነው፡፡ ግን አልገርምም? ክፈትልኝ አልለውም? አይሆንም አርፈህ ትምህርትህን ተማር የሚለኝ መስሎኝ ነበር፡፡ እንዴት እንደሚከፈት ጠየቅኩት ማለትኮ ፌስቡክ ለመክፈት እፈልጋለሁ ማለት ነው አይደል እንዴ?
ፌስቡክ ለመክፈት ያስቸገረኝ አንድ ነገር ነበር፡፡ ያው ስልክ አልነበረኝም፣ በዛ ላይ አባቴ ስልኩን ሰው አያስነካም፡፡ ታበላሹብኛላቹ ይላል፡፡ የማዘር ስልክ ኖኪያ ኮንጎ ነበረች፡፡ የነበረኝ አማራጭ፣ ፋዘር ስልኩን ትቶ በወጣበት፣ ስልኩና እሱ በተለያዩበት አጋጣሚ መጠቀም ነበረ፡፡ ሞክሬ ሞክሬ፣ ስሜን ፅፌ፣ ፎርሞቹን ሞልቼ ምናምን የሆነ ነገር ላይ ደርሼ አባቴ ሲመጣ ቀይዋን ነክቼ እዘጋዋለሁ፡፡ አንዳንዴ ኮኔክሽን እምቢ ይላል፡፡ ሎዲንግ እያለ ደቂቃ ሲቆይ አንድ ሰአት ይመስልሀል፡፡ አባቴና NOKIA xpress music ስልኩ በተለያዩበት አጋጣሚ ኮኔክሽን ፈልድ መባል፣ በጣም ያበሽቃል፡፡ በመከራ፣ ከብዙ ሳምንታት ጥረት በኋላ የፌስቡክ ባለቤት ሆንኩኝ፡፡
ፌስቡክ ት/ቤታችን በፍጥነት ነበር የተሰራጨው፡፡ አድ ተደራረግን ምናምን፡፡ አንዲት በዚያው አመት የኛ ባች የነበረችና ቢ ክፍል ስትማር የነበረች ልጅ ነበረች፡፡ ሁለት ነው ሶስት ወር ከኛ ጋር ተምራ አባቷ ጋር አሜሪካ ሄደች፡፡ በቃ ከሷ ጋር ማውራት ብርቃችን ነበር፡፡ ጠብሰናት አሜሪካ እንደምታስገባን ነገር፡፡

ቸርች መሄድ፣ አንዳንዴ ከቤት እንዳይቆጡኝ፣ አንዳንዴ ከቤት ሲቆጡኝ፣ አንዳንዴ ሁለት ሳምንት ምናምን ሳልሄድ ስቆይ ዛሬማ መሄድ አለብኝ እያልኩ ነበር የምሄደው፡፡ ስምንተኛ ክፍል ስገባ አንድ አመት ከኔ ጋር ከነበሩት ወደኋላ ቀርቼ ትምህርት ጀመርኩ፡፡ የደህንነት ትምህርት፡፡ ትምህርቱ እሁድ ከሰዓት 8 ሰዓት ላይ ነበረ፡፡ ሁሌ ተቀምጬ እሁድ መዝናኛን የማይበት ጊዜ ነበር፡፡ ብዙ ጊዜ እሁድ ከሰዓት ሰው ቤት አይኖርም፡፡ አባቴና እናቴ ሰው ለመጠየቅ፣ ሠርግ፣ ለቅሶ፣ ምናምን ይሄዳሉ፡፡ ወንድሜ፣ ወይ ቸረች ፕሮግራም ይኖረዋል፣ ወይ ከጓደኞቹ ጋር ይወጣል፣ ቤት መቀመጥ አይሆነለትም፡፡ ሚጣ ወይ ከኔ ጋር ተቀምጣ ቲቪ ታያለች ወይ ጎረቤት ቤት ነች፡፡ በፊት ላይ ቤት የነበርን ጊዜ ከነሳሚ ጋር ነበር የምውለውና ዝንቅና ድራማ ሲደረሱ ብቻ ነበር እሁድ መዝናኛን የምናየው፡፡
በዕሁድ፣ በጠራራ ፀሀይ መንገላታት ይከብድ ነበር፡፡ የደህንነት ትምህርት ጀምሬ ትንሽ እንደ ቆየሁ በቤታችን በስተጀርባ ጎረቤቴ የሆነው ዳግም ከኔ ጋር መማር ጀመረ፡፡ 11ኛ ክፍል ነበር የሚማረው፡፡ ተመቸኝ፣ ተጠራርተን ነበር የምንሄደው፡፡ እሱ ከዚህ በፊት ጀምሮ ነበር ትምህርቱን ያቋረጠው፡፡ ከዳግም ጋር ተመቻቸን፡፡ ስለ ትምህርት ቤት ገጠመኞቻችን፣ እየተነጋገርን ምናምን በቃ እየተሳሳቅን ሄደን እየተሳሳቅን ነበር የምንገባው፡፡
እሁድ ከሰዓት ለመማር ስሄድ ጎረቤቴ የነበሩትን የጎረቤቴን ልጆች እንዲማሩ እመክራቸው ነበር፡፡ እነሱ ግን አይሰሙኝም ነበር፡፡

የትምህርት ቤት ጓደኞቼን እንቃቸው ነበር፡፡ የሚያወሩትን የማያውቁ፣ ህጻናት ነገር ይመስሉኝ ነበር፡፡ ትምህርት ቤትም ሰፈርም ጓደኞቼ የነበሩት አሊና አቡሽን ጨምሮ፡፡ አልፎ አልፎ አንዳንድ አሪፍ ሴቶች ነበሩ፡፡ ከነአሊ ጋር 8ኛ ክፍል ጥሩ ጊዜ ብናሳልፍም በቃ የሚያወሩት ነገር ምናምን ያናድድ ነበር፡፡ በውስጤ ፋራ እላቸው ነበር፡፡ በርግጥ ያኔ አራድነትና ፋራነት የሚመዘነው በምትናገረው ነገር ነው የሚል መደምደሚያ ላይ ደርሼ ነበር፡፡ አንድ ጊዜ ብቻ ያወራሁትን ሰው ከሚናገረው ነገር ተነስቼ አራዳ ወይም ፋራ ብዬ እፈርጅ ነበርና ፍረጃዬ ባብዛኛው ትክክል ነበር፡፡ ማለት የሰውን ስሜት እያገናዘበ፣ የሚያወራ፣ ወሬ የሚያውቅ፣ ቀልድ የሚያውቅ፣ ስድብ እንኳን የሚያወቅ ሰው አራዳ ነው ለኔ፡፡ ደግሞ የሚያወራውን የማያውቅ፣ ዝም ብሎ የሚራገጥ፣ ማለት ሰው የሚያስቀይም አይነት ሰው ደግሞ ፋራ ነው፡፡ ቤት፣ እኔ ጓደኞቼ እንደማይመቹኝ ስነግራቸው "ጓደኞችህኮ ሲጀመር በሁሉም ነገር ሊመቹህ አይችሉም፡፡ አንተ ፐርፌክት ጓደኛ ስለምትፈልግ አንተን የሚመች ጓደኛ ለማግኘት አንተው ራስህ ኮፒ መደረግ አለብህ ማለት ነው፡፡ እንጂ ጓደኛ በሁሉም ነገር እንዲመች አይጠበቅም፣ ትዕግስት ይኑርህ፣ በትንሽ ነገር አትናደድ፣ እኛ ስለሚመቹን ይመስልሃል ከዚህ ሁሉ ሰው ጋር ተመቻችተን የምንኖረው? ስለምንታገስ ነው" ይሉኛል፡፡ እኔ ግን እንደዚያ እንደኔ አይነት ሰው መፈለጌ አልነበረም፡፡ በቃ ከነአሊ የሚሻሉ ልጆች እንዳሉ አምን ነበር፡፡ ከቤት እንደዚያ ስባል ግን በቃ እኔ የምፈልገው ጓደኛ ምናባዊ እንደሆነ እያመንኩ መጣሁ፡፡ እውነት ነው እኔ የምፈልገው፣ ዝም ብሎ እንደመጣበት የማያወራ፣ ሀሳቤን የሚረዳ፣ ሊያናድደኝ የማይፈልግ፣ እኔም የምረዳው አይነት ነበር፡፡ ከነአሊና ከነአቡሽ በጣም የተለየ፡፡

የቸርች ጓደኛዬ ዳግም፣ ከጓደኞቼ ጋር ጥሩ ጊዜ ባሳልፍም እንደሚያናድዱኝ ስነግረው "እኔ ከጓደኛዬ ጋር እንገናኛለን፣ ስናወራ እንውላለን፣ እንበሻሸቃለን፣ ደስ ይለኛል፣ ግን እንዲህ ስለዛ አስቤበት ምናምን አላውቅም" አለኝ፡፡ እኔ ግን ቆይ ከጊዜ ወደ ጊዜ ለምንድነው ሌሎች የማያስቧቸውን ነገሮች እያሰብኩ የመጣሁት? አንዳንዴ ሁሉም የሚያስባቸው የሚመስለኝን ነገር አስቤ አላቅም ሲሉኝ እደነግጣለሁ፡፡ ለምን እኔ ብቻ? አንዳንዴ ደግሞ እንዲሁ ለምንድነው ስለዚህ ነገር እያሰብኩ የምውለው እልና ራሴው በራሴው እናደዳለሁ፡፡
ወንድሜ ስለ አንድ ጉዳይ በጣም ታሰላስላለህ፣ ተው ብሎኝ ያውቃል፡፡ አዎ ስለ ሆነ ጉዳይ በጣም ሳስብ እውላለሁ፡፡

ት/ቤት ክፍል ውስጥ ከድሮ ጀምሮ የሆነ ነገር ሳብራራ፣ መልስ ስመልስ ምናምን ቀኝ እጄን ከልቤ እኩል አርጌ ሀሳቡን ከልቤ ውስጥ የማፈልቅ ይመስል እጄን ወደ ላይ ወደ ታች የማረገው ነገር አለኝ፡፡ ክፍል ውስጥ ሁሌ ልጆች እንደሳቁብኝ ነው፡፡ ሀሳቤን መግለፅ በጣም እቸገር ነበርና ከማውራት መፃፍ ይቀልለኝ ነበር፡፡ 8ኛ ክፍል 1ኛ ሴሚስቴር ማስታወሻ(Diary) መፃፍ ጀመርኩ፡፡ ስለ ዕለት ውሎዬ፣ ስለ ትምህርት ቤት፣ ስለ ቤት፣ ብቻ ስለ ሁሉም ነገር፡፡ ደራሲ መሆን እንደምችል እንዳስብ ያደረገኝ አጋጣሚ፡፡ የፃፍኩትን ሳነብ በጣም ይመቸኝ ጀመር፡፡ እየደበረኝ ኡ ዛሬ የፃፍኩት ከአቋም በታች ነው እያልኩ የፃፍኩትን እንኳን ሌላ ጊዜ ሳነበው፣ ስጽፈው የነበረኝ ስሜት መስጦኝ ሊሆን ይችላል፣ በፅሁፉ ተመስጬ ለምንድነው እንደዛ ካቋም በታች ያልኩት? ብዬ ራሴን አገኘዋለሁ፡፡ ሳድግ ያው ዶክተር እሆናለሁ፣ ከዛ ቀን ሰው ሳክም ውዬ ማታ ቤቴ ተቀምጬ ድርሰት ስፅፍ ይታየኝ ነበር፡፡
ዳያሪ የመፃፍ ሀሳቡ የአና ማስተወሻን ከማንበብ የመጣ ነው፡፡ የአና ማስታወሻን ባላነብ ወይም The Vampire Diariesን ባላይ ማስታወሻ ስለ መፃፍ የማስብበትም ሆነ የማልምበት አንድም አጋጣሚ አይኖርም ነበር፡፡
ዳያሪውን ሶስት አራት ወር እንደፃፍኩ አቃጠልኩት፡፡ ምክንያቴ፣ ወንድሜ ለሴሚስቴር እረፍት ሲመጣ ሊያየውና ሊያነብብኝ ይችላል የሚል ነበረ፡፡ በህይወቴ ከምቆጭባቸው ነገሮች አንዱ ነው ያ ስህተት፡፡ ግን ከምር ወንድሜ እንዳያገኘው አርጌ መደበቅ አቅቶኝ ነው? ያኔ ዳያሪ መፃፍ መጀመሬ ይሄን መፅሐፍ ከታሪኬ ጋር አያይዤ ለማቅረቤ ዋነኛ ምክንያት ነው፡፡

እኔና ቲቸር አለሚቱ እንደ ልጅና የንጀራናት ነበር የሆንነው፡፡ ማስተማር አትችልም ተማሪ በማሰቃየት ደግሞ የሚያክላት የለም፡፡ እንደሻው ት/ቤት ተማሪ መግረፍ በጣም የሚበረታታ የአስተማሪዎች ስራ ነው፡፡ ተማሪን እንደ ፈለጉ መምታት ባህል እንዲሆን ያደረገው እንደሻው ራሱ ነው፡፡ አንድ አዲስ አስተማሪ ትንሽ በፀባይ ያስተምርና ከሁለት ቀን በኋላ አካባቢውን ሲቃኝና ተማሪዎቹን እንደፈለገ የመቅጣት መብት እንዳለው ሲረዳ መንጌን ይሆናል፡፡ ተማሪዎቹን ማሸማቀቅ፣ ያለ በቂ ምክንያት ከባድ ግርፊያዎችን ማካሄድ ይጀምራል፡፡ እኔ በበኩሌ ብዙ መምህራን ተማሪ መቅጣትና መምታት ሱስ ሲሆንባቸው አስተውያለሁ፡፡ ሰው እድሉና መብቱ ከተሰጠው ሱስ የማይሆንበት ነገር የለም፡፡ ጭራቅነትም ቢሆን፡፡ የአለሚቱ፣ ሱሷ፣ ማለትም ያለበቂ ምክንያት የምትቀጣን ነገር አልነበረም ያስገረመኝ፣ ያ በንደሻው ቤት ያደግኩበት

ነው፡፡ ተማሪውን እጁ ላይ በእንጨት ገርፋ ተነስታ ተማሪው አሞት እጁን ሲያውለበልብና የጩኸት ድምፅ ሲያሰማ ትስቅበታለች፡፡ መጀመሪያ ጊዜ እንደዛ ስታረግ ሳያት በጣም ነበር የተበሳጨሁት፡፡ ተማሪ የሚቀጣው ከስህተቱ ተምሮ እንዲመለስ ነው አይደል? እኔ እስከ ማውቀው ድረስ ሰው ሰውን የሚቀጣው በተሰራው ስህተት ሲናደድ ነው፡፡ እሺ ንዴት ይቅር፣ ንዴት ለወላጆች ይሁን፡፡ ቀጥቶ ሳቅ? ባብዛኛው የእንደሻው ት/ቤት አስተማሪዎች መብታቸውን ለመጠቀም እንደሚጋረፉ አውቃለሁ፡፡ መጋረፉ እንደሚያዝናናቸው እገምታለሁ፡፡ ተማሪን መትቶ አሰቃይቶ ሲያለቅስ መሳቅ ግን ከፎርሙላው ውጪና የሚያስደነግጥ ነገር ነው፡፡

እንደሻው ት/ቤት ህጉ ጥብቅ ነው፡፡ በሁሉም ዘርፍ፡፡ መገረፍ፣ መገረፍ፣ መገረፍ፣ ነው፡፡ በተለይ እኛ ደግሞ ሚኒስተሪ ተፈታኝ ስለነበርን ልዩ ቁጥጥር ነበር የሚደረግብን፡፡ ከትምህርት በኋላ እስከ 11 ተኩል ድረስ በግድ በቡድን እንድናጠና ይደረጋል፡፡ አንዳችን ካንዳችን ክፍል ውስጥ እንዳንገለባበጥ አሳይመንት በጠዋት ከአንደኛ ፕሬድ በፊት ነው ስም ጠሪያችን መጥታ የምትሰበስበው፡፡ ሁሉም አይኖች እኛ ላይ ነበሩ፡፡ ይሄማ ትምህርት ቤት ሳይሆን እስር ቤት ነው እንል ነበር፡፡ ት/ቤት ሳይሆን እ/ቤት፡፡
ተማሪ ቅሬታዎቹን በሚያሰማበት የክፍል ስብሰባ ላይ፣ ሰብሳቢያችን ስም ጠሪያችን፣ ቲቸር አለሚቱ ነበረችና እጄን ሳወጣ እድል ሰጠችኝ፡፡ “ሰው ሰውን የሚቀጣው ለማስተማር ነው…” ብዬ ማውራት ሳልጀምር ተቀመጥ አለችኝ፡፡ ተናደድኩኝና ተቀመጥኩኝ፡፡ የሆነች ልጅ ራሷን ሰብሳቢያችንን ቲቸር አለሚቱን ተችታ ስትቀመጥ ብቻዬን አጨበጨብኩላት፡፡ ተማሪዎች ሳቁ፡፡ ለምን ብቻህን አጨበጨብክ አትለኝ ነገር ተናድዳ ዝም አለች፡፡ ሰው አውርቶ ሳይጨርስ ጣልቃ እየገባች የሰው ሀሳብ ትበትናለች፡፡ ለምሳሌ ስለ አንድ አስተማሪ ተማሪው ቅሬታ ሲያቀርብ ቅሬታውን መጻፍ ትታ እሱኮ እንዲህ እንዲህ አስቦ ይሆናል ምናምን እያለች ትከራከርለታለች ፡፡ ትንሽ ቆይቼ እንደገና እጄን አወጣሁ፡፡ የምትሰጠኝ አልመሰለኝም ነበር እድሉን ሰጠችኝ፡፡ “መጀመሪያ ነገር ሳወራ ጣልቃ እየገቡ አይረብሹኝ” ስል ተማሪው በሳቅና በጩኸት ክፍሉን አነቃነቀው፡፡ ሁለተኛ ነገር ሰው ሰውን የሚቀጣው ለማስተማር ነው፣ እንዴት ተማሪን ገርፈው ተነስተው ይስቁበታል ብዬ ትንሽ አውርቼ ተቀመጥኩ፡፡ አለሚቱ በሸቀች፡፡
ከስብሰባው ስንወጣ ልጆች ድፍረቴ ገርሟቸው አዳነቁኝ፡፡ ጓደኛዬ አሊ የነፃነት ታጋያችን እየመሰልከኝ ነው ሊለኝ ምንም አላቅማም ነበር፡፡ አንድ ቀን ስምንተኛ ክፍል ስማር እንደዛ መባሌን እንደማልረሳ አውቄው ነበር፡፡

ሙባረክ ከሚባለው የክፍል ጓደኛዬ ጋር ድሮ እኛ ትምህርት ቤት ሲማሩ ስለ ነበሩ፣ ያኔ ሃይስኩል ገብተው የሲጋራ፣ የጫት ሱሰኛ ስለሚሆኑ ልጆች ስናወራ “እኔም ሃይስኩል ስገባ እንደነሱ እንዳልሆን፣ እፈራለሁ፣ እነሱምኮ 8ኛ ክፍል ሲማሩ ይኸኔ እንዲህ አይነት ነገር በጣም ነበር የሚጸየፉት፡፡” ስለው፣ “እኔም” አለኝ፡፡

መጀመሪያ አካባቢ እኔ፣ አሊና አቡሽ ከት/ቤት ስንገባ እነአሊ ቤት የዘይቱና ዛፍ ላይ ወጥተን የትምህርት ቤት ወሬ ስንከካ እንውላለን፡፡ ወይ ያ ጊዜ፡፡ በጣም ደስ ይል ነበር፡፡ አብረን የምንቆየው 2 ሰዓት አይሆንም ግን በቃ ደስ የምትል ጊዜ ነበረች፡፡ ስለ ክፍላችን ሴቶች ነበር የምናወራው፡፡ አቡሽ እኔ እንዲህ አይነት ነገር አላውቅም ስለሚል አያወራም፡፡ እኛ ስናወራ የነበረው ተመስጦ ግን አፍሮ እንደሆነ ያሳብቅበታል፡፡

ሰፈር አቡሽ ኳስ ይጫወት ነበርና እሱ የሚጫወትበት እንድመጣ ነገረኝ፡፡ ሄድኩኝ፡፡ ብዙ የሰፈር ልጆች ነበሩ፡፡ ዳግምም ነበረ፡፡ ከሰፈሬ ልጆች ጋር 8ኛ ክፍል ላይ ጥሩ ግንኙነት መመስረት ቻልኩኝ፡፡ በብዛት ከኔ በላይ ነበሩ፡፡ ፋኑኤል የሚባል ልጅ ነበረ፡፡ ከሱ ጋር፣ ከነባቢ ጋር፣ ከነዳግም፣ አዩቲ፣ ናኤል፣ ጋር ምናምን የቄራ ት/ቤት ግቢ ውስጥ ማሳለፍ ጀመርኩ፡፡ ተመቸኝ፡፡ እኔ በጣም ለመሳቅ ቅርብ የሆንኩ ሰው ነኝና ዳግም በተለይ የት/ቤት ገጠመኞቹን ሲነግረኝ በጣም ነበር የምስቀው፡፡ አንዳንዴ እሱ ነግሮኝ ስቄ ላላባራ ስል ሳቄ የውሸት የሆነ፣ ደስ እንዲለው የምስቅ፣ እየመሰለው ግር ይለዋል፡፡ “ይሄን ያህል ያስቃል እንዴ?” አይነት፡፡ እኔ ግን ብዙ የማያስቅ ነገር የሚያንከተክተኝ ሰው ነኝ፡፡ አንድ ቀን እነዳግም 11ኛ ክፍል ሲማሩ ነው አንዱ መምህር እያስተማረ፣ የዳግም ወንድም ደግሞ ክላስ ውስጥ ተኝቷል፡፡ መምህሩ ይመጣና “ቀስቅሶት ምን እየሰራህ ነው?” ይለዋል፡፡ “እየተኛሁ” ሲለው አስተማሪው እንዴት እንዲህ ትለኛለህ? ንቀት ነው ብሎ ተማሪውን ቢሮ ይከሰዋል ይባላል፡፡ አያስቅም ታድያ?(ተማሪው አስተማሪውን ይቅርታ እንዲጠይቅ ተደረገ፣ ሌላ ቅጣት አልተቀጣም) ያው ሰው ሲስቅልን ቀልድ ተናግረን ሳይሳቅ ሲቀር የሚከፋንን ያህል ደስ ይለን የለ? ዳግም አንዳንዴ እነግረዋለሁ ብሎ አስቦበት የሚያስቅ ነገር ሲነግረኝ በቃ ከዚህ ልጅ ጋር ጓደኛ ሆንኩ ማለት ነው? እል ነበር፡፡

9ኛ ክፍል ስገባ ከክፍሌ ልጆች ጋር የመግባት ፍላጎት አልነበረኝም፡፡ የB ክፍል ልጆች ከድሮው ይመቹኝ ስለ ነበር ከነሱ ጋር መግባት እፈልግ ነበር፡፡

8ኛ ክፍል ላይ የሆነ ጊዜ ሴና የምትባል ልጅ መተላለፊያ መሃላችን ሆኖ ከጎኔ ትቀመጥ ነበር፡፡ ታወራኝ ነበር፡፡ ኮስተር ብዬ ነበር የማወራት፡፡ ሴቶች ኮስታራ ወንድ አይዳፈሩም፣ ግን ይወድዳሉ ሲባል ሰምቼ፡፡ ከሷ ጋር ማውራት ተመችቶኝ ነበር ግን ብሞት ለራሴ ወሬ አልጀምርም፡፡ ሴቶች ፊት ሲሰጧቸው ሰው ይንቃሉ የምለው ፈሊጥ ነበረኝ፡፡ ስለ 7ኛ ክፍል ሰላረግኩት ነገር እንደምትሰማ ምናምን ትነግረኝ ነበር፡፡ ከሴና ጎን ለቀናት ከተቀመጥኩበት ልምድ ተነስቼ ከሴቶች ጋር መጎዳኘት ደስ እንደሚል ገመትኩ፡፡

ስምንተኛ ክፍል ስማር ጥቂት የማይባሉ፣ ልቦለዶችን አንብቤ ነበር፡፡ ታድያ ከቤት እንዳይነቁብኝ በጣም አጠነቀቅና እደብቅ ነበር፡፡ የማነብበው ት/ቤት፣ ቤት ደግሞ ቤቶች ቤት የሌሉ ጊዜና ሌሊት ነበር፡፡ አንድ ቀን ማታ ከተኙ በኋላ እያነበብኩ ነበር፡፡ መፅሐፉ ትልቅ

አይደለም ግን ፊደሎቹ ማይክሮ-ኦርጋኒዝምን ነበር የሚያክሉት፡፡ አንብቤ አንብቤ አልገፋ አለኝ፡፡ በዚያ ላይ መፅሐፉ አልተመቸኝም፣ መጨረሻውን ለማወቅ ብዬ ብቻ ነበር ሳነበው የነበረው፡፡ ያን ምሽት ወደ መጨረሻው አካባቢ ስለደረስኩ ዛሬማ ሳልጨርሰው አልተኛም ብዬ አነበብኩት፣ አነበብኩት፣ እንቅልፍ ይዞኝ እልም ሲል መብራቱ ሳይጠፋ፣ መፅሐፉ ተከፍቶ ደረቴ ላይ እንደተዘረጋ ነበር፡፡ ጠዋት ስነቃ እያነበብኩ እንደነበረ ቆይቶ ነው ትዝ ያለኝ፡፡ መፅሐፉን ብፈልገው፣ ብፈልገው አጣሁት፡፡ አባቴ ሌሊት ሊቀሰቅሰኝ ሲመጣ አይቶ ደበቀብኝ ማለት ነው ብዬ፣ "ሀይል፣ የሆነ መፅሐፍ አይተሃል?" ብዬ ጠየቅኩት፡፡ "የምን መፅሐፍ?" አለኝ፡፡ እኔ ግን ነቃሁ፡፡ በትምህርት ሰዓት አታንብብ አልተባልክም?፣ ክረምት ይደርሳል፣ ሚኒስትሪ ተፈታኝ ነህ፡፡ አልመልስልህም ክረምት ሲደርስ ትወስደዋለህ አለኝ፡፡ ግን የገና ቀን፣ እንደ ገና ስጦታ መልስልኝ ትንሽ ነው የቀረኝ ስለው መለሰልኝ፣ እስክፈተን እንደማላነብ ቃል ገባሁ፡፡ የ8ኛ ክፍልን የሴሚስቴር እረፍት በንባብ ነበር ያሳለፍኩት፡፡ አስኳል የተሰኘ የሲድኒ ሼልደን መፅሐፍ በጣም ነበር የተመቸኝ፡፡ ከመለስ አንደበት የሚል ደግሞ መለስ ከድሮ ጀምሮ ያወራቸውን ነገሮች፣ የሰጣቸውን ቃለ-መጠይቆች የያዘ መፅሐፍም ያኔ ነው ያነበብኩት፡፡ ብዙዎቹን ቲቪ ላይ የሰማኋቸው ቢሆንም ስቦኛል፡፡ መለስን በጣም አከበርኩት፡፡ ለሆነ ሰው የመለስ ስህተት ሐ/ማርያም ደሳለኝን ምክትሉ ማድረጉ ብቻ ነው ማለቴ ትዝ ይለኛል፡፡ ይሄን ያህል፡፡

በቀጣዩ ሴሚስቴር የሆነ 6ኛ ክፍል የሚማር እንደኔው አንባቢ የሆነ ልጅ ነበረና ከሱ መፅሐፍ ተውሼ ማንበብ ቀጠልኩ፡፡ መግባትና መውጣት በበዕውቀቱ ስዩም፡፡ በጣም ሲበዛ አደነቅኩት፡፡ ከማሳቁ ጥበቡ! አንብቦ መጨረስን ለመጀመሪያ ጊዜ ያስጠላኝ መፅሐፍ ነበር፡፡ መጨረስ እያሳሳኝ ነበር የጨረስኩት፡፡ክፍል ውስጥ እያነበብኩ ሆዴን ይዤ ስስቅ የክፍሌ ልጆች ናቲ አበድክ እንዴ ብቻህን የምትስቀው ይሉኛል፡፡ ሳነብላቸው ደግሞ አይስቁም፡፡ አስተማሪ እያስተማረ ምናምን እንግዲህ ሳቅ ለማፈን ትግል ነው፡፡ ልፈነዳ ነበር የምነሳው፡፡ ከበዕውቀቱ መፅሐፍ ላይም እንደ ሌሎች አንዳንድ መፅሐፍት ሁሉ ስለራሴ የመሰሉኝን ታሪኮች አግኝቼአለሁ፡፡ ሳይኮሎጂ ማጥናቱን ከግጥም መድብሉ ላይ ነው መሰለኝ ያነበብኩት፡፡ ያን ሳነብ "እሱም እንደኔ ስለ ሰዎች አስተሳሰብ ማሰብ ይወዳል ማለት ነው" አልኩኝ፡፡ በጎረምሳነቴ ትርጉም ልቦለድ መፅሐፍትን ሳነብ ነበር፣ ከፈረንሳይኛ ወደ እንግሊዘኛ፣ ከዚያ ወደ አማርኛ ነው የሚተረጉሙት፣ ዋና መፅሐፉና የአማርኛ ትርጉሙ አይገናኙም እያለ ተርጓሚዎችን ሲያጣጥል ስለኔ ዛሬና ነገ እያወራ መሰለኝ፡፡ መፅሐፉ(መግባትና መውጣት) ልቦለድ ቢሆንም እንዲህ አይነት ታሪኮች ደራሲው ከራሱ ልምድ የሚጨምራቸው መሆናቸው ብዙ ያነበበ ሰው ይገባዋል፡፡ እኔም እንግሊዘኛ፣ ወይም ፈረንሳይኛ ወይም ጀርመንኛ ችዬ፣ ሳነባቸው የነበርኩትን መፅሐፍት ዋና መፅሐፋቸውን አንብቤ የአማርኛው ተርጓሚዎች ምን ያህል በትክክል ተርጉመውታል የሚለውን ለማነፃፀር እፈልግ ነበር፡፡ ይሄን ይሄን፣ ሌላ ደራሲዎችም ከኔ ጋር የሚመሳሰል ድሯቸውን ወይም ታሪካቸውን ሳይ፣ ደራሲ የምሆን የምሆን እየመሰለኝ መጣ፡፡ በተለይ ዳያሪ መፃፍ ስጀምርና የማንበብ ብቻ ሳይሆን የመፃፍም ተሰጥኦ እንዳለኝ እየተገነዘብኩ ስመጣ፣ ወደፊት ምን መሆን ነው የምትፈልገው የሚለው ጥያቄ እየከበደኝ መጣ፡፡ ዶክተር መሆን ነበር የምፈልገው፡፡ የልብ ወይም የአዕምሮ፡፡

ልቦለድ መፅሐፍት ውስጥ ራሴን የማገኘው ልቦለድ የእውነተኛው አለም ነጸብራቅ ስለሆነ ይሆናል፡፡ አባቴም በተደጋጋሚ ልቦለድ የእውነተኛው አለም ነጸብራቅ ነው ምንም አዲስ ነገር የለውም አታንብብ ይለኝ ነበር፡፡ እኔ ደግሞ ቢሆንም ደስ ይኛል እለው ነበር፡፡ከዚያው 6ኛ ክፍል ከሚማረው ልጅ ራማቶሐራንም አገኘሁ፡፡ አነበብኩት፡፡ ወደድኩት፡፡ ከልጆች ጋር ተቀምጬ ከማውራት ምናምን መፅሐፍ ማንበብን ነበር የምመርጠው፡፡
የገረመኝ፣ ኢትዮጵያ የሚገርሙ ደራሲዎች አሏት የብዙዎቹን መፅሐፍት ባላነብም፡፡ ግን ፊልም ላይ ሁሌ የማይረቡ ፊልሞች ናቸው የሚሰሩት፣ ለምን አሪፍ ፊልም ፀሀፊ አጣን የሚለው ጥያቄ ያብከነክነኝ ነበር፡፡ እነስርየትንና የወንዶች ጉዳይን እያሰብኩ የእነሱ ደራሲዎች ራሳቸው የት ገቡ፣ ለምን ሌላ ፊልም አይሰሩም እያልኩ እናደድ ነበር፡፡

ታደለ የሚባል ደስ የሚል ጎረቤት ነበረን፡፡ በጣም የተከበረ፣ በከተማው የተወደደ ሰው ነበር፡፡ ሳቂታ፣ ተጫዋች፣ የደስ ደስ ያለው በ50ዎቹ የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ የነበረ ሲሆን ሚስትና ሶስት ልጆች ነበሩት፡፡ ሁለቱ ወንድና ሴት ልጆቹ አዳድገው ስራ የያዙ ሲሆን ትንሽዋ እኛ ትምህርት ቤት 3ኛ ክፍል ነበረች፡፡ ለኛ ቤት መብራት ኢንስታሌሽን ሰርቶ እንደዛ ደክሞት ካላበው በኋላ የሚገባውን 2000 ብር አባቴን አሻፈረኝ አልቀበልም ሲለው አጠገባቸው ነበርኩ አስተውሳለሁ፡፡ አባቴ እሳት ያለው ኤሌክትሪክ ሲይዝ አይቶ ባድናቆት አይዝህም እንዴ? ብሎ ሲጠይቀው፣ "ይፈራኛል" አለው፡፡ ሰውየው ቀልደኛ ነው፡፡ ዋና ስራው ሾፌርነት ነው፡፡ በተረፈ ግን የማይሰራው ነገር የለም፡፡ እሱ እንዳለው ኤሌክትሪክ የሚፈራው፣ የሚታዘዝለት ይመስላል፡፡ ሬድዮ ሰርቶልን ያውቃል፡፡
እናቴ ወድቃ እግሯን አሟት ተኝታ ነበር፡፡ የህመሙ ስሜት ለአመታት አልለቀቃትም፡፡ እኔም ያንኑ ሰሞን ቅዳሜ እለት ጠዋት ት/ቤት በረኛ ሆኜ አንዱ፣ እግሬን ብሎ አንገበገበኝና ቤት ገብቼ መኝታዬ ስተኛ፣ እናቴ ደግሞ ሳሎን እየተኛች ታደለ ሊጠይቃት መጣ፡፡ አጫውቷት ምናምን ነገር እኔም ተመትቼ እንደተኛሁ ነገረችውና መኝታዬ መጥቶ እንዴት ያረግሃል? የቱ ጋር ነው ብሎ ጠይቆኝ ሄደ፡፡ ያኔ ነበር ለመጨረሻ ጊዜ ታደለን ያየሁት፡፡ ሰንሻይን ስማር ከሩቅ አይቶኝ መኪናውን አስቁሞልኝ እስከ ሰፈር ያመጣኝ ነበር፡፡ መንገድ ላይ ካዲሳባ እየገቡ ከሙቱ 200 ኪ.ሜ. በማይርቅ ቦታ ላይ ለሽንት ብሎ መኪናውን አስቁሞ ጫካ ውስጥ ራሱን ሰቀለ፡፡ ሰው ግን እንዴት ነው ጨክኖ ራሱን የሚያጠፋው? ምን ያህል የማያልፍ ችግር ቢገጥመው ነው? እሺ ችግሩ ባያልፍስ ራስ ላይ እንዴት ተብሎ ነው የሚጨከነው? ገሃነም እንደሚገባ እያወቀ? ባያምንስ፣ እንኳን ነፍስን የሚያህል ነገር ለማውጣት፣ ሰው ራሱን ይቆነጥጣል እንዴ? በተለይ ታደለ ምን ሆኖ ራሱን እንዳጠፋ ለሙቱ ከተማ ሕዝብ እንቆቅልሽ እንደ ሆነ አለ፡፡ እኔ አንድ ሰው እንዲህ አይነት ውሳኔ ለመወሰን፣ ሀሳቡን እንዲያስብ ራሱ የሚገፋፋውን ነገር ወይም ስሜት ለማወቅ ጓጓሁ፡፡ ጨጓራ በሽታ የሚያሰቃየውን ስቃይ ሰውየውን በማየት ቢያንስ ልትገምት ትችላለህ፡፡ አንዳንድ ነገሮችን ግን በቦታው ላይ ካልተገኘህ፣ ሰዎች ደረሰብን ብለው እየነገሩህ እንኳን አታምናቸውም፡፡

እናቴ ታደለን ሰይጣን ነው ያሳሳተው አለች፡፡ Can you believe it? ለቅሶውን አልሄድኩም፡፡ ፈራሁ? አብሬው የምሄደው ሰው አጣሁ፡፡ ጎረቤት አንድ ፖሊስ የሞተ ጊዜ ግን ባጋጣሚ ብር ካዋጡት ልጆች ጋር ስለነበርኩ ሔጃለሁ፡፡ ከሰፈር ልጆች ጋር የተመቻቸሁ ጊዜ ነበር፡፡

ሚኒስትሪ ተፈተንን፡፡ ከእንደሻው ት/ቤት በመልቀቃችንና ኤሌሜንተሪ መጨረሳችን፣ የመጨረሻ ነበር ያስደሰተን፡፡

ትምህርት ቤት፣ ከአንድ የ7ኛ ክፍል ተማሪ ጋር ስለ መፅሐፍ ስናወራ ዴርቶጋዳን እንዳለውና ግን እንዳላነበበው ነገረኝ፡፡ "ላንብብልህ አምጣው" አልኩት፡፡ አመጣው ሁለተኛ ጊዜ፣ ለሰው ሳነብ፡፡ ሶስት ቀን ነው እንዲህ፣ በእረፍት ሰአት አንብቤለት፣ ደበረው፡፡ እሱንኮ ነው፣ እኔን አይደለም የደበረኝ፡፡ ሰው እኔ ያደነቅኩትን ነገር አይቶ አብሮኝ እንዲያደንቅ እፈልጋለሁ፡፡ ያደነቅኩትን ፊልም፣ መፅሐፍ፣ ምንም ነገር እንዲያዩ የምለምንበት ጊዜ አለ፡፡ "እንዴ አልፈልግም በቃ!"ሲሉኝ "ምን አገባኝ እኔ አሪፍ ፊልም ስለሆነ ነው፣ እንድታየው ብዬ ነው፡፡ ተው ግን እየው" ብዬ ራሴን ለንቀት አጋልጣለሁ፡፡ ከዛ በመለመኔ እናደዳለሁ፡፡

አንድ የት/ቤት ጓደኛዬ የአንድ ደብተሬ ጀርባ ላይ የናቲ ገጽ ብሎ ጽፎ እስከዚያ ጊዜ ድረስ ያነበብኳቸውን መጽሐፎች ርዕስ ዘርዝረህ ጻፍ አለኝ፡፡ ያስታወስኩትን ወደ ሀምሳ የሚጠጉ የመጽሐፍትን ርእሶች የጻፍኩ ሲሆን ከጥቂቱ በተረፈ ሁሉም የልቦለድ መጽሐፍት ነበሩ፡፡ አብዛኞቹ የትርጉም መጽሐፍት የነበሩ ሲሆን አብዛኞቹ ከመምሪያ ላይብራሪ የተዋስኳቸው ነበሩ፡፡ 3 አመት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ ያስታወስኳቸው 50 መፅሐፍት ማለት በጣም ብዙ ነው፡፡

ቤት፣ "እኛ ኢትዮጵያውያን ግን ምን ያህል ደሀ እንደሆንን ራሱ አናውቅም" እላቸው ነበር፡፡ ወንድሜ ይስማማል፡፡ እኔ ራሱ ኢትዮጵያ ብዙም ደሀ አትመስለኝም ነበር፡፡ ለነገሩ ቢመስለኝ ነው የሚገርመው፡፡ አዕምሮዬ በልማታዊ ዜና ተጣብቦ ከድህነት ስለ መውጣት ከ10 አመት በኋላ ኢትዮጵያ አሜሪካ የደረሰችበት እንደምትደርስ እንጂ ደሀ ስለመሆን ለማሰብ አዕምሮዬ ቦታ አልነበረውም፡፡ እናቴ ከፈለጋችሁ እናንተ ተጠቅልላችሁ ደሀ ነን በሉ እንጂ እኔ ደሀ አይደለሁም ደሀ አትበሉኝ ትላለች፡፡ መኪና አለሽ? "አዬ"፡፡ በቃ ደሀ ነሽ፡፡ ውጪ ሀገርኮ መኪና ተራ ነገር ነው፡፡ የሌለው የለም፡፡ ብለን ልናሳምናት እንሞክራለን፡፡ እውነት ነው፡፡ የሆነ ፊልም ላይ፣ ገርል ፍሬንዱ፣ አንተኮ መኪና ራሱ የለህም፣ እንዴት ነው ካንተ ጋር የምቆየው? ትለዋለች፡፡ ለፈረንጆች ያሳዝናል፣ ለኛ ግን ቀልድ ነው ሚመስለው፡፡

ሀብረተሰብ(Hawaasa) ት/ት ላይ ስለ ፐርል ሀርበር(በሁለተኛው የአለም ጦርነት ጃፓኖች ቦምብ ያዘነቡበት የአሜሪካ የባህር ሃይል) ስንማር በተመሳሳይ ስያሜ የተሰራው ፊልም አሜሪካኖች ሂሮሺማና ናጋሳኪ ላይ ላደረሱት ጥቃት ፍትሃዊ እንደሆነ እንኳን ባይሆን ኢፍትሃዊ እንዳልነበረ ለማሳየት የተሰራ መሰለኝ፡፡ በትንሽዋ ጥቃት ፊልም ሰርተው የሰውን አንጀት በልተው፣ ለዚህ ነው ለማለት፡፡ ወይ አሜሪካኖች! ጉደኞች፡፡ እና ፊልምኮ ከፍቅሩ፣ ከሚታየው ታሪክ ጀርባ የሆነ የሚያስተላልፈው "reading between the lines" የሚሉት አይነት መልዕክት እንደሚኖረው ገመትኩ፡፡ ፊልም የተደባበቀ፣ የተወሳሰበ ነገርና ከታሪኩ ጀርባ ማስተላለፍ የተፈለገ ሀሳብ እንዳለው ማሰብ የጀመርኩበት የመጀመሪያው አጋጣሚ፡፡

ክረምት የቸርች ት/ት፣ የአባልነት ት/ት ጨርሰን ፈተና ወሰድን፡፡ ፈተናውን ስንፈተን ፈታኙ ይሄ መደበኛው ት/ቤት አይደለም፡፡ የእግዚአብሔር ቤት ነው እንዳትሰራረቁ አለን፡፡ ከኛ ከተማሪዎቹ መሀል ሁለት እናቶች ነበሩ፡፡ ሁለቱም መፃፍና ማንበብ አይችሉም ነበርና ፈተናውን አስተማሪው በቃል ነበር የሚጠይቃቸው፡፡ አነሱም በቃል ይመልሳሉ፡፡ መልሳቸውን ይመዘግብላቸውና በኋላ ሊያርምላቸው፣ ማለት ነው፡፡ አስተማሪያችን ከእናቶቹ አንዷን አንድ ጥያቄ ጠየቀና ምርጫውን አነበበላት፡፡ ኤ እንዲህ ቢ እንዲህ ሲ እንዲህ፡፡ መልሱ ምንድነው ሲላት፣ ዲ አላለችውም? በሳቅ ተከሰከስን፡፡ ደግነቱ መውደቅ የሚባል ነገር አለመኖሩ፡፡ አባል ሆንን፡፡

- ወደ ቄስ ኢብሳ ተሸጋገርን፡፡ ቄስ ኢብሳ የሙቱ መካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስትያን ዋና ቄስ ሲሆኑ ብዙ የቤተ ክርስትያኒቱ አባላት ቢወድዷቸውም፣ ደረቅ፣ ለየት ያለ አስተሳሰባቸውን ብዙ ሰዎች አይወዱትም፡፡ እኛ ቸርች እንደሌላው የመዝሙር ጊዜ መዝለል መጮህ ምናምን አይቻልም፡፡ እንደሌላው ቸርች በልሳን መናገር፣ ሲነኩ ሃሌሉያ ብሎ መጮህ አይሰማም፡፡ እንደ አታልፍም ብሎ አይነት መዝሙሮች አይዘመሩም፡፡ ለዚህ ሁሉ የቸርቻችን ከሌላው ለየት ማለት፣ ጣቶች ሁሉ ወደ ቄስ ኢብሳ ይቀሰራሉ፡፡ እኔ እስከ ሰማሁት ድረስ፡፡ መካነ ኢየሱስ ከሌሎች ትንሽ ለየት እንደምትል የታወቀ ቢሆንም የኛ ቸርቹ ግን ከሌሎቹ፣ ሙቱ ውስጥ ካሉት ሌላ ሁለት መካነ ኢየሱሶችም ይለያል፡፡ ቄስ ኢብሳ ሰይጣን እናወጣለን የሚሉትን አልሰማም የሚሉና የተቃዋሚ ፓርቲ አይነት ሁሉም ትክክል አይደለም ባይነት ቢኖርባቸውም ለራሳቸው ደግሞ በወጣትነታቸው ሰይጣን ያስጮሁ ነበር አሉ፡፡ በዚያ ላይ ገበያ ውስጥ ሰብከው እንደሚያውቁ ከራሳቸው አንደበት ሰምቻለሁ፡፡ ቄስ ኢብሳ ሲያስተምሩን ኤልሻዳይ ቲቪ ላይ የምታዩትን ሁሉ አትቀበሉ ይሉን ነበር፡፡ በቴሌቪዥን የሚቀርቡትን ነብዮች እንደማይቀበሉ በተደጋጋሚ ተደምጠዋል፡፡ እንደኔው የእምነት ማጽኛ ትምህርት ስላስተማሩት ስለ ሲጄው ስለ ታምራት ታረቀኝ ሲጠየቁ እንደዛ የሚባል ሰው አላውቅም እንዳሉ ሰምቼአለሁ፡፡ መዝለልንስ ስርአት ያስፈልጋል ብለው ነው የጠሉት እንጂ፡፡ ሰይጣን የማውጣት ክፋቱ የቱ ጋር እንደሆነ የጠየቃቸው ያለ አይመስለኝም፡፡ አሳቸው ግን ባካባቢያቸው ያሉት የሚያማርሯቸውን ያህል በሰዎች ላይ ቅሬታ አላቸው፡፡ "ለምን አይሰሙኝም?" ይላሉ፡፡ ብዙ ነገሮችን የከለከሉ ቢሆንም በዚያ ግን የረኩ አይመስሉም፡፡ ለየት የሚሉት የቸርቻችን መሪ፣ ቄስ ኢብሳ፡፡

እኔን ይወዱኝ ነበር፡፡ የሆነ ጊዜ ሲያስተምሩ እኔን የሆነ ነገር ሳይሉ እንደማይወጡ አስተዋልኩኝ፡፡ ወይ ስሜን ይጠራሉ፣ ወይ ይቆጡኛል፣ ወይ ጥያቄ ይጠይቁኛል፣ ወይ የሆነ ነገር፡፡ ብቻ ከክፍሉ ተማሪ ትኩረታቸውን ነበረኝ፡፡

አዳሜ ዲሽ ገዝቶ ገዝቶ እያስገጠመ ነበር፡፡ እኛና እነአሊና እነአቡሽ ምናምን ጥቂት ሰዎች ብቻ ነበርን ከኛ ክፍል ዲሽ ያልነበረን፡፡ የነጆን ሲናና ሬይ ባክ ወሬ ክፍል ውስጥ አንገበገበን፡፡ እንዴት እንደመታው የትናንቱን ማን እንዳሸነፈ፣ማን እንደሚመቻቸው ሲያወሩ ዲሽ የሌለን ዝም ከማለት ሌላ ምን አማራጭ አለን? በተለይ እኔ ከሪስሊንግ ተፋላሚዎች ውስጥ ፊቱንና ስሙን በርግጠኛነት ማገጣጠም የምችለው ጆን ሲናን ብቻ ነበረ(ነው)፡፡ ዲሽ ያላቸው ስማቸውን ይደረድራሉ፡፡ ምን ያህል ቢያዩ ስማቸው እንደሚሸመደድላቸው እኔ አላውቅም፡፡ እንዲሁ አስበውበት ለወሬ፣ ከሌላው እኩል ለማውራት ሸምድደውም ሊሆን ይችላል፡፡ እኛ ዲሽ የሌለን፣ ዲሽ ኖሮን ስለሪሰሊንግ በተነሳ ቁጥር ከወሬ ውጪ መሆናችን ቀርቶ ሳንሸማቀቅ አቤት ሼመስን ቀጠቀጡት እያልን የምናወራበት ጊዜ ናፈቀን፡፡
ስለ ፊልም ከተነሳ እኔንና አሊን የሚበልጥ የለም፡፡ እኛ ብዙ አይተናል፡፡ እንዲያውም አሊ አንዴ ተገርሞ "ዲሽ ያላቸው እነሱ ቢሆኑም የኛን ያህል ፊልም አላዩም" ብሎኛል፡፡ "አሊ፣ ቧንቧው ውሃ እያፈሰሰ ይውላል ማለት ውሃው እየተጠጣ ይውላል ማለት አይደለም" ሳይሆን "ትክክል ነህ" ነበር ያልኩት፡፡
አንድ ቀን አንድ አስደንጋጭ ዜና ሰማሁ፡፡ የፈራሁት፡፡ አሊ አባቱ ዲሽ ገዝቶ ከመንገድ እየመጣ እንደሆነ ነገረኝ፡፡ ከዚህ በላይ ምን የሚያስደነግጥ ነገር አለ? እነአሊ ዲሽ ሲገዙ የማጣቱ ስሜት በእጥፍ ጨመረ፡፡ ቤት ገብቼ እነአሊኮ ዲሽ ገዙ አልኳቸው፡፡ ወዴት ወዴት እያልኩ እንደሆነ ወዲያው የገባት እናቴ ከፈለጉ ለምን ፎቅ አይገዙም? እኛ ምን አገባን አለች፡፡ አባቴ ደግሞ እኛ ብዙ የምንሰራው ነገር አለን፣ ገንዘብ የለንም፣ ደግሞ አንተ እንኳን ዲሽ ተገዝቶ እንዲሁም አስቸግረሃል፣ ዲሽ ካገኘህ ከነጭራሹ አታጠናንም፡፡ እንኳንስ ዘንቦብሽ...ነው ነገሩ አለኝ፡፡ ትንሽ ቆይቶ እነአቡሽ ገዙ፡፡ ዲሽ የአዕምሮዬ አርዕስተ ዜና ሆነ፡፡
አሊ ዲሽ እንደገዙ፣ ቤታቸው ስሄድ ሪስሊንግ፣ በMTV ደግሞ ዘፈን አሳየኝ፡፡ እንግሊዘኛ ዘፈን፡፡ ቢል ቦርድ ላይ ያሉ ዘፈኖች ነበሩ ሲታዩ የነበረው፡፡ የሆነ የሚፀዳ ዘፈን ብሎ ስንት ዘፈን አስጠብቆ አሳየኝ፡፡ "Dynamite" ነበረ ዘፈኑ፡፡ እኔ ደግሞ ምኑ እንደሚፀዳ ግራ ገባኝ፡፡ ምኑ ነው የሚፀዳው አይፀዳም አልኩት፡፡ እይ በና አለኝ፡፡

እሱ ቲኪ ጋር ነው የለመደው፡፡ እሷ ነች ያስለመደችኝ ብሎ ነግሮኛል፡፡ ከኛ ባች ቲኪ ቶሎ ዲሽ ከገዙት መሀል ነች፡፡ 7ኛ ክፍል ስንማር ነበር የገዙት፡፡ እንግሊዘኛ ራሱ ትችላለች፡፡ ታድያ እሷ እንግሊዘኛ ዘፈን ትወድ ነበርና እሷ ጋር ሲሄድ ነው ያስለመደችው፡፡ አሊ በተለይ ጀስቲን ቢበርን በጣም ነበር የሚወደው፡፡ ከላስ ራሱ ጀስቲን ቢበር ብለው ይጠሩት ነበር፡፡
ዮናስ የሚባል ልጅ 8ኛ ስንማር አንዲት ትንሽ ስማድል ስልክ ነበረውና እንግሊዘኛ ዘፈን ነበረው፡፡ አሊ ታድያ ተመስጦ ነበር ዘፈን የሚያዳምጥባት፡፡ ሆጳ ጋንገም ስታይል የወጣ ሰሞን ማለት ነው፡፡
እኔ የመሰጠኝ የእንግሊዘኛ ዘፈን ቢኖር አንዴ ሰባተኛ ክፍል ስማር ይመስለኛል፣ በTV OROMIYAA Sirboota biyya alaa ላይ ያየሁት I just met you, this is is crazy, but here's my number, call me maybe. የሚለው ዘፈን ነው፡፡ የCarly Rae Jepsen.

ክረምት መምሪያ ላይብረሪ ኢንተርኔት በኮምፒዩተር ያስጠቅሙ ነበርና ከነባቢ ጋር ተጠራርተን ሄደን ፌስቡክ እንጠቀም ነበር፡፡ ከስድስት ኮምፒዩተሮች ሶስቱ ብቻ ነበሩ የሚሰሩትና ለ20 ደቂቃ በየተራ ነበር የምንጠቀመው፡፡ እኔ ደስተኛ ነበርኩ፡፡ ስልክ ስላልነበረኝ በጉጉት ነበር የምጠቀመው፡፡ ለወንድሜ ስነግረው "ፌስቡክ ለመጠቀም ብቻ ነው የምትሄዱት?" ብሎ ይገረም ነበር፡፡ እኔም አሁን ሳስበው ለ20 ደቂቃ ፌስቡክ ከቤት ወጥቶ፣ 20 ደቂቃ ተጠቅሞ ከማን ጋር ቻት እያደረግክም ይሁን ምን እየሰራህ፣ ሎግ አውት ማረግና አሁንም ወረፋ መጠበቅ፣ ይገርማል ብቻ፡፡

ያን ክረምት አሊ ሲያነብ የነበረውን የአጋታ ክሪስቲ(Agatha Christie) መፅሐፍት ማንበብ ጀመርኩ፡፡ የሚገርሙ የወንጀል መፅሐፍት፡፡ ገራሚ ደራሲ ነች፡፡ የድርሰት አልበርት አነስታይን እንደሆነች ለጓደኞቼ ማውራቴ ትዝ ይለኛል፡፡

የአጋታ ክሪስቲ መፅሐፍት ሳቢ አደሉም ግን ወንጀሉን ማን እንደ ፈፀመው እየገመትክ፣ ማነው እያልክ በጉጉት እስከ መጨረሻው ትዘልቃለህ፡፡ አንድ ያነበብኩት ስለ አንድ ቤት ነው፣ ሰው ዝም ብሎ ይሞታል፡፡ ቤተሰብ ናቸውና የውርስ ጉዳይ ነበረባቸው፡፡ መጨረሻ ላይ ገዳይዋ ሕፃኗ ሆና ታርፈዋለች፡፡ "አርጅቼ ልሞት ስል፣ ሁሉንም እንዴት እንደገደልኩ የሚያሳየውን ዳያሪ ለህዝብ አጋልጣለው" ብላ የፃፈችበት ዳየሪ ራሱ ተገኝቶ ያሲዛታል፡፡ የአጋታ መፅሐፍት በግድያ፣ ማነው የገደለው ውዝግብና ጥርጣሬ ስለተሞሉ ያስፈራሉ፡፡ ሰው የገደሉ ሰዎችን ሰብስቦ፣ በጥበብ ሳያስነቃ የሚጨርሰውን ሰውዬ ታሪክ ሳስታውሰው ራሱ ያሸብረኛል፡፡
በዚያ ክረምት ብዙ የአጋታን መፅሐፍት አነበብኩ፡፡ ያቺ ሴትዮ ከመፅሐፍ ቅዱስ ቀጥሎ መፅሐፍቶቿን በአለም ብዙ ኮፒ በማሳተም ቀዳሚ ስትሆን ግራ የሚያጋባ ህይወት እንደ ነበራት አንብቤአለሁ፡፡ በ19ኛው ክ.ዘ. ማለቂያና በ20ኛው ክ.ዘ. መግቢያ የኖረችው አጋታ በ14 አመት ትበልጠው የነበረን ሰው አግብታ እንደ ነበር፣ ማንም ሳያውቅ ለወራት ድምጽዋን አጥፍታ ትጠፋ እንደነበር ተፅፎ ነበር፡፡
በዚያ ክረምት በማርዮ ፑዞ የተጻፈውንና ተወዳጅ ፊልምም ጭምር የተሰራለትን በኒው ዮርክ ውስጥ የሚኖሩ የጣልያን የማፍያ ቤተሰቦች ታሪክ የሆነውን የጡት አባት(THE GODFATHER) ማንበቤ ትዝ ይለኛል፡፡ ምርጥ ታሪክ፡፡ ብርቅርቅታስ? ብርቅርቅታ በዳኔላ ስቲል የተጻፈ ሲሆን ሳነበው ማቋረጥ አቅቶኝ እስከ ከሌሊቱ 8 ሰአት ተቀምጬ አንብቤው የጨረስኩት መጽሐፍ ነው፡፡ የሚያሳዝን፣ እምባ ያስወጣኝ መጽሐፍ፡፡

ኦዳ መንገድ ላይ ሲያየኝ አንተ ወጣት አይደለህም እንዴ? ቸርች ወጣቶች ና ይለኝ ነበር፡፡ ስለ ወጣቶች ፕሮግራም የሆነ የሚደብረኝ ነገር ነበር፡፡ የሆነ በጣም የተጋነነ ማህበራዊነት አለና ቸርች ውስጥ ያስፈራኝ ነበር፡፡ ኦዳ ግን አብረን እንሄዳለን ሲለኝ ነበር፡፡

ስምረት

ከመምሸቱ በፊት፣ የሚያንጸባርቀው የጸሐይቱ ውበት...

ይሄ ዘመን ክፉ ዘመን እንደሆነ ስሰማ ነው ያደግኩት፡፡ ነገር ግን ግራ ይገባኝ ነበር፡፡ የመጨረሻው ዘመን ይባላል፣ እኔ ግን ሁሉም ሰላም ጤና ይመስለኝ ነበር፡፡ ቢያንስ ለኔ ሰላም ጤና ነበረ፡፡

በ2005 ዓ.ም. ዋዜማ የስጋ ቅርጫ ለመውሰድ ሄጄ በጣም ቆየሁ፡፡ ወደ አምስት ሰአት ከቤት የወጣሁትን ከስምንት ሰአት በኋላ ነበር ቤት የደረስኩት፡፡ ጸሀይ ለጉድ ወጥታ ነበር፡፡ በቃጠሎው ላይ ሸክሙ ተጨምሮ፣ በዛ ላይ ረሀቡ፡፡ ቤት ስደርስ በረንዳችን ላይ ብዙ የልጆች ስሊፐር ጫማዎች ሰልፍ ገብተው አገኘሁ፡፡ ማን ይሆን ደግሞ የመጣው ብዬ ወደ ቤት ውስጥ ስገባ ማንን ተቀምጦ ባገኝ ጥሩ ነው? ሳሚ! የተዛወረው ጓደኛዬ፡፡ ከሁለት አመት በኋላ ነበር እንደገና ለመገናኘት የበቃነው፡፡ ተቃቅፈን ሰላም ተባባልን፡፡ እንዴ ረዝሞ ጣሪያ ነበር ያከለው፡፡ ምን አከልክ አልኩት፡፡ አንተስ? አንተም አደግክኮ ድምጽህም ወፈረ አለኝ፡፡ አይ ሳሚ፡፡ ወንድሙ ያዕቆብም አድጓል፡፡ ሁለተኛ ነው አንደኛ ክፍል ገብቷል አለኝ፡፡ ሳሚ ቁመት እንጂ ብዙ የተቀየረ ነገር አልነበረውም፡፡ አቢቲም ነበረ፡፡
ከሳሚ ጋር ሁለት ቀን ነበር የተገናኘነው፡፡ ያን የዋዜማ ቀንና በበአል ማግስት፡፡ እንደማነብ፣ ልቦለድ በጣም እንደምወድ ነገርኩት፡፡ ፍቅር እስከ መቃብርን አንብቤ እንደ ሆነ ጠየቀኝ፡፡ እንዳነበብኩት ነገርኩት፡፡ እሱ ሊያነበው ሞክሮ እንደ ደበረው ነገረኝ፡፡ አንብብ ማንበብ ደስ ይላል አልኩት፡፡ በበአመሉ ማግስት ማግስት እነሳሚ ወደ ወንጂ ተመለሱ፡፡

የተፈተንነው ሚኒስትሪ ሳይመጣ ቆየ፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር፣ ሚኒስትሪ በማሽን ሲታረምና ሳይመጣ መስከረም ሲጠባ፡፡ በፊት እዚሁ ከዩኒቨርሲቲ በመጡ ልጆች ነበር የሚታረመው፡፡ ቆየ፣ ቆየ፣ ሚኒስትሪ ተበላሸ ተባለ፡፡ ምን ማለት ነው፣ ተበላሸ ማለት? ይዞት ሲመጣ የነበረው መኪና ሰመጠ? ጳጉሜ ገባ፡፡ ሚኒስትሪ የወሬ ሽታ ሆኖ ቀረ፡፡ አሁንም ሚኒስትሪ ተበላሽቷል ከሚል ወሬ ሌላ ምንም አልነበረም፡፡ መስከረም ገባ፡፡ ሚኒስትሪ ግን አዲሳባ እንዳለ ነበር፡፡
አንድ የመስከረም ቅዳሜ ጓደኛዬ ኦሊ ቤት መጥቶ "ናቲ!" ብሎ ጠራኝ፡፡ ስወጣ ሚኒስትሪ መጣ አለኝ፡፡ ስንት አመጣሁ ታድያ አልኩት፡፡ 43 አለኝ፡፡ 93 ያለ መሰለኝ፡፡ 93 ነበር አመጣለሁ ብዬ የገመትኩት፡፡ አትቀልድ ንገረኝ አልኩት፡፡ ደገመው፡፡ እየቀለድኩ አይደለም፡፡ 43 ነው አለኝ፡፡ ተበላሽቶ ነው አለኝ፡፡ ሲደጋግምልኝ አመንኩት፡፡ ነገር ሲደጋገም ይታመናል፡፡ መርዝ የሆነን ነገር ደጋግመው ለጤና ጥሩ ነው፣ ተጠቀመው፣ ጠጣው ብለው ደጋግመው ሁሌ ቢነግሩህ፣ ታረገዋለህ፡፡ ኦሊ 68 እንዳመጣና ጓደኞችን፣ ጎበዙ አቡሽ ደግሞ 60 እንዳመጣ ነገረኝ፡፡ የወንድ ማለፊያ 37 ነበረ፡፡ ከ37 በታች ቢሆን የሰጡኝ፣ ያስወድቁኝ ነበር ማለት ነው? የሚገርምኮ ነው፡፡

እኔ ምንም እንደ ድሮ ባስተማሪዎች ለመወደድ ባልፈልግና ባላዳምጥ፣ አጥንቼ ነበር፡፡ የሱራፌል ተፎካካሪ ነበርኩ፡፡ እንዲያውም ሞዴል ታርሞ እኩል ነበር ያመጣነው፡፡ ፊዚክስና ሂሳብ የሱ ናቸው፡፡ እኔ በእንግሊዘኛ እቦንሰው ነበር፡፡ እንግሊዘኛን በህጎቹ፣ በጥናት ምናምን ሳይሆን፣ ከፊልም በምሰማው ምናምን ነበር ሌሎቹን የምቦንሳቸው፡፡ በገፍ እየተከራየሁ ሳያቸው የነበሩ ፊልሞች አንግሊዘኛ ለመቻል ካለኝ ፍላጎት ጋር ተደማምረው ልዩነት ሳይፈጥሩ አልቀሩም፡፡ ሌላውን አልሰማም ግን ሲቪክና እንግሊዘኛ ላይ ዋና ተሳታፊ ነበርኩ፡፡ የምወዳቸው ሁለት የትምህርት አይነቶች፡፡ በተለይ የእንግሊዘኛ አስተማሪዎችን እፈትን ነበር፡፡ ፈተና ላይ ሌላው ፓስት፣ ፊውቸር፣ ሲምፐል፣ ፐርፌክት ኮንቲኒየስ እያለ ህጎቹን ከጥያቄዎቹ ጋር እያስታረቀ ለመስራት ሲሞክር እኔ እንዲህ አይባልም፣ ይሄ አብሮ ይሄዳል እያልኩ ነበር እንዲሁ በግምት እየሞላሁ የምበልጣቸው፡፡ አብራራ ብባል እንዲህ የሚባል ስለማይመስለኝ ነው ከማለት የዘለለ ማብራሪያ የለኝም፡፡ ሚኒስትሪ በመበላሸቱ እኔ ብዙም አልተናደድኩም፡፡ ሱራፌል ግን አለቀሰ፡፡

2005 9ኛ ክፍል አብዲ ቦሪ ነበር የምማረው፡፡ ዩኒፎርሜን የሰፋው ሰውዬ ሱሪውን እንዳልሆነ ነበር ያደረገብኝ፡፡ ያ ሳያንስ እናቴ አሪፍ ጫማ ከአዲሳባ አይተሽ ግዢልኝ ስላት በ200 ብር አሪፍ ሸራ በሚገዛበት ዘመን፣ የሽማግሌዎችን ፒኮክ በ460 ብር ገዝታልኝ መጣች፡፡ ምን ብዬ ነው ትምህርት ቤት ለብሼ የምሄደው? ደብተር ሲነር ላይን ግዢ ብዬአት ሳን ላይን የተባለ ደብተር ገዛችልን፡፡ ሉኩ እንደ ሀገር ውስጥ ደብተሮች ሸካራ ነበር፡፡ የምገባበት አጣሁ፡፡ ያለቀልኝ መሰለኝ፡፡ አመቱ መጥፎ የሚሆን መሰለኝ፡፡

በአንፃሩ እንደ ተመኘሁት አብሬአቸው አንድ ክፍል መሆን እፈልግ ከነበሩት ከቢ ክፍል ተማሪዎች ጋር ገባሁ፡፡ ከድሮ ክፍል አብሮኝ የገባ ማንም አልነበረም፡፡ አንድ አቅመኛ ድሮ አብሬው የተማርኩት ወንዴ የሚባል ልጅ ብቻ አብሮኝ ገባ፡፡
ከአሊና ከአቡሽ ጋር ነበር መጀመሪያ ቀን 9ኛ ክፍል አዲሱ ት/ቤታችን አብዲ ቦሪ አብረን የሄድነው፡፡ ስሄድና ክፍሌ ስገባ የመጨረሻው ነበርኩ፡፡ ሁሉም ገብተው ነበር፡፡ እንዲሁ ዝም ብዬ የማውቀውንም ሰው ሳላማርጥ ክፍል ገብቼ ወደ መጨረሻ ቦታ አፈላልጌ ስቀመጥ አቅመኛው ወንዴ፣ ጠርቶ ና እኔ ጋር አለኝ፡፡ ሔድኩኝ፡፡ አጠገቡ ተቀመጥኩ፡፡ በነጋታው የሆነ ልጅ መጣና እኛ ጋር ተቀመጠ፡፡ ወንዴ ለምን ተጠጋህለት ብሎ ተቆጣ፡፡ ቦታ ወደ መጨረሻ ስቀይር ወንዴ ተቆጣ እስረኛ ሆንኩኝ፡፡ እነበረከትና እነኢዩኤል ወደ መጀመሪያ ወደ በር አካባቢ ነበር የሚቀመጡት፡፡ ከሁለት ቀን በኋለ ነው እንዲህ፣ በረከት እነሱ ጋር ሄጄ እንድቀመጥ በምልክት ጠራኝ፡፡ ወንዴ እንደማይፈቅድልኝና እንደሚጮህ በምልክት አስረዳሁት፡፡ መረዳቱን እንጃ፣ ቁም ነገሩ፡ በረከት በመጀመሪያ ቀናት እነሱ ጋር እንድቀመጥ መጋበዙ ነው፡፡

የኔ ክፍል ኢ ነበር፡፡ አብረውኝ ሲማሩ የነበሩት አሊ፣ ኬነሳና ዮናስ አንድ ላይ ዲ ገቡ፡፡ ድሮ አብረናቸው ስንማር የነበርን ልጆች፣ እነአሊ ግሩፕ ፈጥረው የሚያስቀኑን መስሎን ቀናን፡፡ ከድሮ ክፍል ልጆች ጋር ሁሌ እረፍት ላይ አንዲት ቦታ ነበረንና እንገናኝ ነበር፡፡

ባዮሎጂ የመጀመሪያ ፈተና ስንፈተን እኔ እነወንዴ ጋር ተቀምጬ ነበር፡፡ ፈተናውን መሀል አስቀምጠውኝ እንዳለ ገለበጡና ከነቦነሷ ደፈኑ፡፡አስተማሪው ለምን አሳየህ? ካንተም ከነሱም 5 ማርክ እቆርጣለሁ አለ፡፡ ባዮሎጂ አስተማሪያችን ስም ጠሪያች ቲቸር ከበደ ነበረ፡፡ 5 የቆረጠው ከነሱ ላይ ብቻ ነበር፡፡ ተው ሁሉንም አትገልብጡ እያልኳቸው ነበር ሁሉንም የኮረጁት፡፡
የተቀመጥኩበት ቦታ በጣም ደበረኝ፡፡ ከወንዴ ይልቅ ከማላውቀው ከታሪኩ ጋር ተመቻቸን፡፡ በርግጥ ወንዴ ለኔ መጥፎ አልነበረም፡፡ ጓደኛዬ ይለኝ ነበር፡፡ እኔ ግን ከሱ ጋር መጎዳኘት አልፈልግም ነበር፡፡ ምንም ቢሆን ወንዴ ነው፡፡ ትንሽ ቆይቶ መሳደብና መማታት ጀመረ፡፡

ኢዩኤል አንድ ቀን እረፍት ላይ አንድ ቀላል ሂሳብ አስረዳኝ ብሎኝ አስረዳሁት፡፡ ሳስበው እንዲሁ ለመቀራረብ እንጂ ሂሳቡ ሳይገባው ቀርቶ ወይም እንዳስረዳው ፈልጎ አስረዳኝ እንዳላለኝ ገመትኩ፡፡

ቲቸር ከበደ አንድ ቀን መጥቶ በራያ(አንድ ለአምስት) አደራጀን፡፡ ከወንዴ ጋር ተለያየን፡፡ እኔን የት ቢያስቀምጠኝ ጥሩ ነው? ኮርነር አካባቢ የነኢዩኤል ራያ አጠገብ፡፡ ሲጀመር ከኢዩኤል ጋር ለመቀመጥና እኔም ከሱ ጋር ለመቀራረብ ፈልጌ ነበር፡፡ ደስ አለኝ፡፡ እኛ አካባቢ ማንም የምናውቀው ሰው አልነበረምና አብረን መቀመጥ ጀመርን፡፡ ከኢዩኤል ጋር በወሬ በጣም ተጣጣምን፡፡ በጣም ተግባባን፡፡ እኔ የምለውን ነገር፣ አዎ ብሎ ማብራሪያ ይሰጥበት ነበር፡፡ በቃ የምፈልገውን አይነት ጓደኛ ያገኘሁ መሰለኝ፡፡ አስተማሪ ያስተምራል፣ እኛ እናወራለን፣ እናወራለን፣ እንስቃለን ወሬያችን ማለቂያ አልነበረውም፡፡ ችግሩ በረከት መጀመሪያ ላይ ነበርና ራያው፣ ተደበረ፡፡ እኛ ተቀምጠን ወሬያችንን ስንሰለቅጥ እሱ ጭልፊት ሆነ፡፡ እኛ ስናወራ ከሩቅ እያየን ይስቅ ነበር፡፡ “ቀናችኮ” ይል ነበር ኢዩኤል፡፡ ኢዩኤል በረከትን አይወደውም ነበር፡፡ ይልቅ ያማው ነበር፡፡ ፀባዩ እንደማይቻል ይነግረኝ ነበር፡፡ እኔና ኢዩኤል እያወራን ምናምን በረከት እኛ ጋር ይመጣ ነበር፡፡ ሲመጣ ታድያ እኛ ወሬ ይጠፋብናል፡፡ ይሔ የኔ ችግር ነው፡፡ ሰው ቶሎ አልላመድም ከተላመድኩ በጣም እላመዳለሁ፡፡ እሱ ሲመጣ በቃ እንግዳ እንደመጣ ነገር ቶሎ እንዲሄድልን እንመኝ ነበር፡፡ ትንሽ ቆይቶ በረከት እኛ ጋር ሲመጣ ኢዩኤል ሂድ ከዚህ ብሎ ያባርረው ጀመር፡፡ እንዲህ ይገላግለን ጀመር፡፡ በዚህ ሁሉ ውስጥ በረከት እኔን እንደ ጠላቱ እየጠላኝ ነበር፡፡ በፊት ከኢዩኤል ጋር አብረው ሲቀመጡ ነበር፡፡ በየትኛውም መስፈርት የኢዩኤል ጓደኛ መሆን የነበረበት እሱ ነው፡፡ በተቃራኒው ግን እኔና ኢዩኤል best friends አየሆንን ነበር፡፡ እረፍት ላይ በፊት ሲወጡ እኔ “ሰው የሚበዛበት... ምናምን” የምለው ነገር ነበረኝና “አልወጣም ክፍል ውስጥ እቀመጣለሁ” እለው ነበር ኢዩኤልን፡፡ እንዲህ እንዲህ እያልኩ ሲደብረኝ የድሮ ጓደኞቼ ጋር መሄድ ጀመርኩ፡፡ ደስ የሚለው እነሱ ሁሌ አንድ ቦታ ቆመው ነው ሲያወሩ የሚውሉት፡፡ ከዚያ እኔ አልወጣም ስል ኢዩኤል አብሮኝ ክላስ ውስጥ ይውል ጀመር፡፡ ሌሎቹም፡፡ እረፍት ክፍል ውስጥ ተቀምጠን እያወራን መዋል፡፡ እዚህኛው ክፍል ሁሉም የገባው፣ የሚመች ነበር፡፡ “የ9ኢ ተማሪዎች ተመልምለን ነው የገባነው” ብዬ ሌሎች፣ የድሮ ክፍል ልጆች ላይ እራሱ አካብድ ነበር፡፡ የ9ኢ የገጠር ልጆች ራሱ ይመቻሉ፡፡ኢዩኤል ከኔ ጋር እረፍት ላይ ክፍል ውስጥ ሲቀመጥ እነበረከት እንውጣ ብለው ይጨቀጭቁታል፣ ዝም ሲላቸው እነሱም ይቀመጡና ወሬያችንን እንቀጥላለን፡፡ በተለይ በረከት ግን ለምን ኢዩኤል ይሄን ያህል ከኔ ጋር መዋል እንደሚፈልግ ግራ ይገባውና ይናደድ ነበር፡፡ የሌላ ክፍል ልጆች፣ የነሱ የድሮ ክፍል ተማሪዎች በተለይ እነኢዩኤል ጋር መጥተው ክፍል ውስጥ ተጋግረን እንደምንውል ሲያዩ ኧረ ውጡ ብለው ይገረሙ ነበር፡፡ትንሽ ቆይቶ ከነኢዩኤል ጋር ወጥቼ ብስኩት(ፓስቲ) ቤት መሄድ ጀመርኩ፡፡ ብስኩት ቤት ደስ ይል ነበር፡፡ በዛ ግርግር ውስጥ ብስኩት ገዝቶ በሻይ መብላት፡፡ ከሚመኩባቸው፣ የኔ ከሚሏቸው ጓደኞች ጋር፡፡

አንድ የኢዩኤል ጓደኛ ነበረ፡፡ ባጋጣሚ ከት/ቤት ወደ ቤት እየገባሁ መንገድ ላይ ተገናኝተን ፀባይህ አሪፍ ነው አሉ ደግሞ አለኝ፡፡ ማነው ያለው አልኩት፡፡ ምን ያረግልሀል አለኝ፡፡ ማንም ሌላ ሊሆን አይችልምና ኢዩኤል ነው አይደል? ብዬ በርግጠኝነት ጠየቅኩት፡፡ አዎ አለኝ፡፡ “ጸባዩ ይመቻል ግን ቶሎ ይናደዳል”፡፡ ከኢዩኤል ጋር ተመቻቸን አይገልፀውም፡፡ እኔ በባህርዬ ሰው ያበሸቀኝን ነገር ቶለሳ እንዳለው በጣም አሰላስል ነበር፡፡ ቤት ገብቼ “ለምን አለኝ? ምን አረግኩት?” እያልኩ የምናደደው ነገር ነበረኝ፡፡ ወደ ኢዩኤል ስመጣ ግን፣ ዛሬ ኢዩኤል ያናደደኝ ነገር፣ እልና ባፈላልግ ባፈላልግ፣ ባስብ ባስብ አስበው፣ አፈላልጌ አንድ ነገር አላገኝም፡፡ ከተገናኘን ጀምሮ በዚህ አመትስ? ምንም የለም፡፡ አላመንከኝም አይደል? ስመኘው የነበረውን አይነት ጓደኛ እንዳገኘሁ አስተዋልኩ፡፡ ትምህርት ቤት ሲናፍቀኝ አርብ ቀን አስጠላኝ፡፡

ቀኑ ሰኞ መሆኑን ሳስብ፣ አምስት ት/ቤት የምውልባቸው ቀናት እንደሚጠብቁኝ እያሰብኩ ስደሰት፣ የእረፍት ሰአት ደረሰ ሳልል ወደ ቤት ሰአት ሲደርስ the best year of my life አልኩኝ፡፡ ከመቼውም ጊዜ በላይ ትምህርት ቤት ስለ ትምህርቱ ሳይሆን ስለ ጓደኞች እንደሆነ የተማርኩበት አመት ነበረ፡፡

አንድ ቀን እኔ፣ ኢዩኤልና በረከት መንገድ ላይ እያወራን እየሄድን እኔ "ከዘመነ ሉቃስ ወደ ዘመነ ዮሐንስ እንኳን ተሸጋገራችሁ…" ምናምን አልኩኝ፣ አዲስ አመት ስለ ሆነ ሳይሆን እንዲሁ ያ አመት ዘመነ ዮሐንስ እንደ ነበረ እንደ ማውቅ ለመናገር ፈልጌ ነው መሰለኝ፡፡ ከዚያ ኢዩኤል ዘመነ ሉቃስ ዘመነ ዮሐንስ ምንድነው? አለ፡፡ በየአራት አመቱ ለአመታት የሚሰጥ ስም ነው ጳጉሜ… እያልኩ ላስረዳው ሞከርኩ፡፡ ኢዩኤል "እንዲህ አይነት ነገር የለም፣ የወንጌል መጽሐፍት ናቸው…" ሲል፣ በረከት "የማታቅ ከሆነ ዝም በል" አለው፡፡ ከዚያ እኔ ስቄ "እኔ ግን የማታውቅ ከሆነ ዝም በል አልልህም" ስለው ሁለቱም ዞር ብለው አዩኝ፡፡ "የማታውቅ ከሆነ ጠይቅ፡፡" አልኩት፡፡

ኢዩኤል ምን አይነት ሰው ነው ብዬ ራሴን እጠይቅ ነበር፡፡ እንዴት ሰው ይሄን ያህል አሪፍ ይሆናል? ለሁሉም ሰው እንደኔ ይሆን? ብዬ ራሴን እጠይቅ ጀመር፡፡ መልሱ ግን እንዲያውም በጣም መጥፎ ነበር፡፡ ስድቦቹ ሰውን ያሸማቅቃሉ፡፡ ማለት የገጠራዎች ስድብ ሆኖ ሳይሆን ሰውን ማብሸቅ የኔን ያህል የሚችል የለም የሚል አይነት ሰው ነበር፡፡ ኢዩኤል ልገምት ከምችለው በላይ በጣም ተሳዳቢ ነበር፡፡ አሁንም አሁንም ደጋግሜ ልጆችን ሲሰድብ ሳይ በውስጤ ይህቺ ስድብ አንድ ቀን ለኔ መትረፏ አይቀርም አልኩኝ፡፡ እውነቴን ነው፣ ብያለሁ፡፡

አቅመኛው ወንዴ ከመጠን በላይ ራሱን ኮፍሶ ነበር፡፡ የትኩረት ማዕከል ለመሆን አስቦ ነበር፡፡ የኛ ክፍል ግን ለንደሱ አይነት ሰው የሚሆን ቦታ ያለው አልነበረም፡፡ ሊቀርበው የሚፈልግ ሰው አጣ፡፡ ክፍሉ እንዳስጠላው ከፊቱ ያስታውቅ ነበር፡፡ ስምንተኛ ክፍል ከድሮ ክፍል ተማሪዎች ጋር ቢሆን አብረን የገባነው፣ ታሪኩ ሌላ ይሆን ነበር፡፡ ተቀምጦ ከኢዩኤል ጋር ስናወራ እያየ ይናደዳል፡፡ ጓደኛዬ እንዳላለኝ ጠላኝ፡፡

9ኛ ክፍል ያልነበረኝን አመል አመጣሁ፡፡ መኀረር ሆነ ስራዬ፡፡ እነኢዩኤልና እነ በረከት ላይ፡፡ ፈተና ምናምን እኔ ባልኖር ከየት ታመጡ ነበረ? እኔ ነኝ ተሸክሜአችሁ ያለሁት አላቸው ነበር፡፡ ተው አትነርር ናቲ ይለኛል ኢዩኤል፡፡ በረከት ደግሞ "ጉራውን ጀመረ እንግዲህ" ይላል፡፡ ሁሌ፡፡

ቸርች፣ ትምህርት፣ አብረን የምንሄደው ዳግም ዩኒቨርሲቲ ሲሄድ ለብቻዬ ስለምሄድ የመሄድ ፍላጎቴ ቢቀንስም ያን ያህል አልደበረኝም፡፡ ያን ያህል፡፡ ዳግም ከሄደ ከጥቂት ጊዜ በኋላ የእምነት ማጽኛ ትምህርታችንን ጨረስንና ቅዱስ ቁርባን ለመውሰድ በቃን፡፡ ከዚያ የሚቀጥለው ድርጊ..ድርግ የአገልግሎት ት/ት ነበረ፡፡ ቄስ ኢብሳ ነበሩ የአገልግሎቱንም የሚያስተምሩት፡፡ ስንማር፣ ጥያቄ ስመልስ ምናምን ነው መሰለኝ አንድ ካሳሁን የሚባል ልጅ "ምንድነው አንተ መፅሐፍ ቅዱስ ትሸመድዳለህ እንዴ?" አለኝ፡፡ አንድ ቀን እንደዛ መባሌን እንደማልረሳ አውቄው ነበር፡፡ ነገሩ ግን ድሮ 5ኛ ክፍል ላይ ምናምን ሳነብ የነበረው እና የቄስ ኢብሳ ትኩረት ናቸው ከሌሎቹ ነጥሬ እንድወጣና ለዚህ የተጋነነ አድናቆት የዳረጉኝ፡፡ እሱ ብዙም ስለማያነብ የኔ ገርሞት ነው እንጂ እኔ መጽሐፍ ቅዱስን ብዙም አንብቤ አይደለም፡፡

2005 መጀመሪያ አካባቢ ዳያሪ ስፅፍ ነበር እንደገና፡፡ ሁለት ወር ነው እንደዚህ እንደጻፍኩት እሱንም አቃጠልኩት፡፡ የዳያሪው መጀመሪያ ላይ ደግሞ ሌላ አንድ እንዳቃጠልኩና ይሄኛውን በተአምር እንደማላቃጥለው ወይም እንደማልጥለው ገልጬ ነበር፡፡

ቤት፣ የአክስቴ ልጅ ፍሬ ትምህርቷን ጨርሳ ስራ ተቀጥራ ነበርና ከብዙ አመታት በኋላ ቤታችን ቤተሰባችን ብቻ የሚኖርበት ሆነ፡፡ ወደድኩት፡፡ ፍሬ ስትሄድ መቼም አለምዳቸዋለሁ ብዬ ያላሰብኳቸውን እንደ ወጥ መስራት አይነት ስራዎች መስራት ጀመርኩ፡፡ ቤት እኔ ነኝ የምወለውለው፣ ልብስ፣ ወጥ ደግሞ እናቴ ስራ ፊልድ ስትሄድ፡፡ ቢዚ መሆን ጀመርኩ ግን ወደድኩት፡፡ "ሳይሰሩ መብላት" እያለ የሚጨቀጭቀኝ ሰው አለነበረም፡፡ ቤት ውስጥ ሰላም ነገሰ፡፡ ደስተኛ ነበርኩ፡፡ ስራ ሳይነገረኝ እሰራ ነበረ፡፡ ቤት እናቴ ሳትነግረኝ የወለወልኩበት ጊዜ!

ከእናቴ ጋር በጣም ተቀራረብን፡፡ እንደዚህ እንቀራረባለን ብዬ አስቤ አላውም ነበር፡፡ ማታ እሷ ወጥ ስትሰራ አወራታለሁ፣ አስቃታለሁ፣ እቀልድባት ነበር፡፡ በጣም አወቀከኝ ትል ነበር፡፡ ማታ ሳወራት ሂድና አጥና ብላ ታባርረኝ ነበር፡፡ ከዛ እሄድና ቆይ ቆይ ብዬ ያልጨረስኩትን ነገር ሳወራ፣ እያወራኋት እቆያለሁ፡፡ ከእናቴ ጋር በጣም ተቀራረብን፡፡

መጀመሪያ ሴሚስቴር፣ ጠዋት ተምረን፣ ከሰአት ዝም ብዬ ትምህርት ቤት ብቻዬን እሄድና ሳር ላይ ምናምን፣ ወይ ክፍል ውስጥ እቀመጣለሁ፡፡ ከዛ ልጆች ይመጣሉ፡፡ ከመጣው ሰው ጋር የሆነ አጀንዳ እንከፍትና ሳወራ ውዬ ሲመሽ ወደ ቤት እገባለሁ፡፡ ብዙ ጊዜ ሚጣ ከት/ቤት ከገባች በኋላ (ከ10 ተኩል በኋላ) ነበር የምገባው፡፡ ቤቶች ከገቡ በኋላ(ከ11 ተኩል በኋላ) ምገባበት ጊዜም ነበረ፡፡ ከቤት ሲጠይቁኝ ላይብረሪ ነበርኩ እላቸው ነበር፣ ወይም ስንማር ነበረ፡፡ እውነታው ግን ከሰአት ሜክ አፕ ተጠርተን ት/ት ያለን ጊዜ ራሱ እኔ ገብቼ መማር ትቼ ውጪ ከልጆች ጋር ሳወራ እውል ነበር፡፡

ላይብረሪ፣ እኔ የላይብረሪ ወዳጅ አልነበርኩም፡፡ ቤተሰብ መምሪያና ኢሉ ግሪን ሄዶ ማንበብ ሙድ የሆነበት ጊዜ ነበር፡፡ ለጥናቱ ሳይሆን ለሙድነቱ የሚሄዱ ልጆች ነበሩ፡፡ እኔስ? ሌሎች ጓደኞቼ ሄደው ሲያጠኑ እኔ፣ አይ ሰው የሚበዛበት ቦታ አይመቸኝም፡፡ እንዲህ አይነት ሰው የሚበዛበት ቦታ እንኳን ማጥናት፣ መቀመጥ እራሱ እፈራለሁ እል ነበረ፡፡

ብቻ ገነት ነው እንዴ ያለሁት? አልኩኝ፡፡ በፊት በመደበኛነት የሚያጨናንቁኝን ነገሮች እንዴ ስለዛ ነገር ሳላስብ ቆየሁኮ እንዴት ይሆናል? ቆይ ግን እንቅልፍ እንደዛ ይጣፍጣል? ስተኛ ደቂቃም ያልተኛሁ ነበር የሚመስለኝና ከንቅልፌ ተነስቼ ስንጠራራ የሆነ ደስ የሚል ስሜት ይሰጠኛል፡፡ በቃ የሰላም እንቅልፍ ታቃለህ? ት/ቤት ደስተኝነቴ፣ ሳቄ በቃ አፈንግጦ ወጥቶ ሌሎቹን ተማሪዎች እስከማናደድ፣ አለ አይደል፣ በቃ እኔ ስፍነከነክ ሲያዩኝ ምን ተገኘና ነው እንዲህ የሚገለፍጠው አይነት አስተያየት እስኪያዩኝ ድረስ፡፡ የተማሪ ህይወት ውስጥ ትምህርት ቤት በጣም ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡

ዮሴፍ ከሰአት ከሰአት ቤት እየመጣ ይጠራኝ ነበር፡፡ በፊት እሄድ ነበር፡፡ የሆነ ጊዜ ግን መሄድ ትቼ ቤት መተኛት ጀመርኩ፡፡ የቀን እንቅልፍ ሲጣፍጥ! መጥቶ ሲጠራኝ ብዙ ጊዜ እኔ እየተኛሁ እሆንና ወጥቼ ሳናግረው ተኝተህ ነበር አይደል ይለኝ ነበር፡፡ አዎ እለዋለሁ፡፡ እንዲሁ እየጠራኝ እየጠራኝ አንድ ቀን " አይ ናቲ፣ አንተን መሆን ነበር" አለኝ፡፡ እንደዚያ መባሌን እንደማልረሳ አውቄው ነበር፡፡

ትምህርት ቤት እኔ በጣም ወሬኛ እንደሆንኩ የተረዳሁት እኔ ትንሽ ዝም ስል ልጆች(እነበረከት) ዛሬ ደግሞ ዝም አለ ምናምን ሲሉ ነው፡፡ በጣም ሳወራ እውላለሁ ማለት ነው፡፡ አንድ ቀንጆዎቹ የተሰኘ መፅሀፍ ክፍል ውስጥ ለማንበብ ሞክሬ ከኢዩኤል ጋር እያወራን ስለምንውል ዝም ብሎ ይዞ መሄድ ሆነብኝና ትቼው ቤት ውስጥ ብቻ ማንበብ ጀመርኩ፡፡ማነው በንደዚያ አይነት ሀሴት ውስጥ ልቦለድ የሚያነብ? መጽሐፉ በዚህ ዘመን እየተወለዱ ያሉ ልጆች ቀንጆዎች ናቸው በማለት ነበር የሚገባደደው፡፡ ቀንጆዎቹ፡፡

የኢዩኤል የ8ኛ ክፍል ጓደኛ 9ኛ ክፍል የገባው እኛ ጋር ሳይሆን ሌላ ት/ቤት (በተለምዶው ሀይስኩል) ነበረና ከትምህርት ቤቱ ልጆች ጋር ተጃልሶ ኢዩኤልን ጣል ጣል ሲያረገውና ሲያርቀው ኢዩኤል ለኔ ነበር የሚያማርረው፡፡ ታዲያ እሱ "ስጠራው እመጣለሁ ብሎ ዴቭ ጋር ሄደ" ምናምን ሲለኝ ተው በቃ ያልፋል ሌላ ጓደኛ ይገኛል እያልኩ አፅናናው ነበር፡፡ ሌላ ጓደኛ፡፡

ት/ት፡ አስተማሪ አላዳምጥም፣ ሁሉም አስተማሪ ከዱሪዬ ልጆች ጋር ገጥሞ ተበላሽ ይል ነበር ግን ቤት አጠና ነበር፡፡ ጥናትን የወደድኩበት አመት ነበር፡፡ የማጠናው ደግሞ ፈተና አለ ሲባል ከሁለት ቀን በፊት ነው፡፡ ሂስትሪ ምናምን እንዲሁ እያነብብኩ ለመያዝ ስሞክርና ሁለቴ እንኳን ሳላነብ ሲያዝልኝ፣ ገረመኝ፡፡ እንዳነበብኩት፣ ይያዝልኛል፡፡ ረጅም ብዙ ኮማ ያለው አረፍተ ነገር ሲያዝልኝና ለወር ስማር የነበረውን ዞር ብዬ አይቼ የማላውቀው ከሌሊት 9 ሰአት እስከ ጠዋት ባለችው 4 ሰአት ውስጥ ሲያዝልኝ፣ ቆይ እኔ ማነኝ ነበር ያልኩት፡፡ ጉብዝናዬ አስገረመኝ፡፡ እንደዛ ሆኜ ደግሞ አላውቅም፡፡ ትምህርት ቤት ልጆች ምንድነው ፈተና መድፈን አይሰለችህም እንዴ አውቀህ እንኳን እጣ እንጂ ብለው እስኪቀልዱብኝ፡፡ በዚያ አመት አቨሬጅ 94 ነበር ያመጣሁት፡፡ በጣም ደስተኛ መሆኔና አዕምሮዬ የሚጨነቅበት ነገር አለመኖሩ፣ ትምህርትን በጣም ቀላል ነገር አደረገልኝ፡፡

ከአቡሽ(ሱራፌል) ጋር ከትምህርት ቤት አብረን እንገባለን፣ ብዙ ግንኙነት አልነበረንም፡፡ የሰፈር፣ የጎረቤት ህይወቴ ሲሞት፣ ሲጠፋ ግን ይታወቀኝ ነበር፡፡ የእንደሻው ት/ቤት መሄጃ ላይ አንዲት ባለሱቅ ነበረች፡፡ አሪፍ ደስ የምትል ልጅ ነበረች፡፡ ከሆነ ጊዜ በኋላ እንደ በፊቱ አሪፍ መሆኗ ቀረ፡፡ እኔ ጸባይዋ ይመስለኝ ነበር አሪፍነቷ፡፡ ምን አርጌያት ነው የተለወጠችብኝ ብዬ እራሴን እጠይቅ ነበር፡፡ በፊት ለምን አሪፍ ሆነች አሁን ለምን ተቀየረች? በፊትኮ በቃ ወሬ ስለምታበዛብኝ ምናምን ነገር ትደብረኝ ነበር፡፡ ከጊዜ በኋላ ልገዛት ሳይሆን ልለምናት የምሄድ አይነት ነገር ሆነችብኝ፡፡ ምንድነው ብዬ ለረጅም ጊዜ ራሴን የለውጡን ምክንያት ስጠይቅ፣ ለካስ በፊት ሱቋ ውስጥ ሆና ከእንደሻው ት/ቤት ከነአሊ፣ ከነአቡሽ ጋር ስገባ ታየኝ ነበር፡፡ 9ኛ ክፍል ስገባ ደግሞ ወደዚያ የምሄደው ራሱ ሱቅ ስሄድ ብቻ ስለነበረ ከማንም ጋር ስለማታየኝ ነው፡፡ ይሄ የጸባይዋ ለውጥ እንቆቅልሽ የተፈታልኝ 10ኛ ክፍል ላይ ነው፡፡
ሌላ ደግሞ አንድ የጎረቤታችን ልጅ በፊት ስታየኝ አትጠራኝም፡፡ ስምንተኛ ክፍል ስገባ በጓሮ በኩል ባየችኝ ቁጥር ትጠራኝና ሰላም ትለኛለች፡፡ በፊት የማትጠራኝን ምን ተገኝቶ ለምን እየጠራች ሰላም እንደምትለኝ መልሱን ሳላገኝለት እኔ 9ኛ ስገባ እኔን መጥራት አቆመች፡፡ ለካስ እሷ ደግሞ 8ኛ ክፍል ስማር ከሰፈር ልጆች ጋር የፈጠርኩትን ግንኙነት፣ ከብዙ ልጆች ጋር መጎዳኘቴን አይታ ነው ለካስ እኔን መጥራት የጀመረችው፤ ከዛ 9ኛ ክፍል ከሰፈር ልጆች ጋር ያለኝ ግንኙነት ሲቆራረጥ አቆመች፡፡ የሰውን ሳይኮሎጂ እየተረዳሁ ነበር፡፡ ሰዎች ማህበራዊ ህይወታችንን አይተው እንደሚመዝኑን፡፡

9ኛ ክፍል አንድ የሚያንገበግበኝ ነገር ቢኖር የዲሽ ጉዳይ ነው፡፡ ግዙ አንገዛም፡፡ ያዘናጋችኋል፡፡ ኤልሻዳይን ብናይ ደስ ይለናል ግን ብር የለንም፣ ኤልሻዳይን ብናይ ደስ ይለናል ግን ከት/ታችሁ ትዘናጋላችሁ፡፡

ዮሴፍ፣ ከት/ቤት ስንለቀቅ መጥቶ ይጠራኝና አብረን እንሄዳለን፡፡ የኛ ቤት ለትምህርት ቤት በጣም ቅርብ ነው፡፡ በዚያ ላይ ክፍላችን ይራራቃል፣ ያን ያህል ቅርርብ አልነበረንም፡፡ ለምን እየመጣ እንደሚጠራኝ ግራ ይገባኝ ነበር፡፡

ዮሴፍ፣ እንደአዳ ሁሉ ቸርች ወጣቶች እንድሄድ ይጨቀጭቀኝ ነበር፡፡ ዛሬ ወጣቶች አትሄድም፣ አብረን እንሂድ፡፡ ከሰአት ተጠርተን ወደ ቤት ስንመለስ ምናምን ቤቱ ቸርች አጠገብ ነበርና ና እንሂድ ይለኝ ነበር፡፡ እኔ ደግሞ አይ ስራ አለኝ፣ ሰው ቤት የለም እያልኩ አሳብብ ነበር፡፡ ወጣቶች መሄድ እንዳለብኝ አውቀዋለሁ ግን እፈራ ነበር፡፡ አንድ ቀን ተስማማሁና እሁድ ቀን አስር ሰአት ላይ ከሱ ጋር ቸርች ግቢ ለመገናኘት ተስማማን፡፡ አስር ሰአት ተኩል ነበር ከቤት የወጣሁት፡፡ስደርስ ገብተው ነበር፡፡ መግባት ፈራሁ፡፡ የሆነች ልጅ እኔ መግባት ፈርቼ ስቆም አየችኝና ግባ እንጂ ለምንድነው የምትቆመው? አለችኝ እንደፈራሁ ግን ገብቷት ነበር፡፡ አብሬአት ገብቼ መጨረሻ ላይ ተቀመጥኩ፡፡ ዮሴፍ ከቸርች ልጆች ጋር ተቀምጦ ነበር፡፡ ፕሮግራማቸው እውነትም የወጣቶች ይመስል ነበር፡፡ በፊት የወጣቶች ፕሮግራም ሲባል ከእሁዱ ፕሮግራም በምንድነው የሚለየው ብዬ ለማወቅ እጓጓ ነበር፡፡ ግን ወጣቶች ወጣቶች ይሸት ነበር፡፡ ያን ቀን ከመደበኛ ዝግጅቶች፣ ከመዝሙር፣ ከጸሎት፣ ቃል ከመካፈል ባሻገር የተለያዩ አዝናኝ ዝግጅቶች ነበሩ፡፡ የሚያዝናና ገጠመኝ ተብሎ አንዱ ተነስቶ ገጠመኙን ተናገረ፡፡ ካርድ መሙላትም ነበረ፡፡ አንድ ሰው የ25 ብር የሞባይል ካርድ ቁጥር ይናገራል፣ በፕሮግራሙ ላይ የተገኘነው ደግሞ ሰምተን እንሞላለን፡፡ ያው በሰላሳ አርባ ከሚቆጠሩ ሰዎች ካርዱ ለአንድ ሰው ብቻ ይገባል፡፡ የገባለት ሰው እንደገባለት ይናገራል፡፡ እኔ ያው ስልክ አልነበረኝም፡፡ አንዳንዴ ግጥም፣ አንዳንዴ ድራማ ይኖራል መሰለኝ፡፡ አዳን ወጣቶች መምጣት ጀመርኩ ስለው፣ አይቼሀለሁ አለኝ፡፡

አንድ ጎረቤታችን ዲሽ ሲገዙ እኛ ቤትም ከነሱ ጋር ተመካክረው ገዙልን፡፡ ጊዜው የሴሚስቴር እረፍት ነበር፡፡ እኔና ሚጣ ደስ አለን፡፡ ፊልም ማንቀርቀር ጀመርኩኝ፡፡ ጠዋት ትምህርት ቤት ውዬ ከሰአት ፊልም፡፡ ት/ቤት ከሰአት መሄድ አቆምኩኝ፡፡ ለትምህርት እንኳን ስንጠራ፡፡ ፊልም ማየት ተመቸኝ፡፡ ዮሴፍ እኔ ጋር ሲመጣ ሪስሊንግ ላይ አርገው ምናምን አይለኝም? አኔ ደግሞ ሪስሊንግ እንዴት እንዳስጠላኝ! አልሰማህም አልኩት፡፡ እንኳን ሪስሊንግ፣ እንደዚህ ብዙ ምርጫ ሲኖር ከሰው ጋር ተቀምጦ፣ አንተ ሌላ ማየት እየፈለግክ እዚህ ላይ አርገው፣ እዛ ላይ ሲልህ ይደብርሃል፡፡

ጓደኞቼ እነዳግም፣ ዮሴፍ፣ "ምንድነው ልጁ፣ አንዳንዴ ያወራል፣ አንዳንዴ ዝም ይላል፡፡ ጸባዩ አይያዝም" እንዳላቸው ነገሩኝ፡፡ እኔ? ነበር ያልኩት፡፡ አንደዛ እንደሆንኩ አስቤ አላውቅም ነበር፡፡ ማለቴ አንዳንዴ እንደማወራና ሌላ ጊዜ ዝም እንደምል ማለት ነው፡፡ የሚቀያየር ጸባይ ስላለው ግን፣ እኔ ብዙ ሰዎች ጸባያቸው እንደሚቀያየር አውቃለሁ፡፡ ማለት፣ ዛሬ አሪፍ(nice) ይሆኑልኝና፣ ነገ ዛሬ አብሮኝ ሲስቅ ሲጫወት የነበረው ፊት ነገ ይለወጥና አንተን የሚያጥላላ የሚያርቅ ይሆንብሀል፡፡ ያኔ ታዲያ በውስጤ ኡ እገሌ አመሉ ተለዋዋጭ ነው እላለሁ፡፡ አመሉ ተለዋዋጭ ነው ብቻ፡፡ ብዙ ሰዎችን ጸባያቸው ተቀያያሪ እንደ ሆነ ስደመድም ይሄ ነገር የሰው ሁሉ ጸባይ ሊሆን ይችላል ብዬ እኔ አመሌ ይቀያየራል እንዴ ብዬ ራሴን ጠይቄ እንደዚያ እንዳልሆንኩ ደምድሜ ነበር፡፡ እንደዚያ አይነት ነገር የተናገረኝ ሰውም አልነበረም፡፡ ዮሴፍ የመጀመሪያው ነበር፡፡ ተሳስቼ ይሆን? የሰዎች እንጂ የራሳችን ክፋት ስለማይታየን ይሆን የኔ ተለዋዋጭነት ያልታየኝ? ሰዎች ስለሌሎች ክፋት፣ ስለራሳቸው መልካምነት ማውራት ስለቀሚናቸው ይሆን? ደስ ሲለኝ ተጫዋች፣ ስደበር ዘረመረተኛ ስለሆንኩ ሊሆን ይችላል፡፡

ዲሽ ስንገዛ ትርጉም ያልሆኑ እንግሊዘኛ ፊልሞች ማየት ጀመርኩ፡፡ የሚሉትን ለመስማት ትግል ነበር፡፡ ኮሜዲ ፊልሞችን እየመረጥኩ ነበር የማየው፡፡ ኮሜዲ ደግሞ ያው ትርጉም ይፈልጋል፡፡ ድሮም ፊልም በትርጉም በማየቴ ተሞኘሁ፡፡ የሚጠቀሙት አገላለፅ፣ ለያንዳንዷ በካሜራ አይን ውስጥ ለምትገባ እንቅስቃሴ ያላቸው ትኩረትና ጥንቃቄ፣ የትወና ብቃት፣ እነዚህ ሰዎች እነማን ናቸው ነበር ያስባለኝ፡፡ እነዚህ ፈረንጆች ይሄን ጥበብ ከየት ነው ያመጡት፡፡ በቃ፣ ፎቃቸው፣ ቤታቸው፣ ሌላ ብዙ የሚያስገርም ነገራቸው አልነበረም ያስገረመኝ፣ ፊልማቸው ነበር ያስደመመኝ፡፡ በቃ ጥበባቸው አስደነቀኝ፡፡
የቶም ሀንክስን FORREST GUMP ሳይ አድናቆቴ፣ በቃ ተው፣ የሆነ የቡና ሱስ ያለበት ሰው ቡና ሳይጠጣ በጣም ቆይቶ ሲጠጣ የሚሰማው ስሜት ነበር የተሰማኝ፡፡ ምርጥ ፊልም፡፡ ታይታኒክን እንደ አዲስ ደጋግሜ አየሁት፡፡ ድንቅ ነበር፡፡ አንድ የተረዳሁት ነገር፣ ፊልም ደጋግሜ ሳይ ሁሌ ስለ ፊልሙ የምረዳው የሆነ አዲስ ነገር ይኖራል፡፡ የሆነ በቃ ምን ልበልህ፣ ዝም ብሎ ታሪክ ሳይሆን ደጋግመህ ስታያቸው እንድትረዳቸው ተደርገው ነበር የሚሰሩት፡፡ Leonardo Dicapreo የተወነበትን CATCH ME IF YOU CAN አይተሀል? ምን ልበልህ? ሳየው በቃ አሰከረኝ ልበልህ፡፡ ፊልሞቹን ስለ ደራሲው እያሰብኩ ስለማይ ሊሆን ይችላል፡፡ በቃ፣ ሀሳቡ እንዴት መጣለት እያልኩ እደመማለሁ፡፡ዲያሎጎቹ ቅምም ያሉ፣ ደስ የሚሉ በቃ የሚደብር እንግሊዘኛ ፊልም ማግኘት አስቸጋሪ ነበር፡፡ እኛ ሀገር ፊልም ነው እንዴ የሚሰሩት?
ድሮ አንድ ተዋናይ ፊልም መስራት ይችላል ወይም አይችልም የምንለው፣ ሲያወራ ሽምደዳ እንደሆነ ከተነቃ አይችልም፡፡ እየሸመደደ ካልመሰለ ደግሞ ይችላል፡፡ ወደ ካሜራ የሚያይ ከሆነ አይችልም፣ ወደ ካሜራው የማያይ ከሆነ ይችላል ነበር የምንለውና ፈረንጆች ምንም ወደ ካሜራ ስለማያዩ እናደንቃቸው ነበር፡፡ ወደ ካሜራ ሲያዩ ለማየት ስራችን ብለን የምናይበት ጊዜ ነበረ፡፡ ነገሩ ግን ከኛ ድክመት እንጂ ከነሱ ብስለት አልነበረም፡፡ የኛ ሀገር አክተሮች ድሮ ት/ቤት እኛ ስንሰራ እንደነበረው ዲያሎግ እየሸመደዱ ሲየወሩ ምን ትለዋለህ? ቀስ በቀስ አሪፍ የእንግሊዘኛ ፊልም ተዋናይና የማይችለውን መለየት ጀመርኩ፡፡ ሁለቱም ወደ ካሜራ አያዩም፣ ሁለቱም ምርጥ ናቸው ግን እኔ እለያቸው ጀመር፡፡ እንዲሁ ብዙ ፊልም ሳይ ለራሱ እየገባኝ መጣ ማለቴ ሳይሆን፣ መጀመሪያ መቼም ዋና ተዋናይ ከሌሎቹ የበለጠ ክህሎት ይኖረዋል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ዋናዎቹ ያላቸውን ሌሎቹ የሌላቸውን ነገር ማጥናት ጀመርኩ፡፡ አትፍረድብኝ ፊልም ሰሪ እሆናለሁ ብዬ ሶሻል ለመግባት ቆርጬ ነበርና፡፡ እነ ROBERT DE NIRO(ANALYZE THIS, ANALYZE THAT) TOM HANKS(FORREST GUMP,CAST AWAY) LEONARDO DI CAPREO(TITANIC) SANDRA BULLOCK(THE BLIND SIDE, MISS CONGINIALITY) JULIA ROBERTS, JOHNNY DEPP(PIRATES OF THE CARRIBEAN, DARK SHADOWS), SCARLETT JOHANSSON(LUCY), CHRIS EVANS(CAPTAIN AMERICA), BEN STILLER(NIGHT AT A MUSEUM, LITTLE FOCKERS), WILL SMITH(THE PURSUIT OF HAPPYNESS, HITCH), JENNIFER ANNISTON(FRIENDS, WE'RE THE MILLERS), JENNIFER LAWRENCE(THE HUNGER GAMES) ,

JULIANNE MOORE(CRAZY STUPID LOVE), BRAD PITT(WORLD WAR Z, MR. AND MRS. SMITH), ANGELINA JOLIE(SALT, MALEFICENT, MR. AND MRS. SMITH), CAMERON DIAZ(BAD TEACHER, CHARLIE'S ANGELS), JACK BLACK(SCHOOL OF ROCK), ADAM SANDLER(GROWN UPS), MORGAN FREEMAN(THE SHAWSHANK REDEMPTION)), DENZEL WASHINGTON(THE EQUILIZER), NICOLAS CAGE(FACE OFF, NATIONAL TREASURE), MARK WAHLBERG(THE OTHER GUYS, TRANSFORMERS:EXTINCTION), JESSICA ALBA(FANTASTIC 4), MATT DAMON(BOURNE), EMILY BLUNT(AGES OF TOMORROW), EMMA STONE(THE AMAZING SPIDERMAN, EASY A), DREW BARRYMORE(CHARLIE'S ANGELS), CHANNING TATTUM(THE VOW, 21,22JUMP STREET, JOHN TRAVOLTA, JIMMY FALLON(ACCEPTED), JONAH HILL(JUMP STREET, THE WOLF OF WALL STREET), KATE WINSLET(TITANIC), TOM CRUISE(MISSION IMPOSSIBLE)… ፊልም ማየት ብቻ ሳይሆን በተለይ ከድርሰቱ፣ የታሪክ አወራረድ፣ ጠጠር ባለ፣ ደበቅ ባለ መንገድ የሚጽፉት ነገር፣ በጣም ያስደምመኝ ነበር፡፡ የታሪኮቹ በማያስነቃ መንገድ ተያያዥነት፡፡ እንግሊዘኛዬ በፍጥነት እየተሻሻለ ሲመጣ ይታወቀኝ ነበር፡፡ የሚወራው ነገር እንዲያመልጠኝ አልፈልግም፡፡ መጀመሪያ አካባቢ ጆሮዬ ላይ ሲጮሁ የነበሩት እንግሊዘኛዎች "እንደ ስድብ ሳይሆን እንደ ንግግራቸው የሚጠቀሙት አስጸያፊ ቃል፣ are you kidding me?, leave me alone!, are you out of your mind?, that's cool, awesome…"ን የመሳሰሉት ነበሩ፡፡ ቀስ በቀስ የሚነገሩትን ነገሮች ቃል ከቃል እየለየሁ፣ የሚሉትን እየሰማሁ፣ አንዳንዴ ቃላት ሲደጋገሙብኝና አስፈላጊ ሲመስለኝ ከዲክሺነሪዬ ትርጉማቸውን እየተረዳሁ፣ እንግሊዘኛዬን በፍጥነት እያሻሻልኩ መጣሁ እልሀለሁ፡፡
ሆን ብዬ ነበር የተዋናዮችን ስም የምሸመድደው፡፡ ሰው ላይ ለማካበድ ነው መሰለኝ፡፡
ብዙም ሳይቆይ በMBC MAX&MBC2 ሲታይ የነበረው The Insider ትኩረቴን ይስብ ጀመር፡፡ ፊልም ላይ ስለማውቃቸው ሰዎች ታሪክ፣ ስላሉበት ሁኔታ፣ አዲስ እየወጡ ስላሉ ፊልሞች፣ ስለ ዘፋኞች፣ ባጠቃላይ ስለ ሆሊውድ ነበረ፡፡ የሆሊውድ ውስጥ አዋቂ እንደ ማለት ነው፡፡ The Insider ስለ ፈረንጆች የመወዛገቡን በር የከፈተልኝ ሾው ነበረ፡፡ ፊልም ላይ የማያቸው፣ ሲጨፍሩ፣ ሲደንሱ፣ ሲስቁ የማያቸው ተዋንያን የተወሳሰበ ሕይወት እንዳላቸው አስተዋልኩ፡፡ Robin Williams እራሱን አጠፋ ተባለ፡፡ ብዙ ፊልሞቹን አይቻለሁ፡፡ በጣም አስቂኝና በሆሊውድ የተከበረ ሰው ነበረ፡፡ ለምን ራሱን ያጠፋል? ሌላው እሺ ይሁን፣ ሮብን ዊሊያምስ ለምን ራሱን ያጠፋል? እኔ እነ ፍልፍሉ ሲቀልዱ ድሮ በቃ ደስተኛ ስለሆኑ ይመስለኝ ነበር፡፡ ሮብን ዊሊያምስ ደግሞ ከነፍልፍሉ በሺ ይሻላል፡፡ እንዴ ዝነኛ ነው፣ በሚሊየን ነው የሚቆጥረው፡፡ ብዙ ከሱ ጋር ፎቶ ለመነሳት የሚጫረሱ ሰዎች እያሉ ለምን ራሱን ያጠፋል?
ሌላ ጊዜ ሊንዚ ሎሃን(Lindsay Lohan) ብዙ ፊልሞቿን ያየሁላት የደስ ደስ ያላት ልጅ በአልኮል ሱስ ተይዛ ምናምን ፍርድ ቤት ቀርባ ካሜራ ፊት ስታለቅስ አየኋቸት፡፡ እንዴ እነዚህ ሰዎች ምን ጎደለን ብለው ነው? እኔ ድሮ ፈረንጅ የሚያለቅስ ራሱ አይመስለኝም ነበር፡፡ ምቾት ነው፣ ምን የሚያስለቅስ ነገር አለ? ምኑም እንዳሰብኩት እንደ ሰማሁት አልመስል አለኝ፡፡ ስለ ፈረንጆች ለማወቅ ጥረት ሳረግ ይታወቀኛል፡፡ ዘ ኢንሳይደር ላይ ኢንተርቴይመንት ቱናይትን ጨመርኩ፡፡

MTV ላይ ደግሞ ዘፈን፣ የተለያዩ ሾዎች፣ እነ ፍሬንድ ዞን፣ ዲዛስተር ዴት፣ ሪዲኪለስ፣ I used to be fat፣ teen cribs፣ super sweet sixteen ምናምን ይታዩ ነበር፡፡ ደስ ይሉ ነበር ሾዎቹ፡፡ ሳያቸው ግን ይገርሙኝ ነበር፡፡ ሁሉም፣ ያለቅሳል፡፡ ምንድነው እነዚህ ፈረንጆች እምባቸው አይናቸው ላይ ነው ማለት ነው? አልኩኝ፡፡ በየጣብያው የሚያለቅስ ፈረንጅ ሳይ፣ ጎንበስ ቢሉ ዝም ብሎ እምባቸው የሚፈስ ነበር የመሰለኝ፡፡ ፍሬንድ ዞን ጓደኛ(best friend)ቸውን የሚያፈቅሩ ወጣቶች(ቲኔጀሮች) እንደሚወዷቸውና እንደማይወዷቸው የማያውቁትን ጓደኛ የፍቅር ጥያቄ የሚጠይቁበት፣ ወይ ጓደኛቸውን ፍቅረኛ ሲያደርጉ ወይም ከጓደኛቸው ጋር ለዘለአለሙ ሲለያዩ የሚያሳይ ሪያሊቲ ሾው ነው፡፡ ዲዛስተር ዴት ላይ ደግሞ ተዋናዮች ናቸው፣ ሰውየው የሚጠላውን ነገር እየሰሩ ማቃጠል ነው፡፡ ሪያሊቲ ሾዎቹን ሳያቸውና ከማያቸው ፊልሞች ሳልፈልግ የፈረንጆችን ህይወት ማጥናት ጀመርኩኝ፡፡ ስለ ፈረንጆች ብዙ ይወራል፡፡ የትኛው እውነት እንደሆነ፣ የትኛው ትክክል እንዳልሆነ፣ ምቾት በተትረፈረፈበት አለም ህይወት ምን እንደምትመስል መመርመር ጀመርኩ፡፡ በአሜሪካ ብወለድ ምን አይነት ህይወት እንደምመራ፣ የተገኘችውን አጋጣሚ ሁሉ እየተጠቀምኩ መፈተሽ ጀመርኩ፡፡ ስለ አሜሪካ ስሰማ ያደግኩት በደስታና በተድላ ኖሩ ታሪክ እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ፡፡ ከልጅነቴ ማወቅ ስፈልገው የነበረ ነገር ስለነበረ ነው፡፡ ከፍቅር ህይወት እስከ ሀይማኖት፣ ከገንዘብ እስከ ት/ት፣ ከፍልስፍና እስከ ፖለቲካ፣ ከማህበራዊ እስከ ሀገራዊ በገዛነው ዲሽ፣ በፊልሞች፣ በሾዎች፣ በተለያዩ አጋጣሚዎች ፈረንጅነትን መመርመር ጀመርኩ፡፡ በርግጥ ትርጉም መጽሀፍት ማንበብ የጀመርኩ ጊዜ ነው፣ አሀ ፈረንጆች እንዲህ ናቸው እንዴ ማለት የጀመርኩት፡፡ ከዲሳስተር ዴት ላይ ፈረንጆች ብላይንድ ዴት የሚሉት ነገር እንዳላቸው ተረድቻለሁ፡፡ ዴት ምን እንደሆነ ራሱ ከዲዛስተር ዴት ነው የተረዳሁት፡፡ ብላይንድ ዴት ማለት የማይተዋወቁ ወንድና ሴትን የሚያውቅ ሰው ሁለቱን እንዲቀጣጠሩ የሚያደርግበትና፣ እገሌ ማለት አንተ ነህ? አንቺ ነሽ? ተባብለው ከተዋወቁና ካወሩ በኋላ ከተመቻቹ የሚጠባበሱበት ዴት ነው፡፡

ሰው ሲሰድበኝ ወይም ሲያስቀይመኝ በጣም ከመናደድ ያለፈ ምንም የመልስ ምት ምናምን መስጠት አላውቅም፡፡ ደግሞ ንዴቱ እንዲሁ በቀላሉ አይለቀኝም፡፡ ትምህርት ቤት ጠዋት የተሰደብኩትን ቀኑን ሙሉ ስናደድ፣ ስተኛ ስለሱ አያሰብኩ ነበረ፡፡ በተለይ ስተኛ ስለዛች ያን ስለተሰደብኳት ስድብ እያሰብኩ ነው፡፡ አንድ ቀን በረከት አጠገቤ ተቀምጦ ሲያናድደኝ ዋለ፡፡ ሰው መልሶ አይሳደብም? ዝም ብዬ ስናደድ

እውላለሁ፡፡ ተው በረከት ተወኝ፡፡ እየተናደድኩለት እንደ ሆነ ሲያውቅ ባሰበት፡፡ ሲብስበት፣ በዚህ እስክሪብቶ ነው የምወጋህ አልኩት፡፡ የምቀልድ መሰለው መሰለኝ፣ ምንም አላለኝም፡፡ ሲብስበት ትንሽ ቆይቶ እጁን በሆዱ(በነጬ በኩል) ዴስክ ላይ እንዳረገው በእስክሪብቶዬ ወጋ አረግኩለት፡፡ ደማ፡፡ ያስጠላ ነበር፡፡ አስተማሪው ይውጣ አልለቅህም አለኝ፡፡ በናትህ ተው እንዲህ የሚሆን አልመሰለኝም አልኩት፡፡ አልሰማኝም፡፡ ሊመታኝ ስላሰፈሰፈ አልሰማኝም፡፡ ከሰአት እንደባደብ እልኩት፡፡ አልሰማኝም፡፡ ጠርቼው ልቀር እንደሆነ ገብቶት ነበር፡፡ የመጨረሻ ፔሬድ ነበረና ሲደወል እሮጬ እነአቡሽ ክላስ ሄድኩኝ፡፡ አላስጣለኝም፡፡ መጣና ያዘኝ፡፡ ልጆች ተለቅቀው አያዩን ነበር፡፡ ተው አልኩት፡፡ ያዘኝ፡፡ እጄን ሲዘረጋብኝ በእግሬ እግሩን አልኩት፡፡ ከዛ ያዘኝ፡፡ ብዙም ሳንነካካ ድብድባችን ቆመ፡፡ ልጆች ምንም ተደባድቦ የተነሳ ሰው አትመስልም አሉኝ፡፡ የሚደባደቡ ልጆች እኔ በጣም ነው የሚያናድዱኝ፡፡

ያን ቀን ነበር፣ እኔ ሰው ሲሰድበኝ እንዴት ይሄን ያህል መመለስ ያቅተኛል ብዬ መናደድ የጀመርኩት፡፡ ከዚያ ወዲህ ሰው ሲሰድበኝና የምለውን ሳጣ መብሸቅ ጀመርኩ፡፡ ለምሳሌ አንድ እሁድ ቀን ማታ ኢዩኤል ወደኛ ሰፈር ከልጆች ጋር ወክ ለማረግ መጥተው እኔ ወተት ይዤ ስገባ ተገናኝተን ት/ቤት በነጋታው አንተ ህፃን ነህ እንዴ ወተት የምትጠጣው ሲለኝ ያለው ነገር አናደደኝ፣ በሰአቱ እሱ ትክክል እንዳልሆነ ባውቅም በዛች ቅጽበት ዝም ከማለት ሌላ ያልኩት ነገር አልነበረም፡፡ የሆነ ነገር ብዬ ብመልስለት ደስ ይለኝ ነበር ግን፣ የምለውን አጣሁ፡፡ በርግጥ ያቺ ኢዩኤል እኔን ማናደድ የጀመረበት ቀን ሳትሆን አትቀርም፡፡ “ህጻንማ ወተት የሚጠጣው ህጻን ብቻ ነው ብሎ የሚያስብ ሰው ነው” ማለት ነበረብኝ፡፡

ስም ጠሪያችን በጣም ትጉ፣ ከኔ ክፍል ማንም ማትሪክ አይወድቅም የሚል አይነት ስም ጠሪነትን ያከረረ አስተማሪ ነበረ፡፡ ምንም ያህል ሰነፍ ሁን በሁለት አመት ማትሪክ በግድ ታልፋታለህ ይልሃል፡፡ እኔን ገና እንደገባን፣ ከክፍል ስንተኛ እንደወጣሁ ጠየቀኝ፡፡ 2ኛ እንደሆነ ነገርኩት፡፡ 4፡፡ ካንተ ፎር እፈልጋለሁ ብሎ ፈረደብኝ፡፡

አስተማሪዎች እኔን ለስም ጠሪዬ መክሰስ ጀመሩ፡፡ አያዳምጥም፣ ሲያወራ ነው የሚውለው፡፡ ክፋቱ ደግሞ እኔ አለቃ የነበርኩ መሆኔ ነው፡፡ ስምጠሪያችን መጥቶ ራያ ቀየረልኝ፡፡ ወዴት? ከወረዳ የመጡ ተማሪዎችን ብቻ ወደ ያዘው የት/ት ሰራዊት፡፡ ከኢዩኤል ጋር ተለያየን፡፡ ያው እንደ ድሮ ሲያወሩ መዋል ቀረ፡፡ በኔ ቦታ በረከት ከኢዩኤል ጋር ማዘውተር ጀመረ፡፡ በረከት ደግሞ እኛ ስናርቀው ከሴቶች ጋር ይቀራረብ ነበርና እነሄለን፣ እነሜቲ፣ እነቅድስትን የኔ ቦታ ኢዩኤል ጋር መሆን ጀመሩ፡፡ በርግጥ እንደድሮ አይሁን እንጂ እኔም ያው እንዳለሁ አለሁ፡፡

9ኛ ክፍል አለቃ ብቻ ሳልሆን የክፍሉ የራያ መሪ ነበርኩኝ፡፡ ስበሰባ ምናምን ክፍል ውስጥ መምራት፣ ራያ የሚሉት ነገር ጥቅሙ ምን እንደሆነ ግራ ይገባኝ ነበር፡፡ በቡድን መስራት፣ ሰነፍ ተማሪዎችን ለማበርታት ቢሆንም ግቡ፣ ማንም ስራ ፈትቶ ማውራት ትቶ የሚጠናናላቸው የለም፡፡ ብቻ የሆነ ሰሞን ስም ጠሪያችን ቲቸር ዳዊት መጣና ከዚህ በኋላ በየሁለት ሳምንቱ አርብ እለት ትሰበሰባላቹ አለ፡፡ አስበው የቀኑ ት/ት የሚያልቀው 7 ሰአት ላይ ነው፡፡ ተሰብስበን ስለፀባይ ማሻሻል፣ መፅሐፍ ስለ ማምጣት ወዘተረፈ እንወያይ ነበር፡፡ የመጀመሪያው ስብሰባ ላይ ቲቸር ዳዊት ተገኝቶ ነበር፡፡ እኔና ከክፍላችን ሁለተኛ የምትወጣው ሳምራዊት የተባለች ጎበዝ ልጅ ደግሞ ስብሰባውን እንመራለን፡፡ በቀጣዩ ስብሰባ ዳዊት ሳትሰበሰቡ እንዳትሄዱ ስትጨርሱ የቃለ-ጉባኤውን ወረቀት ቢሮ አምጡልኝ ብሎን ሄደ፡፡ ከዚያ ልጆች ጥያቄ እንዲጠይቁ፣ አስተያየት እንዲሰጡ እድል ብንሰጥም የሚቆጣጠር አስተማሪ ስላልነበረ ያው ክፍሉ ተበጠበጠ አስተያየት የሚሰጠው ይቀልዳል፣ ሌላው በተቀመጠበት ያወራል፡፡ በዚህ መሀል ሄለን ጥያቄ ብላ እጇን አወጣች፡፡ እሷ እንደማትቀልድ ስለማውቅ በደስታ ነበር እድሉን የሰጠኋት፡፡ ወደፊት ተቀምጣ ነበርና፣ እኔም ሲገርመኝ ስለ ነበረው ነገር ነበር አሪፍ ጥያቄ የጠየቀችኝ፡፡ “አሁን በቃ በየሁለት ሳምንቱ አመቱን ሙሉ በዚህ ሰአት እየተሰብሰበን እንውላለን ማለት ነው?” ብላ ጠየቀችኝ፡፡ እእም አልኩኝ እንደ ባለ ስልጣን፡፡ እእምም.. ጥሩ ጥያቄ ነው፡፡ መልሱ እም...”አዎ” ነው፡፡ ስላት ሳቀችና አንተኮ ኮሜዲያን ብትሆን ያዋጣሃል አለችኝ፡፡

እኔ ከክፍሌ ልጆች ጋር መቀራረብ የጀመርኩት ከስድስተኛ ክፍል ወዲህ ነው፡፡ ታድያ ከሴቶች ጋር እንዲህ መቀራረብ አይነት መቀራረብ ኖሮኝ አያውቅም፡፡ ሴቶች ሰው ሲቀርባቸው ሰው ይንቃሉ የምለው ፈሊጥ ነበረኝ ብያለሁ፡፡ ድሮም እነ ሄለንና ኢዩኤል መሀል የገባሁ ግርግዳ የነበርኩ መሰለኝ፡፡ እኔ ከኢዩኤል ጋ ስነሳ እነሱ እሱ ጋር መሄድ ጀመሩ፡፡ ትንሽ ትንሽ ከነሄለን ጋር ተቀራረብን፡፡ በርግጥ ከኔና ከነሱ ማን ግርግዳ እንደሆነ አላውቅም፡፡ እነሱ ወይስ እኔ? ምንም ይሁን ማን ግን እነሱ ኢዩኤልን ሲቀርቡ እኔ ደግሞ የኢዩኤል ጓደኛ ስለነበርኩ ከነሱ ጋር ትንሽ መቀራረቤ አልቀረም፡፡

ቦታ ስቀይር ክፍል ውስጥ መጽሐፍ ማንበቢያ ጊዜ አገኘሁ፡፡ መጀመሪያ ከቡስካ በስተጀርባ የተሰኘውን መጽሐፍ አነበብኩ፡፡ ደስ ይላል፡፡ ስለዚያ መጽሐፍ ሰምቻለሁ፡፡ አሪፍ ነበር፡፡ ሌላ ደግሞ መግባትና መውጣትን ኢዩኤል ነበረውና ከሱ ተቀብዬ እንደገና አነበብኩት፡፡ የበፊቱን ያህል አስቂኝ ነበር፡፡ ልጆች እንደበፊቱ ሁሉ ይሄንንም አንብቤ ስስቅ ይገረሙ ነበር፡፡ ሄለን፣ ምንድነው ይሄን ያህል የሚያስቅህ ብላ እኔ ስጨርሰው መጽሐፉን ተቀብላኝ አነበበችውና፣ ይሄን አንብበህ ነው ለካ ስትስቅ የምትውለው ብላኛለች፡፡

አንድ ቀን ኖት ለመጻፍ ሌላ ክፍል ገብተን እኔ፣ ሜቲ፣ ነብዩ የሚባል ልጅና ቅድስት ተቀምጠናል፡፡ አሚር የሚባል ልጅ የእውቀት ማህደር የሚባል መፅሐፍ ይዞ መጥቶ እኔ እጅ ነበርና እንዲሁ እያገላበጥኩ አሳልፌ አሳልፌ ሳነበው ጀርባው ላይ አይዛክ ኒውተን ድንግል እንደነበረ እንደሞተ ተፅፎ ነበር፡፡ እኔ መጽሐፉንም ስለ ኒውተን ድንግልናም በፊት አንብቤአለሁ ግን አጠገቤ ለነበሩት ድምፄን ከፍ አድርጌ እንደገና

አነበብኩት፡፡ እሰኪ ብለው ተቀብለውኝና አዩት፡፡ ሜቲ እንዴት አወቂ? እንዴት ነው የሚታወቀው አለች፡፡ ሁላችንም ተስማማንና እንደማናውቅ ነገርናት፡፡ እንዲህ ተኝቶ ስለማወቅ፣ ስለማግባት እያወራን ቅድስት፣ ግንኮ ከማግባት አለማግባት ይሻላል አለች፡፡ ሜቲ ደግሞ "ኧረ አይሻልም" አለች፡፡ ቅድስት ወደኔ ዞራ አለማግባት አይሻልም? አለችኝ የሚስማማው ሰው በጠማው አዟዟር፡፡ አይሻልም አልኳት፡፡ ነብዩ ከዛ "እእ ተደብቀሽ እንትን ለማለት ነው አይደል?" አላት፡፡ ተናደደች፣ ምንም ግን አላለችም፡፡አልተከላከለችም፡፡ ድሮስ ምን ብላ ትከላከላለች? ገዳም መግባት ይሻላል ማለቴ ነው ካላለች በስተቀር፡፡

አባትና እናቴ ባሉበት ዲሽ ላይ ፊልም ማየት አይቻልም፡፡ ፊልም እንድናይ ፈቃዳቸው የነበረበት ጊዜ ትዝ አይለኝም፡፡ አባቴ እኔ ማታ ምናምን እነሱ ከተኙ በኋላ ፊልም ላይ ስል ሁሌ ይናደዳል፡፡ አንዳንዴ ሂድ ተኛ ይለኛል፡፡ አንዳንዴ ደግሞ እኔ እዛው ቲቪው ስር እንቅልፍ ይዞኝ ሄዶ 7 ሰአት ላይ ምናምን፣ መጥቶ ይቆጣኛል፡፡ ምንድነው፣ እዳ አለብህ እንዴ? እንቅልፍ ከያዘህ ገብተህ አትተኛም? ሱስ ይዞሃል ማለት ነውኮ ይለኛል፡፡ ቆይ የሚመጣው አመት ታገኛለህ፡፡ ዲሹ ሲነቀልብህ ምን እንደምታረግ እናያለን፡፡ አንተኮ እህትንም እያበላሸህ ነው ይሉኛል፡፡
እነሱ ከመጡ ኤልሻዳይ ነው፡፡ እኔ እነሱ በሌሉበት ኤልሻዳይ ላይ አድርጌ አላውቅም፡፡ ፊልም ነው በቃ፡፡ ከኤልሻዳይም ደግሞ የዶ/ር ገመቺስን ት/ት በጣም ነው የሚወዱት፡፡ ወላጆቼ ከሌሉ የማየው ባይሆንም የዶ/ር ገመቺስ ት/ት ከሌሎቹ ጆሮዬን ይስብ ነበር፡፡ጥሩ ተናጋሪ ነው፡፡ በቃ አንተ ፊልም ካልሆነ ኤልሻዳይ አታይም አይደል? ይሉኛል ከቤት፡፡ እኔ ግን ምንም ደስ አይለኝም ነበር፡፡ ደስ የሚሉኝ ዶ/ር ገመቺስ፣ የትዳሩ ሰውዬና ሀንፍሬ አሊጋዝ ነበሩ፡፡ እነሱንም ቢሆን ወላጆቼ ቤት ካሉ ያው አዳምጣቸዋለሁ ማለቴ ነው እንጂ ብቻዬን ስሆን አልሰማቸውም፡፡ ሌሎቹን ደግሞ በግድ ተቀምጠህ ስማ ተብዬ ተቀምጬም አላዳምጣቸውም፡፡

ለወንድሜ ስላየኋቸው ፊልሞች አውርቼ አላባራ ስል፣ አንድ ቀን "አንተ ፊልም ማየት ትልቅ ነገር ይመስልሀል እንዴ?" አለኝ፡፡ እንዴ? ይመስለኛል እንዴ? ኧረ አይመስለኝም፡፡
አንድ ቀን ከሰአት እንደ ወትሮው ፊልም ለማየት ብቻዬን ተቀምጬ ነበር፡፡ አንድ ፊልም እስኪጀምር እየጠበቅኩ ነበር፡፡ መድረስ አይቀርም ደረሰ፡፡ ትሽ! ፊልሙ አኒሜሽን ነበር፡፡ ስንት የሚታይ ነገር እያለ ማን ተቀምጦ አሻንጉሊት ያያል? አኒሜሽን እንደ ቶም ኤንድ ጀሪ አይነት አጫጭሮቹን ነው እንጂ እንዲህ ከረጅሙ ጋር ሁለት ሰአት ተቀምጦ ማን ይዳረቃል?
ፊልሙ መጀመሪያው ደስ ይላል፡፡ ልጁ ሮቦት ያገኛል ምናምን ነው ታሪኩ፡፡ ቆየት ያለ በንደነታርዛን አይነት ስእል የተሰራ አኒሜሽን ነበር፡፡ ተመቸኝ ፊልሙ፡፡ ኧረ አኒሜሽን በሰው ከሚሰሩ ፊልሞች አያንስም አልኩኝ፡፡
ከዚያ ሌላ ቀን በMBC MAX The Simpson's Movie የተባለ ሌላ አኒሜሽን ሙሉ ፊልም አየሁ፡፡ እነኛ ቢጫ ካርቱነኖች Fox Movies ላይ ፊልም ላይ ስቀይር ሁሌ ለምንድነው እነኚህን አስቀያሚ ነገሮች ማሳየት ትተው ትክክለኛ ፊልም የማያሳዩት የምላቸው ነበሩ፡፡ ቆይ ማነው ይሄን ስራዬ ብሎ ተቀምጦ የሚያይላቸው? ምናምን፡፡ የሮቦቱ ስለ ተመቸኝ፣ይሄም እንደዛው ሊመቸኝ ይችላል ብዬ ነበር ያየሁት፡፡ እውነታው፡ ያ ፊልም በህይወቴ ካየኋቸው ጥቂት ምርጥ ፊልሞች መሀል አንዱ ሆነ፡፡ አስቂኝ፣ የሚገርም፡፡ ዘ ሲምፕሰንስ፡፡ ያ ቀን ከThe Simpsons' ጋር የተዋወቅኩበት ብቻ ሳይሆን Fox Movies ላይ በየቀኑ የሚተላለፈውን የነዚህን የቢጫ ካርቱኖች ሾው በጉጉት ጠብቄ ማየት የጀመርኩበት፣ እንዲሁም ለአኒሜሽን ፊልሞች የነበረኝን ጥላቻ ወደ ፍቅር የቀየርኩበት ነበር፡፡ "ወይ ማወቅ ደጉ" አይደል የሚሉት? ከሰአት ከሰአት The Simpsons'ን ብቻ ሳይሆን በFox Movies Family Guyና American Dad ይታዩ ነበር፡፡ በፊትም ተፎግሬ ነበር፡፡ ሶስቱም ምርጥ ነበሩ፡፡ ጠዋት ት/ት ቤት ደስ ሲለኝ ውዬ ከሰአት ደስ የሚሉኝን እነዚህ በአሜሪካ ማየት ባህል የሆኑትን ከ9 እስከ 10 ተኩል ሶስቱን ምርጥ ኮሜዲ የቤተሰብ አኒሜሽኖች አይቼ እየሳቅኩ ውዬ... በቃ ህይወት ምሉዕ ነበረች፡፡ ብቻ ከሰአት ዝም ብዬ ተቀምጬ የምውለው ነገር አጉል ኩርትምትም የማለት ስሜትና ደጋግሞ ያዛጋኝ ነበር፡፡ ጠዋት ጠዋት ከእንቅልፌ ስነሳ ደግሞ ራስ ምታት ይለቅብኛል፡፡ ግን ት/ቤት ስሄድ ይተወኛል፡፡

አንድ ቀን ት/ት ጨርሰን፣ ወደ ቤት አብረን የምንገባው አቡሽ እየጠበቀኝ ነበር፡፡ ተማሪ ሌላው እንደኔ እየገባ፣ ሌላው እንደአቡሽ ጓደኛውን እየጠበቀ ነበረ፡፡ እኔ ወደ አቡሽ እየሄድኩ እያለሁ፣ መሬቱ ሳር ነበረና አንድ እግሬ በሳር በተሸፈነ ትንሽ ጉድጓድ ውስጥ ገብቶ እንደ መውደቅ፣ እንደ መወላከፍ ሲያረገኝ የሆነች ልጅ ከኋላዬ "ወይኔ" ብላ ጮኸች፡፡ ልጅቷን አውቃታለሁ፡፡ ደስ አለኝ፡፡ አቡሽና ብዙ ልጆች የሆነውን አይተዋል፡፡ ምስክሮች ብቻ ሳይሆኑ እነሱ አልጮሁም፡፡ እሷ ለምን ጮኸች? ግራ ሚያጋባ ነገር አለው፡፡ ሰው ስትወድቅ ሲስቅብህ እንጂ ልትወድቅ ስትል ሲጮህልህ ማግኘት ይከብዳል፡፡ በጣም፡፡ መንገድ ላይ ከአቡሽ ጋር ወደ ቤት እየገባን ሳስበው ሳስበውና ምክንያቱን ሳውጠነጥነው ታዋቂነት፣ በት/ቤት ግቢ ውስጥ ፌመስነት ተሰማኝ፡፡ አቡሽን ልጅቷ ለምን እንደጮኸች ጠይቄው ነበረ፡፡ ለምን እንደ ጮኸች ግን አልነገርኩትም፡፡

9ኛ ክፍል፣ ካፌ ቀርቶ ካስተሳሰቤ ይወጣሉ ብዬ የማላስባቸውን ስድቦች መሳደብ የጀመርኩበት አመት ነበረ፡፡ ት/ቤት ከነሄለን ጋር በስድብ ስንቀላለድ ትዝ ይለኛል፡፡ F word፣ የመሀሉን ጣት ማሳየት ምናምን፡፡

5ኛ ክፍል እያለሁ ነበር የኢየሩስ አባት አስተማሪ ተሰማ የቢሮ ላፕቶፕ ቤት ይዘው የመጡት፡፡ ያን ቀን ማታ ነበር ኢየሩስ ጠርታኝ እንዳየውና እንድነካው ያደረገችኝ፡፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እንደነሱ ኮምፒዩተር ይኖረን ዘንድ መመኘት የጀመርኩት፡፡ 9ኛ ክፍል ሁለተኛ ሴሚስቴር ወደ መጨረሻ፣ ማዘር PC ይዛ አልመጣችም? ተመቸኝ፡፡ የቢሮም ቢሆን ኮምፒዩተር ከቤት አለን ማለት ትልቅ ነገር ነው፡፡

ከአቡሽ ጋር ስንገናኝ፣ ከትምህርት ቤት ስንገባ ምናምን በቃ አወራለት ነበር፣ በተለይ ስለ ሴቶች፡፡ ስለ ሴቶች ሳወራለት ምንም ነገር አስተያየት አይሰጥም፡፡ ምስኪኑ አቡሽ እኔ እንዲህ አይነት ነገር አላውቅም የሚል አይነት ተማሪ ነበር፡፡ ከት/ቴ ሌላ ምንም አላውቅም ጸባየኛ ነኝ አይነት፡፡ ጎበዝ ጸባየኛ፡፡ እኔም ድሮ እንደዛ ነበርኩ፡፡ ልጆች ስለንደዚህ አይነት ነገር ሲያወሩ ዝም ነው፡፡ የባለጌ ነገር አታውራ ምናምን፡፡ ትምህርቴን እንጂ እንደዚህ አይነት ነገር አላውቅም ነበረ፡፡ የማያውቅ የለም ብለህ የምትከራከር ከሆነ ደግሞ "ጸባየኛ ነበርኩኛ"፡፡ እስከ 7ኛ ክፍል፡፡ እገሌ እገሊትን ጠበሰ ሲባል፣ እሱ እንዲህ አይነት ሰው አይመስለኝም ነበር፣ ተበላሸ ማለት ነው፡፡ ዱሪዬ ሆነች ማለት ነው እልና እጠላቸው ነበር እንዲህ አይነት ነገር የሚወራላቸውን ልጆች፡፡ ማለት ኤሌሜንተሪ ተማሪ ሆነው ምናምን እንዲህ የሚባልጉትን ማለት ነው፡፡ ይሄ በማህበረሰቡ ውስጥ ያለ ነገርና ከማህበረሰቡ የወረስኩት ነው፡፡ እገሊትን ከወንድ ጋር ስትሄድ አየኋት፣ ከወንድ ጋር ስትዘል ውጤቷ ተበላሸባት ምናምን ሲባል መስማት የተለመደና እንዲህ አይነት ነገር የተወገዘ ነበረ(ነው)፡፡ በቅርብ የማውቃቸው ልጆች የዚህ ውግዘት ሰለባ ሲሆኑ ከአውጋገሮቹ መሀል አንዱ ስለ ነበርኩ በትክክል አስታውሳለሁ፡፡ ስምንተኛ ክፍል ስገባ ፍቅር ያለ ነገር ነው፣ ችግር የለውም፣ ችግር ያለው ሴክስ ነው ማለት ጀመርኩ፡፡ ያ አመት የውግዘቱ ሰለባ የሆንኩበትም ጭምር ነበር፡፡ 9ኛ...

9ኛ ክፍል ላይ ኢዩኤል ሆነ ማን እንደ ሆነ አላስታውስም፣ ከስድብና ከማድረግ የቱ ነው ዱሪዬ የሚያስብለው ብለው ጠየቁኝ፡፡ የጠየቀኝ ሰው ለራሱ ስድብኮ በቃል ነው፣ ማድረግ ግን በተግባር ነው አለኝ፡፡ እኔ ደግሞ ማድረጉን ማንም ያረጋል፣ መሳደቡን ግን ዱሪዬ ነው የሚሳደበው አልኩት፡፡
ታዲያ ጓደኛዬ ሱራፌል(አቡሽ) እንዲህ አይነት ነገር አያውቅም ነበር፡፡ ሳወራለት አታውራ መስማት አልፈልግም አይለኝም፡፡ እንዲሁ ብቻ አልፎ አልፎ ጥያቄ ይጠይቀኛል፡፡ ታዲያ በጥንቃቄ ነው፡፡ በማወራለት ነገር እንደ ተሳበ እንዳስብ አይፈልግም፡፡ ንገረኝ በና፣ ደስ ሲል፣ ከዛስ፣ አይነት የመስማት ከፍተኛ ፍላጎት ያለው ሰውን ቃላትና ጥያቄዎች አይጠቀምም፡፡ ግን እኔ ሳወራለት በጣም እንደሚመሰጥ ምንም እንኳን ሊደብቅ ቢሞክር ነቅቼበት ነበር፡፡ በፊት ሳወራለት እንዲህ አይነት ነገር አታውራ ብሎ የሚያስቆመኝ እየመሰለኝ እየከበደኝ ነበር የማወራለት፡፡ ከዚያ እንዲያውም ደስ እንደሚለው እየተገነዘብኩ መጣሁ፡፡ ከዚህ ጸባዩ ሌላ ደግሞ አንዲት ልጅ አታምርም በና ስለው፣ ምኗ ነው የሚያምረው፣ እኔኮ እሷ ልጅ ታምራለች ስትሉ ትገርሙኛላቹ እያለ ቅስሜን ይሰብር ነበር፡፡ እኔ ደግሞ እናደድና "እና እሷ ካላማረች ማነው ታዲያ የሚያምረው? የግድ ህንድ ፊልም ላይ እንዳሉት ሴቶች መሆን አለባት እንዴ?" እለው ነበር፡፡ ትምህርት ሊያልቅ ሰሞን ከት/ቤት አየገባን "ስማ አንተ ስለ ቺኮች ምናምን እንዲህ አይነት ነገር አላውቅም ብለህ ማካበድ ትፈልጋለህ አይደል?" አልኩት፡፡ "አሁን እንዲህ ሰው ሲያወራልህ ጸባየኛ መሆን የምትፈልገው ስታድግ፣ ስታረጅና የማታወራበት ጊዜ ሲመጣ ምናምን ምነው ያኔ ባወራሁ ብለህ ይቆጭሀል" አልኩት፡፡ ይቆጭሀል!

በቀጣዩ አመት 10ኛ ክፍል ላይ ክረምቱን ያልኩትን ሲያሰላስል ውሎ ነው መሰለኝ "እኔ ከሁሉም የኛ ት/ቤት ሴቶች የምታምረኝ ልጅ አለች" አለኝ፡፡ ማን ነች አልኩት፡፡ አልነግርህም ለልጆች ትነግራለህ አለኝ፡፡ ከዚህ በላይ ምን የሚያጓጓ ነገር አለ? "አልናገርም አንተ አትናገር ካልከኝ" አልኩት፡፡ "አላምህንም፡፡ አንተን?" አለኝ፡፡ ማልኩለት፡፡ አንተ አትናገር ካልከኝ ለምን እናገራለሁ? አንተ አትናግር ብለኸኝ ምን ተናግሬብህ አውቃለሁ ምናምን፡፡ ተው አቡሽ እኔ ሁሉን ነገር አይደል የምነግርህ? እንዲህ አይነት ነገር ደብቄህ አውቃለሁ? ካስለመነኝ ካስለመነኝ በኋላ ስሟን ነገረኝ፡፡ እውነትም ልጅቷ ቆንጆ ነች፡፡ "ኧረ አቡሽ መለወጥ!" ብዬ አደነቅኩት፡፡ ይሄማ መነገር ያለበት ነገር ነው፡፡ እንጣላለን ይኸው ናቲ አለኝ፡፡ ውሸቴን ነው አልኩት፡፡ ምለሃል ይኸው አለኝ፡፡

ኢዩኤል ወደ መጨረሻ እንደ መጀመሪያው አልነበረም፡፡ አንዴ ስፖርት(HPE) እየተማርን ነበር፡፡ እኔ የአዲሱ ራያዩ ልጆች ጋር ተቀምጬ ነበር፡፡ ኢዩኤል ከሄለን ጋር ተቀምጧል፡፡ አስተማሪው ስለ ቮሊ ቦል ጨዋታ እያስተማረ ነበርና "ቮሊ ቦል ስንጫወት ኳስ መንካት የሚቻለው በምን በምናችን ነው?" ብሎ ጠየቀ፡፡ ኢዩኤል እጅ አወጣና በእጃችን፣ ካቃተን በቴስታ አለ፡፡ በርግጥ የኢዩኤል መልሰ ያስቃል፡፡ ካቃተህ፣ ምናምን ብሎ ህግ ጨዋታ ውስጥ፡፡ እኔ ደግሞ እጄን አውጥቼ በፈለግነው የሰውነት ክፍላችን ይመስለኛል" ስል ኢዩኤል "በፈለግነው ይላል እንዴ? እና ለምን እጅ ኳስ ተባለ ታዲያ?" አለኝ፡፡ ከሩቅኮ ነው ልጆች እየሰሙ፡፡ ምንም አላልኩት፡፡ ያቺ ቀን ግን 9ኛ ክፍል ላይ ኢዩኤል እኔን ያስቀየመበት ብቸኛዋ ቀን ነች፡፡ እሺ ሄለን ጋር ሆኖ በልጆች ፊት እንደዚያ ማለቱ ይሁን፣ ጸባዩ ነው፡፡ ምናለበት ትችቱ ትክክል ቢሆን? ምናለበት ቮሊ ቦል የምንጫወተው በእጃችን ብቻ ግን ካቃተን በቴስታ መመለስ ብንችል? ምናለበት ቮሊ ቦል መረብ ኳስ ሳይሆን እሱ እንዳለው እጅ ኳስ ቢሆን? መምህሩ የኔን መልስ አጸደቀ፡፡ ቮሊ ቦልን እንደፈለግን መጫወት እንችላለን፡፡ Mine: face of game, his: face of shame. እኔ እነዚህ እሱ እንደተምታታበት መረብ ኳስ የቱ እንደሆነና እጅ ኳስ የቱ እንደሆነ፣ Handball፣ Volleyball ሲባል ግር ይሉኝ ስለ ነበረ ነው አስቤበት ለመለየት ሞክሬ ያወቅኋቸው፡፡ ብቻ ያን ቀን በኢዩኤል ጉዳይ ላይ ቢጫ መብራት አበራሁ፡፡

ት/ት ሊያልቅ ሲል የክፍል ጓደኛዬ በረከት፣ እንዲህ አለ፡ "ኡፊ! ት/ት አለቀ"፡፡ እኔ ደግሞ መለስኩለት፣ "እኔ ደግሞ ማለቁ እየደበረኝ ነው፣ ባያልቅ እያልኩ ነው፣ አመቱ በጣም ፈጠነ"፡፡ በረከት እንዲህ ስል ሰምቶ ፈገግ አለ፡፡

ሌላኛው የሕይወቴ ምዕራፍ፡ ጭንቀት፣ ውድቀት፣ እንግልት፣ ሞት፣… ቃላት ያጣሁለት፣ መከራ፡፡

የ10ኛ ክፍል ምስጢራት (Mysteries of the 10th Grade)

ክረምቱን በዕቅዴ መሰረት ነበር ያስኬድኩት፡፡ ፊልም፣ ፊልም፣ ፊልም፡፡ ዲሽ ላይ ሳፈጥ መዋል፡፡ እውነትም ዲሽ፡፡ ሰዎች dish ሲባል ሳተላይት መሳብያው ሰሀን የምግብ ሰሀን ስለሚመስል ነው የተባለው ይላሉ፡፡ ለኔ ግን ዲሽነቱ አማርጬ የምበላበት የምግብ አይነት dish ስለሆነ ነው፡፡ የፈለግከውን አማርጠህ ስታይ፣ የአንድ ፊልም ዲስክ ኖሮህ በየልጆች ቤት ፊልም ለመቀያየር ስትዞር የነበረውን ጊዜ እንኳን የምታስታውስበት ጊዜ አይኖርህም፡፡
ከሚጣ ጋር እስኪበቃን ፊልም ኮመኮምን፡፡ እኔ በቀን ከአራት እስከ አምስት ፊልም የማይባቸው ቀናት ብዙ ነበሩ፡፡ በዚያ ክረምት ብዙ ፊልሞችን ነበር ያየሁት፡፡ ድንድንድርድንድንድር ድርንድር ድርንድር ድርንድር… The… Simpso…n's፣ American Dadና Family Guyም አያመልጡኝም ነበር፡፡ MTV ላይ Disaster date, friendzone…ንም አልቀሩኝም፡፡ አንድ ደግሞ የተለያዩ ሙያ ያላቸው ሰዎች ልጆችን አሰልጥነው የሚወዱትን ነገር እንዲያሳኩ የሚያደርጉት ሾውም ይመቸኝ ነበር፡፡ አዎ ሜድ(MADE) ነው የፕሮግራሙ ርዕስ፡፡ በብዛት ገርል ፍሬንድ መጥበስ ነው የሚያሳዩት፡፡ ከርታታ ማንም ዞር ብሎ የማያየውን ልጅ አለባበሱን ሙዱን ያስቀይሩት፣ ነቃ፣ ፓርቲ ምናምን ቤቱ እንዲያዘጋጅ ያስደርጉትና ያስጠብሱታል፡፡ አንድ ተዋናይ መሆን የምትፈልግ ቆንጆ ልጅ ተዋናይ መሆን ስትሰለጥን፣ ካየኋቸው መሀል ትዝ ይለኛል፡፡ አሰልጣኟ አንድ ዱባይ ዋን ላይ ሲታይ የነበረ ተከታታይ የግድያ ወንጀል መርማሪ ፖሊሶች(CSI: New York) ፊልም ላይ ካሉት መሪ ተዋናዮች አንዷ ናት፡፡ መጀመሪያ ቀን ትወና ላንቺ ምንድነው ብላ ሀይ ስኩል ተማሪዋን ልጅ ትጠይቃታለች፡፡ ማስመሰል ነው አለቻት፡፡ ስለ ራስሽ ንሪኝ አለቻት፡፡ ስለስሜትሽ(how you feel) ስለህይወትሽ አለቻት፡፡ ብቸኝነት አይሰማሽም? አይደብርሽም? እያለች አሰልጣኟ ብዙ አወራች፡፡ ልጅቷ it is just that I don't like to talk to people about my feelings እያለች ማልቀስ ጀመረች፡፡ ወይ ፈረንጆች! ዝም ብሎ መነፋረቅ ነው በቃ? "አየሽ ትወና ማለት የተሰጠሽን ገጸ-ባህርይ ማስመሰል ሳይሆን መሆን፣ እንዲሁ አሁን እንዳለቀስሽው እንዲሰማሽ ማድረግ(feel it) ነው" አለቻት፡፡ ልጅቷ ተፈትና አላለፈችም፡፡ ግን ታዋቂ መሆን… ሬድ ካርፔት ላይ ምናምን እያለች ስታወራ ነበር፡፡
ሌላ ደግሞ ጓደኛ ላልነበረው ልጅ ጓደኛ መፍጠር ነበር፡፡ ሜዳ ሄዶ እግር ኳስ እንዲጫወት አደረጉት፡፡ ጨዋታውን አልቻለበትም ግን ዋናው አላማ ተሳክቶለታል፡፡ ከሚጫወቱት ጋር ተመቻቸ፡፡ ሌላም ሌላም፡፡ ገርል ፍሬንድ የሚፈልገውን ሴቶች የሚወዱት አይነት ወንድ መሆንን ያስተምሩታል፣ አክተር መሆን የምትፈልገዋን፣ አክተርነት፣ ዘፋኝ መሆን የሚፈልጉትን፣ የዘፈን ግጥም መጻፍ…፡፡
MTV ያው በዘፈን ነው የሚታወቀው፡፡ ሚዩዚክ ቲቪም አይደል ከነ ስያሜው? ዘፈን አይቼ አይቼ እነአሊ፣ እነቅድስት(የክፍሌ ልጅ) የማይሰሙት ነገር ምኑ ደስ እንደሚላቸው ይገርመኝ ነበር፡፡ የማትሰሙትን ነገር ምኑን ነው የምታዳምጡት ብዬ እጠይቃቸው ነበር፡፡ አልፎ አልፎ የተመቹኝ ግን ነበሩ፡፡ ያ ክረምት የAriana Grande I gotta one less one less one less problem with out you "PROBLEM" የወጣበት ነበርና MTV ላይ ደጋግመው ያሳዩት ነበር፡፡ ታዲያ እኔና ሚጣ ሰምተን ሰምተን አይ ጋረ ዋን ሌስ ፕራብለም ዊዝ አውቹ የምትለዋን ክፍል ብቻ አብረናቸው እንል ነበር፡፡ love runs out፣ I'll be your light, your match, your burning sun, I'll be bright, in black that's makin' you run. And we'll feel alright, and we'll feel alright, 'cause we'll work it out. I'll be doin' this, if you had a dought, 'Til the love runs out, 'til the love runs out… የሚለው አሮጊት ፒያኖ የምትመታበት ዘፈንም ደስ ይለን ነበር፡፡

እኔ ፊልም እያየሁ ስስቅ አይታ ሚጣ ምን አሉ ብላ ትጠይቀኝና የሚያስቁትን ቦታዎች እተሮጉምላት ነበር፡፡ እሷ ማየት የምትፈልገው MBC3፣ ሞዲ ኪድስ ላይ የሚታዩትን እነቶም ኤንድ ጄሪን ምናምን ቢሆንም እኔ ስለማላያቸው እኔ የማየውን ሳትወድ አብራኝ ተቀምጣ ታያለች፡፡ ሁሌ ጭቅጭቅ ነው እንግዲህ፡፡ እዚህ ላይ አርግልኝ፣ እዛ ላይ አርግልኝ፣ ያንተ ሙብት ብቻ ነው እንዴ የሚጠበቀው? እኔ የፈለግኩትን ነገር ማየት አልችልም? ትላለች፡፡ አንድ ፊልም ሲጀምር አሁን ይሄን ምኑን ነው የምታየው? ይደብራል፡፡ ትልና ፊልሙ እየተሟሟቀ ወደ መሀል ሲደርስ ከኔ የበለጠ በፊልሙ ተመስጣ ትገኛለች፡፡ በፊልም መረጣ ደግሞ ታደንቀኛለች፡፡ ከጊዜ በኋላ ከሚጣ ጋር ፊልም እያየን የሚያስቅ ነገር ሰምቼ ስስቅ፣ እሷም እየሳቀች ነው፡፡ ጆሮዬንና አይኖቼን ማመን አቃተኝ፡፡ እሷ ስትስቅ ዞር ብዬ አያታለሁ፡፡ ምንድነው ያሳቀሽ? ያሉትን ሰምተሽ ነው? ምንድነው ያሉት? ስላት በትክክል ትነግረኛለች፡፡ ኧረ ሚጣ በዚህ እድሜ እንግሊዘኛ እየቻለች መምጣት!

ካየኋቸው ብዙ እንግሊዘኛ ፊልሞችና ሌሎችም እንደሾው ያሉ መዝናኛዎች ፈረንጆች ጋር አንድ ነገር እንደ ትልቅ ነገር እንደሚታይ አስተዋልኩ፡፡ ጓደኛ እንዲኖራቸው ይፈልጋሉ፣ ግን የላቸውም፡፡ ስለጓደኝነት ብዙ ያወራሉ፣ የጓደኛ ጥማት አለባቸው፡፡ ታድያ እኔ ይገርመኝ ነበር፡፡ ጓደኛ ይፈልጋሉ ግን ከጎረቤቶቻቸው ጋር እንኳን አይተዋወቁም፡፡ አንድ ጥያቄ ነበረኝ፡፡ የሚያናግራቸው የሚያወሩት ጓደኛ በጣም ካስፈለጋቸው ለምን ዝም ብለው የጎረቤታቸውን ቤት አንኳኩተው ቤቱ ገብተው ተዋውቀው፣ አያወሩም? ለምንድነው ይሄን ያህል የሚያካብዱት?

ከቤት ኧረ አጥና ቀጣይ አመት ማትሪክ ነህ፣ ካሁኑ ጀምር ይሉኛል፡፡እኔ ደግሞ አይሆንልኝም፡፡ ፊልም፣ ፊልም፣ ፊልም፡፡ በተደጋጋሚ አንተ ልጅ ምን ይሻልሀል? ያየኸው ነገር ይዞህ ይጠፋል፡፡ ማቻቻል አታውቅም ይሉኛል፡፡ ማንበብ ጀመርክ፣ የሀገር መጽሐፍ አነበብክ፡፡ አሁን ደግሞ ፊልም ጀመርክ፣ ይኸው ይዞህ ሄደ፡፡ ኧረ ማቻቻል እወቅበት ይሉኝ ነበር፡፡
በርግጥ ይሄ ማለት መጽሐፍ ማንበብ አቁሜ ነበር ማለት አይደለም፡፡በዚያ ክረምት፣ የእስር ቤት ታሪኩን ግብድዬ መጽሐፍ ፓፒዮን ከማሙሽ(የድሮ ሰፈራችን፣ የወንድሜ ጓደኛ) ተቀብዬና የጡት አባትን ቁጥር ሁለት አንብቤ ነበር፡፡ በተረፈ መምሪያ ውስጥ የነበሩ የልቦለድ መጽሐፍትን ከሞላ ጎደል ጨርሼ ነበር፡፡ ይደብራሉ ብዬ የተውኳቸው መጽሐፍት ስላሉ ብዬ ነው፣ ከሞላ ጎደል ያልኩት፡፡ ሌላ ደግሞ አንድ ሸቀጣ ሸቀጦች በሚሸጡበት ቤት መጽሐፍ እንደሚያከራዩ ሰምቼ መከራየት ጀመርኩ፡፡ አንድ መጽሐፍ በቀን 50 ሳንቲም ነበር፡፡ ባለ ሱቁ እኔ ዛሬ የወሰድኩትን በሁለተኛ ቀኑ ወይም በነጋታው ስመልስለት ይገረም ነበርና እንዲያውም በነጻ መስጠት ዳድቶት ነበር፣ እኔ የምከራይበት ቦታ ሩቅ ስለሆነ ገና እዛ መሄድ ደብሮኝ አቆምኩኝ እንጂ፡፡ በርግጥ አቋራጭ መንገድ አለው፡፡ በዋናው መንገድም ቢሆን በባጃጅ ነበር የምሄደው፡፡ ገንዘቡ አሳስቶኝ ሊሆን ይችላል፡፡ ወይ ፊልም ለማየት፡፡ ወይ በቀን በየሁለት ቀኑ የግድ ከቤት መውጣቱ አስጠልቶኝ፡፡
ከሱ የተከራየኋቸው ሶስቱም ወይም አራቱም መጽሐፍት የአጋታ ክሪስቲ ነበሩ፡፡ የወንጀል፡፡ የአጋታ Mirror crackedንና The Clockን የመሳሰሉት መጽሐፍት ያስፈራሉ፡፡ ደግሞ አንዱ መጽሐፍ መጨረሻ ላይ ውድ አንባቢ፣ የገጸ-ባህርያቱን ድርጊት በመከተል ገዳዩ ማን እንደሆነ እንደ ደረሱበት ተስፋ አደርጋለሁ ትላለች፡፡ ሲያናድድ፡፡ ፈጽሞ መገመት አትችልም፡፡ አዎ ካርታ በመጫወት በሚጀምረው መጽሐፍ ላይ ነው እንዲህ ያለችው፡፡ የሚገርመው ያን መጽሐፍ እንኳን ገዳዩን ልገምትና ልደርስበት፣ ታሪኩ ራሱ በትክክል አልገባኝም፡፡ የአጋታ ውስብስብ የግድያ ወንጀል ምርመራ ታሪኮች በትልልቅ የፖሊስ አካዳሚዎች ተማሪዎችን ለማስተማር እንደ ሪፈረንስ እንደሚጠቀሙባቸው ባንዱ መጽሐፍ መጀመሪያ ላይ ተርጓሚው ጽፎታል፡፡

መብራት ሲጠፋና የምሰራውን ሳጣ ምናምን ደግሞ በኮምፒዩተር ENCARTA KIDSን እጎረጉር ነበር፡፡ ፌስቡክም እንዳለ አለ፡፡ ያ ኢንካርታ ያጣው ነገር የለም አንትዬ፡፡ ሳይንስ፣ ታሪክ... በርግጥ ኢንካርታ ፕሪሚየምንም አይቻለሁ፡፡ ግን እዚያ ላይ የተፃፉት ነገሮች ረጃጅምና በጥልቀት የተጻፉ ስለሆኑ የህጻናት የሆነውንና አጠር አጠር ተደርጎ የተጻፈውን ኢንካርታ ኪድስን መረጥኩኝ፡፡ ከጊዜ በኋላ ኢንካርታ ፕሪሚየምንም ማንበብ ጀመርኩኝ፡፡ ከሁሉም የሳበኝ የአሜሪካ ፕሬዝዳንቶች ታሪክ ነበር፡፡ ስልጣን ላይ ከመውጣታቸው በፊት ስለነበራቸው ህይወት፣ በልጅነታቸው ምን አይነት ሰዎች እንደ ነበሩ፣ ማወቅ ፈልጌ ነው፡፡ በኪድስ ሳይሆን በፕሪሚየም ደስ የሚለው የሁሉም ላይ "early ages" እንደ ፍላጎቴ የልጅነት ህይወታቸውን ባጭሩ ይዳስሳል፡፡ ጂኦርጅ ዋሺንግተን እጁን ያስገባበት ስራ ሁሉ የሚሰምርለት አይነት ሰው ነበረ፡፡ ዳንሰኛ ነበረ፣ ቲያትረኛ ነበረ፣ ሰርቬዪንግ ጎበዝ ተማሪና ሰራተኛ ነበረ፡፡ አብረሃም ሊንከን ት/ቤት ገብቶ የተማረው አንድ አመት ብቻ ቢሆንም፣ አንባቢ ነበረ፡፡ ጋዜጦችንና መጽሐፍትን እየተዋሰ ያነብ ነበር፡፡ የነዚህን ሰዎች ታሪክ ሳነብ የነበረው የሰዎቹን ታሪክ ለማወቅ ብቻ ሳይሆን፣ ሀገራቸው አሜሪካ ዛሬ ላይ እንዴት ልዕለ ሀያሷ ሀገር ልትሆን እንደቻለች ከታሪካዊ አመጣጧ ለመረዳት ነበር፡፡ በኔ አስተሳሰብ ያቺን ሀገር አሁን የደረሰችበት ያደረሷት ከመጀመሪያ ሲያስተዳድሯት የነበሩት መሪዎቿ፣ ፕሬዝዳንቶቿ ነበሩ፡፡ ኢንካርታ በተለይ ያልነበረው የታሪክ ክፍል አልነበረም፡፡ ተመቸኝ፡፡ ልክ እንደምፈልገው፡፡ ኢንካርታን ሳነብ የነበረው ኮምፒዩተሩ ላይ ሌላ የሚያዝናናኝ ነገር ስላልነበረ ነው፡፡ ብዙ ሰፈራችን ኮምፒዩተር የነበራቸው ልጆች ነበሩ፡፡ ብዙ ፊልም፣ ጌም የሚኖራቸው፡፡ ከነሱ በፍላሽ ማሳለፍ እችል ነበር ግን እንዲሁ ሳስበው ይደብረኝ ነበር፡፡

መለስ ሲሞት በኢቲቪ ብዙ ዶኩሜንተሪዎች ሲሰሩ እንደ ነበር ይታወሳል፡፡ ስለመለስ እያወቅኩ በሄድኩ ቁጥር ለሰውየው ያለኝ ክብር እየጨመረ ነበር የሄደው፡፡ አስተሳሰቡ፣ የሚያወራቸው ነገሮች፣ መልሶቹ፣ የፖለቲካ አልበርት አነስታይን እንድለው ነበር ያደረገኝ፡፡ በመለስ ህይወት ዙሪያ ከተሰሩት ዶኩሜንተሪዎች መካከል በአንዱ ላይ መለስ ስለጻፋቸው መጽሐፍት እየታየ ነበር፡፡ ከነዚያ መሀል ምን ባይ ጥሩ ነው? ከህፃንነቴ ጀምሮ የኛ ቤት ውስጥ ሳያቸው የነበሩት ስንዴ ያለበት መጽሐፍ፣ ተማሪዎች ዩኒፎርም ለብሰው ያሉበት፣ ፓርላማ ውስጥ የተቀመጡ ሰዎች ያሉበት፣ በማሽን እየሰሩ ያሉ ሰዎች ፎቶ ያለበትን መጽሐፍ ምናምን ሳይና መለስ የጻፏቸው መሆናቸውን

ስሰማ ኸረ ጉድ ቀላል አነበብኳቸው ብዬ በቲቪ ባየሁ በነጋታው ነበር ከተረሱበት ማፈላለግ የያዝኩት፡፡ ብዙም ሳልፈልግ አገኘኋቸው፡፡ ያኔ ስምንተኛ ክፍል ተማሪ ስለበርኩኝ ክረምት አነባቸዋለሁ ብዬ ነበር ራሴ ጋር ያስቀመጥኳቸው፡፡ ሆኖም ግን ፓርላማ ውስጥ የተቀመጡ ሰዎች ያሉበትን፣ ርዕሱ "በኢትዮጵያ የዲሞክራሲ ስርአት ግንባታ ጉዳዮች" የሆነውን መጽሐፍ ትምህርት ሳያልቅ አጋምሼው ነበር፡፡ ሰውየው በጣም ጂኒየስ ነው፡፡ እንዴት ነው እንዲህ ሊሆን የቻለው ብዬ ስራዬ ብዬ መርምሬ አውቃለሁ፡፡ ዊንጌት በእንግሊዛውያን መምህራን ሀይስኩል መማሩን ወጣ ላለው፣ኢትዮጵያ ውስጥ ለማግኘት የሚከብድ ጉብዝናው ምክንያት ሊሆን ይችላል አልኩኝ፡፡ ኤርትራዊ እንደሆነ ስሰማ ከተፈጥሮ ጉብዝና ባሻገር ከዚያ ጋር ላያይዘው ሞከርኩ፡፡ ኤርትራውያን መሀይሞች ብለው እኛን ትዮጵያውያንን ይንቁናል አሉ፡፡ አባቱ ኤርትራዊ ከሆነ የጣልያን ፍልስፍናና አስተምህሮ ጫና ይኖረዋል፡፡ አባትየው በጣልያን መምህራን ተምሮ ሊሆን ይችላል፣ ባይማርም እንኳን ይብዛም ይነስ የሰለጠነ አዕምሮ ሽው ሳይልበት አይቀርም፡፡ በዚያ ላይ መለስ ለጉድ ነው የሚያነበው አሉ፡፡ እንዴ ብዙ ሰዎች ከመለስ በላይ ራሱ የሚያነቡ ይኖራሉ እነሱ ለምን እንደሱ ጎበዝ አልሆኑም ታድያ? ልትል ትችላለህ፡፡ እኔም ያ ነው ትርጉም አልሰጥህ ያለኝ፡፡ ማንበብ፣ ብዙ ኢትዮጵያዊም ያነባል፡፡ ኤርትራዊነት፣ ብዙ ኤርትራዊያን አሉን፡፡ ዊንጌት መማር፣ ብዙ የጄነራል ዊንጌት ተማሪዎች አሉን፡፡ የተፈጥሮ ጉብዝናም ቢሆን፡፡ ግን እንደመለስ አራቱን ያጣመረ ሰው ማግኘት ትንሽ ይከብዳል፡፡ በርግጥ አንዱ ለሌላው ምክንያት አንዱ የሌላው ውጤት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ፡ በተፈጥሮው ጭንቅላቱ ብሩህ ነበረ፣ አባቱ ኤርትራዊ ስለነበሩ ሲያሳድጉት የጣልያኖች የሰለጠነ አዕምሮ አሻራ አርፎበታል፣ እነኚህ ሁለቱ ውጤታማ ተማሪ እንዲሆንና አዲሳባ ጄነራል ዊንጌት ት/ቤት እንዲማር እድሉን ከፈቱለት፣ አዲሳባ መግባቱ የተለያ መጽሐፍት የማንበብ እድል ፈጠረለት፣ አስተማሪዎቹ ከውጪ መሆናቸው ደግሞ ለከፍተኛ የበሰለና የሰላ እንዲሁም እውቀት የጠማው አዕምሮ እንዲኖረው አድርገውታል የሚለው እንዲሁ ተፈጥሮ ነው ከሚል ያቋራጭ መልስ ይልቅ የገመትኩት ነው፡፡

ክረምት ሲገባ ያን የመለስ መጽሐፍ ክረምት ማንበቤን ቀጠልኩኝ፡፡ እኛ ቤት የሚመጡ የወንድሜ ጓደኞች መጽሐፉን ቤት ውስጥ ሲያዩ ማነው ይሄን መጽሐፍ የሚያነበው? እያሉ እኔ መሆኔን ሲያውቁ ይገረማሉ፡፡ አንዱ አንድ ቀን "ይሄን መጽሐፍ እንድታነብ መንግስት ይከፍልሃል እንዴ?" አለኝ፡፡ ከዚያ እንዲህ አልኩት፡ "አሁን ከጓደኞቼ ጋር ስናወራ ስለፖለቲካ ሲነሳ እኔ ምንም አልልም፣ እርግጠኛ ባልሆንኩት ነገር መከራከር አልፈልግም፡፡ እነሱም ደግሞ በማያቁት ነገር ነው የሚከራከሩት፡፡ የፖለቲካ እውቀታችን በጣም አናሳ ነው፡፡ አሁን አንተ ይሄን መጽሐፍ ብታነብ፣ ሌላው ዝም ብሎ የማያውቀውን ነገር የሚዘላብደውን አንተ ግን ከጓደኞችህ በልጠህ ልትገኝ ትችላለህ"፡፡ አንድ ሳምሶን የሚባል ልጅም መጥቶ መጽሐፉን ጠጴዛ ላይ አይቶት "ማንነው ይሄን መጽሐፍ የሚያነበው?" ብሎ የሱ ደግሞ ግርምቱ ውሻ ሲያወራ ያየ ይመስል ነበር፡፡

አንድ ቀን ሰፈር ከአቤ ፊልም ቤት ፊልም ልከራይ እየሄድኩ አንዱ የሚባል የሰፈራችን ፕሪፕ ተማሪ መጣብኝ፡፡ ሶሻል እገባለሁ እንዳልክ ደግሞ ሰማሁ አለኝ፡፡ማን ነገረህ እለዋለሁ ሰማሁ በቃ ወሬ ይደበቃል እንዴ? አለኝ፡፡ ከዛ የት እየሄድክ ነው? አለኝ፡፡ ፊልም ለመከራየት እንደሆነ ነገርኩት፡፡ በቃ አንተ ቤት ውስጥ ተጎልተህ ፊልምና መጽሐፍ ማሳደድ ነው አይደል ስራህ? አለኝ፡፡ ምን ላርግ ታዲያ አልኩት፡፡ ከልጆች ጋር አትገናኝም? አለኝ፡፡ ከማን ጋር? አልኩት፡፡ ኦሊ አለ አይደል አለኝ፡፡ አይመቸኝም ያናደኛል አልኩት፡፡ አቡሽስ አለኝ፡፡ ያው ናቸው ባክህ ምናምን ብዬው ተቀላልደን፣ ተለያየን፡፡ እኔ ወደ አቤ ከቤ ፊልም ቤት እሱ ወደሚሄድበት፡፡ እውነት ነው፣ አንዳንዴ እነኦሊ ጋር ለመሄድ አስብና ምን አረጋለሁ፣ ስለሆነ ነገር እናወራለን፣ ከዚያ እንስቃለን፣ ከዚያ በሆነ ነገር እንበሻሽቃለን፡፡ ታድያ ይሄ ምንድነው ትርጉሙ ብዬ አስብ ነበር፡፡ ተቀምጬ ፊልሜን አላይም? መጽሐፌን አላነብም? የማይደብረኝን? እናወራለን፣ እንስቃለን፣ በቃ አለቀ ትርጉም የለውም፡፡

በዛ ክረምት ስልክ ያዝኩኝ፡፡ የአባቴን NOKIA Xpress Music፡፡ ሰው የሆንኩ ነበር የመሰለኝ፡፡ አባቴ፣ ለራሱ አዲስ ስልክ ሲገዛ ነው ይህቺኛዋን የተረከብኩት፡፡ 34 ቤት ሲሜን ከትቼ ሀሉ ነበር በቃ፡፡ ቤት ተቀምጬ ምናምን ሲደወልልኝ ምናምን ውጪ ወጥቼ ማናገር ምናምን ራሱ ጀመርኩ፡፡ ከስንት ጭቅጭቅ በኋላ ነበር ስልክ የያዝኩት፡፡

ያን ክረምት አንድ ቀን ለወንድሜ ልብስ ለማሰፋት ስሄድ ቸርችም ሰፈርም ጥሩ ጊዜ አብረን ያሳለፍነውን ዳግምን ከብዙ የሰፈራችን ልጆች ጋር አገኘሁት፡፡ ከቤት ሳልወጣ ቆይቼ ነበር፡፡ ድብር አለኝ፡፡ ወደ ኋላ ብመለስ ደስ ይለኝ ነበር፡፡ እሱንም 6 የሚሆኑትን ሁሉንም ሃይ ብዬ ላልፋቸው ስል ቤቢ ብሎ ሀይ ብለህ ማለፍ ትፈልጋለህ እንዴ? አለኝና ሞቅ አድርጎ ሰላም አለኝ፡፡ አንድ አመት ዩኒቨርሲቲውን ጨርሶ ለእረፍት ከመጣ ቆይቶ ነበር ግን ተገናኝተን አናውቅም ነበር፡፡ ጠፋህ እንደድሮ አትታይም አለኝ፡፡ ኸረ አለሁ ምናምን አልኩት፡፡ ምን እንደመለስኩለት በትክክል አላስታውስም፡፡ የማስታውሰው እሱ የሚያውቀውን፣ ከሰፈር ልጆች ጋር በጣም የሚቀራረበውን እኔን ልሆን ባለመቻሌ ማፈሬን ነው፡፡ ያን ቀን የሆነ ነገር ሲጫጫነኝ ነበር፡፡ ከቤት ሳልወጣ ቆይቼ ነበርና ወንድሜ ሲልከኝ በጣም እያስጠላኝ ነበር የሄድኩት፡፡

እነራሄል(የድሮ ጎረቤታችን፣ እነእቴቴ) ቤት በቃ ሳልሄድ በመቆየቴ ሳፍር፣ እናቴ ሄዳ ስትመጣ ቤቢ ጠፋ አሉኝ አለችኝ፡፡ ሚጣ ስትሄድ እሷን ለማምጣት ነበር የምሄደው፡፡ እነሱ ቤት መሄድ ማፈር ጀመርኩ፡፡ የሆነ እንደስራ አየው ጀመር፡፡ ከስምንተኛ ክፍል ወዲህ ነው ቀዝቀዝ፣ ቀዝዝቀዝዝ ማለት የጀመርኩት፡፡ የሚያሳዝነው እቴቴ ያኔ ካንሰሯ እየባሰባት፣ እየባሰባት፣ በፊት እንዲሁ ለመጫወት ምናምን የምሄደውን ያኔ ግን እሷን ለመጠየቅ መሄድ የነበረብኝ ጊዜ ነበር፡፡ የሆነ ጊዜ እንደሻው ስማር እነሱ ቤት ከት/ቤት 10 ተኩል ገብቼ ሳላስፈቅድ ተደብቄ እነሱ ቤት እሄድ እንዳልነበረ እቴቴን እንኳን ለመጠየቅ እነሱ ቤት መሄድ ስራ ሆነብኝ፡፡ ከቤት መውጣት፣ ሱቅ መሄድ ምናምን ያስጠላኝ ጊዜ ነበር፡፡ በቃ ቤት ውስጥ ፊልም እያየሁ መዋል ያስደስተኝ ነበር፡፡

ክረምት የሆነ ጊዜ መምሪያ ግቢ ውስጥ ነበርኩኝና ኢዩኤል(የክፍል ጓደኛዬ) ከአንድ ልጅ ጋር ሲመጣ እኔ ያው ለረጅም ጊዜ ስላልተገናኘን ሞቅ አድርጎ ሰላም ይለኛል ብዬ ጠብቄ ነበር፡፡ እንዲሁ ከሁለት ቀን በፊት እንደ ተገናኘ ሰው ሰላም ብሎኝ ሲያልፍ whattt??? አልኩኝ፡፡ ለአቡሽ እንዴ ኢዩኤል አካበደች አልኩት፡፡ "እኔምኮ በጣም ሰላም የምትባባሉ መስሎኝ ነበር" አለኝ፡፡

ሌላ ቀን ከአቡሽ ጋር መምሪያ ላይብረሪው አጠገብ ከሆኑ ልጆች ጋር እያወራን ነበር፡፡ ኤፍሬም የሚባል የአቡሽ ዘመድም ነበረ፡፡ እያወራን ታድያ ስለፊልም ተነሳ፡፡ እኔ "ኢትዮጵያ ውስጥ ፊልም የለም፣ እኔ ኢትዮጵያ ውስጥ ተሰራ የምለው ስርየት፣ የወንዶች ጉዳይ 1ና 2፣ ስስት አለቀ"፡፡ ስል አሹ " አንተ ከውጪዎቹ ጋር ስለምታወዳድር ነው፣ እዛ ደረጃ ላይ አልደረስንም፣ አሁን ዘመቻ ድንግል ፍለጋ አይጸዳም? አለኝ፡፡ "ትች ፊልም ነው እንዴ እሱ? የሚያወሩት ነገር እየደበረኝ ጆሮዬን እየያዝኩ ነው ያየሁት" አልኩት፡፡ ብዙ ሽልማት አግኝቷልኮ አለኝ፡፡ "የሚሸልሙትም ፊልም ስለማያውቁ ነዋ፣ ወይ ደግሞ ሌሎች በዚያ አመት የተሰሩ ፊልሞች ከሱ የበለጠ ስለሚደብሩ ሊሆን ይችላል፣ ቀና ሲታጣ ይመለመላል ጎባጣ" አልኩት፡፡ "የኢትዮጵያ ፊልም ሰሪዎች ምንም ፊልም አያውቁም፡፡ ዝም ብለው ነው እቃቃ የሚጫወቱት" አልኩት፡፡ ምንድነው ተናደድክኮ አሉኝ፡፡ ዳዌ የሚባል ልጅ ዝም ብሎ እየሰማን የነበረ ከተመቻቹ የተመቻቹን እዩ አለን፡፡
እኔ ደግሞ ኤፍሬምን "እኔ ቆይ ፊልም ሰርቼ አሳይሀለሁ" አልኩት፡፡ "አንተ የምትሰራውን ፊልምማ አላይም" አለኝ፡፡ ከአቡሽ ጋር ወደ ቤት ስንገባ ስለፊልም እያወራሁለት ነበር፡፡ ፊልም፣ ያለ የምናውቀው ነገር መሆን እንዳለበት፣ የምናውቀው ንግግር፣ የምናውቀው ህይወት መሆን እንዳለበት፣ ካልሆነ ግን ፊልሙ የመጨረሻ እንደሚደብር፣ ፈረንጆች እንዴት አሪፍ፣ ደስ የሚል ፊልም እንደሚሰሩ እያወራሁለት እያለሁ፣ እስኪ በቃ ስለሌላ ነገር አውራ አለኝ፡፡ በጊዜው የፊልም ነገር በጣም ነበር የሚያሳስበኝ፡፡ ፊልም ሰሪ እሆናለሁ ብዬ የቆረጥኩበት ጊዜ ነበር፡፡

ያን ክረምት ቸርች ከቄስ ኢብሳ ጋ የአገልግሎት ትምህርት ጨርሰን ፈተና ተፈተንን፡፡ 9ኛ ክፍል ተማሪ ነበርኩ፡፡ ከሳምንታት በኋላ አገልግሎት መዝሙር የመረጥን ተማሪዎች (ከ20 ምናምን ተማሪ 2 ወይም 3ቱ ብቻ ናቸው ሌላ ሌላ የመረጡት) የድምጽ ፈተና(Audition) ነበረን፡፡ መጀመሪያ ቀን እኔ አልሰማሁም ነበር፡፡ እኔ ሳልሰማ የተወሰኑ ተማሪዎች ተፈተኑ፡፡ እኔ ፈተናው አመለጠኝ፡፡ መዝሙር አዘጋጆቹ ምናምን ቤት ስዘምርላቸው ነበር ደግሞኮ፡፡ ድምጽ እንዳለኝ በጣም እተማመን ነበር፡፡
ያን ቀን ወደ 9 ሰአት ወንድሜ ሊወጣ እየለባበሰ "ቀጣዩ አመት ደባሪ ይሆናል" አልኩት፡፡ "ለምን? ቸርች የፈተና ቀን ስላመለጠህ?" ብሎ ጠየቀኝ፡፡ አዎ አንድ ለሱ፡፡ ግን እሱ ብቻ አይደለም፡፡" ምንም አላለኝም፡፡ ወንድሜና እህቴ እንዲህ የሆነ ወጣ ያለ የሚጨንቀኝን ነገር ሳወራላቸው፣ ላያውቁት ይችላሉ ግን ደስ አይላቸውም፡፡ እኔ እንዲህ አይነት ነገር ሳወራላቸው ወይ ዝም ይላሉ፣ ወይ ወሬ ይቀይራሉ፣ ወይ "እንዴ አጨናነከኝኮ እኔን ራሱ" ይሉኛል፡፡ ወንድሜ ታዲያ እንዲህ አለ፡ ዝም አለ፡፡ ብቻ የሆነ ነገር ይታየኝ ነበር፡፡ የታየኝ ይመስለኛል፡፡
የሆነ አስፈሪ ነገር ሊመጣ እንደሆነ የታወቀኝ ይመስለኛል፡፡

ሚጡ(የድሮ ጎረቤታችን)ን ቤታቸው ሄጄ የት ኳየር ልግባ አልኳት፡፡ እሷ ኳየር ውስጥ ስላለች ማለት ነው፡፡ ቸርቻችን 5 ኳየሮች ነበሩ፡፡ ሁለቱ የትላልቅ ሰዎች ሲሆኑ ምርጫዬ ከጉደቱ፣ ከጽዮንና ከጽናት ነበረ፡፡ ጉደቱ እንደ ሚሻለኝ ነገረችኝ፡፡ እነፈይሳ አይመቹኝም ስላት አንተን ማንነው የሚመችህ? አለችኝ፡፡ አንተ ልትቀርባቸው የምትችላቸው ልጆች ያሉት እዛ ስለሆነ ብዬ ነው አለችኝ፡፡ ዮሴፍ ደግሞ የሱ ኳየር፣ ጽዮን እንድገባ መከሮኝ ተስማምቼው ነበር፡፡ ወንድሜም ጉደቱ ግባ አለኝ፡፡ አንድ እሁድ ቀን ከዮሴፍና የጉደቱ ኳየር ኮሚቴ ከነበረው፣ ከወሰን ጋር ቸርች እየሄድን የቸርች ግቢ ውስጥ ወሰን "የት መግባት ነው የምትፈልገው?" ብሎ ጠየቀኝ፡፡ ጉደቱ አልኩት፡፡ ከዚያ ከሱ ጋር ከተለያየን በኋላ ዮሴፍ "ጽዮን ብለህ አልነበር?" አለኝ፡፡ ሀሳቤን ቀየርኩ አልኩት፡፡ እውነታ ስለሆነ ነው፣ ፊልም(ልቦለድ) ቢሆን ኖሮ ይደብር ነበር፡፡ ፊልም ሲሰራ ፊልሙ ላይ የሚደረጉት ድርጊቶች ተመልካቹን ማሳመን አለባቸው፡፡ ምክንያታዊ፡፡ እዚህ ጋር ምክንያታዊ ያልሆነው እነእገሌ ይደብሩኛል ያልኩበት ኳየር መግባቴ ነው፡፡

ጊዜው ሐምሌ መጨረሻ ወይም ነሀሴ መጀመሪያ ነው፡፡ ከዚያ አባቴ ቄስ ኢብሳን ስለ ፈተናው ደውሎ ጠይቆልኝ አርብ እለት አስር ሰአት ላይ ይምጣ አሉ፡፡ ተዘጋጀሁ፡፡ የተዘጋጀሁት ከ1998 ጀምሮ የከር ካሴቱን በነበረን፣ ከስምንተኛ ክፍል ጀምሮ ምርጥ ዘማሪዬና ምርጥ ካሴቴ በነበረው፣ከስምንተኛ ክፍል ጀምሮ እሱን የሚያህል ዘማሪ የለም ብዬ ስከራከርለት ከነበረው ሁሉንም እዚያ ካሴት ላይ የነበሩ መዝሙሮችን ከነቁጥራቸው ጠንቅቄ ከማውቃቸው፣ መዝሙሮች በአንዱ ነበር፡፡ የሚገርመኝ መቱ ላይ መዝሙሮቹ ሲዘመሩም ሆነ ስለ ዘማሪው ሲወራ ሰምቼ አላውቅም ነበር፡፡ መዝሙሮቹ ግን በጣም ነበር ደስ የሚሉት፡፡ በቃ ይገርመኝ ነበር፡፡ የሱን መዝሙሮች ለሁሉም ባውስና ሁሉም እንዲያውቀው ባደርግ ደስ ይለኝ ነበር፡፡ መዝሙሮቹ በመቱ ለምን እንደማይታወቁ እራሴን ጠይቅ(ለነገሩ አዲሳባ ላይ ራሱ ቢታወቁ ቢያንስ ኤልሻዳይ ቲቪ ላይ ከመዝሙሮቹ አንዳቸውን እንኳን ቢያንስ አንዴ እሰማቸው ነበር) መልሴ አንደኛ መዝሙሮቹ እንደሌሎች ዘማሪዎች ወይም እንደ ሌላ መዝሙር ቃላት አይደጋገሙበትም፡፡ አንድ መዝሙሮቹን የወደድኩበት ምክንያት ነው፡፡ ነገር ግን እንደኔ ግጥሞቹን ከወረቀት ላይ ካልሸመደዱ በቃል ይዞ ቸርች ውስጥ በመዝሙሮቹ ለማምለክም ሆነ በግል ለመዘመር ፈታኝ ይመስላሉ፡፡ እንዲሁ እያዳመጥካቸው ስለ ዋልክ የሚያዙልህ አይነት መዝሙሮች ሳይሆኑ እንደኔ ስራዬ ብሎ የሚሸመድዳቸው የሚፈልጉ ይመስለኛል፡፡ አንዴ ከያዝካቸው ግን ሰምተህ አትጠግባቸውም፡፡
ሁለተኛ የክር ካሴቱ የተለቀቀበት ጊዜ(1998) ቪሲዲ የክር ካሴትን እየተካ የነበረበት ጊዜ ነበር፡፡ ሰው የክር ካሴት መግዛት ያቆመበት ጊዜ ስለ ነበረ ይመስለኛል፡፡ የቄስ በሊናና ሳርካ "የከፍታ ዘመን ለኢትዮጵያ" መጽሐፍ በወጣበት አመት፡፡ ያን መጽሀፍ ሚሊኒየም ላይ ነበር ያነበብኩት፡፡ በአስር አመቴ ማለት ነው፡፡ በአስር አመት የተከፋፈሉ ከሶስት ዘመኖች በኋላ ኢትዮጵያ እንደምትበለጽግ እግዚአብሔር ራዕይ አሳየኝ ይላሉ ቄሱ፡፡ ያኔ ሳነበው ከ3ኛው ዘመን በኋላ እድሜዬን ስደማምር ነበር፡፡ በረከቱ እንዳያመልጠኝ፡፡ እንዳልሞት፣ ወይ እንዳላረጅ፡፡ ዘግይቼ ብወለድ ብዬ ተመኘሁ፡፡ በርግጥ መጽሐፉን ከማንበቤ በፊት ራሱ ከነሳሚ(ሌላ ሀገር የገባው ጓደኛዬ) ጋር ገና ህፃን ብሆን፣ ገና ቢሆን የምወለደው እንል ነበር፡፡ ቶሎ ላለማርጀት ነው መሰለኝ፡፡

የተዘጋጀሁበት መዝሙር ግጥሙ እንዲህ ይነበባል፡

ዋጋ ልትከፍለኝ በእጅህ ከያዝከው
ጌታ አንድ ነገር እለምንሀለሁ
አስብልኝ አገልግሎቴን
አስብልኝ እሩጫዬን
ከንቱ እንዳይሆንብኝ
አስብልኝ
ከንቱ እንዳይሆንብኝ
አስብልኝ
አንተ እማታውቀው አገልግሎት
አይታይ በእኔ ህይወት
አይታይ በእኔ ህይወት
ጌታ እማታውቀው አገልግሎት
አይታይ በእኔ ህይወት
አይታይ በእኔ ህይወት

እስኪ መዝገብህን ገለጥ አድርግና
ማገለግለውን ጌታ ጻፍልኛ
ጌታ ጻፍልኛ

በአገልግሎት እድሜዬ ዘመን አስቆጥሬ
በአራቱም አቅጣጫ ዞሬ አገልግዬ
በመጨረሻው ቀን ፊትህ እንዳላፍር
የማገለግለው ይሁን ለአንተ ክብር
እንደ ልቤ ሳይሆን ልኑር እንደ ልብህ
እንደ ልቤ ሳይሆን ልኑር እንደ ልብህ
እንደ ልብህ
እንደ ልብህ
እንደ ሀሳብህ

እንደ ሀሳብህ የሚለውን የእንዳለ ወልደጊዮርጊስን መዝሙር ነበር ያዘጋጀሁት፡፡ ከሁሉም የሚመቸኝ ግን "እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ማራት ባርካት" የሚለው መዝሙሩ ነበር፡፡ ከዚያ ግን ያን ክረምት አዲስ መዝሙር (ይፈውስ ይዳሰኝ እጅህ የሚለው መዝሙር ያለበት ቪሲዲ) ሲያወጣ ማን እንደ እንዳለ ይባል ተጀመረ፡፡

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ማራት ባርካት ማራት ባርካት
ፊትህን በላይዋ ላይ አብራ በላይዋ ላይ አብራ
ያበቃል ያለባት መከራ ያንተ ፊት ሲበራ
ያበቃል ያለባት መከራ ያንተ ፊት ሲበራ
እናት ከልጇ ጋር ጥቂት እንደ ቆዩ
በሀዘን በለቅሶ አየሁ ሲለያዩ
ይሄ ለምን ሆነ ብዬ ብጠይቃት
ነበረ ምላሽዋ ችግርና ማጣት
ችግርና ማጣት
ምህረትን አድርግልን
አንተው አንተው አንተው
ራስህ አንተው
በይቅርታህ ተገኘን
አንተው አንተው አንተው
ራስህ አንተው
ከሰው ልጆች ይልቅ እስኪ አንተ ጎብኘን ወደ ሀገራችን ና
ፍጻሜን የሚያደርስ ልብን የሚያሳርፍ መፍትሄ አለህና
የኢትዮጵያን ጉዳይ አንተ እንድታየው ፊትህ አቀርባለሁ
ላስረዳህ አልሞክርም ሁሉንም ታውቃለህ እንደምታየው ነው፡፡
የብልጥግና ጫፍ ደርሰዋል ሚባሉ

ልብ የጣልንባቸው፣ ሀገሮች በሙሉ
ያለባትን ችግር አይችሉትም መፍታት
በመሀሪነትህ ይበቃል ካላልካት
አይን አለህ እየን
እጅ አለህ ዳስሰን
አንተው አንተው አንተው
ራስህ አንተው

አዲሶቹን መዝሙሮቸ የሚያዳምጡት ሰዎች እኔ የምወዳቸውን የድሮዎቹን አያውቁም፡፡ አልፎ አልፎ የሚያውቁት ደግሞ ከድሮዎቹ አዲሶቹ ይሻላሉ ብለው ይከራከሩኛል፣ ሳይሆን እኔ ነኝ የድሮዎቹ ይሻላሉ ብዬ የምከራከረው፡፡ በርግጥም በተለይ ይሄ ኢትዮጵያን ማራት የሚለው፣ የሙዚቃ ቅንብሩ በበኩሌ ከዘፈንም ይበልጥብኛል፡፡

ትዝ ይለኛል HOW TO TRAIN YOUR DRAGON የሚለውን አኒሜሽን ፊልም አይቼ ልጨርስ አካባቢ ሰአት ሲደርስ ነው አቋርጬ ለኦዲሽኑ ወደ ቸርች የሄድኩት፡፡ የምንዘምረው በቤተ-ክርስትያኒቱ ውስጥ ከሚታወቁ መዝሙሮች መርጠን እንዲሆን ሲነገረን ሁለት ቀለል ያሉ በትክክል የማስታውሳቸውን መዝሙሮች መረጥኩ፡፡ ለኪቦርዲስቱ አዲስ ያልሆነ መዝሙር ማለታቸው ነው በሌላ አማርኛ፡፡ ዳኞቹ የፅዮን ኳየሩ አሼ፣ አንድ ስሙን ያኔ የማላውቀው የጉደቱ ኳየር ልጅና አንድ ልጅ ከሌላ ኳየር፣ ከኪቦርዲስቱ ጋር ነበሩ፡፡
አንዷት ጠባብ ዳኞቹ ብቻ በነሩባት ክፍል ውስጥ ነበር ተፈታኞቹ በየተራ እየገባን የምንፈተነው፡፡ እኔ የመጀመሪያው ገቢ ነበርኩ፡፡ መጀመሪያ ስጀምር እንደ ጀመርኩ አቋርጠውኝ ሪትም እንድጠብቅ ነገሩኝ፡፡ ሪትሙን ባላገሩ አይድል ላይ እንዳየሁት ጣቶቼን በማጋጨት ለመጠበቅ ሞከርኩ፡፡ ይሄን እየጻፍኩ ባለሁበት ጊዜ ላይ ሆኜ ሳስበው ባላገሩ ላይ ለካ ኪቦርድን ለመተካት ነው ያኔ ያየሁት ሰው ጣቶቹን እያጋጨ የነበረው(ችው)፡፡ እንደገና አሼ አሪፍ ነው ግን ድምጽህ አይሰማም ፈርተሀል፡፡ አትፍራ ገና ብዙ ህዝብ ፊት ልትቆም አይደል እንዴ አለኝ፡፡ ኪቦርዲስቱም ድምጽህ የማይሰማ ከሆነ እንዴት እንፈትንሀለን፣ ጮክ በል አለኝ፡፡ አሼ "ቤት እንደ ምትዘምረው ዘምር ብሎ አሳቀኝ፡፡" ጎረቤት በመዝሙር የምበጠብጠው ፊቴ ላይ ግጥም ብሎ ነው የሳቅኩት፡፡ከዛች ሳቅ በኋላ የነበሩት ሳቆቼ ዋጋ አላቸው፡፡ እውነትም ፈርቻለሁ፣ ድምጽ አልወጣ አለኝ፡፡ ግን አልፌአለሁ፡፡ ስወጣ በር ላይ ቄስ ኢብሳ እንዴት ነበር አሉኝ፡፡ አሪፍ ነበር አልኳቸው፡፡ አሪፍ ነበር ትላለህ እንዴ ፈራህ፣ አትፍራ ሲሉህ ሰምቻለሁኮ አሉኝ፡፡ ፈገግ አልኩኝ፡፡ ሌላ ተማሪዎች ለመፈተን በየተራ ሲገቡ እኔ ቄስ ኢብሳን የኳየር ምደባ ቀን ጠይቄአቸው ወደ ቤቴ ገባሁ፡፡ ቀኑንና ሰአቱን ነገሩኝ፡፡
በነገሩኝ ቀን፣ 11 ሰአት ላይ ምደባዬን ለመስማት ሄድኩኝ፡፡ ጽናት ኳየር እንዳስገቡኝ ነገሩኝ፣ ቄስ ኢብሳ፡፡ ጉደቱ አርጉልኝ አልኳቸው፡፡ ወንድምህ ጋር ላለመግባት ነው አይደል? አሉኝ፡፡ ሳቅኩኝ፡፡ ለምን ከወንድሜ ጋር መግባት እንደ ደበረኝ ራሱ አላውቅም፡፡ ከወንድም ጋር ሄዶ ከወንድም ጋር መግባት ምን ክፋት አለው? ግን አዎ፣ የሚደብር ይመስላል፡፡ ግንኮ እሱ ለሁለት ወር ብቻ ነው አዚህ የሚቆየው፡፡ ዩኒቨርሲቲው ይሄዳል፡፡ ተው አንተ ልጅ ጽናት ይሻልሀል አሉኝ፣ ቄስ፡፡ በውስጤ ስለኳየር፣ ስለሚኖረው ማህበራዊ ህይወት አያውቁም ብዬ አይ ይቀይሩልኝ እልኳቸው፡፡ በቀላሉ የሚቀይሩልኝ አልመሰለኝም ነበር፡፡ ቀየሩልኝ፡፡ ለአንድ ሌላ ቄስ ይሄ ልጅ አስተማሪዎቹን በጥያቄ ጭንቅላታቸውን ያዞራል እያሉ አዳነቁኝ፡፡ ከየት አምጥተው እንደዚያ እንዳሉ እኔ አላውቅም፡፡ ያኔውኑ ኳየር ሄድኩኝ፡፡ ሌላ ልጆች ነበሩ የጉደቱን የኳየር ቤት ያሳዩኝ፡፡ የቱ ቤት የማን የኳየር ቤት እንደ ሆነ ራሱ አላውቅም ነበር፡፡ 12 ሰአት አልፎ ነበር፡፡ ከሁለት ሴቶችና ከአንድ ወንድ ጋር ነበር ጉደቱ የገባነው፡፡ የአገልግሎት ት/ት አብረን ብንማርም ያን ያህል ግንኙነት አልነበረንም፡፡ እኔ የምቀርባቸው ልጆች እንዳሉ ጽናት ኳየር ነበር የገቡት፡፡
ኳየር ስሄድ ካሌብ የሚባል የኳየር ልጅ ነበር ተመድቦ ነው ምናምን ብሎ ያደረሰኝ፡፡ እሱ ጽናት ነው፡፡ ወሰን ነበረ ያነጋገረው፡፡እንድገባና እንድቀመጥ ነገረኝ፡፡ ተቀምጬ ሳለሁ ነበር ከኔ ጋር ጉደቱ የተመደቡ ልጆች ሲገቡ አይቼ ማንነታቸውን ያወቅኩት፡፡

ኳየሩ ውስጥ ያሉትን ልጆች በአይኔ አካለልኩ፡፡ አንድም የምቀርበው ሰው አልነበረም፡፡ ስለ ኳየርም ምንም ነገር አላውቅም ነበር፡፡ ኳየር ሲባል፣ መዝሙር ተለማምዶ እሁድ እለት ከማቅረብ የዘለለ ምንም የሚታየኝ ነገር አልነበረም፡፡ ተሳስቼ ነበር፣ ቄስ ኢብሳ ከኔ የበለጠ ስለ ኳየር ያውቁ ነበር፡፡ እንዴት? Wait and find out. ያን ቀን ውይይት ላይ ነበሩ፡፡ ጥግ ጥግ ላይ ክብ ሰርተው ነው የሚቀመጡት፡፡ የሶስቱ ኳየሮች አንድነት ቀን ስለሚዘምሯቸው መዝሙሮች ሲወያዩ ነበር፡፡ ከዚያ ስለ አንድነት ቀን፡፡ (የአንድነት ቀን ማለት የአንድ ኳየር አባላት ብር አዋጥተው፣ የኳየራቸውን የምስረታ አመት በየአመቱ የሚያከብሩት ክበር በአል ነው)፡፡ አንዴት ነው ስለ አንድነት ቀናችን እየተወራ አይደለም አለች ሜሪ የምትባል ልጅ፡፡ ተወራ፣ ተወራና ወሬው ሲያልቅ አዲስ የገባነው ልጆች ራሳችንን እንድናስተዋውቅ ተነገረን፡፡ ናትናኤል ሀይሌ አባላለሁ ወደ አስረኛ ክፍል ስል የኳየሩ ኮሚቴና ፕሮግራሙን እየመራ የነበረው ወሰን፣ 3 አመት ኳየር ታገለግላለህ ማለት ነው አለ፡፡ ሌሎቹ 4ቱ አዲሶችም ራሳቸውን አስተዋወቁ፡፡ ወሰን ኳየር ሰኞና ቅዳሜ እንደ ሆነ፣ መቅረት እንደማይቻል፣ ሌሎቹ የኳየሩን ህጎች ደግሞ ቀስ በቀስ እንደሚነገሩን ነገረን፡፡ መጨረሻ ላይ ተጸልዮ፣ አባታችን ሆይ…የእለት እንጀራችንን ስጠን ለዛሬ…ለዘለአለሙ አሜን፡፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፣ የእግዚአብሔር ፍቅር፣ የመንፈስ ቅዱስም አንድነት ከሁላችን ጋር ይሁን አሜን አሜን አሜን፡፡ ተብሎ ሁሉም ተጨባብጦ፣ ሰላም ተባብሎ ወደ ቤቱ ይገባል፡፡ ያን ቀን ሁሉም እንኳን ኳየራችን ገባህ፣ ምናምን ሞቅ ደመቅ አድርጎ ነበር ሰላም ያለኝ፡፡ ተመቸኝ፡፡ የሚገርመው ሁሉም ሰላም ይባባላል፡፡ ወደ ቤት መግባቱን ከማን ጋር ልግባ? የምቀርበው ሰው ብቻ ሳይሆን የሰፈሬም ሰው አልነበረም፡ ኳየሩ ውስጥ፡፡ ቢቂላ የሚባል ልጅ ነበረ፡፡ ከሱ ጋር ገባሁ፡፡
ኳየር ለመግባት ጓጉቼ ነበር፡፡ ኳየር ከገባሁ በኋላ በቃ ኳየር እሄዳለሁ፣ ቸርች አልቀርም፣ እጸልያለሁ፣ መጽሐፍ ቅዱሴን አነባለሁ፣ በዚያ ላይ ኳየር ውስጥ ጥሩ በመንቀሳቀስ በቃ ኳየር ላሉ ችግሮች መፍትሄ በማቅረብ ጥሩ ኳየር እንዲሆን ለማድረግና በቃ የእግዚአብሔር ሰው ለመሆን ነበር እቅዴ፡፡

አብሬው የምሄደው ሰው አልነበረኝም፡፡ በቃ ኮስተር ብዬ ለብቻዬን እሄዳለሁ፣ በቃ ጣጣ የለውም ነበር ያልኩት፡፡ እንደ አሼ፡፡ እሱ ይገርመኛል፡፡ ብቻውን መንገድ ላይ በኮንፊደንስ እየነጠረ ሲሄድ ያስገርማል፡፡ እኔ ብቻዬን ስሄድ በጣም ነው የምሳቀቀው፡፡ ሰው ሁሉ እኔን እያየ ይመስለኛል፣ ቶሎ ቤቴ ለመግባት እጣደፋለሁ፡፡ ከሰው ጋር ስሆን ደግሞ እንደኔ ኮንፊደንስ ያለው ሰው ራሱ የለም፡፡
እቴቴ አዲሳባ ለረጅም ጊዜ ልጆቿ፣ እነማሬ ጋር ቆይታ መጣች፡፡ ከ20 አመት በላይ የቆየ የሳንባ ካንሰር፡፡ እናቴ ሂድ እንጂ ስትለኝ ከሚጣ ጋር ሄድን፡፡ ብቻዋን ነበረች፡፡ ተጫወትን አወራን፡፡ አዲሳባ ወንድሜና እዚያ ያሉት ልጆች ሲንከባከቧት እንደ ነበረ ነገረችኝ፡፡ እያመማት ነበር፡፡ እያመማት እንደ ሆነ የሚታወቀው ግን ተነስታ ስትንቀሳቀስ ነው፡፡ ትስቃለች፣ ትጫወታለች፡፡ እኔ ምኔንም የማያመኝ የሷን ያህል ፈታ ብዬ መሳቅ አልችልም፡፡ እናቴ "የእቴቴ ፈገግታኮ" ትላለች፣ "ምንም ማስመሰል የሌለበት፣ ደስ የሚል፣ እውነተኛ ነው" ትላለች፡፡ ሌላ ጊዜ ደግሞ "እኔ ከእቴቴ ጋር የማወዳድረው ሰው የለኝም" ትላለች፡፡ እውነት ነው፡፡ እንደዛ እያመማት ተነስታ እያቃሰተች ለኔና ለሚጣ ሻይ ጣደችልን፡፡ እቴቴ እንዲሁ ነች፡፡

ያቺን የድሮዋን ጥቁር ሻርፕ 14 inch ቲቪ ቀይረው አዲስ ፍላት እስክሪን ቲቪ ገዝተው ነበርና ዋጋውን ጠየቅኳት፡፡ 5000ብር እንደሆነ ነገረችኝ፡፡ "ሰው ነው ከውጪ ብሩን የላከልኝ አለችኝ፡፡ "እኔ አሁን በተደላደልኩበት ጊዜ ምንም ቢያረጉልኝ ምንም አይመስለኝም፣ ያኔ ምንም ባልነበረኝ ጊዜ ያቀረቡኝን ሰዎች ነው የማመሰግነው" አለችኝ፡፡ ስታወራ በጣም ብዙ ችግር ውስጥ ያለፈች ትመስላለች፡፡
ለእቴቴ የድምጽ ፈተና አልፌ ኳየር እንደ ገባሁ ነገርኳት፡፡ "አሁን የድሮዎቹና አዲሶቹ ተብሎ መከፋፈል አይቀርም፣ ድሮ በኛ ጊዜ ራሱ እንዲሁ ነበር" አለችኝ፡፡ እንደዛ ስትለኝ አዲስ ከኔ ጋር የገቡትን አሰብኩ፡፡ ከአዲሶቹም ከድሮዎቹም የምቀርበው ሰው አልነበረም፡፡ ያው ችግር የለውም ጊዜ ያራርቃል፣ ጊዜ ያቀራርባል፡፡ ከጊዜ ብዛት መቀራረባችን አይቀርም አልኩኝ በውስጤ፡፡
ከእቴቴ ጋር ስለ ትምህርቴ አወራን፡፡ ሶሻል መግባት እንደምፈልግ ነገርኳት፡፡ ጋዜጠኝነት፣ ድርሰት፣ ፖለቲካ ምናምን እንደምወድ ነገርኳት፡፡ ብዙም አልጣማትም፡፡ ብቻ ከትልቅ ሰው ጋር ያን ያህል ጊዜ አውረቼ ማወቄን አላውቅም፡፡ ብዙ አወራን:: አውርተን አውርተን እኔና ሚጣ ተሰናብተናት ወደ ቤት ገባን፡፡ ሚጣ ወሬያችሁን ዝም ብሎ ማዳመጥ ደስ ሲል አለችኝ እየገባን መንገድ ላይ፡፡ በትክክል አልተሰናበትኳትም ነበር፡፡
አዳም የወንድሜ ጓደኛ አንድ ቀን ቤት መጥቶ እንዴት ሶሻል እገባለሁ ትላለህ ጎበዝ ሆነህ? አለኝ፡፡ ማን ነገረህ ስለው፣ እቴቴ፡፡ እኔንኮ ያኔ ምንም አላለችኝም፡፡ ምከሩት ብላ አዳምን ላከችብኝ፡፡ ሀሳቤን እንድቀይር፡፡ በአዕምሮዬ መጠቀም ስችል እንዲሁ እንዳልባክን፡፡
አዳም "እንዴት ሶሻል እገባለሁ ትላለህ? ሰነፍ ተማሪዎች ናቸውኮ ሶሻል የሚገቡት፡፡ ትምህርት፣ ሂሳብ የመረራቸው" አለኝ፡፡ ምን ልበለው? እኔም ሂሳብ አልወድም፣ ያለ ጥበብ መኖር አልችልም፣ ስሜት የማይሰጠኝን ነገር እየሰራሁ(እየየተማርኩ) መኖር አልፈልግም ልበለው? "አዲሳባ ቢሆን ይሁን" አለ፡፡ "መቱ ግን እኔ ሶሻል እገባለሁ የሚል ጎበዝ ተማሪ ገጥሞኝ አያውቅም"፡፡ ወንድሜ ደግሞ "እኔ ፍርሃቴ ብትገባ እንኳን የምትማረው ት/ት ከመረረው ዱሪዬ ጋር ስለሆነ ሊያበላሹህ ይችላሉ ብዬ ነው" አለኝ፡፡ ምንም የሚረባ አስተያየት አልሰጠኋቸውም፡፡ ገና ማትሪክ ማለፍ መውደቄ ሳይታወቅ፣ አስረኛ ክፍል ት/ት ሳይጀመርኮ ነው ስለ 11ኛ ክፍል ፕሪፓራቶሪ ምርጫዬ የምንወያየው፡፡ ከቤት፣ ሶሻል ነው የምገባው ብያቸዋለሁ፡፡ አይሆንም አትገባትም የሚሉኝ መስሎኝ ነበር፡፡ እነሱ ግን ያንተ ህይወት ነው፣ ያንተ ምርጫ ነው ነበር ያሉኝ፡፡ ግን ጊዜው ሲደርስ አይሆንም እንደሚሉኝና እንዲሁ በቀላሉ እንደማይለቁኝ ይገባኝ ነበር፡፡

ኳየር የምሄደው ብቻዬን ነበር፡፡ ለብቻ መሄድ ይደብራል፡፡ የኳየሮች አንድነት ቀን ላይ ወሰን እኛ አዲስ ገቢዎቹን ትዘምራላቹ አለን፡፡ "ያኔ ብዙ ሰው ስለሚሆን በብዙ ሰው መሀል መድረክ ላይ መውጣት ትለማመዳላቹ" አለን፡፡ የልምምድ ቀን ተነገረን፡፡ የልምምድ ቀን ሄድኩኝ፡፡ ስሄድ የሆኑ ልጆች ተሰብስበው እያወሩ ነበር፡፡ ከነሱ መሀል የማውቀው ሰው አልነበረም፡፡ ከነሱ ፈቀቅ ብዬ ብቻዬን ተቀመጥኩኝ፡፡ ውጪ ነው፣ ልጆች ገና አልተሰባሰቡም፡፡ ልጆቹ ትንሽ ቆይተው ከኔ ራቅ አሉ፡፡ ፈይሳ የሚባል የኳየሬ ልጅ ምንድነው ናቲ ብቻህን እነኛን ልጆች ለምን አትቀላቀልም? አለኝ፡፡ አይ እዚው ልሁን ብዬ ነው አልኩት፡፡ ትንሽ ቆይቶ ዮሴፍ(የትምህርት ቤት ጓደኛዬ) መጣ፡፡ "ና" አለኝ፡፡ የት? አልኩት፡፡ አልገርምም፡፡ ዝም ብዬ አልከተለውም? ከፈለግክ ና ካልፈለግክ ተው ሲለኝ ተነስቼ ከሱ ጋር ሄድኩኝ፡፡ አንዲት ልጅ መጥታ በስሜ ሰላም አለችኝና አጠገቤ ተቀመጠች፡፡ ዮሴፍ እቺን ልጅ አታውቃትም? አለኝ፡፡ ልጅቷን ከነመፈጠሯ አላውቃትም ነበር፡፡ የምለውን አጥቼ "እዚው ነዋ የማቃት" ስል ልጅቷ እእ? አለች፡፡ ት/ቤት አታውቃትም? ያንተ ጎረቤት ክፍል አይደለች? ኤፍ ነች አለኝ፡፡ እኔ ኢ ነበርኩ፡፡ ውይ አልኩኝ የምለውን አጥቼ፡፡ ት/ቤት ብዙ ሰው ያውቀኛል፣ ብዙ ሰው አላውቅም ነበር ግን፡፡ ማለት የፈለግኩት ገብቶሃል አይደል? ልጅቷን አለማወቄ ደግሞ ምን ያህል ከቸርች ጋር የተራራቀ ህይወት እንዳለኝ ያሳያል፡፡ በቸርቻችን ምርጥ ድምጽ አሏቸው ከሚባሉት ሴቶች ቀዳሚዋ ነች፡፡ ወጣቶች ፕሮግራም ላይ ብዙ ጊዜ ትዘምራለች፡፡
ሰአት ደርሶ ጸሎት ቤቱ ውስጥ ስንገባ ዮሴፍ ከኔ ጋር ሳይሆን ከጓደኞቹ ጋር ሄዶ ተቀመጠ፡፡ ብቻዬን አንድ ጥግ ላይ ተቀመጥኩ፡፡ ከዮሴፍ ጋር መቀመጥ ፈልጌ ነበር፡፡ ለምን እንደሆነ አላውቅም ከማውቀው ሰው ጎን መቀመጥ በጣም ነበር የፈለግኩት፡፡ ልጆች በጣም ይረብሹና በጣም ያወሩ ነበር፡፡ የሆነ እንዲሁ የሚያወራኝ ሰው ቢኖር ተመኘሁ፡፡ ልምምዱ ደግሞ ምንም አልሆነልኝም፡፡ ድምጼ አይወጣም፡፡ ከራሴ ድምጽ የበለጠ አጠገቤ የተቀመጠው ሰው ድምጽ ነበር የሚሰማኝ፡፡ እታገላለሁ፣ ጭጭ፡፡ ድሮ በህጻንነቴ ሳየው እንደነበረው ህልም መሰለኝ፡፡ ሌባ በምሽት ቤታችን ይገባል፡፡ እኔ እባንንና አየዋለሁ፣ እፈራለሁ፣ አንዳንዴ እቃ አግዞ ሊሄድ ሲል፣ እንዳንዴ እኔኑ ይዞኝ ሊሄድ ሲል አባቴን ለመጥራት ብሞክር ብሞክር ድምጼ አልወጣ ይለኛል፡፡ "ሀይሌ ሀይል ሀይል" ድምጼ አይወጣም ወይም አይሰማም፡፡ ሌባው ይሰማል ብዬ ፈርቼ ይሁን፣ አላውቅም፡፡ አጠገቤ የሚቀመጡ ልጆች እየዘመርኩ እንደሆነ ለማወቅ ዞር ብለው ያዩኛል፡፡ ቤት ደግሞኮ በጩኸት የቤታችንን ጣሪያ ነው ምሰነጥቀው፡፡ ምንድነው ችግሬ? ስለፈራሁ ነው መሰለኝ፡፡ ጊዜው ረዘመብኝ፡፡ ቤቴ ናፈቀኝ፡፡

ልምምድ ሲያልቅ ወለም ዘለም፣ ሰላም መባባል ሳልል፣ ወደ ቤቴ በፍጥነት ገሰገስኩ፡፡ ስለነበረው ሁኔታ እያስታወስኩ፡፡ በቀጣዩ ልምምድም እንዲሁ፡፡ ድምጼ እንቢ አለ፣ አጠገቤ ያለ ሰው እየዘመርኩ መሆኔን ቼክ ያደርጋል፡፡ ደበረኝ፣ ብቻዬን ገባሁ፡፡
ኳየር አንድ ሁለት ቀን ስሄድ በጣም ደብሮኝ ነበር፡፡ ያ ሰላም የሚባባሉት ነገር ደግሞ አስጠላኝ፡፡ በቃ ስሄድ ድብርብር ይለኛል፡፡ ኳየር ውስጥ ስሆን የሚሰማኝ አንድ ስሜት አለ፡፡ የኳየር ልጆች ከቀን ወደ ቀን ለኔ ያላቸው አመለካከት የሆነ እየወረደ ሲመጣ ይታወቀኛል፡፡ ጭንቅ አለኝ፡፡

አንድ ቀን ከኳየር ከቢቂላ ጋር ገብቼ ፊቴን በመስታወት ለማየት ሄድኩኝ፡፡ ፊቴን ሳላይ እንደቆየሁ እያሰብኩ ነበር የሄድኩት፡፡ ፊቴን ሳይ ደነገጥኩ፡፡ ደብሮኝ ነበር፣ ኳየር አልተመቸኝም፣ እሺ፡፡ ይሄን ፊት ተሸክሜ ነበር ኳየር ውስጥ ስቀመጥ የነበርኩት? ሳለቅስ ፊቴን አይቼ አውቃለሁ፣ ስከፋ፣ ስናደድ፣ ሲጨንቀኝም አይቼ አውቃለሁ፡፡ ፊቴ እንደዛ ሲሆን ግን አይቼ አላውቅም፡፡ ጭፍግግ ያለ፣ ድብርብር ያለው ምን ልበልህ እየተሰቃየ ያለ ሰው ፊት ነበረ፡፡ ይሄን ፊት ነው ኳየር ውስጥ ተሸክሜ ስቀመጥ የነበረው? እኔ በመስታወት እያየሁ ያለሁትን ፊት የኳየር ልጆችም ሲያዩት ነበር? ለዚህ ነው ማለት ነው ልጆች የሆነ ልውጥውጥ ያለ ፊት ሲያሳዩኝ የነበሩት? “ምን ሆኖ ነው የሚጨነቀው አይነት ፊት” ልበል? ኳየር ስሄድ ልቤን ነበር የሚያመኝ፡፡ ልቤን ጭንቅ ይለኛል፡፡ ታዲያ እኔ ከፊቴ ጋር ግንኙነት ያለው አልመሰለኝም ነበር፡፡ ልቤን ለሚያመኝ ፊቴ የምን ቤት ነው? ቢያንስ እንኳን ህመሜን መደበቅ ስሞክር አይተባበረኝም? ፊቴ ግን ከነጭራሹን አጉልቶ ነበር የሚያሳየው፡፡ ልቤ ዘ ቫምፓየር ዳየሪስ ላይ እነዴመን ልባቸውን በተሳለ እንጨት ሲወጋጉ ይሰማቸዋል ብዬ ሳስበው የነበረው ስሜት ነበር ሲሰማኝ የነበረው፡፡ ለረጅም ሰአት ማለት ነው፡፡ ምን ላርግ? ተሰቃየሁ፡፡ በተለይ ፊቴን በመስታወት ካየሁ በኋላ፣ ስሄድ ልጆች የሚያስቡትን ነገር እያሰብኩ ባሰብኝ፡፡ ስሜቱን ለመደበቅ ሞከርኩ፡፡ ለመደሰት ሞከርኩ፣ አልቻልኩም፡፡ ደስተኛ ለመምሰል ሞከርኩ፣ አልቻልኩም፡፡ ደስተኛ ለመምሰል ሳቅ ሳቅ ለማለት ስሞክር እንዲያውም ለዛ አጣና ይባሱኑ “ልንገልህ ነው፣ ለማስታወሻ ፎቶህን እንፈልጋለንና ፈገግ በል” የተባለ ሚች ነበር የምመስለው፡፡
ስሜቱ አልሄድ አለኝ፡፡ ኳየር ውስጥ ወይም እዛ ልምምድ ላይ ስሆን ልቤ እሳት ላይ ተጥዳ እየተጠበሰች ያለች ነበር የሚመስለኝ፡፡ በዚያ ላይ እየተጨነቅኩ እንደሆነ የሚታወቅብኝ እንደሆነ ማሰቡ ደግሞ ሌላ ራስ ምታት ነበረ፡፡ ገና ከመግባቴ ኳየር አስጠላኝ፡፡ የት ገባ ያ ሁሉ እቅድ፣ ያ ሁሉ ህልም? What was happening to me?
ቤት ስገባ ደግሞ በሚያስቁ ፊልሞች ስሜቱን ለማባረር ሞከርኩ፡፡ ፊልም እነደበፊቱ አልጥም አለኝ፡፡ ፊልም እያየሁ ስለ ኳየር ነበር የማስበው፡፡ ልቦለድ ለማንበብ ሞከርኩ፡፡ ማተኮር ራሱ አልቻልኩም፣ እያነበብኩ ሌላ ነገር አስባለሁ፡፡ እያመመኝ ነበር፡፡ ቀኑን ሙሉ ስለ ኳየር፣ ስለቸርች ነበር የማስበው፡፡ ስላጋጠሙኝ ነገሮች፡፡ Every detail. የኳየር ልጆች ለጭንቀታም ፊቴ መልስ መስጠት ጀምረው ነበር፡፡ ለኔ ያላቸው አመለካከት ሲያሽቆለቁል፣ እኔን ሰላም ለማለት ያላቸው ፍላጎት ሲጠፋ ይታወቀኝ ነበር፡፡ እያነበብክ ያለኸው እንኳን ጽፌ አባዝቼ ብዙ ሰው እንዲያነበው ማድረግ ይቅርና ላስታውሰው የማልፈልገውን የህይወቴን የጨለማ ክፍል ነው፡፡ ከቀናት በኋላ ትኩሳት ተጨመረልኝ፡፡ ይሄ ኖርማሉ ትኩሳት ሳይሆን፣ ያቃጥለኛል አንገቴን፡፡ በተለይ ቸርች፡፡ እኔ ቤተ-ክርስትያን ሰው ከጭንቀቱ የሚገላገልበት፣ የሚፈወስበት ቦታ እንደሆነ እንጂ ጭንቀትን በራሱ ላይ ዲስከቨር የሚያደርግበት ቦታ እንደሆነ አልነበረም የማውቀው፡፡

ብቻዬን ነኝ፣ አብሬው የምሄደው ሰው የለኝም፣ ማንም አይቀርበኝም ማለት ጀመርኩ፡፡ ሰው፡፡ አብሮኝ የሚሄድ ሰው፡፡ ኳየር የሚሄድ ሰው፡፡ አንድ ሰው፡፡ ኳየር መሄድ መፍራት ጀመርኩ፡፡ ሶሎነት የት ገባ? ብቸኝነትን መውደድ የት ገባ? ልቅር? ገና ከመጀመሬ? ቤት ምን ብያቸው? በዚያ ላይ መቅረት አይቻልም፡፡ የ3ቱ ኳየሮቸ ልምምድ ወደ መድረክ ወጣ፡፡ መድረክ ላይ አቋቋማችንን አስተካክለን መለማመድ፡፡ ትዝ ይለኛል፡፡ የመጨረሻው መስመር፣ አሼ(የወጣቶች ሀላፊ) ዳር ላይ ነበር የቆመው፡፡ እኔ ደግሞ ከጎኑ ሄጄ ቆምኩኝ፡፡ ልምምድ እስኪጀመር ሌሎቹ እያወሩ ነው፡፡ እኔ ብቸኝነት፣ በውስጤ የሚቀርበኝ ሰው የለም ምናምን እያልኩ ልቤ ልትሰነጠቅ፡፡ አሼ ያየኛል፡፡ “ምን ሆኖ ነው ይሄ ልጅ” አይነት አስተያየት፡፡ ይታዘበኛል፡፡ ምን አርጌ ደህና ልምሰል? ደህና መሆን እንኳን ቢከብደኝ፣ መምሰሉ ያቅተኝ? እሱምኮ ብቻውን ነው ቆሞ የነበረው፡፡ እሱ ለምን አይደብረውም? ለምን ይታዘበኛል?
እንቅልፍ ስተኛ ምንም የተኛሁ አይመስለኝም፡፡ የጭንቀቱን ስሜት ጥላቻና ለመርሳት ቶሎ ብዬ ብተኛም ምንም ለውጥ አልነበረውም፡፡ የገረመኝ ደግሞ ጠዋት ከእንቅልፌ ስነቃ ገና ምንም ነገር ማሰብ ሳልጀምር፣ ኳየር ትዝ ሳይለኝ፣ ልቤን ያመኛል፡፡
ለቤት ነገርኳቸው፡፡ ኳየር ስሄድ ልቤን ጭንቅ ይለኛል ነበር ያልኳቸው፡፡ እስክትለምድ ድረስ ነው፡፡ ስትለምድ ይተውሃል አሉኝ፡፡ የሚተወኝ አልመስልህ አለኝ፡፡ ሊተወኝ አልቻለም፡፡ ኳየር ውስጥ ስሆንማ ያንገበግበኛል፡፡ የኳየር ልጆች እንዲህ ነው እንደዛ ነው አይሉኝም ግን፣ እንዲሁ በአይናቸው ይሄን ልጅ ምን ነክቶት ነው አይነት፣ ብቻ ለኔ ለየት ያለ አስተያየት ነበራቸው፡፡ አይናቸው ሲጠነክርብኝ ይታወቀኛል፡፡ መጀመሪያ እንደ ገባሁ ጊዜ የነበረልኝ ሰው አልነበረም፡፡ ኳየር ምንም ሊመቸኝ አልቻለም፡፡ አንዳንድ ልጆች ሰላም ልላቸው ስል ምናምን እኔን ሰላም ማለት የማይፈልጉ መሰለኝ፡፡ በጣም ናቁኝ፡፡

የኳየሮቹ የአንድነት ቀን እንዴትም እያስጠላኝ እየተሰቃየሁ ቀኑ ደረሰ፡፡ እየዘመርኩ፣ ድምጼ አልወጣ ብሎ ከጎኔ ያለ ሰው ወደኔ ዞሮ እየዘመርኩ እንደ ሆነ ቼክ የሚያደርገው ነገር በጣም የሚያሳምም ነበር፡፡ እንዴት እንደሚያም ቢገባህ ደስ ይለኝ ነበር፡፡
የመጀመሪያ የአገልግሎት ቀኔ በህይወቴ የሚያሳቅቅ ዝምተኛ ስቃይን ከቀመስኩባቸው ቀናት አንዱ ነው፡፡ ዘመርን፡፡ ያው እሁድ ነበረ፡፡ ከዘመርናቸው መዝሙሮች መሀል የጽናት(የነወንድሜ) ኳየሩ፡

ከአንተ ወዴት እሄዳለሁ?
ምንስ ብልጫ ምንስ ደስታ ምንስ ትርፍ

ከአለም አገኘሁ?
ትሻለኛለህ ጌታ አንተን መርጫለሁ
ትሻለኛለህ ኢየሱስ አንተን ወድጃለሁ

የዚህ አለም ደስታ ምቾቱ ድሎቱ
ልቤን እንዳይማርከ በልጦብኝ ውበቱ
የላቀውን ውበት አሳየኝ ከሰማይ
ከአለም ምናምንቱ ተለይቼ እንድታይ...የሚለው ትዝ ይለኛል፡፡

ከፕሮግራም በኋላ ያን ቀን ጉባኤው ሲወጣ፣ መዘምራን ክብ ሰርተው ሞቅ ያለ መዝሙር እየዘመሩ መዝለልና መጨፈር ጀመሩ፡፡ እኔ የት አባቴ ልግባ? ወይ የሚዘምሩትን መዝሙር አላውቅ፣ ወይ አብሬ አልዘል፡፡ መገርሳ መሰረተ ክርስቶ መጥቶ Leenca Qaraaniyoo የሚለውን መዝሙር ሲዘምር መድረክ ላይ ወጥቼ ከሱ ጎን እንዳልዘለልኩ፣ አርነት ቸርች፣ ቢሊሴ መጥታ Amman gubaa garaa diina koo ስትዘምር እስከመታፈን እንዳልደረስኩ፣ የሁለገብ አዳራሽ መድረክ ላይ አንድ ኮንፍረንስ ላይ ልብሳቸውን አውልቀው ሲጨፍሩ ከነበሩት መሀል አንዱ እንዳልነበርኩኝ፣ ዝም ብዬ እጄን ማጨብጨብ ብቻ፡፡ ያኔ ልጅ ስለነበርኩኝ ነው እንዳልል ከፊት ለፊቴ ሲጨፍሩ ከነበሩት ብዙዎቹ እኔን የሚበልጡ ናቸው፡፡ እንደነሱ ፈታ ብዬ በስሜት ብዘምር፣ ብዘልና ብጨፍር ደስ ባለኝ፡፡ ግን ላባርረው የማልችለው፣ በማስመሰል ልሸፍነው የተሳነኝ ልቤን እየቦረቦረ የነበረ የጭንቀትና የድብርት ስሜት አስሮኝ ነበረ፡፡ የምለው ይገባሃል? ምናለበት ቀጥ ብዬ ወደ ቤቴ በገባሁ? ደህና እንዳልሆንኩ ማንም መናገር ይችላል፡፡ ብቻ ተደነጋገርኩኝ፡፡
በጣም አገልግሎት ደስ እያለኝ እንዳልነበረ ለወንድሜ ነግሬው ነበረ፡፡ ከጓደኞቹ ጋር ውጪ ቆሞ ነበርና እኔ ጥግ ይዤ እንዲሁ ለይስሙላ እያጨበጨብኩ ከውጪ በመስኮት በኩል አይቶኝ ቤቢ.. ምናምን ብሎ ለጓደኞቹ አሳይቶኝ፣ ሀይ ምናምን አለኝ፡፡ የሚጠራኝ ሰው አስፈልጎኝ ነበር፡፡
የኳየሮች አንድነት ቀን ስለነበረ፣ ከፕሮግራም በኋላ ያን ቀን የምሳ ግብዣ ነበረ፡፡ በኋላ ምሳ እዚያው ጓሮ ውጪ ላይ ነበረ፡፡ ብቻዬን ነበርኩ፡፡ ብቻህን እንዲህ አይነት ቦታ በጣም ይከብዳል፡፡ “ምንድነው? የምትበላውን ወስደህ፣ መብላት ነው፡፡ ምን ያካብዳል?” ልትለኝ ትችላለህ፡፡ ለኔ ግን ያን ያህል ቀላል አልነበረም፡፡ ሄድኩኝ፡፡ ብቻዬን ሄጄ መውሰድ እየቀፈፈኝ እያለ ለካስ ምግቡን እየሰጠ የነበረው ወሰን የኳየሬ ኮሚቴ ነበረ፡፡ ና አለኝና ወጥ ተጨምሮበት የሚጠብቀውን እንጀራ አቃበለኝ፡፡ በጣም የሚገርመኝ ኳየር በነበርኩበት ጊዜ እንደዛ እየተሰቃየሁ ፊቱን ያልቀያየረብኝ ሰው ያንን ልጅ አየሁ፡፡ ለምን? ወንድሜን በጣም ስለሚያከብረው ይመስለኛል፡፡
እጄን ታጥቤ ተቀምጬ ለመብላት ዙሪያዬን ሳማትር የኳየሬን ልጆች እነጉዲሳን አየኋቸው፡፡ 4 ልጆች የነበሩ ይመስለኛል፡፡ ከፊት ለፊት እያዩኝ ነበር፡፡ “ና እኛ ጋር ተቀምጠህ ብላ” ይሉኛል ብዬ ስጠብቅ አልጠሩኝም፡፡ ዝም ብለው አዩኝ፡፡ ለምን ዝም ብዬ አጠገባቸው ሄጄ አልተቀመጥኩም? ለምን እስኪጠሩኝ ጠበቅኩ? ወይም ለምን እንዲጠሩኝ ፈለግኩ? አጠገባቸው እንድቀመጥ የማይፈልጉ ስለመሰለኝ ይሆን? ምንም ቢሆን ግን ከነሱ ትንሽ ፈቀቅ ብዬ እነሱው አጠገብ ነበር የተቀመጥኩት፡፡ ምንም አላሉኝም፣ ምንም አላልኳቸውም፡፡ እነሱ ወደ መጨረስ አካባቢ ነበሩ፡፡ እኔ ተቀምጬ ብዙም ሳልቆይ ሁሉም ተነስተው ሄዱ፡፡ ብቻዬን ምነው ቤቴ በገባሁ ብዬ እየተቃጠልኩ እያለ ወንድሜ እኔ ወዳለሁበት መጣና አየኝ፡፡ መልአክ ከሰማይ የወረደልኝ ነበር የመሰለኝ፡፡ በጣም ብቸኝነት ተሰምቶኝ ነበር፡፡ ጓደኛ የለኝም፣ ማንም ሊቀርበኝ የሚፈልግ የለም... ወንድሜ “ምነው ብቻህን? ለምንድነው ሁሌ ብቻህን የማይህ?” አለኝና ቆሞ ሌላ ነገር እያወራ ወሰን መጥቶ እኔ ጋር ተቀምጦ መብላት ጀመረና ከወንድሜ ጋር ትንሽ ተበሻሸቁ፡፡ እኔ ከጎናቸው ምን እየተሰማኝ እንደሆነ ቢያውቁ፣ ባስተዛዘኑኝም ነበር፡፡

ከምሳ በኋላ የኳየሮች ውይይት ነበረ፡፡ ቆይ እኔ ግን ምን ነክቶኝ ነው ወደ ቤቴ የማልገባው? መቅረት አይቻልም፣ አቋርጦ መግባት አይቻልም፣ የሚሏቸውን ህጎች ፈርቼ ነው ማለት ነው? ለውይይቱ ወደ ቤት ውስጥ እየገባን አንድ አብሮኝ እምነት ማጽኛ የተማረ ልጅ መጣና፣ ና ወደ መጀመሪያ እንቀመጥ አለኝ፡፡ ደስ አለኝ፡፡ ሰው አገኘኋ፡፡ ሁለተኛው ወንበር ላይ ነበር የተቀመጥነው፡፡ ሳየው ማንም ከኛ ጎን መጥቶ የሚቀመጥ የለም፡፡ ለምን? እኔ አላውቅም፡፡ እድሌ ሊሆን ይችላል፡፡ ፕሮግራሙ ተጀመረ፡፡ እየተጸለየ እያለ ወደ መጀመሪያ እንሂድ ያለኝ ልጅ ከጎኔ ተነሳ፡፡ ምን አይነት ቀን ነው? እድሌ ነው፡፡ ከጸሎት በኋላ ለካስ መዝሙርም ነበረ፡፡ ሶስት ሴቶች ነበሩ የሚዘምሩት፡፡ ሁለቱ(ሀናና ሜሪ) ኳየሬ ነበሩ፡፡ አንደኛዋ ደግሞ ጽዮን ኳየር ስትሆን የኛ ት/ቤት የምትማረዋ ስምረት ነች፡፡ ኪቦርድ የሚመታው ደግሞ ማን ቢሆን ጥሩ ነው? ወንድሜ፡፡ ሜሪ እየዘመረች እያለ እኔንና ወንድሜን እያፈራረቀች ታያለች፡፡ እኔ በልቤ “እንዴ እቺ ልጅ ወንድሜ ኪቦርድ ስለሚመታ ብዬ ወደ ፊት የመጣሁ መሰላት እንዴ?” እላለሁ፡፡ አታቋርጥም ደግሞኮ፡፡ እሱን ታይና እኔን ታያለች፡፡ እኔን ታይና እሱን ታያለች፡፡ የምን ጉድ ነው? ሲቀጥል ቆመን እንዘምራለን አሉ አስዘማሪዎቹ፡፡ ቆምኩኝ፡፡ ተዘመረ ተዘመረ፣ ዘማሪዎቹ ዝም ብለው ያፈጡብኝ ነበር፡፡ እንዴ? ፊቴ በጭንቀት እንደማይሆን ስለሆነ ብቻ ነው ወይስ እኔ ብቻ ነኝ ቆሜ ያለሁት? ብዬ ተወዛገብኩ፡፡ ወደኋላ እንዳልዞር ፈራሁ፡፡ የምሆነውን ሳጣ ወጣሁኝ፡፡ ስወጣ በር አጠገብ ፕሮግራም መሪው ጋሩማ ነበር፡፡ ወደ ቤት እየገባሁ መስሎት ምንም አላለኝም ግን ተናደደ፡፡ ለምንድነው ምትገባው? ገና ስብሰባ አለንኮ አይነት፡፡ በቅርቡ በር ነበር የወጣሁት፡፡ ቸርቹ ከሆዱ ላይም በር አለው፡፡ ፊት ለፊት ባለው በር ወጥቼ ወደ ቸርቹ መሀል በሚያስገባው የሆዱ(የመሀሉ) በር ገብቼ ተቀመጥኩ፡፡ እዛ ደግሞ የጓደኛዬ የዮሴፍ ጓደኛ ብቻውን ተቀምጦ ስልኩን ሲጎረጉር ነበር፡፡ ብቸኝነቱን እያጣጣመ ይመስል ነበር፡፡ እኔ ለምን እንደሱ ዘና ማለት አቃተኝ? ብቸኝነት በጣም እየተሰማኝ ስለነበር ሌላ ሰውን ብቻውን ሳይ እኔ ለምን እጨነቃለሁ፣ እሱ ለምን አይጨነቅም እያልኩ ግራ እጋባለሁ፡፡ ፕሮግራሙ እንዳለቀ ማንም ሳይቀድመኝ ውልቅ፡፡

የወንድሜ ጓደኛ ማሙሽ አይቶ ጠርቶኝ አንተ ሰው ሰላም አትልም እንዴ? አለኝ፡፡ "ሰው ሰላም ለማለት ውስጣዊ ሰላም ያስፈልጋልኮ ማሙሽ" አላልኩትም፡፡ ውስጣዊ ሰላም፡፡ ያን ቀን ነበር እየተጣደፍኩ ወደ ቤት አየገባሁ ቦታው ራሱ ትዝ ይለኛል፣ ወደኛ ቤት በሚያደርሰው መታጠፊያ ላይ እንደ ደረስኩ፣ "ገሀነም ከዚህ በላይ ስቃይ አለው ማለት ነው? ከዚህ በላይ ስቃይ አለ ማለት ነው? እንዲህ ሆኖ ከመኖርማ መሞት ይሻላል" አልኩኝ፡፡ ሞትን መፍራት ያቆምኩበት ቀን፡፡ ረጅም እድሜን የተመኘሁባቸው የልጅነት ጊዜያት ነበሩ፡፡ ዘግይቼ በተወለድኩ ያልኩባቸው የህጻንነትና የየዋህነት ጊዜያትም ትዝ ይሉኛል፡፡ አሁን ግን ብሞት ደስ ይለኛል፡፡ ባዶነት፣ ቀፎነት ተሰማኝ፡፡ አጥንትና ስጋ የሌለኝ አይነት፡፡ ስቃይ አጥንቴ፣ መከራ ስጋዬ የሆኑ አይነት፡፡ ልቤ ደም ሳይሆን ጭንቀት ወደያንዳንዷ የሰውነቴ ክፍል የሚረጭና የሚያሰራጭ መሰለኝ፡፡ ልቤንኮ እንዴት ሲያረገኝ እንደ ነበረ ብታውቅ? "ተሰቃየሁ" ይገልጸዋል እንዴ?

ቤት እንደ ገባሁ ወደ 10 ሰአት ወደ መስታወት ተጣደፍኩ፡፡ ራሴን ጠላሁ፡፡ ቀኑ እሁድ ነበር፡፡ ቀጣዩ ቀን ደግሞ ሰኞ ነው፡፡ ሰኞ በ12 ሰአት ደግሞ ኳየር አለብኝ፡፡ ኳየር የሚባል ነገር መቼ ነው የተፈጠረው?

ስለ አንድነት ቀን ነበር ወሬው፡፡ እኔ በፊት ኳየር ሳልገባ በፊት እንኳን መደባደብ፣ መሰዳደብ ይቅርና ቸርች ግቢ ውስጥ ክፉ ነገር ማሰብ እፈራ ነበር፡፡ ጌታ ሆይ ይቅር በለኝ እል ነበር፡፡ ኳየር ስላልገባኝ ነው፡፡ ይሰዳደባሉ፣ ሊደባደቡ ምናምን፡፡ እንዴ? እላለሁ እኔ፡፡ ምንም የእግዚአብሔር ቤት ይቅርና ሌላ ቦታ የማልሰማቸውን ነገሮች ነበር የማየው፡፡ መናናቅ፣ መሰዳደብ፣ ተንኮል…፡፡ እንዴ? እነኛን ችግሮች ለማስተካከል፣ ኳየሩ እግዚአብሔርን በማያሳዝን መንገድ ላይ የመምራት ፍላጎት ነበረኝ፡፡ ኳየር፣ ወይም ሌላውን ከማስተካከል በፊት ግን የተስተካከለ ማንነት ያስፈልጋል፣ ውስጣዊ እርጋታ ያስፈልጋል፡፡ አንድን ኳየር፣ በትክክለኛው አቅጣጫ መንገድ ላይ ለማስጓዝ ኳየሩ ውስጥ መገኘት ወይም የኳየሩ አባል መሆን ያስፈልጋል፡፡ እኔ ኳየር ውስጥ ህመሙን ማስታመም ያቃተው ሰው እንጂ የኳየሩ አባል አልነበርኩም፡፡ እኔ "ኳየር ደረሰ ደግሞ…ምንድነው ሰአቱ እንዴት ይንቀራፈፋል? መቼ ነው ከዚህ ወጥቼ ወደ ቤቴ የምገባው?" የሚል አይነት አባል ነበርኩ፡፡

ጉደቱ ኳየርን የኛ ኳየር ለማለት ብዙ ጊዜ ነበር የፈጀብኝ፡፡ ፊይሳን ለአይን ጠላሁት፡፡ አስተያየቱ ያሳምም ነበር፡፡ ሰላም እንኳን ሊለኝ አይፈልግም፡፡ ኳየር ውስጥ የልምምድ ጊዜ ሲዘመርና እሱ ሰያስዘምር፣ እኔ ድምጽ አልወጣ ሲለኝ፣ ወደኔ መጥቶ ጆሮውን ወደኔ ያስጠጋል፡፡ That was "disgusting!" ድምጼ ደግሞ፣ ጉሮሮዬ እስኪሰነጠቅ ነው የምዘምረው ግን ምንም አይሰማም፡፡ ፍርሀትና ጭንቀት ነውኮ፡፡ እንጂማ ቤት ስበጠብጥ ነው የምውለው አይደል እንዴ? ቤት ሆኜ ስዘምር ለምንድነው ኳየር እንደዚህ የማልዘምረው? እያልኩኝ እናደዳለሁ፡፡ ብቻ እኔ፣ ኳየሩ እንዳለ ነበር ባጠቃላይ ያስጠላኝ፡፡ መገለል(isolated መደረግ) ተሰማኝ፡፡

ጉደቱ ኳየር ብዙ ቀናት አገልግሎት የሚሰጠው ኳየር ነበረ፡፡ በወር ሶስቴ ምናምን፡፡ በጥቂት ወራት ውስጥ ብዙ ማገልገል ቻልኩኝ፡፡ እዛው ቸርቻችንና፣ ራቅ ብሎ በእግር የሚኬድበት ደግሞ ሶር ወንዝን አልፎ አንድ የቸርቻን ጣቢያ አለ፡፡ አንድ ቀን መጀመሪያ ሄድኩኝ፡፡ ሩቅ ነው ያደክማል፡፡ ስንሄድ ልጆች እያወሩ፣ እየተጫወቱ ነበር የሚሄዱት፡፡ እኔ ደግሞ ከአንዲት እንደኔው ልጆች የማያቀርቧት ግን ምንም የማይመስላት፣ ያንን እንኳን የምታውቅ ከማይመስለኝ ልጅ ጋር ነበር የሄድኩት፡፡ ታወራለች፣ ታወራለች፡፡ እኔ እእ እእ ከማለት ሌላ መልስ አልነበረኝም፡፡ እሷ ግን እያዳመጥኳት እንደሆነ እንኳን እርግጠኛ ሳትሆን ትለፈልፍልኛለች፡፡ የምታወራውን ነገር ደግሞ እኔ አላምናትም፡፡ ስለ ራሷ ነበር ሁሌ፡፡ ግን እሷስ ባትኖር ምን ይውጠኝ ነበር? ብቻ ስንሄድና ስንመለስ "እኔ ማነኝ?" ነበር ያልኩት፡፡ ሌሎቹ ሲጫወቱ አብረው እያወሩ ሲሄዱ፣ እኔ የልጅቷን ወሬ እያዳመጥኩ እየሄድኩ አያቸዋለሁ፡፡ ብቸኝነት ሊገለኝ፡፡ መንገዱ ደግሞ ያደክማል፡፡ በዚያ ላይ ጉንፋን፡፡ ኳየር ከጀመርኩ ወዲህ ኬጂ እንደገባ ህጻን ጉንፋን አከታትሎ ያጣድፈኛል፡፡ በየሁለት ሳምንቱ፣ በየወሩ፡፡ ማስነጠስ ነው፣ ንፍጥ ነው፡፡ እሱ ይመስለኛል እንዲያውም ድምጼን የሚዘጋው፡፡ ጭኝቀቱ የሰውነቴን በሽታን የመከላከል አቅም ሳያመናምነው አልቀረም፡፡ በተለይ መንገድ ላይ እየሄድኩ የሆነ የሞተ እንስሳ፣ ወይም የቱም የሚከረፋ ነገር ሲሸተኝ፣ በነጋታው ጉነውፋን እንደሚይዘኝ እርግጠኛ ነኝ፡፡

ሶር በሄድን የመጀመሪያ ቀኔ፣ ተሰቃይቼ፣ ተሰቃይቼ ወደ ቤት ስንገባ ሌሎቹ አንዲት አቋራጭ ላይ ሲገነጠሉ፣ እኔና ቢቂላ ሰፈራችን ከሌሎቹ ስለሚለይ ከነሱ ተነጥለን ነበር በዋናው መንገድ ጉዟችንን የምንቀጥለው፡፡ ከነሱ ተገንጥለን ትንሽ እንደሄድን አያንቱ የምትባል ልጅ ቢቂላ ብላ ከሩቅ ተጣራች፡፡ ዞር ሲል "ቻዎ" አለችው፡፡ የኔን ስምም ታውቅ ነበረ፡፡ ግን አልጠራችኝም፡፡ እኔን ለማናደድ ብላኮ ነው፡፡ ምን አይነት ኳየር ነው የገባሁት? አዲስ ገቢ እንዲህ ነው የሚያዘው? ያ አያንቱ ቢቂላን ጠርታ ቻዎ ብላው እኔን የተወችው ነገር ባይገርምህ ከምታስበው በላይ በጣም ነበር የተሰማኝ፡፡ ባይሆን ኖሮማ ከሁለት አመት በኋላ የማስታውሰውና የምጽፈው ነገር ባልሆነ፡፡ ደግሞኮ የኔና የልጅቷ ወላጆች ይቀራረቡ ነበር፡፡ ኳየሩን እንድለምድ ታግዘኛለች ስል ኳየሩን እንድጠላ ካደረጉኝ ሰዎች መሀል አንዷ ሆና አረፈችው፡፡

የኳየር ነገር ልሸከመው ከምችለው በላይ እየሆነ ነበር፡፡ በሚቀጥለው ሶር አገልግሎት ሲኖረን ለወንድሜ "አልሄድም" አልኩት፡፡ "ትሄዳታለህ፣ እየመረጥክ ነው እንዴ የመታገለግለው?" አለኝ፡፡ ለርቀቱ ያልኩ መስሎት ነው፡፡ ያን ቀን ስቃዬ ባሰብኝ፡፡ ያን ቀን ከሶር ድልድይ ላይ ራሴን ወርውሬ ብፈጠፋጥ ደስ ይለኝ ነበር፡፡ ጉንፋን ይዞኝ ነበር፡፡ አገልግዬ ወደ ቤት እየገባሁ እያለ ጎረቤታችን አቶ በላቸው አየኝና፣ "ከየት ነው የምትመጣው?" ብሎ እየጠየቀኝ እያለ ይነስረኝ ጀመረ፡፡ እሱ አላየም፡፡ ሀገር ሰላም ብሎ ያወራኛል፡፡ እኔ አፍንጫዬን ይዤ አናግረዋለሁ፡፡ ቤት ስንደርስ አየኝና ደንግጦ "እኔኮ አላየውም ዝም ብዬ ሳናግረው ነበር" አለ፡፡ ጉንፋን ሲይዘኝ ብዙ ጊዜ ይነስረኛል ግን ያን ቀን ጭንቀቱ ሰውነቴን አፍልቶ ባፍንጫዬ ደም ያስወጣኝ ይመስለኛል፡፡

አንዱ(የሰፈራችን ልጅ ነው) ኳየር መምጣት ጀመረ፡፡ አቋርጦ ነበር፣ መምጣት ጀመረ፡፡ ተመቸኝ አብረን ነበረ የምንሄደው፡፡ እንደዛ ጭንቅ እያለኝ እንኳን አንዱ ለኔ አሪፍ ነበረ፡፡ እንደ ጓደኛው ነበር የሚቆጥረኝ፡፡ ፊታ ያለ ልጅ ነው፡፡ ኳየር አብረን ነበረ የምንሄደው፡፡ ለጥቂት፣ በጣም ለአጭር ጊዜም ቢሆን፣ አንዱ የብቸኝነት ስሜቴን አጥፍቶልኝ ነበር፡፡ አንድ ቀን ኳየር፣ ልጆች ሞልተው፣ የምቀመጥበት አጥቼ ግራ ስጋባ በሌለ ቦታ ሰው ተጋፍቶ "ና እዚህ ጋር ተቀመጥ" ብሎ አጠገቡ ሲያስቀምጠኝ ደስ አለኝ፡፡ እንዲህ ነው አዲስ ገቢ መንከባከብ የነበረባቸው፡፡ አይደል? ስፈልገው የነበረው ነገር፡፡ የሚያስብልኝ ሰው፡፡ አንዱ ኳየር ውስጥ ያወራል፡፡ እኔን ሲያወራኝ፣ "ወሰን ይቆጣል፣ ወሰን እያየን ነው" ስለው፣ "ምንድነው ወሰን? በጣም ታካብደዋለህ ማለት ነው" አለኝ፡፡ በርግጥ እኔ ያላካበድኩት ሰው አልነበረም፡፡ በሁሉም መወደድ እየፈለግኩ፣ ሁሉም የናቀኝ ሰው ነበርኩ፡፡ ያንን መቀበል ለኔ በጣም ነበር የከበደኝ፡፡ማንም እዚያ ኳየር ውስጥ እኔን ለመናቅ የሚበቃ ሰው አልነበረም፡፡ መናቁ ከኔ ነበር የሚያምረው፡፡ እውነቴን ነው ክብር ጠማኝ፡፡ጊዜዬን በሙሉ ከኳየር ልጆች ጋር ያለኝን ግንኙነት እንዴት ማሻሻል እንደምችል እያሰብኩ ይመሸና ይነጋ ነበር፡፡ ነገሮች ግን ከቀን ወደ ቀን እየከፉብኝ የሚያስቀይመኝ ሰው ብዛት እየጨመረ ነበር የሄደው፡፡ የተሞኘሁት፣ በጭንቀት ሊፈነዳ የተነሳን ሰው ሊቀርብ የሚፈልግ ሰው እንደሌለ አለማስተዋሌ ነው፡፡ ወይም ይሄን እያወቅኩ ከልጆች ጋር ለመቀራረብ በጣም መፈለጌ ነው፡፡ ጭንቀቴን አይተው ልጆች አልቀርብ አሉኝ፡፡ የጭንቀቴ ምክንያት ብቸኝነት ወይም መገለል ስለሆነ ሊፈውሰኝ የሚችለው ደግሞ ከልጆች ጋር መቀራረብ ነበር፡፡ የጭንቀቴ ምክንያት ከልጆች ጋር መቀራረብ ነው፣ ስለምጨነቅ ደግሞ ከልጆች ጋር መቀራረብ አቃተኝ፡፡ ሲያወሩኝ እንኳንኮ የምመልስላቸውን ነገር አላውቅም፡፡ በቃ ጭንቀት ነው፡፡ የሚያስቅ ነገር ሲወራና ሌሎቹ ሲስቁ እኔ መሳቅ ይከብደኛል፡፡ በዚያ ሰአት ከልጆች ጋር ጥሩ ግንኙነት መፍጠር አንደኛው የህይወቴ ግብ ነበር፡፡ ቆሜ ተቀምጬ፣ ተኝቼ የማስበው ስለኳየርና ከኳየር ልጆች ጋር ስለነበረኝ ውሎ፣ እንዲሁም ከልጆች ጋር ያለኝን ግንኙነት እንዴት እንደማሻሽለው ነበር፡፡

ለአንድነት ቀናቸው 50፣ 50ብረ አዋጣን፡፡ መስከረም በገባ በሁለተኛው እሁድ ነበር ፕሮግራሙ፡፡ የጉደቱ ኳየር የ8ኛ አመት የምስጋና ፕሮግራም፡፡ ወንድሜ ወደ አዲሳባ የሚመለስበት ቀን ነበር፡፡ ጠዋት ተነስቼ ሸኘሁትና ሄድኩኝ በጠዋት፡፡ በግ ታርዶ ምናምን ነበር፡፡ ስራ ሰራን፡፡ በህይወቴ በጣም ረጅሙ ቀን፡፡ አገልግሎት የኛ ነበር፡፡ አንዱም መጥቶ ነበር፡፡ ወደ 9 ሰአት ነበር ፕሮግራሙ፡፡ ከየኳየሩ ልጆች ተጋብዘው ነበር፡፡ ከነዛ መሀል ኦዳ(የድሮ ጎረቤታችን) ነበር፡፡ እኔ አንድ ጎን ላይ ብቻዬን ተቀምጬ ነበር፡፡ ሲዘመር ምናምን በተለይ እንግዲህ እኔ በጣም ነው የሚጨንቀኝ፡፡ ኦዳ ዝም ብሎ ያየኛል፡፡ ኦህ ተሰቃየሁ፡፡ እኔ መጨነቄ አይደለም የሚያናድደኝ፡፡ ሌላው ሰው የሚነቃብኝ ነው እንጂ፡፡ ሲነቃብኝ ደግሞ ይለዋወጥብኛል፡፡ ተጋባዥ እንግዶች ስለኳየሩ አስተያየት የሚሰጡበት ጊዜ ነበረ፡፡ ኦዳ እድሉን ሲሰጠው፣ ማውራት ጀመረ፡፡ እንዴ? ኦዳ ወሬ ይችላል፡፡ "እኔ ድሮ ይሄ ኳየር ያስቀናኝ ነበር፣ ልጆች ሲጸልዩ ምናምን ስሰማ…አሁን የምሰማው ግን ስለጉደቱ ኳየር እንደዚያ አይደለም፡፡ ወደ ድሮዋችሁ መመለስ ብትችሉ ጥሩ ነው" አለ፡፡ ቄስ ታምሩ ደግሞ "ይሄ ኳየር ኪቦርድ ተጫዋች የለውም፡፡ ለምን ከአዲሶቹ መሀል አሰልጥናቹ እንዲጫወቱላችሁ አታደርጉም"፡፡ ብለው የኳየራችንን መሪ ወሰንን ጠየቁት፡፡ "ከነባሮቹም እየተለማመዱ ጥሩ ደረጃ ላይ እየደረሱ ያሉ አሉ፣ ከአዲሶቹም መሀል እናሰለጥናለን" አለ ወሰን፡፡ ቄስ ታምሩ ስለኔ ብቻ ሳይሆን እኔን እያዩ ነበር ሲያወሩ የነበሩት፡፡ ወሰንም እናሰለጥናለን ሲል በዋነኛነት እኔን ነበር፡፡ ወንድሜ ኪቦርድ ስለሚመታ ብለው ነው፡፡ ይመስላል ታዲያ? ት/ት ተጀምሮ ትንሽ እንደ ቆየ አንዱ መምጣት አቆመ፡፡ እንዲህ እንዲህ በህይወቴ በብቸኝነትና በመገለል አስፈሪውን ሆረር የሆነ ስሜት ሳስተናግድ፣ ትምህርት ቤት እስኪከፈት ድረስ ብቻ እንደሆነ አውቀው ነበር፡፡ ከነኢዩኤል ጋር ስገናኝ እነፈይሳ ትዝም አይሉኝም፡፡ ብቸኝነቴም ታሪክ ይሆናል፡፡

ጥቅምት ውስጥ ት/ቤት ተከፈተ፡፡ መጀመሪያ ቀን ስሄድ አስተማሪ ክፍል ገብቶ ነበር፡፡ ያለፈውን አመት 9ኛ ክፍል ላይ የሚገርም ጊዜ አብረን ያሳለፍነው፣ ኢዩኤል ሁለተኛ ረድፍ ላይ የመጀመሪያው ዴስክ ላይ ፊት ለፊት ተቀምጧል፡፡ ሀይ ብዬው አልፌው ወደማውቃትና ወደምወዳት የመጨረሻ ዴስክ ላይ ሄጄ ተቀመጥኩ፡፡ ትንሽ ቆይቶ በረከት መጣና ኢዩኤል ጋር ተቀመጠ፡፡ እኔ ከአሚርና ኢሳያስ ከሚባል ልጅ ጋር ነበር የተቀመጥኩት፡፡ እኔ እንግዲህ እነኢዩኤል ለዛች ቀን ብቻ ነው መጀመሪያ ላይ የተቀመጡት፣ ወደኔ ይመጣሉ ብዬ ነበር፡፡ በነጋታው ስሄድ ኢዩኤል፣ እዛው መጀመሪያ ተቀምጦ አየሁት፡፡ ባጠገቡ አልፌ ወደቦታዬ ልሄድ ስል "ና ባክህ እዚህ ተቀመጥ" አለኝ፡፡ "ፊት ለፊት መቀመጥ አልወድም" ባክህ አልኩትና ወደ ቦታዬ፡፡ አሁንም በረከት መጣና ዱቅ አለ፡፡ ሜቲ ለሁለት እንደሚቀመጡ አይታ እሷም እነሱ ጋር ደቀሰች፡፡ አከተመ፡፡ እስከ አመቱ መጨረሻ የነበረን አቀማመጥ ይባላል፡፡ ከኢዩኤል ጋር ተራራቅን፡፡ ተለያየን፡፡ ጭንቀቴ ት/ቤትም ተከትሎኝ መጣ፡፡ ምን አባቴ ይዋጠኝ፡፡ ክፍላችን አስጠላኝ፡፡ የመጨረሻው ወንበር ላይ አብሮኝ የሚቀመጠው አሚር ሲያወራኝ ወሬ እያማረኝ አይደለም አሚሮ አልኩት፡፡ ተናደደ፡፡ ክፍል ውስጥ አብሮህ የሚቀመጥን ሰው ወሬ እያማረኝ አይደለም ማለት፣ በጣም ከባድ ወንጀል ነው፡፡ በተለይ የምትለው ሰው የሚያውቅህ አስር ደቂቃ ዝም ካልክ "ምነው ዝም አልክ?" የምትባል አይነት ሰው እንደሆንክ የሚያስብ ከሆነ፣ እኔ 9ኛ ክፍል እንደነበርኩት አይነት ወሬኛ አርጎ የሚያስብህ ከሆነ፡፡ እንደኔ ዝም ማለት፣ እንደኔ ለአሚር ወሬዎች መዘጋትና ድብርተኝነት ቢሆን፣ ልጁ ከኔ ጋር ተነስቶ ሌላ ሰው ጋር ተቀምጦ ጭራሹን ብቸኝነቴን ባባባሰብኝ፡፡ ብቻዬን ይተዋኛል ብዬ በጣም እሰጋ ነበር፡፡ ደግነቱ ሌላ ቦታ አልነበረም፡፡ ከኔው ጋር ስንደባበር ቆየን፡፡ እኔ ኢዩኤል ጋር መቀመጥ ነበር ፍላጎቴ፡፡ አልቻልኩም፡፡ ለምን ዝም ብዬ ከአሚር ጋር አልመቻቸም? ከኢዩኤል ጋር መለያየት የአለሜ ፍጻሜ ነበር የመሰለኝ፡፡ ኳየር ጥግ ይገፔ ተመልካች እንደሆንኩ ሁሉ፣ ት/ቴም እሱ ራሱ ተደገመ፡፡ ያለፈው አመት የነበረው በራስ መተማመኔ፣ ሳቄ፣ ተጫዋችነቴ አብሮኝ አልነበረም፡፡ ካደኝ፡፡ ከዳኝ፡፡

ያለፈው አመት ከኢዩኤል ጋር የነበረን ጓደኝነት ሲያስቀናው የነበረው በረከት ምኞቱ ተሳካለት፡፡ ከኢዩኤል ጋር አንድ ወንበር ላይ መቀመጥ ብቻ ሳይሆን በጣም ተቀራረቡ፡፡ እኔ መጨረሻ ላይ ብቸኝነት ሲያሰቃየኝ፣ "ዞሮ ዞሮ ይሄ ልጅ ምን ሆኖ ነው" በሚል አስተያየት ያየኝ ነበረ፡፡

ትምህርት ሲጀመር ከቸርች ያጣሁትን ከት/ቤት አገኛለሁ ብዬ ነበር፡፡ እንደ ኖርማል ሰው የሚያናግረኝ ሰው ናፍቆኝ ነበር፡፡ የሚያከብረኝ ሰው፡፡ እኔ ከኢዩኤል ጋር እንደማልቀመጥና ሞራሌ እንደ ወደቀ ያዩ የክፍሌ ልጆች፣ ያኔ ትኩረቴን ሲሻሙ እንዳልነበረ አይኖቻቸውን አጠነከሩብኝ፡፡ ናቁኝ፡፡ ይሄ የማልወጣው ችግር ነበረ፡፡ የቸርች ልጆች የቸርች ልጆች ናቸው፡፡ ጸባዬን አያውቁም ነበር፡፡ ከሁሉም ጋር እንደ አዲስ ነበር የተገናኘሁት፡፡ እነኚህ ግን የክፍሌ ልጆች ናቸው፡፡ እንደዛ ከፍ ከፍ እንዳላደረጉኝ፣ በወራት ልዩነት ከጫማቸው በታች ነበር ያደረጉኝ፡፡ ያለፈው አመት ተቃራኒ ነበር የሆነው ሁሉም ነገር፡፡

ከ9ኛ ክፍል መጨረሻ አካባቢ ጀምሮ እነኢዩኤል አዲስ ቡድን መሰረቱ፡፡ አብረው ነው የሚያድሩት፣ አብረው ነው የሚውሉት፡፡ ኢዩኤል፣ በረከትና ድሮ 8ኛ ክፍል አብረን የተማርነው ሙባረክ የቡድኑ ዋነኛ አባላት ነበሩ፡፡ ከክፍላችን እነአብዱ፣ ምናምን የነበሩበት ሲሆን፣ ብቻ በኛ ባች አራዳ ናቸው የምላቸው ልጆች ያሉበት ቡድን ነው፡፡ እኔ ልኖርበት ይገባኝ የነበረ ቡድን ነው፡፡ ልጆቹ እረፍት ላይ ይገናኛሉ፣ አብረው ይውላሉ ምናምን፡፡ ኢዩኤል፣ ብንራራቅም አልተለያየንም ብዬ አጠገቡ ሄጄ ስቀልድ በቃ የኔና ያንተ ነገር አብቅቶለታል ነገር ሆነብኝ፡፡ እንዲሁ ለቀልድ ስሰድበው ምናምን ይዞ ግጥም አድርጎ ብብቱ ስር አስገብቶ ይጨምቀኛል፡፡ ያለፈውን አመትም እንደዚያ ያደርግ ነበር ግን አያሳምመኝም ነበር፡፡ በዚህ አመት እንዳለፈው አመቱ ብብቱ ስር ከቶ ያሳምመኛል፡፡ እያመመኝ እንኳን እኔ የጨዋታ ነው ብዬ ስስቅ እሱ ግጥም፡፡ ሳቅ የለም፡፡ ኮስተር፡፡ እኔም በሀሳቤ “በል በቃ መልዕክትህ ደርሶኛል” ብዬ ከኢዩኤል ጋር ተቆራረጥኩ፡፡
አሚር ትንሽ ትንሽ ከነሱ ጋር ይቀራረብ ነበር፡፡ እረፍት ላይ እነሱ ሌላ ክፍል የሚማረው ጓደኛቸው ጋር ሲሄዱ እኔ ምን ይዋጠኝ፡፡ ያለፈው አመት አልፈልግም አልወጣም ክፍል ውስጥ እቀመጣሁ ስል የነበርኩ ሰውዬ የምገባበት አጣሁ፡፡ ሁሉም ገሸሽ ገሸሽ አረገኝ፡፡ የምሰምጥበት አጣሁ፡፡ ከስንት ዘመን በኋላ የድሮ ጓደኞቼ(የስምንተኛ ክፍል) ትዝ አሉኝ፡፡ እነሱ ጋር መዋል ጀመርኩ፡፡ እነሱ ጋር ብሄድም ግን እነኢዩኤል ጋር መሄድ ነበር የምፈልገው፡፡ ጊዜ ለማሳለፍ፣ ብቻዬን እንዳልሆን ነበር የድሮ ጓደኞቼ ጋር የምሄደው፡፡
እንዲያ ሲያከብሩኝ የነበሩ ልጆች፣ ከኢዩኤል ጋር ስለተለያየሁ(ትላለህ) ሲቀያየሩብኝ፣ ክፍላችን ውስጥ ኢዩኤል ምን አይነት ስፍራ እንዳለው፣ እያንዳንዳችን ያለንን ዋጋና ሀይል መመዘንና መስፈር፣ መመርመር ጀመርኩኝ፡፡ ለምንድነው ሁሉም፣ በተለይ እኔ ኢዩኤል ጋር መቀመጥ በጣም የምፈልገው? ልጆች እሱን ስለሚያካብዱት እሱን የተጃለሰ ሰውም እንደዚያው አብሮት ይካበዳል፡፡ ከአሚር ጋር እንደምቀመጠው አይደለም፡፡ ኢዩኤል ጋር ስሆን የወሬ ጎርፍ ነው ምላሴን የሚያጥለቀልቀው፡፡ እኔ በጸባዬ፣ ደስ ሲለኝ ወሬኛ፣ ሲደብረኝ ዝምተኛ ነኝ፡፡ የዚህ አመቱን ግን አንደበቴ ተቆለፈ ማለት ጥሩ የሚገልጸው ይመስለኛል፡፡

ከቤት፣ ማትሪክ ተፈታኝ ስለነበርኩ ዲሻችን ዲኮደሯ ተነሳችና ተቆለፈባት፡፡ ከሰአት በመተኛት ጊዜ ለማሳለፍ ጣርኩኝ፡፡ አልቻልኩም፡፡ 9ኛ ክፍል ላይ በእንቅልፍና በፊልም የማሳልፈው ጊዜ አሁን 7 ሰአት ከት/ቤት ገብቼ ለመተኛት አልጋዬ ላይ የወጣሁ ስለ ት/ቤትና ስለቸርች ሳስብ 10 ሰአት ተኩል አልፎ እህቴ ሚጣ ከት/ቤት ገብታ በር ታንኳኳለች፡፡ ብዙ ጊዜ አለቅሳለሁ፡፡ ስሜቱ እንዲለቀኝ እጸልያለሁ፡፡ ት/ቤት መሄድ አስጠላኝ፡፡ ረጃጅም ጠዋቶች፣ አጫጭር ከሰአቶች፡፡
ከት/ቤት ገብቼ፣ አልጋዬ ላይ ዘፍ እንዳልኩ ምሳዬን አለመብላቴን እንኳን ሳላስታውስ ስለ ት/ቤትና ስለ ቸርች እያብሰለሰልኩ የምውልባቸውና 10 ሰአት ተኩል ላይ እህቴ በር ስታንኳኳ የምነቃበት ቀናት ነበሩ፡፡ ሜዲቴሽን እንደሚሉት ነገር ሳይሆን አይቀርም፡፡ ያለሁበትን ረስቼ ለሰአታት በጥልቅ ሀሳብ ውስጥ እሰምጣለሁ፡፡ በጣም ከመጠን በላይ አስባለሁ፡፡ ሌሊት 9 ሰአት ላይ ለጥናት አባቴ ቀስቅሶኝ ተነስቼ፣ ስለ ቸርችና ስለ ትምህርት ቤት በጣም በጣም በጥቀት ተመስጬ ልቤን እያመመኝ ሳስብ፣ 12 ሰአት ሆኖ ወፎች ሲጮሁ ነው የምነቃውና ከእንቅልፉ እንደሚነቃ ሰው ከመቼው ነጋ የምለው፡፡
ት/ቤትና ቸርች፣ ልቤን እንደ ሜዳ ቴኒስ ኳስ በሀይል እያነጠሩ፣ እየተቀባበሉ አሰቃይዋት፡፡ ከቤት መውጣት መርዶ የሆነብኝ ጊዜ፡፡
ጓደኛ አልነበረኝም፡፡ ከአቡሽ ጋር እንዲሁ እነኢዩኤል እንዲህ ሆኑ፣ እነዲያ እለዋለሁ እንጂ ጭንቀት ሊገለኝ ነው ምናምን አልለውም፡፡ እንኳን መንገር እንዲሁ ፊቴ ጠቁሮ ሙት ስመስል እንደ ሌሎቹ ለምን እንዳልሸሸኝ ወይም እንዳልተለወጠብኝ ይገርመኝ ነበር፡፡ እዲህ አይነት ነገር ለሰው አይነገርም፡፡ አገሌ ናቀኝ፣ እገሊት ሰደበችኝና ተናደድኩ፣ ሳይሆን እገሌን እንዲህ እንዲህ ስለው በሸቀ ተብሎ ነው የሚነገረው፡፡ የራስን ክብር ወይም ሰዎች ላንተ ያላቸውን ሬፒዩቴሽን የሚቀንስ ነገር ለሰው አይነገርም፡፡ የነገርኩት፣ ከነኢዩኤል ጋር እንደ ድሮ እንደማንቀራረብ ብቻ ነው፡፡ ግን ወሬዬ ሁሉ ስለነሱ ሆኖ ነበር፡፡ የሰው ፍቅር ነባራዊው የሚባለው ነገር በዚህ አመት፣ 10ኛ ክፍል ላይ ነበር የገባኝ፡፡ የምተነፍስበት፣ የማረገው ሲጠፋኝ እንደገና ለሶስተኛ ጊዜ ማስታወሻ(Diary) መጻፍ ጀመርኩኝ፡፡

ትምህርት የጀመረ ሰሞን እኔስ ለምን ይቀርብኛል ብዬ ኢሉ ግሪን ላይብረሪ ሄድኩኝ፡፡ ላይብረሪውም ምግብ ቤቱም የቸርቻችን ነው፡፡ ምን አንቀዠቀዠኝ እስኪ? የሁሉም ክፍል የሀይስኩል ተማሪ እዚያ ነበረ፡፡ ግን ለምንድነው ሰው ወደሚፈስበት ዝም ብዬ የማልፈሰው? ለምንድነው ምጨናነቀው፡፡ ልብ አርግ፣ ላይብረሪ መሄድ፣ ከነኢዩኤል ጋር ተመቻችቼ በነበረ ጊዜ፣ ደስተኛ በነበርኩ ጊዜ መሄድ አላማረኝም፡፡ ምክንያቱም ያኔ ስለ ጓደኛ ያለኝን ግንኙነት ስለማሻሻል ስራዬ ብዬ አላስብም ነበር፡፡ ላይብረሪው ውስጥ ስገባ መቀመጥ ድብርብር አለኝ፡፡ ጭንቅ፣ ጥብብ፡፡ ሁሉም ሰው ምን ሆኖ ነው ሚጨነቀው እያለ እኔ ላይ የሚያፈጥ መሰለኝ፡፡ ትንሽ ቆይቼ ከላይብረሪው ስወጣ፣ ላልመለስ ነበረ፡፡

ኳየር ስጀምር፣ የኳየር መዝሙር መጻፍ አንዱ እቅዴ ነበር፡፡ ያው መዝሙር በግጥም ነው አይደል የሚፃፈው? ጽፌ አላውቅም ግን የሆነ ሰሞን ጭንቅላቴን መዝሙር ውለድ እያልኩት ነበር፡፡ ኳየር፣ አንድ ልጅ መዝሙር ብሎ የሆነ በጣም የሚደብር ነገር አደረሰና፣ እንዴ እኔ እሱ ካቀረበው ስንት እጥፍ የሚሻል አላመጣም? ብዬ መዝሙር ለመጻፍ በጣም ጥረት ማድረግ ጀመርኩ፡፡ አንድም “መዝሙር መጻፍ ይችላል”

ብለው ከቀረቡኝ ብዬ ነው፡፡ በርግጥ እኔ በሁሉም ነገር ከሌሎቹ እሻላለሁ ብዬ አስብ ነበር፡፡ ቢቀርቡኝ ከማናቸውም በላይ ተጫወች፣ ቀልድ አዋቂ፣ ወሬ የሚያውቅ፣ ኳየሩን በስርአት ሊይዝ የሚችል ሰው ነበርኩ፡፡ ግን ትክክለኛውን ማንነቴን ማሳየት ተሳነኝ፡፡ የኳየሬ ልጆች የሚያውቁት፣ ፈሪውን፣ ዝምተኛውን፣ ብሶተኛውን፣ ጭንቀታሙን ናትናኤልን ነው፡፡ አንድ ቀን አንዷ የኳየራችን ልጅ ለሆነ ነገር ቤታችን መጥታ ሚጣን "ናቲ ቤትም ዝምተኛ ነው እንዴ" ብላ ጠይቃታለች፡፡ አልፎ አልፎ "ለምንድነው ከልጆች ጋር የማትቀራረበው?" የሚሉኝም ነበሩ፡፡ እንደነፈይሳ አይነት በድከመቱ በኩል ገብተው ጥቁር መጋረጃ የሆኑ ሰዎች እያሉ፣ እንዴት ልቀራረብ?

ብዙ ጊዜ ራሴን ካስቸገርኩ በኋላ እንዲህ የሚል መዝሙር ጠብ አለልኝ፡

ያየናል ሰይጣን አድፍጦ
ይከታተለናል ዲያብሎስ አድብቶ
በተለይ እኛን ክርስትያኖቹን
አይተወንም ይፈልገናል፡፡

ይሄው ነበር የመጣልኝ፡፡ ይሄም በስንት ጥረት ነው፡፡ መዝሙሩን ኳየር ለማድረስ አልደፈርኩም፡፡ ድፍረቱን ቢኖረኝ፣ ግጥሙን 4 ስንኝ ላይ ባላቆምኩት ነበር፡፡

ዳያሪዬን የአስረኛ ክፍል ተማሪ እያለሁ ጥቅምት 19 ቀን፣ 2007 ዓመተ ምህረት፣ ዕለተ ረቡዕ ከቀኑ ወደ 11፡00 ሰአት ነበር የጀመርኩት፡፡ ዳያሪዬ እንዲህ በማለት ይጀምራል፡

ውድ ማስታወሻዬ(Dear diary) ከዘቫምፓየር ዳየሪስ(በቫምፓየሩ ማስታወሻ ቀድሞ የታየ፣ Dear diary፣ ውድ ማስታወሻዬ፣ are you a vampire? ቫምፓየር ነህ? Yes! አዎ፣ I love Damon፣ ዴመንን እወደዋለሁ...ዴቦራ ሪከርድስ፣ ትርጉም በስቪ...) ላይ ነው ያየሁት፡፡ ወይ ኤሌና ጊልበርት፡፡ እስቴፋንና ዴመን ሳልቫቶር፣ ጀረሚ ጊልበርት፣ ካሮላይን፣ ቦኒ፣ ቴይለር፣ ከላውስ፣ ማት፣...ትከታተለው ከነበረ፣ ቪኪ ትዝ ትልሃለች? ስድስተኛ ክፍል ሳሚን መሸንት ትቼ የጀመርኩትን እስከ 9ኛ ክፍል ነበር የቀጠልኩት፡፡ እስከ ክፍል 50 ምናምን፡፡ እስከ ሲዝን 5 መሰለኝ፡፡

እሮብ፣ ጥቅምት 19፣ 2007 ዓ.ም. ከሰአት ወደ 11፡00 ሰአት

ውድ ማስታወሻዬ

እያንዳንዱ ሰው መጽሐፍ ነው ይባላል...እኔ ከሌሎች እኩዮቼ ለየት የሚያደርጉኝ ጥቂት የማይባሉ ባህርያት እንዳሉኝ አምናለሁ፡፡ ሁሉም ሰው የሚለያይ ቢሆንም ቅሉ፣ የእኔ ግን ወዲህ ነው፡፡ ጓደኛ የለኝም፡፡ እዚህ አለም ላይ ጓደኛ የሌለው ማን አለ? እንስሳት እንኳንኮ ጓደኞች አሏቸው፡፡ ታዲያ ይሄ "ልዩ!" አያስብልም? ልዩ ሰው ብቻ ሳልሆን ልዩ ፍጡር ነኝ፡፡ ብቸኛ!

ደግሞ ሰው፣ በተለይ በኔ እድሜ የሚገኝ ወጣት ቤት ውስጥ ከመቀመጥ፣ መንደር ለመንደር መዞር፣ ከተማ ወስጥ መንጦልጦል ደስ ያሰኘዋል፡፡ ለኔ ግን ከቤት የወጣሁባት ቅፅበት ታሳምመኛለች፡፡ የቀን ውሎዬን ከቤት ውጪ ባሰለፍኩት ጊዜ ብዛት ነው የምለካው፡፡ ብዙ ሰአት ውጪ የቆየው ቀን ይደብረኛል፤ ብዙ ሰአት ቤት የምውል ቀን ደስ ይለኛል፡፡ አልፎ አልፎ ወጥቼ የምደሰትባቸው ጊዜያት ቢኖሩም ማለት ነው፡፡ እኔ ከቤት መውጣትና የምጠላውና ብቸኝነትን መውደዴ የቤተሰብ ውርስ ነው እንዳልል አባትና እናቴ እንዲህ አይነት ጸባይ የላቸውም፡፡ ወንድምና እህቴ፡ ወንድሜ፣ በጣም ዟሪ፣ ቤት ውስጥ መቀመጥ የማይሆንለት፣ ሲሆን እህቴ ሚጣም እንዲህ አይነቱን እድል ብታገኝ የምትቀመስ አይደለችም፡፡ እኔ ግን...

እውነቴን ነው፡፡ ልጆች እኔ "ቤት ውስጥ መቀመጥ ነፍሴ ነው" ስላቸው፣ "እረኔ ይጨንቀኛል፣ እንዴት ነው አንተ ደስ የሚልህ?" ይሉኛል፡፡ እኔ ደግሞኮ ከቤት መውጣት ነው የሚያጨናንቀኝ፡፡ የሰው አይን እፈራለሁ፡፡ በተለይ የማውቀውን ሰው፡፡ ሰው ሰላም ማለት፣ ሰላም ይሉኛል፣ ሰላም ልበላቸው? ማለት ብቻውንኮ አንድ ስራ ነው፡፡ ወንድሜ ዙሪት ብቻ ሳይሆን ብዙ ጓደኞች አሉት፡፡ መቱ ውስጥ ያሉ እኩዮቹ ሁሉ ጓደኞቹ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ እሱ ዩኒቨርሲቲ ሲሄድ ሰው ዝር የማይልበት ቤታችን፣ እሱ ለእረፍት ሲመጣ እሱን በሚጠሩት ልጆች ድምጽ ይናጋል፡፡ እሱን ፈልገው የሚዘንቡ ልጆች ለኔም ያካፋሉ፡፡ እሱ ጋር ለመጫወት መጥተው እኔም የወሬው ተቋዳሽ እሆናለሁ፡፡ ከቤት እኔ ተጨነቅኩ ገለመሌ ስላቸው፣ እስኪ ወንድምህን እየው፣ እንደሱ ሁን ይሉኛል፡፡ ከቤት ብቻ ሳይሆን የሚያውቁኝ ልጆችም "እስኪ አንተ እንደሱ ሁን፣ ግን አንተና ወንድምህ የምር ወንድማማቾች ናችሁ?" የሚሉኝ አሉ፡፡ አንዳኦ አንዴ ከወንድሜ ጋር፣ አይቶን "መንትያ ናችሁ?" ብሎ ጠይቆናል፡፡ እኔ ግን ልዩነታችን እንዳለ ሆኖ

በመልክ ብቻ ሳይሆን ከመሰረቱ፣ ጸባያችንም በጣም እንደሚመሳሰል አምናለሁ፡፡ ኢጋጣሚዎች፣ የህይወት ውጣ ውረዶች ወንድሜና እኔን ቀልድ ይሁን እንጂ ወንድማማችነታችንን ጥያቄ ውስጥ እስኪያስገቡ ድረስ ባህርያቶቻችንን እንደለያዩ አምናለሁ፡፡

ሀሙስ ጥቅምት 20፣ 2007 ዓ.ም. 8፡30

ውድ ማስታወሻዬ

ያለፈው አመት ሳላስበው ነበር ያለቀው፡፡ ሳልሰለቸው እየወደድኩት ነበር የተገባደደው፡፡ ይህኛው አመት ደግሞ በጣም ያስጠላል፡፡ የዛሬው ቀንም የዚህ አመት አንድ ቀን ነው፡፡ ዛሬም በጣም ድብር፣ ክፍት ብሎኝ ነው ያሳለፍኩት፡፡ ለኔ ቀን አሪፍነትና ደባሪነት ሁሌም የትምህርት ቤት ውሎዬ ነው የሚወስነው፡፡ ለምሳሌ ዛሬ በራያ አብረውኝ ከተመደቡ ልጆች ጋር ተቀምጬ ሲደብረኝ ነው የዋልኩት፡፡ እኔ አብሬአቸው ልቀመጥ የምፈልጋቸው ልጆች ራቁኝ፡፡ ያለፈው አመት ከት/ቤት ስንለቀቅ አንዳልከፋኝ ዛሬ ክፍል ውስጥ መቀመጥ አስጠላኝ፡፡

ከማህበራዊ ህይወት ስትገለል፣ ቤንች ላይ እንደሚቀመጥ ተቀያሪ እግር ኳስ ተጫዋች ተመልካች ትሆናለህ፡፡ የሚጫወቱት ትኩረታቸው ኳሷ ላይ ብቻ ነው፡፡ ስለ ጨዋታው ብቻ ነው የሚያስቡት፡፡ ተመልካቹ ግን ስለ ብዙ ነገር ያስባል፡፡ እንዴት ዋና ተሰላፊ መሆን እንደሚችል ያሰላስላል፣ የጨዋታውን ኮከብ ተጫዋቾች ምን ኮከብ እንዳደረገው ያሰላስላል፡፡ ምክንያቱም እሱ ተቀምጦ ነው ያለው፡፡ ወደሱ የሚጠረዝ ኳስ የለም፣ ሩጫ አላደከመውም፡፡ ቢዚ የሚያደርገው ነገር የለም፡፡ እኔም ከጨዋታው ውጪ ብሆንም ግን ከሌሎቹ ከሚጫወቱት የበለጠ ስለጨዋታው አስባለሁ፡፡ ስለኮምፒዩተር እያሰበ የሚውለውኮ ያለው ሳይሆን የሌለው ነው፡፡ ያለውማ ስለሱ እያሰበ መዋል አያስፈልገውም፣ ብድግ አድርጎ በፈለገበት ሰአት መጠቀም እንጂ፡፡ የሌለው ግን ቢኖረው ስለሚያደርግበት ነገር፣ ስለሚሰማው ደስታ፣ ስላላቸው ልጆች ጉረኝነት ስለብዙ ነገር፣ ስለኮምፒዩተር ብቻ እያሰበ የሚውልበት ቀን ሊኖር ይችላል፡፡ ታዲያ እኔ ስገለል ኢዩኤልንና ፈይሳን ምናምን አነጻጽር ነበር፡፡ ምንድነው እነኚህን ልጆች ሌሎች እንዲፈሯቸው ያደረገው? ለምንድነው እኔስ ኢዩኤል ጋር ካልተቀመጥኩ ከሱ ጋር ካልተጎዳኘሁ ሞት የሚሸተኝ? ወደ ኋላ ወደ 9ኛ ክፍል ተመልሼ መመርመር ጀመርኩ፡፡ ልመርምር ብዬ ወይ ደግሞ አስቤበት አይደለም፡፡ ይነሳና በቃ ጥያቄ ይሆንብኛል፡፡ ልተኛ ብዬ ጋደም ስል፣ ሀሳብ ይዞኝ ይሄዳል፡፡ ራሴው ጠያቂ፣ እራሴው መላሽ እሆናለሁ፡፡ ብዙ ጥያቄ ለሚሆኑብኝ ነገሮች መልስ አገኛለሁ፡፡ አንዳንዴ ግን ቆይ ግን ለምንድነው ብዬ ሳስብ እውልና፣ ምንም እንቢ ሲለኝ ቆይቶ ቆይቶ፣ ከአመት በኋላም ሊ-ኖን ይችላል፣ መልሱ ሽው ይልብኛል፡፡ እንደ ተወርዋሪ ኮከብ፡፡ እኔ እያሰብኩት በሌለሁበት ሰአት ሽው ይልብኝና ስስስ አሀ... ያስብለኛል፡፡ ጥያቄዬን እኔ ብረሳውም አዕምሮዬ ሴቭ አርጎታል ማለት ነው፡፡ የሆነ ጊዜ ግራ የገባኝን ነገር ከአመት ምናምን በኋላ መልሱን የማገኝበት ጊዜ አለ፡፡

ኢዩኤል የኛ ክፍል ንጉስ እንደሆነ አመንኩኝ፡፡ ልጆች እሱ ጋር ለመቀመጥ፣ የሚያደርጉት ነገር፣ ሁሉ ነገር ብቻ ያንን ነበር የሚያመላክተው፡፡ እኔ ግን እንደ ሌሎቹ እሱን በግልጽ አካብጄው አላውቅም፡፡ ብቻ የሱ ጓደኛ መሆን እፈልግ ነበር፡፡

በረከት አለሙን እያየ ነበር፡፡ ያለፈው አመቱን እኔን ነበር የተካው፡፡ ግን ለምንድነው እንዲህ ኢዩኤልን የምናካብደው? ሜቲ ከነሱ ጋር መቀመጥ እንደጀመረች በሁለተኛው ቀን ኮንፊደንሷ ኮንፊደንስ አልነበረም፡፡ የዴስክ ጠረጴዛ ላይ ምናምን መቀመጥ ጀመረች፡፡ እኔ ምክንያቱ ገብቶኝ አሚርን እያት ሜቲን “ኮንፊደንሷ ጨመረ፣ ደስ ብሏታል” አልኩት፡፡ “ለምን አልክ?” አለኝ፡፡ “ሳይኮሎጂ ነው” አልኩት፡፡ በነጋታው መጣና አንተ እውነትህን ነው በጣም ነው ኮንፊደነሷ የጨመረው አለኝ፡፡ ሌላ ቀን ደግሞ እኔ ከነኢዩኤል ጋር ከተቆራረጥኩ በኋላ፣ አሚርን፣ ኢዩኤል ሀላፊያችሁ ነው አይደል ትፈሩታላችሁ አልኩት፡፡ ኧረኔ አልፈራውም፣ በቃ ጓደኛዬ ነው አለቀ፡፡ ግን ለምን አልክ? አለኝ፡፡ አሚር ይሄን አያውቅም ማለት ነው? ይሔን እንኳን አለማወቁ ነው የገረመኝ፡፡ እኔ ሁሉም የሚያውቅ፣ ግን አውጥቶ የማያወራው ነበር የሚመስለኝ፡፡ እኔ በበኩሌ ከ9ኛ ክፍል ጀምሮ ኢዩኤል ክፍሉን እንደ ተቆጣጠረው አውቀዋለሁ፡፡ ብዙ ልጆችም የሚያውቁ ይመስለኛል፡፡ “ስትሄዱ መሀል አስገብታችሁት ነው...” ምናምን አልኩት፡፡ በነጋታው መጣና “እውነትህን ነው አንተ፣ ግን እንዴት አሰብከው? እኔ አስቤው አላውቅም” አለኝ፡፡ ይሄ እንኳን የአሚር ማሰብ አለመቻል እንጂ ወይም የእግር ኳሱ ተጫዋቾች መሆን እንጂ ተመልካቹ የሚያውቀው ነገር ነው፡፡ ቆይ ለምንድነው ሁሌ መሃል አስገብተውት የሚሄዱት ይሄን ልጅ ብለው ብዙ ጊዜ የድሮ ጓደኞቹ ጠይቀውኛል፡፡

ማክሰኞ ጥቅምት 25 ከቀኑ 8 ተኩል ቤት፡፡

ውድ ማስታወሻዬ

ዛሬ ራሴን ለማጥፋት ካሰብኩባቸው ቀናት አንዱ ነው፡፡ ለካስ ብቸኝነት ሞትን ያስመኛል፡፡ ትናንት ቸርች ኳየር ሄድኩኝ፡፡ እኔ ደግሞ የአገልግሎት ትምህርቴን ጨርሼ ኳየር ከጀመርኩ ገና ሁለት ወሬ ነው፡፡ ወደ ነሀሴ መጨረሻ መሆኑ ነው፡፡ ታዲያ የኳየር ልጆች ምንም አልተመቹኝም፡፡ ልግባባቸው አልቻልኩም፡፡ ሰውን እንዴት መቅረብ እንዳለብኝ አላውቅም ማለት ነው በቃ፡፡ ያስጨንቀኛል እዚያ ስሄድ፡፡ኳየር ማለት ደግሞ መዘመር፣ እግዚአብሔርን ማምለክ ነው፡፡ እኔ ግን አንገሽግሾኛል፡፡ እንዲያውም አሁን አሁን ለማቆም እያሰብኩ ነው፡፡ ነገ ልምምድ አለን፡፡ በፍጹም መሄድ እየፈለግኩ አይደለም፡፡ ለመሄድ እንደማልፈልግና ከነጭራሹም መተው እንደምፈልግ ለእናቴ

ለመንገር እያሰብኩ ነው፡፡ በርግጥ አትፈቅድልኝም፡፡ ትቃወመኛለች፡፡ ሆኖም ይሄን ያህል እንዳስጠላኝ ማወቅ ከቻለች ራሱ በቂ ነው፡፡ ደግሞ የኳየር ልጆች ገገማ ነገሮች ናቸው፡፡ ድሮም ኳየር ሳልገባ በፊት አልወዳቸውም፡፡ አስጠሊታ ኳየር!

ትናንት በኳየር ምክንያት ስቃጠል አድሬ፣ ዛሬ ደግሞ አንደ ከሰሞኑ አሚር ሙድ ያዘብኝ፡፡ የሆነ አለ አይደል በቃ ያለሱ መንቀሳቀስ የማልችል አይነት አስመሰለኝ፡፡ እኔ ደግሞ ይሄ ይቅርና ትንሽ ነገር ታናድደኛለች፡፡ ለኖት ክፍል ስንቀይር ሄጄ ብቻዬን ተቀመጥኩ፡፡ በርግጥ እሱን ከቁብ እንደማልቆጥረው ለማሳየት ፈልጌ ነበር፡፡ ግን ለብቻህ ሆነህ ሌሎቹ ወሬ ሲሰለቅጡ ማየትና ለብቻ መኮራመት ያሳምማል፡፡ ደግሞ ያለፈው አመት ልጆች ያከብሩኝ ነበር፡፡ ልጆች ይፈሩኝ ነበር፡፡ አሁን ግን አዳሜ ብቸኝነቴንና መደበሬን አይታ እየተዳፈረች ነው፡፡ የቸርቹስ ይሁን፡፡ ግን ት/ቤት ያለው ሁኔታዬ "በተከበርኩበት ክፍል...!" የሚያስብል ነው፡፡ ምስኪን ናትናኤል፡፡ በማንም ጭቃክ ነው የተናቅኩት፡፡ ለዚህ ሁሉ ሀላፊነቱን የምወስደው ግን እኔው ራሴው ነኝ፡፡ ምን ማድረግ እንዳለብኝ እያወቅኩኝ መተግበር አቃተኝ፡፡ አላሳዝንም?

ሰው እንዴት መቅረብ እንዳለብኝ አላውቅም ማለት ነው ስል እያመንኩ ነው፡፡ ሰው መቅረብ አታውቅበትም ያሉኝ ትክክል ነው ማለት ነው እያልኩ ነው፡፡ ከቤት ነው እንዲህ የሚሉኝ፡፡ እኔ ከማወራላቸው ነገሮች ተነስተው ነው እንግዲህ እንዲህ የሚሉኝ፡፡ ሰው እንዴት መቅረብ እንዳለብህ አታውቅም፣ ከወንድምህ ተማር፣ ወደ ፊት ዩኒቨርሲቲ ስትሄድ ደግሞ እንዴት ልትሆን ነው? ፍጹም ሰው የለም፡፡ መቻል ነው፣ መቻቻል ነው ሲሉኝ እኔ ፍጹም ሰው አይደለም የፈለግኩት፣ የሚመቸኝ ሰው ነው እንጂ የፈለግኩት አላቸዋለሁ፡፡ አሁን ግን እነሱ ያሉትን አምኜ መቀበሌን ነው የሚያሳየው፡፡ አዎ አሚርም መደበሬን የብቸኝነት ስሜቴን አይቶ እየተበተብኝ ነበር፡፡ ያን አውቄ ብቻዬን የተተቀመጥኩ ቀን እስከዛሬ ያልረሳሁትን ስህተት ነበር የሰራሁት፡፡ የዚያን ቀኑንማ ማስታወስ ራሱ አልፈልግም፡፡ አስተማሪው ራሱ ብቸኝነቴን ልብ ብሏል፡፡

ምን ማድረግ እንዳለብኝ እያወቅኩኝ ስል፣ ጓደኛ ለመፍጠር፣ ከልጆች ጋር ለመቀራረብ ምን ማድረግ እንዳለብኝ አውቃለሁ፣ ልጆች እንዲያከብሩኝ ለማድረግ ምን ማድረግ እንዳለብኝ ከማንም በላይ አውቃለሁ፣ ግን መተግበር አቃተኝ ነው፡፡ የምታውቀውን ነገር ማድረግ ሲያቅትህ በጣም በጥልቀት ለማሰብ ትጋለጣለህ፡፡ ግን ለምን የማውቀውን፣ የምፈልገውን ነገር ማድረግ አቃተኝ? አንዳንዴ ማወቅ ይጎዳል ሊሆን ይችላል፡፡ ሺ እግር ትል የእግሮቹ ብዛት ሲነገረው ተጠላልፎ መሄድ እንዳቃተው፡ እኔም ማህበረሰቡ ውስጥ ተቀባይነት እንዲኖረኝ ምን ማድረግ እንዳለብኝ እየገባኝ በመጣ ቁጥር ከማህበረሰቡ መቀላቀል፣ አብሮ መሄድ ጭራሹን እየከበደኝ መጣ፡፡ ታዲያ ሌላ ምን ይባላል ብዙ እያወቅኩ በሄድኩ ቁጥር ከማህበረሰቡ እየተገለልኩ እየተገለልኩ ስሄድ፡፡ እውቀቴ እንዲያውም መመጻደቂያ ሊሆነኝ ሲገባ፣ ሰውን እንድፈራ፣ የበታችነት ስሜት እንዲያጠቃኝ ምክንያት ሆነ፡፡ ታዲያ ምክንያቱ ሌላ ምን ሊሆን ይችላል? ሌላው የማውቀው ሰው እንዲህ አይነት ስሜት ጎብኝቶት የማያውቅ፣ በከተማው እንዲህ የምሰቃየው እኔ ብቻ ከሆንኩኝ፣ ለምን ብዬ እጠይቃለሁ፡፡ አዎ ከትምህርት ቤት እኔ ብቻ ነበርኩ ክፍል ውስጥ መጽሐፍ ሳነብ የነበርኩት፡፡ እኔ ብቻ ነበርኩ አንባቢ ተብዬ ዝናዬ የናኘው፡፡

ቤታቸው ከኛ ሶስት ቤት ተሻግሮ የሆነች ጎረቤታችን ስትሞት ከሳምንት በኋላ ነበር ለቅሶውን የሄድኩት፡፡ ሰፈር፣ አሁንም በቅርባችን አንድ ሌላ ጎረቤታችን ስትሞት ከነጭራሹን ለቅሶ ልሄድኩም፡፡ ፈራሁ፡፡ ልጇኮ ለኔ እንደ ጓደኛ ነበር፡፡ ከኛ ሁለት ቤት እልፍ ብሎ ያሉት፣ የወንድሜ ጓደኛ፣ አባት የሞተ ጊዜም ለቅሶውን አልሄድኩም፡፡ የልጁ ወንድም መንገድ ላይ አይቶኝ፣ "ምንድነው፣ ጠፋህ፣ ቤት አትመጣም እንዴ? ብቅ በል እንጂ" ብሎኛል አንዴ፡፡ እኔ ግን አልሄድኩም፡፡ ማንም እንደኔ አልነበረም፡፡ እኔ ግን ለምን እንዲህ ሆንኩ? ለምንድነው ሰው ቀለል አድርጎ የሚያየው፣ ከነጭራሹም የማያስበው ነገር እኔን የሚያስፈራኝና የሚያስጨንቀኝ? ሳስበውኮ ለኔ ራሱ ቀላል ነው፡፡ ትሄዳለህ፡፡ ልጆች ካሉ ከልጆች ጋር ትጫወታለህ፡፡ ልጆች ደግሞ ይኖራሉ፡፡ ባይኖሩም ትንሽ ትቀመጥና ትወጣለህ፡፡ ዋናው ሀዘንኛው አይቶህል ወይ? ነው፡፡ እኔ ግን በቃ ሰው የሚሰበሰብበት ቦታ ያስፈራኛል፡፡ ያጨናንቀኛል ምናምን ነው የምለው፡፡ ፍራቻን ሽሽት መሆኑ ነው፡፡ ጭንቀትን ሽሽት ነው ማለት ነው፣ ለቅሶ ቤት፣ የጎረቤት ለቅሶ ቤት መሄድ የምፈራው፡፡

አርብ ጥቅምት 28፣ ከምሳ በፊት ቤት፡፡

ውድ ማስታወሻዬ

ምዕራብ አፍሪካን እያመሰ ያለውና እስካሁን እስከ 5000 ሰዎችን የፈጀው የኢቦላ ቫይረስ ግድል ቢያረገኝ ደስ ይለኛል፡፡ ዛሬውኑ፡፡ ህይወት መርራኛለች፡፡ እያንዳንዷ ት/ቤት ግቢ ውስጥ የምኖርባት ሰከንድ ቁስልን የመቆስቆስ ያህል ትጠዘጥዘኛለች፡፡ ጠዋት ተነስቼ ት/ቤት ልሄድ ስል ያስፈራኛል፡፡ ምክንያቱም ሌሎቹ እየተጫወቱ አብረው(ብዙ ሆነው) ሲሄዱ እኔ ግን የበይ ተመልካች እንደሚሉት   ብቻዬን እሄዳለሁ፡፡ በርግጥ ብቻቸውን ት/ቤት የሚሄዱ ሞልተዋል፡፡ እኔ ግን ከዋጋዬ በታች ሆኜ ነው፡፡ እንዲያውም ሙባረክ የሚባል ልጅ በቀደም "ምነው

ብቻህን?” ብሎ ጠየቀኝ፡፡ በፈገግታ ከማን ጋር ልምጣ ብለህ ነው? ብዬ ብሶቴን፣ ሀፍረቴን፣ገመናዬን ለመደበቅ ሞከሬያለሁ፡፡ ተሳክቶልኝ እንደሆን ግን አላውቅም፡፡ ፊቴ እንደሆን ስሜቴን መደበቅ አይችልም፡፡ ስሜቴን መደበቅ ከቶ አልቻልኩበትም፡፡ ሳዝን፣፣ ስናደድ፣ ሲከፋኝና ሲደብረኝ፣ ያላዘንኩ፣ ያልተከፋሁ መስሎ መታየት እኔ ጋር አይታሰብም፡፡ ደግሞ ሰው ካናደደኝ አሜን ብዬ መቀበል እንጂ አጸፋውን መመለስ አይሆንልኝም፡፡ ያ ነው አንዱ ችግሬ፡፡ በቃ ዝም ብዬ መናደድ እንጂ ሰውየውን መልሼ ማንገብገብ አይሆንልኝም፡፡ አሁን አሁንማ ጨጓራዬን ለመላጥ ያሰፈሰፉ ብዙ አካላት አሉ፡፡ እድሜ ለፊቴ! አንዳንዴ እንዲያውም አንዳንድ ጓደኛ ምላቸው እኔን ለማናደድ ብዙም ጥረት አያስፈልጋቸውም፡፡ በቃ አብረን እየሄድን ከሆነ ጥለውኝ መሄድ ነው፡፡ ያኔ እኔ ብቸኛ እሆናለሁ፣ ይከፋኛል፣ እነሱ ደግሞ ደስ ይላቸዋል፡፡ ሰው ግን ለምን ተከባብሮ መኖር እንደማይችል ይገርመኛል፡፡ ግን አይገርመኝም፡፡ አንዱ ራሱን ዝቅ ካረገ ለምን አይናቅም? እንዲያውም ባይናቅ ነው የሚገርመኝ፡፡ እንዲህ ነች እንግዲህ ህይወት፡ እንደዚያ(እንደ 9ኛ ክፍል) ትጣፍጣለች፣ እንደዚህ(አንደ 10ኛ ክፍል) ትመርራለች፣ ሞትንም ታስናፍቃለች፡፡ እንዲያውም ትገልላለች፡፡ ወይ ኑሮ!!!

በጣም የመናቅ ስሜቱ ከምሸከመው በላይ ሆኖ ነበር፡፡ ክፍል፣ ቸርች፣ መንገድ ላይ የተከሰከሰ ፊቴን ያዩ ሁሉ ንቀት፣ ንቀት፣ ንቀት፡፡ የሚያከብረኝ ሰው እንደጠማኝ ማን በነገራቸው? ችግሩ ይህቺ አለም እንደዚያ አትሰራም፡፡ ጭንቅ አንደሚያረገኝ የነገርኳቸው ሰዎች፣ ተረድቶ ለመርዳት እንደመሞከር፣ ስስ ብልትህን አገኙብህ ነው የሚሆኑት፡፡ ችግሩ ደግሞ የልብህን ለሰው መንገር ችግርህን የሚፈታልህ ይመስልሀል፡፡ ታዲያ ስትነግራቸው በነጋታው ይመጡና ንቀቱን በእጥፍ ይጨምሩታል፡፡ ለምን ነገርኩት? ትላለለህ፡፡ ለሰው ማውራት እንደማይረዳህ እያወቅክ መሸከም ሲያቅትክ ለሰዎች ትንፍሽ ትልላቸዋለህ፡፡ እኔ አሁን አንዳንዴ አልፎ አልፎ ጫፍ ጫፉን ለልጆች ስነግራቸው ዞረው መጥተው እኔ በነገርኳቸው ነገር እንደሚጎዱኝ እያወቅኩ ነው የምነግራቸው፡፡ የሆነ ነገር አፌን ይበላኛል፡፡ ከዚያ እነሱ ራሴው ባቃበልኳቸው መሳሪያ ሲተኩሱብኝ፣ወደ ውስጥ ማቃሰት፡፡ ጆሮ የሚሰጠኝ ካገኘሁ እንደዚህ እንደዚህ አልወድም፣ እንዲህ ሆንኩኝ፣ እገሌ እንዲህ አረገኝ እያልኩ ማማረር ነው፡፡ ነገ እየነገርኩት ያለሁት ሰው ያንን እገሌ እንዲህ በደለኝ እንዳልኩት ይበድለኛል፡፡ ሰው የራሱ ብቻ የሆነ ለማንም፣ ለጓደኛውም፣ ለማንም የማይነግረው የግል ጉዳይ ሊኖረው ይገባል፡፡ እኔ ለምን መንገር እንደሌለብኝ እያወቅኩ እንደምለፈልፍ ግራ ይገባኝ ነበረ፡፡ እኔን ራሴን፡፡

በዚህ ጊዜ እንደ ሄለን አቅሮ የተፋኝ ሰው አልነበረም፡፡ የሆነ ነገር ልጠይቃት ስሄድ እሷ ጋር እየሄድኩ እንደሆነ እያወቀች አውቃ በወሬ የተጠመደች ለመምሰል ትሞክራለች፡፡ በተደጋጋሚ፡፡ ጓደኛዋ እስክትገረም፡፡ ስጠራት አውቃ ዝም ትላለች፡፡ ጓደኛዋ ቅድስት ነበረች እየጠራሽ ነው የምትላትና እየሰማች እንደ አዲስ አቤት የምትለው፡፡አቤት አባባሏስ? እእእ... ስትል ግንባሯን እንዴት እነደምትቋጥረውኮ! ሰው ግን በግንባሩ ብቻ ክብሪት ለኩሶ፣ እሳት አቀጣጥሎ ሰውን እንዲይዝ አድርጎ ሰውን በእሳቱ ለብልቦ መግደል እንደሚችል ያውቀዋል?
እኔ ራሴን የምጠይቀው አንድ ጥያቄ አለ፡፡ እኔ እንደሆንኩት የሆነ ሰው ቢያጋጥመኝ፣ ኢዩኤል አሽቀንጥሮ እንደጣለኝ፣ ፈይሳ እንደ አዲስነቴ አልቀበል እንዳለኝ፣ ሄለን ናላዬን እንዳዞረችው አደርጋለሁ፣ እጨክናለሁ? ሁሌ ጥያቄዬ ምን አረግኳቸው? ነበር፡፡ ምን ስላረግኳቸው ነው እንደዚህ የሚጎዱኝ? ዳሩ ጥያቄው መሆን ያለበት፣ እየጎዱኝ እንደሆነ ራሱ ያውቁታል ወይ? ነው፡፡ ምን ያህል ህይወቴን እየበጠበጡ እንደሆነ ፍንጩን እንኳን አላቸው?

ልቤን ያመኛል፣ ፊቴን፣ አንገቴን ያቃጥለኛል፡፡ ትንፋሼ ማራቶን ሮጦ እንደተነሳ ሰው ሁሌ ትኩስ ነው፣ ይሞቃል፡፡ እንደደከመው ወይም እንደረካ ሰው በትክክል አየር ስቤ ሳልተነፍስ በጣም ቆየሁ፡፡ እንደ ደንበኛ ልቡ ላይ ጩቤ የተተከለለት ሰው፡፡ ልብ ላይ ጩቤ ተሰክቶ በአዕምሮም ሆነ በህይወት መኖር አይቻልምና ነው እንጂ ልቡ ላይ ጩቤ የተሰካ ሰው መኖር ቢችል ቀስ ብሎ ነው አየር መሳብ ያለበት፡፡ ምክንያቱም አየር አብዝቶ ሲስብ ደረቱን ከሚገባው በላይ ማንቀሳቀስ ስለሚኖርበት፣ ያ ደግሞ ልቡን ስለሚያሳምመው ቀስ ብሎ መተንፈስ ይኖርበታል፡፡ እኔም ልቤን እንደሚያመኝ ነገር በትክክል ሳልተነፍስ ቆይቻለሁ፡፡ ትንፋሽ ስቤ ሳልተነፍስ እንደቆየሁ ያስተዋልኩ ጊዜ ሳብ አድርጌ ለመተንፈስ ሞከርኩ፡፡ ትንፋሽ ሳብ አድርገህ ስትተነፍስ የሚሰማህ ደስ የሚል ስሜት አለ፡፡ ደስ ብሎህ ከሆነ የእርካታ፣ ደክሞህ ከሆነ ከድካምህ እፎይ ለማለት(ለእረፍት)፣ ፈርተህ ከሆነ ፍርሀትህ እንዲቀንስልህ(take a deep breath...)፣ ተጨንቀህ ከሆነም ጭንቀትህን ያስታግስልሀል፡፡ እኔ ግን አስቤበት ወደ ውስጥ ለመሳብ ስሞክር የሚሰማኝ ምንም ነገር አልነበረም፡፡ የበለጠ የሚያቃጥል አየር ብቻ፡፡ ከእሳቱ አስኳል በቀጥታ የሚወጣ አየር፡፡ የሚሰማኝ ነገር ቢኖር ትንፋሽ ወደ ውስጥ መሳብ ሲያቅተኝ ነው፡፡

ሰፈር አንድ ቀን አብርሽ(የድሮ ጎረቤታችን ልጅ) መንገድ ላይ እየተላለፍን እያለ “ብቸኝነት እንዴት ነው?” አለኝ፡፡ ፈገግ ብዬ አለፍኩት፡፡ይሄን ያህል አስነቅቻለሁ ማለት ነው?
አንድ እሁድ ጠዋት ደግሞ እንደ ልማዴ ብቻዬን ቸርች እየሄድኩኝ እንደ አብርሽ ድሮ የምንቀራረብ ልጅ ከኋላ ጠራኝና “ዛሬ ይለፍልህና እስኪ ከኔ ጋር ሂድ” አለኝ፡፡ ለአብርሽ ያሳየሁትን አይነት ፈገግታ ነበር ያሳየሁት፡፡ ቀልድ ይመስላል፡፡ ለኔ ግን ቀልድ አልነበረም፡፡ እነኚህ ሁለት ምሳሌዎች 10ኛ ክፍል ላይ ያመጣሁት ለውጥ ምን ያህል አካባቢዬ ላይ ባሉ ሰዎች እንደታወቀና አዕምሮአቸው ውስጥ እንደ ሰረጸ ማሳያ ናቸው፡፡
በዚህ ሁሉ መሀል ቦንቱ የምትባል ዘመዳችን ከቡራዩ መቱ ዩኒቨርሲቲ ደርሷት የእረፍት ቀናትን እኛ ጋር ነበር የምታሳልፈው፡፡ እሷ ደግሞ እኔ ጣረሞት ይዞኝ እሷ ሀገር ሰላም ብላ ታወራልኛለች፣ እናወራለን፣ ከሷ ጋር ሰላም ነበርን፡፡ ሰው ሳያወራ መኖር እንማይችል ተረዳሁ፡፡

ያ ሰው መቅረብ አልፈልግም ስለው የነበረው ምን ያህል ጅልነት እንደሆነ ገባኝ፡፡ ዛሬ ያንን ተረድቼ ላውራ ስል አንደበቴ በጭንቀት ታሰረ፡፡ ከቦንቱ ጋር ሳወራ ግን ለጥቂት ጊዜም ቢሆን ጭንቀቴንና ስቃዬን እረሳ ነበር፡፡

ቀጥሎ ማስታወሻዬ ላይ፡

ዛሬ አርብ ነው፡፡ የት/ቤት ክፍላችንን እናጸዳለን፡፡ የቤት ውልወላ ቀን አሁን እንዲህ የት/ት ክፍሌ አስጠልቶኝ ይቅርና 9ኛ ክፍል የነበርኩ ጊዜ ራሱ አልወደውም፡፡ ከቤት አጠባ በኋላ እንገናኝ፡፡

ያኔው 10፡00 ሰአት

ቤት አጠባ እየሄድኩኝ ዋናው መንገድ፣ ወደ ት/ቤታችን መታጠፊያ ላይ ሁለቱ የክፍሌ ልጆች ከባጃጅ ላይ ወረዱ፡፡ ኢዩኤልና በረከት፡፡
ኢዩኤል ማለት የክፍላችን ሀላፊ ነው፡፡ የተሾመ አለቃ ግን አይደለም፡፡ አለቃውማ እኔ ነኝ፡፡ ያው በአንድ ቡድን ውስጥ እየዋለ እያደር አንድ ገነን ብሎ የሚወጣ ሰው አይታጣም፡፡ ይህ የሰው ልጅ ብቻ ሳይሆን የእንስሳትም ማህበራዊ እውነታ ነው፡፡ እንዲያውም የመንግስት(የንግስና) መጀመሪያ ከእንዲህ አይነት የጥቃቅን ቡድኖች መሪነት የመነጨ ሳይሆን አይቀርም ብዬ እገምታለሁ፡፡
እኛ ክፍል ብዙ ልጆች ኢዩኤል ወደ ነፈሰበት ይነፍሳሉ፡፡ ልጁ በርግጥ ይገባዋል፡፡ የሚወደድ ልጅ ነው፡፡ ግን እኔ እንደ ሌሎቹ አልከተለውም፡፡ ያከብረኛል፣ አከብረዋለሁ፡፡ በተረፈ ከኢዩኤል ጋር ማውራት በጣም ደስ ይለኛል፡፡ አንደኛ ወሬ ይችላል፣ ሁለተኛ ደግሞ ሌላ ልጆች እሱን በጣም ስለሚያከብሩት እሱን የተጃለሰን ሰውም በዛው ከፍ ከፍ ያረጋሉ፡፡ ስለዚህ ወሬ ብቻ ሳይሆን ክብርም ኢዩኤል ጋር በመሆን ይገኛል ማለት ነው፡፡
እንደተለመደው እነበረከት ክብ ሰርተው ማውራት ጀመሩ፡፡ እንዲህ አይነት ክብ መሰንጠቅ ስለማይሆንልኝ፣ ቶለሳ የሚባል ልጅ ራቅ ብሎ ሳር ላይ ተኝቶ ነበርና እሱ ጋር ሄጄ ተኛሁ፡፡ ትንሽ ካወራን በኋላ ኤሌሜንተሪ አብሬአቸው የተማርኩት ልጆች መጡ፡፡ እነሱ ጋር ትንሽ መናቅ ተለማመድኩ፡፡ ጴጥሮስ የሚባል ልጅ መተበት ፈለገና ጦርነቱን የሱ ሜዳ ላይ አረገኩለት፡፡ ከዚያ እነሱ ሄዱ፡፡ ከሁሉም ዛሬ ያስደሰተኝ አብሬው ከኣየር የምገባውን ቢቂላን መንገድ ዳር ተቀምጦ አገኘሁት፡፡ ብዙ አናድዶኛል፡፡ እኔ ገብቼ የምጽፈውን ነገር እያሰላሰልኩ ተመስጬ ነበርና አላየሁትም፣ ካለፍኩት በኋላ ጠራኝ፡፡ “Abbee!” “አንተ!” አለኝ፡፡ ስሜን እንደማያውቅ፡፡ ዞር ስል እሱ ነው፡፡ “ኸ” አልኩት ፊቴን አጨማድጄ፡፡ ተናደደ፡፡ ቲቸር እገሌን ትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ አይተሀል? ብሎ ጠየቀኝ፡፡ኮስተር ብዬ “አዩ” አልኩትና ወደ ቤቴ፡፡ የሚያናድዱኝን ሰዎች ለማናደድ ጥረት ማድረግ ጀመርኩ፡፡

እንዴት ሰው የሚለውን ነገር ያጣል? ዝም ብሎ ይሰደባል? የሆነ ከውስጤ ማውጣት የምፈልገው፣ ሰውን ማብሸቅ የምፈልገው ነገር አለኝ ግን አይወጣም፡፡ ድሮ ት/ቤት ስብሰባ ላይ ለማውራት በጣም እየፈለግኩ ብዙ አስቤ ምንም አላወራ እንደ ነበረው፡፡ አሁን ደግሞ በቃ ምንም ማለት አልችልም፡፡ ቤት ገብቼ ሰው የሰደበኝን ነገር ሳስብ ብዙ ጊዜ አጠፋለሁ፡፡

ከዚያ ወዲህ ቀስ በቀስ ማንም እንደ ፈለገ የሚሰድበው ሰው መሆኔ እየቀረ መጣ፡፡ በርግጥ ልጆች ይፈሩኝ ጀመር፡፡ የምሳደባቸው ስድቦች በጣም የመጠቁና በፊት አስቤባቸው የሰደብኳቸው የሚያስመስሉኝ ነበሩ፡፡ ሰው የሚናገረውን ነገር ማጣጣል፣ አቃቂር ማውጣት ስራዬ ሆነ፡፡ በተለይ በረከትን ምናምን በፊት እሱ አልነበር የሚሰድበኝና የሚያናድደኝ፣ እኔ መሳደብ ስጀምር፣ ተሸነፈ፡፡ እኔ የሆነ ነገር ስል መማታት ሆነ አቅሙ፡፡ ሁሌ እንደበደበኝ፡፡ እኔና እሱ በሰላም ያወራንበት ቀን ቢኖር ያቺ በምልክት እነሱ ጋር ሄጄ እንድቀመጥ እኔን የጠራበትና እኔ እንደማልችል የነገርኩት ብቻ ነው ትዝ የሚለኝ፡፡

አንድ ቀን ከት/ቤት እኔ፣ አቡሽና አንድ ሌላ ልጅ አብረን እየገባን ነው፡፡ ያን ቀን በጣም ከፍቶኝ፣ ሲያወሩ አላወራ፣ ሲያናግሩኝ እንኳን አልመልስላቸውም፡፡ ምንድነው አንተን ነውኮ፣ አታወራም እንዴ? ይሉኛል፡፡ ግራ ይገባኛል፡፡ ታዲያ ያን ቀን በጣም ተደብሬ ዳውን ሆኜ፣ በጣም ያስነቃብኝ ነበርና ያ ልጅ፣ “አንተኮ እንዲሁ ዝም ብለህ ነው እንጂ ምታካብደው ማንም ነህ” ምናምን አለኝ ቀና ብሎ አይቶኝ የማያውቅ ልጅ፡፡ ንዴቴን መቆጣጠር አልቻልኩም፡፡ ግን ዝም አልኩት፡፡ እየሰማሁት የሌለው ለመምሰል ሞከርኩ፡፡ እንዲሁ ሲተርበኝ ሲተርበኝ ውሎ ሲያቆም፣ ትንሽ እንደሄድን ልጁን “አንተኮ ግን ከብት ነገር ነህ” አለኩት፡፡ ተናደደ፡፡ ትንሽ ቆይቼ “ለምን ከብት ነገር ነህ እንዳልኩህ ታውቃለህ?” አልኩት፡፡ “እእ?” አለኝ በሚጠይቅ አስተያየት፡፡ “ከብት ስለሆንክ ነው” አልኩት፡፡ ከዚያ እኔና አቡሽ እኔ ልጁ ሲናደድና እኔ ስስቅበት፣ አቡሽም ሳቁን መቆጣጠር አቅቶት ልጁን የበለጠ አበሳጨው፡፡ የምላሴ ጡንቻ እየፈረጠመ ነበር፡፡

አንድ ቀን አቡሽን እንዲህ አልኩት፡፡ ይሄ አመት ደባሪ እንደሚሆን አውቄው ነበር፡፡ አንተ አመት ደብሮህ ያውቃል? አልኩት፡፡ አመት? አለኝ ተገርሞ፡፡ “አይደብርህም እንዴ? ሙሉ አመት? ቀን ነው እንጂ” አለኝ፡፡ እኔን ያጋጠመኝ ግን እንደዚያ ነበር፡፡ ሙሉ አመት ድብርት ብቻ ሳይሆን ስቃይ፡፡

ቅዳሜ፣ ጥቅምት 29፣ 9፡00 ሰአት

ውድ ማስታወሻዬ

አሁን ያለሁት ሰፈራችን የሚገኘው ቁራ(አቡነ ጴጥሮስ) ት/ቤት ክፍል ውስጥ ከጓደኛዬ ከአቡሽ ጋር ነው፡፡ እሱ ሞቶበት ያጠናል፡፡ ለማትሪክ፡፡ እኔን ግን ልቤ ውስጥ ተሰንቅሮ ያለው ነገር ማጥናትን አልፈቀደልኝም፡፡ በዚህ ሁኔታ እንኳን ስትሬት ኤ ይቅርና 4 ማምጣት የምችል አይመስለኝም፡፡ሰውዉ ደግሞ ከ4 በታች ካመጣሁ የሚያስቆም የሚያስቀምጠኝ አይመስለኝም፡፡

የሆነ የተሰማኝን ነገር ለሰው የመግለጽ አመል አለብኝ፡፡ የኔ ለምለው ሰው ማለት ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ሰው ያስደሰተውን፣ የሚኮራበትን ነገር እንደሚናገር፣ እኔ ደግሞ የተከፋሁበትን፣ ያናደደኝን ነገር ለሰው የመተረክ ጸባይ አለኝ፡፡ አሁን ሲያንቀለቅለኝ የትናንቱን የኳየሬ ልጅ አንተ ብሎ የጠራኝንና እንዴት እንደመለስኩለት ለአቡሽ ነግሬው "የህጻን ልጅ ጸባይ አለብህ" አለኝ፡፡ "በትንሽ ነገር ትናደዳለህ፣ በትንሽ ነገር ትደሰታለህ"፡፡ ስሜቴን መረዳት አቅቶት ነው ወይስ እውነትም ህጻንነት ቢጤ ተጠናውቶኝ? ለነገሩ ከአቡሽ ከዚህ በላይ አልጠብቅም፡፡ በርግጥ ውጪ ሀገር ልጆች "loser" ስላሏቸው፣ "you are not cool" ስለተባሉ ብቻ እራሳቸውን የሚያጠፉ ተምሪዎች እንዳሉ ሰምቻለሁ፡፡ አንዳንዴ እራሴን ከነሱ ጋር አነጻጽራለሁ፡፡ እንደዚያ ያለኝ ሰው የለም ግን ለራሴው ነው እንደዚያ የማስበውና ማህበረሰቡ ውስጥ እንደሚጠበቅብኝ መሆን አለመቻሌ የሚሰማኝና በጣም የሚሳስበኝ፡፡

ዛሬ ኳየር ሄጄ ነበር፡፡ በጣም ደብሮኝ፣ የብቸኝነት ስሜቱም አይሎብኝ ነበር፡፡ ነገ ኳየር አለን፤ አገልግሎት ነው፡፡ መዝሙሩ እየተያዘልኝ አይደለም፡፡ በዚያ ላይ ብቸኝነቱ አለ፡፡ አሁንም ህይወት አስጠልታኛለች፡፡ አገልግሎቱን ስለማቆም እናቴን እንዳላማከራት ድፍረቱን አጣሁ፡፡

ከአቡሽ ከዚህ በላይ አልጠብቅም ያልኩት፡ አቡሽ ከኔ በላይ በትምህርት ጎበዝ ቢሆንም አስተሳሰቡ እንደኔ አይደለም፡፡ ሰውን አይረዳም፡፡ እዚህ ላይ ብቻ ሳይሆን ሌላም ጉዳይ ላይ፡፡ ችግር አለበት፡፡

መዝሙር እየተያዘልኝ አይደለም፣ ኳየር በጣም ያስቸገረኝ ነገር፡፡ በጣም ከመጨነቄ የተነሳ ጥናት እንዳስቸገረኝ፣ ድምጽ አልወጣ እንዳለኝ፣ መዝሙርም አልያዝ ብሎ ሲያስቸግረኝ ነበር፡፡ ኳየር ደብተር አንይዝም፣ በቃላችሁ ሸምድዱ የሚሉት ነገር አላቸው፡፡ አንድ ቀን ለማገልገል በተቀመጥንበት፣ ፈይሳ "የት/ቤቱ አንጂ የእግዚአብሔር ቤቱ አይያዝለትም ብሎ ልጆችን አስቆብኛል፡፡ ወይ ያ ጊዜ፡፡ ዞር ብዬ ሳየው ያሳለፍኩትን አባባ ጎርባጣ ጉድጓድ ገደሉን ብሎ ሲዘምር ዘማሪው ስለኔ ይመስለኛል፡፡ በብቸኝነት ቤት እኔው ከኔው ጋራ... ብቻ እግዚአብሔር ለምን እንዲህ ያሰቃየኛል ብዬ እራሴን እጠይቃለሁ፡፡ ለካስ ኤልሻዳዩ ጠብቆኝ ቆሜአለሁ ብዬ የምዘምርበት ቀን እንደሚኖር ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

ትምህርት ቤት፣ እንደ እረፍት ጊዜ የጠላሁት ነገር የለም፡፡ ብቻዬን የምገባበት፣ የምሸሽግበት የማጣበት ጊዜ ነው፡፡ የምሆነውን ሳጣ ማንም የማያየኝ ቦታ ራቅ ብዬ የአቡካዶ ዛፍ ስር መደበቅ ጀመርኩኝ፡፡ ለሁለት ቀን እንደዚያ አርጌ ሶስተኛው ላይ ልጆች ከሩቅ አይተው ሲያፈጡብኝና ሲገምቱኝ፣ አቆምኩት፡፡ የክፍሌ ልጆች ከመቼውም ጊዜ በላይ ተባብረው አንድ ሆነው ነበር፡፡ እረፍት ላይ ከድሮ ጓደኞቼ ጋር ስቆምና ሳወራ ምናምን ምንም ደስተኛ አልነበርኩም፡፡ የክፍሌ ልጆች እነኢዩኤል፣ እነሄለን፣ እነበረከት፣ እነነብዩ፣ እነአሚር፣ እነቅድስት፣ እነሜቲ ሻይ ቤት ሲስቁና ሲጫወቱ ከሩቅ ይታዩኛል፡፡ ወደነሱ ላለማየት ጥረት አደርግ ነበር፡፡ ግን ዋጋ የለውም፡፡ ልቤ እነሱ ጋር ነበረች፡፡ እነሱ ጋር መሆን ነበረብኝ፡፡ መሆን ያለብኝ ቦታ አለመሆኔ ደግሞ ከባድ ስሜት ውስጥ ከትቶኛል፡፡ አንድ ቀን እረፍት ላይ ተሰባብሬ ኩምሽሽ ብዬ ከድሮ፣ ከስምንተኛ ክፍል ጓደኞቼ ጋር የምንቆምበት ቦታ ነበርኩኝና፣ የሆነ ነገር ለማንሳት እንደፈለገ ሰው ጎንበስ ብዬ ቁጢጥ አልኩኝና የሆነ ነገር እንደሚጽፍ ሰው መሬቱን ጫር ጫር ማድረግ ጀመርኩኝ፡፡ ማልቀስ አምሮኛል፡፡ ቤት ስቅስቅ ብዬ ባለቅስ ልቤን የሚያመኝ የሚወጣልኝ ይመስለኝና እራሴን ለማስለቀስ እሞክር ነበር፡፡ ግን ስቅስቅ ብሎ አይለቀስልኝም፡፡ አቀማመጤ እምባ እንደያዘውና ሰው እንዳያየው እንደፈለገ ሰው ነበረ፡፡ ቡከር የሚባል ልጅ መጣና "በጣም ደብሮሀል አይደል? አንጨቱን ለማንሳት አይደለም የተቀመጥከው" አለኝ እየታዘበኝ እንደነበረ ሰው፡፡ በመጨረሻ ህመሜን አይቶ እኔን ከመጉዳት ይልቅ የጠየቀኝ ሰው፡፡ የጠፋ ወንድሜን ያገኘሁ ነበር የመሰለኝ፡፡ አዎ አልኩት ባንገቴ ፈገግ ብዬ፡፡ ይሄ አስቀያሚ ጭንቀት ዋና አስከፊነቱ፣ ፊትን ዝቅ ማድረጉ ነው፡፡ የሆነ ደህና እያወሩኝ ፊቴን ሲያዩ ማውራት ያቆማሉ፣ ፊቴን አይተው መሳደብ ይጀምራሉ፡፡ ፊቴን አይተው ይሸሹኛል፡፡ ማንም ምን ሆንክ? ብሎኝ የሚያውቅ የለም፡፡ የሚከፋው ደግሞ ቀና ብለው ያዩኛል ብዬ የማላስባቸው ልጆች ንቀት፡፡ የማረገው ነገር አልነበረኝም፡፡ ጭንቀቱ ባመጣው መዘዝ ሌላ ጭንቀትና ንዴት፡፡ እንዲህ ፊቴ በተከሰከሰበት ጊዜ አንድ ሰው ሳይጎዳኝ፣ ሳልሸማቀቅ መዋል አይታሰብም፡፡ ያን ለማራቅ ያለኝ አማራጭ ከቤት አለመውጣት ይባላል፡፡

ስለ ሰዎች በፊት የማላስባቸውን ነገሮች ማሰብ ጀመርኩኝ፡፡ አንድ ሰው በፊት ሰላም ሲለኝ የነበረ ከሆነና ሰላም ሳይለኝ ካለፈ፣ ናቀኝ ነው በቃ፡፡ ቀኑን ሙሉ ስለሱ ሳስብ ነው የምውለው፡፡ በፊት ለምን ሰላም ሲለኝ ነበር አሁን ደግሞ ለምን አላለኝም? ሰዎች ምን ያህል ነው

የሚያከብሩኝ፣ ምን ያህል ነው የሚንቁኝ የሚለውን ዝም ብዬ አስባለሁ፡፡ ሰውየውኮ ዛሬ እንዳየኝ እራሱ አያስታውስም፡፡ እኔ ግን እንዲህ ስለሆነ ነውኮ እንዲህ ያደረገው፣ እንዲህ ስለሆነ ነውኮ እንደዛ ያደረገው እያልኩ በቃ እመራመራለሁ፡፡ ለሰው ስነግር ደግሞ ለምንድነው ነገር አጣምመህ የምታስበው? ሰው መጥፎ ነገር ሲያደርግ በመልካሙ አስበው እንጂ በመጥፎ አትተርጉመው ይሉኝ ነበር፡፡ ብዙ ሰው ነው እንደዚህ የሚለኝ፡፡ እንዲያውም እኔ ሰው ያላሰበውን ግን እያደረገ ያለውን ክፋት በተለይ እኔ ላይ አስቤ አንተኮ እንዲህ እንዲህ እንዲህ እያደረግክ ነው፣ እንዲህ እንዲህ የሆንከውኮ እንዲህ ስለሆነ ነው እለዋለሁ፡፡ "አንተ ግን ምን አይነት ሰው ነህ? እንዴት እንዴት ነው ምታስበው? እኔ እንደዚህ አስቤም አላውቅም" ይለኛል፡፡ ያሰብከውን ሳይሆን ያደረግከውን ነው እየነገርኩህ ያለሁት እልና የአለማችን ቁጥር አንድ ደግ ሰው ነኝ ብሎ የሚያስበውን ሰው የአለማችን ቁጥር አንድ ክፉ አድርጌ አርፈዋለው፡፡ እኔ ያሰብኩትና የገመትኩት ነገር እውነት ይሆናል፡፡ አስበው እስኪ፣ እንዲህ እንዲህ እየሆነ አንተ እንዴት እንደዚህ አታደርግም? እያልኩኝ ሰውየውን አሳምነዋለሁ፡፡ ሰውን ክፉ እንደሆነ ማሳመን ለሰውየው ይደብራል፡፡ እኔ ግን ደስ ይለኛል፡፡ ትክክል መሆን ነዋ፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ በማስባቸው ነገሮች ትክክል ትክክል እየሆንኩኝ ነበር፡፡ የምሳሳታቸው ነገሮች ጥቂት ነበሩ፡፡ ከሰው ጋር ሁሌ መከራከር እየሆነ መጣብኝ፡፡ አስተሳሰቤ እየተቀየረ ነበር፡፡ በርግጥ ከቤት ቆይቷል ይሄን ፍልስፍናህን ተው ይሉኝ ከጀመሩ፡፡ የሆነ ነገር ከተነሳ ሁሉንም የታሪኩን ሜፍ መዳሰስ ያምረኝና እነሱ ወደ ሌላ ርዕስ ሊያልፉ ሲሉ ቆይ ይሄ ይሄ አልገባኝም ማለት ለምን አንዲህ ሆነ፣ ለምን ወጣ? ለምን ወረደ? ማን፣ ምን? ብዬ ስጠይቃቸው ይመልሱልኝ ይመልሱልኝና ኡፍ አትጨቅጭቀኝ እስኪ፡፡ ሁሉንም ነገር ካላወቅክ አይሆንም? ይሉኛል፡፡ አቡሽን ሁሌ እንዳማረርኩት፡፡ የሆነ ጊዜማ እሱ የሚያወራው ነገር እንዳለ አስጠልቶኝ፡፡ ምን ማለት ነው እንዲህ ማለት? የሚጋጭ ነገር ለምን ታወራለህ? እለዋለሁ፡፡ እንዲህ ማለት ከፈለግክ እንዲህ ነው አትልም እለዋለሁ፡፡ "በቃኮ ካንተ ጋር ማውራት ከባድ እየሆነብኝ ነው፣ ለማወራው ነገር ሁሉ እንከን ታወጣለህ" አለኝ አንድ ቀን፡፡ ይሄ ጸባይ እያገረሸብኝ ነበር፡፡ ሰው ትችቱ ትክክል ቢሆንም የምታወራውን ነገር ሲያጣጥል፣ ምንም ደህና ነገር ማውራት እንደማትችል ሲነግርህና ሲያሳይህ ደስ ይልሃል እንዴ? ይደብርሃል፡፡ ሰው ሸር ሲያስብብኝ ከሰውየው ቀድሜ ነበር የምነቃው፡፡ በቃ ይሄ ልጅ እንዲህ ያረጋል ስል ይሆናል፡፡

ኳየር ልጆችን መቅረብ አልሆንልህ ሲለኝ ለመከበር ከፈለግክ ናቅ የሚለውን ፕሪንሲፓል ለመጠቀም ማሰብ ጀመርኩ፡፡ እኔ አሰብኩ ማለት አረግኩ ነው፡፡ አንድ ቀን ልንዘምር እየተዘጋጀን ነበር፡፡ ብቻዬን ሆንኩና አንዷት ቆርቆሮ ቤት ሄድኩኝ ልጆች እንዳሉ አውቄ፡፡ ቢቂላ፣ ጉዲሳና ታምራት የተባሉ ልጆች ተቀምጠው በስልክ የሆነ ነገር እያዩ ነበር፡፡ ስሄድ የሚያገሉኝ ነገር መሰሎኝ ነበር፡፡ ሳይ ሪስሊንግ ተመስጠው አይ እይ እንዲህ አደረገ እያሉ ያያሉ፡፡ "አንደ ህጻን ሪስሊንግ ታያላችሁ እንዴ? አልኳቸው፡፡ ከዚያ ቢቂላ የህጻን ከሆነማ አትይ ብሎ ከለለኝ፡፡ ሶስቱም እውነት ነውኮ ብለው ከለሉኝ፡፡ እኔ ደግሞ ምንም እንዳልመሰለው ሰው ኤጭ ብዬ ስልኬን አወጣሁና ቴትሪሴን ከፍቼ መጫወት ጀመርኩ፡፡ በነገራችን ላይ ቴትሪስ ሀይ ስኮሬ 162000 ነው ብታምንም ባታምንም፡፡ ሲደብረኝ፣ቴትሪስ፣ ሰው ሲያገለኝ፣ ቴትሪስ፡፡ ዲሽ ስለሌለ ቴትሪስ፡፡ ጉዲሳ ይሄ ደግሞ የትልቅ ሰው መሆኑ ነው? አለኝ፡፡ አዎ የጭንቅላት ጨዋታ ነው አልኩት፡፡ያን ቀን ውሸቴን ዛሬ ባጥም ደስ ብሎኛል ምን እንዳገኘሁ አላውቅም ምናምን ብዬ ደስተኛ ለመምሰል ሞከርኩ፡፡ ቃላት ሲደክሞ ፎቶ ይናገራል ነው ያሉት? ፊት ማስመሰል ሲያቅተው፣ ቃላት ለማስመሰል ይሞክራሉ፡፡ ከተሳካላቸው፡፡

ሰኞ ኅዳር 7 ከቀኑ 9፡30

ውድ ማስታወሻዬ

አሁን ቢያንስ ልቤን የሚያመኝ ተወግዶልኛል፡፡ ኳየር ስለማቆም አባትናና እናቴን አናግሬ ነበር፡፡ የእናቴ ለኔ እንደዚያ መቆርቆር ያልጠበቅኩት ነበር፡፡ እሷ ልጁ ተጨነቅኩ እያለ ነው ያቁም አለች፡፡ አባቴ ደግሞ ማቆም መፍትሄ አይሆንም፡፡ ከእግዚአብሔር ቤት መሸሽ የለብህም ነበር ያለኝ፡፡ ሁለቱም ተመችተውኛል፡፡ ታዲያ እኔም ለመቀጠል ወሰንኩ፡፡ ጉዲሳ የሚባል ልጅ ስዘምር ሰምቶ የሚመጣው ሀሙስ፣ 6 ልጆች ሆነን የወጣቶች ፕሮግራም ላይ እንዘምራለን፡፡ በህይወቴ ወጣቶች የሄድኩት አንዴ ብቻ ነው፡፡ ታዲያ እኔን መምረጣቸው አስደስቶኛል፡፡ ከኳየሩ ጉዲሳ ተመችቶኛል ግን አሁንም ቢሆን ኳየር አስጠልቶኛል፡፡ ከኳየርና ከትምህርት ቤት ልጆች የሚበልጠው የማትሪክ ዝግጅት በጣም አሳስቦኛል፡፡

አንድ ቀን ት/ቤት ከእረፍት በኋላ ባዶ ፔሬድ ነበረን፡፡ 10ኛ ክፍል እንደ አስተማሪ እንደ ማጣት የምጠላው ነገር አልነበረም፡፡ ተማሪ ተሰብስቦ ስለሚያወራ ብቸኝነቴን ያጎላዋል፡፡ አስተማሪ ሲኖር ማንም አያወራም፣ ማንም ወደኔ አያይም አሪፍ ነው፡፡ አንድ ቀን አስተማሪ አልነበረምና ብቻዬን ሆንኩኝ፡፡ አሚር ቀርቶ ሆነ የት እንደ ገባ አላውቅም፡፡ ከክፍል ወጣሁና ሄጄ ጥላ ስር ሳር ላይ ተኛሁ፡፡ ተኝቼ ስልኬን እየነካካው ነበር፡፡ ሌላ የክፍሌ ልጆችም ከኔ ፈቀቅ ብለው ተኝተው እያወሩ ነው፡፡ ዘበኛ መጣና ተነሱ በትምህርት ሰአት ውጪ መቀመጥ አይቻልም አለን፡፡ አስተማሪ እንደሌለን ነገርኩት፡፡ እዛ ት/ቤት ስልክ ይዞ መሄድ አይቻልም፡፡ ከተያዘ 100 ብር ያስከፍላሉ፡፡ ዘበኛው ስልኬን አላየም ነበር፡፡ ከኔ ፈቀቅ ብለው ተኝተው ለነበሩ ልጆች ውሸቴን "አንድ ቀን እንዲሁ ስልክ ስነካካ ዘበኛው ያዘኝና ስልክህን ይገፍብህ ቢሮ አስገብቼ 100 ብር ትከፍላለህ፣ ወይስ ለኔ 50 ብር ሰጥተኸኝ ልለፍህ? ሲለኝ እኔ ደግሞ ትተወኛለህ ወይስ እንዲህ ያልከኝን ሄጄ ቢሮ ልናገር? አልኩት፡፡ ቢሮ አያምኑህም ሲለኝ ድምጽ እየቀዳሁ ነው ብዬው ጠፋሁኝ አልኩት" አልኳቸው፡፡

ሀሙስ ህዳር 11፣ 11:30

ውድ ማስታወሻዬ

ይህ የወጣቶች ፕሮግራም የሚጀመርበት ሰአት ነው፡፡ ታዲያ እንዴት በዚህ ሰአት ቤት ኖርኩኝ? ተውኩት እንዴ? በርግጥ 11 ሰአት ላይ እዚያ ልምምድ ላይ ነበርኩ፡፡ ሙሉ ዘገባው እንደሚከተለው፡

ቅዳሜ ምሽት ኳየር እንዳለቀ ፈይሳ የሚባለው ልጅ አያንቱ፣ ለሲሴ ጉዲሳ፣ ሄራን ወደ ኋላ ቅሩ፣ ሌሎቻችሁ ግቡ እንዳለ፣ ጉዲሳ "ናቲ" ብሎ እኔን አስታወሰው፡፡ ፈይሳም እና "ናቲ" አለ፡፡ ነገሩ ገብቶኛል፡፡ የመጠራቴ ምክንያት፡፡

ኳየር በገባሁ ሰሞን አንድ ቀን፣ ትዝ ይለኛል ለአንድነት ቀናችን ከቸርች ግቢ ውስጥ የማገዶ እንጨት እየለቀምን ነበር፡፡ እኔ ጉዲሳና ታሜ ስለ ዘማሪዎች እያወራን እኔ የእንዳለ የድሮ መዝሙሮች ከአዲሶቹ ይበልጣሉ ብዬ እየተከራከርኩ ነበር፡፡ አውቄ ድምጼን እንዲሰሙ የምወደውን "እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ማራት ባርካት" ዘመርኩላቸውና ከነጭራሹ ራሱ ይሄን መዝሙር የሚበልጥ አለ? አልኳቸው፡፡ ለካ ጉዲሳሆዬ ድምጼን ሴቭ አርጓታል፡፡ የድምጼን ጥሩነት ለነፈይሳ ሳይነግር አልቀረም፡፡ ስለዚህ የጉዲሳ ምርጫ ሆኖ ነው እንጂ ፈይሳ እንድዘምር ፈልጎ አይደለም ለማለት ነው፡፡ ያን ስለ ሪስሊንግ ያበሸቅኳቸው ቀን ደግሞ ጉዲሳ ዎርሺፕ መግባት አትፈልግም ብሎ ጠይቆኝ ነበር፡፡ እጀምርና ከተመቸኝ እቀጥላለሁ ነበር ያልኩት፡፡ አልፈልግም ማለት ደብሮኝ እንጂ ወጣቶች ፕሮግራም ላይ መዘመር እንደሆነ አልገባኝም ነበር፡፡ ሌሎቹ ልጆች ከኳየር ቤቱ ከወጡ በኋላ 6ታችን ተጠጋግተን ውይይት ጀመሩ፡፡ ወጣቶች ላይ እንደምንዘምር ሰማሁ፡፡ አልፈልግም እንዳልል እነሱ ራሳቸው መርጠውኝ ብዬ አሰብኩ፡፡ ለልምምድ ስንገናኝ ደግሞ ግኝኙነታችን ሊሻሻል ይችላል ብዬም ገመትኩ፡፡ ከዚያ የጉዲሳ እህት ለሲሴ መጨመር የምትፈልጉት መዝሙር ካለ ስትል እስኪ ምን አንቀለቀለኝ? የእንዳለን ኢትዮጵያን ማራት የሚለውን እንዘምር ስል አያንቱ አንዘምርም አለች፡፡ መዝሙሩ ሰምታ ራሱ የምታውቅ አይመስለኝም፡፡ ከኔ ስለመጣ ነውኮ፡፡ የሆዴን በሆዴ ያዝኩት፡፡ እኒያ ልጆች እኔ ሳወራ ሆን ብለው ጆሮ ዳባ ልበስ ይላሉ፡፡ በተለይ የፈይሳ አይወራ፡፡ የቀረውን ታሪክ ሌላ ጊዜ ልቀጥል፡፡

ሌላ ጊዜ ልቀጥል ብዬ ያቆምኩት ጊዜ ስላጠረኝ አይደለም፡፡ ለቀጣይ 3 አመታት ማስታወሻዬን ስጽፍ ይሄን ታሪክ(ገጠመኝ) አልቀጠልኩበትም፡፡ ያልቀጠልኩበት ምክንያት ግን ስላልመቸኝ ወይም ጊዜ ስላጠረኝ ሳይሆን ማስታወሱ፣ እንደገና ማስታወሱ ስላስጠላኝና ስለከበደኝ ነው፡፡ ማን ከደረጃው ዝቅ ተደርጎ የተረገጠበትን ቀን ማስታወስ ይፈልጋል? መጥፎ ትዝታን በሩቁ ነው፡፡ በተለይ ማን እንደኔ ለራሱ ማስታወስ የማይፈልገውን ነገር ገሀድ ያወጣል? ምክንያት ያለው maybe? ትዝታው እንዲህ ይቀጥላል፡

እስከ ሀሙስ ማለትም እስከ ፕሮግራሙ ቀን እየተገናኘን እንድንለማመድ ተስማማን፡፡ ያን ቀን ነበር ግን እኔ ለምን ሰው ሲሰድበኝ ዝም ብዬ አዳምጣለሁ? ለምን አልሳደብም? ለምን ራሴን አላስከብርም ብዬ እነፈይሳን ስለማኮላሸት ማሰብ የጀመርኩት፡፡ የመጀመሪያ የልምምድ ቀን ፈይሳን ዝም ብዬ አላየሁትም፡፡ ያን ቀን ዝናብ ዘንቦ ልጆች አልመጡምና አልተለማመድንም፡፡ ዘንቦ ሲያባራ በቃ እኔ ወደ ቤት እገባለሁ አልኳቸው፡፡ ፈይሳ ጉዲሳን ጠራውና ፊቱን አጨማዶ ውውው በሚል ድምጽ "ስማ `ወደ ቤት እገባለሁ` አለ" አለው፡፡ "አንተ ነህ ያልከው እኔ እንደዚያ አላልኩም፣ እንደዚያ ስትል ምን እንደምትመስል ግባና በመስታወት እራስህን እይ" አልኩት፡፡ ምንም አላለም፣ ሀሳቡ ከየት እንደመጣልኝ ገርሞኝ እኔ ሳቄን ለቀቅኩት፡፡ ዝም ብሎ አየኝ፡፡ ያን ቀን ፈይሳ በጣም ነገሬን ሲፈልግ ነበር፡፡ እኔም እንደዚያው፡፡ ግን ጥያቄው እሱ ከሶስት አመት በኋላ የዚያን ቀን ምልልሳችንን እንደኔ ያስታውሳል ወይ? የሚለው ነው፡፡

ከጉዲሳ(የቄስ ልጅ ነው) ጋር እያወራን እኔ ትምህርት ቤት 5ኛ ፔሬድ ምናምን ስል፣ እሱ፣ ፔሬድ የሴቶች የወር አበባ ነው፣ ክፍለ ጊዜ፣ ፕሬድ ነው የሚባለው አለኝ፡፡ ክፍለ ጊዜ ፔሬድ አይባልም ብሎ ሳቀ፡፡ አጻጻፉ አንድ ሆኖ አነባበቡን ስንቀይረው የተለያየ ትርጉም ይሰጣል ማለት ፈልጎ ነው፡፡ እኔ ደግሞ ሁለቱም አንድ ነው አልኩት፡፡ እንዲያውም የሴቶች ፔሬድ ወቅታዊ ስለሆነ ነው ፔሬድ የተባለው፣ በትርጉምም ቢሆን ሁለቱም አንድ ናቸው አልኩት፡፡ ከዚያ ጥቂት ተከራከርን፡፡ አልሰማ ሲል "በቃ እንግሊዘኛ አትከራከረኝ" አልኩት፡፡ እየሄድን ነበርና ስንከራከር የነበረው ሄራን የምትባለዋ ልጅ ከፊት ለፊታችን ለካስ እየሄደች ታዳምጠን ነበር፡፡ እኔ እንግሊዘኛ አትከራከረኝ ስለው ጉዲሳ "እንግሊዘኛ እችላለሁ ማለትህ ነው?" አለኝ፡፡ "አዎ" አልኩት፡፡ "አወቅኩ፣ አወቅኩ ብላ፣ የቄስ ሚስት…" ሲል ከፊታችን የነበረችው ሄራን እየሰማችን ነው ሳትባል "…መጽሐፍ አጠበች" ብላ ጨረሰችለት፡፡ እኔ ላይ ማበሯ ነውኮ፡፡ "አወቅኩ አወቅኩ ብላ የቄስ ሚስት መጽሐፍ አጠበች"፡፡ "እና ማንነው የቄስ ሚስት?" ብዬ ምሳሌውን ራስ በሚያሳምም ጥያቄ መለስኩለት፡፡ As soon as I said it, I regretted it. ወለም ያለ ምላስ፣ በቅቤ አይታሽም፡፡
ይሄን መፅሐፍ ስጽፍ፣ እርግጠኛ ለመሆን፣ 'period' የሚለውን ቃል ትክክለኛ አነባበብ ከስልኬ ዲክሺነሪ ላይ ስሰማው፣ ሴትየዋ "ፒሪየድ" ነው የምትለው፡፡ we were both not correct after all.

ቀጣይ ቀን መዝሙሮቹን ተለማመድን፡፡ ጭንቀቱ ሊገለኝ፡፡ ከልጆች ጋር መቀራረብና መግባባት የትየለሌ ሆነ፡፡ ቀጣይ ቀንም ተለማመድን፡፡ ተለማምደን ተለማምደን ቀኑ ደረሰ፡፡ የፕሮግራሙ ቀን ከአስር ሰአት በኋላ እየተለማመድን የሆነ ነገር ስል ፈይሳ ያንን ያልኩትን ነገር የሚደግመውን ደገመልኝ፡፡ ተናደድኩኝ፡፡ አቋቋማችን እንዴት እንደሚሆን አሬንጅ እያደረጉ፣ ሄራን የምትባለዋ ልጅ እኔ “እፈራለሁ ስትል ነበር አይደል? እዚህ ጋር ቁም” ብላኝ ከጎኗ ከጉባኤው ጋር ፊት ለፊት የማልተያይበት ቦታ አስቆመችኝ(ጨረቃ ሰርተን ነበር የምንቆመው) ሄጄ ቆምኩኝ፡፡ ወዲያው ፈይሳ “ናቲ ና እዚህ ጋር ሁን” ሲለኝ ምንድነው፣ እሷ እዚህ ጋር ሁን ትላለች፣ አንተ እዚህ ጋር ትላለህ እያልኩ እሱ ያለኝ ቦታ ስሄድ አያንቱ “ዝም ብለህ ቁም የተባልክበት ቦታ ቁም፡ ነንሴንስ” አለችኝ፡፡ ብልጭ አለብኝ፡፡ ልብ በል፣ የቤተ-ክርስትያን መድረክ ላይ ቆመን ነው እንዲህ የምትለኝ፡፡ ጭው አለብኝ፡፡ በጥፊ ቿ ያደረገችኝ ነበር የመሰለኝ፡፡ በልጆች መሀል፡፡ በልጆች መሀል ዝም ብለህ...ነንሴንስ አለችኝ፡፡ ቃላቱ የንቀቷን ብዛት ለመግለጽ በቂ ስለሆኑ ስትለኝ ፊቷ እንዴት እንደነበረ ማብራራት ያለብኝ አይመስለኝም፡፡ ማንም እንደዚያ አናግሮኝ አያውቅም፡፡ “ታካብጃለሽ እንዴ? ቆይ ለማገልገል ነው አይደል እንዴ የምትመጡት?” አልኳቸው፡፡ ከዚህ በፊት ቤት ሆን ብዬ ክፉ ክፉ ቀናቶቼን እያሰብኩ ለማልቀስ ሞክሬያለሁ፡፡ ሳለቅስ ጭንቀቴ ይወጣልኛል ብዬ አስብ ነበር፡፡ ከተልሚድ ላይ መሰለኝ በሳምንት ሶስቴ ማልቀስ፣ በቀን ሶስቴ መሳቅና በሰአት ሶስቴ ፈገግ ማለት ለጤና መልካም መሆኑን ያነበብኩት፡፡ በሳምንት ሶስቴ ማልቀሱን ባለቅስ ደስ ይለኝ ነበር፡፡ ግን እንኳን በሳምንት በወር በሁለት ወር ማልቀስ አልቻልኩም፡፡ እልቅሼ ለመገላገል ስሞክር አንድ ዘለላ እምባ ብቻ ነው እንዲሁ ከመሬት ተነስቶ ወይም ለፊልም፣ ከልቡ ሳይሆን ለማስመሰል እንደሚያለቅስ ሰው የሚወጣኝ፡፡ እሱም በመከራ፡፡ መሳቅ፡ መሳቅ ናፈቀኝ፡፡ ማለት የሚያስቅ ነገር ፊልም ላይ ሳይ ምናምን እስቃለሁ፣ ሰው ሲቀልድ ከሌላው ላለመለየትም ቢሆን እስቃለሁ፣ ግን ሰው ሲስቅ የሚሰማው መፍታታት(relaxation) ናፈቀኝ፡፡ የሚሰማኝ ነገር ቢኖር ጭፍግግ የማለት፣ ጠባብ ሳጥን ውስጥ ተዘግቶበት መውጣት የሚፈልግ፣ መሳቅ የሚፈልግ፣ ወደ ድሮው መመለስ የሚፈልግ ሰው ስሜት ነበር፡፡ ከዚያ አመት በፊት በትንሽ ነገር ስናደድ ወይም ስከፋ የአለማችን ቁጥር አንድ ሀዘንተኛ ሰው አድርጌ ነበር ራሴን የምቆጥረው፡፡ እንዲህ አይነት ሙት ስሜት እንዳለ አላውቅም ነበራ፡፡ አያንቱ “callisii iddoo namni dhaabbadhu siin jedhe dhaabbadhu, nonsense!” ስትለኝ በሶስት ወራት ውስጥ በየቀኑ የሰበሰብኩት የሚያሳምም ስሜት በሙሉ መጥቶ ፊቴ ድቅን፡፡ ለካስ ያ ሁሉ ጭንቀት የሚፈጥው ብሶትና እምባ ሁሉ በየቀኑ ራሱን ሲያጠራቅም ነበር፡፡ ግድብ እየተሰራለት ነበር፡፡ የመጥፎ ትዝታዎች፣ የመናቅ፣ የጭንቀት፣ የውድቀት፣ መሞት የመፈለግ ስሜቶች ብሶትና እምባ ተገድቦ ተገድቦ ግድቡ እየሞላ ነበር፡፡ የአያንቱ ስድብ በጣም ብዙ አምባን መፍጠር ብቻ ሳይሆን በቅጽበት የእምባ ግድቡን የማፍረስ አቅም ነበረው፡፡ ለዚያ ነበር እሷ እንደዚያ ስትለኝ እምባ ከየት መጣ ሳልለው እንደ ደራሽ ውሀ ወደ አይኔ መፍሰስ የጀመረው፡፡ ሲመጣ ይታወቀኛል፡፡ መጥፎ ጊዜ፡ በልጆች ፊት፣ ለአገልግሎት ደቂቃዎች ሲቀሩኝ፡፡ እምባ አይኔን ይሞላው ጀመረ፡፡ ልቆጣጠረው ሞከርኩ ያን ቀን እምባዬን ልቆጣጠረው የሞከርኩትን ያህል ምንም ነገር ሞክሬ አላውቅም፡፡ አይኔ በእምባ ይሞላ ጀመረ፡፡ እምባዬን ስለ ጥሩ ነገር በማሰብ ላባርረው ሞከርኩ፡፡ አዕምሮዬ ግን ባለፉት ሶስት፣ አራት ወራት ያሰቃዩኝን አጋጣሚዎች ከፊቴ እየደቀነ እያፋፋመው ነበር፡፡ ከአዕምሮዬ ጋር ግብግብ፡፡ በጣም እንደተበሳጨሁ ያዩት አጠገቤ ተሰብስበው የነበሩት ልጆች፣ ግራ ሲጋቡ ነበር፡፡ ይሄን ያህል ያናድዳል እንዴ እያሉኝ ያሉ ይመስል ነበር ፊታቸው፡፡ አይኔ በእምባ እየተሞላ እየተሞላ ሲመጣ እንዳያዩኝ ቀና ብዬ ጣሪያ ጣሪያውን ማየት ጀመርኩ፡፡ ታውቃለህ፣ እንዳያዩኝ ለምን አላቀረቀርኩም? ብዬ ቀና ማለቴ አልተዋጠልኝም ነበር፡፡ ላለመታየት ሰው ጎንበስ ነው እንጂ የሚለው ወደ ላይ አያንጋጥጥም፣ ለምን ወደ ታች አላልኩም ብዬ እየተወዛገብኩ ነው እንዳያዩኝ ቀና አልኩኝ ያልኩት፡፡ ይሄን ጽሁፍ እየጻፍኩ እያለሁ ነው ወደታች ማየት ትቼ ወደ ላይ ማንጋጠጥ የጀመርኩት፣ እምባ ከአይኔ ውስጥ እንዳይወጣና ልጆች እምባዬን እንዳያዩ መሆኑን የተረዳሁት፡፡ ወደ ታች ካልኩ እምባዬ ይዘረገፋል፡፡ አያንቱ “ናቲ ይቅርታ” አለችኝ፡፡ ምንም አላልኳትም፡፡ እኔ እንደዛ እያለሁ መዘመር ጀመሩ፡፡ እያለቀስኩ መዘመር ጀመርኩ፡፡ ቀና ብያለሁ፣ እምባ ከአይኔ ወጥቶ ፊቴ ላይ እንዳይፈስ እየታገልኩ ነው፡፡ ልምምድ ተጀመረ፡፡ ኪቦርዲስቱ ኪቦርዱን እየመታ ነው፡፡

Madda haara galfii gaaddisa boqonnaa
Sitti hirkadhee ani argadhee boqonnaa
Harki kee inni waan guutuu
Naaf ta’eera boqodheeraa
Naan jette hin beektuu
Ani siinnuuffee sirratti haara galfadheeraa
Siin shakkuu maal ta’iinnaa jedhee
Raawwadhee sitti of gateeraa
Kaleessa inni dabarsitee
Boris qoodi koo si biraa…

መኖሪያዬ ነህ ጌታዬ መኖሪያዬ ነህ ኢየሱስ
አሳርፈኸኛል እፎይ ብያለሁ አንተን አግኝቼአለሁ
ወዳጅ እንደሌላቸው አልተዋችሁም አልረሳችሁም
ብለህ ተናግረሃል ያልከውን ልትፈጽም አንተ ሔደሃል…

አይጓደል ልማዴ እሰዋለሁኝ ለውዴ
ሆነ አልሆነ ነገሩ አባቴ አለ በመንበሩ …

እነኚህ መዝሙሮች ከዚያ በኋላ በሰማኋቸው ቁጥር ያንን ቀን ያስታውሱኛል፡፡ ምን ላርግ ራሴን መቆጣጠር አቃተኝ፡፡ እምባ አይኔ ውስጥ እንደሞላ አውቀዋል፡፡ እያለቀሰ ነው ብለውም ሊሆን ይችላል፡፡ እንደዚህ ሆኜ ማገልገልማ አልችልም፡፡ እምባዬ በደቂቃዎች ውስጥ የማስቆመው ሳይሆን በደቂቃዎች ውስጥ የሚዘረገፍ ነው የሚመስለው፡፡ ልጆቹ እየዘመርን ምን ሆንክ፣ ተው በቃ የሚሉኝ መስሎኝ ነበር፡፡ እነሱ ግን እንዲያውም እኔ ለማልቀስ እያኮበኮብኩ ይቀልዳሉ፡፡ ጉዲሳና አያንቱ እየተቀላለደዱ ነው፡፡ ትንሽ ቆይቶ እየዘመርን እጆቼን ከሆዴ በታች አያይዤ ነበርና ለሊሴ ወደኔ መጥታ አስፈታቸኝ፡፡ እየቀለደችብኝ ነበር፡፡ እንዲሁ ነው፡፡ ስታዝን ሰው ይጠይቅሃል፣ ያስተዛዝንሃል፣ ስትከፋ፣ ስታለቅስም…ም እንዲሁ፡፡ እንዲህ ስትጨነቅና ዲፕሬሽን ሲጫወትብህ ግን ማንም ምንም እንደማይልህ(ማንም እንደማይገደው) እኔ የአይንም፣ ቋሚም ምስክር ነኝ፡፡ የሚጨምሩልህ ነገር ካለ ንቀት ነው፤ ሚጨምሩልህ ነገር ካለ ስድብ ነው፡፡ ማንም ምን ሆንክ ብሎ ሊያጽናናህ የሚሞክር የለም፡፡ ሳት ብሏቸው የጠየቁህ እንደሆነ እንኳን አንተ የሚሰማኝ፣ ሊረዳኝ፣ ሊረዳኝ የፈለገ ሰው አገኘሁ ብለህ የሆድህን ዘክዝከህ ስትነግራቸው በነጋታው አስታማሚ ሳይሆን ከሌሎቹ የባሱ አሳማሚ ይሆኑልሀል፡፡ ሰው ሁሌም አንተን ለመጣል የተዘጋጀ ሽጉጥ አለው አዕምሮው ውስጥ፡፡ ሁሌ አንተን ለመጣል ይፈልጋል፡፡ የሽጉጡ ቀለሀ ደግሞ ያንተ አዕምሮ ውስጥ ነው ያለው፡፡ እንዲህ ተጨነቅኩኝ፣ ገለመሌ ዘለመሌ አልከው ማለት ቀለሀውን አስረከብከው ማለት ነው፡፡ ምንድነው ያልኩት? ሽጉጥ አለው ብቻ አይደለም፣ ሁሌም አንተን ለማጥቃት የሚፈልግ ሽጉጥ ነው፡፡ ሽጉጥ ሰው እስካልተጠቀመው መተኮስ አይችልም ብለህ ይሆናል፡፡ ግን ሰውየው አንተ የሆድህን ስትለፈልፍለት አውቆ፣ አስቦበት ስላልሆነ የሚጎዳህና የሚያሸማቅቅህ፣ ሽጉጡ ሰውየውን እንደሚያስገድደው እናስብ፡፡ ሁሌ አንተን ሊያጠቃ የሚፈልገው ሽጉጥ፡፡ አንተ ለማንም አለመናገሩን ችለህበት የሆድህን በሆድህ ይዘህ የምትሰቃይ ከሆነ ደግሞ መናገሩ(ቀለሀውን በፈቃድ መስጠቱ) አይኖርም እንጂ ጥቃቱ አይቀርልህም፡፡ ባትናገር የሚጨናነቀው ፊትህ ይናገራል፡፡ አንተ ባትናገር ብቸኝነትህ ይናገራል፡፡ የተጨነቀ አዕምሮህ ያለፈቃድህ፣ አንተ ምንም ሳትል ቀለሀውን ሰርቆ ለባለ ሽጉጡ ሰው ያስረክባል፡፡ ከዚያ ይተኮስብሃል፡፡ ከዚያ ሰው ሁሉ፣ ሊገልህና ሊያጠፋህ የተዘጋጀ፣ ተኳሽ አዳኝ ይመስልሃል፡፡ ሰው ሽጉጡን ሳይዝ ቢቀርብህ እንኳን ሽጉጡን ታፈላልገዋለህ፣ ትጠራጠራለህ፡፡

የወጣቶች ፕሮግራም ሊጀመር ከሩብ ሰአት በታች እየቀረው ሲመጣ፣ እምባዬን መቆጣጠር እንደተሳነኝ እያመንኩ ስመጣ፣ እንደዛ ሆኜ ማገልገል ስለማልችል ጉባኤተኛው መምጣት ጀምሮ ሳያየኝ ወደ ቤቴ ለመግባት ወሰንኩ፡፡ ሸንቴን ሸንቼ መጣሁ ብዬ ተለይቼአቸው ወደ ቤቴ ገሰገስኩ፡፡ እምባዬን እያዘራሁ፡፡ መንገድ ላይ፣ እያለቀስኩ ማንም ሊያየኝ አይገባም፡፡ ፈጠን ፈጠን እያልኩ በየመሀሉ እየሮጥኩ ነበር ስሄድ የነበረው፡፡ ከቸርች ብዙም ሳልርቅ አንድ መታጠፊያ ቸርች ፕሮግራም እየሄዱ አቢቲና ኩኩ መጡብኝ፡፡እንዳየኋቸው ጎንበስ ብዬ ጫማዬን የማስር መሰልኩኝ፡፡ ቆሙና ኩኩ ምን ሆንክ አለኝ፡፡ እያለቀስኩ እንደሆነ አውቋል ማለት ነው? ምንም አልኩትና ቀና ሳልል ጫማዬን ማሰሬን ቀጠልኩ፡፡ ዝም ስላቸው ትተውኝ ሄዱ፡፡ ወደነሱ ሳልዞር ፍጥነቴን ጨምሬ፣ መሄዴን ቀጠልኩ፡፡ ከዚያ በኋላ ያጋጠመኝ ሰው አልነበረም፡፡ ቤቴ ገብቼ ስቅስቅ ብዬ አለቀስኩ፡፡ ጌታ ሆይ ምን በድዬ ነው እንደዚህ የምታሰቃየኝ አልኩኝ፡፡ ድምጼን ከፍ አድርጌ ተንሰቀሰቅኩኝ፡፡ በጣም ነበር ሆድ የባሰኝ፡፡ የሶስት ወር ብሶት፡፡ ትራሴን በእምባዬ አራስኩት፡፡ አልቻልኩም፡፡ አለቀስኩ፡፡ ሳለቅስ ግን የሆነ የአዕምሮዬ ክፍል እፎይ ተገላገልኩ እያለ ነበር፡፡ ስቅስቅ ብዬ ማልቀሴን ሲመኝ የነበረው የአዕምሮዬ ክፍል፡፡ ያን ቀን ቸርች፣ ጥሩ እድሌን ነበር ያበላሸሁት፡፡

ፈይሳ ና እዚህ ጋር ቁም ሲለኝ እሱ ወዳለኝ ቦታ ዝም ብዬ መሄድ ነበረብኝ፡፡ ራሴን ነጻ ለማውጣት ወይም ንጹህ ነኝ ለማለት አይደለም ግን፣ እኔ ዝም ብዬ ከመሄድ `እሷ እዚህ ጋር፣ አንተ እዛ ጋር ቁም ትሉኛላችሁ" እያልኩ እያንገራገርኩ የሄድኩበት ምክንያት፡

1. አንድ ኳየር ውስጥ ያስተዋልኩት ነገር አለ፡፡ መታዘዝ የሚባል ነገር የለም፡፡ አንድ ሰው እንዲህ አርግ ካለህ፣ በግልጽ አላረግም ማለት ትችላለህ፡፡ ምክንያት እንኳን ሳታቀርብ አላረግም በቃ አላረግም ማለት ትችላለህ፡፡ ያለመታዘዝ ብዛት፣ አድርጉ የተባሉትን ነገር ቢያደርጉት እንኳን እየተቃወሙ፣ አላደርግም ባክህ፣ አልሄድም ባክህ፣ እዚህ ይሻለኛል ባክህ እየተባባሉ እንደሚያደርጉት አስተውያለሁ፡፡ መተዛዘዝን እንደ ውርደት ነው የሚቆጥሩት፡፡ በጣም ይገርሙኝ ነበር፡፡ ያ ተጋብቶብኝ ነው፡፡
2. ያን ሰሞን ፈይሳን ለማብሸቅ እየሞከርኩ ስለነበረና አናዶኝ ስለነበር ባለመታዘዝ ላበሽቀው መሞከሬ ነበር፡፡ ፈይሳን ቆዳውን የማይዘልቅ ንዴት አናድደዋለሁ ብዬ የህይወቴን የመጨረሻ አስከፊዋን ቀን(worst day of my life) አተረፍኩ፡፡

እናቴ ነበረች ከስራ ቶሎ የገባችው፡፡ አልቅሼ አልቅሼ ሲመጡ ማልቀሴን እንዳነይቁ እምባዬን ጠርጌ ፊቴን ታጥቤ ማልቀሴ እንዳይታወቅ ብዙ ከጣርኩ በኋላ ነበር የመጣችው፡፡ እንዴ አልሄድክም እንዴ አለችኝ፡፡ ሄጄ ነበር ፈርቼ ገባሁ አልኳት፡፡ ታድያ ፕሮግራም እንኳን አትሳተፍም? አለችኝ፡፡ ምንም አላልኳትም፡፡ አላመነችኝም፡፡ ኳየር ማቆሜ እርግጥ የሆነበት ቀን ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ ያን ቀን ምን ሆኜ ትቼ እንደገባሁ አባቴም እናቴም ብዙ ጊዜ ጠይቀውኛል፡፡ እኔ ግን እየዋሸኋቸው እየዋሸኋቸው እውነተኛውን ምክንያት አልነገርኳቸውም፡፡

ዲሻችንን እኔ ለማትሪክ እንዳጠና ዘግተውት ነበር፡፡ አንድ ቀን በጣም እየተጨናነቅኩ ነበርና ሄጄ ፊልም ከአቤ ቤት ተከራየሁ፡፡ አስቂኝ ፊልም ነበረ፡፡ ግን እንደድሮው በሳቅ አላንከተከተኝም፡፡ ፊልሙን እያየሁ ጭንቀቴን መርሳት አልቻልኩም፡፡ አንዴ ደግሞ ቀኑን ሙሉ በጣም የሚያስቁ የእንግሊዘኛ ቀልዶችን ሳነብ ዋልኩ፡፡ በጣም ነበር የሚያስቁት፡፡ በጣም ነበር ስስቅ የነበረው፡፡ ግን በጣም በሳቅኩ ቁጥር የሆነ ባዶነቴ የበለጠ እየተሰማኝ ነበር፡፡ እየሳቅኩ ብውልም አላስደሰተኝም፡፡

አንድ ቀን ሳት ብሎኝ ለአሚር ዝም ብሎ ያጨናንቀኛል፣ ልቤን ያመኛል አንገቴን ያቃጥለኛል አልኩት፡፡ ያኔ ዝም ብሎ ነው ያዳመጠኝ፡፡ በነጋታው ተቀምጠን ባለንበት ከመሬት ተነስቶ "አንተኮ ሞኝ ነህ" አለኝ፡፡ አናደደኝ፡፡ ለምንድነው ያልከው? አልኩት፡፡ እኔ ራሴን የመጨረሻ ጠቢብ፣ አራዳና በሳል አድርጌ ስለምቆጥር ከምን ተነስቶ እንዳለ ለማወቅ ጓጓሁ፡፡ለምን አልክ ስለው እንዲሁ ሳይህ ሞኝ ነህ አለኝ፡፡ ሳስበው ለካስ ምክንያቱ ትናንትናውን ይጨንቀኛል ምናምን ብዬ ማውራቴ ነው፡፡ ከዛ "እኔ ሞኝ ከሆንኩ አንተ ደግሞ ምን ልትባል ነው?" አልኩት፡፡ ተናደደ፡፡

ህዳር 17 9፡30

ውድ ማስታወሻዬ መቼም ማስታወሻ የምጽፈው ሲከፋኝ ብቻ ነው፡፡ በርግጥ የኳየር ጣጣዬን አቃልዬአለሁ፡፡ ያኔ ነው የወሰንኩት፡፡ እንደማቆም የደመደምኩት, ያለፈው ሀሙስ በነበረን የመጨረሻ ልምምድ፣ መዝሙራችንን ለማቅረብ ስንዘጋጅ አያንቱ ነንሴንስ(ብላ ስለሰደበችኝ ነበር፡፡ እኔን ለማናደድ ሲረባረቡብኝ ተናድጄ ወደ ቤት፡፡ ተመልሼ አልሄድኩም፡፡

የት/ቤት ህይወቴ ባለፉት ሁለት ቀናት መሻሻል አሳይቷል፡፡ ዛሬ ግን በጣም ደባሪ ቀን ነበረ፡፡ ለሚቀጥሉት ቀናቶቼ ደባሪነትም መሰረት ጥሎ ነው ያለፈው፡፡ እኔ ከማህበራዊ ህይወቴ ባለፈ ስለ ማትሪኬ ማሰብ ከብዶኛል፡፡ ጓደኛ ማጣት የመሞት ፍላጎቴን እያናረው ነው፡፡ አሚር ከሱ ሌላ አብሬው የምቀመጠው ሰው ስለሌለኝና እንደተገኛ ስለሆንኩበት በሚሰራብኝ ተንኮል ልቤን እያቆሰለ ነው፡፡ ብቸኝነቴ አንገፍግፎኛል፡፡ አብዲ ቦሪ ት/ቤትን የምለቅበት ቀን ንፍቅ አለኝ፡፡ ሰው ሰው ሲጎዳ ለመርዳት የሚነሳሳውን ያህል ሰው ብቻውን ሲሆን ደግሞ ተንኮል ለመስራት ፍላጎቱ ይንራል፡፡

ግን እኔ ማስታወሻ የምጽፈው እውነት እነዚህን መራራ ቀናት ማስታወስ ስለምፈልግ ነው እንዴ? አይደለም፡፡ ለወረቀትም ቢሆን ትንፍሽ ማለቴ የሆዴን ህመም ያስታግስልኝ ስለመሰለኝ ነው፡፡ ውርደቴን ያወርድልኝ እንደሆነ ብዬ ነው፡፡

ትኩረቴን ት/ቴ ላይ ለማድረግ እሞክራለሁ፡፡ ለራሴ ያለኝ ሀዘን ግን ከልብ የመነጨ ነው፡፡ ሰው ከፍ ይላል፡፡ዝቅም ይላል፡፡ ዝቅ ማለቴን መቀበል ስላልቻልኩ የሚታዘንልኝ ሰው ነኝ፡፡ እኔን ሊጎዱኝ የሚፈልጉ የክፍል ጓደኞቼ፣ የትምህርት ቤት ልጆች የውስጥ ህመሜን ቢረዱልኝ ኖሮ ከንፈራቸውን በመጠጡ፣ ላያሳዝኑኝ ምለው በተገዘቱ ነበር፡፡ ዳሩ ማን ማንን እየጎዳ እንደሆነ አያውቅም፡፡ እኔ ማንን ጎዳሁ? ጥሩ ለሆነልኝ መጥፎ ሆኜ አላውቅም፡፡ ጥሩ ሰው ጥሩ አያጋጥመውም እንደመሚሉት ሆኜ ነው እንዳልል ያን ያህል የተጋነነ መልካምነት የለኝም፡፡ ብቻ አሳዛኝ ሰው ነኝ፡፡ ይሄን ስጽፍ እምባ ከአይኖቼ እየፈሰሰ ነው፡፡ አዘንኩኝ፡፡ ለራሴ፡፡

ከፍ ከፍ አሁንም ከፍ
የወደቅክ እንደሆን አጥንትህ እንዳይርፍ አለ ገጣሚው፡፡

ታዲያ እኔ ምኔ ተረፈ? እንዲያ ተጋግዘው ከፍ እንዳላረጉኝ ተጋግዘው፣ ሳላስበው ለቀቁኝ፡፡ ታዲያ ምኔ ተረፈ? ተንፈጠፈጥኩኝ፡፡

እንደዛ እየተጨነቅኩ የማስበው ስለ ቸርች፣ ስለ ት/ቤት ነበረ፡፡ ለማጥናት ሌሊት ተነስቼ ምናምን ማጥናት ትቼ ሳስብ ይነጋል፡፡ የሆነ ጊዜ ደግሞ ፌስቡክ ላይ ፈረንጆችን አድ አድርጌ አናግራቸው ጀመርኩ፡፡ ፌስቡክ ላይ ፈረንጆች እንዴት እንደሆኑ ማወቅ ፈልጌ ነበር፡፡ እንደኛ በጣም ተቆነጃጅተው ፎቶ ለመልቀቅ ይፈልጋሉ ወይ? አጻጻፋቸው፣ ስታየላቸው፣ የሚለቋቸው ነገሮች ምናምን፡፡ ከስሜቴ፣ ሽሽት ነው፡፡ ከራስ ሽሽት፡፡ እንደዚያ እየተጨነቅኩ ማጥናት እንደማልችል ገብቶኛል፡፡ እንዴትም ብዬ ላልፍ እችል ይሆናል፡፡ ግን 4 አላመጣም፡፡ ቤት "እንደዚህ እየተጨነቅኩኝ ጥናት እየከበደኝ ነው፣ አጠናለሁ ብዬ ተቀምጬ የማስበው ስለቸርች ነው" ብዬአቸው ነው ኳየር ማቆም እንዳለብኝ የነገርኳቸው፡፡
አንዲት ወጣት ፈረንጅ የሀይ ስኩል ተማሪ አንዴ አንድ ፎቶ ፖስት አደረገች፡፡ የታካሚዎችን ሰማያዊ ሽርጥ ለብሳ ነገር የሆነች ጠባብ ክፍል ውስጥ፡፡ "ጭንቀቴ(depression) ልሸከመው ከምችለው በላይ ሲሆን ለወላጆቼ ነገርኳቸው፡፡ በጣም ያሰቃያል፡፡ በጣም ያምሃል ግን ምንህን እያመመህ እንደሆነ አታውቀውም፡፡ ሆስፒታል አደረሱኝና ሳይኮሎጂስቷ ቃለ መጠይቅ ስታረግልኝ ወደፊት ምን መሆን ነው የምትፈልጊው ብላ ስትጠይቀኝ "happy"(ደስተኛ) አልኳት" ትላለች፡፡

እሮብ ታህሳስ 1

ውድ ማስታወሻዬ

የማትሪክ ጊዜው እየተቃረበ ነው፡፡ ጊዜው እያነሰ ነው፡፡ ያነሰው ቀኑ ብቻ አይደለም፡፡ የማንበብ ፍላጎቴም እየተሸመደመደ ነው፡፡ በዚህ አመት መጨረሻ ስትሬት ኤ እንደማመጣ እርግጠኛ የነበርኩ ሰውዬ 4 ማምጣቴን ራሱ መጠራጠር ጀመርኩ፡፡ አሁን ደግሞ ማለፌንም ልጠራጠር ነው፡፡ የዛሬ አመት ለመያዝ 15 ደቂቃ የማይፈጅብኝ አንድ ሰአት እየወሰደብኝ ነው፡፡ ፊዚክስ ፈተና ሁለቴ 6 ከአስር አገኘሁ፡፡

በፊት ጎበዝ ነው ብሎ እኔ ላይ የሚያፈጠውና አይኑን ከኔ ላይ ካነሳ የሚምታታበት የፊዚክስ አስተማሪ አይን ላፈር ብሎኛል፡፡ ይሄ አመት አይን ላፈር ብሎኛል፡፡ እግዚአብሔር ካልረዳኝ መሳለቂያ መሆኔ ነው፡፡

ሰኞ መጋቢት 6፣ 2007 ዓ.ም.

ውድ ማስታወሻዬ

ጠፋሁ አይደል? ለመጨረሻ ጊዜ ከጻፍኩበት ቀን በጣም ለየት ያለ ሁኔታ ውስጥ ነው ያለሁት፡፡ ከክፍሌ ልጆች ጋር ያለኝ ግንኙነት በአዲስ መልኩ ታድሷል፡፡ በተለይ ከሴቶቹ ጋር፡፡ በቃ አሁን የሚያስጨንቀኝ የዚያኔው አይደለም፡፡ ወሬኛ ሆኛለሁ፡፡ በተለይ ከሴቶቹ ጋር ያመጣሁት ቅርርብ ለኔ ራሱ ማመን የሚያቅትና ከወንዶቹም ጋር ካለኝ የባሰ ሆኗል፡፡
ደስታዬን በቀናት ሳሰላው በጣም ጥቂት እንደሆነ ይሰማኛል፡፡ ጊዜውን ከፍ አድርጌ በሳምንት፣ በወር በአመት እያደረግኩ ሳስበው ደግሞ አዝኜ የማውቅ ራሱ አይመስለኝም፡፡
ደራሲያን እንደኔው የማዘን፣ በጥልቅ የማሰብ፣የብቸኝነት ስሜትና በብዙ ሰዎች መካከል መሆን ያለመፈለግ ፍላጎትና ባህርይ እንዳላቸው ከብዙ ታላላቅ ደራሲያን ግለ-ታሪኮችና ከተለያዩ ምንጮች ተገንዝቤአለሁ፡፡ ለምሳሌ ዘሲምፕሰንስ ላይ ባለቡና ቤቱ ደራሲዎች መሀል ይገባና “ደራሲዎች መሀል መሆን ደስ ይላል፣ “the happiest people on earth”(ከሁሉም ሰው በላይ ደስተኛ ሰዎች) ብሎ ይቀልዳል ደራሲያን ላይ፡፡ ቀልድ መሆኑ የሚገባው ደራሲያን በአለም ከማንም በላይ ሀዘንተኛ ሰዎች መሆናቸውን የሚያውቅ ሰው ነው፡፡
ሙያዬ ከፖለቲካ ወይም ከጥበብ በተለይ ከድርሰት ውጪ መሆን እንደሌለበት ከተረዳሁ ሰነባበትኩ፡፡ በእርግጠኝነት ስምንተኛ ክፍል እያለሁ ነው የወሰንኩት፡፡

ከታህሳስ 1 እስከ መጋቢት 6 ማለት ሶስት ድፍን ወሮች ልዩነት ነው፡፡ ማስታወሻ ሳልይዝ ይሄን ያህል መቆየቴ የሚያሳየው ከቸርች ውድቀት እያገገምኩ መሆኔን ነው፡፡ በጣም ተከፍቼ ካለሁ ቶሎ ቶሎ እጽፋለሁ፡፡ ስደሰት ደግሞ አልጽፍም፡፡ ለዚህ ማስታወሻዬ ምስክር ነች፡፡ ባለፉት ሶስት ወራት ውስጥ የነበሩትን ሁኔታዎች እንደከፉ ቀናቶቹ በጣም አብራርቼም ባይሆን አልፎ አልፎ የነገሮች ቅደም ተከተል ትዝ እንዲለኝ ብቻ አጫጭር ማስታወሻዎችን ብይዝ በተለይ ለዚህ መጽሐፍ ግብአትነት በጣም ጥሩ ይሆን ነበር፡፡ ውድ አንባቢ ሆይ ጊዜው ከአመት ተኩል ያህል በፊት ቢሆንም ለማስታወስ ጥረት አድርጌ የተሳኩልኝን ላስነብብህ እወድዳለሁ፡፡ ስለጽሁፉ ታማኒነት አትጨነቅ፡፡ ገጠመኞቹን አጣምሜ ወይም ጨማምሬባቸው እንዳይመስልህ፡፡ በርግጥ ላስታውሳቸው ስላልቻልኩት ምንም ማድረግ አልችልም፡፡ መጻፍ የነበረበት ታሪክ እንደረሳሁና እንዳጎደልኩ ይሰማኛል፡፡ ለማንኛውም ማስታወስ የቻልኩት እንዲህ ይነበባል፡-

ከሄለን ጋር ብንቀራረብ በጣም እንምንመቻችና ሙዳችን አብሮ እንደሚሄድ አስብ ነበር፡፡ ለጊዜው ግን እኔ በጭንቀት በጣም አስከፊ ጊዜ እያሳለፍኩ በነበርኩበት ሰአት ከሄለን በላይ ያወረደኝም ሆነ የናቀኝ ሰው አልነበረም፡፡ በጭንቀቴ ምክንያት ተናቅኩ፣ ስለተናቅኩኝ ደግሞ ሌላ ጭንቀት፡፡ ሄለን በአዕምሮዬ አርዕስተ ዜና ነበር የሆነችው፡፡ ቤት ገብቼ “ለምን እንደዚህ፣ ምክንያቱን፣ ድሮ እንደዚህ አልነበረችም፣ የኢዩኤል ጓደኛ የነበርኩ ጊዜ ልትቀርበኝ ትፈልግ ነበረ” ብዬ የሆነ እሷ በጣም ፊት የነሳችኝ ጊዜ ቤትም ት/ቤትም ሆኜ አስብ ነበር፡፡ አንድ ቀን ቤት እንዲህ ስለሷ በንዴት እያሰብኩኝ ልሰድባት ወሰንኩኝ፡፡ የሚንቅህን ሰው ለመስደብ በጣም ድፍረትን ይጠይቃል፡፡ በጣም ያስፈራል፡፡ ሄለን ደግሞ የክፍላችን ንግስት ነበረች፡፡ ት/ቤት ጠዋት እንደሄድን አሚሮን ሄለንን እሰድባታለሁ አልኩት፡፡ ለምን? አለኝ፡፡ “እንዲሁ” አልኩት፡፡ “በጣም ትንቀኛለች፣ አንድታቆም” ብዬ የሆዴን ልዘርግፍለት ታዲያ? ክፍል ቀየርን፡፡ እሷን የምቀርብበት አጋጣሚ እየፈለግኩ ነበር፡፡ ፈርቻለሁ፡፡ ወደኔና ወደ አሚር ዴስክ መጣች፡፡ ወረቀት ነገር ይዛ ነበር፣ አሳይመንት ነገር ለመስራት ነው መሰለኝ፡፡ ለአሚር እሷ እንድትሰማ አድርጌ “እቺ ሄለን ግን ሰው አይደለችም እሺ፣ ምን አይነት ሰው ነች?” አልኩት፡፡ “ተሳደብክኮ ናቲ” አለችኝ፡፡ እንዴ? እኔ ግን የተሳደብኩ አልመሰለኝም፡፡ “እኮ እኔም እሱ ነበርኮ እቅዴ” በሚል አስተያየት ዝም ብዬ አየኋት፡፡ አሚር “ያምሃል እንዴ? ምን ሆንክ?” ሲለኝ እኔ ሸክሙ እንደወረደለት ሰው ደስ አለኝ፡፡ ከዚያ በኋላ የሄለን አልሰማም ባይነት፣ ንቀት ጥሩ ለመሆን በመሞከር ተለወጠ፡፡ ያን ቀን ገብታ “ለምን አለኝ?” ብላ በጣም እንደተማረርኩባት ገባት መሰለኝ፡፡ ሄለን እያወቀች እንደዚያ እንደማታረግ ስለማምን ነው እየጎዳችኝ እንደሆነ ፍንጩን ላስይዛት የሞከርኩት፡፡ ተሳካልኝ፡፡ ከዚያ በኋላ እኔን ሲያይ ይቋጠር የነበረው ፊቷ ፈገግ ማለት ጀመረ፡፡ ያ ፈገግታዋ ግን ከልብ ሳይሆን እኔን “ከዚህ በኋላ አላገልልክም እሺ ናቲ” የሚል የሚያባብል መልዕክት ስላለው አልወደድኩትም፡፡ ከቀናት በኋላ እንግሊዘኛ ስንማር መማሪያ መጽሐፍ ያለበት ቦታ ሄዳችሁ ተቀመጡ ሲባል ስንት መጽሐፍ የነበረበት ቦታ እያለ መጥታ እኔ ጋር ተቀመጠች፡፡ ደስ አለኝ፡፡

ያን ቀን አወራን፡፡ ስለ ፌስቡክ፡፡ ፈረንጆችን አናግር እንደሆነ ጠየቀችኝ፡፡ እንደማናግርና አንዴ አንዷ እያወራን “idk” ብላ እንደላከችልኝ፣ ሌላ ፈረንጅ “what is idk?” ስለው I don’t know እንዳለኝና እንደማያውቅ እየነገረኝ እንደመሰለኝና idk፣ I don’t know አጥሮ ሲጻፍ መሆኑን

ከቆየ በኋላ ባጋጣሚ ከዚያ ፈረንጅ ጋር በፊት ያደረግነውን ቻት ሳይ እንደገባኝ ነገርኳት፡፡ ሳቀች፡፡ NVM ምን አጥሮ ሲጻፍ ነው ብዬ ጠየቅኳት፡፡ አሰበችና ኖቬምበር አለች፡፡ እኔም እንደዚያ ነበር ያሰብኩት፣ ኔቨር ማይንድ ነው አልኳት፡፡ ብቻ መማር ትተን አወራን ያን ቀን፡፡ የወሬ ድርቁ እያለፈ ነበር፡፡ ያን ቀን ከሰአት አንድ የክፍላችን ልጅ አያቷ ሞተው ለቅሶ ሄድን፡፡ ቤታቸው እሩቅ ሶር ሰፈር ነበር፡፡ ምን ነበረበት ቀርቼ ቤቴ በተኛሁ? ሄድን፡፡ እነኢዩኤል እነሄለን እየተቀላለዱ ይሄዳሉ፡፡ አሚር ከሜቲ ጋር ተያይዟል፡፡ ብቻዬን ሆንኩ፡፡ መንገዱ አያልቅም፡፡ ፊቴ፣ ልቤ አንገቴ ተቃጠለ፡፡ ያን ቀን ነበር ነብዩና እኔ መቀራረብ የጀመርነው፡፡ እራሱን ያካብድብኛል፡፡ እኔ “ይሄ ልጅ ብቻዬን ጥሎኝ እንዳይሄድ” ብዬ እየፈራሁ ብቻ ደረስን፡፡ ሶር ውሀው ቦታ ደርሰን እንመለስ ተባለና ሄድን፡፡ እኔና በረከት ስሊፐር አርገን ነበረና ውሀው ውስጥ በእግራችን ገብተን ድንጋይ ላይ ተቀመጥንና እግራችንን ተለቃለቅን፡፡ እኔ ፊቴ ቅጥል ብሎ ሊሞት ስለነበረ አንድም እንዲያቀዘቅዝልኝ፣ ሁለትም ተጨናንቄ እንዳለሁ እንዳይነቃ ፊቴን በውሀው ታጠብኩ፡፡ በረከት ተቀምጧል፡፡ ቅድስት መጣችና ለምንድነው ፊትህን በወንዝ ውሀ የምትታጠበው ይሄኔኮ ከላይ ተሸንቶበት ነው እየመጣ ያለው አለችኝ፡፡ “አይ ምንም ችግር የለውም ወንዙ በጣም ትልቅ ነው፣ ወደ ሁሉም ቦታ ስለሚሄድ ወደኔ የሚመጣው በጣም ትንሽ ነው የሚሆነው” አልኳት፡፡ እሷ በቤቷ እኔን ለማሸማቀቅ ብላ ነበር፡፡ ከቁብም አልቆጠርኳትም፡፡ አብሮኝ ሲተጣጠብ የነበረው በረከት እሷ እየሰማች “ተመቸኸኝ” አለኝ፡፡

ለቅሶ ቤቱን የሄድነው አምስት አምስት ብር አዋጥተን ነበር፡፡ ስንገባ ሴቶቹ ሻይ ማፍላትም ስለነበረባቸው ወደ ውስጥ ገቡ፡፡ እኛ ወንዶቹ ደግሞ ውጪ ተቀመጥን፡፡ እኔ ደብሮኝ ጭንቅ ብሎኛል፡፡ ያለፈው አመት የወሬ አቀጣጣይ ነበርኩኝ፡፡ ዛሬ ዝም ብዬ የሚያወሩትን አዳምጣለሁ፡፡ እያወሩ እያወሩ እያለ በረከት “ግን እኔ ብሞት ታለቅሳላችሁ?” አለ፡፡ ማንም ምንም አላለውም፡፡ ትክክል ነው፡፡ ትክክለኛ ጥያቄ አልነበረም፡፡ ምን ማለት ነበረብን? እኔ አለቅሳለሁ፣ እኔ አላለቅስም? ትንሽ ተጫውተን ወደ ቤት መልስ ላይ የክፍሌ ልጆች እነሄለን እየተቀላለዱ ነበር፡፡ እዚያ ለቅሶ ቤት ለሊሴ የምትባለው እኛው ጋር ግን ሌላ ክፍል የምትማር የኳየሬ ልጅ ወደ ቤት መልሱን ከኛ ጋር ነበር የገባችው፡፡ እንዴት እንደገረመችኝ? ከክፍሌ ልጆች ጋር እንዲሁ በቀላሉ ስትቀራረብ ታዘብኳት፡፡ በፊት ከማትቀራረባቸው ልጆች ጋር ነውኮ፡፡ ሰው ብዙም ስለማንቀራረብ፣ ስለማንተዋወቅ አይልም? ይባስ ብላ የኳየር ልጆች ሶር አገልግለው ሲመለሱ የሚጫወቱትን ጨዋታ እንጫወት ብላ እያሳየቻቸው ነበር፡፡ አቦሰም ነበር ጨዋታው፡፡ እኔ ባጃጄን ይዤ ወደ ቤቴ ገባሁ፡፡ ባለ ባጃጁ እስኪ ምን አገባው? ሱቅ የሆነ ነገር ልትገዛ ስትሄድ ለምን መግዛት አትተውም ወይም ለምን ገዛህ ብሎ የሚጠይቅ ገንዘብህን የማይፈልግ ባለ ሱቅ አለ? “ለምንድነው ከጓደኞችህ ተለይተህ የምትሄደው?” አለኝ፡፡ ስለምቸኩል ነው ብዬ ዋሸሁት፡፡ እውነተኛውን ምክንቴን ግን እግዚአብሔር፣ እኔና አንተ (የዚህ መጽሐፍ አንባቢ) እናውቀዋለን፡፡ ቤት ገብቼ ምናለበት ቀርቼ ቢሆን አልኩኝ፡፡

እረፍት ላይ ሻይ ቤት ከነኢዩኤልና ከነሄለን ጋር መሄድ ስመኘው የነበረ ነገር ነው፡፡ ከማን ጋር ልሂድ? ማን ይጥራኝ? ዝም ብዬ ለብቻዬ ሄጄ ከክፍሌ ልጆች ጋር እንደ አንድ ክፍል ተማሪ የማልተውን ከሆነ በጣም ይደብርና አውክዋርድ ይሆናል፡፡ እረፍት ላይ አንዴ ከኢዩኤልና ከበረከት ጋር ድንገት ቆመን እያለን ውሸቴን ቁርሴን አልበላሁም አልኳቸው፡፡ ኢዩኤል “ና ከኛ ጋር ብስኩት ብላ” አለኝ፡፡ የምስራች ነበር ለኔ፡፡ በረከት ብልጥ ነው፣ ኢዩኤል እኔን ሲጋብዘኝ ተናደደ፡፡ ያን ቀን ብስኩት ስጡኝ እያልኳቸው ሲሰጡኝ ነበር፡፡ ኢዩኤልም ናቲ ቁርሱን አልበላም አለልኝ፡፡ ሄለንን አይታኝ “ሲያሳዝን” አለችኝ፡፡ “ሰው ሲያዝንልኝ ደስ ይለኛል” ብያት ተነስቼ ለምን እንደዚያ አለችኝ? ለምን አልኳት? ብዬ ተናደድኩ፡፡ ከዚያ በኋላ ማንም ብስኩት ቤት ከመሄድ የሚያግደኝ አልነበረም፡፡ ዘና ብዬ ከአሚር ጋር እሄዳለሁ፣ ከነሄለን ጋር ብስኩት እየተከፋፈልን፣ እየተከፋፈልን እንበላለን፡፡ ሰው የሚበቃውን ያህል ገዝቶ አይከፋፈልም? እኛ አንድ ወይም ሁለት እንገዛና እሷን ብዙ ቦታ እየተሻማን እንከፋፈላለን፡፡ አሁንም ትንሽ እንገዛና እንሻማለን፡፡ መለማመን እኛ ብስኩት ቤት ምንም ክፋት የሌለው ነገር ነበረ፡፡ ከሁሉም ሻይ እየተቀባበልን የምንጠጣውን ሳስበው ደስ ይለኛል፡፡ የሚያቃጥል ትኩስ ሻይ እያቀዘቀዝን፣ እየተቃጠልን የምንጠጣው፣ ጥሩ የ10ኛ ክፍል ትዝታ ነው፡፡ መጨረሻ ላይ ብዙ ቀርቶ ሻይውን የያዘው ሰው አልሰጥም ብሎ ሊጨርሰው ሲል፣ ኧረ ይደብራል ልትጨርሰው ነው እንዴ፣ እዩት ይሄ ሻይውን ይዞ ጠፋ…

ነገሮች እየተሻሻሉ የመጡ ይመስላሉ ግን እኔ ደስተኛ ነበርኩ ማለት ይቸግረኛል፡፡ እረፍት ላይ መኖር የምፈልግበት ቦታ መሆን የቻልኩ ቢሆንም ግን ደስተኛ አልነበርኩም፡፡ በርግጥ ልቤን የሚያመኝ ላይመለስ የሄደ ይመስላል፡፡ በጣም ስትፈልገው፣ ቀንና ሌሊት ስታልመው የነበረውን ነገር ስታገኝ የሚሰማህ ስሜት ምን ነበረ ስሙ?

አንድ ፍሪ ፔሬድ ሻይ ቤት ሄደን፣ በዚያው እንጨት ላይ በዛ ብለን ተቀምጠናል፡፡ ስድስት ሰባት ሆነን፡፡ እነኢዩል ኳስ እንችላለን ብለው እያካበዱ ነበር፡፡ ለሄለን እኔ ስፖርት ቀለል ያሉትን ነው የምችለው፣ ቴኒስ፣ ዳርት ምናምን አልኳት፡፡
ሆራይዘን ስማር ዳርት ነበረ፡፡ እዚያ ነው የጨዋታውን ስም ራሱ ያወቅኩት፡፡ ስፖርት አስተማሪ አንድ ቀን በየተራ እንድንወረውር አድርጎን ያውቃል፡፡ “መጀመሪያ ስወረውር መሀል ላይ ተሰክቶ፣ ሁለተኛ ላይ የወረወርኩት የተሰካው ላይ ተሰክቶ ያውቃል፣ ገብቶሻል?” አልኳት፡፡ “እእእ?” አለችኝ በመገረም ስሜት፡፡ እኔ “ውሸታም” ትለኛለች ብዬ ስጠብቅ ነበር፡፡ ምንም ሳትለኝ ስትቀር ውሸቴን ነው ፊልም ላይ አይቼ ነው አልኳት፡፡ BRAVE ላይ ነበር ያየሁት፡፡ አንተ ውሸታም ብላ ያልኩትን ለሌላ ልጆች ነገረች፡፡ ያን ቀን ብዙ ነገር ነበር ያወራሁት ብቻ፡፡ ክፍል ስንቀይር ሜቲ፣ ናቲ ና እኔ ጋር ተቀመጥ ብላኝ የነሱ ቡድን ሄጄ እንድቀመጥ አደረገችኝ፡፡ ከነሄለን ኋላ ከኢዩኤልና ከሷ ጋር፡፡ ያን ቀን ክፍሉ በሙሉ ነበር ጉድ ያለው፡፡ እንዲህ እንዲህ እያለ ነገሮች እየተስተካከሉ የማይቻሉ የመሰሉኝ ቀላል እየሆኑ መጡ፡፡ ከልብህ ፈልገው እንጂ ምንም ነገር ጊዜው ቢረዝምም መገኘቱ አይቀርም የሚሉት አባባል እውነት ሳይሆን አይቀርም፡፡

ነብዩ እኔና አሚር ጋር መጥቶ መቀመጥ ጀመረ፡፡ ነብዩ በጣም የሚያስቀና ባህርይ ያለው ልጅ ነው፡፡ እንዲህ ቡድን ምናምን የሚባል ነገር አያውቅም፡፡ እነኢዩኤል ጋር ይሄዳል፣ ከነሄለን ጋር ይቀመጣል፣ እነኢየሩስ(የድሮ ጓደኛዬ) ጋርም ነው፡፡ ድንበር የሌለው ልጅ ነበር፡፡ ከኔና ከአሚር ጋር የሚያስቁ ነገሮችን እናወራ ነበር፡፡ ነብዩ አራዳ ነኝ ባይ ነገር ነው፡፡ ዘፈንና ዳንስ እችላለሁ ይላል፡፡ እንግሊዘኛ፣ ህንድኛ ዘፈን ይዘፍንልን ነበር፡፡ ቡንቱሬ ቹኩሀ ምን ማለት እንደሆነ ታውቃለህ? ይለኛል፡፡ ህንድኛ ነው? ስለው አዎ ምን ማለት ነው ይለኛል፡፡ እኔ ምን አቅልህለሁ? የኔ ፍቅር አፈቅረሻለሁ ማለት ነው ይልና በዜማ ይለዋል፡፡ ነገም ይመጣና እንዲህ ማለት ምንድነው? ይለኛል፡፡ አንተ ልጅ እኔ ህንድኛ አልችልም እለዋለሁ፡፡ የኔ ማር አፈቅርሻለሁ ማለት ነው ይላል፡፡ እንዲህ እያለ ያደርቀኛል እንግዲህ፡፡ ህንድ ፊልም ትርጉም በጌቾ ይመቸዋል መሰለኝ፡፡

ሻይ ቤት አሪፍ ጊዜ ነበር የምናሳልፈው፡፡ ብር ያለው ይገዛና ያከፋፍላል፡፡ ብር ሳይዙ ሄደው፣ ከልጆች ጋር መሻማትን፣ ቅፈላ ነበር የምንለው፡፡ “ምን ችግር አለው፣ ሄደን እንቀፍላለን”፡፡ ሻይ እየተቀባበልን መጠጣት ነው እንግዲህ፡፡ አንድ ቀን ልጆች ብስኩት እየበሉ እያየሁ ለሄለን “እኔ ግን ልጆች አንድ ሙሉ ብስኩት እንዴት እንደሚጨርሱ ይገርመኛል” ስላት እህ እንደማለት አለች፡፡ “እኔ ግን ሁለት እንኳን ችዬ አልጨርስም” ስላት አንተ ልጅ እንደው ብላ ከትከት አለች፡፡ ያን ያህል የሚያስቅ አልመሰለኝም ነበር እኔ፡፡

ብስኩት ቤት ሻይ እየጠጣን ውለን ክፍል አስተማሪ ከገባ ገብተን አስተማሪ የሚሳደበው እራሱ ያዝናና ነበር፡፡ ፊዚክስና ሂሳብ አስተማሪዎች በጣም ይወዱኝ ነበር፡፡ አንድ ቀን እኔ እረፍት ወጥቼ ሻይ ቤት ሄደን ፊዚክስ አስተማሪ ቀድሞን ገብቶ አላስገባ አለን፡፡ ከዚያ እኔ ክፍል ስላልነበርኩ ማስተማር አስጠልቶት ግቡም አላለንም አስር ደቂቃ ሳያስተምር ወጣ፡፡

አንድ ቀን አሚርን “የፈረንሳይ የህዳሴ ግድብ ስንት ሜጋ ዋት ነው የሚያመነጨው? ብዬ ጠየቅኩት፡፡ “አላውቅም 10ሺ ነው? ግምት ነው” አለኝ፡፡ በሳቅ ተንፈረፈርኩ፡፡ ሄለንን ጠርቼ “የፈረንሳይ የህዳሴ ግድብ…” እልኳት፡፡ “ፈረንሳይ የህዳሴ ግድብ አላት እንዴ?” አለችኝ፡፡ አሚር ያለኝን ነገርኳትና ሳቀች፡፡ ያን ቀን የመጨረሻ ፔሬድ ላይ ጂኦግራፊ አስተማሪ አልመጣ ስትል ወጥተን ሻይ ቤት ሄድን፡፡ እኛ ወጥተን ሳንቆይ አስተማሪዋ ክፍል ገባች፡፡ ሻይ ቤቱ ለክፍላችን ቅርብ ነው፡፡ እዛ እኔ፣ ሄለን፣ አሚር፣ ቅድስት፣ ሜቲ፣ ነብዩ፣ ኢዩኤል፣ በረከት፣ አብዱ ሆነን እያወራን ሄለን ናቲ በቃ ይሄን ግሩፕ ተቀላቀለ አለች፡፡ አዎ ተቀላቀልኩ፡፡ እያወራን እኔ አሚርን የህዳሴ ግድብ ብዬ የፎገርኩትን ነገረቻቸው፡፡ ኢዩኤል ፈረንሳይ የህዳሴ ግድብ ሊኖራት ይችላል ሲል እኔ በሳቅ ፍርስ፣ “እሱም ደገመው” ብዬ፡፡ ኢዩኤል ስለተጃጃለና ስለሳቅኩበት ተናደደ፡፡ እንዲህ ቆመን እያወራን ደራርቱ የምትባል የት/ቤታችን ባለስልጣን መጣች፡፡ ቶሎ ብለን ሻይ ቤቱ ጀርባ ተደበቅን፡፡ አሚር ሜቲን ይዞ ከሻይ ቤት ውሀ ይገችራታል፡፡ አሟት ይዣት ወጥቼ ነው ለማለት መሆኑኮ ነው፡፡ ደራርቱ መጣችና እነአሚርን ምን እየሰራችሁ ነው አለቻቸው፡፡ እንዲህ እንዲህ…፡፡ ኑ እናንተ ደግሞ ውጡ፡፡ የማትታዩ መሰላችሁ እንዴ? አለችን፡፡ ሻይ ቤቱ እንደ ኩሽና አልፎ አልፎ ጭቃ ካለው በስተቀር ሊፈርስ አንድ ሀሙስ የቀረው እንደ አጽም ፍልጥና ማዕገር ብቻ ሲሆን ሻይና ብስኩት የሚያስቀምጡበት ቦታ ተማሪ እጁን እንዳያስገባ በቆርቆሮ ተሸፍኖ ነበር፡፡ ቆርቆሮው ኋላ ነበር የተደበቅነውና ለካስ ቆርቆሮው ጉርድ ነበር፡፡ ጫማችን ይታይ ነበር፡፡ ወጣን ቢሮ አደረሰችን፡፡ ተቆጡን፣ አስፈረሙን፡፡ እኔ ምንም አልመሰለኝም፡፡ ያን ቀን ነበር ጨርሼ ደስ ያለኝና ፈታ ያልኩት፡፡ ከጓደኞቼ ጋር ስንፎርፍ፣ ስናወራ ተያዝን፡፡ ጭንቀቴ ለቅቆኝ ሲሄድ ይታወቀኝ ነበር፡፡ ለወራት እንዳልተነፍስ ተከልክዬ በመጨረሻ የተፈቀደልኝ ነበር የመሰለኝ፡፡ ከዚያን ቀን በፊት በተለይ ኳየር የነበርኩ ጊዜ ልቤን ሲያመኝ አንድ አራት ቦታ ሚቆራረጥ የእንጀራ ቁርጥ በግድ ነበር የምጨርሰው፡፡ ስትደነግጥ፣ የሆነ ነገር ሲጨንቅህ ምግብ አይዘጋህም? ያን ቀን ደስታ አጥንቶቼን ሲያጥለቀልቅ ይታወቀኛል፡፡ ልቤ ደም ሳይሆን ደስታ የሚረጭ መሰለኝ፡፡ ስትመኝ የነበረውን ነገር ስታገኝ እንዲሁ ነው፡፡ ያን ቀን ምሳዬን አንድ እንጀራ ነበር የበላሁት፡፡ በጣም ነበር አፒታይቴ የተከፈተው፡፡ 9ኛ ስማር ደግሞ እንዲያውም አንድ እንጀራ በልቼ አልጠግብም ነበር፡፡ ወትሮውን ሲጣፍጠኝ 3 ቁርጥ ካልጣፈጠኝ ወይም ሽሮ ሲሆን ደግሞ 2 ቁርጥ ነበር የምበላው፡፡ ያን ቀን ከሰአት እንደተጋደምኩ፣ ያ ሁሉ፣ ገብቶ መብሰልሰል፣ ስላሳለፍኩት ጊዜ እያሰብኩ መሰቃየት ቀርቶ፣ ጠዋት ከነሄለን ጋር ያሳለፍኩትን ጥሩ ጊዜ እያሰብኩ እንቅልፍ ይዞኝ ጥፍት፡፡ ሚጣ 10:30 መጥታ በር እስክታንኳኳ፡፡

ያን ቀን ማታ ከአራት ሰአት ጀምሬ ማጥናት ጀመርኩ፡፡ በዚያ ሰአት አጥንቼ አላውቅም፡፡ እንቅልፍ በጣም ያስቸግረኛል፡፡ ከዚያ ቀን በፊት ለማጥናት በጣም እየፈለግኩ እየጣርኩ እንቅልፍ ይዞኝ እልም፣ ስለ ት/ቤትና ስለቸርች ሳስብ ሁለት ሶስት ሰአት አቃጥላለሁ፡፡ወይም ፌስቡክ ገብቼ ከልጆች ጋር አወራለሁ፡፡ አንዳንድ ሌሊት ፌስቡክ የሚገቡ ልጆች ኧረ ናቲ አጥና ይሉኝ ነበር፡፡ አጠናሁ የምል ቀን ደግሞ አንድ ገጽ ላይ በጣም ረጅም ጊዜ ነበር የማሳልፈው፡፡ አሁን እያጠናሁ አስባለሁ፡፡ የማጠናው አይገባኝም፡፡ ግራ ተጋብቼ ነበር፡፡ ያን ቀን ግን እሱንም አልጋዬ ላይ፣ ሌላ ጊዜ ሳሎን ሶፋ ላይ ተቀምጬ ነው እንቅልፍ የሚይዘኝ፣ ያን ቀን ግን አልጋዬ ላይ ሆኜ እስከ ሌሊቱ 10 ሰአት አጠናሁ፡፡ የ9ኛ ክፍልን ኬሚስትሪ ኖት አያወጣሁ ከመጀመሪያው ምዕራፍ እስከ አራተኛው ድረስ አነበብኩ፡፡ 9ኛ ክፍል ላይ በትክክል ስለገባኝ ክለሳ ነበር፡፡ ትዝ አለኝ ቀኑ አርብ ነበር፡፡ እናቴ ሌሊት እንጀራ ልትጋግር ስትነሳ ተቀምጬ አግኝታኝ ኧረ አንተ ልጅ ተኛ ባትለኝ ለማንጋት ነበር ሀሳቤ፡፡

“ኡፍ ኡፍ፣ ተገላገሉኩ፣ ጭንቀቴ ተወኝ፡፡ ወደ ድሮዬ ተመለስኩ፡፡ አሁን በቃ እንደገና ነጻ ሰው ነኝ፡፡” ማለት ብችልና እውነት ቢሆን ደስ ባለኝ፡፡

ከዚያ ቀን በኋላ እንደዛ ቀን ደስ ባይለኝም ት/ቤት መሄድ አይቀፈኝም፡፡ መንገድ ላይ ስሄድ ብቸኝነት አይሰማኝም፡፡

የነኢዩኤል ውሀይት ሀውስ በት/ቤታችን ብቻ ሳይሆን በመቱ ታዋቂ እየሆነ ነበር፡፡ ከነሱ መሀል ሙባረክ(8ኛ ክፍል አብረን የተማርነው) ስሙን የፈጠረው ሲሆን የሚያድሩትም እነሱ ቤት ነበርና መሪያቸው ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ሙባረክ ከሁሉም ገንኖ የወጣና ታዋቂ የሆነ ልጅ ነበረ፡፡ ከኢዩኤል ጋር የተነካካ ሰው ሁሉ ለምን ከፍ ከፍ እንደሚል ይገርመኝ ነበር፡፡ አንድ ቀን እኔ ተደብሬ የነበረ ጊዜ ኢዩኤል አሳይመንት አስገብተሀል ወይ? አለኝ፡፡ አብሮኝ ቢሮ ለመሄድ ብሎ ነው፡፡ አዎ ግን ችግር የለውም ካንተ ጋር እመጣለሁ አልኩት፡፡ ሳይጋብዘኝ፣አብረን እንሂድ ሳይለኝ ካንተ ጋር እመጣለሁ በማለቴ ግር አለው፡፡ ከሱ ጋር ለመታየት ፈልጌ ነበር፡፡ እየሄድን አንድ ደምመላሽ የሚባል የHPE(ስፖርት) አስተማሪ ነበርና "ደምመላሽ የነዚህ ግሩፕ አልተቻለም ምናምን ሲል ነበር" አለኝ፡፡ ያውቃችኋል እንዴ? ስለው፣ "የማያውቀን ሰው አለ እንዴ?" አለኝ፡፡

ሻይ ቤት የድሮዎቹ ባለሻይ ቤቶች ተቀየሩና አዲስ መጡ፡፡ የማይጣፍጥ ብስኩት ሁለት ብር የበፊቱ አንዳንድ ብር ነበር፡፡ እንደ ድሮ ተማሪ ሄዶ መግዛት አቆመ፡፡ እኛም ተውን፡፡ እነኢዩኤል እነሄለንን ጣል ጣል አርገው ከሌላ ክፍል የግሩፓቸው አባላት ጋር መዋል ጀመሩ፡፡ ክፍል ውስጥ ወሬያቸው ሁሉ ስለግሩፓቸው ከሰው ጋር ስለመደባደብ ምናምን ሆነ፡፡ እኔም እንደገና በእረፍት ጊዜ ብቸኛ የምሆን መሰለኝ፡፡ ነብዩ መጣና ምርጥ አምባሻ ከግቢ ውጪ ይሸጣል አለኝ፡፡ "አትመጣም?" አግኝቼ? ከሱ ጋር እረፍት ላይ እየወጣን ሻይ በአምባሻ ሙብላት ጀመርን፡፡ ከሁሉም በላይ እኔ እረፍት ሰአት ላይ ብቸኛ መሆኔ ቀረ፡፡ ለአስራ አምስት ዲቂቃ ከዚያ የት/ቤት ግቢ መውጣት ደግሞ እውነተኛ እረፍት ይሰጣል፡፡ ነብዩኮ ደፋር ነው፡፡ ሄደን እየበላን እየበላን እነሄለንን ይዘን እንሂድ ማለት ጀመረ፡፡ ማለት ለሄለንና ለቅድስት ነገራቸው፡፡ እሺ አሉ፡፡ ከነሱ ጋር ደግሞ የጎረቤት ት/ቤት ሻይ ቤት ነበር፡፡ ቅዳሜ ቅዳሜ ሄጄ የማጠናበት ቄራ(አቡነ ጴጥሮስ አንደኛ ደረጃ)፡፡ በቃ ሻያችንን እየጠጣን እናወራለን፡፡ ከነሄለን ጋራ ብዙ የሚያሳፍሩ ነገሮችን እናወራ ነበር፡፡ ወይ ጉድ፡፡ ስናወራ ስንስቅ ነበር የምንውለው፡፡ ሄለን ደግሞ ለየት ያለች በቃ እንደሌሎቹ ሳትሆን የምለው ነገር የሚገባት የምትረዳኝ ልጅ ነበረች፡፡ በተራቸው እነኢዩኤል መቅናት ጀመሩ፡፡ እነሄለንን ነጠቅኳቸው፡፡ እኔ ብቻዬን ስሆን እራሱ ናቲ ና እዚህ ጋር ተቀመጥ፣ ና እንዲህ ሁን ትለኝ ነበር ሄለን፡፡ I know the killer እንጫወት ነበር፡፡ ብቻ ብዙ ብዙ፡፡ በጣም ደስተኛ መሆን ነበረብኝ፡፡ ከመቼውም ጊዜ በላይ፡፡ ግን እንደዛ አልነበረም ሲሰማኝ የነበረው፡፡ ከነሄለን ጋር ተቀምጬ ምናምን እንኳን አንዳንዴ ጭንቅ ጭንቅ ይለኝ ነበር፡፡ አንዳንዴ ደግሞ እንዲያውም ያገረሽብኝና አንገቴን ያቃጥለኝ ይጀምራል፡፡ ፊቴ ቀላ ቢል ደም የሚመስል ይመስለኛል፡፡ አንዴ ነብዩን ግንባሬን ያዝ አልኩት ትኩሳቴን እንዲለካ፡፡ ይዞ "ምንድነው?" አለኝ ደንግጦ፡፡ እያመመኝ ነው አልኩት፡፡ ለጉድ ያተኩሰኝ ነበር፡፡ ከነኢዩኤል ጋር እንደገና ለመጎዳኘት እፈልግ ስለነበረ ይሆናል ጭንቀቴ አልተው ያለኝ፡፡ ይሄ ውሀይት ሀውስ የሚሉት ነገር ያናድደኝ ነበር፡፡ እኔ የሌለሁበት ውሀይት ሀውስ!

ሰኞ ሚያዝያ 9፣ 2007 ዓ.ም

ውድ ማስታወሻዬ

ቀን ይመጣል ቀን ይሄዳል፡፡ ማታም ይመጣል፣ ደግሞም ይሄዳል፡፡ በአንዳንድ ቀናት በጣም እንደሰታለን፣ በአንዳንድ ቀናት ደግሞ በጣም እናዝናለን፡፡ በእነዚህ ሁለት አመታት ሁለት ትልልቅ ነገሮችን አሳልፈአለሁ፡፡የመጀመሪያው ያለፈው አመት ደስታ ነው፡፡ ሁለተኛው የዚህኛው አመት ሀዘን ነው፡፡ ማዘን ማዘን ማዘን ሆነ የኔኮ፡፡ አላሳዝንም? የምጽፈው ሁሉ ጠፋብኝ፡፡ ወይ ከት/ቴ አልሆንኩ፣ ወይ ከሶሻል ላይፌ አልሆንኩ፡፡ ሰው ሁሉ የሚያከብረው የሚወደው አይነት ሰው መሆን ነበር የምፈልገው፡፡ አሁንም ቢሆን፡፡ ዛሬ የነበረችኝን እንጥፍጣፊ ክብር አስረከቤ ገባሁ፡፡ የክላስ ልጆች በርዝ ዴይ ፓርቲ አዘጋጁ፡፡ ሄድን፡፡ ቆይ እኔን በዚህ ሰአት የሚያከብረኝ ሰው አለን? ማነው? የለም እንዳልል ያስፈራኛል፡፡ አለ እንዳልል ደግሞ አልመጣልህ አለኝ፡፡ ይሄ የት/ት አመት ሲያልቅ የማገግም ይመስለኛል፡፡ እስከዚያው ግን ጊዜው አዘገመብኝ፡፡ አላሳዝንም? ዛሬ የነበረችኝን እንጥፍጣፊ ቦታ፣ በትንሽ ትታይ የነበረችውን ክብሬን ውሃ ቸልሼባት ገባሁ፡፡ ይሄ ዛሬ ነው፡፡ ነገ ደግሞ የንቀት አይኖች፣ ምጸቶች ይጎርፉልኛል፡፡ ያኔ በጦር እንደተወጋሁ ሁሉ በአይኔ ሳይሆን በልቤ፣ በድምፅ ሳይሆን በሀሳቤ እህህ እያልኩ አለቅሳለሁ፡፡ ከት/ቤት ገብቼ ሚስቱ እንደሞተችበት ሰው በሬን ዘግቼ እነባለሁ፡፡

ሰው ዱሪዬ ሲሆን ጓደኛ ሲያበዛ፣ ከት/ቱ ይዘናጋ የለ? ጓደኛ የማያበዛ፣ የማይዞር ደግሞ አርፎ ያጠናል ይባል የለ? እኔኮ ከሁለቱም የለሁም፡፡ እኔኮ የዛሬን አያርገውና ት/ቤት ውዬ ስገባ የማጠናት አጠናን አጠናን አልነበረችም፡፡ ብዙ ጓደኛ፣ የሚሞች ማህበራዊ ህይወት ቢኖረኝ ኖሮ ለማትሪክ ጥናት ጨርሼ ነበር ይኼኔ፡፡ ማትሪክ ያለፈው አመት ቢሆን ኖሮ ስትሬት ኤ እንደማመጣ እርግጠኛ ነበርኩ፡፡ አሁን ግን 4 ማምጣቴን ራሱ መጠራጠር ጀምሬያለሁ፡፡ እንዴት ላጥና? ከሰው ደንታ ያልነበረኝ እነኛ የ5ኛ፣ 4ኛ ክፍል ትዝታዎቼ ውልብ ይሉብኛል፡፡ ምነው አሁንም እንደዚያኔው በሆንኩ? ያኔኮ ጓደኛዬ ት/ቴ ብቻ ነበረ፡፡ ቢሆንም ሁሉም ያልፋል፡፡ ሲያልፍም እንዳያልፉት የለም አሀ ያ ሁሉ ታለፈ ብዬ እዘፍን ይሆናል፡፡ መከራው ቀጣይነት ከሌለው ማለት ነው፡፡ አንዳንዴ ልዩ ስለሆንኩ ነው ብዬ አስባለሁ፡፡ ስፔሻል ስለሆንኩ ይሄ ሁሉ ጓደኞቼ፣ ወላጆቼ፣ ማንም የማያውቀው ለማስረዳት የሚከብድ ስሜት የሚሰማኝ ብዬ ለማሰብ እቃጣለሁ፡፡ ግን አያጽናናኝም፡፡ እውነት እንኳ ቢሆን ምንም ስሜቴ ሊያንሰራራልኝ አልቻለም፡፡ ግን አላሳዝንም?

ራሳቸውን የሚገሉ ሰዎች ያስገርሙኝ ነበር፡፡ አሁን ግን አድናቂያቸው ሆኜ አርፈያለሁ፡፡ ከአንድ ወደ ሌላ ቦታ ስንሄድ አስደሳች፣ አሳዛኝ፣ ብዙ ነገሮች ይገጥሙናል፡፡የተለያዩ ነገሮች የተለያየ ስሜት ይፈጥሩብናል፡፡ በመንገድ ላይ መድከምም አለ፡፡ በመጨረሻ መዳረሻችን ጋር እንደርሳለን፡፡ ታዲያ በመንገድ ላይ የተለያዩ ስሜቶችን የሚፈጥሩብንን ሁኔታዎችና አጋጣኒዎች ዘልለን የምናርፍበት መዳረሻ ቦታችን ላይ ብንደርስ ምን አለበት? ብዙ ሳንሰቃይ የምንደርስበት ብንደርስ ምን አለበት? ብዙ ሳንሰቃይ ብንሞት ምናለበት? እኔ ዝም ብዬ ጓደኞቼን በምን እንደሚሞቱ አስገምታቸው ነበር፡፡ አቡሽ፡ እንዲሁ አርጅቼ፣ በእርጅና ምክንያት ነው ምሞተው" አለ፡፡ እኔን ደግሞ "አንተን ግፊት ነው የሚገልህ፣ በትንሽ ትልቁ ትናደዳለህ፣ ሰው ለምን ሰላም ሳይለኝ አለፈ? ብለህ ትናደዳለህ" አለኝ፡፡ ለምን ነገርኩት? እኔ ግን የምሞተው እራስን በማጥፋት ወንጀል ይመስለኛል፡፡ተስፋዬ የለም፡፡ ጠፍቷል፡፡

በዚህ ጊዜ በጣም ሶሾሎጂስት ነበር የሆንኩት፡፡ ለራሴ፡፡ ሰዎች ስለኔ ስለሚያስቡት ነገር ማወቅ መፈለግ፣ ምን ያህል እንደሚያከብሩኝ መገምገም፣ ብቻ በጣም እመራመር ነበረ፡፡ በጓደኞቼ ፊት ዋጋ እንዲኖረኝ ምን ማድረግ እንዳለብኝ ጠንቅቄ አውቀው ነበር፡፡
በፋሲካ በአል ማግስት ለነሄለን እንዲህ አልኳቸው፣ "ከሰፈር ልጆች ጋር ወጥተን ስንዞር ነበር፣ ፑል ምናምን ተጫወትን"፡፡ ውሸቴን ነበር፡፡ ብዙ ጓደኞች እንዳለኝ ዘና ብዬ በአሉን እንዳሳለፍኩ ነግሬ የሆነ ነገር አዕምሮአቸው ውስጥ ለማስቀመጥ ነበር፡፡ እንጂ ቤት ውስጥ ተጎልቼ ፊልምና የበአል ፕሮግራሞችን እያየሁ ነበር በአሉን ያሳለፍኩት፡፡ ውሸታም!

አዎ የልደት ፓርቲ አዘጋጁ፡፡ የሜቲና የቅድስትን ስዊት ሲክስቲን ነበር ያከበርነው፡፡ ከአንድ ጆሳ የሚባል የሰፈሬ ልጅ ጋር ነበር የሄድነው፡፡ ድብር ነበር ያለኝ፡፡ ኬክ ነበረ፡፡ ኬክ ተቀባባን፣ ለስላሳ ተረጫጨን፡፡ ወይን ነበረ፡፡ ከዚያ ሙዚቃ፡፡ 9 ሰአት ነበር መሰለኝ የሄድነው፡፡ ጨፈሩ፡፡ መጨፈር ሲጀምሩ እኔና ጆሳ ውልቅ አልን፡፡ በቃ ድብር ነበር ያለኝ፡፡ እና ልጆች ሲያዩኝ ነበር፡፡ መለኛዋ ሄለን እመጣለሁ ብላ ቀረች፡፡ እኔ እሷና ጆሳ ጴንጤ ነበርን፡፡ በርግጥ ጴንጤ ሆነው የጨፈሩም ነበሩ፡፡ የማትጨፍር ከሆነ ሲጀመር ለምን ትሄዳለህ? እነሱ አምሽተው ነበር የገቡት፡፡ ጠዋት ስሄድ ለምን ገባህ? አመለጠህ ወደ አንድ ሰአት ነው ወደ ቤት የገባነው፣ እንቅልፍ አልይዝ አለኝ፣ እነእገሌ እንዲህ ሆኑ እገሌ ዳንስ ይችላል አሉኝ አሚርና ነብዩ፡፡ ሜቲና አብዱ ደግሞ ጆሳ ባይኖር ናቲ ይጨፍር ነበር አሉ፡፡ እ ጨፍር ነበር ግን? ይሄን ጥያቄ የጆሳ አለመምጣት ብቻ ነው ሊመልስ ይችል የነበረው፡፡ ሌላ እኔ ማስታወሻዬ ላይ እንዳካበድኩት አይነት ንቀት ምናምን አልነበረም፡፡ ቪዲዮ ተቀርጾ ተበተነ፡፡ የፒሪፒ ተማሪዎች፣ ኤሌሜንተሪዎች፣ ያላየ አልነበረም፡፡ የኛ ባች ሙደኛ ልጆች ያሉበት መሆኑን አስመሰከረ፡፡ እንዲህ ከፍ ባለው ባች የተካበደ ባች አልነበረም፡፡

10ኛ ክፍል ሞትን መፍራት ያቆኩበት ጊዜ ነው፡፡ ተስፋዬ ሲጨልም ይታየኛል፡፡ በፊት በፊት ዶክተር ሆኜ፣ የኢትዮጵያ ፊልም ላይ የሚታዩትን ከምትመስል ቤት ውስጥ መኪናዬን እያወጣሁ፣ የቤቴ ዘበኛ በሩን ሲከፍትልኝ ነበር የሚታየኝ፡፡ ሁሌ የሚያወዛግበኝ ደግሞ ቤት እሰራለሁ ወይስ እገዛለሁ? መስራት ገና መጉላላት፣ ድካም አለው፡፡ ግዢ ግን መግዛት ብቻ ነው፡፡ ሳሰራ በተመቸኝ መንገድ ነው፣ ግዢ ግን እንደዚያ ላይሆን ይችላል፡፡ ከዚያ ዩኒቨርሲቲ ገብቼ ስለሚኖረኝ ህይወት ደግሞ እያሰብኩ እጓጓና እደሰት ነበር፡፡ አስረኛ ክፍል ስገባ ምንም ነገር ስሜት አልሰጥህ ይለኝ ጀመር፡፡ የምፈልገው ነገር ቢኖር ከዚህ አስሰቃቂ ገዳይ ጭንቀት ለመገላገል ብቻ ነበር፡፡ ብቸኝነት በጣም ይሰማኝ ነበር፡፡ ያን ማጥፋት የምችለው ደግሞ ከሰው ጋር ያለኝን ግንኙነት በማሻሻል ብቻ ነበር፡፡ ስለማህበራዊ ህይወቴና ስለ ሰዎችን ጸባይ በጣም እያሰብኩና እየተረዳሁ ስመጣ ደግሞ እየባሰብኝ እየከበደኝ መጣ፡፡ ራሴን ጠላሁ፡፡ ት/ቤት ከኔ በላይ ስንት ሊያሳስባቸው የሚገባ ነገር እያለ ተረጋግተው የሚቀመጡትን ከሰው ደንታ የሌላቸውን የገጠር ልጆች እያየሁ ምነው እነሱን በሆንኩ ማለት ጀመርኩ፡፡ አንድ ቀን የኛ ክፍል አንድ የገጠር ልጅ ነበርና እንግሊዘኛ እየተማርን አስተማሪው መጽሐፍ ያለበት ፈልጋችሁ ተቀመጡ፣ መጽሐፍ የሌለው ተማሪ እንዳላይ አለ፡፡ አንድ ዴስክ ሶስት ተማሪ ማስቀመጥ ይችላል፣ የሆነች ልጅና ሜቲ መጽሐፍ ነበራቸው፣ አንድ ሌላ ሰው ማስቀመጥ ይችሉ ነበር፡፡ ይሄ የገጠር ልጅ የት ልቀመጥ? በቃ ቦታ የለም ልውጣ ሲል እነሜቲ ጋር ቦታ እንዳለ አይቼ ሂድ እዛ ተቀመጥ አልኩት፡፡ ፈራ፡፡ አጠገቧ እንድቀመጥ አትፈልግም ብሎ ነው የደበረው፡፡ ትክክል ነው፣ አጠገቧ እንዲቀመጥ ልትፈልግም አትችልም፡፡ እየደበረው ሄዶ ተቀመጠ፡፡ ተጠጋችለት፡፡ ማለት የፈለግኩት ነገር እንደዚህ ልጅ የሚገለሉ፣ የከተማ ልጆች አብረዋቸው ሊቀመጡ የማይፈልጓቸውና ይሄንን ጠንቅቀው የሚያውቁ ብዙ የገጠር ልጆች አሉ፡፡ እኔ ግን ማንም ያገለለኝ የለም፡፡ ግን የምጨነቀው ተናቅኩ፣ ተገለልኩ የምለው እኔ ነኝ፡፡ እኔ ሰው የማያገለኝ እነሱ ሚያገላቸው፣ እኔ ጭንቀታም፣ እነሱ የማይጨነቁ ፈታ ያሉ እንዲያውም ይሄ ልጅ ምን ሆኖ ነው የሚጨነቀው የሚሉ ከሆነ፣ እነሱ ውስጣዊ ሰላም ካላቸው የሚሰማህ ስሜት ነውኮ ዋናው፣ ለምን እነሱን መሆን አልመኝም? ለምን ውስጣዊ ሰላምን አልመኝም?

ቤት ለእናቴ እኔ ሰው ራሱን አጠፋ ሲባል ድሮ ይገርመኝ ነበር፡፡ አሁን ግን እራሱን የሚያጠፋን ሰው አደንቀዋለሁ አልኳት፡፡ ተቆጣችኝ፡፡ ይባስ ብዬ ብሞት ደስ እንደሚለኝ ነገርኳት፡፡ በዚህ ውስጥ ቸርች ማቋረጤ አስተዋጽኦ አለው፡፡ ሳቆም "the best, at the same time the worst decision of my entire life" ብዬ ነበር፡፡ ስሄድ የምሰቃይ፣ ሳቆም የምገላገል፣ ስሄድ ሰው ጎበዝ የሚለኝ፣ ሳቆም ደግሞ ተበላሸ፣ ተሸነፈ የሚለኝ ከሆነ መጥፎም ጥሩም ውሳኔ አይደለም ታዲያ? ኳየር ማቆም በተለይ ከኔ፣ ከኛ ቤት ልጅ የሚጠበቅ ነገር አልነበረም፡፡ ለዚህ ነው፡፡ ሰው ለምን አቆምክ ሲለኝ፣ የኳየር ልጆች አልተመቹኝም ስለው "አንተ ለምን ሰውን ታያለህ፣ ሰውን ለማገልገል ነው እንዴ የምትሄደው? ዝም ብለህ አገልግለህ መግባት አትችልም?" መባል ከሁሉም በላይ አስቸጋሪው ነገር ነበር፡፡ ለመታገስ ሞክሬ ነበርኮ፡፡ ታገስኩ

ታገስኩ፣ እየባሰብኝ ሲሄድ ገሀነም ከዚህ በላይ ያስጨንቃል ማለት ነው? ያስባለኝን ጭንቀት ለመገላገል ወሰንኩ፡፡ ቢቀልልኝም ግን ለዘለአለም ይሄን ጭንቀት የምገላገለው አልመሰለኝም፡፡ ተሸሎኝ ራሱ ይኸው ልደት ስሄድ አልተነሳብኝም? አንዳንዴም ከመሬት ተነስቶ ይነሳብኛል፡፡

ማትሪክ እየደረሰ ሰሞን የስንታየሁ(የድሮ ጎረቤታችን) ሰርግ ነበረ፡፡ መሄድ አልፈለግኩም፡፡ ግን እንዴት እቀራለሁ? ልሂድ አልሂድ እያልኩኝ ወደ አስራ አንድ ሰአት ከእናቴና ከሚጣ ጋር ሄድኩኝ፡፡ ሰርጉ ዛሬ ከሆነ ትናንትናውን የስንቱ ወንድም ዳግም ከእኛ ቤት እቃ ለመውሰድ መጥቶ "ምነው ጠፋህ" አለኝ፡፡ አዎ ጠፍቻለሁ፡፡ ሄጄ ስራ መርዳት አልነበረብኝም? ፈራሁ፣ ደበረኝ፡፡ ደግሞ ቢጨኝቀኝስ እዚያ ሄጄ? ቢያንስ የሰርጉ ቀን እንኳን ጠዋት ነበር መሄድ የነበረብኝ፡፡ እኛ ስንሄድ ሽርሽር ተሂዶ ትላልቅ ሰዎች ብቻ ነበሩ የነበሩት፡፡ የምገባበት ጉድጓድ ነበር ያጣሁት፡፡ መሄዴ ቆጨኝ፡፡ መሄድ ነበረብኝ፡፡ መሄድ ያስጠላኛል፣ ከቀረሁ መሄድ ነበረብኝ፣ ምን አይነት ሰው ነኝ እያልኩ ጭንቀት፡፡ ከሄድኩ ይደብረኝና ጭንቀት፡፡
ትንሽ ቆይቶ አሁንም ደግሞ ጎረቤት እነእቴ ሽታዬ ቤት ሰርግ ነበረ፡፡ አልረዳሁም ከከነጭራሹ ይሄን ደግሞ ዝርም አላልኩበትም፡፡ አላሳዝንም?

- ት/ት አለቀ፡፡ በመጨረሻ ኢዩኤል፣ ሄለን ማለት አከተመ፡፡ አዎ ከሄለን ጋር ጥሩ ጊዜ ብናሳልፍም ከፍሉ አስጠልቶኝ ነበር፡፡ የት/ቤት የመጨረሻ ቀን፣ በዚያ አመት ስትናፍቀኝ የነበረች አንድ ነገር ነበረች፡፡

- አንድ ቀን በኢቢሲ እሁድ ከሰአት ከእሁድ መዝናኛ በኋላ 11 ላይ የአለም ሙዚቃ የሚባል ፕሮግራም ጀመሩና የማይክል ጃክሰንን ድሮ አነሰይፉ ዘፈን በሚያቀርቡበት ጊዜ በህጻንነቴ የማየውን የማይክል ጃክሰን what about sun rise, what about rain, ahahahahahahahaha ahahahahhahaha ዝሆኖች፣ ሰዎች ሞተው፣ መሬት ምድረበዳ ሆና ዛፎች ወዳድቀው፣ ከዚያ ወደኋላ ሲመለሱ አይቼ ተመቸኝ፡፡ what about sun what about sun rise የምትለዋን ሰምቼያለሁና እንግሊዘኛ ዘፈን ጆሮ ከሰጡት መስማቱ ብዙም አይከብድም አልኩኝ፡፡ ያው አማርኛም ቢሆን የሚሉትን አንዳንዴ ለማወቅ ይቸግራል ግን ቢያንስ አዝማቿን መያዝ አይከብድም፡፡ ቪኦኤ ላይ ከሰአት ከሰአት የሚመጡትን ዘፈኖች መስማት ጀመርኩ፡፡ በስልክ ደግሞ አማርኛ አወረድኩኝ፡፡ ባላገሩ ላይ ተወዳዳሪዎች የሚዘፍኗቸው የድሮ ዘፈኖች ይመቹኝ ነበርና ላውርዳቸው ብዬ ማውረድ ጀመርኩ፡፡ ትዝ ይለኛል ከሁሉም አስቀድሜ የኔ አበባ በ... አድርገህ ግባ አዲስ አበባ...ግባ ሻሸመኔ... የሚውን ነበር ያወረድኩት፡፡

- ከዚያ አሊ፣ የረሳሁት ጓደኛዬ፣ ቤት መምጣት ጀመረ፡፡ ስለክፍላችን፣ ስለ ስንት አመቱን ሙሉ ሳስባቸው ስለነበሩ ነገሮች ነገርኩት፡፡ ስለኳየር ግን መጀመሪያ አልነገርኩትም፡፡ ስነግረው ግን፣ አሰለቸሁት፡፡ ከአሊ ጋር ባንዴው እንደገና ጓደኛ ሆንን፡፡ "አቤት 10ኛ ክፍልማ በቸርች ብሶትህ ጆሮዬን አደማኸውኮ" ይላል 12ኛ ክፍል ደርሰን፡፡ እሱ ድሮም ዘፈን ይወድ ነበር፣ ባሰበት፡፡ መጀመሪያ የጀስቲን ቢበርን ቤቢና ላቭ ሚን ነበር ያሳለፈልኝ፡፡ ለማንም እንዳትናገር ብዬው ነበር፡፡ እሱ ጴንጤ ቢሆንም ሰው ምን ያመጣል ይል ነበር፡፡ ከሱ ጋር ፑል ቤት፣ እንሄዳለን፡፡ከዚያ ነፍ ዘፈን አሳለፍኩኝ፡፡ ከKATY PERRY እስከ JUSTIN BIEBER፣ ከTAYLOR SWIFT እስከ BRUNO MARS፣ ከMAROON FIVE እስከ ONE DIRECTION፣ ከBEYONCE እስከRIHANNA፣ ከCHRIS BROWN እስከSELENA GOMEZ፣ ከWIZ KHALIFA እስከ EMINEM፣ ከJENNIFER LOPEZ እስከ CARLY RAE JEPSEN፣ ከJASON DERULO እስከ PITBULL፣ ከARIANA GRANDE እስከ COLDPLAY፣ ከWILL PHERREL እስከ ENRIQUE IGLESIAS፣ ከDRAKE እስከ KANYE WEST፣ ከNICKI MINAJ እስከ LADY GAGA፣ ከSHAKIRA እስከ RITA ORA፣ ከSIA እስከ ADELE .... የእንግሊዘኛ ዘፈን ሱሰኛ ሆኜ እርፍ አልኩኝ፡፡

ማትሪክ ተፈተንን፡፡ ዋሸሁ ማለት ነው፡፡ ውሸቴን እያጠናሁ አይደለሁም ብዬ ነው ማለት ነው፡፡ ወይም እያጠናሁ፣ እያጠናሁ ያልነበርኩ መስሎኛል ማለት ነው፡፡ አባቴ ሌሊት ሳንቀላፋ እያየኝ አንተ ልጅ ሁለት ወር ነውኮ የቀረህ፣ ብዙ ጊዜ ያለህ መሰለህ እንዴ? ብሎ ተኝቼ ሳስቸግር ከኔ ጋር እንዳጠና ሌሊት አብሮኝ ተቀምጦ፣ እሱ እያየኝ አልተኛሁም ማለት ነው፡፡ ሎጂኩ እኔንም አልገባኝም፣ ግን ማትሪክ በጣም ነበር የቀለለኝ፡፡ 9ኛ ክፍል በትክክል ወጥሬ ስለ ሰራሁ ሊሆን ይችላል፡፡ 10ኛ ክፍል አንደኛ ሴሚስቴር 2ኛ ነበር የወጣሁት፡፡ ማንም ጥሩ ውጤት ያመጣል ብሎ የገመተኝ አልነበረም፡፡ ሁሉም ተስፋ ቆርጦብኛል፡፡ የሚደሰተውም ተደስቷል፡፡ ውጤት ከተበላሸብኝ ኳየር ስላቆመ ነው ይባልልኛል፡፡ ያ ልሸከመው የማልችለው ስድብ ሊሆንብኝ ማትሪኬን እየተጠባበቅኩ ነበር፡፡

ያን ክረምት የኦሊን አዕምሮ አበላሸሁ፡፡ ዝነኛ ስለመሆን አወራሁለት፣ ት/ቤታችን ማን ፌመስ እንደሆነ እንዴት እንደሆነ ስለሁሉም ነገር፡፡ ዝና ብቻ ጭንቀቴን የሚያስቆምልኝ መሰለኝ፡፡ ከኦሊ ጋር ትምህርት ቤት ውስጥ እንዴት ዝነኛ መሆን እንደሚቻል ለማወቅ አብረን ጉግል ማድረጋችን ትዝ ይለኛል፡፡ ያን ክረምት አንድ ቀን ቤታቸው ሄጄ ቲቪያቸው አንድ አስቂኝ ፊልም ላይ ነበረ፡፡ የሮን በርጋንዲን(ዊል ፌረል) አንከርማን የሚለውን የዜና አንባቢውን ሰውዬ ፊልም አይተሃል? እሱን እያየሁ ስስቅ ኦሊ እንዴ የሚሉትን ነገር ትሰማለህ እንዴ? እኔኮ ዝም ብዬ ነው የማየው ደግሞ አክሽን ነው የማየው አለኝ፡፡ ስማ በጣም ደስ ይላል፣ ያስቃል አልኩት፡፡ ከዚያ በኋላ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ነበር ኦሊ እንግሊዘኛው የተሻሻለው፡፡

ስለዝና ሳነሳ ሰፈር ከኛ ቤት ቀጥሎ ያለው ቤት ቀጥሎ ያለው ቤት ያሉ እትዬ መሰረት የሚባሉ ሴትዮ አይተውኝ አንድ ቀን ጎረቤታችን በቀሉን "የማን ልጅ ነው?" ብለው ይጠይቋታልና የት ነው ይሄ? ነበር ያልኩት፡፡ አሜሪካ? አንድ ሌላ የሰፈር ሰውዬም እንዲሁ ይሄ ልጅ የማነው? አይቼው አላውቅም አለ፡፡

ወንድሜ የክረምት እረፍት መጣ፡፡ አንድ ቀን እንግሊዘኛ ዘፈንኮ ግን ደስ ይላል አለኝ፡፡ እኔ ምንም አላልኩትም፡፡ በእንግሊዘኛ ዘፈን ፍቅር እንደሰከርኩኝ እሱ ይቅርና እኔን የማያውቀኝ ሰው እንኳን ማወቅ የለበትም፡፡ ሌላ ጊዜ ደግሞ "I think I wanna marry you" ሲል ሰማሁት፡፡ እኔ የምወደው የብሩኖ ማርስ ዘፈን ነበር፡፡ እሱ ሲለው እሱም የሚሰማ መስሎኝ ደስ አለኝና ዘፈን ትሰማለህ ማለት ነው? አልኩት እንደሚታዘብ ሰው፡፡ የጋብቻ ፕሮፖዛል ፕራንኮችን በብዛት እንዳየና ሁሉም ላይ ይሄን ዘፈን እንደሚለቁ ነገረኝ፡፡ ሌላ ቀን ቤት ውስጥ የሱን ቁጥር አልኩት፡፡

ሌላ ዘፈኖችንም ስል ሰምቶ ከየት ነው እንደዚህ የለመድከው? አለኝ፡፡ ቪኦኤ ላይ ሰምቼ ነው አልኩት፡፡ እኔ ግን በስልኬ ከዋፐ ዳም ላይሪክስ እያነበብኩ ስራዬ ብዬ ነበር የማጠናው፡፡ ግን እነዚህ ፈረንጆች ለምንድነው የነኩት ነገር ሁሉ የሚያምርላቸው? እኛ ሀገር ሁሉም ነገር አይሆንልንም፡፡ እነሱ ሁሉም ነገር ምርጥ አርጎ መስራት ያውቁበታል፡፡ የእንግሊዘኛ ዘፈኖች ስሜትን የመንካት፣ የሆነ ስሜት የመፍጠር አቅም አላቸው፡፡

ብዙ ዘፈኖች፡፡ ፈረንጆች ግን እንዴት ነው ሁሉም ነገር የሚያምርላቸው? እኛስ ለምንድነው ምንም ነገር የማያምርልን? ነጭ ስለሆኑ ነው? ማለቴ በተፈጥሮ ነው? ወይስ በየትኛው የታሪክ አጋጣሚ ነው ይሄ ሊከሰት የቻለው? ምንድነው ፈረንጆችን እንዲህ ከኛ የለየው? ብዙ ጥያቄዎች ነበሩኝ፡፡

እሁድ ነሐሴ 25 2007 ወደ 6፡00 ሰአት

ውድ ማስታወሻዬ

ት/ት ሲዘጋ ብቸኝነት ተጫነኝ፡፡ እዚሁ ሰፈር ከኦሊና ጫላ ጋር ስፖርት(ከብደት ማንሳትና ፓራለል) ጀምሬ ነበር፡፡ ትንሽ ጥሩ ጊዜ አሳልፌያለሁ ማለት እችላለሁ፡፡ እኔ እነሱ ጋር የምሄደው ለስፖርቱ ሳይሆን ከሰው ጋር የመቀራረብ ጥማት ስለነበረብኝ ነው፡፡ ትንሽ ሰርተን አቆምን፡፡

አንድ ያመጣሁት ጸባይ ነበረ፡፡ አመቱን ሙሉ በህይወቴ የተከሰቱ ነገሮችን ለወንድሜ እነግረዋለሁ፡፡ 9ኛ ክፍል ከነኢዩኤል ጋር ስለነበረኝ አስገራሚ ፓራዳይዝ፣ ስለ10ኛ ክፍል ጭንቀት፡፡ 10ኛ ክፍል ደግሞ ቸርች የገጠመኝን ነገር እንዳለ ዘክዝኬ ነገርኩት፡፡ ስለ ፈይሳ፣ ስለ አያንቱ፣ ስለነሄለን፣ ፈይሳ እኔን ሰላም ላለማለት የሚያደርገውን ነገር ነገርኩት፡፡ እንዴ?? አለ፡፡ ሰው ሰላም አላለኝም ብለህ ትናደዳለህ እንዴ አለኝ፡፡ አንተኮ እራስህን በጣም እንደጠቃሚ ሰው ነው ማየት ያለብህ ሰዎች አንተን ሰላም አላለኝም ሊሉ እንጂ አንተ እንዲህ ልትል አይገባም፡፡ እንዲህ ስለሰው የምትጨነቅ ከሆነማ አለቀልህ አለኝ፡፡ ሳስበው የበታችነት ችግር(inferiority complex) አለብህ አለኝ፡፡ አይ እኔ የበላይነት እንጂ የበታችነት ችግር የለኝብም አልኩት፡፡ የሚገባኝ ቦታ ስላልሆንኩ፣ ያንን መቀበል አቅቶኝ ነው ማለቴ ነው፡፡ ግን እሱ ነው ትክክል፡፡ እኔ በውስጤ ስለራሴ የማስበው ነገር ጥቅም የለውም፡፡ ለሌሎች የማሳየው ፊት እንጂ፡፡ የማሳየው ፊት ደግሞ የበታችነት ብቻ ሳይሆን ናቁኝ ናቁኝ የሚል ነው፡፡ አይ እኔ በጣም ነው እራሴን የማከብረው ሌላው ሰው እንደዚያ ስለማያከብረኝ ነው የምጨነቀው አልኩት፡፡ ግን ምንም ያህል ራሴን ባከብር የበታችነት ፊት ነበር ሳሳይ የነበረው፡፡ ሄጄ ከመቀመጥ እስከጠራ እጠብቃለሁ፡፡ ያን ስሜት አይተው ነው ልጆች ሲንቁኝ የነበሩት፡፡ ወንድሜ እራስህን በጣም ቫሉአብል አድርገህ ነው መቅረብ ያለብህ አለኝ፡፡ መች ቫሉአብል መሆኔን አጣሁት? መች እንደዛ ይሰራና?

አጠቃላይ የዲፕሬሽን ማሰሪያ፣ ማህበራዊ ድቀት ነው፡፡ ወደ ታች የመጫን፡፡ `depression` የሚለውን ቃል የስልኬ የእንግሊዘኛ ዲክሽነሪ፡
"2 a state of mind producing serious, long-term lowering of enjoyment of life or inability to visualize a happy future.
3 a period of unhappiness or low morale which lasts longer than several weeks and may include ideation of self-inflicted injury or suicide" ይለዋል፡፡

ከዚህ ቀጥሎ በህይወቴ አልመለስበትም ያልኩት፣ ሌላ የቸርች ምዕራፍ አለ፡፡

የነኦሊና የነጫላ ጉዳይ ማስታወሻዬ ላይ ጠቃቅሼ እንዳለፍኩት ቀላል አልነበረም፡፡ የሰፈር ህይወቴን ለማሻሻል በጣም እፈልግ ነበርና ከኦሊ ጋር ስንቀራረብ አዲስ እቅድ አወጣሁ፡፡ ኦሊ የነጫላና የነዮናስ ጓደኛ ነው፡፡ ዮናስና ጫላ ደግሞ የነአብርሽ(አስበው የድሮ ጎረቤቴ) ጓደኛ ናቸው፡፡ በኦሊ በኩል ዮናስና ጫላን፣ በነሱ በኩል ደግሞ እነአብርሽን ለመጃለስ እቅድ አወጣሁ፡፡ እና ጓደኝነት በኔ ቤት ሳይንሳዊ ትንተና ይሰጠው ጀመረና አረፈው፡፡ ኦሊን እነጫላ ጋር እንሂድ እያልኩ ሁሌ ስጨቀጭቀው ምንድነው አካበድካቸውኮ ይለኝ ነበር፡፡ አቡሽም ስለነኢዩኤል ሳወራ እኔ አንተ ከምታወራው ተነስቼ ያንን ልጅ ጣሪያ ሰቀልኩት ይለኝ ነበር፡፡

ወንድሜ እየሰማ ለመዝፈን ድፍረት አገኘሁ፡፡ ግን ስልኬ ውስጥ እንደነበረኝ አልነገርኩትም፡፡ ሚጣ ነች ያቃጠረችው፡፡ ከዚያ ለዘፈንህ ብሎ አንድ ነገር በፍላሽ አሳለፈልኝና በፒሲ አየሁ፡፡ ስለኢሉሚናቲዎች ነበር፡፡ ስለዘፋኞች፣ ስለምልክታቸው፣ ስለነቢዮንሴ፣ ሪሃና አይ ላቭ ዩ ሴጣን ብላ ስለመዝፈኗ፡፡ ሰይጣንን እንደሚያመልኩ፣ ስለፊልሞች፣ ያ የወደድኩት ኢንታይም የተባለ የጀስቲን ቲምበርሌክ ፊልም ኢሉሚናቲ ስለመሆኑ ይናገራል፡፡ ስለነአባማ፣ ብዙ ሰዎች በእጃቸው የቀንድ ምልክት ሰርተው... አጭር ቪዲዮ፡፡ ብቻ አስፈራኝና ወዲያው ስልኬ ውስጥ ያሉኝን ዘፈኖች እንዳሉ ደለትኳቸው፡፡ ትንሽ ቆይቼ እኔ አላልኩ፣ እነሱ ናቸው ያሉት እኔ ምናገባኝ እኔ ማዳመጥ ብቻ ብዬ ከኦሊ ጋር እንደገና ከሌላ ብዙ ዘፈኖች ጋር አሳለፍኩ፡፡

ቸርች እንደገና ላለመመለስ አልነበረም ያቆምኩት፡፡ ማትሪኬን ከተፈተንኩ በኋላ ለመመለስ ነበር፡፡ የነበረው ሁኔታ ት/ቴን እንዳጠና አልፈቀደልኝም፡፡ ክረምት ወንድሜ ሲመጣ ወደ ኳየር ተመለስኩ፡፡ ስሄድ ኳየር ቤታቸው አልነበሩም፡፡ ዋናው ጸሎት ቤት ስሄድ፣ መዝሙር እየተለማመዱ ነው፡፡ ሄጄ ፊት ለፊታቸው ተቀመጥኩኝ፡፡ ጨነቀኝ፡፡ ማንን እንደማይ፣ ወዴት እንደማይ ግራ ገባኝ፡፡ ከጨረሱ በኋላ ሲያለማምዳቸው የነበረው ፈይሳ ዌልካም አለኝ፡፡ ተጸለየ፣ ሁሉም ሰላም አለኝ፡፡ አሪፍ ቀን ነበረ፡፡ ከዚያ ጥቂት ቀናት ኳየር ሄድኩኝ፡፡ የልብ ህመም አልነበረም፡፡ ግን ጭንቀቱ ከነሙሉ ሀይሉ አብሮኝ ነበረ፡፡ ቸርች እንደበፊቱ አላስጠላኝም፡፡ ፈይሳ ጥሩ ሊሆንልኝ ሲሞክር ነበር፡፡

ቸርች ክረምት ክረምት ካስ(CAS) የሚባል በዋነኝነት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የሚያካሂዱት ፕሮግራም ነበረ፡፡ ወንድሜ ከመስራቾቹ መሃል ነው፡፡ ከሌላ ሀገር ተማሪዎች ተሞክሮ ወስደው ነው መሰለኝ፡፡ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ያልሆኑ ቡድኑ ውስጥ የነበሩ ልጆችም ነበሩ፡፡ ቡድኑ ከተቋቋመ 4 አመት ነበር ያን ክረምት፡፡ ዋናው ነገር ያን ክረምት የመዝሙር ቡድኖች መዝሙር ተለማምደው፣ ሊትሬቸሮች(ስነጽሁፎች) ደግሞ ድራማ፣ ግጥም አዘጋጅተው በክረምቱ መጨረሻ አንድ እሁድ ፕሮግራማቸውን የሚያቀርቡበት ነው፡፡ ቃል የተሰጣቸው ቄስም ይሰብካሉ፡፡ ዮናስ የሚባል የወንድሜ ጓደኛ አግኝቶኝ ለምን ካስ አትመጣም አለኝ፡፡ እኔ? አልኩት፡፡ አዎ ምነው? አለኝ፡፡ ስቄ ዝም አልኩት፡፡ እኔም ፈልጌ ነበር ግን ደግሞ ብጨነቅስ እንዳመሌ ቢደብረኝስ? ብዬ ፈርቼ ነው የተውኩት፡፡ ዮናስ እንዲህ ሲለኝ ተበረታታሁኝና ወንድሜን ጠየቅኩት፡፡ ካስ አስገባኝ አልኩት፡፡ ወንድሜ ደግሞ ሊቀመንበራቸው ነበር፡፡ እሺ ስምህን አቀርባለሁ አለኝ፡፡ ስም ማቅረብ ማለት እንዲገባ የተፈለገው ሰው እንዳይገባ ተቃውሞ ያለው ሰው ካለ ተብሎ ነው፡፡ ገባሁ፡፡ የመጀመሪያውን ቀን መሄድ ፈራሁ፡፡ ወንድሜ ተቆጣኝ፡፡ ሁለተኛውን ስሄድ ደበረኝ፡፡ ሶስተኛውንም እንዲሁ፡፡ አራተኛ ቀን እኔ ከመዘመር ሊትሬቸር ብገባ እንደሚሻለኝ ለወንድሜ ነገርኩት፡፡ እንዲያውም ጥሩ ነው፣ እነማሙሽ ሰው አጥሯቸዋል አለኝ፡፡ በጣም አሪፍ ውሳኔ ነበር፡፡ አንድ ላይ ሁሉም ከጸለየ በኋላ ዘማሪዎች እዚያው ቤት ውስጥ ሲለማመዱ ሊትሬቸሮች የቸርቹ ጓሮ እንሄዳለን፡፡ ብዙ ልጆች አልነበሩም፡፡ ማሙሽና አቤል(የወንድሜ ጓደኞች) የሊትሬቸር መሪ ነበሩ፡፡ እነአባነጋ፣ አቤኔዘር፣ ናኒ፣ ሜላት፣ ጉዲሳ(ኳየሬ)...ነበሩ፡፡ ምርጥ ልጆች፡፡ መጀመሪያ ሊትሬቸር ስሄድ ሁሉም ጥሩ ተቀበለኝ፡፡ እኔ ግን ጭንቅ ይለኛል፡፡ እንዴ በቃ እኔ ሰው መሀል መቀመጥ አልችልም ማለት ነው? ማሙሽ አዲስ ገቢ እንደመሆኔ ስለኔ ማውራት ጀመረ፡፡ ቤቢ ማለት ብዙ መጽሐፍት ያነበበ፣ አንድ ከአራት መቶ ገጽ በላይ ያለው ልቦለድ በአራት ቀን ጨርሶ ቂጭ የሚያረግላችሁ፣ ሲሆን ከሱ ብዙ ነገር ትማራላችሁ፣ ማንበብን ከሱ ተማሩ ብሎ ብዙ ነገር አወራ፡፡ ማንም እንደዛ ስለኔ ለሰው አውርቶ አያውቅም፡፡ በቃ ለነፈይሳ ማሳየት ያቃተኝን ማንነቴን ለነማሙሽ አሳያቸዋለሁ ብዬ ሳስብ ነበር ካስ ስገባ፡፡ ማሙሽ እንደዛ እኔን ማካበዱ በፍጹም ያልጠበቅኩት ነገር ነበር፡፡ ብዙም ቅርርብ አልነበረንም፡፡ አንዳንዴ ወንድሜ ጋር ይመጣል፡፡ መጥቶ ሰላም ይለናል፡፡ ከሱ ጋር መጽሐፍ ተውሼ አውቃለሁ፣ ከወንድሜ ጋር ስለኔ አውርተው ያውቃሉ ሊሆን ይችላል፣ በተረፈ ቤት ሲመጣ እንዲያውም ያናድደኝ ነበር፡፡ አንድ ቀን ቤት መጣና ሚጣን ሰላም በልልኝ ብሎኝ እኔን ሰላም ሳይለኝ ሄደ፡፡ ማሙሽ ይንቀኛል ብዬ እብድ አልኩኝ፡፡ እሱ ብዙም የማያውቀኝ እንደዚያ ካጋነነኝ አብሬያቸው የምውለው እነኢዩኤል፣ እነሄለን፣ እነበረከት እንዴት ያድንቁኝ? በልባቸው በጣም እንደሚያደንቁኝ እኔም አውቀዋለሁ፡፡ በተለይ በረከት እኔን ጣል ጣል ማረግ ይፈልጋል ግን በልቡ በጣም እንደሚያከብረኝ አውቀዋለሁ፡፡ ለጓደኛዬ ለአቡሽ ደግሞ እኔ ነኝ አራሴን የማካብደው፡፡ እንዲህ እንዲህ ነኝ ስለው አንተ እራስህን ታካብዳለህ ግን እኔ አንተ የምትለው ምንም ነገር አይታየኝም ይለኛል፡፡ ፲ኛ ክፍል ከገባን በኋላ አንተ ምንም ስለማታውቅ ነው እንደማሙሽ የሚያውቁት ግን ያደንቁኛል አልኩት፡፡

ማሙሽ ሲያደናንቀኝ ደስታዬን መቆጣጠር ነው ያቃተኝ፡፡ ማለት ኩራቴን፡፡ በጣም ደስ ላላለኝም፡፡ ደስ ሊለኝ ይገባ ነበር፡፡ ግን ለምንድነው ደስ ያላለኝ ብዬ እራሴን ስጠይቅ ነው ያገኘሁት፡፡ ማለት በጣም መደሰት ነበረብኝ፡፡ ጭንቀቴ ለቆኝ ሊጠፉ ይገባው ነበር፡፡ ሁለተኛው ቀን ነበር ከአቤል ጋር የተገናኘነው፡፡ እና ከየት እንዳመጣው አላውቅም፣ ዘቡሌ(ዘበኛ) ብሎ ይጠራኛል፡፡ እሱ እኮ መቀለዱ ነው፡፡ ዘቡሌ እያለ እየጠራኝ ያን ቀን ፕሮግራም አልቆ ምናምን “ዘቡሌ ስልህ ተናደድክ እንዴ? እኔኮ ለጨዋታ ነው አለኝ፡፡ አውቃለሁ አልተናደድኩም አልኩት፡፡ አይ ፊትህ፣ የተናደድክ ትመስላለህ አለኝ፡፡ እኔ ከመሬት ተነስቼ የምጨነቀውን እሱ ዘቡሌ ስላለኝ የተናደድኩ መስሎት ነው፡፡ አይደለም ለሌላ ነገር ነው አልኩት፡፡ ብቻ ቀስ በቀስ እነማሙሽን ተለማመድኩ፡፡ የሆነ አንድ ነገር ትሰራለህ ብለውኝ ካሌብ(ጎረቤታችን) ታሪኩን የነገረኝን ልቦለድ ጽፌ በቃ አደናነቁኝ፡፡ አቤል ቤቢ በጣም የሚገርም ተሰጥኦ ነው ያለህ አለኝ፡፡ ብቻ ተመቸኝ፡፡ ምኑም እንደ ኳየር አልነበረም፡፡ እኔ በቃ እንዲህ ሰው በተሰበሰበበት ማውራት አልችልም ብዬ ተስፋ ቆርጬ ነበር፡፡ አዎ ኳየር ውስጥ አልናገር አልጋገር፡፡ ካስ ግን እንደኔ የሚያወራ ራሱ አልነበረም፡፡

ካስ ውስጥ እነፈይሳም ነበሩ፡፡ ማለት መዝሙር ውስጥ፡፡ አንድ ቀን እኔ ተቀምጬ ፈይሳ ከኔ ጎን፣ ከሱ ጎን ደግሞ ጓደኛው ዮሴፍ፣ ከዮሴፍ ጎን ደግሞ አለም(የነወንድሜ ጓደኛ) ተቀምጧል፡፡ አቀማመጡ ክብ ተሰርቶ ነበርና ወንድሜና እነሜሪ ከሌላ አቅጣጫ ተቀምጠው ነበረ፡፡ እኔ

አቀማመጣችንን ሳየው አለም ከዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች(ከነወንድሜ) ተነጥሎ መቀመጡን አስተውያለሁ፡፡ ትንሽ ቆየና አለም ተነስቶ ከነወንድሜ ጋር ተቀመጠ፡፡ እኔ አይደብረውም እንዴ? እኛ ደብረነው እነሱ ጋር ሄደ ብለው ያስባሉ ብሎ አያስብም? አልኩኝ በውስጤ፡፡ ትንሽ ቆይቶ ዮሴፍና ፈይሳ ወጡ፡፡ ለምን እንደወጡ አላወቅኩም፣ አላሰብኩም፡፡ ባስብም ግን ለዚያ ነው ብዬ ላስብ አልችልም፡፡ ማታ ወንድሜ ሲነግረኝ ፈይሳ፣ የኛ ኳየር የሆነችውንና ዩኒቨርሲቲ ተማሪ፣ ግን ከሱ ጋር የምትቀራረበዋን ልጅ አለም ለምን ከኛ ጋር ተነስቶ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ጋር ሄደ? እኛ ጋር መቀመጥ አስጠልቶት ነው? አላት፡፡ ዮሴፍና ፈይሳ ከዚያ በኋላ ካስ አልመጡም፡፡ እኔ እዚያ አያንቱ ነንሴንስ ብላ ሰድባኝ ኳየር ያቋረጥኩ ጊዜ ደግሞ ት/ቤት ተገናኝተን ልጆች ፊት አንተ አያንቱን ነው እንዴ ምታገለግለው ብሎ ሲያላግጥብኝ ነበር፡፡

ብቻ ካስ ጥሩ ጊዜ አሳለፍኩ፡፡ አዳር ነበረን፡፡ የአዳር ቀን ከነማሙሽ ጋር ጥሩ ጊዜ አሳለፍን፡፡ ለማያውቀን ሰው እውነተኛ፣ ተጫዋች፣ ደስተኛ ማንነታችንን ማሳየት እንዴት ደስ ይላል? አሁንስ እውነተኛው ማንነቴ የቱ እንደሆነ ግራ እየገባኝ ነው፡፡ ጭንቀታምነት ወይስ ተጫዋችነት? እሁድ የፐሮግራሙ ቀን ሁሉም ደስተኛ ይመስል ነበር፡፡ አቤል best day ever ሲል ሰምቼዋለሁ፡፡ እኔ ግን በጣም ነበር የደበረኝ፡፡

ጉዲሳ አብሮን ነበረ፡፡ የኳየራችን ልጅ፡፡ ማንነቴን አይቷል፡፡ ኳየር ሰርጌ ለመግባት ልጠቀምበት አሰብኩ፡፡ ጓደኛዬ ላረገው፡፡ ከኳየር ልጆች ጋር ትንሽ እየተመቻቸሁ የመጣሁ መሰለኝ፡፡ የፐሮግራሙ ቀን ብቻዬን ከሆንኩ ስለሚደብረኝ፣ ጉዲሳን "አልለይህም፣ ወደ ሄድክበት እሄዳለሁ" አልኩት፡፡ ከዚያ ስከተለው ስከተለው "ዝም ብለህ አትከተለኝ እስኪ" አለኝ፡፡ ምን ላርግ ሰው መሃል ብቻዬን ከሆንኩ ፊቴ "ብቸኝነት ሊገለኝ ነው" የሚል ታፔላ ራሱ ላይ ይለጥፋል፡፡

ሀሙስ ነሐሴ 28 ከቀኑ 6 ሰአት

ውድ ማስታወሻዬ

Life is getting worse and worse. ሰዎች ሱሰኞች የሚሆኑት መጠቀሙ አራድነት ስለሚመስላቸው ብቻ ይመስለኝ ነበረ፡፡ እንደዚያ የሚመስለኝ አንዲህ አይነት ስሜት ያለ ስለማይመስለኝ ነበረ፡፡ እንዴት? በቃ ህይወት የምትጨልምበት፣ ደስታ ሚናፍቅበት ጊዜ፣ አርቲፊሻል ደስታ ለማግኘት ሰዎች የሚጥሩበት መንገድ እንደሆነ አይገባኝም ነበር፡፡ አሁን ግን በኔ ላይ ደርሶ አየሁት፡፡ አሁን ሲጋራ ወይም ጫት ማግኘት ብችል ከመጠቀም ወደ ኋላ የምል አይመስለኝም፡፡ ምክንያቱም ብቸኝነትና መገለል በጣም እያጠቁኝ ነው፡፡ ደስታ ርቃኛለች፡፡

ከካስ በኋላ ወንድሜ እነማቲ(የእቴቴ ልጅ)ለጸሎት ሊመጡ እንደሆነ ነገረኝ፡፡ የፈራሁት፡፡ እነዛ ልጆች እኔ እንዲህ ኳየር አስጠልቶኝ እዚህ ፖዚሽን ላይ ሆኜ እንዲያዩኝ አልፈልግም ነበርና እንዲመጡ አልፈልግም ነበር፡፡ መጡ፡፡ ብዙ አዲሳባ የሚኖሩ የሙቱ ልጆች፡፡ መጀመሪያ ት/ትና ጾም ጸሎት ነበረ፡፡ መጀመሪያ አልሄድኩም፡፡ ከሁለት ቀን በኋላ ወንድሜ "ማቲ ቤቢን ይዘኸው ና አለኝ" ብሎ ነገረኝ፡፡ ምን ማለት እንደሆነ ገብቶሀል? ቤቢ ቸርች አይመጣም ማለት ነው? ቤቢ የእግዚአብሔር ቤት አይመጣም ማለት ነው? ብሏል ማለት ነውኮ፡፡ ሌሎች ወጣቶችኮ እዚያው ነበር የሚያድሩት፡፡ ወይ ያ ጊዜ፡፡ እኔ ምንድነኝ? ያልኩበት ጊዜ ነበር፡፡ ከሁለት ቀን በኋላ ሄጄ ከማቲ ጋር ተገናኘን ሰላም አለኝ፡፡ ያን የኔ ኳየር ነበር የዘመረው፡፡ ኳየር ገብቼ እንደሆነ ጠየቀኝ፡፡ ገደቱ ኳየር እንደሆንኩ ነገርኩት፡፡ ታድያ ለምን ዛሬ አልዘመርክም አለኝ፡፡ አልተለማመድኩም፣ ቤት ስራ ነበረኝ ብዬ ቀበጣጠርኩ፡፡ ብቻ የኔ ነገር እንደ ጠበቀው እንዳላገኘው እርግጠኛ ነኝ፡፡ ብቻ ስለዛ ጊዜ ማስታወስ አልፈልግም፡፡ በጣም መገለል የተሰማኝ ጊዜ ነበር፡፡ ከማሬ ጋርም ተገናኘን፡፡ ብቻ ከባድ ጊዜ ነበር፡፡ ከሰው ጋር መቀራረብ እንደማልችል ራሴን ያሳመንኩበት ጊዜ፡፡ መከራዬን የበላሁበት ጊዜ፡፡ ያን ቀን ትምህርት ነበረ፡፡ የሚያስተምረው ሰውዬ ከአዲሳባ ነው ከነማቲ ጋር የመጣው፡፡ ያን ቀን ስለሰይጣን መዋቅሮች ሉሲፈር፣ ፈሪሜሰን፣ ምናምን ብሎ ነው እያስተማረ የነበረው፡፡ ያ ሰውዬ ናይት ክለብ ውስጥ ገብቼ እጸልያለሁ ሲል ነበርና ቀላል ሰው እንዳልሆነ ከአነጋገሩ ያስታውቃል፡፡ ከሁሉም በላይ ትኩረቴን የሳበው፡ "ስለሀገራችን የሚጸልይ የጸሎት ቡድን አለን" አለ፡፡ "አባይ እንደሚገደብ ይፋ ሳይደረግ በፊት ፐላኑ ለጸሎት ቡድናችን በሚስጥር እንድንጸልይበት ተሰጥቶን ስንጸልይበት ነበር"፡፡

ያን ሰሞን አንድ ቀን ቸርች ስሄድ ማንም አልነበረም፡፡ የጸሎት ፐሮግራም አለ ተብሎ ነው የሄድኩት፡፡ ወደ አስራ አንድ ሰአት፣ ዘንቦ ነበር፡፡ ጸሎት ቤቱ ተቆልፎ አልነበረምና፣ ገብቼ መጸለይ ጀመርኩ፡፡ ማልቀስ ጀመርኩ ብል ይቀላል፡፡ ጌታ ሆይ እንደ ሌላ ልጆች ከሰው ጋር መግባባት እንድችል እርዳኝ፡፡ ለምንድነው እንደሌሎች ያልሆንኩት? ለምንነው ህይወቴ እንዲህ የመከራ የሆነው? ጌታ ሆይ እባክህ እርዳኝ ከብዶኛል.... እኔ ጋር ሁሉም ነገር ወድቆ ነበር፡፡ ሁሉም ነገር ወድሞ ነበር፡፡ የዚህ ሁሉ በጣም አስከፊ ክፍል የልጅነት ዘመኔን አብሬ በመጫወት አብሬ ጥሩ ጊዜ ያሳለፍኳቸው ሰዎች ፊት እንደዚያ ድሮ እንደሚያውቁኝ ሆኜ መቅረብ አለመቻሌ ነው፡፡ የተራቆተ ውስጣዊ መንፈስ ያለኝ ሰው ነበር የሆንኩትና ድሮ አብሬ ያደግኳቸው ልጆች እንደድሮው እኔን እንደማያዩ፣ የድሮው ትዝታ ሆኖ እንደቀረ ሳስበው ያምመኛል፡፡ በዚህ መንፈስ ነበር 2007 10ኛ ክፍል የስቃይና የመከራ አመቱ የተገባደደው፡፡ እውነት ይሄ አመት አለቀ? ነበር ያልኩት፡፡ የዚያን አመት መጨረሻ ናፍቄው ነበርና፡፡ አመቴ የተረገመ መስሎኝ ነበርና፡፡

ማትሪክ መጣ፣ 10ሩንም ኤ አመጣሁ፡፡ ብዙም አልገረመኝም፡፡ ስጠብቀው ነበርና፡፡ ቤት አባቴ ደስ አላለህም? ብሎ ጠየቀኝ አንድ ቀን ማታ እኔ፣ እሱ፣ እናቴ፣ ወንድሜና እህቴ ተቀምጠን ባለንበት፡፡ ብዙም ደስ አላለኝም አልኩት፡፡ ከዚህ በላይ የሚያስደስት ነገር ምናለ? አለኝ፡፡ "በጣም

ደስተኛ የነበርኩ ከመሆኑ የተነሳ አንተን መሆን ነበር የተባልኩበት ጊዜ ነበረ” አልኩት፡፡ በርግጥ ስትሬት ማምጣቴ የስሜት ለውጥ ያመጣብኝ አይመስለኝም፡፡ ቅድሙኑ ያጠናሁት ከሀሜት ለመዳን እንጂ 10ኛ ክፍል እንኳን ለማጥናት ለመኖርም የተቸገርኩበት ጊዜ ነበር፡፡ አባቴ ግን ትክክል ነበር፡፡ በህይወቴ አሳካሁ ከምላቸው ነገሮች ከፍተኛው ነበረ፡፡ በጣም ደስተኛ መሆን ነበረብኝ፡፡ ሲጀመር እሱ ራሱ የጠየቀኝ ደስ ያለኝ ስላልመሰለው ነው፡፡
ቸርች ያው ነጥቤን ሰምተው ነበረ፡፡ እሁድ እለት ጠዋት እንኳን ደስ አለህ ተባልኩኝ፣ ጋሩማ የሚባል የወጣቶች አባት አይነት የነበረ ልጅ “አኮራኸን፣ እንኳንም የኛ ሆንክ፣ ግን በት/ቱ ብቻ ሳይሆን በመንፈሳዊውም እንደዚያው መሆን አለብህ፣ ትምህርት ብቻውን ጥቅም የለውም” አለኝ፡፡ ጋሩማ ያልገቡት ነገሮች ነበሩ፡፡ እኔም ገና ከዚያ ወዲያ የሚገቡኝ፡፡

በዚያ ክረምት ጥቂት መጽሐፍትን አንብቤ ነበር፡፡ አመጸኛው ክልስ፣ የአሌክስ አብረሃም፡ ዙቤይዳና ዶ/ር አሸብር፣ የመለስ የት/ት ፖሊሲ...

ሮብ መስከረም 11 2008 ዓ.ም.

ውድ ማስታወሻዬ

አሁን 2007 ሄዷል፡፡ ላይመለስ፡፡ ላይመለስ ያለፈው ግን አመቱ ነው፡፡ ያ ባለፈው አመት ውስጥ ያሳለፍኩት ጭንቅና መከራ ግን ሊመለስ ይችላል፡፡ በዚህ በ2008፡፡ እኔ ግን ያለፈውን አይነት መከራ የሚሸከም ትከሻ የለኝም፡፡ ትከሻዬ ዝሏል፡፡ አሁን ካለፈው አመት ስቃዬ ማገገም ነው ያለብኝ፡፡ እንደዚያ ካልሆነ የምሞት የምሞት ነው የሚመስለኝ፡፡

ጥቅምት 17፣ 2008

አዳዲስ ነገሮች አዲስ አመት፣ አዲስ ጓደኞች፣ አዳዲስ የኳየር አባላት፣ አዲስ ት/ቤት፡፡ በአዲስ አመት ቢያንስ ብቸኝነት እየተሰማኝ አይደለም፡፡ በዚህ አመት ብቸኝነት ባይሰማኝም ግን ደስተኛ አይደለሁም፡፡

ወደ ት/ቤት የምሄደው ከአቡሽ፣ አሊና ዮናስ ጋር ነው፡፡ እነሱ ተጠራርተው፣ የኔ ቤት ለመጠራራት ስለማይመች መታጠፊያ ላይ ተጠባብቀን እንሄዳለን፡፡ ከት/ቤት 7 ሰአት ላይ ስንለቀቅ ደግሞ ብር ካለን ፑል ተጫውተን እንገባለን፡፡ ከነዚህ ልጆች ጋር በጣም ተመቻችተናል፡፡ ለዚህ ነው ብቸኝነት እየተሰማኝ የሌለው፡፡ አቡሽና አሊ ድሮም ጓደኞቼ ነበሩ፡፡ ከዮናስ ጋር ግን አንቀራረብም ነበር፡፡ እንኳንም ት/ቤት ከቤት ራቀ፡፡ እያወራን፣ እየተጫወትን ነው የምንሄደው፡፡

የገባሁት ናቹራል ነው፡፡ የሶሻል ሰው ነበርኩ፡፡ የተሳሳተ ውሳኔ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ ይቆጨኛል፡፡ ሶሻል ገብቼ ከቆጨኝ የሚቆጨኝን ያህል ግን አይደለም፡፡ እንደ ምንም ተሟሙቼ ሜዲስን ገብቼ የሶሻል ት/ት በርቀት ለመማር አስቤአለሁ፡፡ ናቹራል የመግባት ጥቅሙ ይሄ ነው፡፡ ሶሻል ት/ት መማር ይቻላል፡፡ ሶሻል ከተገባ ግን ሶሻል ነው፡፡ ኖ ናቹራል፡፡ ጎበዝ የተመሰከረለት የሶሻል ተማሪ መሆን ነው የምፈልገው፡፡ ማትስን ፈርተህ ነው ሶሻል የገባኸው መባል አልፈልግም፡፡ ሌላው የአንተ ምርጫ ነው፣ እኛን አታማክረን ቢሉም የዶክተር እገሌ አባት፣ የዶክተር እገሌ እናት፣ የደሜ ልጅ የህክምና ዶ/ር ሆነ፣ የሀይሌ ልጅ ሜዲካል ዶክተር ነው እንዲባልላቸው የሚፈልጉ፣ የኔን ሜዲስን መግባት ሳይተኙ ያለሙት፣ ሳያልሙ የፈቱት ወላጆች አሉኝ፡፡ የሀገር መጀመሪያ ቤተሰብ ነው፣ የቤተሰብ መጀመሪያ ደግሞ ያው ወላጆች ናቸው፡፡ ስለዚህ ወላጆቼን አስቀየምኩ ማለት ሀገሬን አስቀየምኩ ማለት ነው፡፡ የሀገሬ ህልም እውን መሆን አለበት፡፡ እንዲህ እንዲህ እያልን ራሳችንን እናጽናናለን፡፡

የክፍል ህይወት፣ እነሄለን እነኢዩኤልና እነበረከት ከሚኖሩበትና የድሮ 8ኛ ክፍል አብሬ የተማርኳቸው ጓደኞቼ ካሉበት ክፍል መምረጥ ነበረብኝ፡፡ እነሄለን ማንም ሊቀርባቸው የሚፈልግ፣ ብዙ እንደኔ እነሱን የማይቀርቡ ልጆች ከነሱ ጋር ለመቀራረብ ብቻ የነሱ ክፍል የገቡ ሲሆን የድሮ ክፍል ልጆች ደግሞ ከድሮ ጀምሬ አብሬአቸው የተማርኳቸው ናቸው፡፡ ከነሄለን ጋር ከገባሁ ከበረከት ጋር መነታረክ፣ ያ እነኢዩኤል ጋር ልቀመጥ እያሉ መጨነቅ ሊቀጥል ይችላል፡፡ እዛኛው ደግሞ አይኖርም፡፡ በፊትም እኔ ከነኢዩኤል ጋር መቀራረጥ ፈልጌ ነበር፡፡ ከነሱ ጋር ተለያየሁ፡፡ ከነሱ ጋር ቀጥዬ በነበረ ብያለሁ ብዙ ጊዜ፡፡ አዲሶቹ አብሬአቸው የገባሁት፣ እነኬኔሳ፣ ሲሳይ፣ ሚያ፣ አቡሽ...ከጠበቅኩት በላይ አሪፍ የክፍል ህይወት ነበር፡፡ የ10ኛ ክፍል ተቃራኒ፡፡ የክፍሉ ኮከብ ነበርኩ፡፡ የክፍሉ ኢዩኤል ልበል? እያወራሁ ነው የምውለው፣ አስቃቸዋለሁ፣ ት/ቤት መሄድ አይደብረኝም፣ ሁሉም ነገር አሪፍ ነበረ፡፡ ግን ደስተኛ አልነበርኩም፡፡ እንደገና ኳየር አቁሜ እንኳን፡፡

ኳየር፣ የአንድነት ቀናችን ሞራሉ ከየት እንደመጣልኝ አይታወቅም መጨረሻ ላይ ሲጨፈር አቀወጥኩት፡፡ በርግጥ እኔ አይታወቅም ብዬ የማልፈው ነገር የለም፡፡ በፊት ለምን እፈራቸዋለሁ፣በፊት ለምን ሲዘሉ እኔ ዝም ብዬ በጭንቀት አያቸዋለሁ፣ ያን ቀን ደግሞ ለምን በሙሉ ኮንፊደንስ የኳየሩ ልጆች እስኪገረሙ፣ እነፈይሳ ዛሬ ምን አገኘ እስኪሉ ጨፈርኩ?

እስካሁን የቸከቸኩትን የቸከቸኩት ሪስኩን ወስጄ ነው፡፡ እንኳን በመጽሐፍ መልኩ ማሳተም፣ ለጓደኛ የማይነገር የውስጤን ነገር ጎልጉዬ እያስነበብኩህ እንደ ሆነ ይገባኛል፡፡

 ከዚያ ነገሮች ከበፊቱ እየተሻሻሉ እየመጡ ነበር፡፡ አዲስ የኳየር ልጆች ሊጨመሩ እንደ ሆነ ሰማሁ፡፡ ለኛ ኳየር አስራ ምናምን ልጆች ነበሩ የተጨመሩት፡፡ ያለፈውን አመት እኔ ጉደቱ ኳየርን ስቀላቀል 5 ብቻ ነበርን አዲስ ገቢዎቹ፡፡ በዚህ አመት ደግሞ 14፡፡ ከነኛ ልጆች መሀል አብሮ አደጌ አቢቲ አንዱ ነበር፡፡ አቢቲና ሌሎችም ልጆች ሲገቡልን ነገሮች ለየት ያለ ቅርጽ እንሚይዙ አምኜ ነበር፡፡ ግን እንደዛ አልነበረም፡፡ ኳየር ውስጥ የሚሰማኝን ጭንቀት መጣል አልቻልኩም፡፡ ከዚያ መቅረት ጀመርኩኝ፡፡ ቀረሁ፣ ቀረሁ፣ ግን ለማቆም አልነበረም፡፡ አቢቲ ና እንጂ አብረን እንሄዳለን ልጆችኮ ማትሪክ ስትሬት አመጣና አሁን ደግሞ ኢንትራንስ 700 ለማምጣት ነው እያሉ ነው ምናምን አለኝ፡፡ ለማጥናት ብዬ ቸርች ኳየር እንደምቀር ነገር ማለት ነው፡፡ ወር ይሞላኛል፣ ሳልሄድ ቆይቼ ስሄድ፡፡ ከሰኞ ቅዳሜ፣ ከቅዳሜ ሰኞ እሄዳለሁ ስል አንድ ቅዳሜ ሄድኩኝ፡፡ ህዳር 4 ነበር ቀኑ፡፡ ኳየር የማልሄድ ጊዜ ተመችቶኝ፣ ይሄ ጭንቀት ትቶኝ ነበር፡፡ ያው ወደ ድሮው ማንነቴ ባልመለስም ማለት ነው፡፡ ቢያንስ የት/ቤት ጓደኞቼ “ናቲ ሁሌ እንደሳቀ ነው፣ ደስተኛ ነው” እንዲሉ ማድረግ ችዬ ነበር፡፡ ኳየር ስሄድ ፈይሳ ነበር ፕሮግራሙን እየመራ የነበረው፡፡ እንዴ የተወኝ መስሎኝ፡፡ አንገቴን ይሞቀኝ ጀመር፡፡ ፈይሳ ነቃ፡፡ እኔን አይቶ ፊቴን ማየት አስጠላችሁ አንዴ? ልውጣላቹ? ለምን አትዘምሩም? ምናምን ይላል፡፡ እውነት እኔ እሱን ጠልቼ ነው እንዴ የምጨናነቀው? እሱ ቢወጣ ይተወኛል? ብዬ ራሴን ጠየቅኩኝ፡፡ “ችግር ካለባችሁ ለኮሚቴ ደውላችሁ መንገርና ችግራችሁን መፍታት ትችላላችሁ፡፡ እንጂ ቂም ይዛችሁ ኳየር ውስጥ አትቀመጡ”፡፡ ቂም ይዤለሁ ማለት ነው? እኔንጃ፡፡ በፊት ሊሆን ይችላል፡፡ ያን ቀን ሁሉም ነገር የኔ ችግር እንደ ሆነ አምኜ ነበር፡፡ ቂም ብይዝም ባልይዝም ግን ተጨናንቄ የነበረው በሱ ምክንያት የነበረ አይመስለኝም፡፡ በፈይሳ ምክንያት ተጨናንቄ ፊቴ የተቀየረ ቢሆን እንኳን እሱ ቢወጣ ይተወኝ እንዳልነበር እርግጠኛ ነኝ፡፡ ከዚያ ትንሽ ቆይቶ ያለፈውን ቀን ያልመጣችሁ ቁሙ አለ፡፡ ያልመጣን ቆምን፡፡ የኔ ያው የተለየ ችግር ነው፡፡ ያለፈውን ቅዳሜ ቀን ብቻ ሳይሆን ያለፈውን ከወር በላይ ሙሉ አልሄድኩም፡፡ ምክንያታችሁን ተናገሩ ተባለ እንግዲህ፡፡ተናገሩ ተናገሩ፡፡ እኔ ምን ልበል? ኳየር መምጣት አስጠልቶኛል፣ ያስጨንቀኛል፣ ዛሬ ስለመጣሁ ራሱ ልትገረሙ ይገባል ልበል? ሌላ ምክንያት አልመጣልህ ሲለኝ “ምክንያቴ አይጠቅማችሁም” አልኩኝ፡፡ ንገረን የኳየሩ ባህል ነው” ምናምን አለኝ፡፡ ከዚያ “ኳየር የክብት በረት አይደለም፣ ወይ አትምጣ፣ ወይ በስርአቱ ና፡፡ መቅረት አይቻልም” አለኝ፡፡ አቢቲ “አንተ ና፣ አትምጣ ልትለኝ አትችልም በለው” አለኝ፡፡ አላልኩም፡፡ እሱ የሚለውን ብሎ ሲጨርስ ለኳየሩ ”እኔ እንድታውቁልኝ የምፈልገው፣ ለት/ት ብዬ ኳየር ቀርቼ አላውቅም” አልኩኝ፡፡ ፈይሳ ያለው ነገር ከኔ የበለጠ እነአቢቲን ነበር ያስቆጣው፡፡ እኔ ለምን አልተናደድኩም?

ህዳር 18 ማስታወሻዬ ላይ እንዲህ ብዬ ነበር ስለህዳር 4 የጻፍኩት፡፡

ከዛ የኳየራችን ህግ ነው ምናምን ብሎ ሊጨቀጭቀኝ ሞከሮ ተወና(እዚህ ጋር ኳየር ውስጥ ተናግሬ ስለማላውቅ በጣም ልቤ እየመታ ነበርና የሚሰነዝርብኝን ጥቃት ለመከላከል አልቻልም ነበር፡፡) በተለይ ፐሪፐ ገባን ብላችሁ ኳየር የምትቀሩ ልጆች ጊዜአችሁን ብትጠቀሙ ይሻላችኋል፡፡ ቢበዛ ሁለት አመት ነው ያላችሁ፣ ዩኒቨርሲቲ ትሄዳላችሁ አለ፡፡ በተለይ ደግሞ ናቲ አለ ወደኔ ዞሮ፡፡ እንዲያውም ኳየር አትምጣ፡፡ ኳየር የክብት በረት አይደለም፡፡የእግዚአብሔር ቤት ነው፡፡ የምትመጣ ከሆነ ደግሞ መቅረት አይቻልም፡፡ Kuwaayerii hin dhufiin(ኳየር አትምጣ) ሲል ያልደነገጠ ሰው ያለ አይመስለኝም፡፡ ይሄ ፈይሳ እንኳን የኳየሩ ኮሚቴ ቀርቶ፣ የቄስ ኢብሳን ቦታ ተክቶ የቤተ-ክርስቲያኒቱ መሪ ቢሆን እኔን ከኳየር የመከልከል መብት እንዳሌለው አሳምሬ አውቃለሁ፡፡ ማን ስለሆንክ ነው አትምጣ የምትለኝ፣ ቤትህ መሰለህ እንዴ አትምጣ የምትለኝ? ኮሚቴ መሆን ኳየሩን መግዛት መሰለህ እንዴ? እኔ እንደ ሌሎቹ የማካብድህ መሰለህ? ልለው እችል ነበር፡፡ ግን ቦታው አልፈቀደልኝም፡፡ ቦታው እንደፈልኩ የማወራበት ቤቴ ወይም ት/ቤቴ አልነበረም፡፡ ጉደቱ ኳየርን ኳየራችን ወይም የኛ ኳየር ለማለት የፈጀብኝን ጊዜ እኔ ነኝ የማውቀው፡፡ ኳየር ውስጥ እንኳን ተናድጄ እንደዛ መናገር፣ ዝም ብዬ አንዷን ሰአት መቀመጥ እራሱ በጣም ነበር የሚከብደኝ፡፡ ከዚያ አቢቲ አትምጣ ብለህ ልትከለክለኝ አትችልም በለው አለኝ፡፡ እኔ ግን ፈይሳ ተናግሮ ሲጨርስ የተናገርኩት “እኔ እንድታውቁልኝ የምፈልገው፣ እኔ ለት/ት ብዬ ኳየር ቀርቼ አላውቅም”፡፡ ከኳየር ስንገባ አቢቲ እኔ ሰው እንደዚያ ሲለኝ መታገስ አልችልም አለኝ፡፡ “አይ ትክክል ነው፡፡ አጥፍቻለሁ” አልኩት፡፡

ያን ቀን ፈይሳ እንደዚያ ሲለኝ በውስጤ ሲመላለስ የነበረው፣ “ከዚህ በኋላ ኳየር ተመልሼ እመጣለሁ ወይስ አልመጣም?” የሚለው ጥያቄ ነበር፡፡ ለአቢቲ እንዲህ አልኩት፡ ከዚህ በኋላ አልመጣም፣ ድሮም ለማቆም እፈልግ ነበር ምክንያት አገኘሁ”፡፡ እንደ ባለፈው አመት አያንቱ ሰድባኝ እንዳቆምኩት፡፡ ያቺ ሀሙስ ህዳር 11 2007 ዓ.ም. ነበረች፡፡ ህዳር ጠላቴ ነች ልበል? ያን ቀን የወሰንኩት ኳየር ለማቆም ብቻ አይደለም፡፡ ከዚያች ቀን ወዲህ እግሬ ያንን ቸርች እንዳይረግጥ ለራሴ ቃል ገባሁ፡፡ ማንም የማይሰብረው ቃል!! ከዚህ በኋላ የማልሄደው አስካሁን የተጎዳሁትን ያካክሰዋል፡፡ ኳየር ስጀምር አወጣጤ እንዲህ ይሆናል ብዬ አስቤ አላውቅም ነበር፡፡፡ እኔ ኳየር የማቋርጠው ዩኒቨርሲቲ ስገባ ብቻ ነው ብዬ ነበር ሳስብ የነበረው፡፡ በኔ ከኳየሩ መለየት ልጆች አዝነው፣ ስጦታ ሰጥተውኝ፣ ጸልየውልኝ ብዬ ነበር የማስበው፡፡ ነገር ግን እንኳን በኔ ከኳየሩ መውጣት ሊያዝኑ፣ ከተከዘው፣ ከዝምተኛው፣ ጭንቀታሙ፣ ፈሪው ማንነቴ ባለፈ በትንሹ እንኳን ትክክለኛን ማንነቴን አላወቁትም፡፡ እንኳን ኳየር ይኸው ቸርችም አቆምኩ፡፡ ካሁን በኋላ እሁድ እሁድ ጠዋት የሚቀርበኝን ሙሉ ወንጌል እሄዳለሁ፡፡ አሁንስ ትክክለኛው ማንነቴ የቱ እንደሆነ ራሱ ግራ እየገባኝ ነው፡፡ አቡሽ “ከሁለቱም ጫፍ አለህ” ይለኛል፡፡ በነጻነት ሰውን ታሳፍራለህ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ጭንቀታም ነህ፣ ከሁለቱም ነህ ይለኛል፡፡

በነጋታው እሁድ ሁለገብ አዳራሽ ጥሩ ውጤት ላመጡ ልጆች ሽልማት ነበረ፡፡ ከአቡሽ ጎን ነበር የተቀመጥኩት፡፡ የትናንቱ ትዝታ ረብሾኝ ነበር፡፡ አቡሽን ፊቴን አንብብ አልኩት፡፡ ሊስቅ የተዘጋጀ ሰው ትመስላለህ አለኝ፡፡ እኔ ግን በጣም ጨንቆኝ ነበር፡፡ ከሰአቱን ከሱ ጋር ስንገናኝ “ጸሀይ ምንድነው ናቲ ሽልማቱን ሲወስድ ደስተኛ አይመስልም ነበር” አለችኝ አለ፡፡ እኮ ጠይቂህ ነበር አልኩት፡፡ የሚያሳዝነው ደስተኛ ለመምሰልና ለመሳቅ ሞክሬ ነበር፡፡ ያን ቀን 1000 ብር ተሸለምን፡፡ ከዚያ በፊት 700፣ ከዚያ በኋላ አዳማ ጉዞ ወደ ሶስት ሺህ ብር፣ ከአዳማ መልስ ደግሞ አሁንም 1000 ብር፡፡ ስትሬቱን ለነሱ ያመጣን አስመሰሉትኮ፡፡

መጀመሪያ ጭንቀት የጀመረኝ ያው ቸርች ነው፡፡ አስረኛ ክፍል ት/ት ሲጀመር ይተወኛል አልኩኝ፡፡ ት/ቤትና ቸርች እየተቀባበሉ አሰቃዩኝ፡፡ ከዚያ ቸርች ባቆም ይተወኛል አልኩኝና ስተው ያው ዋናው ልቤን ሲያስጨንቃት የነበረው ተወኝ፡፡ ግን ትቶ አልተወኝም፡፡ ት/ት ሲዘጋ ይተወኛል አልኩኝ፡፡ አልተወኝም፡፡ ት/ት ሲጀመር ይተወኛል እያልኩ ወደ ኳየር ተመለስኩ፣ ካስ፣ እነማቲ፡፡ ት/ት ተጀመረ፡፡ በተለይ ቸርች በማልሄድባቸውና ካቆምኩ ወዲህ ሁሉም ነገር እንደ እቅዴ እየሄደ ነበረ፡፡ ግን ጥቃቅን ነገሮች ይረብሹኝ ነበር፡፡ ውህይት ሀውስ፣ ጓደኞቼ የሚሰሩብኝ ተንኮል፣ ብቻ ጥቃቅን ነገሮችን ሳስብ ደሜ ይፈላል፡፡ ከዚያ በእውነቱ ከመቱ ካልወጣሁ ወደ ራሴ መመለስ እንደማልችል ማሰብ ጀመርኩ፡፡ ቸርች ለሁለተኛ ጊዜ አቆምኩ፣ ምንም እንኳን ከጓደኞቼ ጋር ጥሩ ጊዜ እያሳለፍኩ የነበረ ቢሆን ከመቱ ካልወጣሁ ደስተኛ መሆን እንደ ማልችል እርግጠኛ እየሆንኩ መጣሁ፡፡ ለጓደኞቼም፣ ለቤትም ሁሌ መቱ እንዳስጠላችኝ ነበር የማወራው፡፡ ቤት እንደዛ ስል አንተ እንዲህ ስትል ሌላ ሰው እንዳይሰማህ ይሉኝ ነበር፡፡ ጓደኞቼ ደግሞ ምንድነው ይሄን ያህል ይሉኝ ነበር፡፡ አቡሽ እንዲያውም አፍ አውጥቶ፣ አንተ የምትለው ጭንቀት ምንም አይገባኝም ይለኝ ነበር፡፡ አዎ ማንም አይገባውም፡፡ ዩኒቨርሲቲ የምገባበትን ጊዜ እየናፈቅኩ ነበር አዳማ እንደምንሄድ የሰማሁት፡፡ አምስታችን ስትሬት ያመጣን ልጆች፡፡ ባጭሩ ምርጥ ጊዜ ነበር ያሳለፍኩት፡፡ 2002 ላይ ነበር አዳማም መንገድም የሄድኩት፡፡ ለመጨረሻ ጊዜ ከመቱ ወጥቼ በሄድኩባት ከተማ 5 ቀናት፡፡ አምስት አስገራሚ ቀናት፡፡ በጣም ነበር የተመቸኝ፡፡ ስንሄድ ዘፈን እያዳመጥኩ ነበር የሄድኩት፡፡

ብቻ ምርጥ ጊዜ ነበር፡፡ ከጓደኞች ጋር መብላት፣ መሄድ፣ ከቤተሰብ ቁጥጥር ስር መውጣት፣ መንገድ ላይ ሰው ሰላም ሳይለኝ አለፈ ብሎ መናደድ አለመኖሩ፣ ለአምስት ቀን ሳይናደዱ መቆየቱ ይመቻል፡፡

አዳማ እያለን አንዴ ከአንድ ምግብ ቤት ውጪ ላይ ምሳችንን በልተን ተቀምጠን እያወራን ነው፡፡ ከኛ መሀል አብዱ ውህይት ሀውስ ግሩፐ ነበረና ያን ሰሞን(ያን አመት) በት/ቤታችን ወሬው ሁሉ ውህይት ሀውስ ነበረ፡፡ ከመሀላችን አንድ ሰው ውህይት ሀውሳችሁ በጣም ነው የሚያስጠላኝ አለ፡፡ የቀሩት ሁለቱም ተከተሉ፡፡ በጣም ነው ማታስጠሉት፡፡ አብዱ ምንም አላለም፡፡ ሰው እንደ ሚጠላቸው የሚያውቅ ይመስላል፡፡ ባይጠሉ ነበር የሚገርመው፡፡ በጣም በሚገርም ሁኔታ ተጋንነው ነበር፡፡ በጣም ታዋቂ ሆነው ነበር፡፡ እኔ ደግሞ “እኔ ግን በጣም ነው ምትመቹኝ፣ ከናንተ የሚደብረው ምን መሰለህ?” ብዬ እእ እስኪል ጠበቅኩት፣ እእ ሲልልኝ “የሚደብረው እኔ ግሩፓችሁ ውስጥ አለመኖሬ ነው” አልኩት፡፡ እኔ ያለፈውን አመት ግባ ብዬ ስጠይቅህ እምቢ አላልከም? አለኝ፡፡ አላልከኝም አልኩት፡፡ እርግጠኛ ይመስላል፡፡ ረስቼው ይሆናል(እንዲህ አይነት ነገር የሚረሳ አይነት ሰው ከሆንኩ)፡፡ እኔ የነሱ ግሩፕ አባል የመሆን እድል ነበረኝ፡፡ ከሰው ጋር እንዴት መሄድ እንዳለብኝ ስለማላቅ ይሆናል፡፡ እነኛ ልጆች(ኢዩኤል፣ በረከት፣ ሙባረክ) ይፈሩኛል፡፡ እኔ ኢዩኤል ነህ፣ በረከት ነህ፣ ሙባረክ ነህ ብዬ ሰውን ማካበድ አላውቅም፡፡ ሁሌ እራሴን የቻልኩ ነኝ፡፡ ሌላ ሰው እንደጭራ ሲከተላቸው እኔ እንዲህ አይነት ባህርይ የለኝም፡፡ እንዲያውም በልጆች ፊት ሰድቤአቸው እንደማልፈራቸው ማሳየት ደስ ይለኛል፡፡ በፊት፣ ሌሎች ለምን እንደሚያካብዷቸውና እንደሚፈሯቸው ነበር የሚገርመኝ፡፡ ከዚያ እኔ ራሴ ለምንድነው ሰው ወደ ፈሰሰበት የማልፈሰው? ብዬ እራሴን መጠየቅ ጀመርኩ፡፡ እነሱን እንዳለማክበሬ ደግሞ ከነሱ ጋር መሆን ባልፈልግ፣ ብጠላቸው ጥሩ ነበር፡፡ ግን እኔ የነሱ ቡድን አባል መሆን ስታተስ ላይ የሚጨምረውን ነገር እያሰብኩ እናደድ ነበር፡፡

መስከረም መግቢያ ምዝገባ ሳይጀመር አንድ ቀን ኢዩኤል በፌስቡክ ከመሬት ተነስቶ ገደል ግባ ብሎ ሰደበኝ፡፡ መልእክቱ ገብቶኛል፡፡ ምን አረግኩህ አልኩት፡፡ ሰደበኝ፡፡ ምንም ቢሆን አብረን ያሳለፍናትን ጥሩ ጊዜ አትርሳ... አልኩት፡፡ በእንግሊዘኛ ነበር፡፡ ጥሩ ተናጋሪ ነህ አለኝና (ደደብ) ብሎ ሰደበኝ፡፡ ጥሩ ተናጋሪ መሆኔን አውቃለሁ አንተም ከደደብ በጣም እንደምሻል ታውቃለህ አልኩት፡፡ ናቲ የሆነ ነገር ሳልነግርህ አለኝ፡፡ ምንድነው? ደደብ እንዳልከኝ ነው? አልኩት፡፡ አዎ ጎበዝ ነህ አለኝ፡፡ ከዚያ እያልን እያልን ትግሉን ከኔ ክልል ወደሱ አድርጌ ዘረርኩት፡፡ በስድብ አጣጥፌ አስቀመጥኩት፡፡ እሱ በጀመረው ካንተ ጋር መሰዳደብ ተመችቶኛል ቀጥል ብዬ ብለምነው ዝም አለ ራሱ እንዳልጀመረው፡፡ በነጋታውም እንደገና ፌስቡክ ላይ አግኝቼው እንቀጥል አልኩት፣ ዝም፡፡ ነጥቡ ማን መሰዳደቡን ያሸንፋል አይደለም፡፡ እኛ ጋር እንዳትገባ የኮድ መልእክት እያስተላለፈልኝ ነበር፡፡ ከዚያ በኋላም ተገናኝተን ባንደበቱ እኛ ጋር አትግባ ባክህ ብዙ ልጆች ገብተዋል ብሎኛል፡፡ ምክንያቱን ስለማውቅ ለምን እንዲህ ትላለህ ኢዩኤል ሁለት ድፍን አመታት አብረን ተምረን አላልኩትም፡፡ ይገባኛል፡፡ ማንም በሚያከብሩት ሰዎች ፊት ከሚያሸማቅቀው ሰው ጋር መግባት አይፈልግም፡፡

አዳማ የሄድን ጊዜ የኦሮሚያ ተቃውሞ ከአምቦ መቀጣጠል የጀመረበት ጊዜ ነበር፡፡ ስንመለስ አብዱ ለረጅም ሰአት መንግስትን እያማረረ ነበር፡፡ እኔ ምን አርጉ ነው የምትለው? ማስተር ፕላኑኮ ባዲሳባ አጠገብ ያሉትን የኦሮሚያ ነዋሪዎች ለመጥቀም የተዘጋጀ ነገር ነው አልኩት፡፡

ዝም በል ባክህ ብሎ በቃ ይናደዳል፡፡ አንተኮ ቪኦኤና ኦኤምኤን ሞልተውህ ነው አልኩት፡፡ አንተ ራስህ ኢቲቪ ሞልቶህ ነው አለኝ፡፡ ከብዙ ክርክር በኋላ ምንም እንደ ማይለወጥ ገብቶኝ ዝም አልኩት፡፡
እኔ አዳማ ስሄድ እንደዛ ፈታ ማለቴ በጣም ነበር ያስገረመኝና መቱ መቱ ስል የነበረው ነገር እውነት መሆኑን ያረጋገጥኩት፡፡ ቤት አዳማ እንዴት እንደ ተመቸችኝና ከመቱ እውነትም ለኔ ከፉ እንደ ሆነች ነገርኳቸው፡፡ ከጓደኛዬ ከአሊ ጋር አረንጓዴ ማርከር ተውሼ በልሙጥ ወረቀት ላይ “LIFE OUT OF METTU IS SO BRIGHT” ብዬ ፅፌ የመኝታዬ ግርግዳ ላይ ለጠፍኩኝ፡፡ ከሶስት ቀን በኋላ ከቤት አይተው ንቀለው አሉኝ፡፡ ነቀልኩት፡፡

ት/ቤት ክፍላችን የሞት ምድብ ነበረ፡፡ ብዙ ጎበዝ ተማሪዎች፡፡ ሰው ጎበዝ ተማሪዎች መሀል ሲሆን ተፎካክሮ የበለጠ ጎበዝ ይሆናል አይደል? እኔ ግን ከአቋም በታች እየተንቀሳቀስኩ ነበር፡፡ ነገ ፈተና ያለንን ዛሬ ሌሊት ለማጥናት ተነስቼ፣ ትንሽ እንዳጠናሁ ምናባቱ ከአቡሽ እሰራለሁ፣ ከእገሌ እሰራለሁ እያልኩ መተኛት ጀመርኩ፡፡ እንደዚያ ስል ግን እንዳሉ የክፍሌ ልጆች ጎበዝ ስለ ሆኑ ነው እኔ ማንበብ ያቆምኩት ማለት አይደለም፡፡ አዎ በተለይ ከአዳማ ከተመለስን ወዲህ ምን እንደ ነካኝ አላውቅም ማንበብ አስጠላኝ፡፡ አቆምኩኝ በቃ፡፡ ለማንበብ ሌሊት ሁሌ እንደ ተነሳሁ ነው ግን እተኛለሁ፣ ወይ ፌስቡክ፡፡ ፈተና ከነአቡሽ፣ ከነዳንዲ፣ ከነአብዱሌ ሆነ፡፡ እንዳንሰራረቅ ብለው ቦታ ቢቀያይሩ እንኳን እኔ ያው የስትሬት ባለቤት ስለ ሆንኩ ሄደው ከጎበዙ ጋር ነው ፊት ለፊት፣ ከሆነ ፊት ለፊት የሚያስቀምጡኝ፡፡ አስተማሪን ማዳመጥ ድሮም ያን ያህል አልነበርኩም፡፡ በዚህኛው አመት ግን እንግሊዘኛና ሲቪክ ብቻ ነበር የማዳምጠው፡፡ ሌላውን ስንተኛ ዩኒት ላይ እንደ ሆነ አላውቅ፣ ምንም አልሰማም፣ ሳወራ ነው የምውለው፡፡ ልጆች አፍህን አይደክምህም እንዴ? ይሉኝ ነበር፡፡ የ10ኛ ክፍሉን እየተበቀልኩ ነበር መሰለኝ፡፡

ህዳር 17 ኦሊ አብረን ብቻችንን መንገድ ላይ እየሄድን እንዲህ አለኝ፡ አንተ ለብቻችን ስንሆን የምታማርርብኝ ነገርህ ሰለቸኝ፡፡ እገሌ እንዲህ እንዲህ አረገኝ ትላለህ፡፡ ለምን እንዲህ እንዲህ አርጌ ደስ አለኝ አትልም? በአንድ ቀን ከገጠሙህ ነገሮች በጣም ጥቂት የደበረህ ነገር አዕምሮህን ይሞላዋል አለኝ፡፡ እውነቱን ነው፡፡

ያቺ 9ኛ ክፍል ላይ ሳጣጥማት የነበረችው እንቅልፍ ናፍቃኛለች፡፡

አንድ ቀን ክፍል ውስጥ እኔ ኬነሳ፣ ሲሳይ፣ ሚያ ሆነን እያወራን እኔ “በፊት መጽሐፍ ማንበብ ጀመርኩና ይዞኝ ሄደ፣ ከዚያ ፊልም፣ አሁን ደግሞ ዘፈን” ስል ሚያ “ወደ ፊት ደግሞ ምን እንደሚሆን እናያለን” አለች፡፡ ፈገግ አልኩኝ፡፡ በርግጥ እኔ ከሁሉም በፊት ልቤን ያጠፋሁት ለት/ት ነበር፡፡ ፊልም እያየሁ ነበር፡፡ ቤተሰብ መምሪያ ላይብረሪ መሄድ ስጀምር ቋጥር አንድ አንባቢ ሆንኩኝ፡፡ ቀስ በቀስ ለት/ት ያለኝ ፍላጎት እየቀነሰ መጣ፡፡ ዲሽ ስንገዛ ፕሮፌሽናል የፊልም ተመልካች ሆንኩኝ፡፡ እራሴን እንደ ተመልካች ብቻ ሳይሆን እንደ ፊልም ሃያሲ ነበር የምቆጥረው፡፡ አልፎ አልፎ አሁንም አነብ ነበረ፡፡ ከዚያ ያለፈውን ክረምት ዘፈን ማዳመጥ ጀመርኩ ወሬዬ ሁሉ ስለ ዘፈን ሆነ፡፡ አስተማሪ እያስተማረ ኢርፎን ሰክቼ እስከ ማዳመጥ ነበር ያበድኩት፡፡ ይኸኔ ለፊልም ያለኝ ፍላጎት ቀነሰ፡፡ ት/ት ደግሞ አቅለሸለሸኝ፡፡ ይሄን ጊዜ ህይወት እሬት እሬት እያለችኝ ነበር፡፡ ከመቱ መውጣት ምንንም እንደ ማይፈታ እየገባኝ ነበር፡፡ የአዳማው አጋጣሚ ነው፡፡ አንድ እኔን ሊቀይር የሚችል ነገር እራሴን መቀየር ነው፡፡ ሰዎች እንዲህ አታድርግ እንዲህ አድርግ ብለው ይመክሩናል፡፡ ግን ያ ነገር በህይወታችን ልናደርግ የማንችለው አንድ ነገር ይሆናል፡፡ ለምሳሌ የአሊ ምክር፡ ስለ በጎው ማሰብ፡፡

አንዴ ዝም ብዬ ጎረቤታችን ገመቹ በፍላሽ ያሳለፈልኝን መአት መጽሐፍት ስበረብር አንድ እንግሊዘኛ የሳይኮሎጂ መጽሐፍ አገኘሁ፡፡ አነበብኩት፡፡ ተመቸኝ፡፡ መጽሐፏ ትንሽ ነች፡፡ እስከ ግማሽ ድረስ አነበብኳት፡፡ የአዕምሮ ባለሙያ ብሆን እንደሚዋጣልኝ ነበር ያሰብኩት፡፡ በፊት ያነበብኩትን ነገር እንደ ማንበብ ነበረ፡፡ የሆነ የማውቀው ነገር እየመሰለኝ ነበር ያነበብኩት፡፡

ከዚህ በኋላ ማስታወሻዬ ላይ የጻፍኩት በብዛት ስለ ማህበራዊ ኪሳራዎቼ ነው፡፡ አሊን አዕምሮውን መርዤ መርዤ እኔ ባልነግረው የማያስባቸውን ነገሮች እንዲያስብ አድርጌ እሱ በኋላ እኔ በነገርኩት በዚሁ ነገር መጥቶ እኔን እንደ ሚጎዳ እያወቅኩኝ ባደረግኩት ነገር ይጎዳኝ ጀመር፡፡ ስለ ጓደኞቼ ማሰብ፣ ብቻ ውድቀት የሚለው ቃል ይግለጸው፡፡፡ የሌላ ሰው አዕምሮ መመረዝ ስለ ማልፈልግ ነው፡፡ብቻ ብዙ ማሰብ ጥሩ አይደለም፡፡ አመቱ በሚገርም ሁኔታ እያስገረመኝ ቀጠለ፡፡ እንዲህ እንዲህ እያለ የሴሚስቴሩ የፋይናል ፈተና ደረሰ፡፡ አንድ ቀን ከዮናስ ጋር ለሱ ጫማ ልንገዛ ሄድንና አንድ ጫማ ቤት ባለቤቱ አንባቢ ነበርና አንድ አብዮቱና ትዝታዬ የሚል መጽሐፍ እያነበበ ነበር፡፡ እስኪ መጽሐፉን አልኩት፡፡ የዚህ ዘመን ልጆች ጫማ ምናምን ከማለት ሌላ የሀገራችሁን ታሪክ አታውቁም አታነቡም ምናምን አለ፡፡ አይ እኔ አነባለሁ አልኩትና መጽሐፉን እንዲያውሰኝ ጠየቅኩት፡፡ ሲጨርስ እንዲያውሰኝ ተቀጣጠርን፡፡ መጽሐፉን ከሳምንት ነው ከሁለት ሳምንት በፊት ሰይፉ ሾው ላይ ደራሲው የደርግ ምክትል ፕሬዝዳንት ቃለ-መጠይቅ ተደርጎለት መጽሐፉን ባገኘው ብዬ ስመኘው ነበር፡፡ ሰውየው አዋሰኝ፡፡ አብዮቱና ትዝታዬ፣ በሌ/ኮ ፍስሀ ደስታ፡፡ የስድስት መቶ ገጽ የሀገሬ ታሪክ፡፡ አነበብኩት፡፡ አነበነብኩት፡፡ ባጭሩ ስለ ደርግ የማወቅ ጥሜን ነበር የቆረጠው፡፡ ስለ ሐይለስላሴስ ቢሆን? ያንን መጽሐፍ አንብቤ የጨረስኩት የፋይናል ፈተና በሚጀምርበት ቀን ነበረ፡፡ ምንም አልተዘጋጀሁም ማለት ነው፡፡ ለወጉም እንኳን፡፡ ከዚያን ጎረቤታችን ገመቹ ክረምት ያሳለፈልኝን መጽሐፍት አሁንም ዝም ብዬ ስበረብር አንድ መጽሐፍ ከፍቼ(ገልጬ) ማውጫውን ሳይ በረከት ስምኦን የሚል ርእስ አይቼ አጓጉቶኝ ቶሎ ሄጄ አነበብኩት፡፡ አንደ ርእሱ ስለ በረከት ስምኦን አሪፍ ተደርጎ ነበር የተጻፈው፡፡ ሚስጥር ነው እንዳለ፡፡ ያስቃል፡፡ ስለ በረከት ስምኦን ካነበብኩ በኋላ የመጽሐፉን ርእስ አየሁ፡፡ የጋዜጠኛው ማስታወሻ በተስፋዬ ገብረአብ፡፡ ዛሬ ነገ ሳልል መጽሐፉን ከመጀመሪያው ማንበብ ጀመርኩ፡፡ ሌላ ወጣቶች ይሄን መንግስት እንደ ሚጠሉት ለመጥላት እፈልግ ነበር፡፡ ግን የምሰማቸው ነገሮች አሉባልታ እንጂ እውነት አይመስሉኝም ነበር፡፡ ኦኤምኤንና ቪኦኤን ውሸታም ብዬ ፈርጄአቸው ነበር፡፡ እንዲህ አይነት ሊያሳምነኝ የሚችል መጽሐፍ ማንበብ እፈልግ ነበር፡፡ ስለ መለስ ስለ ህወሃት ስለ አባ ዱላ ስለ

ኦፒዲኦ ስለ ኦነግ ሳነብ ምንም የማላውቅ እንደ ነበርኩ አመንኩ፡፡ ጭንቅላቴ ሊፈነዳ ነበር የደረሰው፡፡ ለመለስ የነበረኝ ፍቅርና ክብር በጥላቻ ሲተካ ይታወቀኝ ነበር፡፡ ይሄ ከይሲ፡፡ እኔ ለካስ እውነቱን ውሸት፣ ውሸቱን እውነት ብዬ ተቀብዬ ነበር፡፡ መጽሐፉን በሁለት ቀን ጨረስኩት፡፡ ያቺ መጽሐፍ አይነ-ጥላዬን የገፈፈች ስለ ነበረች አንዴ ስለ ተስፋዬ ገ/አብ ፌስቡክ ላይ ተጽፎ "Tesfaye is my ahun aye ayne" ብዬ ኮሜንት ማድረጌ ትዝ ይለኛል፡፡ ተስፋዬን በጣም አደነቅኩት፡፡ ጎበዝ ጸሐፊ ነው፡፡ ሌላም የቡርቃ ዝምታ የሚል መጽሐፍ ነበረ(ው)፡፡ እሱን እንኳን ፈተና ጨርሼ ላንብብ ብዬ ፈተና ሲያልቅ ነበር ያነበብኩት፡፡ በርግጥ የተስፋዬ መጽሐፍም የተጨማመሩበት የውሸት የፈጠራ ሀሳቦች እንዳሉበት አንብቤአለሁ፡፡ ሆኖም ግን እኔ ማወቅ የሚገባኝን አውቄአለሁ፡፡

እኛ ፈተና ላይ እያለን እናቴ ያለ ወትሮዋ ቶሎ ከቢሮ ገብታ፣ እቴቴኮ አረፈች አለችኝ፡፡ አይኗ ቀልቶ ነበር፡፡ ደከማ እንደ ነበረም ነግራኝ ነበር፡፡ ሬሳ ከአዲሳባ ነው እንግዲህ የሚመጣው፡፡ ተነስተው እንደ ሆነ ጠየቅኳት፡፡ ተነስተዋል ማታ ነው የሚገቡት አለችኝ፡፡ ብዙ ሰው ነበር ካዲሳባ የሚመጣው፡፡ ወንድሜና ጓደኛው አቤል ፈተና ስለ ነበረባቸው አልመጡም፡፡ ያኔው እንደ ሰማሁ ሮጬ ራሄል ጋር መሄድ እንደ ነበረብኝ አውቀዋለሁ፡፡ አላረግኩትም፡፡ እዚያ ሆኜ ሬሳ መቀበል እንደ ነበረብኝም አውቀዋለሁ፡፡ ግን አላረግኩትም፡፡ ማድረግ ያለብኝን ነገር ባለ ማድረግ አባዜ የተለከፍኩበት አመት ነበር፡፡ ሁለት አመት፡፡ ውድ አንባቢ፣ 1000% ማድረግ ያለብህን ነገር እያወቅክ አለማድረግ የሚያመጣው መከራ ምን ያህል እንደ ሆነ ፍንጩን የለህም፡፡ መሆን እንዳለብኝ እየሆንኩ እንዳልሆነ እያሰብኩና በራሴ እያፈርኩ በነጋታው ጠዋት ሁለት ሰአት ላይ ሚጣን ይዤ ለቅሶ ቤት ሄድኩኝ፡፡ በጣም ያሳዝናል፡፡ እኛ ዘመዶቻችንን አናውቅም፡፡ አሁን ከቤተሰቤ ቀጥሎ ቢሞት የማዝንለት፣ የማለቅስለት ሰው ማናለ? ዘመዶቼን አላውቃቸው፡፡ ከሩቅ ዘመድ የቅርብ ጎረቤት አይደል የሚባለው? በተለይ ለኔና ለወንድሜ እቴቴ ካክስት በላይ ነች፡፡ እኔ ግን እንዳክስት አላለቀስኩላትም፡፡ ስንሄድ ግቢ ውስጥ ሰው ሞልቶ ነበር፡፡ ከሚጣ ጋር ከሰው ተገፋፍቼ ወደ ሳሎኑ በር ጠጋ አልኩኝ፡፡ ከቤት ውስጥ እያለቀሱ ነበር፡፡ ወጣቶች የነማቲ ጓደኞች ይታዩኛል፡፡ ማንናቸውም የኔን ያህል ለእቴቴ አይቀርቧትም፡፡ ከማናቸውም በላይ እዚያ ቦታ ላይ መሆን የነበረብኝ እኔ ነበርኩ፡፡ ግን እንደ ማንም እቴቴን መንገድ ላይ ደህና ነሽ ብሎ የሚያልፋት ሰው ውጪ ግራ ገብቶኝ ቆሜአለሁ፡፡ በጓሮ በኩል መሄድ እንደ ምችል አውቀዋለሁ፡፡ ግን ፈራሁ፡፡ ምን እንደምፈራ አላውቅም፡፡ እዚያው ቆሜ አለቀስኩ፡፡ እቴቴ ብታየኝ ምን ትለኝ ይሆን? አባቴን ቤት ውስጥ ሳየው ነበር፡፡ መጣና በጓሮ ሂድ አለኝ፡፡ ሚጣን ደግሞ ፈተና ታርሞ ትወስድ ነበረና ወደ ት/ቤት ላክናት፡፡ በጓሮ ሄጄ ኮሪደር መሀል ሰው ብዙ ነበርና ኮሪደሩ መሀል ግርግዳ ተደግፌ ቆምኩኝ፡፡ አለቀስኩኝ፡፡ ወይኔ...! እቃ ቤት ውስጥ ራሄልን አንዲት ልጅ ስታባብላት ይታየኛል፡፡ ብዙም ሳይቆይ ወደ ቀብር መሄድ ተጀመረ፡፡ ባጭሩ እቴቴን ሄደን ቀበርን፡፡ ያን ቀን አርብ ነበረ፡፡ ከሰአት ፈተና ተፈትነን ወደ ማታ እንደ ገና ለቅሶ ቤት ሄድኩኝ፡፡ እነማቲን፣ እነማሬን፣ ራሄልንም ሰላም አልኳቸው፡፡ ካዲሳባ ከነማቲ ጋር የመጡትን የማሙሽን ወንድም ምናምን፡፡ ሄጄ ቶሎ ነበር ወደ ቤት የገባሁት፡፡ ማደር ነበረብኝ፡፡ ቀጣዩን ቀን ጠዋትም ሄድኩኝ፡፡ በጣም እየደበረኝ፣ መሄድ ስለ ነበረብኝ ብቻ ነበር ስሄድ የነበረው፡፡ ከሰአት ሚጣ ሄደች፡፡ በጣም ነበር የተመቻት፡፡ እሷ የራሷንና የኔንም ድርሻ ሸፍና ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ከዚያ ሁለት ወይም ሶስት ቀን ነበር የሄድኩት፡፡ አስጨናቂ ቀናት፡፡ ቤት ጭንቀቴን በቡርቃ ዝምታ ለመርሳት ሞከርኩ፡፡ እንዲህ አይነት ነገር ካስረኛ ክፍል ወዲህ አይሰራም፡፡ ከዚያ ወዲህ ከዚያ ቤተሰብ ጋር እንደ ተቆራረጥኩ ነው የሚሰማኝ፡፡ ከዚህ በኋላ እነሱ ቤት መሄድ አልፈልግም፡፡

"ህይወቴን መቱ ውስጥና ከመቱ ውጪ ብዬ የመከፋፈል እቅድ ነበረኝ፡፡ አሁን ግን ከ2007 ፊትና በኋላ ብዬ ነው የምከፋፍለው፡፡ አሁን ከመቱ መውጣት ልዩነት ያለው አይመስለኝም፡፡ ችግሬ ኳየርም አይደለም፣ ት/ቤትም አይደለም፣ ልጆችም አይደሉም፣ እኔው ራሴ ነኝ ችግሬ፡፡ ትናንት ዘፈን ማዳመጥ አቆምኩ፡፡ እግዚአብሔርን አሳዝኜአለሁ፡፡ አሁን ወደ እግዚአብሔር መመለስ እፈልጋለሁ፡፡ በቃልና በጸሎት ራሴን ማጎልበት ያለብኝ ጊዜ ነው፡፡" ብዬ የጻፍኩት መጋቢት 24፣ 2008 ዓ.ም. ነበረ፡፡ በርግጥ ይሄ የጸሎት እቅዴ ቸርች ባቆምኩ ማግስት የመጣ ነው፡፡ ቤተ-ክርስቲያን ያቆምኩትን ለማካካስ፡፡

መጋቢት 24 ቀጥዬ ማስታወሻዬ ላይ፡ ያለፉት አራት ወራት በመላው ኦሮሚያ የመንግስት ተቃውሞ ነበረ፡፡ በተለይ በት/ቤቶችና በዩኒቨርሲቲዎች፡፡ እስካሁን 500 ያህል ሰዎች(ወጣቶች) በመንግስት ታጣቂዎች ተገድለዋል ይባላል፡፡ ብዙዎች ታስረዋል ሀገሪቱ ጭንቅ ውስጥ ነች፡፡ የዚህ መንግስት የ25 አመት አገዛዝ ፍጻሜዋን ልታገኝ ትመስላለች፡፡ ያለፈው ሴሚስቴር መጨረሻ አካባቢ የኛ ት/ቤትም የዚህ ተቃውሞ አካል ሆና ነበር፡፡ ተጮኸ፣ ድንጋይ ተወረወረ፡፡ በነጋታው አስተማሪዎች ሰብስበው ሀሳብ አቅርቡ አሉን፡፡ ያኔ 100% የመንግስት ደጋፊ ነበርኩ፡፡ የተስፋዬ መጽሐፍት ከመንግስት መቶ በመቶ ደጋፊነት ወደ መቶ በመቶ ተቃዋሚነት ቀየሩኝ፡፡ የትኛውና አስቤው የማላውቀው ኦሮሞነቴ ተቀሰቀሰ፡፡ ተቀስቅሶ እንደ ማያውቅ ሁሉ፡፡ ተዋጋ ብባል ለመዋጋት የቆረጥኩበት ጊዜ ነበር፡፡ ለምንድነው የሚኖረው? ታግለህ ራስህን ነጻ ማውጣት ነው እንጂ 25 አመት ደምህን ከጠባ ሙትቻ፡፡

አንደኛ ሴሚስቴር 82 አምጥቼ 9ኛ ወጣሁ፡፡ አይገባኝም ነበር፡፡ ያለፈውን ክረምት የመለስን የት/ት ፖሊሲና ስትራቴጂ ሳነብ በጣም ብዙ ነገር ነው ያወቅኩት፡፡ እንደ ተማሪነቴ ፖሊሲዎቹና ስትራቴጂዎቹ ተፈጻሚነታቸው ምን ያህል ነው የሚለውን መገምገም አይከብደኝም፡፡ ያለውን እቅድና ተፈጻሚነቱን ሳነጻፅር አርቃቂውን መለስ ከማድነቅ ያለፈ የታዘብኩት ነገር ቢኖር በትክክል ቢተገበር ምን አይነት ት/ቤቶች ሊኖረን እንደሚችል፣ ምን አይነት የማስፈጸም አቅም እንደ ሚኖረን ነበር፡፡ ይሄ ነገር በፊትም የማሰላስለው ነበር፡፡ ፈረንጆች ለምን እንደዚያ ደሳስ የሚሉ ፊልሞች ይሰራሉ፣ እኛ ለምን አቃተን? በፊት በፊት እዚያ ሰው ታለንቱን እያየ ነው የሚሰራው እኛ ጋር ግን የመሰለንን ነው ምንማረው ለምሳሌ እኔ ሶሻል መግባት እያለብኝ ናቹራል ገባሁ፡፡ እኛ ጋር ባጋጣሚ ነው፡፡ ሳስበው ፈረንጆች ሲያወሩ በጣም በሚገርም ሁኔታ

ነው፡፡ እኛ ጋር ፖለቲከኛ ነኝ ባዩም፣ ጋዜጠኛውም ሁሉም የሚያወራውን ነገር አያውቅም፡፡ ስለሆነ ነገር እያወራ ወሬ ይዘባርቃል፡፡ ሁሌ ቲቪ አይቼ አይቼ ለቤቶች ቆይ እንዲህ ማለት ምን ማለት ነው? እንዴት እንዲህ ብሎ ተነስቶ እንደዛ ይላል፡፡ እኔ ብሆን እንዲህ ነበር የምለው እያልኩኝ የሚያወሩትን እተቻለሁ፡፡ ቲቪ ላይ ብዙ ሰው ተሰብስቦ ስለ አንድ ጉዳይ እያወራ አንድ ደህና ሀሳብ የሚያነሳ ሳጣ ምንድነው ችግራችን ብዬ ራሴን እጠይቅ ነበር፡፡ የኛ ዶክተሩ፣ ፕሮፌሰሩ፣ ፖለቲከኛ ነኝ ወሬ እችላለሁ ብሎ የሚጎርር ኡላ ዝም ብሎ ቀፎ ነው፡፡ ፈረንጅ ሀገር እንዲሁ ጋዜጠኞች ሰዎችን ስለ ሆነ ጉዳይ ቃለ-መጠይቅ ሲያረጉ ሳይ በቃ የሚያወሩት ነገር ይገርመኛል፡፡ የአንድ የትንሽ ሆቴል ቤት አስተናጋጅ ስንት ጊዜ እኛ ሀገር ምሁር ነኝ ከሚል ሰው የበለጠ ምክንያታዊና ምሁርም ጭምር ነው፡፡ የሆነ ጊዜ ዘር ነው ብዬ ራሴን ለማሳመን ሞክሬ ነበር፡፡ እና ቋንቋ፡፡ እንግሊዘኛ ሀሳብ ለመግለጽ ስለሚመች ነው ብዬ አስብ ነበር፡፡ ውጪ ሀገር በጣም ምሁራን እንደሆኑና እኛ በጣም ጥልቅ መሀይምነት እንዳለብን የኛ ልዩነት የሰማይና የምድር ልዩነት እንደ ሆነ እየገባኝ ነበር፡፡ በፊት በፊት ጠንክረን ከሰራን በአስር አመት አሜሪካ የደረሰችበት መድረስ የሚቻል ይመስለኝ ነበር፡፡ ከቲቪ፣ ከኢንተርኔት ከተለያዩ አጋጣሚዎች ተነስቼ ፈረንጆች በጣም ስማርት እንደ ሆኑ ተገነዘብኩ፡፡ ኢትዮጵያ ደግሞ እንደ ድህነቷ ነች፡፡ የመጨረሻ ደሀ ነን፣ የመጨረሻ መሀይሞች ነን፡፡ ቀስ በቀስ የዚህ ሁሉ ቁልፍ ችግርና ምክንያት ት/ት እንደ ሆነ ገባኝ፡፡ ት/ቤት ስለምንማርበት ሁኔታ፣ ስለ አስተማሪዎች ማሰብ ጀመርኩኝ፡፡ ሁሌ አስተማሪ እንዳማረርን ነው፡፡ ሁሌ በት/ቤቶች ውስጥ ችግር አለ፡፡ ተማሪዎች፣ እኔ ከአስተማሪ እገሌ እሻላለሁ ማለት አለ፡፡ እኔ 2007 ላይ ያነበብኩት፣ 1994 ላይ የተጻፈ ግሩም መጽሐፍ አለ፡፡ ያ ፖሊሲና ስትራቴጂ ለምን ተግባራዊ አልሆነም? ነገሮች ለምን እንደተጻፈው አልተፈጸሙም? ምክንያቱም መለስ ጻፈ፣ እስከ አስተማሪና ተማሪ ድረስ ስንትና ስንት እርከኖች አሉ፡፡ ለማስፈጸም አስፈጻሚ ይፈልጋል፡፡ መጽሐፉ በራሱ ቢሮ ውስጥ የሚቀመጡ ሰዎችን ስለ ማጎልበት አቅማቸውን ስለ ማሳደግ ነው የሚናገረው፡፡ እንደ ሚመስለኝ ከሆነ ያ መጽሐፍ ብቻውን ጮኸ፡፡ መጽሐፉ ላይ የተጻፉ ነገሮችን ለማስፈጸም በራሱ ብቁ ስራ አስፈጻሚ ይፈልጋል፡፡ ታዲያ እኔ ብዙ ሀሳቦች ጭንቅላቴ ውስጥ ይመላለሱ ጀመር፡፡ ማን ሀገሩ አድጋ ማየትን ይጠላል፡፡ እኔ ተማሪ ነኝ፡፡ መለስ ከፍተኛው የሀገራችን ባለ ስልጣን ነበር፡፡ የእሱ ፖሊሲ እኔን መንካት ነበረበት፡፡ እሱ እንደ ሀገር መሪነቱ በተጠቃለለ መንገድ ነበር ፖሊሲውን ማርቀቅ የነበረበት፣ እኔ ደግሞ መለስ ያረቀቀው ፖሊሲ ተግባራዊ ቢሆን ት/ቤቶች እንዴት ሊሆኑ ይችሉ እንደ ነበር በሚያሳይ መንገድ መጽሐፍ መጻፍ ጀመርኩኝ፡፡ ሁሉም ነገር ከት/ቤት ስለሚጀምርና የተማርንበት ት/ቤት ማንነታችንን እንደ ሚወስነው ስለ ገባኝ ብዙ መለሶችን እንዴት መፍጠር እንደ ሚቻል ነበር መጻፍ የጀመርኩት፡፡ በዋነኛነት ሃይስኩል ላይ ነበር ያተኮርኩት፡፡ ነገሩ ግን ለሁሉም የት/ት ደረጃ የሚጠቅም ነበር፡፡ ርእሱን ሃይስኩል(Hi SCHOOL) አልኩት፡፡ የምንጠላውን ት/ቤት የምንወደውና ከልቡ ት/ቤት ስለ ማድረግ እንዲመስል ነው Hi ያደረግኩት፡፡ የአስተማሪዎች፣ ስለ እያንዳንዱ የት/ት አይነት… ስለመልመጃዎች፣ ስለ ኩረጃ፣ በት/ቤታችንም ሆነ በየትኛውም ት/ቤት የጋራ ስለ ሆኑ ችግሮች አንስቼ መፍትሄዎቻቸውን ለማስቀመጥ እየሞከርኩኝ ነበር፡፡

ሚያዝያ ውስጥ የማሙሽ እህት ሊሊ በመኪና አደጋ ሞተች፡፡ በጣም የሚያሳዝን ሞት ነበር፡፡ ህጻን ልጇቿን ለባሏ ጥላ፡፡ ሌላ መገኘት በነበረብኝ ቦታ ያለመገኘት ታሪክ ይቀጥላል…

ፌስቡክ መጎርጎርን ዋነኛ ስራዬ አደረግኩ፡፡ የሆነ ሰው ፌስቡክ ሄይ ቤቶች የተባለ እኔ ስገባ ከ50 ሺ በላይ አባላት የነበሩት ግሩፕ ውስጥ እንድገባ ኢንቫይት አደረገኝ፡፡ በብዛት የሃይስኩል ተማሪዎች ሲሆኑ፣ የአዲሳባ፣ የብዙ ቦታ የኢትዮጵያ የነገ ትውልዶች ነበሩበት፡፡ ከሙቱ ውጪ ያሉ ኢትዮጵያውያን ወጣቶችን አስተሳሰብ ለመገምገም ጥሩ አጋጣሚ ነበር፡፡ በዋነኛነት የሚያማምሩ ልጆች ፎትቶአቸውን የሚለቁበትና ታዋቂ የሚሆኑበት ግሩፕ ሲሆን ያልጠበቅኩት፣ ተገላልጠው ፎቶ የሚለቁ ሴት ልጆች ይበዙ ነበር፡፡ የመሀል ጣታቸውን እያሳዩ የሚለቅቁ፣ እየተሳሳሙ…፡፡ ካሰብኩት በላይ በውጪ ዘፋኞች የተወረሱ ልጆች፣ ፊልም ጠጥተው የጠገቡ የሚመስሉ ታዳጊዎች፡፡ ዝነኛ የመሆን ጥማት የተጠናወታቸው ወጣቶች ”don’t make stupid people famous”, “I,m not famous but…” የሚሉ ልጆች፡፡ ለሆሊውድ በጣም የተጋለጡ፡፡ ከሁሉም የገረመኝ አንድ ተለቅቆ ያየሁት ፎቶ ነው፡፡ ልጁ በእጁ የሰይጣን የቀንድ ምልክት ሰርቶ ጭንቅላቱ ላይ አድርጎት ነው ፎቶውን ተነስቶ የለቀቀው፡፡ ኮሜንቶቹን ለማንበብ ተጣደፍኩ፡፡ አንዳንዶች ይገስጹታል፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ፎቶ መነሳት ማለት ከልብ ማድረግ አይደለም ይሉታል፡፡ ለማንኛውም ምንድነው እየተዘራብን ያለው ብዬ እንድጠይቅ አድርጎኛል፡፡

የፖለቲካ ሙቀቴን ፌክ አካውንት በመክፈት ማስተንፈስ ጀመርኩ፡፡ ጀዋር መሀመድ ፖስት በሚያረጋቸው ነገሮች ላይ፣ የተለያዩ ነገሮች ላይ ኮሜንት እሰጣለሁ ያለምንም ፍርሀት፡፡ አንድ ጀዋር በለቀቀው ነገር ላይ ኮሜንት አድርጌ ከመቶ በላይ ሪፐላይ ነበረው፡፡ ….Atrevolution ነበር ስሜ፡፡ በፖለቲካ ማእበል ተመታሁ፡፡ ፌስቡክ ነው፣ ስልኬን መጎርጎር ነው፣ ኦኤምኤን ተዘግቶ ነበረ፣ ቪኦኤን ማዳመጥ ነው፡፡ በቃ ራሴን እንደ ፕሮፌሽናል ፖለቲከኛ ነበር የምቆጥረው፡፡ ግለቱ ኢንካርታ ላይ ያነበብኩትን የአሜሪካ ሪቮሊውሽንን ማቀጣጠያ ክብሪት ተብላ የምትታወቀው ጽሁፍ ርዕስ የሆነችውን “give me liberty or give me death” የምትል ቀስቃሽ አባባል ት/ቤት ክላስ ፐላዝማ ስታንድ ላይ እስክጽፍ ድረስ ነበር፡፡

በዚያው የፖለቲካ የሚዲያ አውታሮችን እነቢቢሲን በፌስቡክ ላይክ አደረግኩ፡፡ የተለያዩ የውጪ ታዋቂ ሰዎችንም ጭምር፡፡ እነኛ ሰዎችና ሚዲያዎች የሚለቋቸው ነገሮች ላይ ሰዎች ከሚሰጧቸው ኮሜንቶች ስለ ውጪ ሰዎች ብዙ መረዳት ችያለሁ፡፡ አንድን ነገር ጫፏን ይዤ የማስፋፋት ባህርይ አለኝ፡፡

ወደ መንፈሳዊ ነገሬ ለመመለስ ሳስብ የክርስትያን ጣብያዎችን እነኤልሻዳይን፣ እነሲጂን ማዳመጥ ጀመርኩ፡፡ ብዙ የክርስትናም ሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት የለኝም ግን አንዳንዴ የሚሰበኩ ነገሮች አይዋጡልኝምና እውነት ቃሉ እንዲህ ይላል ወይ? ብዬ ራሴን እንድጠይቅ ያደርጉኝ

ነበር፡፡ በፊት በፊት የነታምራት ታረቀኝ ፈውስ ውሸት ነው ሰዎቹ ብር ተከፍሎአቸው ነው ይባል ነበር፡፡ ቼክ ለማድረግ ሞከርኩ፡፡ ውሸት ከሆነ አሪፍ አሪፍ ተዋንያን አሉን ማለት ነው ብዬ ውሸት ነው ማለት እንደ ማያዋጣ ተረዳሁ፡፡ ሰዎች ተፈውሰው ሲመሰክሩ እናያለን፣ እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብ ጀምሬ ነበር፡፡ በጣም ደስ ይላል፡፡ እንደ በፊቱ አይደለም፡፡ በፊት አልፎ አልፎ ሳነብ ምንም ስሜት አይሰጠኝም ነበር፡፡ በአስራ አንደኛ ክፍል ሁለተኛ ሴሚስቴር ግን እየገባኝ ነበር፡፡ እናቴ ሁሌ መጽሐፈ ምሳሌን አንብብ ትለኝ ነበር፡፡ እጀምረው እጀምረውና ለወላጆች ስለ መታዘዝ ጠቢብ፣ ሰነፍ...እያነበብኩ ምንም ትርጉም አይሰጠኝም ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ ግን መጽሐፍ ቅዱስ እየተገለጠልኝ መጣ ስል እየተመካሁ አይደለም፡፡ መጽሐፈ ምሳሌ በጣም ነው የገረመኝ፡፡ ያንተን ታሪክ ሲነበብ ካንተ በላይ ታሪኩን ሊረዳና ሊገባው የሚችል ሰው የለም፡፡ መጽሐፈ ምሳሌን ሳነብ እንደበፊቱ ሳይሆን ድራማ እየሰራሁ ያለሁ ነው የመሰለኝ፡፡ ስክሪብቱ የተጻፈ እኔ ግን ያላነበብኩት፣ ግን ሳላነበው እየተወንኩት ያለሁት ድራማ፡፡ መጽሐፈ ምሳሌ ስለኔ ነው ማለት እችላለሁ፡፡ እኔ የማስባቸው ነገሮች፣ ሌላ ሰው ያስባቸዋል፣ ብዬ የማላስባቸው ነገሮች፣ ስላሳለፍኩት ህይወት፣ መጽሐፈ ምሳሌ እየነገረኝ ነበረ፡፡ ብቻ ገረመኝ፡፡

11ኛ ክፍል ቴንክስ ጊቪንግ ቀን ላይ የአስረኛ ክፍል ጓደኛዬ ሄለን በፌስቡክ እንዲህ ብላ ሜሴጅ ላከችልኝ፡፡

“One day I may die without saying goodbye to you. But I won’t forget to say thank you. You’ve given me one of the loveliest friendships ever in my life. Hard is to find a friend like you that can be a real bro. so I choose to thank you for everytime you made me smile. I apologize for everytime I was rude. Thank you for becoming the big part of my small life.”
“አንድ ቀን አንተን ሳልሰናበት እሞት ይሆናል፡፡ ግን “አመሰግናለሁ” ማለትን አልረሳም፡፡ በህይወቴ ጣፋጭ ከምላቸው ጓደኝነቶች አንዱን ሰጥተኸኛል፡፡ እንዳንተ አይነት እውነተኛ ወንድም መሆን የሚችል ጓደኛ ማግኘት በጣም ይከብዳል፡፡ ስለዚህ ፈገግ ስላስደረግከኝ ጊዜያት ሁሉ ላመሰግንህ መርጫለሁ፡፡ ለጎዳሁህ ጊዜያት በሙሉ ይቅርታን እጠይቅሃለሁ፡፡ የትንሽዋ ህይወቴ ትልቅ ክፍል ስለሆንክ አመሰግናለሁ፡፡”

ደስ አይልም? እውነታው ሄለን እኔን አለማወቋ ነው፡፡ እውነት ነው በጣም ተጫዋች ነበርኩ፡፡ እውነት ነው ከሄለን ጋር በጣም ተመቻችተን ነበር፡፡ እውነት ነው ሄለን ለልጆች “ናቲ የዋህ ነው ምንም አያውቅም” ብላለች፡፡ እውነታው ግን ያ እኔ ሳልሆን እኔ ሄለንን እንድመስላት የፈለግኩት ሰው ነው፡፡ ቀልደኛ ምንም ክፉ የማያስብ ተጫዋች የዋህ ሰው የለም? ይቀልዳል እንጂኮ ምንም አያውቅም አይነት? እንደዚያ ነው የቀረብኳት፡፡ እኔም እንደዚያ ነበረ ራሴን የማስበው፡፡ እውነትም ተጫዋች፣ ተወዳጅ ልሆን እችላለሁ፡፡ ግን የዋህ አይደለሁም፡፡ በጣም ሰውን መመርመር የምወድ የሰው ክፋት ሰውየው ቆዳ ስር ገብቼ የማይ ተጠራጣሪ ሰው ነኝ፡፡ ከሰው አንደበት ለሚወጡት ተራ ቃላት ዋጋ እየሰጠ የሚመረምር ሰው በፍጹም የዋህ ሊባል አይችልም፡፡ በራሱ የቃላት መረጣ ግን የዋህ ሊመስል ይችላል፡፡

በውጪ ሀገር ዲፕሬሽን በጣም የተለመደ ነገር እንደ ሆነ ገባኝ፡፡ ሁሉም የብቸኝነት ህይወት ነው የሚመራው፣ ስራ ነው፣ ማንበብ ነው እንደዚህ፡፡ እኛ ደግሞ እንዲህ አይነት ነገር የለንም፡፡ ስናወራ መዋል ነው፣ ከፍተኛ ማህበራዊ ህይወት አለን፡፡ ጥያቄዬ የነበረው፣ ት/ቱን፣ ልማቱን ከነሱ ወስደን እንደነዚህ አይነት በነሱ ዘንድ ባህል የሆኑ የብቸኝነት ህይወትና ጭንቀታምነት ማስቀረት እንችላለን ወይ? የሚለው ነበር፡፡ ጥያቄው ያለንን ማህበራዊ ትስስር ማቆየት እንችላለን ወይ? የሚል ነበር፡፡ ይሄን ጉዳይ አንድ ጊዜ በኢቢኤስ ርዕዮት ላይ ሲያወሩ ሲያወሩ ውለው አጓግተውኝ ለዚህ ጥያቄ መልስ ሳይሰጡ ነበር የተውት፡፡ በዚያን ጊዜ፣ እኔ ግን መልሱን አግኝቼ ነበር፡፡

አንድ ቀን ቪኦኤ ላይ የዙቤይዳና የዶክተር አሸበር ደራሲ የሆነው አሌክስ አብረሃም ተጋብዞ የመጠጥ ማስታወቂያዎች ወጣቱ ትውልድ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሊያሳድሩ እንደሚችሉ ሲናገር ነበር፡፡ ከዚያ በፊትም አንድ ፓናል ውይይት ላይ “አንበሳ ቢራ” ሲባል ይሄን እየሰማ የሚያድግ ልጅ ሲያድግ ምን ሊሆን ነው ሲባል ሰምቼአለሁ፡፡ ማስታወቂያ እኔ ላይ ተጽእኖ ያረጋል ማለት ነው? አልኩኝ፡፡ የማያቸው ፊልሞች፣ በቲቪ የማያቸው ነገሮች እኔ ላይ ተጽእኖአቸው ምን ያህል ነው? ብዬ እራሴን መጠየቅ የጀመርኩት ያን ሰሞን ነበር፡፡ በፊት እንዲሁ ለመዝናናት እንጂ ለሌላ ነገር አይደለም የማየው፣ ቢሆንም ጥሩውን ወስጄ ክፉውን እተወዋለሁ አይነት አስተሳሰብ ነበር የነበረኝ፡፡ ቴሌቪዥን ላይ የማያቸው ነገሮች በጣም ትኩረቴን ይስቡ ጀመር፡ ኤልሻዳይ ላይ የማያቸው ሰዎች ወሬ፣ የተለያዩ ቻናሎች፡፡ በኤልሻዳይ የወጣቶች ፕሮግራም አዘጋጇ ሰው ለሰው ድራማ ላይ የፍሬዘር ሚስት የምትሆነዋና መለከት ላይ አለማየሁ ታደሰን የምታስቸግረውን ጴንጤ ተዋናይ ከቤተ-ክርስትያኗ ፓስተር ጋር ትጋብዛቸዋለች፡፡ በቤተ-ክርስትያን አርት እንዴት ነው የሚታየው? አርት ጥሩ ነገር ነው በሚለው ነበር የተስማሙት፡፡ ጥላሁን ጉግሳ ሲጄ ቲቪ ላይ ቀርቦ አርት ማለት ይላል፡ ይሄን ሳውንድ ሲስተም አለማውያኑ ለዘፈን ይጠቀሙታል፣ እኛ ደግሞ ለበጎ ነገር መጠቀም እንችላለን ይላል፡፡ ቤቶች ላይ የዘሩ ጓደኛ ሆኖ የሚተውነው ፕሮቴስታንት ተዋናይም፡ ጥበብ የማናት? ሲጀመርኮ ጥበብ የእግዚአብሔር ነች፡፡ የቤተ-ክርስትያን ነች፡፡ ጥበብ ቤተ-ክርስትያን ውስጥ አያስፈልግም ማለት የቤተ-ክርስትያንን ንብረት ለአለም አውጥቶ መስጠት ነው ይላል፡፡ ከዚህ ሁሉ እኔን የሳበኝ ግን የኤልሻዳይ ቲቪ የወጣቶች ፕሮግራም አዘጋጅ ያካፈለችው ገጠመኝ ነበረ፡፡ ደቡብ አፍሪካ የነበርኩ ጊዜ ነው አለች፡፡ ያው ፕላዝማ ከደቡብ አፍሪካ አይደል የሚተላለፈው? “ፕላዝማ ላይ ሰሌዳ እያጸዳሁ እንድቀረጽ ተመረጥኩኝ አለች፡፡ እሺ ብዬ ከተስማማሁ በኋላ አንድ ሰውዬ መጥቶ ተይ አትስሪው፣ እንዲህ አይነት ነገር የአለማውያን ነው አለኝ፡፡ ከዚያ ተውኩኝ፡፡ አሁን ነው ሰውየው ትክክል እንዳልነበረ የተገነዘብኩት፡፡ በዚያች አጋጣሚ ብዙ እድሎችን ላገኝ እችል ነበር፡፡ ያው ግን አሁንም ቢሆን ቲቪ ላይ ነኝ አለች፡፡” እኔ ደግሞ ሰውየው ትክክል ቢሆንስ? አልኩኝ፡፡
በኤልሻዳይ ላይ አንዴ ስለ ዘፈን ይከራከራሉ፡፡ ዘፈን ችግር የለውም የሚለው፣ ልቦለድ ታነቡ የለ፣ ዘፈን ምን ችግር አለው? ብሎ ይጠይቃል፡፡

የአፒል ፎር ፒዩሪቲዋ ዶክተር መስከረም ደግሞ ከኤልሻዳይዋ በለጡ ጋር እያወሩ፣ እኔ ት/ቤት ፎር ማምጣት ብፈልግ፣ ከሁሉም ሙብለጥ ፈለግኩ፣ ሁሉንም በልጬ አንደኛ መሆን ፈለግኩ ማለቴ ስለሆነ ሀጢአት ነው ትላለች፡፡ አስቤው አላውቅም ነበር ግን እውነትነት አለው፡፡ በህይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ እውነትን መመርመር ፈለግኩኝ፡፡ ጀመርኩኝ፡፡

ስለ ፈረንጆች ዲፐሬሽን ሳስብ የጭንቀቱ ምክንያት፣ በጣም የተጋነነ መዝናኛ እንደ ሆነ ገባኝ፡፡ ወጣቱ እንደኔው ቲቪ ስር ተጎልቶ ስለሚውል፣ አሪፍ አሪፍ ፊልሞችን ስለሚያይ፣ ጌሞች አሉ፣ ኮምፒዩተር አለ፣ ጓደኛ አያስፈልገውም፣ የሚያወራው ሰው ሲያጣ ያ ሰው ሀሳቡን የሚያካፍለው እውነተኛ ከነኑ ተቀምጦ የሚያናግረው ሲያጣ ለአስከፊ ጭንቀት ይጋለጣል ነበረ ድምዳሜዬ፡፡ በጣም ብዙ ሰዎች የዚህ ችግር ሰለባ ከሆኑ ለምንድነው መንግስታት ችግሩን ለመቅረፍ የማይሞክሩት? ለምንድነው ፖለቲከኞች ይሄን አስቀያሚ ስሜት የሚያጠፋ መፍትሄ በምርጫ ቅስቀሳቸው ላይ የማያነሱት ብዬ ራሴን ስጠይቅ ነበር፡፡ ችግሩ እንዳለ አያውቁም? የማይመስል ነገር፡፡ የአሜሪካ ምርጫ እየተቃረበ ነበር፡፡ ፊልም ለማየት ቻናል እየቀያየርኩኝ አይቼ የማላውቀውን ቢቢሲና ሲኤንኤን ላይ ፕራይመሪ ዲቤት ሲደረግ ድንገት አይቼ እዚያው ላይ አረግኩት፡፡ ወደ መጨረሻው ነበርና ብዙ ሳላይ አለቀ፡፡ አስራ አራት ሪፐብሊካኖች ነበሩ የሚከራከሩት፡፡ ቴድ ክሩዝና ዶናልድ ትራምፕ ነበሩበት፡፡ ክርክሮቹን ለማየት ብዬ ከዚያን ቀን ወዲህ ፊልም ለማየት ስል ቢቢሲና ሲኤንኤንን ቼክ ማድረግ ጀመርኩኝ፡፡ አንድ ቀን እንዲህ ቼክ ሳረግ የአንድ ላቲን አሜሪካ ፕሬዝዳንት ቢቢሲ ሃርድቶክ ላይ ቀርቦ ሲያወራ አየሁት፡፡ ገረመኝ፡፡ ከየት አምጥቶ መልሶቹን እንደ ሚመልስ ደነቀኝ፡፡ ጋዜጠኛውም አይቻልም፡፡ ፕሬዝዳንት ነው ብሎ ማክበር የለም፣ እያወራ ካፉ ቀምት፣ እኔ የፕሬዝዳንቱ ቦታ እሳቀቃለሁ፣ ፕረዝዳንቱ የሆነ ነገር ሲያወራ፣ ጋዜጠኛው አቋርጦ ስለሱ አውቃለሁ አሁን ጥያቄዬን መልስልኝ YES or NO?! የፕሬዝዳንቱ ሀገር አንድ የማላስታውሰውን የድራግ(ሀሺሽ) አይነት ህጋዊ ስለማድረግ ነበር እየተወያዩ የነበሩት፡፡ የሆነ ሰሞን ሃርድ ቶክ አያመልጠኝም ነበር፡፡

በሌላ ጊዜ ደግሞ ቅዳሜ ማታ ወደ 12 ሰአት አንድ ተመልካች ያሳተፈ ክርክር፡፡ ተመቸኝ፡፡ ብሬግዚት መጣ፡፡ ሲኤንኤንና ቢቢሲ ላይ የሚሰጡ ትንተናዎችን ተቀምጬ መጠጣት ጀመርኩ፡፡ እኔ ስለ ማላውቀው ስለ ኢኮኖሚ ምናምን ሲያወሩ ሰለሚያወሩት ነገር ጉግል አርጌ ለመረዳት ሞከርኩ፡፡ ሂላሪና ትራምፕ የመጨረሻ የምርጫ ተፎካካሪዎች ሆኑ፡፡ ንግግራቸውን ማዳመጥ፣ መሰጠኝ፡፡ ሚጣ አሁን ደግሞ ቢቢሲ፣ ተቃጠልን፣ እስኪ ፊልም ላይ አርገው እያለች ትጨቀጭቀኛለች፡፡ የጋዜጠኞቹንማ አያድርስ ነው፡፡ በዚያች ጊዜ ውስጥ ሳይሆን የሚናገሩትን ነገር እድሜ ልካቸውን አጥንተው የሚናገሩ ነው የሚመስሉት፡፡
ያን ሰሞን ማታ ማታ ቪኦኤ ላይ በኦሮምኛና በአማርኛ ስለትራምፕና ሂላሪ ፉክክር ሰው ጋብዘው ትንታኔ ይሰጥበት ነበር፡፡ እና እኔ በጣም ፉክክሩን ስከታተል ስለነበረ ሆነ አላውቅም፣ የሚሰጡት ትንታኔ በጣም ያናድደኝ ነበር፡፡ እኔ ከነሱ አስር እጥፍ የበለጠ አሪፍ አርጌ አብራራላቸው ነበር ብዬ ቤት ውስጥ መናገሬ ትዝ ይለኛል፡፡

የሆነ ጊዜ ዱባይ ዋን ላይ ግራውንድ ብሬከርስ የሚል ፕሮግራም በየሳምንቱ ቅዳሜ ማታ ወደ አንድ ሰአት እንደሚተላለፍ ማስተዋወቅ ጀመሩ፡፡ የአለማችንን ታዋቂ ካምፓኒዎች ስለ መሰረቱ ሰዎች የኋላ ታሪክ፣ ማለትም ከየት ተነስተው አሁን የደረሱበት ደረሱ ስለሚለው በየሳምንቱ አንድ ሰው እየመረጠ ነው ፕሮግራሙ በዶኩሜንተሪ መልኩ የሚያቀርበው፡፡ የፌስቡኩ ማርክ ዙከርበርግ፣ የአፕል መስራች፣ ባለ ናይክ ጫማ፣ ቢል ጌትስ ትዝ የሚሉኝ ናቸው፡፡ እንዳለመታደልና እንዳለማስታወስ ሆኖ እኔ ያየሁት የመጀመሪያውንና ስለ ማርክ ዙከርበርግ የቀረበውን ዶኩሜንተሪ ብቻ ነበረ፡፡ ከሁሉም የሳበኝ፣ ይሄ ጋዘጠኞች ህዝብ ፊት ማርከን ሲያነጋግሩት ድንግጥግጥ ብሎ ላብ በላብ ሆኖ ሹራቡን ሲያወልቅ የሚያወጣው በጃኬቱ ውስጠኛው በኩል የኢሉሚናቲ አርማ ጋዜጠኞቹ ጃኬቱን ተቀብለው ለህዝብ ገሀድ ያወጡበት ነው፡፡ ብዙ ጥያቄ ነበር የፈጠረብኝ፡፡ ፌስቡክ ለምን ኢሉሚናቲ ሆነ? ያው የሰይጣን ከሆነ የሆነ ችግር አለበት ማለት ነው፡፡ አርማው ላይ ኮኔክት ዘ ዎርልድ ይላል፡፡ አለምን ማስተሳሰር ምንድነው ችግሩ? መቼም ሰይጣን የሚሰራው ጥሩ ነገር የለም፡፡ አለምን መንደር ከማድረግ ጀርባ የተሸረበውን ሴራ ማወቅ ፈለግኩ፡፡ እኔ እዚህ ተቀምጬ ውጪ ያለን ሰው እንደ ልቤ ማግኘቴ ምንድነው ችግሩ?

ቃና ቲቪ ስርጭት ሲጀምር ዘ11ኛ ክፍል፣ የትምህርት አመት ሊገባደድ ሰሞን ነበር፡፡ እኔ ታዲያ እንደ አንድ ፊልም እንደሚወድ ሰው ቃና ሲመጣ አልተደሰትኩም፡፡ ምክንያቱም ቃና የጀመረበት ጊዜ፣ እኔ ስለፊልሞች መመራመር የጀመርኩበት ስለ ነበረ ነው፡፡ የሆነ ጊዜ ፊልም ሰሪ እሆናለሁ ስል የነበርኩት ሰውዬ ፊልሞች ምን ያህል አደገኛ እንደሆኑ ማሰለላሰል የጀመርኩበት ጊዜ ስለነበር በቃና መምጣት እንደ መደሰት ተናደድኩኝ፡፡ የሰዎች ለቃና የነበራቸው አቀባበል ግን ከልክ ያለፈ ብቻ ሳይሆን አስፈሪ ነበረ፡፡

አንድ ቀን በኤልሻዳይ ቲቪ ቄስ ዶ/ር ገመቹስ ስለ ሴኪዩላሪዝም ክፋት ሲያወራ ሰምቼ ጉግል ማድረግ ጀመርኩኝ፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት በት/ቤቶች ውስጥ ሊሰጥ ይገባል እያለ ነበር፡፡ አለማችን ላይ ሴኪዩላሪዝም የሚሉት ነገር ያደረሰውን ተጽእኖ ለማወቅ ብዬ "history of secularism" ብዬ ሰርች ሳደርግ ያልጠበቅኩትን ነገር ነበር ያገኘሁት፡፡ ዊኪፒዲያ ላይ ላቼቴ ምናምን የሚል ጽሁፍ አነበብኩኝ፡፡ ላቼቴ ማለት ማንም የፈለገውን ሀይማኖት የመከተል ሙብት አለው የሚል ሀሳብ ያለው ቃል ነው፡፡ ከዚህ ቀጥዬ ያነበብኩት ደግሞ "ያልጠበቅኩት" ነበረ፡፡ ጸሀፊው እንዲህ በማለት ይጀምራል፡ "የአለምን ታሪክ መመርመር ከፈለግክ ፍሪሜሰን ከሚል ቃል ጀምር" ይላል፡፡ ዳርዊኒዝምን(Evolution theory)(ሰው የመጣው በዝግመተ ለውጥ ከዝንጀሮ ነው፣ አለም ጥቂት ሺህ አመታት ሳይሆን 3.6 ቢሊየን አመት እድሜ አስቆጥራለች የሚለው ቲዮሪ) Evilution theory/devilution theory ይለዋል፡፡ ይሄ ቲዮሪ የሰይጣን ተረት ተረት እንደሆነና ሰይጣን ይሄን ቲዮሪ ሲያስተዋውቅ ያኔ የሰው ልጅ ዳግም ወደቀ ሲል ጽሁፉ ያስረዳል፡፡ ሰዎች ራሳቸውን እንደ እንስሳት መቁጠር ጀመሩ... የት/ቤት

ካሪኩለም ውስጥ ከትተው ህጻናት በእግዚአብሔር ላይ ያላቸው እምነት እንዲሸረሸር እንዳደረጉ ይገልጻል፡፡ ጸሀፊው ይሄን ቲዮሪ ከተማረ ወዲህ ለእግዚአብሔር ያለው እምነት እንደጠፋ ይናገራል፡፡ እኔንም ወደዚያ 5ኛና 6ኛ ክፍል ወደምማርባቸው ጊዜያት መለሰኝ፡፡

ብታምንም ባታምንም በነጋታው የት/ቤት መጽሐፍ ለመመለስ ከዮናስ ጋር ሄድን፡፡ መጽሐፍቶቹን በቦርሳ ይዘን ነበር የሄድነው፡፡ ለካስ እዚያ ስንደርስ ዮናስ ቦርሳው ውስጥ ረስቶ ይዞ የመጣው አንድ መጽሐፍ ነበረ፡፡ የመጽሐፉ ርእስ ምን ቢሆን ጥሩ ነው? የሽፋን ገጹ የተገነጠለ ነበር፡፡ ኢሉሚናቲ የሚል መጽሐፍ፡፡ ሳነበው በጣም እንደምፈልግ ነግሬ መጽሐፉን ተዋስኩት፡፡ ሳነበው፣ ለማመን ያዳግታል ልሽሽ ብል እንኳን የማልችለው እውነት፡፡ “If something happened, in politics it was planned.” (Theodore Roosevelt) 26ኛው የአሜሪካ ፕሬዝዳንት፡፡.

የ9/11 ጥቃት በአሜሪካ መንግስት ስለ መቀነባበሩ፣ ይከብዳል፡፡ በፊትኮ አሜሪካ አንድ ዜጋዋ ከተገደለባት ጦርነት ነው የምታስነሳው እንል ነበር፡፡ የማነበውን ነገር ከኢንተርኔት ላይ ቼክ እያደረግኩ ነበር የማነበው፡፡ እንዳለ እውነት ነው፡፡ እነኛን ረጃጅም ፎቆች ያፈነዳሁት እኔ ነኝ አለ ተብሎ የተለቀቀው ኦሳማ ቢን ላደን የፌክ መሆኑን ከኢንተርኔት ላይ አረጋገጥኩ፡፡ ቢቢሲ ሪፖርተሯ ገና ያልፈረሰውን የአንደኛውን ህንጻ 7ኛ ፎቅ ከመፍረሱ ከሀያ ደቂቃ በፊት ፈረሰ ብላ መዘገቧን አንብቤ ጉግል ሳረግ፣ የቢቢሲ ዌብሳይት ራሱ፣ አንድ ሰው ነግሯት ነው፣ ያጋጥማል ብሎ አድበስብሶ ማለፉን ቼክ አደረግኩ፡፡ ያ መጽሐፍ ስለዚህች አለም ያለኝን አመለካከት ከስሩ ነው የገለበጠው፡፡ ት/ቤት ስለ ምንማራቸው ነገሮች፣ ሰው ከዝንጀሮ መጣ የሚሉት መሰረተቢስ የሀሰቶች ሀሰት፡፡ ስለ ዘፋኞች፣ ስለ ተለያዩ ምልክቶች ስለ ተለያዩ ነገሮች፡፡ ሰይጣን ምን ያህል ማንነታችንን ተቆጣጥሮት እንዳለ ነው የተረዳሁት፡፡ የምንማረው ሂስትሪ ውሸት ስለ መሆኑ፣ ስለ አሜሪካ፣ ስለ አውሮፓ ህብረት ስለ... እውነቱን ውሸት፣ ውሸቱን እውነት አድርገውብናል፡፡ አዛብተውብናል፡፡ ጥበቡን ሞኝነት፣ ሞኝነቱን ጥበብ አድርገውብናል፡፡ እኔ ድሮ በልጅነቴ ፊልም ላይ ያሉት የወንጀል ድርጊቶች፣ ይሄ ከተማ ውስጥ ሰላዮች ሰውን የሚከታተሉት፣ በድብቅ የሚደረጉ ነገሮች እንዲሁ ፊልም ሊሰራባቸው እንጂ የምር በእውነተኛው አለም እንደዚያ ሚስጥር በሚስጥር የሆኑ ነገሮች ያሉ አይመስለኝም ነበር፡፡ ይህቺ አለም ግልጽ እንደ ሰማያዊው ሰማይ፣ ቅርብ እንደ አፍንጫ ለከንፈር ትመስለኝ ነበር፡፡ ስህተት፡፡ እንዲያውም ይህቺ አለም ፊልም ላይ ከሚታየው የባሰ የማይታዩ ድብቅ ሲአይኤዎች የሞሉባት ናት፡፡ እንዲያውም ፊልም እራሱ የተወሳሰበ ችግር አለበት፡፡ አንድ በኢሉሚናቲዎች ነው የተገደለው የሚባለው(እኔም በነሱ መገደሉን አምናለሁ) የማይክል ጃክሰን ዘፈን እንዲህ ይላል፡

Skin head, dead head
Everybody gone bad
Situation aggravation
Everybody allegation
In the suite, on the news
Everybody dog food
Bang bang, shot dead
Everybody's gone mad
All I wanna say is that
They don't really care about us
All I wanna say is that
They don't really care about us
Beat me, hate me
You can never break me
Will me, thrill me
You can never kill me
Jew me, sue me
Everybody do me
Kick me, kike me
Don't you black or white me...
I am the victim of police brutality, now
I'm tired of being the victim of hate
You're ripping me off my pride
Oh, for God's sake
I look to heaven to fulfill its prophecy
Set me free
Tell me what has become of my rights
Am I invisible because you ignore me?
Your proclamation promised me free liberty,
Now I'm tired of being the victim of shame

They're throwing me in a class with a bad name
I can't believe this is the land from which I came
You know I really do hate to say it
The government doesn't wanna see
But if Roosevet was living
He wouldn't let this be, no, no
But if Martin Luther was living
He wouldn't let this be, no, no
Trepidation speculation
Everybody allegation
Situation speculation
Everybody litigation
Hit me kick me
You can never get me
All I wanna say is that
They don't really care about us

ማስታወሻ፡ በዚህ ዘፈን ላይ የተጠቀሰው ማርቲን ሉተር፣ አሜሪካዊው የጥቁሮች መብት ታጋይ፣ ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየር እንጂ በዚህ መጽሐፍ ላይ ርዕስ የሰጠሁት ጀርመናዊው የሪፎርሜሽን ጠንሳሽ ማርቲን ሉተር አይደለም፡፡

ይህቺ አለም ከማስበው በላይ በሰይጣን ቁጥጥር ስር እንዳለች ሲገባኝ፣ ሰይጣን በህይወቴ ላይስ ያለው አንደምታ ምን ይመስላል ብዬ ወደኋላ ማጠንጠን ጀመርኩኝ፡፡ ሰዎች ሰይጣን አይችለኝም፣ ሲሉና እንዲህ የሚሉት ራሳቸው አንዳንዴም አገልጋዮች አጋንንት ሲወጣላቸው በጣም ይገርመኝ ነበር፡፡ ስለማናውቅኮ ነው፡፡ እንጂማ ከራስ ጸጉራችን እስከ እግር ጥፍራችን ሰይጣን ተቆጣጥሮናል፡፡

ስሜቱን የምገልጽበትን ቃላት ያጣሁለትን ጭንቀት አንድ የክርስትያን ዌብሳይት " depression feels like drowning" ውሀ ውስጥ የመስመጥ(የመበላት) ስሜት ነው ይላል፡፡ የልቤን ነው ያደረሰልኝ፡፡ መውጣት ትፈልጋለህ፣ መተንፈስ ትፈልጋለህ፣ አትችልም፣ ይጨንቅሀል፣ ጭንቀቱ እንዲቆም ትፈልጋለህ፣ ይብስብሀል፡፡ ውሃ ውስጥ እየሰመጥክ ትንፋሽ እንደ ሚያጥርህ ይሆንብሀል፡፡ ውሀ ውስጥ ስትሰምጥ ለጥቂት ጊዜ ነው ስቃዩ፡፡ ይሄ ግን ለአመታት ነው፡፡ ወይ ሞተህ አትገላገለው ወይ ዋና የሚችል ሰው መጥቶ አያድንህ፣ ነፍስህ ትሰቃያለች፡፡

አቡሽ የኔ ጭንቀት ቀልድ ነው የሚመስለው፡፡ አብረን እየሄድን የማውቀው ሰው ሰላም ሳይለኝ ካለፈ "ግባና እንግዲህ እገሌ ለምን ሰላም አላለኝም እያልክ አልቅስ" ይለኛል፡፡ አንድ ቀን ስለጭንቀቴ እያወራን "ኧረኔ እንኳንም አንተን አልሆንኩ" አለኝ፡፡ ይሄን ስሜት እንኳንስ ለአቡሽ ለጠላቴም አልመኘውም፡፡ እኔ ለማንም ያለኝ ምርቃት ይሄ ነው፡ እኔን አትሁን፣ የኔ ጭንቀት ዝር አይበልብህ፡፡ እንደኔ አትሁን፡፡ ይሄ ነው የኔ ምርቃት፡፡ ይሄን ስሜቴን በእንግሊዘኛ ዜማ አውጥቼበታለሁ፡፡

Let me bless you*2
Accept my bless
Say Amen
I am not that person,
Who blesses people
But please let me,
Let me bless you
Don't be like me
Don't become who I am
Please don't be…

ስለ ሁሉም ነገር ደግሞ እንደዚህ ራፕ አደረግኩበት፡

There was a day, when I was a kid
With many friends
There was a time when I was a child

With a charming face
Here I’m today I can’t feel good
Always bad
Here I am now everything feels lame

Yeah, things do change
Yes, people do change
Aha we may all change
Yep, you can also change.
Once I was a questioner
Question question question
I sought an answer
Now, I got the answer
Now I got the answers.
I used to ask my self
Why people do a suicide.
Now I got the answer
I know why they suffer
Because, they feel hopeless
Because they feel helpless.
I’m afraid I’m dead
I can feel my soul
It’s like a dark hole
Don’t look at my face
It is just a face
My face is smiling
My soul is crying
They see me smiling
They think I am happy
It’s so sad that they can’t
They can’t see my heart
It’s so sad that they can’t
They can’t live my life
It’s so sad that they can’t
They can’t wear my shoes.
Don’t judge a book by cover.
I gotta a wounded spirit
I just couldn’t bear it.
When is my last day?
I miss death sometimes
To be honest always
Now I got the answers.

“ባለማስተዋል የሰበሰብኩት፣
ከንቱ ብቻ ነው ለካስ ያከማቸሁት፡፡”

ምዕራፍ ሁለት

አስተማሪ የታሪክ ክፍሎች

የአሁኑ ዛሬና የድሮው ትናንት፣ አስገራሚ ቁርኝት

CHAPTER TWO
SOME IMPORTANT STORIES IN HISTORY
The stories that shaped today

“Civilization means a wiser son, than his father.”

ማሳሰቢያ፡ ውድ አንባቢ፣ ይህ ቀጥሎ የምታነበው ምዕራፍ፣ የኔ ወይም የማንም የሌላ ሰው አስተያየት ወይም አመለካከት ሳይሆን የታሪክ እውነታ ብቻ ነው፡፡

ቅድመ ምዕራፍ ሁለት

ስልጣኔ መቼ ጀመረ?

ሰውን ከእንስሳት የሚለየው ምንድነው? ማሰቡ? ስልጣኔ መቼ ጀመረ? ሰው ከዝንጀሮ ነው የመጣው የሚሉ ሰዎች ሰው የመጣው በዝግመተ ለውጥ(ኢቮሊዩሽን) ነው ሲሉ በዋናነት ጭንቅላቱን ነው፡፡ ሰውን ከእንስሳት የሚለየው ማሰቡ ነው ስለሚሉ ስልጣኔ ደግሞ የጭንቅላት ውጤት ስለሆነ ለእነርሱ ስልጣኔም የዝግመተ ለውጥ ውጤት ነው፡፡ ይሄ ቲዮሪ ያለፈበት ቲዮሪ ይባላል፡፡
ለኛ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን በውስጣቸው የሚኖሩ ፍጡራንንም፣ ሰውንም ፈጠረ ለምንለውስ፣ ስልጣኔ መቼ ነው የጀመረው? ሰውን ከእንስሳት የሚለየው ማሰቡ ነው ካልን አዳምና ሔዋን ክፉንና መልካምን የምታስታውቀውን ፍሬ እስኪበሉ ሰዎች አልነበሩም ማለት አይሆንም?
አዎ ስልጣኔ የጀመረው ሄዋን መልካምና ክፉን የሚያሳውቀውን ፍሬ ለራሷ በልታ ለባሏ ለአዳም በሰጠች ቅጽበት ነው፡፡ ያኔ ነው እርቃንን መሸፈን የተጀመረው፡፡ ያኔ ነው እርሻ የተጀመረው፡፡ ያኔ ነው ማሰብ የተጀመረው፡፡ ያኔ ነው ስልጣኔ የጀመረው፡፡ ያኔ ነው ውድቀት የጀመረው!

ሰውን ከእንስሳት የሚለየው ማሰቡ ነው ከሚሉት ጎራ ነህ? ተረት ተረት፣ የላም በረት ምንኛ አጃጅሎሃል ጃል?...

ቅድመ ስልጣኔ

ስልጣኔ ማለት በፊት በእግር ት/ቤት ትሄድ ከነበረ በባጃጅ ወይም በታክሲ መሄድ ማለት ነው፡፡ መሻሻል፣ ጊዜ መቆጠብ፣ በጥራትና በብዛት ማደግ...

በ4000 ዓመተ ዓለም (ከክርስቶስ ልደት በፊት)
ርዕሱ ላይ 4000 ዓ.ዓ፣ ከ4000 እስከ 3000 አመተ አለም ያለውን ጊዜ ይወክላል

- የአለም የህዝብ ብዛት ከ20 ሚሊየን በታች ነበረ ተብሎ ተገምቷል፡፡
- የሸክላ ስራዎች፣ የብረት ስራዎች፣ እንደ ጎራዴ ያሉ የጦር መሳሪያዎች ከሰው ልጆች ጋር የተዋወቁበት ሚሊኒየም ነው፡፡

- ከሁሉም በላይ በሜሶፖታሚያው(ባቢሎን) ኪዩኒፎርምና በግብጹ ሂሮግሊፊክስ የሰው ልጅ ሀ ሁ ማለት የጀመረ፡፡ እነኚህ ቀደምት የመጻፍ መጀመሪያዎች በየሂስትሪ መጽሐፉ ዛሬ ላይ የቀለም ተማሪው እንዲያውቃቸው የሚደረጉ የጽሁፍ የራሱ ሀ ሁ ናቸው፡፡
- የከተማዊነት (ከተሜነት) (urbanization) መስተዋል የጀመረበት ጊዜም ነው፡፡ ታድያ ስልጣኔ መሰረቱ ተጣለ ቢባል ስህተት ነው?

3000 ዓ.ዓ

- የጦር መሳሪያዎችን በገፍ ማምረት ተቻለ፡፡
- የግብርና ምርት ጨመረ፡፡
- በጽሁፍ የተሻለ ግንኙነት፡፡
- በአውሮፓ፣ በግብጽና በሌሎችም ቀደምት ስልጣኔዎች ቤተ መንግስቶች በአዳዲስና የበላይነትን ለማሳየት በሚሞክሩ ኪነ ህንጻዎች ይሰሩ ጀመር፡፡
- የጦር መሳሪያዎች መብዛትና በግብርና ብዙ ሀብት ማካበት መቻል፣ እንዲሁም የእውቀት ማደግ በፖለቲካው መድረክ መጣላቶችን፣ ጦርነቶችንና አለመግባባቶችን ፈጠረ፡፡ እንዲሁም መሪዎች የበለጠ ሀብትና ስልጣን ሰፊ ግዛትንም የመያዝ ፍላጎት ማሳየት ጀመሩ፡፡ በዚህም ምክንያት ኢምፔሪያሊዝም(የራስ ያልሆነን መግዛት)ና መሪዎች በአብሶሊዩቲዝም(መሪው ፍጹም ሀይል ያለውና ውሳኔው ያለማቅማማት እንዲፈጸም የሚደረግበት ስርአት) ተንሰራፉ፡፡ ይሄም ተገዢውን ህዝብ ከማስቆጣቱ የተነሳ ውስጣዊ አብዮቶችን ይቀሰቅስ ጀመር፡፡ በዚህ ጊዜ ጦርነት ወትሮአዊ ሆነ፡፡ ብዙ ሰዎች የሚሞቱበት፣ ሀብትና ንብረት የሚወድምበት ሆነ፡፡ ባንጻሩ ትላልቅና ሀያላን ኢምፓየሮች ተነስተዋል፡፡
- በግብጽ ፒራሚዶች ተገንብተዋል፣ ይኸው የዚያኔውን ስልጣኔ የሚያንጸባርቁና ለሺ አመታት ረጃጅምና ትላልቅ ሰው የሰራቸው እንዲሁም አስገራሚ የኪነ ህንጻ ጥበብ የታየባቸው ቅሪቶች በመሆን ዛሬን ዘልቀዋል፡፡
የግብጽ ፈረኦኖች ራሳቸውን በህይወት ያሉ አማልክት አድርገው በማቅረብ ይመለኩና ከሌሎች ሰዎች ተለይተው ይታዩ ነበር፡፡
- በዚህ ሚሊኒየም የተረጋጉና በአግባቡ የተዋቀሩ መንግስታትም መታየት ችለዋል፡፡
- ህንድ የረቀቀች ስልጣኔ ሆናለች፡፡ ፈረስን ማላመድና እንደመጓጓዣ መጠቀም በህንድ፣ በዚህ ዘመን ነው የተጀመረው፡፡

2000 ዓ.ዓ

- የፈረስ ሰረገላ መጠቀም ተጀመረ፡፡ የውጊያ ስልት አሁንም በእግረኛ ወታደሮችና መሳሪያዎችን በአህዮች ላይ በማጓጓዝ ላይ የተመሰረተ ነበር፡፡ ከደካማ ኢኮኖሚና ትዕዛዝን ባግባቡ ካለመከተል የተነሳ ትላልቅ ግዛቶች፣ ሊቋቋሟቸው ባልቻሏቸው የውጪ ወራሪዎች ቁጥጥር ስር እዲገቡና እነኚህ የውጪ ሀይሎች እንዲከፋፈሏቸው ሆነ፡፡ ምሳሌ፡ ግብጽና ባቢሎን፡፡
ይሄ ሚሊኒየም ከመጋመሱ በፊት ኢንዶ-አውሮፓውያን ወራሪዎች ከመካከለኛው እስያ ተነስተው ምዕራባዊ እስያንና ሰሜን ምስራቅ አፍሪካን ተቆጣጠሩ፡፡ ፈጣን፣ በሁለት ፈረሶች የሚጎተቱ ተሽከርካሪ ሰረገሎችን ተጠቅመው ነበር ወረራውን የፈጸሙት፡፡ ይሄ የውጊያ መሳሪያ በከፍተኛ ደረጃ በሰለጠኑት በግብጽና በባቢሎናውያን የታወቀ አልነበረም፡፡ የግብጽና የባቢሎን እግረኛ ወታደሮችም ራሳቸውንና ስልጣኔያቸውን ከወራሪ ሀይል መከላከል አልቻሉም፡፡
- በሁለተኛው ግማሽ ሚሊኒየም ብዙ እድገቶች ታዩ፡፡ አዳዲስ የህንጻ ዲዛይኖች፣ አዳዲስ የልብስ ፋሽኖች፡፡
አንዳንድ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቶች ብቅ ብቅ ማለት ጀመሩ፡፡ ኢኮኖሚያዊ ግንኑነቶች ደግሞ መጧጧፍ፡፡
- ዝቅተኛ ደረጃ አርበናይዜሽን፣ ቤተ-መንግስቶችን ማዕከል ያደረጉ ትናንሽ፣ ብዙ የታሪክ ፊልሞች ላይ እንደሚታዩት አይነት፣ አጥርና ትላልቅ መግቢያ በሮች(gate) ያሏቸው ከተሞች፡፡
- ጥብቅ የመደብ ክፍፍል፡ በባርያው፣ በገበሬው፣ በእጅ ሰሪውና የታጠቀውን ሀይል በሚመራው በከፍተኛውና የንጉሳውያን ቤተሰብ መሀል፡፡
- ማንበብና መጻፍ እንዲሁም መማር ለጥቂት ንጉሳውያን ቤተሰቦችና ጻፎች የተገደበ ነበረ፡፡ ይሄም በዘር ሀረግ ላይ ለተመሰረተው አሪስቶክራቲክ ህይወት ምክንያት ሆነ ይላል ታሪክ፡፡ ይሄም የንጉስ ልጅ የሚነግስበት ስርአት ነው፡፡ የሚማሩት ንጉሳውያኑ ብቻ ስለሆኑ ለረጅም ዘመናት ቀሪውን ህዝብ እንዳሻቸው እንዲያሽከረክሩ ሆነ፡፡ ተቃውሞን በጥበብ የመመከት፣ ህዝቡን የማሞኘት የተለያዩ ዘዴዎችን ተጠቅመው አስፈላጊ ከሆነም ህዝቡን ራሱን በመጠቀም ለዘመናት የደም ሀረጋቸውን ጠብቀውና ስልጣናቸውን ሳያስነኩ ኖረዋል፡፡

1000 ዓ.ዓ

- ሮማን ኢምፓየር የተነሳበት ጊዜ ነው፡፡
- በቻይና ኮንፊሺስ ኮንፊሽያኒዝም የሚባለውን ፍልስፍና እና ሀይማኖት መሰረተ፡፡
ሂንዱኢዝም፣ ቡድሂዝም፣ ዞሮአስተሪያኒዝምን የመሳሰሉ እምነቶችም የተመሰረቱበትም ጊዜ ነው፡፡

- በአፍሪካ የግብጽ ስልጣኔ መውደቅ የጀመረበትና ኑቢያን ኢምፓየር ማደግ የጀመረበት እንዲሁም አክሱም የተወለደበት ዘመን ነው፡፡
- በግሪኮ-ሮማን አውሮፓ፣ በህንድና በቻይና ስነ-ጽሁፍ የማደግ ተስፋን አሳየች፡፡
- የህዝብ ብዛት ከ170 ወደ 400 ሚሊየን አድጓል ተብሎ ይገመታል፡፡
- በሂሳብና ሳይንስ፡ ቡአያንሲ፣ ጂሜትሪ፣ ፓይታጎሪያን ቲዮረም፣ ከብ መሬት፣ አተምስ፣ የውሃ ሰአት የተፈጠሩበት፣ የተገኙበትና የተዋወቁበት ጊዜ ነበረ፡፡
- በመጓጓዣ የመጀመሪያው ሀዲድ፣ ትላልቅ መርከቦች በአውቅያኖሶች ላይ መንሳፈፍ ጀመሩ፡፡ እድሜ ለቡአያንሲ፡፡
- ከክርስቶስ ልደት በፊት በ5ኛው ክፍለ ዘመን የግሪክ ፍልስፍና አንጸባረቀ፡፡ Greek philosophy flourished.

የግሪክ ፍልስፍና

ፍለስፍና (philosophy) `philosophia' ከሚል የግሪክ ቃል የመጣ ሲሆን የቃሉ ትርጉምም የጥበብ ፍቅር(the love of wisdom) ማለት ነው፡፡

በሜዲቴራንየን ባህር ዙሪያ ከሶስተኛው ሚሊኒየም እስከ አንደኛው ክፍለዘመን የዘለቀው የጥንታዊት ግሪክ ስልጣኔ (ancient Greek civilization)፣ በፍልስፍና፣ በኪነህንጻ፣ ድራማ፣ አስተዳደርና ሳይንስ ላይ ባደረገው አስተዋጽኦ ይታወቃል፡፡
ጥንታዊት ግሪክ ፖለቲካዊና ወታደራዊ ሀይሏን በሮማውያን ከተነጠቀች ከብዙ ዘመናት በኋላ እንኳ፣ ጥላ ያለፈቻቸው ባህላዊ ስኬቶች ሃያሲያን፣ ጸሀፊዎችና አርቲስቶች ላይ በተለይ በጥንታዊት ሮማ እንዲሁም በመካከለኛው ዘመን አረብያና የአውሮፓው ሬኔሳንስ ላይ ጥልቅ ተጽእኖን ማሳደር ችለዋል፡፡ ግሪክ የዘመናዊው ዲሞክራሲ የትውልድ ቦታ ነች፡፡

የጥንታዊት ግሪክ ፍልስፍና ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ6ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ግሪክ ሮማን ኢምፓየር ስር እስከትጠቃለል ድረስ በግሪክ የነበረው የአስተሳሰብ አብዮት ነው፡፡ የግሪክ ፍልስፍና ሰፊ ጉዳዮችን ይዳስሳል፡፡ የፖለቲካ ፍልስፍና፣ ስነ-ምግባር፣ ሜታፊዚክስ(የህይወት ፍልስፍና፡ ስለ ህይወት አፈጣጠርና ስለ ፍጥረታት እንዲሁም ስለ መኖር(existence) ጊዜ፣ ህዋ(space)ና casuality(ለሁሉም ውጤት ምክንያት አለው ብሎ ማመንና አንድ ነገር የሆነበትን ምክንያት ማጥናትን የሚያጠቃልል የፍልስፍና ዘርፍ ነው፣ Metaphysics)፣ ሎጂክ(የምክንያት ቲዮሪ)፣ ባዮሎጂ፣ ርሄቶሪክ(የውጤታማና ቀስቃሽ ንግግር ጥናት)፣ እስቴቲክስ(የጥበብ(አርት) ጥናት)ና ሌሎችንም የጥናት ዘርፎችን፡፡
ዛሬ የምንማረው ትምህርትና በአለም ላይ የምናየው ስልጣኔ የግሪክ አዋቂዎች ውጤት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ዛሬ ላይ የድሮው የግሪክ ፍልስፍና በተለይ በምዕራባዊው አስተሳሰብ፣ አኗኗር፣ አለም ላይ ከፍተኛ ተጽእኖን እንዳደረገ የማይካድ እውነታ ነው፡፡ ተጽእኖው ከዲሞክራሲ ይጀምራል፡፡
ከክርስቶስ ልደት በፊት በአንደኛው ሚሊኒየም አጋማሽ የግሪኳ አቴና (Athens) ድንቅ የዲሞክራሲ ማዕከል ሆና ነበር፡፡

Humanism የሚባለው የፍልስፍና ዘርፍ ሰው የተፈጠረው ለመደሰት ነው የሚል ሀሳብን ያቀነቅናል፡፡ ሰው የተፈጠረው ለመደሰት ነው፣ በተቻለ መጠን ደስታን የማብዛትና ሀዘንን ወይም ህመምን የመቀነስ ፍልስፍና ነው፡፡ ዛሬ በምድር ላይ የመጨረሻዋ ቀንህ እንደሆነች እያሰብክ ኑርባት፡፡ ይሄ ፍልስፍናም ሰው በተፈጥሮው እንጂ በመንፈሳዊ አስተምህሮዎች መመራት የለበትም የሚል ሲሆን የሰው መሰረታዊ ፍላጎቶች ምግብ፣ ልብስና መጠለያ ናቸው የሚለው አስተሳሰብ መሰረተድንጋይ ነው፡፡ ሌላውን አትንካ እንጂ ብላ ጠጣ፣ እንደፈለግክ ኑር፣ የሰው የመጨረሻ ግቡ ተደስቶ መሞት ነው የሚለው ይሄ ፍልስፍና ከዘመናችን የኢሉሚናቲዎች "make the world a better place" መፈክር ጋር ይቀራረባል፡፡ A better life ማለት ኑሮን ማቃለል፣ የተደላደለ ኑሮ፣ ልፋትን መቀነስ፣ ላይፍን ኢንጆይ ማድረግ... ማለት ነው፡፡

የሮማን ሪፐብሊክ አስተዳደር

ሮማ ወደ መጀመሪያ በነገስታት ነበረ የምትተዳደረው፡፡ ነገር ግን ከዚያ ወዲህ ጥንታዊት ሮማ፣ ሮማውያን ራሳቸውን በራሳቸው የሚያስተዳድሩበት መንግስት አቋቋመች፡፡
በአንድ በኩል፣ አስፈሪ የጦር ሃይሉን ተጠቅሞ ሌላ ግዛቶችን እንደሚቆጣጠርና ሰዎችን ወደ ባርያነት እንደሚያቃልል አገዛዝ ሳይሆን ሮማ ለራሷ ዜጎች እጅግ በሚደንቅ ሁኔታ ዲሞክራሲያዊት ነበረች፡፡ የሮማ ዜጎች ተሰብስበው ባለስልጣኖቻቸውን ይመርጡ ነበር፡፡ የሮማ ከፍተኛ ባለስልጣናት ሁለት ሲሆኑ እነሱም ለአንድ አመት ነበር የሚያገለግሉት፡፡ በመጀመሪያው አመት በትክክል ካልሰሩ በመጪው ምርጫ ስልጣናቸውን እንዲለቁ ሊደረጉ ይችላሉ፡፡

ሁለቱ የበላይ ባለስልጣናት ሁሉንም ነገር እንዲያውቁ አይጠበቅባቸውም፡፡ በሴኔት ይመከሩ ነበር፡፡ ሴኔቱ፣ ከተከበሩ የሮማ ዜጎች የተዋቀረ ሲሆን ሴኔቱ ስለተረቀቁ አዲስ ህጎች፣ የፋይናንስ ጉዳዮች ወዘተ. ይወያያል፡፡ በሴኔቱ ውስጥ 600 ያህል ሰዎች በአባልነት ይይዛል፡፡ እኚህ የሴኔት አባላት ባብዛኛው ከባለጠጋው ገዢ መደብ ቤተሰቦች ሲሆኑ የነዚህ ሰዎች ሀሳብ ጭማቂ ነው የሮማ ህግ ሲሆን የነበረው፡፡

ሮማን ኢምፓየር እያደገና ሮማ የበለጠ ጠንካራ ከተማ እየሆነች ስትመጣ ከፍተኛው የስልጣን ወንበር የበለጠ አጓጊ እየሆነ መጣ፡፡ ስለዚህም ብዙ ተስፈኞች ወንበሯን ማለም ያዙ፡፡ እነኚህ ሰዎች የሴኔቱን ስልጣን በሚቃወም መልኩ የሮማ ከተማና ሮማን ኢምፓየር በአንድ ሰው ቢመሩ ይሻላል የሚል ሀሳብ ማናፈስ ጀመሩ፡፡
እነኚህ ሶሎ ገዢዎች እንዲህ ይላሉ፡ “ምርጫዎችቻችን በአሳማኝ መንገድ ዲሞክራሲያዊ ናቸው ከተባለ፣ የሴኔቱ ድርሻ ግን አሳማኝ አይደለም፡፡ሁሉም ባይሆን፣ ከሞላ ጎደል ውሳኔዎች የሀብታሞች ጥቅም አስከባሪዎች ናቸው፡፡ ሀብታሞች ብቻ ናቸው ጥቅማቸውን ለማስከበርና በሀብታቸው ውሳኔዎች ላይ ተጽእኖ ለማድረግ ሴኔቱ ውስጥ የሚካተቱት”፡፡
ቢሆንም ጥቂት ሰዎች ብቻ ናቸው ከዝቅተኛው መደብ ይሄን አሰራር ሲቃወሙ የነበሩት፡፡ ብዙዎቹ ሀብታሞቹ የሴኔቱን ስራ እንደሚሰሩና ቦታው ለእንደነሱ አይነት ድሆች እንዳልሆነ ነበር የሚያስቡት፡፡

ቄሳር(Julius Ceasar) መሪ መሆኑ አንሶት እንዳለ የሮማን ኢምፓየር ለብቻው መቆጣጠር ፈለገ፡፡ ይሄ የጥንታዊት ሮማን ለብዙ አመታት የዘለቀ የሰከነ ስርአት መጨረሻ ሊሆን፡፡ ቄሳር በሴኔቱ ውስጥ ለሶሎ አገዛዝ ያለውን ድጋፍ ለመግለጽ ንግግር ሲያደርግ የቀድሞው ስርአት እንዲቀጥል በሚፈልገው በብሩተስ ተገደለ፡፡ ይሄ ግድያ ግን ችግሩን አላስቆመም፡፡ የሴዛር ደጋፊዎች ፍላጎታቸውን በሀይል ሮማ ላይ ለማስፈጸም የእርስ በርስ ጦርነት ከፍተው ነበርና፡፡ ጦርነቱ በጣም ረጅምና ብዙ ገንዘብ የጠፋበት ነበረ፡፡ ጦርነቱ ባመጣው ድካምና ስልችት ምክንያት ብዙ ሮማውያን የቄሳርን ወንድም ልጅ አውገስተስ(Augustus Ceasar)ን እንዲደግፉ ሆነ፡፡ ለብዙ ሰዎች አውገስተስ ሮማ ከገባችበት አዘቅት የምትወጣበት ቀላሉ መንገድ መሰለ፡፡ አውገስተስ በ27ኛው ዓ.ዓ. በሮማ ኢምፓየር ላይ ነገሰ፡፡ ጠንካራ መሪ ሆኖም ታየ፡፡ በርግጥ ከቀዳሚው የሴኔት አገዛዝ የበለጠ ጠንካራ መንግስት ማቋቋምና እስራኤልን ጨምሮ ሰፊ ግዛቶችን መቆጣጠር ችሏል፡፡ ይሄም የሮማ ሪፐብሊክ ማብቂያ መጨረሻ ነበረ፡፡ ሪፐብሊኩ፣ በኛ ዘመን ፖለቲካ ላይ ያሳረፈው አሻራ ግን፣ አሌ የማይባል ነው፡፡

የጥንት ሰዎች ሀይማኖቶች

ከአይሁዳውያን ባለፈ በአንድ አምላክ የሚያመልክ ጥንታዊ ሰውም ሆነ ህዝብ አልነበረም፡፡
የአንድ አምላክ አምልኮ (Monotheism): አንድ አምላክ ብቻ፣ ሌላ አምላክ የለም፣ ሌላው ትክክል አይደለም የሚለው የእምነት አይነት ሲሆን ጁዳይዝም(ከክርስቶስ በፊ፣ የአብርሃም፣ የነይስሃቅ፣ የነያዕቆብና ዛሬም የአይሁድ አምልኮ)፣ ክርስትና እና እስልምና የዚህ ሁነኛ ምሳሌዎች ናቸው፡፡ ጁዳይዝም ደግሞ የጥንቱ ጊዜ ብቸኛው ሞኖቲክ ሀይማኖት ነበረ፡፡
የብዙ አማልክት አምልኮ (polytheism): ሰው ለተለያዩ ችግሮቹ መፍትሄ የተለያዩ ሰዎች ጋር እንደሚሄደው፣ ሲታመም ዶክተር ጋር እንጂ ኢንጂነር ጋር እንደማይሄደው፣ ለተለያዩ ፍላጎቶችና ችግሮች የየራሳቸው፣ የፍቅር፣ የመድሃኒት፣ የጦርነት፣ የብልጥግና አማልክትን ለየብቻ የሚያመልክበት የአምልኮ አይነት ነው፡፡ ጦርነት ለማሸነፍ የጦርነቱ ጋር፣ ለመድሃኒትም የመድሃኒቱ ጋር፡፡ ይሄ በጥንቱ ዘመን በስፋት ሲተገበር የነበረው የአምልኮ አይነት ነው፡፡
ከአማልክቱ አንዱን አግዝፎ የማምለክ አምልኮ (henotheism): ይሄ ደግሞ ከብዙዎቹ አማልክት አንዱ ገንኖ ሲወጣና ሰዎች ያ አምላካቸው ለሁሉም ጥያቄዎቻቸው መልስ የመስጠት ሀይል አለው ብለው የሚያስቡበት ነው፡፡ በፍጹም ግን እንደ ሞኖቲዝም አይደለም፡፡ ይሄኛው ሌሎቹን አማልክት አክብረው እንዳሉ አንዱን ሀይለኛ የሚሉትን የሚያመልኩበት ነው፡፡ ይሄኛው አይነት አምልኮ በታሪክ በጥቂቱ የታየ ነው፡፡

በተለይ የግብጽ ሐይማኖት፣ የጥንቆላ፣ የመድሃኒቶች፣ የአፈ-ታሪኮች፣ የሳይንስ፣ ሳይካትሪ(ስነ-አዕምሮ)፣ ሙታንን የማነጋገርና የሞት በኋላ ህይወት እምነት፣ የነኚህ ሁሉ ጥምረት ነው፡፡ ግብጽንና ዋና ከተማዋ ባቢሎን የነበረችውን ሜሶፖታሚያን ጨምሮ ሁሉም የስልጣኔ መነሐሪያ የነበሩ ጥንታውያን ሀገራትና ግዛቶች ከፍተኛ የጣኦት አምልኮ ይካሄድባቸው እንደ ነበር ታሪክ ያስረዳል፡፡
እነኚህ ጣኦታት የራሳቸው ቤተመቅደስና ቀሳውስት ነበራቸው፡፡ እኚህ ቀሳውስትም ቤተመቅደሱ ውስጥ የሚደረገውን ስርአት ያስፈጽማሉ፡፡ እንዲሁም እነኚህን ጣኦታት ለማክበር የሚደረጉ ክብረበአላትን(ፌስቲቫሎችን) ያቀናጃሉ፡፡

ከክርስቶስ ልደት ወዲህ

ሀይማኖቱ ትውልድ እየተቀባበለው ከ2000 አመት በላይ ሊዘልቅ፣ አስተምህሮቱ በአለም ሊሰራጭ፣ የክፉዎችን አፈና ተቋቁሞ፣ ዛሬም በኛ ዘመን ያለው የክርስትና ሀይማኖት ሊመሰረት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተወለደ፣ በጴንጤናዊው ጲላጦስ ዘመን መከራን ተቀበለ፣ ተሰቀለ፣ ሞተ፣ ወደ ሲኦልም ወረደ፣ በሶስተኛውም ቀን ከሙታን ተነሳ፡፡ ኢየሱስም መንፈስ ቅዱስን እንደሚልክልን ተናግሮ ወደ አባቱ በማረግ ተመለሰ፡፡ እግዚአብሔር ለሰው ያለውን ፍቅር አሳየ፡፡

ከክርስቶስ ማረግና፣ ከደቀመዛሙርቱ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት በኋላ የእግዚአብሔርን ጣት በገሃድ ትሰራ ጀመር፡፡ እግዚአብሔር ለአህዛብ ደረሰ፡፡ አለም ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኟ አድርጋ በመቀበል እግዚአብሔርን ማምለክ ጀመረች፡፡

የሮማን ጣኦታትን ማምለክን አሻፈረን ያሉትንና እምነታቸውን አስበልጠው የተላለፈባቸውን የሞት ፍርድ አሜን ብለው ተቀብለው ለሰሙት ወንጌል እንደታመኑ የተሰዉት ሰማዕታት፣ ዛሬም ድረስ የእውነተኛ እምነት አንጸባራቂ ምሳሌዎች ናቸው፡፡

2ጢሞ3፤12፡ በእውነትም በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ፡፡

ሮሜ8፤18፡ ለእኛም ይገለጥ ዘንድ ካለው ክብር ጋር ቢመዛዘን የአሁኑ ዘመን ሥቃይ ምንም እንዳይደለ አስባለሁ፡፡

ማቴ10፤28-33፡ ስጋን የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ ይልቅስ ነፍስንም ሥጋንም በገሃነም ሊያጠፋ የሚቻለውን ፍሩ፡፡ ሁለት ድንቢጦች በአምስት ሳንቲም ይሸጡ የለምን? ከእነርሱም አንዲቱ ያለ አባታችሁ ፈቃድ በምድር ላይ አትወድቅም፡፡ የእናንተስ የራሳችሁ ጠጉር እንኳ ተቆጥሮአል፡፡ እንግዲህ አትፍሩ ከብዙ ድንቢጦች እናንተ ትበልጣላችሁ፡፡ ስለዚህ በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ በሰው ፊትም የሚክደኝን ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እክደዋለሁ፡፡

ሮማን ኢምፓየር

ሮማን ኢምፓየር ለአምስት ምዕተአመታት ያህል የሮም ከተማን መዲናው በማድረግ የተመሰረተ አገዛዝ ነው፡፡ የታሪክ አጥኚዎች የሮማን ኢምፓየር መነሻ አመት 27ዓ.ዓ. ነው ይላሉ፡፡ ኢምፓየሩ ከክርስቶስ ልደት ወዲህ በ4ኛውና 5ኛው ክፍለዘመን ከገጠመው ኢኮኖሚያዊ ድቀትና ውስጣዊ አለመረጋጋት በኋላ የጀርመኖች ወረራ ታክሎበት፣ በሮም ያንን የሚያህል ሰፊ ግዛት (ከግብጽ እስከ ቻይና) መቆጣጠር ካለመቻል የተነሳ መውደቅ አይቀርም ወደቀ፡፡

ሮማውያንና ኢምፓየራቸው በቀጣይ ዘመናት ለመጡት ለመካከለኛው ዘመን(middle ages)ና ለተሀድሶ(Renaissance) እንዲሁም እስካሁን ድረስ ላሉት ዘመናት ባህላዊና ፖለቲካዊ ቅርጽ ሰጥተው አልፈዋል፡፡ ሮማን ኢምፓየር የግሪክን አርትና ፍልስፍና፣ እንዲሁም የባቢሎን አስትሮኖሚ(የህዋ ጥናት)ና አስትሮሎጂ(የፀሀይና የጨረቃ እንዲሁም የሌላ ፕላኔቶች እንቅስቃሴ ከሰው ልጅ ጋር ያላቸውን ግንኙነት የሚያጠና የጥናት ዘርፍ) እና ሌላም ባህላዊ ግብአቶች ከፔርሺያ፣ ግብጽና ሌላም ምስራቃዊ ስልጣኔዎች ወደ ቀጣዩ ትውልድ እንዲተላለፉ መሸጋገሪያ ድልድይ ሆኗል፡፡ ሮማውያን የራሳቸው የአስተዳደር ችሎታ፣ ህግና ኪነህንጻ፣ እንዲሁም ቋንቋቸው የሆነውን ላቲንን ማሳለፍ ችለዋል፡፡ በዚህ መንገድ ምዕራባዊውን አለም የቀረጸውን የግሪኮ-ሮማን ቅይጥ የሀብታም ባህሎች ቅልቅል የሆነ አኗኗር መፍጠር ቻሉ፡፡ ሮማውያን ይሄን ቅይጥ ባህል የፈጠሩት አንደኛውንና ሁለተኛውን ክፍለዘመን በሚያጠቃልለው pax romana በተሰኘው በረጅሙና በሰላማዊው የብልጥግና ጊዜ ነው፡፡ አንዳንድ የታሪክ አጥኚዎች የአለማችን ረጅሙ ሰላማዊ ጊዜ ይሉታል፡፡

ሮማውያን በዚህ ዘመን እየተሰሩ ባሉ ፊልሞች ላይ እንደሚታየው በግላድያተር(የሜዳ ላይ ፍልሚያ)ና በዘቀጠ ስጋዊ ህይወታቸው ነው የሚታወቁት፡፡ የበላይ አመራሮችን ጨምሮ ጋብቻን ወደጎን እስከመተውና የተጋቡትም በተደጋጋሚ እስከመፋታት፡፡ በሮማ ከትዳር ውጪ እንኳን ያለ በዚህ ዘመን፣ ቦይ ፍሬንድ ገርል ፍሬንድ የሚባለው አይነት ግንኙነት እንኳን የጠፋበትና ሰው እንደእንስሳ እስከመሆን የደረሰበት ጊዜ ነበረ፡፡ ዝሙት የነገሰበት፡፡

ጥንታዊት ቤተ-ክርስትያን

ቢዛንታይን ረጅም እድሜን (ከ330-1453ዓ.ም.) የዘለቀ ኢምፓየር ሲሆን ይሄ ኢምፓየር ከሚታወቅባቸው ነገሮች አንዱና ዋነኛው ከክርስትና ጋር የተያያዘ ነው፡፡

ከፍተኛ የጣኦት አምልኮ ይካሄድባትና ስርአት አልበኝነት የነገሰባት ሮማ፣ ክርስትና እየተስፋፋ ሲመጣ ክርስትያኖችን ያለ ርህራሄ ማሳደድ ጀመረች፡፡ ቁጥራቸው ያልታወቀ ክርስታያኖች የሞት ፍርድን ተቀበሉ፡፡ አንዳንዶቹ እንደሌባ በድንጋይ ሲወገሩ፣ ሌሎቹ ተሰቀሉ፡፡ ሌሎቹም

ግላድያተሮች በሚፋለሙበት አሬና ውስጥ በአንበሳ እንዲበሉ ሲደረጉ፣ ወንጌል ከሰው ወደ ሰው እየተቀጣጠለና እየተስፋፋ እንጂ እየጠፋ አልነበረም፡፡
በሮማ ሁለት ክፍለዘመናትን ከዘለቀ ስደት በኋላ ኮንስታንታይን የተባለ የሮማ ገዢ የክርስትያኖችን ስደት ማስቆሙ የጥንታዊ ቤተክርስትያንን አቅጣጫ ቀያሪ ውሳኔ ነበረ፡፡ ኮንስታንታይን በ313ዓ.ዓ. የክርስትያን አምልኮን ወንጀልነት የሚሽር Edict of Milan (የሚላን አዋጅ) የተሰኘ አዋጅ አወጀ፡፡ ኮንስታንታይን ለክርስትያኖች የማምለክ መብት ከሰጠ በኋላ ክርስትያኖችን በገንዘብ መርዳትና ትላልቅ የኦርቶዶክስ ቤተክርስትያኖችን ማስገንባት ጀመረ፡፡ ኮንስታንታይን ከ324-330ዓ.ም. ኮንስታንቲኖፕል የተሰኘችውን ከተማ ከመሰረተበት ምክንያቶች አንዱና ቀዳሚው የሌላ ሀይማኖት(የጣኦት አምላኪዎች) ቤተመቅደሶች የሌሉበት ከተማን መፈለጉ ነው፡፡ የዛሬዋ ኢስታንቡል የዚያኔዋ ኮንስታንቲኖፕል በ330 የሮማን ኢምፓየር ዋና ከተማ ተደረገች፡፡ በቀጣይ የሮማ ኢምፓየር ሲወድቅና ሮማ በምስራቅና በምዕራብ ሮማ ለሁለት ስትከፈል የቢዛንታይን(የምስራቅ) ሮማን ኢምፓየር ዋና መቀመጫ ሆና ቀጠለች፡፡ በኮንስታታይን አገዛዝ ክርስትያኖች ለከፍተኛ የመንግስት ስልጣን የመወዳደር መብት ተሰጣቸው፡፡ የግላድያተሮች ፍልሚያ በ325 ዓ.ም. ታገደ፡፡ ወንጀለኛን በመስቀል ላይ የመስቀል ባህል ከዚያ ወዲያ ታሪክ ሆነ፡፡ በመጨረሻም ክርስትና እየተስፋፋ፣ የጣኦት አምልኮ ደግሞ እየተመናመነ መጣ፡፡
ጌታችንና መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሞቱና በትንሳኤው ቤተ-ክርስትያንን መስርቶ ወደ አባቱ ከሄደ በኋላ የውሸት ትምህርት ቤተ-ክርስትያን ውስጥ ሊንሰራፋ ብዙ ውሎ እንዳላደረ ከጳውሎስ መጽሐፍት እናነባለን፡፡ ጳውሎስም አብያተ-ክርስትያናት ከሀሰተኛ ትምህርቶች ራሳቸውን እንዲጠብቁ ደጋግሞና አጥብቆ ያስጠነቅቃል፡፡ በክርስትና ላይ የተለያዩ ሀሳቦች በመነሳታቸው የተነሳም ብዙ ቡድኖች ተፈጠሩ፡፡ ከጠዋቱ ቀስ ብሎ እያደገ በ11ኛው ክፍለዘመን የለየለት የምስራቅ የኦርቶዶክስ ቤተ-ክረስትያንና የምዕራብ የካቶሊክ ቤተ-ክርስትያን መለያየት ግን የትምህርት ልዩነት ብቻ ሳይሆን የባህልና የፖለቲካ አለመጣጣሞችና መቃቃሮች ውጤት ነው፡፡ አንድ ወጥ የክርስትና ሀይማኖት እንዲኖር በተደረገው ጥረት ውስጥ የመጀመሪያው ወደ ክርስትና የተቀየረ የሮማ ንጉስ የሆነው ኮንስታንታይን ተካፋይ ነበረ፡፡ ታድያ ንጉሱ በተገኘበት የዘመኑ ቀሳውስትና መነኮሳት ተሰባስበው አንድ የሀይማኖት መግለጫ አወጡ፡፡ ይሄም ሰዎችን በወቅቱ ከነበሩ ብዙ አይነት የውሸት አስተምህሮዎች ለመጠበቅና እውነተኛይቱ ቤተ-ክርስትያን ሳትበረዝ ለቀጣዩ ትውልድ እንድትተላለፍ የተደረገ ጥረት ነው፡፡ የኒቂያውን የመሳሰሉ ጉባኤዎችም የዚህ ጥረት ምሳሌዎች ናቸው፡፡
ቤተ-ክርስትያን እንዳትከፋፈል ታድያ የሀይማኖት መግለጫ ማውጣት ብቻ ሳይሆን ህዝቡን ማስተማር ያስፈልጋል የሚል ሀሳብ ተጠነሰሰ፡፡ ይሄ ጥንስስ ሀሳብም የሰኮላሰቲሲዝም ውልደትና የኦርቶዶክስና የካቶሊክ ቤተ-ክርስትያን መለያያ ከሆኑ ዋና ዋና ምክንያቶች አንዱ በመሆን ብቅ አለ፡፡
ክብዙ አንዲት ቤተ-ክርስትያንን ለመጠበቅ የተደረጉ ሙከራዎችና ከብዙ ክፍለዘመናት በኋላ ቀስ በቀስ ልዩነታቸው እየሰፋ እየሰፋ ከሄደ በኋላ በ11ኛው ክፍለዘመን በ1054 የምስራቅ ኦርቶዶክስና የምዕራብ ካቶሊክ ቤተ-ክርስትያኖች ተቆራረጡ፡፡ እንደ ሁለት የተለያዩ ሀይማኖቶች በመሆንም በመሃላቸው የነበረውን መገናኛ ድልድይ አፈረሱ፡፡

ለአውሮፓ ብቻ ሳይሆን ለአለም የተረፈውና በታሪክ ታላቁ የክርስትያኖች ክፍፍል ተብሎ የሚታወቀው የ1054ቱ የምስራቅ-ምዕራብ ክፍፍል(The East-west schism)(The great schism)፣ በ11ኛው ክፍለዘመን የተመሰረቱት የኦርቶዶክስና የሮማ ካቶሊክ ቤተ-ክርስትያናት ህብረት ማብቂያ ነው፡፡ ተቋማዊ መዋቅሮችና አስተዳደር ላይ የነበሩ ልዩነቶችና ስነ-መለኮታዊ(theological) አለመግባባቶች በ1054 የተደረገው ህጋዊ(formal) መሰንጠቅ የአንድ ሌት ወይም የአንድ አመት ውጤት እንዳልሆነ ያመላክታሉ፡፡ ምዕተ አመታትን ያስቆጠረ፣ ቀስ በቀስ የመጣ ነው፡፡

ኦርቶዶክስ ማለት የድሮ፣ ባህላዊ፣ የተለመደ፣ ተቀባይነት ያለው ቀጥተኛ፣ ትክክለኛ (conservative) ማለት ነው፡፡ ካቶሊክ ማለት ደግሞ እንደ አጠቃላይ(universal) ማለት ነው፡፡

ከምዕራባዊው ሮማ በተለየ፣ የክርስትና እምብርት የሚባሉት ጥንታውያን የመጀመሪያ ምስራቃዊ ቤተ-ክርስትያናት በደቀ-መዛሙርት የተመሰረቱ ናቸው፡፡
የአንጾኪያ ቤተ-ክርስትያን በጴጥሮስና በጳውሎስ፣ የአሌክሳንድሪያ ቤተ-ክርስትያን በማርቆስ፣ የኮንስታንቲኖፕል ቤተ-ክርስትያን በእንድርያስ፣ የቀሬና ቤተ-ክርስትያን በበርናባስ፣ የኢትዮጵያ ቤተ-ክርስትያን በማቴዎስ፣ የህንድ ቤተ-ክርስትያን በቶማስ፣ በምስራቅ ሶሪያ ውስጥ የምትገኘው የኤዴሳ ቤተ-ክርስትያን፣ በታዴዎስ፣ የአርሜኒያ ቤተ-ክርስትያን በበርቶሎሜዎስ፣ የጆርጂያ ቤተ-ክርስትያን በቀነናዊው ስምኦን፡፡ በዮሐንስ ራዕይ የመጀመሪያ ምዕራፎች ላይ የተጠቀሱት "ሰባቱ የእስያ(በሮማ ግዛት ስር የነበረችው እስያ) ቤተ-ክርስትያናት"ም የክርስትና መሰረት ተብለው ከሚታወቁት ቤተ-ክርስትያናት መሃል ነበሩ፡፡

የሮም(ከተማ) ቤተ-ክርስትያን በሌላ ቤተ-ክርስትያናት ላይ ስልጣን እንዳላት ሆና ብትቀርብም በዚያ ዘመን ጳጳሳዊ የበላይነትን የሚፈቅድም ሆነ የሚቀበል ግልጽ ማስረጃ የለም፡፡

በደቀ-መዛሙርት በተመሰረቱ የምስራቅ ቤተ-ክርስትያናትና በምዕራባዊቱ የሮም ቤተ-ክርስትያን መሃል የተለያዩ አለመግባባቶች ሲከሰቱ ኮንስታንታይን መዲናውን ከሮም ወደ ኮንስታንቲኖፕል ማዛወሩ የክፍፍሉ የመጀመሪያ ምክንያት ነው፡፡ የኮንስታንታይን አዲሲቷ መዲናው ኮንስታንቲኖፕል በመባል በድሮ ስሟ ብትታወቅም ኮንስታንታይን ግን ኖቫ ሮም (Nova Rome) (New Rome) ብሎ ሰይሟት ነበር፡፡ የስልጣን ክብደት ወደ ምስራቅ ማዘንበሉ ግድ ሲሆን ሮም ክብርና ዝናዋን ተነጠቀች፡፡ በ381 እንደ ኒቂያው አይነት ሌላ ጉባኤ በአዲሲቷ መዲና ሲደረግ አንድም የምዕራብ የሀማኖት መሪ(አቡን) አልተጋዘም፡፡ ያ ጉባኤም ኮንስታንቲኖፕል አዲሲቷ ሮም ስለሆነች የኮንስታንቲኖፕሉ ፓትሪያርክ ከሮም ፓትሪያርክ የሚተካከል ክብር ይሰጣቸዋል የሚል ውሳኔን አስተላለፈ፡፡ እንዲህ አይነቱ ሽግሽግ ያስጋቸው የምዕራቡ መሪዎች የሮም የጵጵስና ስልጣን በምድር ሁሉ ላይና በሁሉም ቤተ-ክርስትያን ላይ ነው እያሉ ሀይልን በሮም ለማስቀረት ሞከሩ፡፡ በ395 ዓ.ም.

የሞተው ንጉስ ቲዎዲሲየስ የመጨረሻው የአንዷት ለሁለት ያልተከፈለችው ሮማ ገዢ ነበረ፡፡ በአራተኛው ክፍለዘመን የተነሳውና መቀመጫው ኮንስታንቲኖፕል የሆነው ቀጣዩ የሮማ ገዢ በራሱ ክልል ውስጥ ያሉትን ቤተ-ክርስትያናት ብቻ መቆጣጠር ጀመረ፡፡ ምዕራቡን ክፍልም ሌላ ሰው እንዲገዛ አደረገ፡፡ ምዕራባዊውን የሮማ ክፍል መቆጣጠር የጀመሩት የጀርመን ዝርያ ያላቸው ሰዎች፣ በ476 የሮማን የምዕራቡ ክፍል ገዢ ከስልጣኑ ላይ አስወግደው እናት መዲናው ወደ ሆነችው ወደ ኮንስታንቲኖፕል ላኩት፡፡ ይሄ የላቲን ምዕራብና የግሪክ ምስራቅ መለያየትም በቀጣይ ዘመናት የጸናው የላቲንና የግሪክ ክርስትያኖች ክፍፍል መጀመሪያ ነው፡፡

በምዕራቡ ብዙ ሰው የሚናገረው ቋንቋ ላቲን ነበረ፡፡ በምስራቅ ደግሞ ግሪክ፡፡ ምዕራብ ሮማ በወራሪዎች እጅ ከገባች በኋላ ሁለቱን ቋንቋዎች የሚናገር(ግሪክን በምዕራብ፣ ላቲንን በምስራቅ የሚናገር) ሰው ብዛት እየቀነሰ መጣ፡፡ ይሄም የምዕራቡንና የምስራቁን ተግባቦት ከባድ አደረገው፡፡ የቋንቋ አንድነት ሲጠፉ የባህል አንድነትም መቀነስ ጀመረ፡፡ ከመሰረቱ ሁለቱ ቤተ-ክርስትያናት የተለያየ መስመር ይዘው ነበረ፡፡ የተለያዩ ስርአቶችንና አስተሳሰቦችን ማራመድ ጀመሩ፡፡ ክፍፍሉ ገና ክፍለዘመናትን ቢጠብቅም በመሃል የተሰመረው መስመር ግን በግልጽ የሚታይ ነበር፡፡ ቀዳማዊ ጀስቲኒያን የተባለው የቢዛንታይን ገዢ፣ ንጉሱ ሁሉንም በቤተ-ክርስትያን ውስጥ የሚደረጉ ስርአቶችና ትምህርቶች የመቆጣጠር መብት አለው የሚል ህገ-መንግስት አስተዋወቀ፡፡   ይሄም ከዋናዎቹ የምዕራብና የምስራቅ ክፍፍል ምክንያቶች እንደ አንዱ ይወሰዳል፡፡ በመንግሰትና በቤተ-ክርስትያን መሃል ያለውን ግንኙነት የአውገስቲኑ ሒፖ “የእግዚአብሔር ከተማና የምድር ከተማ ይላቸዋል፡፡ ኢዩሲቢየስ ደግሞ “መንግስት ቤተ-ክርስትያንን ይጠብቃል፣ ንጉሱ ደግሞ በምድር የእግዚአብሔር ሹም ነው፡፡”

የሒፖው አውገስቲን(354-430) በአራተኛውና በአምስተኛው ክፍለዘመን የኖረ ክርስትያን ቲዮሎጂያንና ፈላስፋ ነበረ፡፡ የዚህ ሰው ጽሁፎች የምዕራቡ(የካቶሊክ) ክርስትናና ፍልስፍና ላይ ከፍተኛ ተጽእኖን አሳርድረዋል፡፡ አውገስቲን ከትላልቆቹ የምዕራብ ክርስትና አባቶች ውስጥ እንደ አንዱ ይታያል፡፡ አውገስቲን በወጣትነቱ ማኒቺዝም(መንፈሳዊ የብርሃን አለምና ቁሳዊው የጨለማ አለም እምነት)ና ኒዎፕላቶኒዝም(ስለ ተፈጥሮ እውነታ ጥቂት ተመሳሳይ አቀባበሎች ቢኖረንም እንደዚያው አስተያየትና አመለካከት ላይ የየራሳችን ልዩነት አሉን የሚል ፍልስፍና ነው፡፡ ስለዚህ የኒዎፕላቶኒዝምን ትርጉም ይሄ ነው ያ ነው ለማለት ይከብዳል) ከፍተኛ ተጽዕኖን አድርገውበታል፡፡ በ386 ከተጠመቀና ክርስትናን ከተቀበለ በኋላ የተለያዩ ስልቶችንና ግምገማዎችን በማካሄድ የራሱን ፍልስፍናና ቲዮሎጂ አሳደገ፡፡ አውገስቲን “የክርስቶስ ጸጋ ለሰው ነጻነት በጣም አስፈላጊ ነው” በሚል እምነቱ ይታወቃል፡፡ ከደህንነት(የመዳን ት/ት)ና የመንፈሳዊ ጸጋ ትምህርቱ የተነሳ ፕሮቴስታንቶች፣ በተለይ ሉተራኖችና ካልቪኒስቶች፣ አውገስቲንን ከቲዮሎጂ አባቶች እንደ አንዱ ያዩታል፡፡ በተለይ ማርቲን ሉተርና ሉተራኖች ከመጽሐፍ ቅዱስና ከጳውሎስ ቀጥሎ የሚከተሉት የአውገስቲንን ትምህርት ነው፡፡
ኦርቶዶክሶች ከአውገስቲን ጽሁፎች ይጠቅመናል የሚሉትን ተቀብለዋል፡፡ ነገር ግን ኦርቶዶክሶች “እኛ ጳውሎስ ይበልጥብናል፣ ምዕራባውያን ግን ባጠቃላይ ጳውሎስን በአውገስቲን አይን ነው የሚያዩት” ይላሉ፡፡
የኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስትያን የኤፌሶን ጉባኤ አጠቃላይ አዋጅ 7ኛ አንቀጽ እንዲህ ይላል፡ “መንፈሳዊ አባቶች መንፈስ ቅዱስ አግዟቸው በኒቂያ በመሰብሰብ የመሰረቱትን ሀይማኖት የሚጻረር ጽሁፍም ሆነ ሀይማኖት ህገወጥ ነው፡፡ ነገር ግን ሀይማኖት ከማጣትም ሆነ ከግራ መጋባት፣ የተለየ ሀይማኖትን መፍጠር የሚፈልጉ፣ ወይም የፈጠሩትን ሀይማኖት፣ እውነቱን ለመቀበል ለሚፈልጉ ሰዎች ማቅረብ ወይም ማስተዋወቅ የሚፈልጉ፣ ቄስ ወይም የሀይማኖት መሪ ከሆኑ ከቦታቸው እንዲነሱ ይደረግ(they shall be deposed)፡፡ የሀይማኖት መሪ ሳይሆኑ ከሆነ ደግሞ ይወገዙ(they shall be anathematized)፡፡”

በ7ኛው ክፍለዘመን ነቢዩ መሐመድ እስልምና የተባለውን ሐይማኖት ለአረቡ አለም አስተዋወቀ፡፡ ጨረቃንና ኮከብን ምልክቱ ያደረገውን አዲስ ሃይማኖት፣ አረቡ አለምና ሌላም ሀገሮች መከተል ጀመሩ፡፡ ይሄም ሙስሊሞችን ከአይሁዶችና ከክርስትያኖች ቀጥሎ፣ ሶስተኛው ሞኖቲክ ሃይማኖት ያደርጋቸዋል፡፡

10ኛው ክፍለዘመን በመካከለኛው ዘመን ተመራማሪዎች ከ3000 ዓ.ዓ. ወዲህ ጨለምተኛው ዘመን ተብሎ ይታወቃል፡፡ የግሪኮች ፍልስፍና የደረቀበት፣ የሮማውያን እውቀት የጠፋበት ዘመን ነበር፡፡ ትኩረት ሁሉ ሀይማኖት ላይ የነበረበት ክፍለዘመን ነበር፡፡ በሌላ በኩል ብዙ የሃይማኖት መሪዎች ለግሪክ ፍልስፍና ጆሮአቸውን መቀሰር የጀመሩበትም ነው፡፡

የክርስትያን ቲዮሎጂ

የክርስትያን ቲዮሎጂ የግሪኮች የምክንያታዊነት(የአመንክዮ) ባህል ውጤት ነው ይባላል፡፡ የጥንት ቲዮሎጂያን የነበረው ቴርቱሊያን ስለዚህ ጉዳይ “የፍልስፍናዋ አቴንስ የአምነቷን ኢየሩሳሌም እያጭበረበረች ነው” ሲል ቅሬታውን ገልጽዋል፡፡

በ2ኛውና 3ኛው ክፍለዘመን የነበረው ቀደምት ክርስትና ቅድመ-ኦርቶዶክስ ተብሎ ይታወቃል፡፡ ምክንያቱም በ4ኛው ክፍለዘመን ራሳቸውን ኦርቶዶክስ ብለው መጥራት የጀመሩት ክርስትያኖች ከሌሎች የበለጠ የቀደመውንና ኦሪጂናሉን ክርስትና ስለወረሱ ነው፡፡

የሮም ጳጳስን መንግስታዊ ጳጳስ የማድረግ ቲዮሎጂ ቀስ በቀስ ነው የመጣው፡፡ (ማቴ.16፡18-19)፡፡ ጳጳሶች የጴጥሮስ ወራሽ ወይም ተከታይ ተደርገው ነው የሚታዩት፡፡
የኦርቶዶክስ ሀይማኖትን የመመስረት ሂደት፣ ከክርስቶስ በኋላ በመጡ የተለያዩ የክርስቶስን ትምህርቶች የሚያጣምሙ አተረጓጎሞችን ለማጥፋትና እውነተኛውን ትምህርት ለማስረጽና ለማስቀጠል የመጣ ነው፡፡ ክርስቶስም ስለ ሀሰተኛ ነቢያትና አስተማሪዎች እንዲሁም ሀሰተኛ ክርስቶሶች ተናግሯል፡፡ (ማርቆስ 13፡22 ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉና፣ ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ ያስቱ ዘንድ ምልክትና ድንቅ ያደርጋሉ)፣ ማቴ.7፡5-20፣ ማቴ.24፡4፣ ማቴ.24፡11፣ ማቴ.24፡24፡፡ ጳውሎስም በመጽሐፍቱ ቤተ-ክርስትያናትን ከሐሰተኛ ወይም እሱ የሚያስተምራቸውን ትምህርት የሚጻረር የትኛውንም አይነት ትምህርት ከሚያስተምሩ አስተማሪዎች ራሳቸውን እንዲጠብቁ ያስጠነቅቃቸውና ይከላከላቸው ነበር፡፡ የዮሐንስና የይሁዳ መልዕክቶችም ቤተ-ክርስትያናት ከሐሰተኛ አስተማሪዎችና ነቢያት ራሳቸውን እንዲጠብቁ ያስጠነቅቃሉ፡፡ 2ኛይቱ የጴጥሮስ መልዕክት 2፡1-3ም እንዲሁ፡፡

በመጀመሪያዎቹ ሶስት ክፍለዘመናት የሮማ ንጉሰ ነገስትንና የሮማን ጣኦታት ለማክበር ሲባል ክርስትና ህገ-ወጥ ተደርጎ ስለነበር ቤተ-ክርስትያን ከተሰበሰበው ህዝብ(congregation) ውስጥ የተለየ ትምህርት የሚያመጡ ጠላቶች ላይ እርምጃ መውሰድ አልቻለችም፡፡ ነገር ግን እነኚህ አጭበርባሪዎች፣ “ሞኞች”፣ “ልክስክስ ውሾች”፣ “የሰይጣን አሽከሮች” እየተባሉ ይወገዙና ይገለሉ ነበር፡፡

የምዕራብና የምስራቅ ቲዮሎጂ

የኦርቶዶክስና የካቶሊክ **መሰረታዊ ልዩነቶች** እንዲህ ይብራራሉ፡
የኦርቶዶክስ(ምስራቃውያን) ቲዮሎጂ “ክርስትና እውነቱ ነው” ይላል፡፡ “ክርስትና የሁሉም ነገር(የሚታየው፣ የማይታየው፣ የሚታወቀው፣ የማይታወቀው) ፈጣሪ የሆነው እግዚአብሔር የሚታወቅበት ብቸኛውና እውነተኛው መንገድ ነው፡፡ ክርስትና ሰው ከሚናገረው፣ በፍልስፍናዊ እውቀትና ምክንያት ከሚገኘው እውነት ይልቅ የማይነቃነቅ እውነት ነው፡፡” ኦርቶዶክስ፣ በተረፈ ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር ለአዕምሮ ቀለል ባለ መንገድ ለማቀራረብ የሚደረግ የሰዎች ጥረት፣ የተወሰነ እውነት ቢኖረውም መጨረሻው ውድቀት ነው ይላል፡፡ ኦርቶዶክሶች የአንድ ሰው ሀይማኖት፣ ነፍሱ የሚያስፈልጋትን መንፈሳዊ ምግብ ማቅረብ አለባት ይላሉ፡፡ ኦርቶዶክሶቹ፣ ፍልስፍና፣ እግዚአብሔርን ለመቅረብ ከሚቻልባቸው መንገዶች አንዱ እንደሆነ ይቀበሉታል፡፡ ነገር ግን በመንገዱ ላይ ከሙሉነትና የሚያስፈልጉትን መስፈርቶች ከማሟላት አንጻር ሲታይ ፍልስፍና እጅ ያጥረዋል ይላሉ፡፡

ቪላድሚር ሎሲኪ የተባለ የምስራቅ ኦርቶዶክስ ቲዮሎጂያን፣ “የምስራቅና የምዕራብ ዋነኛው ልዩነት የሮማ ካቶሊክ ቤተ-ክርስትያን በመንፈሳዊና እውነተኛ ልምምድ አግዚአብሔርን ከማወቅ ይልቅ በሜታፊዚካል ፓጋን ፍልስፍና(metaphysical pagan philosophy) በመመራመርና ለስጋዊ አዕምሮ የሚመች ትርጉምን ለመፍጠር በመሞከርና ስኮላስቲሲዝም(የሃይማኖት አመክዮ)ን በማሳደግ መጠመዷ ነው” ይላል፡፡ ሎሲኪ ቀጥሎ “እግዚአብሔር፣ ባወጀው እውነት(በመጽሐፍ ቅዱስ) እና በሰው አስተሳሰብ ወይም በፍልስፍና ሊደረስበት በሚችለው እውነት መሃል ማለቂያ የሌለው ገደል አለ” ይላል፡፡ የምስራቅ ኦርቶዶክሶች “ቲዮሪያ”(theoria) የሚሉት ቲዮሎጂ፣ “በቀደምት የቤተ-ክርስትያን አባቶች የተመሰረተውና እውነተኛው ክርስትና፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ በተመሰረተ መንፈሳዊ ህብረት እግዚአብሔርን ማመን ነው” ይላል፡፡ ቲዮሪያ፣ ቃሉ በራሱ እግዚአብሔርን ማየት ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ዋናው ልዩነት ምስራቃውያኑ እንደ ምዕራባውያኑ ምክንያታዊ(rational) ማብራሪያ ከመስጠት ይልቅ በመንፈሳዊነት ማመናቸው ነው፡፡ ምስራቃውያኑ ማንም ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት የሚደረግበትን መንገድ ያልተከተለ ሰው መንፈስን መመርመር ወይም ቲዮሎጂያን መሆን አይችልም ብለው ያምናሉ፡፡
የምስራቁ የኦርቶዶክስ ሀይማኖተኞች ማንኛቸውም የቤተ-ክርስትያን አባቶች(ሐዋርያት) የአሪስቶትልን ሜታፊዚክስም ሆነ ስኮላስቲሲዝም እንዳልተቀበሉት ወይም እንዳልሰበኩ ነው የሚያስተምሩት፡፡ ስለዚህ የምዕራቡ ስኮላስቲሲዝም በምስራቅ የለም፡፡ ይሄም ማለት አንድ ሰው ቲዮሎጂያን ወይም የሥነመለኮት መምህር ወይም የእግዚአብሔር ሰው ለመሆን እንደ ድሮ በእግዚአብሔር የማያምኑ ፓጋን ማህበረሰብና የግሪክ ት/ቤቶች የዩኒቨርሲቲ ዲግሪ እንዲኖረው አይጠበቅበትም፡፡ አንድ ሰው የስነ-መለኮት አስተማሪ ወይም አዋቂ የሚሆነው ስጋን በመካድ ልምምድ ውስጥ እግዚአብሔር ሲገለጥለት ነው ይላሉ፡፡
ካቶሊክ ከፍልስፍናዋ ብዛት “በቀጣይ በሚመጡ ዘመናት ሰው በአዕምሮውና በጸጋ እርዳታ የእግዚአብሔርን ትክክለኛ ማንነት ያያል” ብላ ስታስተምር ነበር፡፡ ኦርቶዶክስ ደግሞ እንዲህ ስትል አወጀች፡ “እግዚአብሔርን ራሱን ማየት የማይቻል ነገር ነው፡፡ መንፈሳዊ ጸጋ እንኳን እንዲህ አይነቱን ሀይል አይሰጠንም፡፡ ነገር ግን የሚድኑት፣ በከበረው የክርስቶስ ስጋ አማካኝነት እግዚአብሔርን ያዩታል፡፡”

ስኮላስቲሲዝም(scholasticism)

ስኮላስቲሲዝም “scholasticus” ከሚል የላቲን ቃል የመጣ ሲሆን የት/ቤት(which belongs to school) ማለት ነው፡፡ ስኮላስቲሲዝም በመካከለኛው ዘመን ዩኒቨርሲቲዎች፣ በተማሩ ሰዎች(academics or schoolmen) የመማርና ማስተማር መንገድ ሲሆን ከገዳማዊ መማር ማስተማር ተገንጥሎ የወጣ ነው፡፡ ስኮላስቲሲዝም የጥንቱን ፍልስፍና ከመካከለኛው ዘመን የክርስትያን ቲዮሎጂ ጋር ማስታረቅ ጀመረ፡፡ ስኮላስቲሲዝም በራሱ ፍልስፍና ወይም ቲዮሎጂ አይደለም፡፡ ግን ወጣ ባላለ ምክንያታዊነት ክርስትናን የመማማሪያ ዘዴ ነው፡፡ መጀመሪያ ስኮላስቲሲዝም የተፈለገው ለጥያቄዎች መልስ ለመሻትና የተሳሳቱ ትምህርቶችን ለማጥፋት ነበረ፡፡

በ10ኛው ክፍለዘመን በምዕራባዊ ላቲን የጠፉ ብዙ የግሪክ ስራዎች ከተጣሉበት መፈለግ የጀመሩበት ነው፡፡ በ10ኛው ክፍለዘመን መጀመሪያ የስፔን ምሁራን እነኛን የግሪክ ስራዎች ትርጉም ጽሁፎች በማከማቸት በክፍለዘመኑ ሁለተኛ አጋማሽ በመላው አውሮፓ አሰራጩ፡፡

አውሮፓውያን የአረቦችን የሂሳብና የአስትሮኖሚ እውቀት በተለያዩ አጋጣሚዎች በገፍ መቀበል ጀመሩ፡፡ ከዚያ የሀይማኖት ምሁራን ለሴኪዩላሩ እውቀት ለዘብተኛና ተቀባይ ፍላጎት ማሳየት ጀመሩ፡፡
13ኛው ክፍለዘመን ስኮላስቲሲዝም በከፍተኛ ደረጃ የተንሰራፋበት ሲሆን ሳይንስ የተባለው የተፈጥሮ ፍልስፍና በስነ-መለኮታዊው መሬት ላይ በሙብቀል እንደገና ማበብ የጀመረበትም ዘመን ነው፡፡ የግሪክ ፍልስፍናም ከሞተበት ተነስቶ መራመድ ጀመረ ማለት ይቻላል፡፡ 13ኛው ክፍለዘመን ስኮላስቲሲዝም ከፍልስፍና ጋር ተቀይጦ ለሚወሳሰብበትና ለሚረቅበት 14ኛው ክፍለመን መግቢያ በር ሆነ፡፡ በ13ኛው ክፍለዘመን በገዳማት ውስጥ ጥበቃ ሲደረግላቸው የነበሩ መጽሐፍት ወደ ከተማና ወደ ዩኒቨርሲቲዎች መውጣት ጀመሩ፡፡ በዚህ ጊዜ በትላልቅ ከተሞች ትላልቅ ዩኒቨርሲቲዎች(University-ሁሉን አቀፍ) ተመሰረቱ፡፡
በአውሮፓ፣ 15ኛው ክፍለዘመን፣ በመካከለኛው ዘመን መጨረሻና በዘመናዊው ጊዜ(modern age)ና በሬኔሳንስ መጀመሪያ መሀል ያለ ድልድይ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡
ቢዛንታይን ኢምፓየር ወደቀ፡፡ ኮንስታንቲኖፕል በኦቶማን ቱርኮች እጅ ላይ ወደቀች፡፡ አብዛኛው ምስራቃዊ የኦርቶዶክስ ግዛቶችም፣ በኦቶማኖቹ፣ የእስልምና ሃይማኖት ስር ወደቁ፡፡ ኮኒስታንቲኖፕል ስሟ ወደ ኢስታንቡል ሲቀየር፣ ኮንስታንታይን ያስገነባቸው ትላልቅና ውብ ቤተ ክርስትያናት ወደ መስጊድነት ተቀየሩ፡፡
ይሄም ምዕራብ አውሮፓውያን አዲስ የገበያ ማዕከል የምትሆን ከተማ ማሰስ እንዲጀምሩ ምክንያት ሆነ፡፡ የአሰሳ ዘመን መጀመሪያ፡፡
የስፔናውያንና ፖርቹጋላውያን በአሰሳ ሁለቱን አሜሪካና አውሮፓን ከህንድ ጋር የሚያገኛኘውን የባህር መንገድ ማግኘታቸው፣ ቀጥሎ ለሚመጣው የፖርቹጋልና የስፔን የቅኝ ግዛት ኢምፓየር መነሳት ምክንያት ነው፡፡
በአስራ አምስተኛው ክፍለዘመን ኮንስታንቲኖፕል በመውደቋ የግሪክ አዋቂዎች ጽሁፎቻቸውን ይዘው ወደ ጣልያን እንዲፈልሱ ሆነ፡፡ ይሄም ጉተንበርግ ተንቀሳቃሽ የታይፕ ማሽን የፈጠረበትና የህትመት ስራ የተጀመረበት ጊዜ ነበር፡፡
16ኛው ክፍለዘመን ፕሮቴስታን የሚባለው ከካቶሊክ ተገንጣይ፣ የክርስትና ሃይማኖት የተመሰረተበት ምዕተአመት በመሆን ይታወቃል፡፡

የማርቲን ሉተር ሪፎርሜሽን ትሩፋቶች

(The Legacies of Martin Luther's Reformation)

14ኛው ምእተአመት፣ እስከ 17ኛው ምዕተአመት የዘለቀው ተሀድሶ ወይም ሬኔሳንስ የሚሉት የአስተሳሰብ አብዮት የጀመረበት ክፍለዘመን ነበረ፡፡ ሬኔሳንስ (Renaissance, rebirth:-of greek philosophy) የመካከለኛው ዘመንና የሰለጠነው(modern) ዘመን መሃል ያለ መሸጋገሪያ ድልድይ ነው፡፡ በጣልያን ውስጥ የባህል እንቅስቃሴ በመሆን የጀመረው ሬኔሳንስ በ15ኛው ክፍለዘመን የሰለጠነውን ዘመን በማምጣት በመላው አውሮፓ ተሰራጨ፡፡
በፊት እንደ ተገለጸው የሬኔሳንስ እሳቤ መሰረት፣ ከጥንት ግሪኮች ጽሁፎች እንደገና ግኝት(rediscovery) "ሰው የሁሉም ነገር መለኪያ ነው" ከሚሉት ፍልስፍና ተቀንጭቦ በራሱ በሬኔሳንስ የተቀረጸው ሂዩማኒዝም(humanism) ሲሆን ይሄ አዲስ አስተሳሰብ በአርት፣ በኪነህንጻ(አርኪቴክቸር)፣ ፖለቲካ፣ ሳይንስና ስነጽሁፍ ታይቷል፡፡ ተንቀሳቃሽ የብረት ታይፕ መፈጠሩ በ15ኛው ክ.ዘ. ሀሳቦችን በፍጥነት እንዲንሸራሸሩ አደረገ፡፡ ቢሆንም ግን በሬኔሳንስ የመጡ ለውጦች በሁሉም የአውሮፓ ክፍሎች እኩል አልተዳረሱም፡፡

ሬኔሳንስ ከሚታወስባቸው ትላልቅ አሻራዎቹ መሃል የስዕል አርትና ቀስ እያለ የተሰራጨው የትምህርት ሪፎርም በዋነኝነት ይጠቀሳሉ፡፡ በፖለቲካ፡ ከፍተኛ የዲፕሎማሲ ባህል፣ በሳይንስ፡- በምልከታ(observation)ና በጥልቅ ምክንያታዊነት (reasoning) ላይ መደገፍ፡፡

ሬኔሳንስ ካፈራቸው ከነዊሊያም ሼክስፒር፣ አይዛክ ኒውተን፣ ሊኦናርዶ ዳቪንቺ፣ ማይክል አንጄሎ፣ ጋሊሊዮ ጋሊሌንና ክሪስቶፈር ኮለምበስን ከመሳሰሉ ብዙ የብዙ ሙያ አባቶች መሃል የማይጠቀስ፣ ነገር ግን ሬኔሳንስ ወልዳው እሱ ሬኔሳንስን ያሳደጋት አንድ ሰው ነበረ፡፡

የሮማን ካቶሊክ ቤተ-ክርስትያንን የማሻሻል፣ የማደስ ወይም መልሶ የማዋቀር ሙከራ ቀድሞ በአንዳንድ ሰዎች የተደረገ ቢሆንም ስኬታማውንና ፕሮቴስታንት ሪፎርሜሽን የሚባለውን ሪፎርሜሽን ያስጀመረውና ፕሮቴስታንት የሚባለው አዲስ የክርስትና ሀይማኖት ጠንሳሽ የሆነው ማርቲን ሉተር ኖቬምበር 10፣ 1483ዓ.ም. ከአባቱ ከሃንስ ሉተርና ከእናቱ ማርጋሬት ሊንደርማን በቅድስት ሮማን ኢምፓየር፣ የጀርመን ግዛት ውስጥ በምትገኘው ሳክሶኒ፣ ኢዝልበን ከተማ ተወለደ፡፡ በ1484 የጨቅላው ማርቲን ቤተሰብ የማርቲን አባት የብረት ማእድ ማውጫና ማቅለጫ ባለቤት ወደሚሆንባትና ማርቲን ወደሚያድግባት ማንስፊልድ ተቀየሩ(ተዛወሩ)፡፡ ማርቲን ሉተር ብዙ ወንድምና እህቶች ነበሩት፡፡ የማርቲን አባት ለራሱና ለቤተሰቡ ስኬት በጣም ተነሳሽነት የነበረው ጉጉ ሰው የነበረ ሲሆን የሁሉም ልጆች ታላቅ የሆነው ልጁ ማርቲን፣ ሲያድግ ጠበቃ እንዲሆንለት ይመኝ ነበር፡፡ ማርቲን እድሜው ለትምህርት ሲደርስ ማንስፊልድ ውስጥ የሚገኝ አንድ የላቲን ት/ቤት ገባ፡፡ በ1497 በማግደበርግ ውስጥ በሚገኝ የቤተክርስትያን መዋቅር ውስጥ የሌሉ(ቄስ ያልሆኑ) ሰዎች በሚመሩት የህብረት ህይወት ወንድማማቾች የተባለ ት/ቤት፣ ትምህርቱን ቀጠለ፡፡ የህብረት ህይወት ወንድማማቾች(Brethren of the common life) በ14ኛው ክ.ዘ. በኔዘርላንድስ ውስጥ የሮማን ካቶሊክ ጠንካራ አማኞች ማህበር ነው፡፡ ይሄን ማህበር የመሰረተውም ጀራርድ ግሩት የተባለ የሀይማኖት ልምድ የነበረው የቀድሞ አለማዊ ትምህርት አስተማሪ ነበረ፡፡ ይሄ ሰውም በማይከብድ ሁኔታ ህይወትን ለኢየሱስ ክርስቶስ መስጠት(devotion)ን ይሰብክ ነበር፡፡ ማህበሩ የማይሰብሩትን ቃል ሳይገቡ የሚያገለግሉበት ማህበር ነው፡፡ ያላቸውን አለማዊ ነገር በመስጠትና በመታቀብ በጣም ጥብቅ በሆነ ህይወት ይኖራሉ፡፡ ሁሌ ማልደው በመነሳት መፈሳዊ አገልግሎቶች ላይ ይሳተፋሉ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ያነባሉ፣ ይሰብካሉ፡፡ የመስክ ስራ ይሰራሉ፡፡ እንዲሁም ት/ት ይማራሉ፡፡ ይሄ ህይወት ራስን ከአለም ከማራቅና ከአላማው አንጻር ከገዳማዊ ህይወት ጋር ቢመሳሰልም የሚለዩት ጥቂት ባህርያት አሉት፡፡ ማርቲን በቀጣዩ አመት በ1498 ኤይዘናክ የተባለ ት/ቤት ገባ፡፡ ሶስቱም ማርቲን ሉተር የተማረባቸው ት/ቤቶች ትሪቪየም(trivium) የሚሉት ግራመር፣ ርሄቶሪክንና ሎጂክን የሚያጠቃልል ትምህርት ላይ ነው የሚያተኩሩት፡፡ ሉተር በኋላ ላይ በሶስቱ ት/ቤቶች የነበረውን ህይወት ከቅጣትና ከገሃነም ጋር ያወዳድራል፡፡

በቀጣይ ማርቲን ሉተር በ19 አመቱ ኤርፈርት ዩኒቨርሲቲ ገባ፡፡ ይሄኛውን ደግሞ የስካርና የግልሙትና ቤት ይለዋል፡፡ ሽምደዳንና አስጨናቂ መንፈሳዊ ስርአቶችን ለመፈጸም በጠዋት በማለዳ ት/ቤት መሄድ ነበረበት፡፡ በ1505 ማስተርስ ዲግሪውን ተቀበለ፡፡ ሉተር የአባቱን ምኞት በመከተል እዚያው ኤርፈርት ዩኒቨርሲቲ ያኔው በ1505 የህግ ት/ት ጀምሮ ነበር፡፡ ነገር ግን ህግ፣ የማይገመትና የማይታወቅ ተሞላላጭ እንደሆነ ስላመነ ወዲያው ነበር የህግ ትምህርቱን ያቋረጠው፡፡

ሉተር ስለ ህይወት ዋስትናን ማግኘት፣ እርግጠኛ መሆን ፈለገ፡፡ መመራመር ጀመረ፡፡ እናም በስነ-መለኮትና በፍለስፍና ውስጥ ሰመጠ፡፡ በተለይ የአሪስቶትል፣ የዊሊያም ኦክሃምና የጋብሪኤል ቤል ስራዎች በጣም ይስቡት ነበር፡፡ ሁሉንም ነገር፣ ታላላቅ አሳቢ ሃያሲያንን እንኳን እንዲጠረጥርና ሁሉንም ነገር በራሱ ልምድ እንዲመረምር ያስተማሩት በርቶሎሜዎስ አርኖልዲ ቮን ዩዚንጀርና ጆዶከስ ትሩትፌተር የተባሉ ሁለት አስተማሪዎችም ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድረውበታል፡፡ ሉተር ፍልስፍና ስለ ምክንያት ጥቅም፣ መሳመን ቢችልም፣ ፍልስፍና እንደማያጠግብ አረጋገጠ፡፡ “ፍልስፍና ብዙ ይናገራል” አለ ማርቲን ሉተር፡፡ “ፍልስፍና ብዙ ምክንያት ይደረድራል፣ ነገር ግን ስላፈቀረን አምላክ፣ ምንም”፡፡ ለሉተር ከምንም በላይ አስፈላጊ ስለነበረው ጉዳይ፡፡ ሉተር “ምክንያት ወደ እግዚአብሔር አያደርስም” አለ፡፡ የአሪስቶተልን ፍልስፍና ቢወድም በእግዚአብሔር ላይ የሰጠው ትንታኔ ግን አልተመቸውም፡፡ ለሉተር፣ ሰውንና ተቋማትን በምክንያት መጠየቅ ይቻላል፡፡ እግዚአብሔርን ግን በምክንያት አይቻልም፡፡ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር መማር የሚችሉት በመንፈሳዊ መገለጥ ብቻ ነው ብሎ ስላመነ የእግዚአብሔርን ቃል በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ገብቶት ማንበብ ጀመረ፡፡ በጁላይ 2፣ 1505 ዓመተ-ምህረትም ውሳኔውን አጸና፡፡

በጁላይ ሺ አምስት መቶ ዜሮ አምስት ዓመተ-ምህረት ማርቲን ሉተር ለእረፍት የአባቱ ቤት ውሎ፣ ወደ ዩኒቨርሲቲ ሲመለስ፣ ቀኑ ዝናባማ ነበር፡፡ ሉተር ፈረስ ላይ ተፈናጦ፣ ወደ ትምህርት ቤቱ፣ በግልቢያ እየተመለሰ እያለ፣ መንገድ ላይ ከርሱ ብዙም ሳይርቅ አጠገቡ፣ መብረቅ ወደቀ፡፡ ሉተር ለአባቱ ሲነግረው “ሞትንና ዘላለማዊ ቅጣትን ፈራሁኝ፣ ቅድስት አና እርጂኝ መነኩሴ እሆናለሁ! ብዬ በለቅሶ ጮህኩኝ” አለ፡፡ (ቅድስት አና የማርያም እናት ነች) ለእርዳታ ያለቀሰውን ለቅሶም የማይሰብረውን መሃላ የገባበት መንገድ በማድረግ ተቀበለው፡፡ የህግ ትምህርቱን አቆመ፣ መጽሐፍቶቹን ሸጠ፡፡ ከዚያም በቀጥታ ጁላይ 17፣ 1505 ኤርፈርት ውስጥ የምትገኘው የአውገስቲን ገዳም ገባ፡፡ የሉተር አባትም በልጁ ትምህርት እንዲሁ መባከን በጣም ተናደደ፡፡
ሉተር በገዳሙ በመጾም፣ ለረጅም ሰአታት በመጸለይ፣ መንፈሳዊ ጉዞ በማድረግና በተደጋጋሚ ሃጢአቱን በመናዘዝ ለገዳሙ ስርአቶች እየተገዛ መኖር ጀመረ፡፡ ሉተር በገዳሙ የኖረበትን የህይወቱን ክፍል “መንፈሳዊ ተስፋ ማጣትን ያየሁበት” በማለት ይገልጸዋል፡፡ “ከአዳኙና ከተንከባካቢው ክርስቶስ ተለያየሁ፣ ክርስቶስን የደሃዋ ነፍሴ አሳሪ፣ አሰቃይና አንገላታች አድርጌ ወሰድኩት፡፡ በገዳሙ የሉተር የበላይ የነበረው ጆሃን ሰታውፒትዝ ሉተር አዕምሮውን ባለማቋረጥ ሃጢአቱ ላይ ከማንጸባረቅ ይልቅ የክርስቶስን መልካምነት እንዲያስብ መከረው፡፡ ማርቲን ሉተርም “ከስታውፒትዝ ጋር ባልገናኝ ነፍሴ በገሃነም ውስጥ በተቃጠለችም ነበር” ብሏል፡፡ እውነተኛ ንስሃ ራስን ማሰቃየትንና መቅጣትን እንደማያካትት ገባው፡፡ ይልቅ እውነተኛ ንስሃ ልብን መለወጥ ነው የሚል መደምደሚያ ላይ ደረሰ፡፡ በ1507 በቄስነት ተሾመ፡፡ በ1508 ደግሞ አዲስ የተመሰረተው የዊተንበርግ ዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያ ዲን የነበረው ራሱ ጆሃን ስታውፒትዝ ሉተር በዩኒቨርሲቲው ቲዮሎጂ እንዲማር ጋበዘው፡፡ ሉተርም በሁለት አመት በዩኒቨርሲቲው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና ሌላ አንድ በቲዮሎጂ ዙሪያ የሚሰጥ ትምህርት በመማር ሁለት የመጀመሪያ ዲግሪዎችን ተቀበለ፡፡ በ1512 ዶክተር ሆነ፡፡ (Doctorate of theology(D.Th.)፣ የPhilosophy Doctorate(Ph.D.) አቻ ነው)፡፡ በዚያው አመት በዊተንበርግ ዩኒቨርሲቲ ከስታውፒትዝ በመቀጠል የቲዮሎጂ ፋካልቲ ሃላፊ ሆነ፡፡
በ1515 የሳክሶኒና ተሪንጂያ ግዛቶች መንፈሳዊ መሪ ሆነ፡፡ ሀላፊነቱም በግዛቶቹ ስር ያሉትን አስራ አንድ ገዳማት በየጊዜው መጎብኘትና መምራትን ያጠቃልላል፡፡

የሮማን ካቶሊክ ቲዮሎጂ እንዲህ ይላል፡ “አንድ ሰው እምነቱ እውነተኛም ቢሆን ብቻውን አያጸድቀውም፡፡ ጽድቅ የሚወሰነው በመስጠትና በጎ ስራ በማድረግ ባለን እምነት ላይ ነው፡፡ በጎ ስራ የማድረግ ጥቅሞች የሚገኙት ደግሞ ለቤተ-ክርስትያን የገንዘብ ስጦታን በመስጠት ነው፡፡” እናም ቤተ-ክርስትያን ስጦታ ለሚሰጡ ሰዎች ወረቀት ትሰጣለች፡፡ ወረቀት ትሸጣለች፡፡ ሰዎች ይሄን ወረቀት የሚገዙት ቤተ-

ክርስትያኒቱ “በምድር ለሰራነው ሃጢአት፣ ወደ እግዚአብሔር መንግስት ከመግባትዋ በፊት ነፍሳችን ለመንጻት ከሚጠብቃት ስቃይ ለማምለጥ ነው” ብላ ስለምታስተምር ነበር፡፡ ወደ እግዚአብሔር መንግስት ከመግባት በፊት የምንቀበለው ስቃይ ተብሎ ሚታመነው ‘Purgatory’ ይባላል፡፡ ከፐርገቶሪ ያስመልጣል ተብሎ የሚገዛው ወረቀት ደግሞ የኢንደልጀንስ(indulgence) (የስርየት) ወረቀት፡፡ ታዲያ በዚያ ዘመን የሮማን ካቶሊክ ቤተ-ክርስትያን የኢንደልጀንስ ሀላፊ የነበሩት ጆሃን ቴዝል እንዲህ ሲሉ የኢንደልጀንስን ጥቅም አጋነኑ፡፡ “ከመቀሌ ውስጥ ሳንቲም ማቃጨል እንደ ጀመረች፣ ፐርገቶሪ ውስጥ ያለች ነፍስ ትፈነጥዛለች፡፡” (As soon as a coin in the coffer rings, the soul from purgatory springs.)

በ1516 የኢንደልጀንስ ሀላፊ የነበሩት ጆሃን ቴዝል በሮም የሚገነባው የቅዱስ ጴጥሮስ ቤተ-ክርስትያን ማሰሪያ የሚሆን ገንዘብ ለማሰባሰብና የስርየት ወረቀቱን ለመሸጥ ወደ ጀርመን ይሄዳሉ፡፡

በኦክቶበር 31፣ 1517 ማርቲን ሉተር የአውራጃው የቤተ-ክርስትያን መሪ ለሆኑት አልበርት ሜንዝ የስርየት ወረቀትን(indulgences) መሸጥ በመቃወም የተቃውሞ ደብዳቤ ጻፈላቸው፡፡ በደብዳቤው ውስጥ The Ninety-five theses(95ቱ አቤቱታዎች) ተብለው የሚታወቁት ማርቲን ሉተር በስርየት ወረቀት ሃይልና አቅም ላይ ያለውን ተቃውሞ የገለጸበትን ዝርዝር ነጥቦች ኮፒ አካቷል፡፡ ሒለርብራንድ የተባለ ጸሃፊ ሉተር በቤተ-ክርስትያን ስርአት ላይ ያለውን ጥያቄ ከመግለጽ ሌላ ምንም ቤተ-ክርስትያኒቱ ላይ ችግር የመፍጠርም ሆነ ቤተ-ክርስትያኒቱን የማጥቃት አላማ እንዳልነበረው ይናገራል፡፡ ነገር ግን በጥቂት አቤቱታዎቹ በተለይ አቤቱታ 86 ላይ ሉተር፡ “ዛሬ ላይ ሀብታቸው ከክሬሰስ(በሮማ ታሪክ በጣም ሀብታሙ ንጉስ) የበለጠ ሀብታም የሆኑት ጳጳሳችን ለምን የራሳቸውን ገንዘብ አስቀምጠው የቅዱስ ጴጥሮስን ቤተ-ክርስትያን በደሃው አማኝ ገንዘብ መስራት ፈለጉ?” የሚለው ድብቅ ሽኩቻን ያሳያል የሚሉ አሉ፡፡

ሉተር ጆሃን ቴዝለር ያሉትን መንግስተ ሰማያት ለመግባት ማረጋገጫ ሆኖ የቀረበውን “as soon as the coin…” አባባልም ተችቷል፡፡ “ምህረት እግዚአብሔር ብቻ የሚሰጠው እስከሆነ፣ የስርየት ወረቀት ገዢውን ከቅጣት አስመልጦ ዘላለማዊ ህይወት ይሰጣል የሚሉ በስህተት ውስጥ ናቸው፡፡ ክርስትያኖች እንዲህ አይነቱን የውሸት ዋስትና ተማምነው ክርስቶስን ከመከተል ወደ ኋላ ሊሉ አይገባም፡፡” ብሎ ተቃውሞውን ገለጸ፡፡

“ጌታችንና መሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስ ንስሃ ግቡ ሲለን ንስሃ መግባት የአማኞች ህይወት አንድ ክፍል አንዲሆን ፈልጎ ነው” የምትለው የሉተር የመጀመሪያ መግለጫ በጣም ታዋቂ ሆና ነበር፡፡ ሉተር በቀጣይ የመጀመሪያ ነጥቦቹ ንስሃ፣ ውጫዊና በስርአት የሚደረግ መናዘዝ ሳይሆን አንድ ክርስትያን በውስጡ ከሀጢአት ጋር የሚያደርገው ትግል እንደሆነ የሚገልጸውን ሀሳብ አስፍቶ ይከራከርበታል፡፡ ከ5-7 ያሉት መግለጫዎች ጳጳሱ፣ የሚያድኑት ራሳቸው ካዘዙት ወይም በቤተክርስትያን የቅጣት ስርአት ከተላለፈው ቅጣት እንጂ ሀጢአት ከሚያመጣው ጥፋት እንዳልሆነ ያብራራል፡፡ ጳጳሱ የሀጢአት ስርየትን ማወጅ የሚችሉት በእግዚአብሔር ስም እንጂ በራሳቸው አይደለም ይላል፡፡

ሉተር በላቲን ቋንቋ የጻፋቸው መግለጫዎች በ1517 ዓ.ም. ጀርመን ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ተባዝተዋል፡፡ ጃኑዋሪ 1518 የሉተር ጓደኞች 95ቱን አቤቱታዎች ከላቲን ወደ ጀርመንኛ ተረጎሙ፡፡ በሁለት ሳምንት ውስጥ የመግለጫዎቹ ኮፒዎች ጀርመንን አዳርሰው ነበር፡፡ በሁለት ወር ውስጥ ደግሞ በመላው አውሮፓ ተሰራጩ፡፡

ከ14-29 ባሉት አቤቱታዎች በፐርገቶሪ ዙሪያ ያለውን እምነት ይቃወማል፡፡ ከ14-16፡ የፐርገቶሪ ቅጣትን ሊሞቱ ያሉ ሰዎች ከሚሰማቸው ፍርሃትና ተስፋ መቁረጥ ጋር እያነጻጸረ ያወራል፡፡ 17-24፡ ፐርገቶሪ ውስጥ ስላሉ ሰዎች መንፈሳዊ ሁኔታ በእርግጠኝነት ምንም ማለት አይቻልም፡፡ በ25ና 26፡ ጳጳሱ ፐርገቶሪ ውስጥ ባሉ ሰዎች ላይ ምንም አይነት ስልጣን የላቸውም ይላል፡፡ ከ27-29 ባለው አቤቱታ ደግሞ ክፍያ እንደተከናወነ የከፋዩ ወዳጅ ከፐርገቶሪ ይለቀቃል የሚለውን ሀሳብ ይተቻል፡፡ይሄንንም ሀጢአት የመስራት ፍላጎትን ማበረታታት ነው ይለዋል፡፡ እናም ፐርገቶሪ ውስጥ ያሉትን ይቅር የማለት ሃይል የእግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ ይናገራል፡፡ ከ30-34 ባሉት መግለጫዎቹ የስርየት ወረቀት ሰባኪዎች ለክርስትያኖች ስለሚሰጡት የውሸት የማረጋገጫ ወረቀት ጽፎአል፡፡ አንድ ሰው በእውነት ንስሃ መግባት አለመግባቱ ሳይታወቅ የሚሰጥ የስርየት ማረጋገጫ ወረቀት አደገኛ አይሆንምን? ይላል፡፡ 35-36፡ የስርየት ወረቀት ንስሃ መግባትን አላስፈላጊ የሚ ያደርግበትን ሀሳብ ይቃወማል፡፡ ሉተር በእውነት ንስሃ የገባ ክርስትያን ያለምንም ወረቀት ከሀጢአቱና ከሚከተለው ቅጣት ይቅር ይባላል ይላል፡፡ ከ41-47፡ አንድ ሰው ኢንደልጀንስ ከሚገዛ ይልቅ በገንዘቡ ደሃ ቢረዳ የበለጠ ምንም ማወዳደር በማይቻል መልኩ ጠቃሚ እንደሆነ ነው ቤተ-ክርስትያን ማስተማር ያለባት ይላል፡፡ አንድን ሰው ደሃን መርዳት የተሻለ ሰው ያረገዋል፡፡ ኢንደልጀንስ መግዛት ግን አያረገውም ነው፡፡ ከ48-52 ባለው መግለጫ ደግሞ ጳጳሱን ይደግፋል፣ “ጳጳሱ በስማቸው ምን እየተሰበከ እንዳለ ቢያውቁ፣ የቅዱስ ጴጥሮስ ቤተ-ክርስትያን በበጎቻቸው ስጋና ደም ተገንብቶ ከሚቆም ይልቅ ተቃጥሎ አመድ ቢሆን ይመርጣሉ” ይላል፡፡ ከ55-66 ደግሞ Treasury of merit የሚሉትን የመልካም ስራ ክፍያ መዝገብ ማከማቻን ይቃወማል፡፡ ክርስትያኖች ዶክትሪኑ እንደማይገባቸውና ወደ ተሳሳተ አቅጣጫ እየተነዱ እንደሆነ ይናገራል፡፡ ለሉተር እውነተኛው የቤተ-ክርስትያን ውድ ሀብት የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ነው፡፡ በማቴ.19፡30ና 20፡16 ላይ “ኋለኞች ፊተኞች፣ ፊተኞችም ኋለኞች ይሆናሉ” የሚለውን ቃል በመጠቀም ይሄ ትሬዠሪ ሜሪት ፊተኞችን ኋለኞች ስለሚያደርግ በክርስትያኖች መጠላት አለበት ይላል፡፡ ሉተር የወንጌል ሀብት ባለጠጋ ሰዎችን ለማጥመድ፣ የኢንደልጀንስ ሀብት ደግሞ የባለጠጎችን ሀብት ለማጥመድ የተዘረጉ መረቦች እንደሆኑ ለማብራራት ሜታፎር(metaphor) እና ዎርድፕሌይ(wordplay) የተባሉ የንግግር ስልቶችን ይጠቀማል፡፡ ከ67-80፡ ሰባኪዎቹ ኢንደልጀንስ ቤተ-ክርስትያን ከምትሰጣቸው የጸጋ ስጦታዎች ከፍተኛው እንደሆነ አድርገው ሲያስተምሩ እንደነበረና የሚሰብኩት ግን ስስትን እንደሆነ ይገልጻል፡፡ ከ81-91 ሉተር ማህበረሰቡ በኢንደልጀንስ ላይ ያለውን ተቃውሞ ይገልጻል፡፡ “ጳጳሱ

ከፐርገቶሪ የማውጣት ስልጣን ካላቸው ለምን ሁሉንም ሰው እንዲሁ አያወጡም ብዬ ስጠየቅ ምን ብዬ ልመልስ?` ይላል፡፡ እግዚአብሔርን ለሚፈሩ ሰዎች እንደፈለጉ ኖረው ፐርገቶሪ ውስጥ ምህረት ይደረግላችኋል መባል ግራ ያጋባል፡፡
ሉተር 95ቱን አቤቱታዎች "ከሐሰተኛ ደህንነት፣ ቅጣትን ተቋቁሞ የእግዚአብሔርን መንግስት መውረስ ይመረጣል በማለት ክርስትያኖች መከራና ስቃይ ቢኖረውም ክርስቶስን እየመሰሉ እንዲኖሩ በማሳሰብ ያገባድዳል፡፡

እኚህን አቤቱታዎች ተደርጎ ስለማወቁ ማስረጃ ባይኖርም ለስነ መለኮት ተማሪዎችና አስተማሪዎች መከራከሪያ ሀሳብ እንዲሆን ነበር ሉተር የጻፈው፡፡ ሉተር በአቤቱታው መጀመሪያ ላይ ለመራከር ፍላጎቱን ያላቸውን ምሁራን ከየከተማው እንዲሳተፉ ጋብዟል፡፡ ሉተር ያኔ የክርክር መድረክ ማዘጋጀቱ እንደ ዶክተር ከሚኮራባቸው ነገሮች አንዱ ሲሆን ይሄም በት/ቤት ውስጥ ያልተለመደ ነገርም አልነበረም፡፡ የሉተር አቤቱታዎች አላማ ምሁራን አዋቂዎች እንዲከራከሩበት እንጂ ታዋቂ አብዮትን መጀመር አልነበረም፡፡ አንዳንዶች ግን በቤተ-ክርስትያን ውስጥ ውዝግብ መፍጠር ፈልጎ ነው ይሉ ነበር በጊዜው፡፡ ነገር ግን እሱ ራሱ ስራውን እንደ ትንቢታዊና በጣም አስፈላጊ አድርጎ እንዳየው የሚያሳዩ ምልክቶች ነበሩ፡፡

ሉተር ከካቶሊክ ቤተ-ክርስያን የተነሳበትን ቁጣና የሚቀርብበትን ክስ በመመከት ሲጠመድ፣ 95ቱ አቤቱታዎቹ በመላው አውሮፓ እየተዳረሱ ነበር፡፡ ሉተር ይሄንን የአቤቱታ መልዕክት ከካቶሊክ ቤተ-ክርስትያን ለመለያየት አይደለም የጻፍኩት ይላል፡፡ የሆነው ግን ሪፎርሜሽን ነበረ፡፡ ነገሮች ስር ከሰደዱ ወዲህ ሉተር ከካቶሊክ ቤተ-ክርስትያን ጋር ስላለው ቅራኔ ሲናገር የስርየት ወረቀት ዋናው ከካቶሊክ የምንለይበት ዶክትሪን አይደለም ይላል፡፡ "ከካቶሊክ ቤተ-ክርስትያን የሚለዩን ብዙ አስተምህሮዎች አሉ፡፡"

ከ1510 እስከ 1520 ሉተር መዝሙረ ዳዊትን፣ ዕብራውያንን፣ ሮሜንና ገላትያን ሲያስተምር ነበረ፡፡ ከእነዚህ መጽሐፍት ስለ ጽድቅና ኩነኔ ሲያስተምር ታዲያ የካቶሊክ ቤተ-ክርስትያን ከምታስተምርበት መንገድ ወጣ ባለ መንገድ ነበር የሚያስተምረው፡፡ ቤተ-ክርስትያን በተለያዩ መንገዶች ሙሰኛ እንደነበረችና የክርስትናን ዋና ዋና እውነታዎች እንደሳተች ራሱን አሳመነ፡፡ ለሉተር ዋነኛውና በጣም አስፈላጊው ዶክትሪን የጽድቅ ዶክትሪን ነው፡፡ እግዚአብሔር ኃጢአተኛን የዋጀበት ጽድቅ፡፡ በእምነትና በእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ የሚገኘው ጽድቅ፡፡ ምህረትና ደህንነት የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታዎች እንደሆኑና ምህረትን ማግኘት የሚቻለውም አዳኝ በሆነው በመሲሁ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ እንደሆነ ማስተማር ጀመረ፡፡ "ይሄ የማዕዘን ድንጋይ የምንለው የጽድቅ ዶክትሪናችን የሁሉንም መዳን የሚያጠቃልለው የሁሉም የክርስትያን መመሪያዎች መመሪያችን ነው" ብሏል፡፡ ሉተር ጽድቅ ባጠቃላይ የእግዚአብሔር ብቻ ስራ እንደሆነ በተለያዩ መጽሐፍቱ ላይ በግልጽ ጽፏል፡፡ "ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፣ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም፡፡ እኛ ፍጥረቱ ነንና፤ እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን፡፡" የሚለውን የኤፌ.2፡8-10 ጥቅስ በመጥቀስ በዚያ ዘመን የተንሰራፋውን "የጽድቅ ስራዎች ከእግዚአብሔር ጋር ለመተባበር ነው የሚደረጉት" የሚለውን ትምህርት ይቃወማል፡፡ ሉተር ክርስትያኖች እንዲህ አይነቱን ጽድቅ በሙሉ ከራሳቸው ውጪ ነው የሚያገኙት ብሎ ጽፏል፡፡ ጽድቅ ከክርስቶስ ብቻ ሳይሆን ይላል፣ ክርስቶስ ሀጢአታችንን ተቀብሎ የሰጠን በእምነት የምንቀበለው የክርስቶስ ጽድቅ ነው፡፡ "ለዚህ ነው እምነት ብቻውን አንድን ሰው ጻዲቅ የሚያደርገውና ሰውየው ህግን የሚፈጽመው፡፡ እምነት በክርስቶስ ስራ መንፈስ ቅዱስን የሚሰጠን ነው፡፡" ለሉተር እምነት የእግዚአብሔር ስጦታ ነው፡፡ "በእምነት የመጽደቅ ልምምድ እንደገና መወለድ ነው፡፡ ካመኑ በኋላ የእግዚአብሔር መንግስትና የእግዚአብሔርን ጽድቅ ስለመፈለግ አይደለም፡፡ በሮሜ 1፡17 እንደተጠቀሰው ጽድቅን ካገኙ በኋላ በእምነት ስለመኖር እንጂ፡፡ "ጻድቅ በእምነት ይኖራል ተብሎ እንደተጻፈ የእግዚአብሔር ጽድቅ ከእምነት ወደ እምነት በእርሱ ይገለጣልና፡፡"

"የመጀመሪያውና የሁሉም መሪ ዶክትሪናችን ይሄ ነው፡ ጌታችንና መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞቷል፣ ስለ ጽድቃችንም ከሙታን ተነስቷል፡፡ (ሮሜ 3፡24-25)፡፡ እርሱ ብቻውን የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግደው የእግዚአብሔር በግ ነው፡፡ (ዮሐ. 1፡29)፡፡ እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ፡፡ (ኢሳ. 53፡6)፡፡ ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋል፣ በኢየሱስ ክርስቶስም በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ፡፡ እርሱንም እግዚአብሔር በእምነት የሚገኝ በደሙም በሆነ ማስተስርያ ነው፤ (ሮሜ 3፡23-25)፡፡ ይሄን ማመን በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ይሄም በሌላ መንገድ በየትኛውም አይነት ስራ፣ በችሎታና በሕግ ሊገኝም ሆነ ሊደረስበት አይችልም፡፡ ስለዚህም በእምነታችን መጽደቃችን ግልጽና እርግጥ ነው፡፡ ከዚህ ዶክትሪን ምንም ነገር ሊቀነስም ሆነ ሊጨመር አይችልም፡፡ ሰማይና ምድር፣ ሁሉም ነገር ቢወድቅ እንኳን፡፡ (ማር. 13፤31)፡፡"

የሉተር ክርስቶስንና የክርስቶስን ማዳን እንደገና ማግኘት የሪፎርሜሽን መሰረት ከሚባሉት ሁለት ነጥቦች መሃል አንዱ ነው፡፡ የስርየት ወረቀት(ኢንደልጀንስ) ላይ የከፈተው ተቃውሞ የዚህ ግኝት ውጤት ነው፡፡
የሜንዝና የማግደበርግ ዲያቆናት መሪ የነበሩት ቄስ 95ቱን መግለጫዎች የሚያካትተውን የሉተር ደብዳቤ መልስ አልጻፉለትም፡፡ ደብዳቤው ባዕድ ስለሆነባቸው ወደ ሮም ላኩት፡፡ ፖፕ ሊዮ 10ኛ አለመግባባቶች እንደተፈጠሩ አወቁ፡፡ "በተቻለ መጠን ሁኔታውን በከፍተኛ ጥንቃቄ ለመገምገም" እንዳሉት በቀጣይ ሶስት አመታት በተከታታይ በሉተር ላይ ቲዮሎጂያኖችን አሰማርተው አዘመቱ፡፡ ይሄም የሪፎርመሮችን የጸረ-ጳጳስ ቲዮሎጂ ከማጠናከር ባለፈ ምንም አልጠቀመም፡፡ በኦክቶበር 1518 ውስጥ ለሶስት ቀናት ሉተር ለቃለ-መጠይቅ የጳጳሱ ባልደረቦች ፊት

እንዲቀርብ ተደረገ፡፡ የጳጳሱ የስርየት ወረቀት የመስጠት መብት ማዕከላዊው፣ ክርክር የተካሄደበት ጉዳይ ነበር፡፡ በተደረገው ቃለ-ምልልስ ክርክር ከመብዛቱ የተነሳ የጩኸት ውድድር እየተደረገ የነበረ ነበር የሚመስለው፡፡ መግለጫውን ከመጻፉም በላይ ሉተር ቤተ-ክርስትያንን መጋፈጡ የጳጳሱ ጠላት ተደርጎ እንዲቆጠር አደረገው፡፡ ዕቅዱ ሉተር ይሄን ሀሳቡን የማይተው ከሆነ ሊያሳስሩት ነበረ፡፡ ነገር ግን ሳያደርጉት ቀሩ፡፡ ሉተርም ከከተማዋ ተደብቆ ጠፋ፡፡

በጃኑዋሪ 1519 አልተበርግ ሳክሶኒ ውስጥ ጳጳሱ ካርል ቮን ሚሊትዝ ተግባቢ ሆነው ቀረቡት፡፡ ሉተር ለሳክሶኒው ጳጳስ እንደሚያቆም ቃል ገባላቸው፡፡ ተቃዋሚዎቹም የሚተዉት ከሆነ ዝም ለማለት ተስማማ፡፡ ነገር ግን ጆሃን ኤክ የተባለ ቲዮሎጂያን የሉተርን ዶክትሪን በህዝብ ፎረም ላይ መወያያ ርዕስ እንዲሆን አደረገው፡፡ በጁንና በጁላይ 1519 ሌፐዚግ በተባለች የጀርመን ከተማ ኤንድሪስ ካርልስታት የተባለ የሉተር ባልደረባን የክርክር መድረክ አዘጋጅቶ ሲገጥመው ሉተርንም እንዲናገር ጋብዞት ነበረ፡፡ ሉተር አጽእኖት ሰጥቶ የተከራከረበት ሀሳብ ማቴ. 16፡18 ለጳጳሶች የእግዚአብሔርን ቃል ለመተርጎም የተለየ መብት አይሰጣቸውም፣ ስለዚህም ጳጳሱና የቤተ-ክርስትያን አማካሪዎች የሚባሉት ተቀባይነት ሊኖራቸው አይገባም፡፡ ለዚህ አስተሳሰቡ ጋባዡ ኤክ ሉተርን፣ በ1415 በታሰረበት እንዲሰቀል ከተደረገው ጃን ሁስ ከተባለ ቼክ-ሪፐብሊካዊ አዲስ ትምህርት አምጪና ሪፎርመር ጋር አነጻጸረው፡፡

የሉተርን 95 መግለጫዎች የማሳገዱ ሂደት ወደ ሴኪዩላሩ ባለ-ስልጣናት ተሸጋገረ፡፡ በኤፕሪል 18፣ 1521ም አስጠርተው አነጋገሩት፡፡ ከጃኑዋሪ 28-ሜይ 25 1521 በንጉሰ-ነገስት ቻርለስ አምስተኛ የሚመራ ስብሰባ ተካሄደ፡፡ የሳክሶኒው ልዑል፣ ፍሬድሪክ ሶስተኛ ሉተር ላይ ምንም አይነት ጥቃት እንዳይደርስበትና ደህንነቱ ተጠብቆ ስብሰባውን እንዲሳተፍ ሁኔታውን አመቻቸ፡፡

ስረወ መንግስቱን ወክሎ የተናገረው ጆሃን ኤክ የተቃውሞ አቤቱታዎቹን ለሉተር በማሳየት የሱ እንደሆኑና በያዙት ሀሳብ ያምን እንደሆነ ጠየቀው፡፡ ሉተርም ጽሁፎቹ የራሱ እንደሆኑ አመነ፡፡ ለሁለተኛው ጥያቄ ግን አስቦበት እንዲመልስ ጊዜ እንዲሰጡት ጠየቀ፡፡ ሉተር እውነትም ጊዜ ያስፈልገው ነበር፡፡ ምክንያቱም ቀጥሎ አዎ ትክክል ነኝ ወይም አይ ተሳስቻለሁ ብሎ የሚናገረው ነገር፣ በርግጥም የሰውን ልጅ የህይወት ግብ የመቀያየር አቅም ነበረው፡፡ ጸለየ፣ ጓደኞቹን አማከረ፣ በቀጣዩ ቀንም ቃሉን ሰጠ፡፡ አለምን የሚገለብጠውን ቃል፡፡ ያቺ ቀን ከክርስቶስ ኢየሱስ የልደት ቀን፣ ከሞተበት፣ ከሞትም ከተነሳበትና ወደ ሰማይ ካረገበት ቀን ቀጥላ በሰው ልጅ ታሪክ አቅጣጫ ቀያሪ ተርኒንግ ፖይነት የሆነች ቀን ነች፡፡

"በእግዚአብሔር ቃል ማረጋገጫ እስካላገኘሁ ወይም በግልጽ ምክንያት እስካልሆነ በጳጳሱም ሆነ በአማካሪዎቻቸው ውሳኔዎች ብቻ ስለማላምን፣ በተለይ የተሳሳተ መንገድ ላይ መሆናቸውና ለስህተት ራሳቸውን ማጋለጣቸው ግልጽ እስከሆነ ድረስ፣ በነሱ ሳይሆን በጽሁፌ ላይ በጠቀስኳቸው የእግአብሔር ቃል ጥቅሶች እገደባለሁ፡፡ ህሊናዬም የእግዚአብሔር ቃል ግዞተኛ ነው፡፡ ህሊና የማይፈቅደውን ነገር ማድረግ ትክክልም፣ አግባብም ስላልሆነ ምንም ነገር ልመልስ ወይም ልክድ አልችልም፡፡ አልክድምም፡፡ እግዚአብሔር ይርዳኝ፡፡ አሜን፡፡" የአሸናፊ ወታደር ሰላምታ ሰጠ፡፡

በቀጣይ አምስት ቀናት ሉተርን ምን እንደሚያረጉት ለመወያየት ዝግ ኮንፍረንሶች ተደረጉ፡፡ ንጉሰ-ነገስቱ የመጨረሻውን የዎርምስ አዋጅ(Edict of worms) ረቂቅ አስተዋወቁ፡፡ አዋጁም ሉተርን ህገ-ወጥ እንደሆነ ያውጃል፡፡ ጽሁፎቹን ያግዳል፣ እንዲታሰር ትእዛዝ ያስተላልፋል፡፡ "እንደ ባዕድና አዲስ እምነት አምጪነቱ እንዲያዝና እንዲቀጣ እንፈልጋለን"፡፡ አዋጁ ማንም ጀርመናዊ ለሉተር ምግብ ቢሰጥ ወይም ቢያሳድረው ወንጀለኛ እንደሆነ ያትታል፡፡ ማንም ሉተርን ቢገድል ምንም አይነት የህግ ጣጣ እንደማይከተለውም ማረጋገጫ በመስጠት ሉተርን የመግደል ፈቃድ ይሰጣል፡፡

ሉተር በጉዞው ላይ ወደ ዊተንበርግ ሲመለስ መጥፋቱ ቀድሞ የታቀደ ነበር፡፡ ፍሬድሪክ ሶስተኛ ሉተርን ያሳፈነው ሉተር በጫካ ውስጥ ወደ ቤቱ እየተጓዘ እያለ ዊተንበርግ ሊደርስ አካባቢ ነው፡፡ ያፈኑት ፈረሰኞችም ፊታቸውን በጭምብል የሸፈኑ የነበሩ ሲሆን እንደ ታጣቂ መንገደኛ ዘራፊዎች መሰለው ነበር፡፡ ዋርትበርግ ቤተ-መንግስት እስኪደርሱ ድረስ ሉተርን በተጠንቀቅ ጠበቁት፡፡ ሉተር በዋርትበርግ ቤተ-መንግስት ቆይታው አዲስ ኪዳንን ከግሪክኛ ወደ ጀርመንኛ ተረጎመ፡፡ ብዙ ዶክትሪኖችንና ልብ የሚገዙ ጽሁፎችንም ጻፈ፡፡ በዚህ ስራው በእምነት ላይ ከሰጣቸው መግለጫዎች ሃይለኛ በሚባለው ይከራከራል፡፡ "በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት የትኛውም መልካም ስራ ኃጢአት ነው" ይላል፡፡ "ሁሉም ሰዎች በተፈጥሮ ኃጢአን ናቸው፡፡ እናም በገንዘብ የማይገዛው የእግዚአብሔር ጸጋ ብቻውን ሊያጸድቃቸው ይችላል፡፡" ሉተር በተመሳሳይ እንዲህ ሲል ለአንድ ሰው ጽፏል፡ "ኃጢአተኛ ሁን፣ ኃጢአትህም ጠንካራ ይሁን፣ ነገር ግን በክርስቶስ ያለህ እምነት ከዚያ የበለጠ ይጠንክር ኃጢአትን፣ ሞትንና ዓለምን ድል በነሳው በክርስቶስም ደስ ይበልህ፡፡ ይሄ ህይወት ፍትህ ስለሌለበት፣ በዚህ ዓለም እስካለን ኃጢአትን እናደርጋለንና፡፡"

ሉተር በ1521 ክረምት ትኩረቱን ከስርየት ወረቀትና መንፈሳዊ ጉዞ አይነት ጉዳዮች የቤተ-ክርስትያን ልብ ወደ ሆኑ ስርአቶች አሰፋው፡፡ ርዕሱ Confession, whether the pope has the power to require it በሆነው ጽሁፉ ላይ ስርአት የሆነውን፣ ኃጢአትን ለቄስ መናዘዝን ይቃወማል፡፡ እናም የግል ኑዛዜንና ንስሃን ያበረታታል፡፡ "ሁሉም ክርስትያን ተናዛዥ እስከሆነ የሚናዘዙለት ሰው አያስፈልግም" ይላል፡፡ በኖቬምበር ውስጥ The Judgement of Martin Luther on Monastic Vows የሚል ርዕስ ያለው ጽሁፍ ጻፈ፡፡ በዚህ ጽሑፉ ደግሞ

መነኮሳት ያለ ምንም ኃጢአት ቃል ኪዳናቸውን መስበር እንደሚችሉ ያረጋግጥላቸዋል፡፡ ምክንያቱም ቃል ኪዳኖች አግባብ ያልሆኑ ጥቅመ-ቢስ የዘላለም ህይወትን ለማግኘት የሚደረጉ ሙከራዎች ናቸው፡፡”

ማርቲን ሉተር በ1521 የካቶሊክ እምነትን ከትንቢት ጋር በማገናኘት የሪፎርሜሽንን መሰረት አሰፋ፡፡ ዋናው የሉተር ፍላጎት በትንቢተ ዳንኤል 8፡9-12፤23-25 የተጠቀሰውን ታናሽ ቀንድ ማዕከል ያደረገ ነው፡፡ 2 ተሰሎንቄ 2 ላይ የተጻፈው የክርስቶስ ተቃዋሚ፣ የጳጳሱ ስልጣን ነው ይላል፡፡ “ሮማ ምትክፋፈልበት የዳንኤል 7ቱ ታናሽ ቀንድ ትንቢትም ተፈጽሞአል፡፡”

ሉተር በደህና ከተደበቀበት የዋትበርግ ቤተ-መንግስት፣ ቤተሰቡ በሚኖሩባት ዊተንበርግ እየተካሄደ ስለነበረው ከፍተኛ ለውጥ በሙሉ መረጃ ሲደርሰውና በጽሁፍ መግለጫ ሲሰጥበትም ነበር፡፡ ኤንድሪስ ካርልስታት አውገስቲኒያን በነበረው ጋብሬል ዝዊሊንግ በመታገዝ ጁን 1521 በሉተር የተጀመረውን ስራ በማሳደግ ትልቅ የማሻሻያ(reform) ማዘጋጀት ጀመሩ፡፡ ሪፎርሞቹ ረብሻን ቀሰቀሱ፡፡ የካቶሊክ ቤተ-ክርስትያን አውገስቲኒያን ተከታዮች በመሪ ቄሶቻቸው ላይ ተነሱ፡፡ የቤተ-ክርስትያን ሀውልቶች ተደረማመሱ፣ ስዕሎች ተቀዳደዱ፡፡ ብዙ ሰዎች ለጳጳሱና ቤተ-ክርስትያን ውስጥ ላለው የስልጣን ተዋረድ እውቅና እንደማይሰጡ በድፍረት ገለጹ፡፡

በዲሴምበር መጀመሪያ 1521 ዓ.ም. ሉተር በድብቅ ዊተንበርግን ከጎበኘ በኋላ “ሁሉም ክርስትያን ሁከትንና ብጥብጥን እንዲቃወም” የሚል ጥብቅ መግለጫ ጽፎ ላከ፡፡ ዊተንበርግ፣ ከገና በኋላ “ዝዊካው ፕሮፌትስ” ብለው ራሳቸውን የሰየሙት ባለ-ራዕይ ሀይማኖተኞችን መምጣት ተከትሎ ለመገመት አስቸጋሪ ሆነች፡፡ እነኚህ አክራሪዎች፣ በሪፎርሜሽን አብዮታዊ ዶክትሪኖች የሆኑትን የሰዎች እኩልነት(equality of men)(ከሀብትና ከሀይማኖት አንጻር)፣ ራስን ካወቁ በኋላ መጠመቅንና የክርስቶስ መመለሻ መቃረቡን መስበክ ጀመሩ፡፡ የዊተንበርግ ምክር-ቤት ሉተር ወደ ከተማው እንዲመለስ ሲጠይቀው ሉተር የመመለስ ሀላፊነት እንዳለበት አመነ፡፡

ማርች 6፣ 1522 ሉተር በድብቅ ወደ ዊተንበርግ ተመለሰ፡፡ ሉተር ለከተማው ርዕሰ መስተዳደር “እኔ ባልነበርኩበት፣ ሰይጣን ከበረቴ ዘልቆ፣ በአካል በመገኘትና በእግዚአብሔር ቃል ካልሆነ፣ እኔ በጽሁፍ ብቻ የማልመልሰውን ከፍተኛ ጥፋት አድርሷል”ሲል ተናገረ፡፡

በሌንት(Lent)(የፋሲካ ጾምና ጸሎት ቀናት) ውስጥ ለስምንት ቀናት፣ “ከመጀመሪያዋ የጾም ወቅት እሁድ” ማርች 9 ጀምሮ ሉተር ስምንት ትምህርቶችን ሰበከ፡፡ በስብከቱም የክርስትያን ትርጉም(value) የሆኑትን ፍቅር፣ ትዕግስና መልካምነትን አጉልቶ በማውጣት ዜጎች ረብሻ አስፈላጊውን ለውጥ ያመጣል ብለው ከማሰብ ይልቅ በእግዚአብሔር ቃል እንዲታመኑ አሳሰበ፡

“ጠላት፣ ሰዎች ወንጌልን ለማስፋፋት ረብሻን ሲጠቀሙ ምን እንደሚያስብ ታውቃላችሁ? ከገሃነም እሳት ኋላ ትከሻውን አስፍቶ ይቀመጥና በክፉ አስተያየትና በሚያስፈራ ሳቅ፡ “አሀ እነኚህ አመጸኞች ጨዋታዬን ለመጫወት ምን ያህል ብልጥ ናቸው! ይጫወቱ፣ ጥቅሙን እኔ አገኘለሁ፡፡ ደስ እሰኝበታለሁ፡፡” ግን በውጊያ ሜዳው ላይ ቃሉ፣ ሲንቀሳቀስና ለብቻው ሲፋለም ሲያይ፣ በፍርሃት ይንቀጠቀጣል፣ ሚገባበት ያጣል፡፡”

የሉተር ጣልቃ መግባት ውጤታማነት፣ ፈጣን ነበረ፡፡ አንድ ዳኛ ለዊተንበርግ ከተማ ርዕሰ-መስተዳደር “የዶክተር ማርቲን መመለስ ምን አይነት ደስታን ነው ያጥለቀለቀን! በመንፈሳዊ ምህረት ካፉ የሚወጡት ቃላት የተሳሳቱትን ሰዎች በየቀኑ ወደ እውነተኛው መንገድ እየመለሱ ነው፡፡” ሲል ደብዳቤ ጽፏል፡፡

በቀጣይ ሉተር የአዲሲቷን ቤተ-ክርስትያን ስርአት በማበጃጀትና በማስተካከል ተጠመደ፡፡ ከባለ-ስልጣናት ጋር ሰላም ለማስፈን ሲሰራ በካቶሊክ ቤተ ክርስትያንና በአመራሯ ላይ አመጽ ያስነሳው ሰው፣ በሪፎርሜሽን ውስጥ ራሱን በአዲስ መልኩ ወግ አጥባቂ መሆኑን አሳየ፡፡ ዝዊካው ፕሮፌቶችን ካጠፋ በኋላ እንኳን፣ ግጭቱ ከካቶሊክ ቤተ-ክርስትያን ጋር ብቻ ሳይሆን ማህበራዊ አለመረጋጋትንና ረብሻን በመቀስቀስ አዲሱን ስርአት ካሸበሩት አክራሪ ሪፎርመሮች ጋር ሆነ፡፡ ሉተር ዊተንበርግ ላይ አሸናፊነትን ከመቀዳጀቱ ባለፈ፣ ከዊተንበርግ ርቆ በመላው አውሮፓ እየተሰራጨ የነበረውን የሪፎርሜሽን አክራሪነት ማስቆም አልቻለም፡፡ ከ1521-1525 የዝዊካው ነቢይ የሆነው ኒኮላስ ስቶርችና ቶማስ ሙለርን የመሳሰሉ ሉተር ከከተማ ያወጣቸው ሰባኪዎች የደሃ ከተሞችንና የገበሬዎችን ድጋፍ አገኙ፡፡ ከ15ኛው ምዕተአመት ጀምሮ በትንሹም ቢሆን በገጠር አመጾች ነበሩ፡፡ ታዲያ ቤተ-ክርስትያንንና መዋቅሩን በመቃወም በሉተር የሚበተኑትን በተለይ ነጻነትን በሚሸቱ ቃላት የተቀቡትን ፓምፕሌቶችና ፍላየሮች እያነፈነፉ ያነበቡት ገበሬዎች፣ ሉተር ባጠቃላይ በላይኛው መደብ ላይ የሚደረግን ጥቃት ይደግፋል የሚል አቋም ይዘው ነበር፡፡ በ1524 በፍራንኮያ፣ በሰዌቢያና በተሪንጂያ አመጾች ተቀጣጠሉ፡፡ ይሄ አመጽም የተገለሉና እዳ ባለባቸው የንጉስ ቤተሰቦች መረዳት ሲጀምር፣ አገርሽቶ መዛመት ጀመረ፡፡ በተሪንጂያ ሙለርን፣ በደቡብ-ምዕራብ ሂፐለርና ሎዘርን የመሳሰሉት የሪፎርሜሽን አክራሪዎች በሚሰጡት አመራር ሃይልን የተጎናጸፈው አመጽ ወደ ጦርነት ተሸጋገረ፡፡

ሉተር የገበሬዎቹን ብሶት እንደሚረዳ ቢገልጽም በ1525 ብሶተኞች ለባለስልጣናት እንዲገዙ አሳሰበ፡፡ ተሪንጂያን ሲጎበኝ ባየው የእምነት ተቋማት፣ ገዳማት፣ የሊቀ-ካህናት ቤተ-መንግስቶችና ላይብረሪዎች በከፍተኛ ደረጃ የተዛመተ ቃጠሎ በጣም ተበሳጨ፡፡ ከተሪንጂያ ወደ ዊተንበርግ ሲመለስ በጻፈው Against the Murderous, Thieving Hordes of Peasants ጽሁፍ የወንጌል የብልጥግና ትምህርት ላይ ማብራሪያ ሰጠ፣ ብጥብጡን ደግሞ የሰይጣን ስራ ነው ሲል ፈረጀው፡፡ እናም አማጺ ንጉሳውያን አመጻቸውን እንዲያቆሙ ጥሪ አደረገ፡፡

“ስለዚህ በድብቅም ይሁን በግልጽ ምንም ነገር ከአመጽ በላይ መርዛማ፣ ጎጂ፣ ወይም ሰይጣናዊ የሆነ ነገር እንደሌለ እያወቀ ማጥቃት፣ ማቁሰልና መግደል የሚችል ሁሉም ሰው... ጥምቀት ሰውን በነፍስ እንጂ በሰጋና በሀብት ነጻ አታደርግም፡፡ እናም ሐዋርያትና ደቀ-መዛሙርት በሐዋርያት ስራ 4፡32-37 እንዳደረጉት በራሳቸው ፈቃድ ከሚያደርጉት ባለፈ ወንጌል ሀብትን የጋራ አታደርግም፡፡ ሐዋርያት ማሰብ ያቆሙ ገበሬዎቻችን በቁጣ እንደገለጹት የሌሎች ሀብት የጋራ እንዲሆን ሳይሆን የፈለጉት የራሳቸውን ብቻ ነበር፡፡ ይሁንና የኛ ገበሬዎች፣ የራሳቸውን ለራሳቸው አስቀርተው የሌላውን ንብረት ግን የጋራ ማድረግ ይፈልጋሉ፡፡ እንዴት አይነት ደስ የሚሉ ክርሰትያኖች ናቸው?! ሳስበው በገሃነም ውስጥ የቀሩ አጋንንቶች ያሉ አይመስለኝም፡፡ ሁሉም በገበሬዎቹ ውስጥ ገብተዋል፡፡ ስርአት አልበኝነታቸው ከልክ አልፏል፡፡”

ሉተር በአማጺ ሪፎርመሮቹ ላይ የነበረውን ተቃውሞ በ3 ነጥቦች ያብራራል፡፡

1. ለሴኪዩላሩ መንግስት እንደ ስርአቱ ከመገዛት ይልቅ አመጽን መምረጣቸው፡፡ የክርስቶስን “የቄሳርን ለቄሳር” ምክርና ጳውሎስ በሮሜ 13፡1-7 ሁሉም ባለስልጣናት በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው፣ ስለዚህ ባለስልጣንን የሚቃወም እግዚአብሔርን ይቃወማል ብሎ የጻፈውን መልዕክት ችል ማለታቸው፡፡
2. አመጻን፣ ዝርፊያንና ስርቆትን የመሳሰሉ አፍራሽ ስራዎች ገበሬዎቹን “ከእግዚአብሔር ህግና ግዛት ውጪ” ያደርጓቸዋል፡፡ ስለዚህ እንደ መንገድ ላይ ዘራፊችዎና ገዳዮች ብቻ ራሱ ሞት ይገባቸዋል፡፡
3. በመጨረሻ ሉተር አማጽያኑ፣ ራሳቸውን “ክርስትያን ወንድማማቾች” ብለው በመሰየም ኃጢአት ለተሞላበት ስራቸው ወንጌሉን ሽፋን በማድረግ፣ በማለት በሃይማኖት ላይ በመሳለቅ ይከሳቸዋል፡፡

ሉተር አመጹን እንደማይደግፍ ያዩ ብዙ አማጽያን አመጹን ትተው ወደ ቤታቸው ሲመለሱ፤ ሌሎቹ እንደተካዱ ተሰማቸው፡፡ የሙለርን የሞት ቅጣት ያስከተለው የሜይ 15፣ 1525ቱ የፍራንከንሃውስን ጦርነት፣ የአብዮታዊው የሪፎርሜሽን ደረጃ የመዝጊያ ስነስርአት ነበር የሆነው፡፡

በቀጣይ መሰረታዊ ለውጥን መሻት(ራዲካሊዝም)፣ ወደ አናባፕቲዝም ንቅናቄና ወደ ሌሎችም ሀይማኖታዊ እንቅስቃሴዎች ተሰደደ፡፡ የሉተር ሪፎርሜሽን ደግሞ በሴኪዩላሩ ሀይል ከንፍ ስር አንጻባረቀ፡፡ የሉተር ሪፎርሜሽንም በዙሪያው እየተካሄደ ስላለው ነገር እንዲያጠነጥን በማድረግና በዓለምና በሃይማኖት መሃል ያለውን ግድግዳ በመደርመስ፣ ለሬኔሳንስ ከፍተኛ ግብአት ሆኗል፡፡

ማርቲን ሉተር በ1526 እንዲህ ሲል ጻፈ፡ “እኔ ማርቲን ሉተር፣ በአመጹ ጊዜ ሁሉንም ገበሬዎች ጨፍጭፌያለሁ፡፡ እስከ ሞት ድረስ እንዲቀጡ ያዘዝኩት እኔው ነኝና፡፡”

እነሉተር ሪፎርሜሽንን ሲያጧጥፉ ካቶሊክ ቤተ-ክርስትያን ደግሞ በበኩሏ ካውንተር ሪፎርሜሽን የሚሉትን የራሷ ማሻሻያ ማድረግ ጀመረች፡፡

ሉተር በ1523 ሚስት በማግባት ቄስ የማያገባበትን የካቶሊክ ስርአት አፍርሶ ለተቀረው ፕሮቴስታንት ምሳሌ ሆነ፡፡ ከዚያ ወዲህም ከፕሮቴስታንት ባልደረቦቹ ጋር አዲሲቷን የፕሮቴስታንት ቤተ-ክርስትያን በመመስረትና በማደራጀት ተጠመዱ፡፡

አንድ ያነበብኩት ጽሁፍ እንዲህ ይላል፡

HUMANISM AND RENAISSANCE + REFORMATION = SCIENTIFIC REVOLUTION

ህይወት በሬኔሳንስና በሪፎርሜሽን ዘመን

ሬኔሳንስ እንዲህ እንደኛ ዘመን ተጽዕኖው ጎልቶ ህዝቡን ሳይቀያይር በፊት የነበረው የዚያ ዘመን ህይወት በመካከለኛው ዘመን ከነበረው ዘመን ጋር ብዙም ልዩነት አልነበረውም፡፡
ጾታና መደብ የቀን ተቀን ህይወትን ይቀርጹ ነበር፡፡ የከፍተኛው መደብ ሴቶች በቤታቸውና በፍርድ ቤት የታጠሩ ነበሩ፡፡ የከፍተኛው መደብ ሴቶች ገበያ፣ ቤተ-ክርስትያንና የመሳሰሉት ቦታዎች የሚሄዱት ተያይዘው በቡድን ነው፡፡ የመካከለኛው መደብ ሴቶችና ደሃ ሴቶች ደግሞ ብዙ ጊዜያቸውን በስራ ነው የሚያሳልፉት፡፡ የመካከለኛው መደብ ሴቶች የእጅ ስራ ባለሙያዎችና ባለሱቆች ሲሆኑ ደሃ ሴቶች ደግሞ የገበሬ ሚስት ከሆኑ እርሻ ላይ፣ ባርያዎች ከሆኑ ደግሞ በቤት ውስጥ ይሰራሉ፡፡ የምርጡ መደብ ሴቶች የቤት ውስጥ ስራዎችን ሲቆጣጠሩ የልጆቻቸውን የትምህርት ሁኔታ ይከታተላሉ፡፡
ገዢዎቹ ወንዶች ደግሞ ጊዜያቸውን በፍርድ ቤት፣ በጦርነት፣ ወይም የሀገር ጉዳይ በመቆጣጠር ጊዜያቸውን ያሳልፋሉ፡፡ በከተማ ደግሞ አንዳንዶቹ የንግድ ስራ ውስጥ ራሱ ይገባሉ፡፡ ያው የዝቅተኛው መደብ ወንዶች ደግሞ ገበሬዎች፣ ባለ ሱቆች ወይም የእጅ ስራ ባለሙያዎች ነው የሚሆኑት፡፡

የዚያ ዘመን ሴቶች

ሴቶች በቤተሰባቸው ውስጥ በእድሜያቸውና ባገቡት ሰው ላይ በመመርኮዝ ብዙ ስራዎች ነበሯቸው፡፡ ሴት መጀመሪያ ልጅ ነች፡፡ ከዚያ ሚስት፣ እናት ወይም ባሏ የሞተባት ሴት(widow) ትሆናለች፡፡ ከሴቶች ጋር ሲነጻጸር የወንዶች ድርሻ የሚወሰነው በማህበራዊ ቦታቸው ወይም በስራቸው ነው፡፡ ነጋዴ፣ ጠባቂ፣ ቄስ፣ ገበሬ፣ ሸማኔ ወዘተ፡፡ የከፍተኛው መደብ ሴቶች ህይወት በጣም የተገደበና ጥብቅ የነበረ ሲሆን በአንጻሩ የዝቅተኞቹ ሴቶች ደግሞ ባጠቃላይ ነጻነት አላቸው፡፡ ቤታቸውን ለመደገፍ ቤት ውስጥ ጉድ ጉድ ሲሉ ውጪ ደግሞ ከወንዶች ጋር እርሻ ላይ ወይም ሱቅ ውስጥም ይሰራሉ፡፡ ስለዚህ ዝቅተኞቹ ሴቶች ነጻ ነበሩ ማለት ይቻላል፡፡

ሴት ልጅ "ድንግል" ተብላ ነበር የምትጠራው፡፡ ማለትም ግንኙነት አድርጋ የማታውቅ ማለት ነው፡፡ ሴት ልጆች እስኪያገቡ ድረስ ካላገቡም ሙሉ ህይወታቸውን ድንግልናቸውን እንዲጠብቁ ይጠበቅባቸው ነበር፡፡ በሬኔሳንስ ዘመን የክብር ጽንሰ-ሀሳብ በድንግልና ላይ የተመሰረተ ነበር፡፡ የሴት ልጅ ድንግላ መገርሰስ ለልጅቷ ብቻ ሳይሆን ለመላው ቤተሰቧ እንደ ውርደት ነበር የሚቆጠረው፡፡ አንዷት ልጃገረድ ድንግልናዋን ካጣች ትቀጣለች፡፡ ቅጣቱ ታዲያ እንደ ዘመድ አዝማዶቿ ማህበራዊ ደረጃ ይለያያል፡፡ የከፍተኛው መደብ ልጅ ከሆነች ቤተሰቧ በማህበረሰቡ ውስጥ ከፍተኛ ክብር ስላለው፣ ከሌሎቹ ሴቶች የበለጠ በጣም ትቀጣለች፡፡ ልጃገረዶች ድንግልናቸውን በትዳር ሳይጣመሩ ሲያጡ በቤተሰባቸው ይገለላሉ፡፡

ልጃገረዶች ድንግልናቸውን መጠበቅ ብቻ ሳይሆን ሲያገቡ የሚጠቀሙበት ሙያን ይይዛሉ፡፡ ከሁሉም በላይ ማዘወር፣ ስፌትንና ሌሎችንም ሙያዎች ታላላቆቻቸው ከሆኑ ሴቶች ይማራሉ፡፡ ይሄ ብቻ ሳይሆን ገንዘብ አያያዝ፣ ባሪያ ማሳደርን፣ በቤት ውስጥ የታመመን ሰው ማስታመምና መንከባከብን ይማራሉ፡፡ በመጨረሻም ልጃገረዶችን በጋብቻ ውስጥ ታማኝ መሆንን፣ ታዛዥነትን እና ጸጥተኛነትን በማስተማር በትዳር ውስጥ ለሚጠብቃቸው ሀላፊነት እንዲዘጋጁ ይደረጋል፡፡

አንዷት ልጃገረድ ባሏን በመምረጡ ውስጥ ድርሻ አልነበራትም ማለት ይቻላል፡፡ በሀብታም ቤተሰቦች ውስጥ ጋብቻውን የሚያመቻቹት ወንድ ዘመዶቿ ሲሆኑ ይሄም እናትየውን ማማከርንም ያካትታል፡፡

ሰባኪዎችና ሌሎችም መሪዎች የባልና የሚስትን ጥብቅ ግንኙነት ያበረታቱ ነበር፡፡ የማመንዘር፣ ከአንድ በላይ ሚስት ማግባትንና ክልከላንና ድብደባን ከሰሙ መሪዎቹ ይቆጣሉ፡፡ የማመንዘር ወንጀልነት በሚስቲቱ ላይ የጠነከረ ሲሆን እንደ ከፍተኛ ወንጀል ነው የሚታየው፡፡ በብዙ ቦታዎች ባል ሚስቱ ስታመነዝር ተይዞ፣ ቢገላት ይቅርታ ይደረግለታል፡፡ እንዲያውም በአንዳንድ ቦታዎች እንዲህ አይነት ግድያ ከወንጀልም አይቆጠርም፡፡ የንጉሳውያኑ ሚስቶች በሆኑት ሴቶች ላይ ደግሞ ማመንዘር፣ በሀገር ላይ እንደተደረገ ክህደት የሚታይ ሲሆን ባጠቃላይ በሞት የሚያስቀጣ ወንጀል ነው፡፡
ፕሮቴስታንት ሪፎርሜሽን ከመምጣቱ በፊት ፍቺ ችግር ላለበት ትዳር እንደ መፍትሄ ሆኖ የሚቀርብበት ሁናቴ አልነበረም፡፡

የሚስት ቀዳሚ ስራ ልጅ ማርገዝ፣ መውለድና ማሳደግ ነበረ፡፡ ብዙ ልጆች መውለድ በጣም ሲደገፍ፣ እርግዝናንም ሆነ ወሊድን መከላከል ደግሞ በጥብቅ ነበር የሚወገዘው፡፡

ፕሮቴስታንት ሪፎርሜሽን ከመምጣቱ በፊት ባላቸው የሞተባቸው ሴቶች በብዛት ገዳም ነበር የሚገቡት፡፡ ፕሮቴስታንቲዝም ሲመጣ አንዳንድ ሴቶች በነቂስ ሀሳባቸውን ማንጸባረቅ ጀመሩ፣ ፕሮቴስታንትነትን በተቀበሉ አካባቢዎች የሴት ገዳማት ተዘጉ፡፡ ቀስ በቀስ ከ16ኛው ክፍለዘመን ጀምሮ እስከሚፈረጥሙበት እስከ 18ኛው ክፍለዘመን ባለው ጊዜ ውስጥ የሴቶች መብት ተከራካሪዎች፣ አፈሩን ጥሰው ብቅ ብቅ ማለት ጀመሩ፡፡

ልጆች ደግሞ የሚማሩት ወንዶች ብቻ የነበሩ ሲሆን ሬኔሳንስ በማህበረሰቡ ላይ ተጽእኖ ሊያደርግ የቻለውም ተማሪዎቹ የሚማሩት የሬኔሳንስን ውጤቶች ስለነበረ ነው፡፡

16ኛው ክ.ዘ. ምዕራባውያን ማደግ የጀመሩበት ዘመን በመሆን ይታወቃል፡፡ ፖርቹጋልና ስፔን የአለም ባህሮችን በማሰስ አለማቀፍ የእውቅያኖስ የገበያ ማዕከላትን ሲያቋቁሙ አዲሲቷ አለም(አሜሪካ) የስፔንና የፖርቹጋል ቅኝ ግዛት ስር ገባች፡፡ ፖርቹጋሎች በአፍሪካና በእስያ የህንድ እውቅያኖስ ላይ ንግድ ገዢዎች ሲሆኑ፣ ስፔን በፓሲፊክ እውቅያኖስ ላይ አሜሪካንና እስያን የሚያገናኝ ንግድ ጀመረች፡፡ ይሄ ዘመን "ሜርካንቲሊዝም" የተባለው የቅኝ ግዛት ጠበቃ የሆነ የኢኮኖሚ አስተምህሮ የተጠነሰሰበት ጊዜ ነበር፡፡ ይሄም የኢኮኖሚ መዋቅሩ እንደ ዜሮ ድምር ጨዋታ የሚታይበት አስተሳሰብ ነው፡፡ "አንድ ቡድን ምንም አይነት ትርፍ ለማግኘት ሌላው ቡድን መክሰር አለበት፡፡" ይሄ አስተሳሰብም ብዙዎቹን በአውሮፓ ውስጥ ለተነሱ ጦርነቶች ምክንያት እንደሆነ ሲታመን፣ የአውሮፓ ሀገራት እስከ 19ኛውና 20ኛው ክፍለዘመን መጀመሪያ በአለም ላይ የከፈቷቸውን ወረራዎች ደግሞ አቀጣጥሏል ብለው ያምናሉ፡፡

በአውሮፓ ፕሮቴስታንት ሪፎርሜሽን የካቶሊክ ቤተ-ክርስትያንን ስልጣን ያናጋ እንቅስቃሴ ሆኖ በታሪክ ተመዘገበ፡፡ የአውሮፓ ፖለቲካ በሀይማኖታዊ ግጭቶች ተጽዕኖ ስር ወደቀ፡፡ በክፍለዘመኑ መጨረሻ፣ ማለትም በ17ኛ ክ.ዘ. መጀመሪያ የሪፎርሜሽን ጦስ የሆነውና በካቶሊክና በፕሮቴስታንት ሀገራት መሃል የተደረገው፣ በታሪክ ረጅምና ብዙ ሰው ከሞታታቸው ጦርነቶች አንዱ የሆነው የ30ዎቹ አመታት ጦርነት ተካሄደ፡፡
በጦርነቱ ማግስት ጣልያናዊው አልቤሪኮ ጄንቲሊ የመንግስትን አስተዳደር ከሮማን ካቶሊክ ቤተ-ክርስትያንና ከሃይማኖታዊ ህግጋቶች የሚለየውን የመጀመሪያውን አለማቀፍ የህዝብ ህግ መጽሐፍ ጻፈ፡፡
ኮፐርኒከስ መሬት እንጂ በጸሃይ ዙሪያ የምትሽከረከረው ጸሃይ አይደለችም የሚለውን ሃሳቡን ያረቀቀበትና ያስተዋወቀበት ዘመንም ነው፡፡

17ኛው ክ.ዘ. የሬኔሳንስ መገባደጃ ሲሆን የዘመናዊነት ደግሞ መጀመሪያ በመሆን ይታወቃል፡፡ በ17ኛው ክ.ዘ. ሳይንሳዊ አብዮት የተነሳበት ዘመን ነው፡፡ ሳይንሳዊ አብዮት የታሪክ ተመራማሪዎች የዘመናዊውን ሳይንስ መጀመር ለመግለጽ የሚጠቀሙበት ጽንሰ ሀሳብ ሲሆን በሂሳብ፣ በፊዚክስ፣ በአስትሮኖሚ፣ በባዮሎጂና በኬሚስትሪ ማህበረሰቡ ለተፈጥሮ ያለው አመለካከት ከመሰረቱ የተቀየረበት ጊዜ ነው፡፡ ሳይንሳዊ አብዮት በሬኔሳንስ መጨረሻ ጀምሮ እስከ 18ኛው ክ.ዘ. መጨረሻ ሲቀጥል የማህበራዊ አስተሳሰብ ንቅናቄ የሆነውን ኢንላይትመንት ላይ ተጽዕኖ አድርጓል፡፡ የሳይንሳዊ አብዮት ወይም ሳይንሳዊ ሬኔሳንስ(ሳይንሳዊ ተሀድሶ) ጅማሬ የጥንታውያን ግሪኮችን እውቀትና ጥበብን በማንሰራራት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ይሄም የነጋሊሊዮ ጋሊሌንና የነአይዛክ ኒውተንን ፈጠራዎችና ግኝቶች ያጠቃልላል፡፡
በ17ኛው ክ.ዘ. አውሮፓ በጥልቀት አሜሪካን መግዛት ብቻ ሳይሆን መጠቀም ጀመረች፡፡ በዚህ ጊዜ ነበር የብረት ክምር በማውጣት አንጡራ ሀብት ወደ አውሮፓ መጉረፍ የጀመረው፡፡

በታላቋ ብሪቴን የኢንደስትሪ አብዮት መነሻ ምክንያት የሆነውና የሰውን ህይወትና አካባቢውን የሚለውጠው የእንፋሎት ሞተር የተፈጠረው በ18ኛው ክ.ዘ. በጄምስ ዋት ነበረ፡፡
በ18ኛው ክ.ዘ. በፈረንሳይ ኢንላይትመንት ጣሪያ ነካ፡፡ ኢንላይትመንት (Enlightment) ወይም የምክንያት ዘመን ወይም የብርሃን ክፍለዘመን ተብሎ የሚታወቀው ዘመን በ18ኛው ክ.ዘ. በአውሮፓ ውስጥ ያለውን አስተሳሰብ የቀየረ የፍልስፍና ንቅናቄ ነው፡፡ ኢንላይትመንት በምክንያት ላይ የተመሰረቱ የተለያዩ ሀሳቦችን የስልጣንና የህግ ምንጮች ሲያደርግ፣ ነጻነት፣ እድገት፣ መቻቻል፣ ወዳጅነት፣ ህገ-መንግስታዊ አስተዳደርና የቤተ-ክርስትያንና የመንግስት መለያየትን በውስጡ የያዘ ትልቅ የዘመናችን መጀመሪያ ዘመን ነው፡፡ ኢንላይትመንት ሳይንሳዊ ዘዴዎችንና ነገሮችን አበጥሮ በመተንተን ላይ የተመሰረተ ሲሆን በከፍተኛ ደረጃ ሀይማኖታዊነትን ወይም ወግ አጥባቂነትን ወይም ስርአተኝነትን፣ በሀይል ጥያቄ ውስጥ ይከታል፡፡ ይሄም ከፍተኛ የማወቅ ፍላጎትና ለምን ለምን የማለት ውጤት ነው፡፡ የዚያ ዘመን ፈረንሳውያን ፈላስፎች ሀሳቦቻቸውን በሳይንሳዊ ት/ቤቶች፣ በሜሰናዊ(ሰይጣን አምላኪዎች የሚስጥር ማህበራት) የገጠር ቤቶች፣ የጽሁፍ ማቅረቢያ ሳሎኖች፣ ቡና ቤቶች ውስጥና በሚታተሙ መጽሐፍትና ፓምፕሌቶች ነበር ሀሳቦቻቸውን ሲያንሸራሽሩ የነበሩት፡፡
ኢንላይትመንት የዘውዳዊ አገዛዝንና የቤተ-ክርስትያንን በመንግስት ስራ ውስጥ ጣልቃ መግባት ሲያጣጥል፣ በዚሁም በ18ኛውና 19ኛው ክፍለዘመናት ለተነሱ ፖለቲካዊ አብዮቶች መንገዱን ከፍቷል፡፡ በ19ኛው ክፍለዘመን የተነሱት የሊበራሊዝምና ኒዎ-ክላሲሲዝም እንቅስቃሴዎች የኢንላይትመንት ውጤቶች ናቸው፡፡

ከ1765-1783 ዓ.ም. የአሜሪካ አብዮት ተቀሰቀሰ፡፡ የአሜሪካ አብዮት አሜሪካውያን ለታላቋ ብሪቴን ንጉስና ፓርላማ መገዛት አሻፈረን ያሉበትና ከብሪቴን ቅኝ ግዛት ስር ለመውጣት ተዋግተው ነጻነታቸውን የተቀዳጁበት ትግል ነው፡፡

ከ1789-1799 በፈረንሳይ የተካሄደው አብዮት፣ ህጉ ሁሉን ሀይል ጠቅልሎ ለንጉሱ ከሚሰጥበት ዘውዳዊ አገዛዝ፣ ለጥቂት ጊዜም ቢሆን በቲዮሪ(በሀሳብ) ደረጃ ነጻና እኩል ዜጎች ወደሚል ሪፐብሊካዊ አገዛዝ አሸጋግሯታል፡፡ ይሄ የፈረንሳይ አብዮትም በአለም ትልቅ ስፍራ ከሚሰጣቸው ታሪካዊ ክስተቶች አንዱ ነው፡፡ በአስር አመቱ አብዮት ፈረንሳይ የቀድሞውን አገዛዝ በተከታታይ የተለያዩ መንግስታት ተካችው፡፡፡ ይሄ የአስር አመት አብዮት ፈረንሳይን ጭንቅ ውስጥ የከተተና ብዙ ህይወት የጠፋበት እንዲሁም ብዙ ዜጎች ለስቃይ የተዳረጉበትና ከ4 አመት በላይ የዘለቀ መንግስት ያልነበረበት ፍጹም መረጋጋት የታጣበት የነበረ ቢሆንም መንግስት ሆነው ለጥቂትም ጊዜ ቢሆን ወደ ስልጣን የወጡት አስተዳዳሪዎች ያወጧቸው እቅዶች፣የፈረንሳይን የፖለቲካ ስርአት ከመሰረቱ ለውጠዋል፡፡ እነዚህ ዕቅዶችም፡ የሙብት ረቂቅ ህጎችንና ህገ-መንግስትን፣ በዜጎች መሃል ህጋዊ እኩልነትን መፍጠርን፣ የውክልና ዲሞክራሲ ሙከራን፣ መንግስትንና ቤተ-ክርስትያንን ነጣጥሎ ግን አብሮ ማስኬድን፣ የመንግስታዊ አስተደደር ህንጻን አዲስ ግንባታን ያጠቃልላል፡፡ ከዘውዳዊው ውድቀት በኋላም ብዙ ፖለቲካዊ ውዝግቦችን ያስከተለው የፈረንሳይ ሪፐብሊክ፣ ፈረንሳይን በመጨረሻ በናፖሊዮን ቦናፓርቴ አንባገነናዊ ቁጥጥር ስር አስገባት፡፡

19ኛው ክ.ዘ. በስፔን፣ በናፖሊዮንና ቅድስት ሮማን ኢምፓየሮች ወድቀት ይጀምራል፡፡ ይሄም በ1815 የብሪቲሽ የታፈረ የበላይነት በኋላ ለብሪቲሽ ኢምፓየር፣ ራሽያን ኢምፓየር፣ ዩናይትድ ስቴትስ፣ ጀርመን ኢምፓየር፣ የፈረንሳይ የቅኝ ግዛት ኢምፓየር፣ መንገዱን ከፈተ፡፡ በናፖሊዮን ጦርነቶች የፈረንሳይ ኢምፓየርና አጋሮቿ ከተሸነፉ በኋላ የብሪቲሽና የሩሲያ ኢምፓየሮች የአለም ልዕለ ሀያላን በመሆን በከፍተኛ ደረጃ ተስፋፉ፡፡ የሩሲያ ኢምፓየር በመካከለኛውና በሩቅ ምስራቅ እስያ ተስፋፋ፡፡ የብሪቲሽ ኢምፓየር ደግሞ በምዕተአመቱ የመጀመሪያው አጋማሽ በካናዳ፣ በአውስትራሊያ፣ በደቡብ አፍሪካና በህንድ በጣም ትላልቅ መሬቶችንና በምዕተአመቱ የመጨረሻ 2 አስርት አመታት ደግሞ ብዙ የአፍሪካ መሬቶችን በኢምፓየሯ ስር በማስገባት በፍጥነት አደገ፡፡ በምዕተ አመቱ መጨረሻ የብሪቲሽ ኢምፓየር የአለምን አንድ አምስተኛ መሬትና አንድ አራተኛ(ሩብ) ህዝብ ተቆጣጠረ፡፡ ከናፖሊዮን ዘመን በኋላና የናፖሊዮን ኢምፓየር ከወደቀ በኋላ ሁነኛ ተቀናቃኝ ያልነበራት ታላቋ ብሪቴን ፓክስ ብሪታኒካ የተሰኘ አለማቀፍ ህግ በስራ ላይ አዋለች፡፡ ይሄም በኢንደስትራላይዜሽን ወደ ግሎባላይዜሽን የሚደረገው ኢኮኖሚያዊ ውህደት ግስጋሴ መጀመሪያ ነው፡፡

የመጀመሪያው በኤሌክትሪክ የሚሰራ ኤሌክትሮኒክስ ለአለም የተዋወቀው በዚህ ምዕተአመት ነበር፡፡ ቴሌግራፍ በ1837፣ የመጀመሪያው የቴሌፎን ጥሪ በ1876፣ ለመጀመሪያ ጊዜ የአምፖል ብርሃን አገልግሎት ላይ የዋለው ደግሞ በ1878 ነበር፡፡
19ኛው ክ.ዘ. በሂሳብ፣ በፊዚክስ፣ በኬሚስትሪ፣ በባዮሎጂ፣ ኤሌክትሪሲቲና በብረት ስራ ትላልቅ እድገቶች የታዩበት ሲሆን ሳይንሳዊ ግኝቶችና ፈጠራዎች የተጧጧፉበት ነበር፡፡ በዚህም በ20ኛው ክፍለ ዘመን ለሚከተለው የቴኬኖሎጂ ምጥቀት መሰረቱን እየተከለ ነበር፡፡ በታላቋ ብሪቴን የጀመረው የኢንደስትሪ አብዮት ወደ መላው አውሮፓ፣ ወደ ሰሜን አሜሪካና ወደ ጃፓን ተዛመተ፡፡

የኢንደስትሪ አብዮት

የኢንደስትሪ አብዮት፣ በእንፋሎት የሚንቀሳቀስ ማሽን(steam engine) የመሳሰሉ አዳዲስ ፈጠራዎችን ተከትሎ የመጣ ወደ ማንዩፋክቸሪንግ የተደረገ የዝውውር ሂደት ነው፡፡ ይሄ ዝውውርም በፊት በሰው ጉልበት የሚሰሩ ምርቶችን በማሽኖች መተካት መቻሉ ነው፡፡
የኢንደስትሪ አብዮት በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ የቀን ተቀን ህይወት ላይ ተጽዕኖ በማሳረፍ ትልቅ የታሪክ አቅጣጫ ቀያሪ ነጥብ ሆነ፡፡ ተራ ሰራተኞች ቢገለቱም በዋነኛነት የሰዎች ገቢና የህዝብ ብዛት ታይቶ የማይታወቅ እድገት ማሳየት ጀመረ፡፡

በታላቋ ብሪቴን በ18ኛው ክ.ዘ. የጀመረው የኢንደስትሪ አብዮት እስካሁን ድረስ በሀገራችንና በሌሎችም የአፍሪካና የአለም ክፍሎች እንደቀጠለ ይገኛል፡፡ ሰዎች ስራ ፍለጋ ከገጠር ወደ ከተማ በስፋት መፍለስ በመጀመራቸው ምክንያት ትላልቅ ከተሞች መስፋፋትና ማደግ ጀመሩ፡፡

በ18ኛው ክ.ዘ. ኮንሲዩመሪዝም(ተጠቃሚነት) ማደግ ጀመረ፡፡ ሰዎች አዳዲስ ልብሶችንና አዳዲስ የቤት ውስጥ እቃዎችን መሻትና ማከማቸት ጀመሩ፡፡ በሳይንስና በተነሳሽነት ጠንክሮ በመስራት በማመን ላይ የተመሰረተው ኢንላይትመንት የተባለው የአስተሳሰብ እንቅስቃሴ የማህበረሰቡን አስተሳሰብ መቀየር ያዘ፡፡ በኢኮኖሚ፣ በዲፕሎማሲና በጦር ሀይል ጠንካራ ሆነው ለመታየት የሚፎካከሩት መንግስታት ለፈጠራዎችና ለቴክኖሎጂ ውጤቶች መበራከትና ማደግ የተቻላቸውን ያህል ሁኔታዎችን ያመቻቹ ነበር፡፡ መንገዶች፣ ካናሎችና የባቡር ሃዲዶች እንዲሰሩ አበረታቱ፡፡ አዳዲሶቹን ፋብሪካዎች የሚጎዱ የሰራተኞች ተቋሞዎችን ተከላከሉ፣ የእጅ ስራዎች እንዳይስፋፉ አቀቧቸው፡፡

ለመጀመሪያ ጊዜ ከግማሽ በላዩ የህዝብ ብዛት በከተሞች መኖር ጀመረ፡፡ በፊት ስራ በብዛት እርሻውም ሌላውም በቤት አቅራቢያ የነበረ በመሆኑና ፋብሪካዎች ከቤት ስለሚርቁ ለመጀመሪያ ጊዜ ባሎች ከቤታቸው ርቀው ሄደው መስራት ነበረባቸው፡፡ ኢንደስትራላይዜሽን የኢንደስትሪ ባለቤቶችን በከፍተኛ ደረጃ ከማበልጸጉ የተነሳ በባለቤቶቹና በሰራተኞች መሃል ከፍተኛና መራር የመደብ ልዩነቶችን ይዞ ብቅ አለ፡፡
ኢንደስትራላይዜሽን ስራን እንዳቃለለ ወዲያው የሰዎችን ህይወት የመዝናኛ አላደረገም፡፡ ሰራተኞች ለረጅም ጊዜ በስራ ቦታ በጣም ከመድከማቸው የተነሳ ቤታቸው ሲገቡ ይነጫነጩ ነበር፡፡ በመጀመሪያም በነጻነት የመዝናናት ህይወት ኢንደስትራላይዜሽንን ተከትሎ በጣም ቀነሰ፡፡ በከተሞች መዝናኛ በምትታወቀዋ በጃፓን እንኳን ባህላዊ ፌስቫሎች፣ ከንቱ ጊዜ ማጥፋቶች ናቸው ብለው ባሰቧቸው ሰራተኞች ጥቃት ደርሶባቸዋል፡፡ ሰራተኞች፣ እንደመጠጣት ባሉ የትርፍ ጊዜ መዝናኛዎች ላይም ባይሳካላቸውም ጥቃት አድርሰዋል፡፡ እንደዚያም ሆኖ አዳዲስ የመዝናኛ ዘዴዎች ብቅ ብቅ ማለት ጀመሩ፡፡ ፕሮፌሽናል ስፖርትቶች፣ የህዝብ ቲያትሮች እንዲሁም ዘግይቶ፣ ፊልሞች፡፡

በአለም የባሪያ ንግድና ባሪያን መጠቀም በጣም ቀነሰ፡፡

አለምን ከመሰረቷ የቀየሩ ተከታታይና ብዙ ክስተቶችን ያስተናገደውና እንኳን በእውን በህልም የማይታሰቡ የተለያዩና የተራቀቁ፣ የሰውን አኗኗር እንደ አዲስ የፈጠሩ ፈጠራዎች ዘመን የሆነው 20ኛው ምዕተአመት እነሆ፡፡ አንደኛውና ሁለተኛው የአለም ጦርነቶች፣ የኒውክሌር ሃይል፣ የህዋ ምርምር፣ ናሽናሊዝም(ብሄራዊ ስሜት)፣ የቅኝ ግዛቶች ማክተም፣ ቀዝቃዛው ጦርነትና የድህረ ቀዝቃዛው ጦርነት ግጭቶች፣ መንግስታትን የሚያስተሳስሩ ድርጅቶችና በትራንስፖርትና በግንኙነት ትስስሮች የመጣ የባህል ልዩነቶች መጥበብ፣ የድህነት ቅነሳ፣ የህዝብ ብዛት መጨመር፣ የተፈጥሮና አካባቢያዊ መራቆትና የዲጂታል አብዮት ውልደት፡፡ ክፍለዘመኑ በግንኙነትና በጤና ቴክኖሎጂ በ1980ዎቹ መላው አለምን በኮምፒዩተር ግንኙነቶች ማስተሳሰርና ነፍሳትን በዘረመል ምርመራ ማሻሻል አስቻለ፡፡
የተማረ ሰው ብዛት በአለም 80% ደረሰ፡፡ ሰዎች በከፍተኛ ደረጃ ሀብት ማካበት ቻሉ፡፡
በአውሮፓ ብሄራዊነት ከማደጉና የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት የሚል አስተሳሰብ በቋንቋና በዘር ላይ ለተመሰረቱ መንግስታት መመስረት ምክንያት ሆነ፡፡
በፖለቲካ፣ በአስተሳሰብ፣ በኢኮኖሚክስ፣ በማህበረሰብ፣ በባህል፣ በሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና በመድሃኒት የብዙ ሰዎችን አኗኗር እንደ አዲስ ገነባ፡፡ 20ኛው ክ.ዘ. ከሮማን ኢምፓየር ውድቀት በኋላ ከነበሩ ሌሎች ክፍለዘመናት አንድ ላይ በጠቅላላ ሲጨፈለቁ ካሳዩት የበለጠ የቴክኖሎጂና የሳይንስ እድገቶችን አሳይቷል፡፡ እንደ “አይዲዮሎጂ”፣ “ጄኖሳይድ”፣ “የኒዩክሌር ጦርነት” የተባሉ ቃላትና ሀረጎች በስፋት ጥቅም ላይ ዋሉ፡፡ የሪሌቲቪቲ ቲዮሪና ኩዋንተም ፊዚክስን የመሳሰሉ ሳይንሳዊ ግኝቶች የፊዚካል ሳይንስን መሰረታዊ ሞዴሎች በመቀየር ሳይንቲስቶች በፊት ከሚታሰበው የበለጠ ህዋ፣ በጣም ውስብስብ እንደሆነ እንዲረዱ አደረገ፡፡

20ኛው ክ.ዘ. በፈረሶችና በትናንሽ አውቶሞቢሎች የጀመረ፣ ነገር ግን በተወንጫፊ ባቡሮች፣ በትላልቅና በፈጣን መርከቦች፣ በአየር ላይ አለማቀፍ ጉዞዎች፣ ወደ ህዋ በሚላኩ መንኩራኩሮች ያለቀ በታሪክ አጭሩ ምዕተአመት ተብሎ የሚታወቅ ዘመን ነው፡፡ ለሺ ዘመናት የመጓጓዣ ስልት የነበረው የፈረስ ላይ ጉዞ በጥቂት አስርት አመታት በአውቶሞቢሎችና በባሶች ተተካ፡፡ ሰዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ህዋን አሰሱ፣ የሰው ልጅ ለመጀመሪያ ጊዜ ጨረቃን ረገጠ፡፡

በሌላ በኩል ፈጣን የቴክኖሎጂ መሻሻሎች ጦርነቶች በሰው ህይወትና በንብረት ላይ ታይቶ የማይታወቅ ውድመትን አድርሰዋል፡፡ ሁለተኛው የአለም ጦርነት ብቻውን 60 ሚሊየን የሰው ልጆችን ቀጥፏል፡፡ የኒዩክሌር መሳሪያዎች ደግሞ ለሰው ልጅ በአጭር ጊዜ ውስጥ ዘሩን ከምድር ገጽ ላይ የማጥፋት ሀይልን ሰጡት፡፡
ሁለተኛው የአለም ጦርነት ማብቃቱን ተከትሎ ሊግ ኦፍ ኔሽንስን የተካው ዩናይትድ ኔሽንስ ተመሰረተ፡፡

በምዕተአቱ በመንግስታት የተገደሉ ሰዎች ብዛት በመቶ ሚሊየኖች ይቆጠራል፡፡
በብዙ ሀገራት በተለይ በአፍሪካ የእርስ በርስ ጦርነቶች ተበራከቱ፡፡
ከሁለተኛው የአለም ጦርነት በኋላ ብዙ በቅኝ የተያዙ የአፍሪካና የእስያ ሀገራት ነጻነታቸውን ተቀዳጁ፡፡ እንደዚያም ቢሆን እንደ ዩኬ፣ ዩኤስኤ ሩስያ፣ ቻይናና ጃፓንን የመሳሰሉ ሀገራት ሀያላን በመሆናቸው በአለም ጉዳዮች ውስጥ እጃቸውን ማስገባትና አለም ላይ ተጽዕኖ ማሳደራቸውን አላቆሙም፡፡

በስነ ጽሑፍ የተለያዩ የተራቀቁ ልቦለዶች፣ ከወንጀል ምርመራ እስከ ሳይንሳዊና ታሪካዊ ልቦለዶች ከፍተኛ ተቀባይነት አገኙ፡፡ በ1961 ግሮቭ ፕሬስ የተባለ ማተሚያ ድርጅት ትሮፒክ ኦፍ ካንሰር የተሰኘና ሄንሪ ሚለር በተባለ ደራሲ የተጻፈ በህትመት ውስጥ በፖርኖግራፊ ሳንሱር(censorship) ላይ አዲስ እይታን የሚፈጥር መጽሐፍ አትሞ አሰራጨ፡፡
ብዙሃን መገናኛዎች፣ ቴሌኮምዩኒኬሽንና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ በተለይ ኮምፒዩተሮች፣ መጽሐፍት፣ መማር ማስተማርና ኢንተርኔት የአለምን እውቀት ለአለም ህዝብ የበለጠ ተደራሽ አደረጉት፡፡ የህክምና ቴክኖሎጂ በከፍተኛ ደረጃ መሻሻል፣ የብዙ ሰዎችን ጤና አሻሻሉ፡፡
በሆሊውድ ተንቀሳቃሽ ምስሎች ኢንደስትሪ፣ ትያትሮች፣ ሮክ ኤንድ ሮል፣ የፖፕና ሂፕ-ሃፕ ሙዚቃ፣ የታሸጉ ምግቦች
ትላልቅ የሳጥን ማከማቻዎች ሲበራከቱ፣ በቴክኖሎጂ፣ የሬድዮና የቴሌቪዥንን መምጣት ተከትሎ የአሜሪካ ባህል ወደ መላው አለም ተዛመተ፡፡፡ በሙዚቃ እነ ጄምስ ብራውንን፣ ዘ ቢትልስን፣ ማይክል ጃክሰንን፣ ኤልቪስ ፕረስሊን፣ቦብ ማርሊ፣ ማዶናን፣ ማርአያህ ኬሪን፣ ውሂትኒ ሆውስተንንና ሌሎች በጣም ታዋቂ ዘፋኞች የአለምን ህዝብ አሳበዱ፡፡
በፊልም ቻርሊ ቻፕሊን በብዙ የአስቂኝ ድምጽ አልባ ተንቀሳቃሽ ምስሎቹ ይታወቃል፡፡ ከሱ በኋላም በጥቁርና በነጭ እስክሪንና በቀለምም ጭምር በሲኒማ ብዙ ሰዎች ተነስተው አልፈዋል፡፡ ፊልም ማየት በጣም ሰዎች የሚያዘወትሩት መዝናኛ ሲሆን የአሜሪካን ባህል በአለም ላይ በማሰራጨት የፊልም ኢንደስትሪ አንበሳውን ድርሻ ይወስዳሉ፡፡ አንዳንዶች አለምን እየመሩ ያሉት ፖለቲከኞች ብቻ ሳይሆኑ የሆሊዎድ ፊልሞች ናቸው ይላሉ፡፡
በምዕተ አመቱ የመጨረሻ 25 አመታት ኮምፒዩተር ጌሞችና ኢንተርኔት አዲስና ተቀባይነት ያገኙ የመዝናኛ ዘዴዎች ሆነው ለአለም ህዝብ እንካችሁ ተባሉ፡፡

በአሜሪካና ባብዛኛው አውሮፓ በምዕተአመቱ የመጀመሪያ ክፍል ፖለቲካዊ መብትን ከተቀዳጁና አዲስ የወሊድ መቆጣጠሪያ ስልቶች ከመጡ በኋላ ሴቶች የበለጠ ራሳቸውን እየቻሉና ኢንዲፔንደንት እየሆኑ መጡ፡፡
በምዕተአመቱ መጨረሻ ሴቶች እኩል ህጋዊ መብት ተሰጥቷቸዋል፡፡
በ20ኛው ክ.ዘ. የወሊድ ቁጥጥር የህዝብ ብዛትን ለመቆጣጠር እንደ ሁነኛ ዘዴ ሆኖ በጥቅም ላይ ዋለ፡፡

በታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ድግግሞሽ፣ በብዙ የአለም ክፍሎች የመሬት መንቀጥቀጥ፣ መንሸራተትና፣ ጎርፍን የመሳሰሉ አካባቢያዊ ውድቀቶችና ውድመቶች ጨመሩ፡፡

ባጠቃላይ የሰው ልጅ የስልጣኔ ጫፍ ላይ ደረሰ ማለት ይቻላል፡፡ "Nothing is impossible" መባል ተጀመረ፡፡ የሰው ልጅ የልቡን አደረሰ ማለትም ይቻላል፡፡ ኑሮ ቀለለ፣ ሰው ነጻነቱን አወጀ፡፡

አለም ዛሬ ላይ ብዙ የማትግባባቸው ጉዳዮች አሉ፡፡ ከመቶ ዘጠና በላይ ሀገራት፣ ብዙ፣ ብሔሮች፣ ብዙ ባህሎች ባሉባት አለም፣ ሰዎች ቢግባቡ እንኳ ባይግባቡ አይገርምም፡፡ አለም የማትግባባት ብዙ ጉዳይ ቢኖርም አንድ አለም መግባባት ብቻ ሳይሆን በአለም ላይ ዛሬ ህግ የሆነ ጉዳይ አለ፡፡ መማር(እውቀት)፡፡ መማር ያስከብራል ሀገርን ያኮራል፡፡ የሚገርመው ታዲያ፣ በዚህ አለም ላይ መማርን የሚቃወም አንድ ሀገር ላይ አለመኖሩ ነው፡፡ ዛሬ ላይ በዚህ አለም፣ የመጨረሻው ክፉ፣ የመጀመሪያው መልካም ተደርጓል፡፡ The worst evil has become the best good. ምክንያቱም፣ ይሄ የመጨረሻው ዘመን ነው፡፡

ገና 2 አስርት አመታት እየሞላው ስላለው፣ ስለ 21ኛው ክ.ዘ. መጻፍ አስፈላጊ ስለመሆኑ እርግጠኛ አይደለሁም፡፡ ባጠቃላይ ግን፣ በሔዋን ውስጥ መብቀል የጀመረችው ፍሬ፣ በዝታ ተባዝታ፣ ወደ ሃያላን፣ ተገዳዳሪ ዛፎች አድጋለች፡፡ በቅርቡ ተመንጥረው፣ ወደ እሳት የሚወረወሩ ዛፎች፡፡ ዓለም፣ ከጫፍ እስከ ጫፍ በሰይጣናዊ አሰራሮችና በእርኩሰት ተሞላች፡፡ "መንደር ሆናለች አለማችን" ያሉት ነገር ትክክል ነው፡፡ 7 ቢሊየን በአምሳሉ የሰራው አምላኩ ላይ ያመጸ ትውልድ፣ የረከሰባት መንደር፡፡ እውቀትና ገንዘብ ያመጧቸው፣ ቲቪው፣ ስልኩ፣ ኮምፒውተሩ፣ ቴክኖሎጂው፣ ሰውን የሰይጣን ባርያ ያደረጉበት፡፡ ለካስ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል 6፡34 "ነገ ለራሱ ይጨነቃልና ለነገ አትጨነቁ፤ ለነገ ክፋቱ ይበቃዋልና፡፡" ያላቸው ለዚህ ነው፡፡

ውድ አንባቢ ይሄ ያነበብከው የዚህ መጽሐፍ 2ኛ ምዕራፍ፣ አንዱን ተቋም ከፍ አድርጎ ሌላውን ዝቅ የሚያደርግ እንደሚመስል ግልጽ ነው፡፡ ነገር ግን ጥሩ ታሪክ፣ ጥሩ የድሮ ማንነትን እንኳ የዛሬን መልካምነት እንደማያሳይ ከግንዛቤ ውስጥ ይግባልኝ፡፡

ምዕራፍ ሶስት

እውነተኛው እውነት

(The True Truth)

ሰዎች እንዳስተማሩን ሳይሆን እንደ እግዚአብሔር ቃል፡፡

አንድ እውነት አለ፡፡ ሶስት ሰዎች አሉ፡፡ አንደኛው እውነቱ አረንጓዴ ነው ይላል፡፡ ሁለተኛው ቢጫ፣ ሶስተኛው ደግሞ ቀይ ነው ይላሉ፡፡ እውነቱ ግን አንድና አንድ ብቻ ነው፡፡ እውነቱ ወይ አረንጓዴ ነው፣ ወይ ቢጫ ነው፣ ወይ ቀይ ነው፡፡ ወይ ደግሞ እውነቱ ከሶስቱ ውጪ ሌላ ነው፡፡ ግን እውነቱ አንድ ብቻ ነው፡፡ ይሄ እውነት ሰዎች ያሉት ወይም የሚሉት እውነት ሳይሆን እግዚአብሔር ያለው እውነት ነው፡፡ ሰዎች ያወረሱን እውነት ሳይሆን ሰማይና ምድር ሲያልፉ የማያልፈው የእግዚአብሔር ቃል የሆነው እውነት ነው፡፡ ሶስቱም የየራሳቸው እውነት ቢኖራቸውም እውነቱ ግን አንድ ብቻ ነው፡፡ ያ እውነትም፣ እውነተኛው እውነት ነው፡፡

" እውነት ላይ ያልተመሰረተ እውነት በውሸት ላይ የተመሰረተ ሐሰት ነው፡፡"
"A truth that is not based on the truth is a falsehood, a deception, a total deceit!"

“መስማትማ ትሰማላችሁና አታስተውሉም፣ ማየትማ ታያላችሁና አትመለከቱም፡፡ በዓይናቸው እንዳያዩ፣ በጆሮአቸውም እንዳይሰሙ በልባቸውም እንዳያስተውሉ ተመልሰውም እንዳልፈውሳቸው የዚህ ሕዝብ ልብ ደንድኖአልና ጆሮአቸውም ደንቁሮአል ዓይናቸውንም ጨፍነዋል፡፡” (የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ቅዱስ ማቴዎስ እንደ ጻፈው፣ ምዕራፍ 13፣ ከቁጥር 14 እስከ 15፡፡)

እውነት ውብ ነች፡፡ እውነት ጣፋጭ ነች፡፡ ሊቀበሏት ለማይሹ ግን እውነት መራራ ነች፡፡
The truth is beauty, the truth is sweet. But for those who will not accept the truth, the truth is bitter.

ቅድመ ምዕራፍ ሶስት

አንባቢ ሆይ፣ ይሄን ክፍል ስታነብ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ መንግስተ ሰማያት ቀርባለች ካለ ሁለት ሺህ አመት እንደሆነው እንድታስብ እፈልጋለሁ፡፡ የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ ካለ 2000 አመታት እንደተቆጠሩ እንድታስብ እሻለሁ፡፡ አብባቢ ሆይ ይሄን ክፍል ስታነብ፣ በነቢያት የተጻፉልን የመጨረሻው ዘመን ምልክቶች እየታዩ እንደሆነ እያስተዋልክ እንዲሆን እፈልጋለሁ፡፡ አንባቢ ሆይ ይሄን ክፍል ስታነብ ሰይጣን ብዙዎችን ተቆጣጥሮ፣ ገዝቶ ያለበት ጊዜ ላይ እንደሆንን እንድታውቅ እፈልጋለሁ፡፡ አንባቢ ሆይ ይሄን ክፍል ስታነብ የምንኖር ያለነው በውሸታም አለም ውስጥ እንደሆነ እያስብክ እንዲሆን እፈልጋለሁ፡፡ የኔ ትንሸዋ ኦክስፎርድ ዲክሽነሪ 666 ገጾች እንዳሏት እንድታውቅ እፈልጋለሁ፡፡(ራዕይ 13፡18) ከምንም በላይ ይሄን ክፍል ስታነብ “ሰማይና ምድር ያልፋሉ፣ ቃሌ ግን አያልፍም” ያለ አምላክ ለቃሉ ታማኝ እንደሆነ እንድታስብ አጥብቄ ላስታውስህ እወድዳለሁ፡፡ እንኳንስ ለ21ኛው ክፍለዘመን፣ ቢኖር፣ ለ921ኛው ክፍለ ዘመን የእግዚአብሔር ቃል ህያውና ያው ነው፡፡ የአምላኬ ቃል አያረጅም፣ የኢየሱስ ቃል አያረጅም፣ ዘላለም ይኖራል እያበራ፣ ከሚያምኑት ጋራ...

ሉቃስ 21፡29-33
ምሳሌንም ነገራቸው እንዲህ ሲል፡ **በለስንና ዛፎችን ሁሉ እዩ ሲያቆጠቁጡ ተመልከታችሁ በጋ አሁን እንደ ቀረበ ራሳችሁ ታውቃላችሁ፡፡ እንዲሁ ደግሞ እናንተ ይህ ሁሉ መሆኑን ስታዩ የእግዚአብሔር መንግስት እንደ ቀረበች እወቁ፡፡** እውነት እላችኋለሁ፣ ይህ ሁሉ እስኪሆን ድረስ ይህ ትውልድ አያልፍም፡፡ ሰማይና ምድር ያልፋሉ፣ **ቃሌ ግን አያልፍም፡፡**

ጌታችንና መድሃኒታችን የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ዛሬ ወይም ነገ፣ ወይም በዚህ አስር ወይም መቶ አመታት ይመጣል ብዬ ጊዜውን እየገመትኩ ወይም እየተነበይኩ አይደለም፡፡ ግን መጥምቁ ዮሐንስ መጀመሪያ፣ ከዚያ ኢየሱስ ክርስቶስም(ማቴዎስ 3፡2፤4፡17፤10፡7) "መንግስተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሀ ግቡ" ያለው ከ2000 አመታት በፊት ከሆነ ከ2000 አመታት በኋላ መንግስተ ሰማያት በጣም ቀርባለች ማለት አይደለም?

ካለፈው ምዕራፍ የቀጠለ

...ታድያ ሰውን ከእንስሳት የሚለየው ምንድነው? ሰውን ከእንስሳት የሚለየው፣ ሰው ከሰማይና ከምድር፣ ከፍጥረታት(ምን ያህል ነፍስ ያላቸው ፍጥረታት እንዳሉ ቁጥራቸውን አላውቅም) ሁሉ ተለይቶ አንዱ ፍጡር፣ ብቻውን በስድስተኛው ቀን መፈጠሩ ነው፡፡ ሰውን ከእንስሳት የሚለየው እግዚአብሔር ሰውን በመልኩና በአምሳሉ መፍጠሩ ነው፡፡ ሰውን ከእንስሳት የሚለየው እግዚአብሔር "...ምድርንም ሙሉአት፣ ግዙአትም፣ የባሕርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ግዙአቸው፡፡" ያለው ሰውን ብቻ መሆኑ ነው፡፡ ሰው የስጋ፣ የነፍስና የመንፈስ ጥምረት፣ መሆኑ ነው ሰውን ከእንስሳት የሚለየው፡፡ ሰውን ከእንስሳት ጋር ማወዳደር ብቻውን ትልቅ ፍልስፍናዊ ሃጢአት(የእግዚአብሔርን ስራ መገዳደር) ነው፡፡

ሰው የዝንጀሮ ዝርያ አይደለም፡፡ ሰው የእግዚአብሔር አምሳል ነው፡፡
2 ጴጥሮስ 1፡16፡- የእርሱን ግርማ አይተን እንጂ በብልሃት የተፈጠረውን ተረት ሳንከተል የጌታችንን የኢየሱስን ክርስቶስን ኃይልና መምጣት አስታወቅናችሁ፡፡
1 ጢሞቴዎስ 4፡7-10፡- ነገር ግን ለዚህ ዓለም ከሚመችና የአሮጊቶችን ሴቶች ጨዋታ ከሚመስለው ተረት ራቅ፡፡ እግዚአብሔርን ለመምሰል ግን ራስህን አስለምድ፡፡ ሰውነትን ለሥጋዊ ነገር ማስለመድ ለጥቂት ይጠቅማልና፡፡ እግዚአብሔርን መምሰል ግን የአሁንና የሚመጣው ሕይወት ተስፋ ስላለው፣ ለነገር ሁሉ ይጠቅማል፡፡ ይህ ቃል የታመነ ሁሉም እንዲቀበሉት የተገባ ነው፡፡ ይህን ለማግኘት እንደክማለንና፣ ስለዚህም እንሰደባለን፡፡ ይህም ሰውን ሁሉ ይልቁንም የሚያምኑትን በሚያድን በሕያው አምላክ ተስፋ ስለምናደርግ ነው፡፡

ከመጀመሪያው፣ ሰይጣን፣ አዳምና ሔዋንን፣ እግዚአብሔር እንደሱ እንዳትሆኑ ነው የከለከላችሁ ብሎ መልካምንና ክፉን የምታስታውቀውን ፍሬ እንዲበሉ እንዳታለላቸው፣ የሰይጣን አሰራር ሁሌም በመልካሙ ላይ ክፋትን፣ በክፋት ላይ መልካምነትን የመቀባት አታላይ መንገድ ነው፡፡ ምን እንደምትሰሙ ተጠበቁ ተብሎ የተጻፈልንም ለዚያ ነው፡፡

እግዚአብሔር አምላክም አዳምና ሔዋንን በኤደን ገነት ውስጥ አኖረ፡፡ እነርሱ ግን በሰይጣን ተታለው እግዚአብሔር የከለከላቸውን ፍሬ በሉ፡፡ እግዚአብሔርም ከገነት አስወጥቶ ወደ ምድር ወረወራቸው፡፡ እግዚአብሔርም አዳምን " የምድርን ቡቃያ ትበላለህ...በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ" አለው፤..." አለው፡፡ ሴት ወደ ምድር ስትወርድ፣ አምጣ ልጅን እንድትወልድ እንደሆነ ሁሉ፣ ሰው፣ ሰርቶ የላቡን ፍሬ እንዲበላ ነው፡፡

እውነቱ ከመሰረቱ

The TRUTH from the ROOT

የአለም እውነት

ሀገራችን ካለችበት አስከፊ ድህነት ወጥታ ማየት የማይፈልግ ማናለ? ሀገሩ የምግብ ዋስትናዋን አረጋግጣ ዜጎቿን መመገብ የምትችልበት፣ ደረጃ እንድትደርስ የማይመኝ ኢትዮጵያዊስ የት አለ? ከአደጉት ሀገራት ተርታ ተሰልፈን፣ አንገታችንን ቀና አድርገን በኢትዮጵያዊነታችን ኮርተን፣ ሲለን ዲቪ ወደኛ ሀገር ሲጀመር ማየትን ማን ይጠላል? ከተሞቻችን ፎቅ በፎቅ ሆነው ከኒው ዮርክና ከዱባይ ጋር ሲነጻጸሩ ማየትን ያላለመ ኢትዮጵያዊ የትስ አለ? በቄስ በሊና ሳርካ ትንቢቶች፣ ህልማችን ወደ ተስፋ ተለውጧል፡፡ አንድ ቀን ኢትዮጵያ ያደገች፣ የሰለጠነች ሀገር እንደ ምትሆን ተነግሮናል፡፡

መንግስታችን(ኢህአዲግ) ከሌላ ሀገሮች ተሞክሮ የመውሰድ፣ ልምድ የመካፈል፣ ከሌሎች ሀገራት የመማር ከፍተኛ ፍላጎት አለው፡፡ ከቻይና በፍጥነት ማደግን፣ ከአሜሪካ ዲሞክራሲን...
ሁሉም እድገትን እንደ ሚፈልግ ግልጽ ነው፡፡ ጥያቄው እንዴት የሚለው ነው፡፡ እንዴት እንበልጽግ? ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የኢትዮጵያን ብልጽግና ለማሳካት ሞክሮ ሁላችንም እንደ ምናውቀው ሳያሳካው አለፈ፡፡ ድንቅ እቅድ፣ ድንቅ ፖሊሲ ነበረ፡፡
ኢትዮጵያ ከብዙ መቶ አመታት በፊት የተፈራ ስልጣኔ ነበረች፡፡ ያ ስልጣኔ በዘመነ መሳፍንት እየወደቀ እየወደቀ እንዳይነሳ ሆኖ ወደመ፡፡
አጼ ምኒሊክ ባቡር አስተዋወቁን፡፡ በቀዳማዊ ሀይለስላሴ ከሁሉም በላይ ጠቃሚው ት/ት ይስፋፋ ጀመረ፡፡

ከሁሉም በላይ ሀገርህን ለማልማትና ለማሳደግ ከፈለግክ ትውልዱን ነው የምትኮተኩተው፡፡ ይሄን ስላወቅኩ ነው ስለ ት/ታችን ጥራት፣ ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው ከሀይስኩል ጋር አያይዤ መጻፍ ጀምሬ የነበረው፡፡ ከቴዎድሮስ እስከ መለስ ዜናዊ፣ ከመለስ ዜናዊ እስከ ቀጣዩ መሪ፣ ጥያቄው ሁሌም "እንዴት እንልማ?" እንጂ "እንልማ ወይ?" ሆኖ አያውቅም፡፡ አንልማ አንድነታችን፣ እንዴት ደግሞ ልዩነታችን የሆኑ ይመስላሉ፡፡ አልቀሰቀስ ያለውን ልማት ለማንሳት፡፡
በሁለት መንገዶች መልማት ይቻላል፡፡ በገንዘብና በስራ፡፡ አንደኛው እንደ አረብ ሀገራት ሙስና የማይቀንሰው፣ መሀይምነት የማይቋቋመው ልማት ነው፡፡ አለም በሚሽከረከርበት ነገር ላይ ትፈጠርና ትንሽ መሬቱን ቆፈር ቆፈር ስታረገው ነዳጅ ይፈልቃል፡፡ በነዚህ ሀገራት የፈለገው ሙሰኛና መሀይምነትህ የተንደላቀቀ ህይወት ከመምራት አያግዱህም፡፡
ሁለተኛው፣ ስራ ይባላል፡፡ እንዴት እንደምትሰራ ማወቅ፣ ምን መቼ እንደ ምትሰራ ማስላት፣ ብዙ ዋጋ የሚያስከፍሉህን ውሳኔዎች ማስወገድ፣ ያለህን ሀብት ባግባቡ በጥበብ እንዴት እንደምትጠቀም ማወቅ ብቻ ሳይሆን ያንተ ያልሆነውን የሌሎች ረብጣ ሀብት እንዴት ለራስህ ማድረግ እንደምትችል ማወቅ ብቻም ሳይሆን የሌለን ሀብት ለራስህ ፈጥረህ መጠቀም ነው፡፡

የመጀመሪያውን የለንም፡፡ ሁለተኛውንና አስተማማኙን ግን ትውልዱን በመኮትኮት እውን ማድረግ ይቻላል፡፡ ወደ ማይቀለበስ ብልጥግና ሀገራችንን ማድረስ የምንችለው የዜጎችን አዕምሮ በማይቀለበስ አስተሳሰብ ስናበለጽገው ነው፡፡ ፈረንጆች የሚሰሩትን ነገር በፍጥነት፣ በጥራት፣ በጊዜ ነው የሚሰሩት ይባላል፡፡ በጣም ትክክል ነው፡፡ ከመለስ የት/ት ፖሊሲ መጽሐፍ ያነበብኩትን ታሪክ ላካፍልህ፡፡ ጀርመን በሁለተኛው የአለም ጦርነት እንዳትነሳ ተደርጋ ትወድማለች፡፡ ያልወደመችበት ዘርፍ አልነበረም፡፡ በገንዘብ፣ በመሰረተ ልማት የነእንግሊዝ ጦሮች ሆነ ብለው ነበር ጀርመንን ለማድከም ፋብሪካዎቿ፣ ህንጻዎቿ፣ መሰረተ ልማቶቿ ላይ የቦንብ ናዳ አውርደው አመድና የተራቆቱ ከተሞችን ለቀሩት ጀርመናውያን ያስታቀፏቸው፡፡ ሁሉንም የነበራቸውን ነገር ቢነጠቁ ቀሪ ጀርመናውያን የማስፈጸም አቅማቸውና አደረጃጀታቸው ከነሱ ጋር ነበር ይለናል የቀድሞው መሪያችን፡፡ አዕምሮአቸው፣ አስተሳሰባቸው ማለት ነው በግልጽ አማርኛ፡፡ ጀርመን በአለማችን አስተማማኙ ሀብት አዕምሮ እንደ ሆነ አስመሰከረች፡፡ በጥቂት አመታት ማንሰራራት ቻለች፡፡ መሳሪያዎቿን በአዲስና በተሻሉት ተክታ በ10 አመት ውስጥ ወደ ነበረችበት መመለስ ብቻ ሳይሆን እነእንግሊዝንም ለመብለጥ በቃች፡፡ መለስ ይሄን ታሪክ ከመሳሪያ በላይ ያንን መሳሪያ የሚጠቀመው ሰው ውድ ሀብት እንደሆነና የሰው አዕምሮ ላይ መስራት እንዳለብን፣ የሰውየው አዕምሮ ካልበለጸገ መሳሪያ ምንም እንዳልሆነ፣ ሰውየው ብስል ከሆነ ግን ተአምር መስራት እንደሚቻል ለማስረዳት ይጠቀምበታል፡፡

አስተሳሰባችን ማደግና መበልጸግ እንዳለበት ሁላችንም እንስማማለን፡፡ አሁንም እንዴት የሚለው ነው ጥያቄው፡፡ እንዴት በፍጥነት? ት/ቤት አዕምሮአችን የሚቀረጽበት፣ አስተሳሰባችን የሚቀየርበት ቦታ ነው፡፡ በየጊዜው የተማረ ሰው ብዛታችን እየጨመረ ነው፡፡ ብዙ ዶክተሮች፣ ብዙ ኢንጂነሮች፣ ብዙ ባለሙያዎችንም እያፈራን ነው፡፡ የአስተሳሰብ ለውጥ ማለት፣ መማር፣ ዲግሪ መያዝ፣ ዶክተር መሆን ማለት ብቻ ግን አይደለም፡፡ ወይ እንደኔ ስትሬት ኤ ማምጣት ማለትም አይደለም፡፡ አንድ የተማረ ሰው ካልተማረው የተሻለ እንደሚያስብ ግልጽ ነው፡፡ የአስተሳሰብ ለውጥ ማለት ግን ከዚያም በላይ ነው፡፡ እንደ ጀርመኖቹ ታሪክ ነው፡፡ እኛ ሀገር ፎቅ ፈረሰ፣ ፎቅ ወደ ኋላ ተገልብጦ ተሰራ ይባላል፡፡

አንዴ በናሁ ቲቪ የህግ ፕሮግራም ላይ፡ ባልና ሚስት ቢበዛ 6 አመት የሚሆነውን ህጻን ልጃቸውን ለማስገረዝ ሆስፒታል ያደርሱታል፡፡ ልጁ ከ3 ሰአት በኋላ ሲወጣ አዕምሮ ታማሚ ይሆናል፡፡ ምነው ልጃችን ምን ሆነ ብለው ሲጠይቁ ለትንፋሽ ባፍንጫው የገባለት ቱቦ ወደ ጨጓራው ሄዶ ደም ለ8 ደቂቃዎች ከአዕምሮው ብሎክድ ሆኖ ነው አሏቸው፡፡ ከወራት በኋላ የጨነቀው አባት ሆስፒታሉ ይሄድና የሆስፒታሉን ዳይሬክተር ያነጋግራል፡፡ አሁን ምንድነው የማረገው፣ ምንድነው የምታረጉልኝ ብሎ ግራ የገባው አባት ይጠይቃል፡፡ ዶክተሩም "ከ90 ሚሊየን ኢትዮጵያዊ ያንተ ልጅ እንዲህ ቢሆን ምን ይገርማል?" ይለዋል፡፡ ዶክተሮች ናቸው አይደል ግን የሆስፒታል ዋና ዳይሬክተር የሚሆኑት? አንድ ዶክተር እንዲህ አዕምሮ የሌለው ሰው ንግግር የሚናገር ከሆነ ይሄ ለኔ በተለይ በሀገራችን የት/ት ደረጃ የአስተሳሰብ መለኪያ እንዳልሆነ ማሳያ ነው፡፡ እሺ ዶክተሮቹ ልጁን ያሳመሙትን ሊፈጠር ይችላል እንበለው፡፡ ዶክተሮች ሰው እየቀደዱ ስለሚውሉ ሰውን ከእንስሳ ለይተው አያዩም የሚባለው እውነት ነው እንበል፡፡ ግን ምን አይነት ሰው ነው ስንትና ስንት ሊመልስለት የሚችለው መልስ እያለ በግድ የለሽነት ምን ይገርማል? የሚል? አንድ ልጅህ ጭንቅላቱን እንኳን መሸከም የማይችል የአዕምሮ በሽተኛ ቢሆን ምን ይርማል እያለው እንደ ሆነ እንዴት ማስተዋል ያቅተዋል፡፡ እያጣራን ነው እንኳን አይለውም? ማንነው ለስምንት ደቂቃ አዕምሮው ደም ያጠረው ግን? ህጻኑ ወይስ ማኔጂንግ ዶይሮክተሩ?

ከሆስፒታል ካፌ ገመና ድራማን እያየ ድንገተኛ(emergency) ደም የሚፈሰው ሰው መጥቶ እንዲያክመው ሲጠራ፣ ድራማውን አይቼ ካልጨረስኩ ያለው ዶክተርስ? እሱ ድራማውን እስኪጨርስ ሰው ሊሞት እንደሚችል ጠፍቶት ማለት ነው፡፡ እንዴት ነው ብዙ እያወቅን ስንሄድ እየተምታታብን፣ ማገናዘብ እያቃተን ነው እንዴ የሚሄደው? ብዙ የምታውቀውን ታሪክ ልትጨምርበት ትችላለህ፡፡

አየህ የነቃ አስተሳሰብ ያለው ሰው ማለት በህይወቱ ውስጥ ስህተቶችን ለማስወገድ የሚጥር፣ ስህተትን የሚጸየፍ፣ የሚሰራው ስራ ብቻ ሳይሆን የሚናገረውን ጠንቅቆ የሚያውቅ፣ ሲያወራ መሳሳት የማይፈልግ፣ ለእያንዳንዷ ቃል ዋጋ የሚሰጥ፣ የሚናገረው ነገር ምን ያህል ጠቃሚ እንደ ሆነ፣ ምን ያህል ጎጂ እንደ ሆነ ምን ያህል እንደ ሚሄድ የሚያውቅ፣ አላስፈላጊ ጉዳቶችን ሰዎች ላይ የማያደረስ፣ ሊነኩት በቃጡ ላይ ግን እንዳያገግሙ አድርጎ በምላሱ ሊገርፋቸው የሚችል፣ ጥቅሙን የሚያውቅ፣ ጉዳቱንም የሚያውቅ፣ ለጥቅሙ የሚዋጋ፣ ከተጎዳ የሚታገል አይነት ሰው ነው፡፡ ጠቢብ የምንለው አይነት ሰው ነው፡፡ ጠቢብ የተሰጠውን ሀላፊነት በተሰጠው ጊዜ ከሚጠበቀው በላይ በፍጥነት፣ ከሚጠበቀው በላይ በጥራት፣ ያልተሰጠውንም ሀላፊነት ጭምር ለመወጣት የሚተጋ፣ ስህተቶችን ለማስወገድ የሚጥር፣ በስራውም ሆነ በሚያወራው ነገር፣ በህልሙም ቢሆን ፍጹም(perfect) መሆን የሚፈልግ ሰው ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ ከሁሉም ቀድሞ መገኘት ይፈልጋል፡፡ ቀዳሚ፣ አሸናፊ መሆን፡፡

እኛ ያንን ነው ያጣነው፡፡ በየደረጃው፣ በየቀኑ፣ በየግላችን ትክክለኛ ውሳኔዎች፡፡ ከአንድ ሰው ብዙ ለመሰብሰብ ከፈለግክ በሁሉም ነገር ላይ ጠቢብ ታረገዋለህ፡፡ የኤሌሜንተሪና የሀይስኩል ተማሪ እያለ ስለ ሁሉም ነገር በሚያመራምር መልኩ ታስተምረዋለህ፡፡ ትምህርት ደግሞ ሎጂክ ነው፡፡ ምክንያት ምክንያት፡፡ ምርምር ምርምር፡፡

ጥሩ የማስፈጸም አቅም ያለው ዜጋን ለማምረት መጀመሪያ በልጅነቱ ለሁሉም እንዲጋለጥና ጠቢብ እንዲሆን አርገህ ትኮተኩተዋለህ፡፡ ከዚያ ሁሉንም አይቶ የተመቸውን አንዱን ከሌሎቹ አብልጦ ያይና ዩኒቨርሲቲ ሲገባ በፍቅር የወደደውን ት/ት ይማራል፡፡ አንተ ደግሞ በአሪፉ ታሰለጥነዋለህ፡፡ ከዚያ በሰለጠነበት ሙያ አካባቢውን ያንቀጠቅጣል፡፡

ተማሪን ጠቢብ በማድረግ መንገድ ላይ አንባቢነትን ረስቶ ጉዞ መጀመር ዘበት ነው፡፡ ፈረንጆች ልጆቻቸው ሆድ ውስጥ እያሉ ነው ታሪክ የሚያነቡለቸውና በነሱ አለም የንባብ ፍቅር ከሆድ ውስጥ ነው የሚጀምረው፡፡ ማንበብ በፈረንጆች ዘንድ በጣም ባህል የሆነ ነገርና በጣም ለጠቢብነታቸው ከፍተኛውን ድርሻ ይጫወታል፡፡ ንባብ የሚጀመረው ያው ከህጻናት ታሪክ፣ ከተረት ተረቶች ነው፡ ከዚያ ወደ አጫጭር፣ ረጃጅም ልቦለዶች መሸጋገር፡፡ ልቦለድ ለኔ አዝናኝ ነገር ብቻ ሳይሆን አስተማሪም ጭምር ነው፡፡ አንተ ያሰብከውን አስተማሪነት አይደለም፡፡ እገሌ እገሌን እንዲህ አደረገው፣ ከዚያ ለራሱ ደግሞ እንዲህ እንዲህ ሆኖ ከዚያ የባሰ ችግር ደረሰበት፡፡ ከዚህ ታሪክ የምንማረው "ከፋት ለራሳችን እንደ ሚጎዳን ነው..." አይነቱን አስተማሪነት አይደለም፡፡ በዚህ በዚህ እንዲያውም ታሪኮች ሳይለንት ኪለሮች ናቸው፡፡ ለኔ ልቦለድ ታሪኮች በሂሳብ መጽሐፍ ላይ በየዩኒቱ መጨረሻ ላይ ያሉትን ዎርድ ፕሮብሌሞች ይመስሉኛል፡፡ የሌለ ነገር ነው፣ ምን ይጠቅመኛል? ስል ሁለት ብርቱካን በዚህ ያህል ብር ከገዛህ...ይልና ስማር የነበርኳቸውን ባዶ ቁጥሮች ከእውነተኛው አለም ጋር አያይዞ ህይወት ይዘራባቸዋል፡፡ ልቦለድ መጽሐፍትም እንዲሁ ናቸው፡፡ ልዩነታቸው፣ ዎርድ ፕሮብሌሞች ይከብዳሉ፡፡ ት/ቤት የምትማረው ሂሳብ፣ ፎርሙላ ካለውም አስገብተህ ይሄ ሲደመር እንዲህ ይሆናል፣ ያ ሲቀነስ እንዲህ ይሆናል ስለዚህ መልሱ እንዲህ ይሆናል ነው፡፡ ልቦለድም ምክንያታዊ ነው፡፡ ካላሳመነህ ይደብርሀል፡፡ ደራሲው በማያሳምን መንገድ፣ በማያሳምን ጊዜ ሽፍታውን ድንገት መኪና ገጭቶት ዋና ገጸ ባህርይውን መከታተልና መፈታተን አቆመ ሲልህ ይደብርሀል፡፡ ሂሳብ ጥያቄ እየሰራ እየሰራ መሀል ደርሶ ቁጥር ተሳስቶ ወይም ቀጣዩ ስቴፐ ጠፍቶበት መልሱን እንዲሁ በግምት የሞላ ተማሪን ይመስልሀል፡፡ ስቴፑን እያየህ ጥሩ አብረህ እየሄድክ እዛች ቦታ ስትደርስ አይዋጥልህም፡፡ ከየት መጣ ትላለህ፡፡ መኪናው ከየት መጣ? ታሪኩን እንደፈለገው ማሽከርከር ይችላል ግን አይዋጥልህም፡፡ በምን ሂሳብ ነው እንደዚያ ሊሆን የቻለው? ይደብርሀል፡፡ ምክንያታዊ ስላልሆነልህ፡፡ ልቦለድ መጻፍ ማለት ተማሪዎችን ሂሳብ ማስተማር እንደ ማለት ነው፡፡ እንዲህ ሲደረግ እንዲህ ይሆናል፡፡ ከዚያ እንዲህ አይሆንም ተማሪዎች? ታብራራላቸዋለህ፡፡ ለሚጠይቁት ጥያቄ በቂ ማብራሪያ መስጠት አለብህ፡፡ ካልሆነ ት/ትህ ተማሪውን ይደብረዋል፡፡ ጎበዝ አስተማሪ አይደለህም ማለት ነው፡፡ ጎበዝ ደራሲ አይደለህም

ማለት ነው፡፡ ስለ ድርሰት ማውራት ፈልጌ አይደለም፡፡ ግን ልቦለድ ማንበብ ማለት ወይም ልቦለድ ማንበብን መውደድ ማለት 1+1=2, 2x+3=0, x=-3/2….. እያሉ መዋልን መውደድ ማለት ነው፡፡ ሂሳብ መማር ማለት ነው፡፡ ልቦለድ ሂሳብ ስለ ሆነ ነው ብዙ ሰዎች ለማንበብ እየፈለጉ አንድ መጽሐፍ ማንበብ ጀምረው የሚያቆሙትና ደበረኝ የሚሉት፡፡ ተማሪው ሂሳብ አስተማሪውን ትንሽ አዳምጦ ሲከብደው እንደ ሚያቆመው፡፡ የት/ቱ ሂሳብ የሚቀርብልህ በቁጥሮች ነው፡፡ የልቦለዱ ሂሳብ ደግሞ በህይወት ነው፣ በፍቅር፣ በቤተሰብ፣ በሀይማኖት፣ በፍልስፍና፣ በስራ… ስለዚህ ልቦለድ በህይወትና በሂሳብ(በት/ት) መሀል ያለ ድልድይ ነው፡፡ ከዚያም በላይ፡ ፊልም፣ ጽሁፍ፣ በእውነተኛ ሰዎች፣ በእውነተኛ ድምጽ፣ በአይንህና በጆርህ የምትቀበለው፣ ጆሮና አይንን ብቻ ማዘጋጀት የሚፈልግ ታሪክ ነው፡፡ ልቦለድ ወይም ተረት ሲሆን ግን፣ ሰዎቹን፣ ቦታዎቹን፣ ድምጾቹን፣ እንቅስቃሴዎቹን፣ ደራሲው የዘራቸውን ፊደላት በመልቀም፣ በራስህ ህይወት የምትዘራባቸው፡፡ እናም ያ ነገር፣ ከሂሳቡና ከምክንያቱ የበለጠ፣ መገመት ከምትችለው በላይ አዕምሮህን ይለጥጠዋል፡፡ ሰው፣ ክብደት ሲያነሳ ጡንቻዎቹ እንደሚያድጉ፣ ያ ንባብ ደግሞ አዕምሮን ያሰፋል፡፡ ከዚያ ብዙ ባነበብክ መጠን፣ አዕምሮህ በአዳዲስ ሀሳቦች ይዳብራል፡፡ ፊደላትን ለቅመህ ህይወት ዘርተህባቸው፣ ምስልንና ድምጾችን ስትፈጥርበት፣ ምክንያቶችን፣ ስታዥጎደጉድበት የነበረው አዕምሮ፣ ያንን ያስለመድከውን ነገር ይለማመደዋል(አዳፕት ያረገዋል)፡፡ እያነበብክ በሌለህበት ጊዜ እንኳን ጥቃቅን ነገሮች ላይ ብዙ፣ ሀሳቦችን ይፈጥራል፡፡ እያሰበ መዋል ይፈልጋል፡፡ እንደ አዲስ ልቦለድ፣ አዲስ ነገር መስማት፣ እያሰላሰለ መዋል ይፈልጋል፡፡ የራሱ የሆነ ውስብስብ ታሪክና ሌሎች ያላሰቡትን ችግር እየፈጠረ፣ ሊፈታው ሲሞክር ይውላል፡፡ የሰማውን ነገር እያሰፋ፣ እያሰፋ ትልቅ ነገር ያሳክለዋል፡፡ ያም ራስህን፣ የምትኖርበትን ማህበረሰብ፣ ታሪክን፣ ተፈጥሮን፣ እግዚአብሔርን ወደ መመርመር ይመራሃል፡፡ ትምህርት ቤት፣ ሰዎች፣ ማህበረሰባቸውን፣ ታሪክን፣ ተፈጥሮን(ባዮሎጂ፣ ፊዚክስ፣ ኬሚስትሪ)፣ መርምረው የደረሱብትን ማጥናት ሲታከልበት ደግሞ ምን እንደሚሆን ገምተው፡፡ ምን ልበል፣ ሀገርን በአንዴው ሊያወድም የሚችል የጦር መሳሪያ ፈጣሪ ልትሆን ትችላለህ፡፡ የፈረጠመ፣ የጠነከረ አዕምሮ ይኖርሃል፡፡ ከጥንካሬ ብዛት፣ በህይወትህ ውስጥ ሰዎች የማያስፈልጉህ ይመስልሃል፡፡

አንድ ልቦለድ የማያነብ ጎበዝ ተማሪ ጠቢብ የመሆኑ ነገር በጣም የማይመስል ነገር ነው፡፡ አንባቢ ተማሪ ግን የተማራትን ጥቂት ነገር በህይወት ሚዛን ላይ ነው የሚያስቀምጣት፡፡ ልቦልድ የኖረውን ህይወትና የተማረውን ሂሳብ ስለሚያስተሳስር ሲያወራ፣ ፈተና ላይ ስቴፕ ላለመሳሳት የሚያደርገውን ጥንቃቄ እየተጠነቀቀ ይሆናል የሚያወራው፡፡ የሚያስባቸው ነገሮች ይሄ ሲቀነስ ይሄን ከሆነ በዚያ ሳካፍለው እንደዚህ መሆን አለበት ማለት ይጀምራል፡፡ አመንክዮ ይሉታል፡፡ ታዲያ ይሄ አስተሳሰብ ነው ስራ ላይ ማዕበል ሆኖ ሀገር የሚያናውጠው፡፡ እንዲህ አይነት ሰዎች በበዙ ቁጥር ማእበል መፍጠሩና ሀገር ማናወጡ ወይም መለወጡ ቀላልና ፈጣን ይሆናሉ፡፡ ማዕበሉ ግን የሚጀምረው ከሀገር አይደለም፡፡ ከራስ ነው፡፡

እውነተኛው እውነት

ት/ቤት 1 + 1 = 2 እንደሆነ ያስተምሩሃል፣ እንዴት ብዙ ችግሮችን በማቲማቲካል ሎጂክ እንደምትፈታ ያስተምሩሃል፡፡ ት/ቤት የትየለሌ ነገሮችን የምታውቅበት ቦታ ነው፡፡ ነገር ግን ሳይንስ ስለሚታየው ቁሳቁ ዓለም እንጂ ስለማይታየው ስላልሆነ፣ የማይታይን ነገር ማብራራትም ስለማይቻል፣ ከማየትና ከመስማት፣ ከመዳሰስ ባሻገር ያለውን ዓለም አያውቅም፡፡ አንተ፣ ወደዚህች ምድር ስትመጣ፣ ተምረህ ብዙ ነገር ከማወቅህ በፊት(ያልተማረ ሰው፣ ፊደል ያልቆጠረ ሰው መሆንም አለ) ከሁሉም ነገር በፊት ግን አንተ የአንድ ወንድና የአንድ ሴት ልጅ ነህ፡፡ ሰው ወይም አጋጣሚ፣ ወይ ምርጫህ፣ የተማርከ ሰው፣ መሃይም፣ አርጅቶ የሞተ ሰው፣ በልጅነቱ የሞተ ሰው፣ በሆድ ውስጥ የሞተ ሰው ሊያደርጉህ ይችላሉ፡፡ ምንም ቢያደርጉህ ግን የአንድ ወንድና የአንዲት ሴት ልጅ መሆንህን ሊያስቀሩት አይችሉም፡፡ ቤተሰብ በአንድ ሰው ህይወት ውስጥ በጣም ከፍተኛው አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ አንድ ሰው፣ እጁን ቆርጦ መጣል ቢችል፣ ቤተሰቡን ቆርጦ ከራሱ ሊጥል አይችልም፡፡ ምክንያቱም ቤተሰብ በጣም መንፈሳዊው የሰው ልጅ ተፈጥሮ ነው፡፡ ታዲያ ሳይንስ የዓለምን ቅራቅምቦና ልጅ እንዴት እንደሚፈጠር፣ ምክንያታዊ ትንታኔ ሲሰጥ፣ ቤተሰብን ግን ሊያብራራው አይችልም፡፡ ምክንያቱም ሳይንስ ቁሳዊውን ዓለም እንጂ መንፈሳዊውን ዓለም ሊመረምር አይችልም፡፡ ሳይንስ የቤተሰብ ሁኔታ ከምንም በላይ በአንድ ሰው ህይወት ላይ ተጽእኖ እንደሚያሳድርና የተፋቱ ሰዎች ልጆች በጣም እንደሚጎዱ በጥናቱ ቢደርስበት፣ ሳይንስ ለእንደዚህ አይነት ችግሮች መፍትሄ የመስጠት አቅም የለውም፡፡ ምክንያቱም ይሄ መንፈሳዊ ጉዳይ ነው፡፡ ምክንያቱም የችግሩ መጀመሪያ መሰረት፣ ሳይንስ ራሱ ነው፡፡

"መንፈስ ግን በግልጥ፡ በኋለኞቹ ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንትን ትምህርት እያደመጡ፣ ሃይማኖትን ይክዳሉ ይላል፡፡" ጢሞቴዎስ 4፡1

በዚህ አለም ላይ ብዙ የምናስበውና የምናውቀው ነገር ሁሉ ውሸት እስኪሆን ድረስ የምንሰበካቸው የውሸት ስብከቶችና ትምህርቶች አሉ፡፡ ምክንያቱም ይሄ የሰይጣን ግዛት ነው፡፡ ሰይጣን ደግሞ ውሸታም፣ የውሸት አባት ነው፡፡ ችግሩ ሰይጣን የሚሰብከን እኛ ስብከትን በምናውቅበት መንገድ አለመሆኑ ነው፡፡

በህይወቴ በሁለት ትላልቅ የውሸት ስብከቶችን ተታልያለሁ፡፡ አንደኛው የኢህአዴግ የውሸት ስብከት ነው፡፡ መንግስት በቲቪ ዴሞክራሲያዊ ነኝ፣ ኢትዮጵያን እያሳደግኩ ነው፣ እያለ ራሱን በውሸት የሚያሞጋግስበት ስብከት፡፡ በኢቲቪ በመታለሌ ኢህአዴግንና መለስን፣ በጣም ስወዳቸው፣ ተቃዋሚዎችን እጠላቸው ነበር፡፡ ይሄኛው የመንግስት የውሸት ስብከት ላይ ያለፈው አመት(2008) ስነቃ፣ በመታለሌ በጣም ነበር የተናደድኩት፡፡

ሁለተኛውና ትልቁ የውሸት ስብከት ደግሞ የአለም ስብከት ነው፡፡ የራሱ፣ የዴሞክራሲና ሁሉም የፖለቲካ ስብከት፣ የኢኮኖሚ ስብከት፣ የልማት ስብከት፣ የባለጠግነት ስብከት፣ የእውቀት ስብከት፣ የሐሰተኛ ነቢያቶችና አስተማሪዎች ስብከት፣ የ"ሁሉም ይቻላል" ስብከት፣ የፊልም ስብከት፣ የዝና ስብከት፣ የቴክኖሎጂ ስብከት፣ የመብትና የእኩልነት ስብከት፣ ውሸተኛው የሰላም ትርጉም ስብከት…

የመንግስት ስብከት ላይ ከነቃው በኋላ፣ ትልቁናሐሰተኛ የአለም ስብከት ላይ ለመባነን ግን ሌላ 18 አመት ይቅርና፣ 8 ወር አልፈጀብኝም፡፡ አለም ውሸትን ስታጠጣኝ፣ እውነቱን እየሰማሁትና እያየሁት ባድግም ማስተዋል ግን አልተቻለኝም ነበር፡፡ በርግጥ አይናቸው በውሸት በጣም ከተጋረዱት መሃል አንዱ ነበርኩ፡፡ ዴሞክራሲ በራሱ ትልቅ ውሸት ሆኖ ሳለ፣ የመንግስትን ዴሞክራሲያዊ ነኝ ባይነት አምኜ መቀበሌ፣ በጥልቀት ተታልዬ እንደ ነበረ ያሳያል፡፡

ከህጻንነቴ ጀምሮ በህይወቴ ውስጥ የሰማሁትና ያየሁት ነገር ሁሉም ማለት በሚቻል መልኩ ውሸት እንደሆነ ሳውቅ፣ ስሰማውና ሳነበው ያላስተዋልኩትን እውነት፣ ላስተውለውና ልኖረው ይገባኝ የነበረውን እውነት ለመረዳት ራሴን አተጋሁ፡፡ እውነቱን ከህጻንነቴ ጀምሮ ሳነበውና ስሰማው ባድግም ለዚህች ውሸታም አለም የነበረኝ ጉጉት አይኖቼን ጋርዶ ነበር፡፡ ይህቺ አለም ውሸታም እንደ ሆነች፣ ምንም እውነት እንደሌለባትና ይሄ ዘመን የመጨረሻው እንደሆነ አውቄ የምወግንለት አለም ሳይኖር፣ ለሰለጠንኩበት የባለጠግነት ትምህርት ሳላደላ፣ ከወገንተኝነት አዕምሮዬን አጽድቼ እውነተኛውን የእግዚአብሔር ቃል ሳነበው፣ እየገባኝ የነበረው እውነቱ ብቻ ሳይሆን፣ ይህቺ አለም ከእውነቱ ምን ያህል እንደ ራቀች ጭምር ነበር፡፡ እግዚአብሔር ከመርፈዱ በፊት ማስተዋሉን ይመልስልን፡፡ አሜን፡፡

አለም ሃብታም እንድንሆን ትመክረናለች፡፡ አለም አዋቂ ምሁራን እንድንሆን ትነግረናለች፡፡ እውቀት ያለው የትም ሄዶ መኖር ይችላል ትለናለች፡፡ አንብብ ትለናለች፡፡ ይሄ የአለም መስፈርት ነው፡፡ ምክንያቱም ይሄ የመጨረሻው ዘመን ነው፡፡ የእግዚአብሔር መስፈርትስ ምንድነው?

አንድ ያደግንበት እውነት አለ፡፡ እኔ ስወለድ ጀምሮ ጎበዝ ተማሪ መሆን እንዳለብኝ፣ ዶክተር ሆኜ፣ ሀብታም ሆኜ ራሴን፣ ቤተሰቤንና ሀገሬን መርዳት እንዳለብኝ ነው ሲነገረኝ ያደግኩት፡፡ ወላጆቻችን፣ እያጠናን ብንውልና እንቅልፋችንን አጥተን እያጠናን ብናድር ደስ ይላቸዋል፡፡ በጥናት ምክንያት የሚኖረውን የልጅና የወላጅ ንዝንዝ ቤት ይቁጠረው፡፡ ማትሪክ ወደቀ፣ ከዩኒቨርሲቲ ተባረረ እየተባለ በየአመቱ የሚለቀሰውን የእምባ መጠን፣ አይን ይቁጠረው፡፡ ግን ለምን?

ዴሞክራሲ፣ የተለያዩ ለሀገራቸው ነጻነት የታገሉ ሰዎች፣ ራሳቸውን የሰዉ፣ እንደ መለስ ትልልቅ አለማዊ ስራዎችን የሰሩ ሰዎችን በሚዲያም፣ በት/ቤትም ስንሰበክ ኖረናል፡፡ ስለ ብሔር ብሔረሰቦች፣ ስለ ሙብት፣ ስለ ሴቶች እኩልነት፣ ስለ ብዙ ነገር፡፡ እንደ አንድ ዜጋ፡፡ ሃይማኖት እንዳለው ሰው ደግሞ የምንሰማው ነገር ይኖራል፡፡ እኔ ፕሮቴስታንት ነኝ፡፡ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስራ፣ ስለተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች፣ ክፍሎች፣ እየሰማሁ፣ እየተሰበኩ፣ እየተማርኩ፣ እያነበብኩም ጭምር አድጌያለሁ፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በሰራው ስራ፣ ለሃጢአቴ መክፈል የሚገባኝን ዋጋ በተቀበለው መከራ፣ በመሰቀሉ፣ በሞቱና በሶስተኛውም ቀን በመነሳቱ ካመንኩኝ ከሰራሁት ሁሉ ሃጢአት እንደምነጻ አውቀዋለሁ፡፡

ሃይማኖት ምንድነው? አንዳንድ ሰዎች ሃይማኖትንና ባህልን ለያይተው ሲተረጉሙ ይስተዋላል፡፡ አንዳንዶች ሃይማኖትን በባህል ስር ይከቱታል፡፡ አንድ ሰው ኦሮሞ ነው እንበል፡፡ ሃይማኖቱ ደግሞ ክርስትና ከሆነ፣ እንዳደገበት እንደ ኦሮሞ ማህበረሰብ ይኖራል፣ እንደ ክርስትያኖች ደግሞ ቸርች ሄዶ ያመልካል፡፡ እውነቱ ግን ያ አይደለም፡፡ ሲጀመር አምልኮ ማለት ቸርች ሄዶ መዘመር ወይም ቸርች መሄድ ማለት ሳይሆን በህይወት እግዚአብሔርን ማምለክ ማለት ነው፡፡ የክርስትና ሃይማኖት ለምሳሌ ከሞት በኋላ ስለሚኖረን ህይወት ይነግረናል፡፡ የእግዚአብሔር መንግስት አለ፣ ገሃነመ እሳት አለ፡፡ መንግስተ ሰማያት ለመግባትና ከገሃነመ እሳት መከራና ስቃይ ለመትረፍ፣ ሃይማኖታችን፣ በምድር ላይ እንዴት መኖር እንዳለብን ይነግረናል፡፡ ባህል ደግሞ ሰዎች በምድር ላይ ሲኖሩ የሚኖሩቸው ደግም መልካምም ይሁን ክፉ በማህበረሰቡ ተቀባይነት ያገኘና የተለመደ ልምድ ነው፡፡ አንድ እንግዳ ሰው አንድ ማህበረሰብ ውስጥ ገብቶ ህብረተሰቡ የማያውቀውን አንድ ነገር ቢያደርግ፣ "ባህላችን አይደለም" ይባላል፡፡ ሊወገዝና ሊገለልም ይችላል፡፡ ታዲያ ሃይማኖትኮ አንድ ህብረተሰብ ሊቀበለው ስለሚገባውና ሊያወግዘውም ጭምር ስለሚገባው ነገር ነው፡፡ ስለሁሉም ነገር፡፡ ሃይማኖታችንኮ የቀን ተቀን እያንዳንዱ እርምጃችንና ሀሳባችን ሳይቀር እንዴት መሆን እንዳለበት የሚያስተምረን አይደለም? ታዲያ ሃይማኖት ባህላችን ምንና እንዴት መሆን እንዳለበት የሚመክረንና የሚያሳየን ሲሆን ሃይማኖትና ባህል የተለያዩ ነገሮች፣ ወይም ሃይማኖት የባህል አንድ አካል ሳይሆን፣ ሃይማኖት፣ ሃይማኖታችንን የሚቃወሙ ባህሎችን ትተን የምንከተለው፣ ስለ ምድር ብቻ ሳይሆን ስለ ዘላለም የሆነ ህይወታችን፣ ከባህልም በላይ ነው፡፡ ባህል ስለምናደርገው ነገር ነው፣ ስለምንለብሰው፣ ስለምንበላው፣ ስለምናመልከውም ነው፡፡ ሃይማኖት ግን ስለ ሁሉም ነገር ነው፡፡ ባህል ስለማህበራዊ ህይወት ነው፡፡ ሃይማኖት ግን ስለማህበራዊ ህይወትም፣ ስለሰማይና ምድርም፣ ስለሚታየውም፣ ስለማይታየውም፣ ስለሁሉም ነገር የሆነ ነው፡፡ እደግመዋለሁ፣ ሃይማኖት ስለሁሉም ነገር ነው፡፡

ይሄ መጽሐፍ ስለ እውነት ነው፡፡ እውነቱም ክርስትና ነው፡፡ የእግዚአብሔር ቃል እውነት ነው፡፡ አወቅኩ አወቅኩ ብሎ እግዚአብሔር የለም የሚል ሰው እንኳን ሞኝነቱን ነው የሚያረጋግጠው፡፡ በመዝሙር 14፡1 "ሰነፍ በልቡ፡ አምላክ የለም ይላል፡፡" ተብሎ ተጽፎአልና፡፡ "The fool hath said in his heart, There is no God."

ስለዚህ ሃይማኖት ስለ ሁሉም ነገር ከሆነና ክርስትና ሃይማኖት የእውነት ሃይማኖት ከሆነ፣ ለብዙ ዘመናት ባህላችን ስላደረግናቸው፣ ስለ መማር፣ ትልቅ ደረጃ ስለ መድረስ፣ ዴሞክራሲና ዘመን አመጣሽ ስለሆኑ ብዙ ነገሮች ባይቃወምም ባይደግፍም፣ መጽሐፍ ቅዱሳችን የሚናገረው የሆነ ነገር መኖር አለበት፡፡ ሃይማኖት ስለሁሉም ነገር ነው ማለት፣ የምናደርገው ሁሉም ነገር እምነታችንን ይነካል፣ ከእምነታችን ጋር ይነካካል ማለት ነው፡፡
አንድ "በመንፈሳዊውም በአለማዊ" የሚባል ዘመን አመጣሽ አባባል አለ፡፡ በመንፈሳዊውም(በክርስትናም) በአለማዊውም መጠንከር አለብህ ይባላል፡፡ እውነታው ግን "በመንፈሳዊውም በአለማዊውም" የሚባል ነገር አለመኖሩ ነው፡፡ ያለው መንፈሳዊ ወይም አለማዊ የሚባል ነገር ብቻ

ነው፡፡ በመንፈሳዊውም በአለማዊውም ጠንክር የሚባል ነገር የሚኖረው፣ "በመልካሙም በክፉውም ጠንክር" የሚባል ነገር ሲኖር ብቻ ነው፡፡ ያለው መልካም፣ ወይም ክፉ ብቻ ነው፡፡ ወይ መንፈሳዊ፣ ወይ አለማዊ ብቻ ነው፡፡ ወይ መንፈሳዊ ወይ አለማዊ ትሆናለህ፡፡ ሁለት እጅ ስላለን ሁለት ጀሪካን መሸከም እንችል ይሆናል፣ ብዙ ነገር መቋቋም የሚችል አዕምሮ ስላለን አንድ ላይ ማስኬድ እችላለሁ እንል ይሆናል፡፡ እውነቱ ግን ይሄ ነው፡ እግዚአብሔር አትችሉም ብሎናል፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ደግሞ እውነት ነው፡፡ የማይቀበለው ወይም የሚቃወመው፣ ወይም ችላ የሚለው ቅጣቱም ይቀበላታል፡፡ የተቀየጠና ከዚህም ከዚያም የሆነ፣ ከመልካሙም ከክፉውም፣ ከመንፈሳዊውም ከአለማዊውም የሆነ ህይወት ታዲያ በቆሸሸና በሚሸት ሰውነት ላይ ሽቶ እንደመነስነስ ነው፡፡ ይቀረናል፡፡ ዞሮ ዞሮ አለማዊ ነው፡፡ የእኔ ወይም የማንም ሰው ውሸታም ምላስ ሳይሆን እውነተኛውና ቅዱሱ የእግዚአብሔር ቃል፣ ስለዚህ ነገር በትክክልና በማያሻማ መንገድ ያስረዳናል፡፡
ስለዚህ ሃይማኖት ስለ ሁሉም ነገር ከሆነ መጽሐፍ ቅዱሳችን ላይ፣ አሁን ባህላችን ስለ ሆኑ ብዙ ነገሮች የተጻፉ ጥቅሶች መኖር አለባቸው ማለት ነው፡፡ ሰዎች ሲወያዩ፣ ሲሰብኩ፣ ወይም ሲያነቡ አይታይምና፣ ያነበቡትም አላስተዋሉትምና ነው እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳችንማ የጎደለው ምን ነገር አለ?

በዘመናችን የተነሱ ብዙ አለማቀፍና ሀገር አቀፍ፣ እንዲሁም በከተሞች በየሰው ቤቱ ትንቢት የሚናገሩ፣ አጋንንት የሚያስወጡ፣ ነቢያቶች አሉን፡፡ በነዚህ ነቢያት ላይ የተለያዩ ሀሳቦች ይነሳሉ፡፡ እነዚህን ነብያቶች የእግዚአብሔር በረከቶች ናቸው፣ በመጽሐፍ ቅዱሳችን በመዝሙር 68፡31 ላይ "ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋች" ተብሎ የተጻፈው ትንቢት እየተፈጸመ ነው ብለው የሚያምኑ ሰዎች እንዳሉ፣ የሚጠራጠሩ፣ ይሄ ነው ማለት የከበዳቸውና ግራ የተጋቡ፣ ደግሞ "ከተፈወስኩና ትንቢት ከተነገረኝ እኔ ምናገባኝ" የሚሉ፣ እናም ፈጽመው የሚቃወሟቸውም የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች አሉ፡፡ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ያልሆኑ ብዙ ሰዎች ደግሞ የሚነገረውን ትንቢት፣ ፈውስና ምስክርነት እያዩ ወደ እምነቱ እየፈለሱ ነው፡፡ ብዙዎችም በነዚሁ በነቢያቶቻችን ምክንያት ለእምነቱ ያላቸውን ጥላቻ አጠናክረዋል፡፡ ድራማ ነው ብለው የሚያስቡ ሰዎች ሳይረሱ፡፡ እኔ የነዚህ ነቢያት ጉዳይ ያሳስበኛል፡፡ በነዚህ ሰዎች ምክንያት በሀገራችን ብዙ ሰው ከእግዚአብሔር እየራቀ ነው፡፡ እነኚህን ሰዎች በአጭሩ ካልተቀጩ መዘዙ የከፋ ነው የሚሆነው፡፡ አዎ ክርስቶስ ሀሰተኞች ነቢያቶች ያላቸው እኚሁ ናቸው፡፡ ከፍሬያቸው ትለዩአቸዋላችሁ ብሎናል፣ ፍሬያቸውን ማየት ነው፡፡ ፈውሳቸው፣ ይሄን ያህል ገንዘብ..አቸውና ሌላም ስጋዊ ችግሮቻችንን ሊቀርፉልን የሚችሉ ጥቅማጥቅማቸው እስካላታለለን፣ የእነሱን ሀሰተኛነት ለማወቅ ነቢይ መሆን አያስፈልግም፡፡ ለሚናገሩት ጆሮ፣ ለሚሰሩት አይንና መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ እንጂ፡፡ እኔም እንደ አንድ መአት ችግሮች እንዳሉባቸው፣ በነሱ ቸርቾች ውስጥ ቤት አጣበው ከታጨቁና ፈውስን ከሚጠባበቁ ሰዎች እንደ አንዱ ራሴን ሳየው ለብዙዎች እንደሚያረጉት ትንቢት ቢነግሩኝ በጣም ደስ ይለኛል፡፡ በነዚህ ሰዎች ምክንያት የሚጠፋውን የነፍስ ብዛት ሳስበው ግን፣ ያብረከርከኛል፡፡

የዘመናችን ነቢያትና አስተማሪዎች

እግዚአብሔር በነቢያቶች በኩል ታላላቅ ድንቅና ተአምራቶችን መስራቱ በመጽሐፍ ቅዱሳችን ላይ በተደጋጋሚ ተጽፎ የተቀመጠልን እውነታ ነው፡፡

በዚህ በመጨረሻው ዘመን ነቢያት መምጣት የጀመሩት በአፍሪካ አይደለም፡፡ በአሜሪካና በአውሮፓ፣ በሌላውም አለም በተለይ ከ19ኛው ክ.ዘ. ጀምሮ፣ ምድሪቱን ሲያጥለቀልቁ፣ ይኸው ዛሬም አሉ፡፡ እነዚህ ነቢያትም በፍጹም ክርስቶስም ሆነ ጳውሎስ ካስተማሩን የቤተ-ክርስትያን ስርአት ወጣ ያለ መዋቅር፣ ስርአትና ትምህርት ይዘው ብቅ አሉ፡፡ እነኝህ ነቢያት ከእግዚአብሔር ናቸው ብለን እንዳንቀበል፣ ብዙ ድንቃድንቅና ተአምራትን የሚያደርጉበት፣ የሚፈውሱበትና ትንቢት የሚናገሩበት ሃይል ሲሰጣቸውና ብዙ ሚሊየኖች ሲከተሏቸው፣ አንዳቸውም የህዝቡን ከእግዚአብሔር ጋር መለያየት አፋጠኑት እንጂ መንጋውን ለእግዚአብሔር ፈቃድ በሚገዛበት መንገድ ላይ አላስኬዱትም፡፡ በልተው፣ ጠጥተው፣ ዝናቸው በአለም ላይ ናኝቶ፣ ህዝቡን ወደ ገሃነም መርተው አለፉ፡፡ ሲጀመር ቃሉን የምንሰማ ከሆነ እነዚህን ነቢያት ስናይ ቀይ ማብራት እንጂ ስለ እግዚአብሔር በረከት ማሰብ አለማስተዋል ነው፡፡ በሁሉም ሪቫይቫል እያሉ በእግዚአብሔር ስም አሳሳች መንፈስ ባናፈሱበት ሀገራት ሁሉ የሀገራቱን ውድቀት አሰመሩ እንጂ ምንም የፈየዱበትም ሆነ እንደ ጉራቸውና እንደሚከተላቸው ህዝብ ብዛት ትውልድን ወደ እውነት የመሩበት ሀገር እንደሌለ የእግዚአብሔር ቃልና ታሪክ ምስክር ናቸው፡፡ የነሱ ስራ አለማዊነትን ማጽደቅ ነው፡፡ ቸርች መንፈስን ለማነጽ ሲኬድ እንዳልነበረ ሰው ለገንዘብና ለፈውስ፣ ብቻ ይሄዳል፡፡ ስለ መንፈሳዊነት ይረሳል፡፡ ተአምራትና ድንቃድንቆቹ እግዚአብሔር የተገለጠ ያስመስላሉ፡፡ ከቃሉ አንበቦ ገንዘብን መውደዱ ጥፋት ሲመስለው የነበረ ሰው ፓስተሩ ስለ ገንዘብ ሲሰብክ እግዚአብሔር ባለጠጋ እንድሆን ይፈልጋል ይላል፡፡ አዲስ የተሸቃቀጠ ወንጌል፡፡ ዛሬም የጥፋትና የአመጻ ማማ ላይ እያሉ፣ እግዚአብሔር ባለጠጋ እንደሚያደርጋቸው ይነግሯቸዋል፡፡ ዛሬም እንደሚፈወሱ ይነግሯቸዋል፣ ዛሬም ብዙ መልካም ነገር ይነግሯቸዋል፡፡ በጥፋት መንገድ ላይ የነበረ ህዝብ፣ በእነዚህ አታላይ ሰዎች፣ ተጠራርጎ ይጠፋል፡፡

ይሄን መጽሐፍ መጻፍ ከመጀመሬ ከአመት በፊት፣ እኚህ የዘመናችን ነቢያቶች ከእግዚአብሔር ናቸው ወይስ አይደሉም ብዬ ስወዛገብ አንድ ራሴን የምጠይቀው ጥያቄ ነበረ፡፡ እግዚአብሔር እነኚህን ነብያት ለምን አስነሳ? የእግዚአብሔር አላማ ምንድነው? ነብያቶቹ ይፈውሳሉ፣

ሚሊዮነር ያደርጋሉ፣ ወደ አሜሪካ ስለሚሄድ ሰው፣ ኢትዮጵያ በጥቂት አመታት ውስጥ እንደምታድግ ይተነብያሉ፣ ኢጋንንት ያስወጣሉ፣ አንድ ተማሪ ጥሩ ውጤት አምጥቶ ጥሩ ስራ እንደሚያገኝ… እግዚአብሔር ለዚህ ነው ያስነሳቸው? ለህዝቡ ምን ለማሳየት? አዎ ክርስቶስ ትንቢት ተናግሯል፡፡ ስለእውነተኞቹ ሐዋርያት ክርስቶስ ማረጋገጫ እንደሰጠን ስለኛ ዘመን ሐዋርያትም እንዲያውም በጣም በተደጋጋሚ ትንቢት ተናገሯል፡፡ እንደዚህ ሲል፡

ማቴ. 24፡24፡- ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉና፣ ቢቻላቸውስ የተመረጡት እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ፡፡

ሉቃ. 6፡26፡- ሰዎች ሁሉ መልካም ሲናገሩላችሁ፣ ወዮላችሁ፣ አባቶቻቸው ለሐሰተኞች ነቢያት እንዲሁ ያደርጉላቸው ነበርና፡፡

ማለትም ሐሰተኞች ነቢያትም እንደ መልካም ነገር በልጅነታቸው በሌላ ሐሰተኛ ነቢያት ነቢያት እንደሚሆኑ፣ ሌላም መልካም መልካም ነገር ሲነገራቸው ነበር ማለት ነው፡፡

ማቴ. 7፡15-23፡- የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ በውስጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኩላዎች ከሆኑ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ፡፡ ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ፡፡ የእሾህ ወይን፣ ከኩርንችትስ በለስ ይለቀማልን? እንዲሁ መልካም ዛፍ ሁሉ መልካም ፍሬ ያደርጋል፣ ክፉም ዛፍ ክፉ ፍሬ ያደርጋል፡፡ መልካም ዛፍ ክፉ ፍሬ ማፍራት፣ ወይም ክፉ ዛፍ መልካም ፍሬ ማፍራት አይቻለውም፡፡ መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ ሁሉ ይቆረጣል፣ ወደ እሳትም ይጣላል፡፡ ስለዚህ ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ፡፡ በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፣ ጌታ ሆይ፣ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም፡፡ በዚያ ቀን ብዙዎች፡ ጌታ ሆይ፣ ጌታ ሆይ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን፣ በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን፣ በስምህስ ብዙ ተአምራትን አላደረግንምን? ይሉኛል፡፡ የዚያን ጊዜም፡ ከቶ አላውቃችሁም፣ እናንተ ዓመፀኞች፣ ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ፡፡

ጥንት የኖሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ነቢያትና ሐዋርያትም አሁን ስለሚመጡት ነቢያት ትንቢት ተናግረዋል፡፡

በሐዋርያት በኩል፡

2ጴጥ. 2፡1-3፡- ነገር ግን ሐሰተኞች ነቢያት ደግሞ በህዝቡ መካከል ነበሩ፡፡ እንዲሁም በመካከላችሁ ደግሞ ሐሰተኞች አስተማሪዎች ይሆናሉ፡፡ እነርሱም የዋጃቸውን ጌታ እንኳን ክደው የሚፈጥንን ጥፋት በራሳቸው ላይ እየሳቡ የሚያጠፋ ኑፋቄን አሾልከው ያገባሉ፡፡ ብዙዎችም በመዳራታቸው ይከተሏቸዋል፣ *በእነርሱም ጠንቅ የእውነት መንገድ ይሰደባል፡፡* ***ገንዘብንም በመመኘት*** *በተፈጠረ ነገር ይረቡባችኋል፤* ፍርዳቸውም ከጥንት ጀምሮ አይዘገይም፣ ጥፋታቸውም አያንቀላፋም፡፡

1 ዮሐ. 4፡1፡- ወዳጆች ሆይ መንፈስን ሁሉ አትመኑ፣ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደ ሆነ መርምሩ፣ ብዙዎች ሐሰተኞች ነቢያቶች ወደ ዓለም ወጥተዋልና፡፡

2ጢሞቴዎስ 4፡3፡- ሕይወት የሚገኝበትን ትምህርት የማይታገሱበት ዘመን ይመጣልና፤ ነገር ግን ጆሮቻቸውን የሚያሳክክ ስለ ሆነ እንደ ገዛ ምኞታቸው አስተማሪዎችን ያከማቻሉ፡፡

2 ተሰሎንቄ 2፡9-10፡- ይድኑ ዘንድ የእውነትን ፍቅር ስላልተቀበሉ ለሚጠፉ፣ የእርሱ መምጣት በተአምራት ሁሉና በምልክቶች በሐሰተኞች ድንቆችም በዓመጽም መታለል ሁሉ እንደ ሰይጣን አሰራር ነው፡፡

2 ጢሞቴዎስ 3፡13-14፡- ነገር ግን ክፉዎች ሰዎችና አታላዮች፣እያሳቱና እየሳቱ፣ በክፋት እየባሱ ይሄዳሉ፡፡ አንተ ግን በተማርህበትና በተረዳህበት ነገር ጸንተህ ኑር፣ ከማን እንደ ተማርኸው ታውቃለህና፡፡

በብሉይ ኪዳን ደግሞ፡

ኤርሚ. 23(ሙሉው)፡16፡- የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡ ትንቢት የሚናገሯችሁን የነቢያትን ቃል አትስሙ፡፡ *ከንቱነትን ያስተምሯችኋል፡፡* ***ከእግዚአብሔር ቃል ሳይሆን*** *ከልባቸው የወጣውን ራእይ ይናገራሉ፡፡*

ሕዝቅ. 13፡9-10፡- እጄም ከንቱ ራእይ በሚያዩ፣ በውሸትም በሚያምዋርቱ ነቢያት ላይ ትሆናለች፡፡ እነርሱም በሕዝቤ ማህበር ውስጥ አይገኙም፡፡ በእስራኤልም ቤት መጽሐፍ አይጻፉም፡፡ ወደ እስራኤልም ምድር አይገቡም፡፡ እኔም ጌታ እግዚአብሔር እንደ ሆንኩ ያውቃሉ፡፡ **ሰላም ሳይኖር ሰላም እያሉ ህዝቤን አታልለዋልና፡፡ አንዱም ሰው ቅጥር ሲሰራ እነሆ ገለባ በሌለበት ጭቃ ይመርጉታልና፡፡**

ታዲያ ክርስቶስ በዚህ በመጨረሻው ዘመን ሐሰተኞች ነቢያቶች እንደሚነሱ እንጂ የሐዋሪያት ትንሳኤ እንደሚኖር አይደለም የሚናገረን፡፡ የሐዋሪያትን ትምህርት የሚቃወምና ሰዎችን ከእውነቱ የሚያርቅ ትምህርት እንደ ማስተማራቸውማ ሐዋርያ ብለው ራሳቸውን ባልሰየሙና ስለ እውነት በተሰዉት በነጳውሎስ ላይ ባልተሳለቁ ነበር፡፡

የነቢያቶቻችንን እውነተኛነት ከምንመረምርባቸው መንገዶች:

1. የነቢዩ ህይወት በቅድስና መገዛትን ይገልጻል? ኤርሚያስ 23፡13-15
2. የነቢዩ ትምህርት የመንፈስን ፍሬ(ገላ. 5፡22) ያመርታል? ማቴ. 7፡15-16፣ 18
3. ነቢዩ በጎ በጎ መልዕክቶችን ብቻ ያስተላልፋል ወይ? ኤርሚ. 23፡16-17(አንባቢ ሆይ ምዕራፍን 23 ሙሉውን እንድታነብ አበረታታሃለሁ)፡፡ 17 ለሚንቁኝ ሁል ጊዜ፡ እግዚአብሔር፡ ሰላም ይሆንላችኋል ብሎአል ይላሉ፡፡ በልቡም እልከኝነት ለሚሄድ ሁሉ፡ ክፉ ነገር አያገኛችሁም ይላሉ፡፡ (ለሚንቁኝ ማለት ትእዛዜን ለማይፈጽሙ ማለት ነው፡፡) ተው፣ እንመለስ እግዚአብሔር አዝኖብናል በማለት ሕዝባቸውን ማስጠንቀቅ በሚገባቸው ጊዜ፣ እግዚአብሔር ከናንተ ጋር ነው እያሉ፣ ህዝቡን በተአምራትና በድንቃድንቅ አሳስተው፣ ከውድቀት፣ ወደ ዝቅጠት ይመራሉ፡፡
4. ነቢዩ ገንዘብ አሳዳጅ ነው ወይ? ኤርሚ. 8፡10-12
5. የመጨሻውና ለመለየት ቀላሉ መንገድ ደግሞ፣ የነቢዩ መልዕክት የእግዚአብሔርን ቃል ፈተና ያልፋል ወይ?
   ገላ. 1፡7-10፡- **እርሱ ግን ሌላ ወንጌል አይደለም፡፡ የሚያናውጡአችሁ የክርስቶስንም ወንጌል ሊያጣምሙ የሚወዱ አንዳንዶች አሉ እንጂ፡፡ ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ፣ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ፣ የተረገመ ይሁን፡፡ አስቀድመን እንዳልን እንዲሁ አሁን *ሁለተኛ እላለሁ፣* ከተቀበላችሁት የተለየውን ማንም ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን፡፡ ሰውን ወይስ እግዚአብሔርን አሁን እሺ አሰኛለሁን? ወይስ ሰውን ደስ ላሰኝ እፈልጋለሁን? አሁን ሰውን ደስ ባሰኝ የክርስቶስ ባሪያ ባልሆንሁም፡፡**

የዘመናችን ነቢያት የክፉ ትውልድ ጭማቂ ጠብታ ናቸው፡፡ የክፉ ትውልድ ፍሬ ናቸው፡፡ የክፉት ፍሬ ናቸው፡፡ ጀርባውን የሰጠን ትውልድ ፊቱን ወዳዞረበት የሚመሩት መሪዎች ናቸው፡፡ 2 ተሰሎንቄ 2፡9-12፡፡

ብዙ ሰዎች ሀገራችን ለምዕራባውያን ተጽዕኖ እጅ እየሰጠች መሆኑ ያሰጋቸዋል፡፡ አንዳንዱ ባህላችንን፣ አለባበሳችንን፣ ቋንቋችንን እየረሳን መሆኑ ያብከነክነዋል፡፡ አንዳንዱ የሃይመኖት ጉዳይ ያሰጋዋል፡፡ ሁሉም በሃይማኖትና በባህል ምዕራባውያን ጥሩ እንዳልሆኑ ሳይሆን መጥፎ እንደሆኑ ያውቀዋል፡፡ በሌላ በኩል እድገታቸውን የማይመኝ፣ ስልጣኔያቸውን የማይጎመጅ፣ ዴሞክራሲያቸውን የማይፈልግ፣ ኢትዮጵያ እንደነሱ ሀብታምና ሀያል ሀገር እንድትሆን የማይሻ ደግሞ የለም፡፡ ታዲያ ጥያቄው ገንዘባቸውን፣ መንግስታቸወን፣ ብዙ ነገራቸውን ተመኝተንና እንበልና አግኝተን፣ ባህላዊ ውድቀታቸውን መከላከል እንችላለን ወይ? የሚለው ነው፡፡ ሌላኛው ጥያቄ ደግሞ ባህላዊ ውድቀቱን መከላከል ቢቻልም ባይቻልም፣ የሚያሳስበንን ያህል ባህላችንንም ሆነ ሃይማኖታችንን ለመከላከል ምን እየሰራን ነው? የሚል ነው፡፡ የሁለተኛው ጥያቄ መልስ ግልጽና አጭር ነው፡፡ መልሱም "ምንም" ነው፡፡ እኔ ባህል ምኔም አይደለም፡፡ ኢትዮጵያዊነትን መካድ ለእምነት ይጠቅማል ብባል፣ ኢትዮጵያዊነቴን አሽቀንጥሬ ለመጣል አላቅማማም፡፡ ሃይማኖተን የማይነካ እስከ ሆነ ድረስ ነገ ጠዋት ስነሳ ሀገሬው በሙሉ እንግሊዘኛ ማውራት ቢጀምር ምንም አይመስለኝም፡፡ በአንጻሩ አማርኛ ወይም ኦሮምኛ ማውራት እምነትን የሚጎዳ ቢሆን ባህሌ ነው፣ ቋንቋዬ ብዬ ማውራት ላለማቆም አሻፈረኝ አልልም፡፡ ሃይማኖትና ባህል ጥብቅ ቁርኝት ኖራቸውና እንጂ ባህሌ ምኔም አይደለም፡፡ ኢትዮጵያዊነቴ ወይም ኦሮሞነቴ መንግስተ-ሰማያት አያስገባኝም ወይም ከገሃነመ እሳት አያድነኝም፡፡ በዚህች አለም ያለኝ እድሜ ላይም አንድ ሰከንድ አይጨምርልኝም፡፡ ታዲያ፣ ስለ ሃይማኖት ሳስብ ነው የሚያንገበግበኝ፡፡

የዚህ ዘመን ክርስትያን እንደገና ሊያጤናቸውና ሊያስተውላቸው ከሚገባው እውነትና ህያው፣ ህይወት ከሆነው የእግዚአብሔር ቃል ጥቅሶች መካከል፡

Ija koo banii siinan hubadhaa,
Gurra koo banii siin dhaggeeffadhaa.
Yoo arguu baatee iji koo gooftaa,
Maal waa'ee baasaa iyyuun koo?

Yoo arguu baatee keessi koo Iyyesuus
Maal waa'ee baasaa iji koo?

አይኔን ከፈተው፣ እንድመለከት፣
ጆሮዬን ከፈት እንዳዳምጥህ፣
ካልተመለከትኩኝ ጌታዬ፣
ምን ዋጋ አለው ማየቴ?
ውስጤ ካላየ ኢየሱሴ፣
ምን ዋጋ አላቸው አይኖቼ

በክርስትና ስር፣ የመጽሐፍ ቅዱስን ጥቅሶች በተለያዩ መንገዶች ከመተርጎም የተነሳ ብዙ ሃይማኖቶች አሉን፡፡ ኦርቶዶክስ፣ ካቶሊክና ፕሮቴስታንትም ከነዚህ መካከል ናቸው፡፡
ኦርቶዶክስና ጴንጤ ሲከራከሩ ሃይማኖታቸውን ወግነው ነው፡፡ ማለትም ሃይማኖትህ ምንድነው ሲባል ፕሮቴስታንት ወይም ኦርቶዶክስ እንደሚባለው፣ ሃይመኖትን የእምነት ተቋም መገለጫ አርገን ስለተቀበልነው፡፡ አንድ ፕሮቴስታንት በአንዳንድ በኦርቶዶክስ ዶክትሪኖች ይሳባል፣ ኦርቶዶክሱም እንዲሁ፡፡ ሁለት ፕሮቴስታንቶች በአንድ ዶክትሪን ላይ የሚኖራቸው እምነት ወይም አቀባበል ደረጃ የተለያየ ሊሆን መቻሉ ግልጽ ነው፡፡ ልዩነታችን ከአረዳዳችን መለያየት የመነጨ ነው፡፡ ነገር ግን ከአንድ መጽሐፍ እንደሚያነብ፣ ምንም የማንለያይባቸው በግልጽና በተደጋጋሚ የተጻፉልን ክርስትያን የሚያስብሉን ምንም ጥርጥር የሌለን የክርስትናችን መሰረቶችና የክርስትናችን መሰረት ሊሆኑ የሚገባቸው ነጥቦች ደግሞ ይኖሩናል፣ ሊኖሩን ይገባል ፡፡ ታዲያ አንድ ሰው ከፕሮቴስታንትነቱ ወይም ከኦርቶዶክስነቱ የበለጠ በክርስትናው አያምንምን? ያም ማለት ሁላችንም ከማሪያም አማላጅነት ይልቅ በክርስቶስ ኢየሱስ አዳኝነት እናምናለን እርግጠኞች ነን፡፡
በእግዚአብሔር መንገድ ላይ መሄድና ቃሉን መረዳት ሃይማኖትን ያጠናክራል፡፡ እምነታችን ሲያድግም ሃይማኖት ይጠነክራል፡፡ ስለዚህ ሃይማኖት፣ የእምነት ተቋማት ስለሚለያዩባቸው አከራካሪ ዶክትሪኖች አይደለም፡፡ ሃይማኖት ሐዋርያት ያወረሱን ክርክርና ውዝግብ የሌለበት ክርስትና ነው፡፡ ችግሩ፣ በግልጽ የክርስትና ሃይማኖት ዋና መመሪያ የሆኑ ነጥቦችን የማንቀበል፣ ሆን ብለንም ሆነ በሌላ ሀሳብ(ተቀባይነት ለማግኘት)፣ ልናጣምም የምንሞክር፣ የምንሸሽ፣ የምናጣጥል እንደሆነ ነው፡፡ እንደዚያ ከሆነ የትኛውንም የእምነት ተቋም እንከተል፣ ሃይማኖትን የማጥፋት ዘመቻ ላይ ነን ማለት ነው፡፡

ብዙ ኦርቶዶክሶች ከፕሮቴስታንቶች ጋር፣ ፕሮቴስታንት ከካቶሊክ ጋር የሚከራከሩባቸው ርዕሶች አሉ፡፡
የመጽሐፍት ብዛት፡ የመጽሐፍት ብዛት ላይ እንከራከራለን፡፡ ነገር ግን በምንስማማባቸው፣ ሁላችንም በተቀበልናቸው መጽሐፍትስ እየኖርን ነው እንዴ? በተቀበልነው ሳንኖር ሌላውን ለመሻር ምን አፍ አካፈተን?
የመላዕክት አምልኮ፡ ስለ መላዕክት አምልኮ እንከራከራለን፣ የምንስማማበትን፣ ሁላችንም አምልኮ ይገባዋል ብለን የምናምነውን ክርስቶስን፣ እንደሚገባን እያመለክነው ነው እንዴ? የተስማማንበተን ደግሞ እያከበርነው ነው? እንደ ፈቃዱ እየኖርን ነው?
ሁሉም ስለ ቅርንጫፉ ሲያወራ፣ ሲከራከር የሚውለው፣ መሰረቱ ስለተበላ ነው፡፡ ሁሉም በዶክትሪኖቹ ልዩነቶች ላይ ያተኮረው፣ ህይወት የሚገኝበትን ቃል ስለካደ ነው፡፡ ሁሉም ስለ ቤተ ክርስትያን የተቆረቆረ ይመስላል፡፡ ሁሉም ግን በእግዚአብሔር አይኖች ክርስትያን ስለመሆኑ ይጠራጠር፡፡
እየራቅነው ካለነውና ልንኖርበት ይገባን ከነበረው መሰረታዊ እውነት ይልቅ በተከፋፈልንባቸው መሰረታዊ ባልሆኑ ጉዳዮች ላይ አዕምሮአችንን ሰቅለን ሃይማኖትን ወደ መካድ እየመራን ያለው የዲያብሎስ አሰራር በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የፈረሰ ይሁን፡፡

ሉተር እንዳለው የኢየሱስ ክርስቶስ ለሃጢአታችን መሞትና ለጽድቃችን ከሞት መነሳት የመመሪያዎቻችን ሁሉ መመሪያ ነው፡፡ በዚህ ዘመን ግን ገንዘብ መሰብሰብ፣ ሀብታም መሆን፣ አዋቂ የተማረ ሰው መሆን በቤተ ክርስትያንም ሆነ በተለያዩ አጋጣሚዎች ከክርስቶስ በላይ የሚሰበክና አማኞች ዋጋ ምንሰጥበት ጉዳይ ሆኗል፡፡ ህይወታችንን በሙሉ ወደ ፊት ስለምንኖረው ህይወት እያለምን፣ ስለምንደርስበት ደረጃና ስለምንይዘው ዲግሪ እያቀድን ስለመኖራችን ስናገር ራሴን ብቻ እየወከልኩ እንዳልሆነ እርግጠኛ ነኝ፡፡ ሃይማኖት ቸርች ከመሄድም በላይ ስለ ህይወታችንና ስለሁሉም ነገር እንደመሆኑ ስለነኘህ ባህላችን ስለሆኑ ነገሮች መቼም የእግዚአብሔር ቃል በርግጠኝነት የሚለው ነገር ይኖራል፡፡

"ወንጌላችን የተከደነ ቢሆን እንኳ የተከደነባቸው ለሚጠፉ ነው፡፡ ለእነርሱም የእግዚአብሔር ምሳሌ የሆነ የክርስቶስ የክብሩ ወንጌል ብርሃን እንዳያበራላቸው፣ የዚህ ዓለም አምላክ የማያምኑትን አሳብ አሳወረ፡፡" 2 ቆሮንቶስ 4፡3-4፡፡

እውነቱ ስለ ገንዘብ

ደሃው ከሞተ ሃብታሙም ከሞተ

ደሃዋ ደስ ካላት፣ ሃብታሟ ካዘነች፣
ህይወት ምንድነች?
የሰው ሁሉ ህልሙ ሀብት ማካበት ነው፣
ደሃው ግን ካብታሙ ይልቅ ደስተኛ ነው፡፡
ሂሳብ ተምሬአለሁ፣
አንድ ሲደመር አንድ መልሱ ሁለት ነው፡፡
ግራ የገባኝን የሀብትን ሚስጥር ግን
ሚያስረዳኝ መምህር ከቶ አላገኘሁም
እባክህ አስረዳኝ
እባክህ ጌታ ሆይ፡፡

"የኢትዮጵያ ተስፋ እግዚአብሔር አምላክ እንጂ ገንዘብ አይደለም፡፡"

በዘመናችን በክርስትያኖች ዘንድ ገንዘብ እንደ እግዚአብሔር በረከት የሚቆጠርበት፣ ሰው፣ መኪና ስለሌለው፣ የሚያምር ቤት ስለሌለው፣ የሚበላ፣ የሚለብሰውን ሳያጣ እግዚአብሔርን የሚያማርርበት ጊዜ ላይ ደርሰናል፡፡ በ2 ቆሮ. 2፡17 ላይ ብዙዎች የእግዚአብሔርን ቃል ቀላቅለው እንደሚሸቃቅጡት ተጠቅሷል፡፡ ሰባኪዎችም፣ ነቢያትም፣ ማንም ቢሆን እንደየፍላጎቱ የእግዚአብሔርን ቃል በሀሰት እየተረጎመ መንጋውን ሊያስትና ቃሉን ሊደብቅ፣ የሀሰት ትምህርት ሊያስተምር ይችላል፡፡ ሲሰብክ ቃሉን ሊያጥፍ እንጂ ግን፣ ቃሉን ሊያጠፋው አይችልም፡፡
ሐሰተኞች ነቢያት እንደነጋዴ የሰዎችን ትኩረትና ገንዘብ ለመሳብ፣ እንዳሻቸው ለመሸቃቀጥ በመጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ለተጻፉ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በለምድ ከተሸፈነ አላማቸው ጋር የሚሄድ ትርጉም ሲሰጡና ሲያጭበረብሩ ታዝበናል፡፡ የፈለጉትን ቢሉና መንጋውን ቢያስቱም ግን የእግዚአብሔር ቃል እውነት ነው፣ ይቀጡበታል፡፡

በመጽሐፍ ቅዱሳችን ገንዘብ በጣም እግዚአብሔር ትኩረት ከሚሰጥባቸው ነገሮች አንዱ ነው፡፡ የገንዘብ መጠናችን፣ ግላዊ፣ ቤተሰባዊ፣ ማህበራዊ፣ ሀገራዊ፣ ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ አስተሳሰባችን ላይ፣ ሁለንተናዊ ህይወታችንን ምን ያህል እንደሚቀርጸው ስናስብ ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ገንዘብ በስፋትና በግልጽ የመጻፉን ምክንያት እንረዳለን፡፡ ከነዚህም ጥቅሶች መካከል፡

ማቴ. 19፡ 21-24፡-
ኢየሱስም፡ ፍጹም ልትሆን ብትወድ፣ ሂድና ያለህን ሸጠህ ለድሆች ስጥ፣ መዝገብም በሰማያት ታገኛለህ፣ መጥተህም ተከተለኝ አለው፡፡ ጎበዙም ይህን ቃል በሰማ ጊዜ ብዙ ንብረት ነበረውና እያዘነ ሄደ፡፡ ኢየሱስም ለደቀ መዛሙርቱ፡ እውነት እላችኋለሁ፣ ለባለጠጋ ወደ መንግስተ ሰማያት መግባት ጭንቅ ነው፡፡ *ዳግመኛም እላችኋለሁ፣* ባለጠጋ ወደ እግዚአብሔር መንግስት ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢገባ ይቀላል አለ፡፡

ማር. 4፡18-19፡-
በእሾህም የተዘሩት ሌሎች ናቸው፣ ቃሉን የሰሙት እነዚህ ናቸው፣ የዚህን አለም አሳብና የባለጠግነት መታለል፣ የሌላውም ነገር ምኞት ገብተው ቃሉን ያንቃሉ፣ የማያፈራም ይሆናል፡፡

ምሳ. 23፡3-5፡-
ጣፋጩ መብል አይመርህ፡፡፡ የሐሰት እንጀራ ነውና፡፡ ባለጠጋ ለመሆን አትድከም፤ የገዛ ራስህን ማስተዋል ተው፡፡ በእርሱ ላይ ዓይንህን ብታዘወትርበት ይጠፋል፡፡ ባለጠግነት ወደ ሰማይ እንደሚበርር እንደ ንስር ለራሱ ክንፍ ያበጃልና፡፡

መዝሙር 37፡16፡- ለጻድቅ ያለው ጥቂት ከብዙ ከኃጢአተኞች ሀብት ይበልጣል፡፡

መዝሙር 37፡21፡- ኃጢአተኛ ይበደራል፣ አይከፍልምም፤ ጻድቅ ግን ይራራል፣ ይሰጣልም፡፡

ያዕ. 5፡1-6፡-
አሁንም እናንተ ባለ ጠጎች፣ ስለሚደርስባችሁ ጭንቅ ዋይ ዋይ እያላችሁ አልቅሱ፡፡ ሀብታችሁ ተበላሽቶአል፣ ልብሳችሁም በብል ተበልቶአል፡፡ ወርቃችሁም ብራችሁም ዝጎአል፣ ዝገቱም ምስክር ይሆንባችኋል፣ ስጋችሁንም እንደ እሳት ይበላል፡፡ ለኋለኛው ቀን መዝገብን አዘጋጅታችኋል፡፡ እነሆ፣ እርሻችሁን ያጨዱት የሠራተኞች ደመወዝ በናንተ ተቀምቶ ይጮሃል፣ የአጫጆችም ድምጽ ወደ ጌታ ፀባኦት ጆሮ ገብቶአል፡፡ በምድር ላይ ተቀማጥላችኋል፣ በሴሰኝነትም ኖራችኋል፤ ለእርድ ቀን እንደሚያወፍር ልባችሁን አወፍራችኋል፡፡ ጻድቁን ኮንናችሁታል፣ ገድላችሁትማል፤ እናንተን አይቃወምም፡፡

መክ. 5፡10፡-
ብርን የሚወድ ሰው ብርን አይጠግብም፤ ባለጠግነትንም የሚወድ ሰው ትርፉን አይጠግብም፣ ይህም ደግሞ ከንቱ ነው፡፡

1 ዮሐ. 2፡15-17፡-
ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ፡፡ በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የስጋ ምኞትና የአይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት ከዓለም ስለ ሆነ እንጂ ከአባት ስላልሆነ፣ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም፡፡ ዓለሙም፣ ምኞቱም ያልፋሉ፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘላለም ይኖራል፡፡

ሉቃስ 16፡13-14፡-
ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው ባርያ ማንም የለም፡፡ ወይም አንዱን ይጠላልና ሁለተኛውንም ይወዳል፤ ወይም ወደ አንዱ ይጠጋል፣ ሁለተኛውንም ይንቃል፡፡ ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም፡፡ ገንዘብንም የሚወዱ ፈሪሳውያን ይህን ሰምተው ያፌዙበት ነበር፡፡

ማቴዎስ 6፡19-34፡-
ብልና ዝገት በሚያጠፉት ሌቦችም ቆፍረው በሚሠርቁት ዘንድ ለእናንተ በምድር ላይ መዝገብ አትሰብስቡ፡፡ ነገር ግን ብልም፣ ዝገትም፣ በማያጠፉት ሌቦችም ቆፍረው በማይሠርቁት ዘንድ ለእናንተ በሰማይ መዝገብ ሰብስቡ፡፡ መዝገብህ ባለበት ልብህ ደግሞ በዚያ ይሆናልና፡፡ የሰውነት መብራት ዓይን ናት፡፡ ዓይንህ እንግዲህ ጤናማ ብትሆን፣ ሰውነትህ ሁሉ ብሩህ ይሆናል፡፡ ዓይንህ ግን ታማሚ ብትሆን፣ ሰውነትህ ሁሉ የጨለመ ይሆናል፡፡ እንግዲህ በናንተ ያለው ብርሃን ጨለማ ከሆነ፣ ጨለማውስ እንዴት ይበረታ! ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው ማንም የለም፡፡ ወይም አንዱን ይጠላል፣ ሁለተኛውንም ይወዳል፡፡ ወይም ወደ አንዱ ይጠጋል፣ ሁለተኛውንም ይንቃል፡፡ ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም፡፡ ስለዚህ እላችኋለሁ፣ ስለ ነፍሳችሁ በምትበሉትና በምትጠጡት፣ ወይም ስለ ሰውነታችሁ በምትለብሱት አትጨነቁ፡፡ ነፍስ ከመብል፣ ሰውነትም ከልብስ አይበልጥምን? ወደ ሰማይ ወፎች ተመልከቱ፡፡ አይዘሩምም አያጭዱምም በጎተራም አይከቱም፣ የሰማዩ አባታችሁም ይመግባቸዋል፡፡ እናንተ ከነሱ አትበልጡምን? ከእናንተ ተጨንቆ በቁመቱ ላይ አንድ ክንድ መጨመር የሚችል ማን ነው? ስለ ልብስስ ስለ ምን ትጨነቃላችሁ? የሜዳ አበቦች እንዴት እንዲያድጉ ልብ አድርጋችሁ ተመልከቱ፡፡ አይደክሙም አይፈትሉምም፡፡ ነገር ግን እላችኋለሁ፣ ሰለሞንስ እንኳ በክብሩ ሁሉ ከነዚህ እንደ አንዱ አልለበሰም፡፡ እግዚአብሔር ግን ዛሬ ያለውን ነገም ወደ እቶን የሚጣለውን የሜዳን ሣር እንዲህ የሚያለብሰው ከሆነ፣ እናንተ እምነት የጎደላችሁ፣ እናንተማ ይልቁን እንዴት? እንግዲህ፡ ምን እንበላለን? ምንስ እንጠጣለን? ምንስ እንለብሳለን? ብላችሁ አትጨነቁ፡፡ ይህንስ ሁሉ አሕዛብ ይፈልጋሉ፡፡ ይህ ሁሉ እንዲያስፈልጋችሁ የሰማዩ አባታችሁ ያውቃልና፡፡ ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፣ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል፡፡ ነገ ለራሱ ይጨነቃልና ለነገ አትጨነቁ፡፡ ለቀኑ ክፋቱ ይበቃዋልና፡፡

ዕብራውያን 13፡5-7፡-
አካሄዳችሁ ገንዘብን ያለመውደድ ይሁን፣ ያላችሁም ይብቃችሁ፡፡ እርሱ ራሱ፡ አልለቅህም ከቶም አልተውህም ብሎአልና ስለዚህ በድፍረት፡ ጌታ ይረዳኛልና አልፈራም፣ ሰው ምን ያደርግልኛል? እንላለን፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል የተናገራችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ፣ የኑሮአቸውንም ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሉአቸው፡፡

1 ጢሞቴዎስ 6፡5-12፡-
...እንደነዚህ ካሉት ራቅ፡፡ ኑሮዬ ይበቃኛል ለሚለው ግን እግዚአብሔርን መምሰል እጅግ ማትረፊያ ነው፡፡ ወደ ዓለም ምንም እንኳ አላመጣንምና፣ አንዳችንም ልንወስድ አይቻለንም፡፡ ምግብና ልብስ ከኖረን ግን እርሱ ይበቃናል፡፡ **ዳሩ ግን ባለ ጠጎች ሊሆኑ የሚፈልጉ በጥፋትና በመፍረስ ሰዎችን በሚያሰጥምና በሚያስጎፍ በሚጎዳም በብዙ ምኞትና በፈተና በወጥመድም ይወድቃሉ፡፡ ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ስር ነውና፣ አንዳንዶችም ይህን ሲመኙ ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ሥቃይ ራሳቸውን ወጉ፡፡ አንተ ግን የእግዚአብሔር ሰው ሆይ ከዚህ ሽሽ** ጽድቅንና እግዚአብሔርን መምሰል እምነትንም ፍቅርንም መጽናትንም የዋህነትንም ተከታተል፡፡...

ኢዮብ 36፡19፡-
ባለጠግነትህ የኃይልህም ብርታት ሁሉ ያለ ችግር እንድትሆን ሊረዳህ ይችላልን?

ማቴዎስ 21፡12-13፡-
ኢየሱስም ወደ መቅደስ ገባና በመቅደስ የሚሸጡትንና የሚገዙትን ሁሉ አወጣ፣ የገንዘብ ለዋጮችንም ገበታዎች የርግብ ሻጮችንም ወንበሮች ገለበጠና፡ ቤቴ የጸሎት ቤት ትባላለች ተብሎ ተጽፎአል፣ እናንተ ግን የወንበዶች ዋሻ አደረጋችኋት አላቸው፡፡

ሉቃስ 12፡33፡-
ያላችሁን ሽጡ ምጽዋትም ስጡ፡፡ ሌባ በማይሰርቅበት ብልም በማያጠፋበት በሰማያት በማያልቅ መዝገብ የሚሆኑትን የማያረጁትንም ኮረጆዎች ለራሳችሁ አድርጉ፡፡

ሉቃስ 12፡15-34፡-
15 የሰው ህይወት በገንዘቡ ብዛት አይደለምና ተጠንቀቁ፣ ከመጎምጀትም ሁሉ ተጠበቁ አላቸው፡፡...19 ነፍሴንም አንቺ ነፍሴ ፣ ለብዙ ዘመን የሚቀር ብዙ በረከት አለሽ፡፡ ዕረፊ፣ ብዪ፣ ጠጪ፣ ደስ ይበልሽ እላታለሁ አለ፡፡ 20 እግዚአብሔር ግን፡ አንተ ሰነፍ፣ በዚች ሌሊት ነፍስህን ከአንተ ሊወስዱአት ይፈልጓታል፡፡ ይህስ የሰበሰብኸው ለማን ይሆናል? አለው፡፡ 21 ለራሱ ገንዘብ የሚያከማች፣ በእግዚአብሔር ዘንድም ባለ ጠጋ ያልሆነ እንዲህ ነው፡፡....

ያዕቆብ 2፡1-7፡-
ወንድሞቼ ሆይ፣ በክብር ጌታ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ያለውን እምነት ለሰው ፊት በማድላት አትያዙ፡፡ የወርቅ ቀለበት ያደረገና የጌጥ ልብስ የለበሰ ሰው ወደ ጉባኤአችሁ ቢገባ፣ እድፍ ልብስም የለበሰ ሰው ድሀ ሰው ደግሞ ቢገባ፣ የጌጥ ልብስም የለበሰውን ተመልክታችሁ፡ አንተስ በዚህ በመልካም ስፍራ ተቀመጥ ብትሉት፣ ድሀውንም፡ ወደዚያ ቁም ወይም ከእግሬ መረገጫ በታች ተቀመጥ ብትሉት፣ ራሳችሁን መለያየታችሁ አይደለምን? ክፉ አሳብ ያላቸውም ዳኞች መሆናችሁ አይደለምን? የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፣ ስሙ፤ **እግዚአብሔር በእምነት ባለጠጎች እንዲሆኑ ለሚወዱትም ተስፋ ስለ እርሱ የሰጣቸውን መንግሥት እንዲወርሱ የዚህን ዓለም ድሆች አልመረጠምን?** እናንተ ግን ድሆችን አዋረዳችሁ፡፡ ባለ ጠጎቹ የሚያስጨነቁአችሁ አይደሉምን? ወደ ፍርድ ቤትም የሚጎትቱአችሁ እነርሱ አይደሉምን? የተጠራችሁበትን መልካሙን ስም የሚሰድቡ እነርሱ አይደሉምን?...

ማቴዎስ 19፡25 የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ሰምተው እጅግ እንደተገረሙና “እንኪያስ ማን ሊድን ይችላል?” ብለው እንደጠየቁት ይናገራል፡፡ እነሱስ ያኔ የገንዘብ ክፋት ስላልገባቸው ነበር እንደዚያ ብለው የጠየቁት፡፡ እኛ ቃሉን ያነበብንና ቃሉን እያነበቡ ማስተዋል የተሳናቸው ሰዎች ገንዘብን አንፈልግም ብለው እግዚአብሔርን ከመምረጥ ይልቅ እግዚአብሔርን ባለ መምረጣቸውና ለእግዚአብሔር ባለመገዛታቸው ሰይጣን በገንዘብ ምን ያህል አለምን እንዳበላሸ ያየንና የሰማን የዚህ ዘመን ሰዎች ዛሬም ከእግዚአብሔርና ከገንዘብ ከመምረጥ ይልቅ በግልጽ የተጻፈውን ቃል ትርጉም ለማጣመም ዘመቻ መክፈታችን ያሳዝናል፡፡ ቃሉ ከእግዚአብሔርና ከገንዘብ ምረጡ ይለናል፡፡ ይሄም ከእግዚአብሔርና ከሰይጣን ማለት ነው፡፡ በአውሮፓና በአሜሪካ፣ ገንዘብ ሲገባ፣ ክርስትና ወጣ፣ እኛ ጋር ኢትዮጵያም ያ የማይሆንበት ምክንያት የለም፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር ከኔና ከገንዘብ አንዱን ውደዱና አንዱን ጥሉ ነው ያለው፡፡ የግመል፣ የመርፌና የባለጠግነቱን ምሳሌ አንዳንዶች፣ መርፌው የግመል ማሰሪያ ነው ይላሉ፡፡ ብዙ ሰዎች ደግሞ ባለጠጋ ይገባ ዘንድ አይቻለውም ሳይሆን ይከብዳል ማለት ብቻ ነው ይላሉ፡፡ አንዳንዶች፣ ባለጠጋ ሆኖ እግዚአብሔርን እየፈሩ ከተኖረ ችግር የለውም ይላሉ፡፡ ቃሉ ግን አንዱን ምረጡ ነው የሚለው፡፡ ለሁለቱ መገዛት አትችሉም ነው የሚለው፡፡ አይናችንን ከፍተን ዙሪያ ገባውን ስንቃኝም ይሄንኑ ነው የምንገነዘበው፡፡ ታሪክም ይሄን ነው የሚያስረዳን፡፡፡ ለሁለቱ መገዛት እንዳልተቻለ ነው የምንረዳው፡፡ በዚያ ላይ “ባለጠጋ መንግስተ ሰማያት ይገባ ዘንድ ከባድ ነው እንጂ አይቻልም አይደለም” የሚል ሰው፣ እሺ፣ ለምን አጠራጣሪውንና ከባዱን መንገድ ከመምረጥ ቀላሉን፣ ያለውን ሁሉ ለደሃው አካፍሎ፣ በእለት እንጀራና በሚለበስ ብቻ የሚኖረውን ህይወት አይመርጥም? ምክንያቱም ገንዘቡ ከእግዚአብሔር በለጠበት፡፡ ምክንያቱም ገንዘቤን ሁሉ አሳልፌ ልስጥ ካለ፣ ያለውን ክብር፣ በፊት ተከብሮ፣ ታፍሮ ይኖር እንዳልነበረ፣ ዝቅ ብሎ፣ ከደሃው በታች ሊኖርበት ነው ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ገንዘቡ ከእግዚአብሔር በልጦበታል ማለት ነው፡፡ ለገንዘብ መገዛት ማለትም ይሄው የገንዘብ ምኞትና የአለምን ብልጭልጭ መውደድና በግድ ከሁለቱም መሆን የሚቻልበትን በፍጹም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ መንገድን ማፈላለግ እንጂ ሌላ ትርጉም የለውም፡፡ ለዚህ ነው ባለጠጋ የእግዚአብሔርን መንግስት እንዲወርስ የማያስችለው፡፡ እግዚአብሔርን ለመከተል፣ ያከማቸውን፣ ሃብት፣ ንብረትና ክብር ከእግዚአብሔር እንደማይበልጥበት ማመንና ከሁለት አንዱን መምረጥ አለበት፡፡ ደሃው ግን ባንጻሩ ያከማቸው ክብርም ሆነ እግዚአብሔርን ለመከተል እንዲያቅማማ የሚያደርገው ገንዘብ የለውም፡፡ ስለዚህ ደሃው የሚጠበቅበት እግዚአብሔርን መከተልና እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መኖር ብቻ ነው፡፡ ባለጠጋው ግን መጀመሪያ ገንዘቡን መተውና መደባለቅ የሌለበት፣ እግዚአብሔርን መምረጥ አለበት፡፡ ለዚህ ነው ለባለጠጋ የሚከብደው፡፡ በገንዘብ ላይ መጨከን የማይቻል ይመስላል፡፡ ማቴ. 19፡26፡- “ይህ በሰው ዘንድ አይቻልም በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ሁሉ ይቻላል አላቸው፡፡”

ሰዎች ለገንዘቡ መገዛትና ገንዘቡን ማምለክ እንጂ ባለ ጠግነት ችግር የለውም ይላሉ፡፡ ለገንዘብ መገዛትና ገንዘብን ማምለክ ምን ማለት ነው? ገንዘብኮ ወረቀት ነው፡፡ ለወረቀቱ የሚሰግድ ሰው ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም፡፡ ገንዘብ ሃይል ነው ይባላል፡፡ ትክክል ነው፡፡ ገንዘብ በአለም ላይ ሃያል ያደርጋል፡፡ ይሄም ገንዘብን ማምለክ ወይም ለገንዘብ መገዛት ማለት አይደለም፡፡ ሲጀመር በግልጽ የተጻፈን ቃል እንደ ተጻፈ ከመቀበል ይልቅ የምናጣምመው ለምንድነው? ለገንዘብ ስለ ተገዛን አይደል? ከገንዘብ ፍቅራችን ጋር የሚሄድ ዶክትሪን ማውጣት ስለምንፈልግ አይደል? አንድ ሰው እግዚአብሔር ተው ያለውን ነገር፣ ነገር ግን መተው የማይፈልገውን ነገር ከሃይማኖቱ ጋር ለማጣጣም ሲል የአምላኩን ቃል ከማጣመም የበለጠ ምን ሊያደርግ ይችላል? ሰው በራሱ ሊያደርገው አይችልም፡፡ የእግዚአብሔር ጸጋ ግን ሰውን ያስችለዋል፡፡
19፡29-30፡- ስለ ስሜም ቤቶችን ወይም ወንድሞችን ወይም እህቶችን ወይም አባትን ወይም እናትን ወይም ሚስትን ወይም ልጆችን ወይም እርሻን የተወ ሁሉ መቶ እጥፍ ይቀበላል፡፡ የዘላለምንም ህይወት ይወርሳል፡፡ ነገር ግን ብዙዎች ፊተኞች ኋለኞች፣ ኋለኞችም ፊተኞች ይሆናሉ፡፡
እውነት ነው፡፡ እግዚአብሔር ደጋግሞ ተናግሮናል፡፡ ባለጠጋ ወደ እግዚአብሔር መንግስት ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢገባ ይቀላል ማለት እንደዚያው ማለት ነው፡፡ የእግዚአብሔር ቃል እውነትና ህያው ነው፡፡ የዚህን ቃል ትርጉም ሊያጣምሙና ባለጠጋ ሆኖ ወደ እግዚአብሔር መግባት የሚቻልባቸውን መንገዶች የሚያስተምሩ ሰዎች ግመልን በመርፌ ቀዳዳ ለማሹለክ እንደሚሞክር እብድ ይቆጠራሉ፡፡ በጣም በግልጽ የተጻፈ ቃል ነው፡፡ በእግዚአብሔር መንገድ ሂድ፣ ትእዛዛቱን ፈጽም፣ ጴንጤ ነኝ በል፣ ኦርቶዶክስ ነኝ በል፣ ካቶሊክ ነኝ በል፣ ሐዋርያት ሁሉንም ነገር ትተው ተከተሉትና ሐዋርያ ለመሆን እንደነሱ መሆን ያስፈልጋልና ነው እንጂ ሐዋርያም ሁን፣ ምንም ሁን ማን፣ የአለማችን አንደኛው ሰዉ፣ ደግ ሁን፣ እግዚአብሔር የከፋት ሁሉ መሰረት ያለውን ነገር አሳዳጅና በጉያው የሸሸገ ሰው ሆነህ፣ ወደ እግዚአብሔር መንግስት አትገባም፡፡ አንገባም፡፡ ከእግዚአብሔርና ከገንዘብ አንዱን ምረጥ ይላል ቃሉ፡፡ በአጭሩ ገንዘብ የሰይጣን ነው፣ ለኔና ለሰይጣን መገዛት አትችሉም እያለን ነው እግዚአብሔር በግልጽ፡፡ ታዲያ በሰይጣን ፈረስ እየጋለብን፣ የእግዚአብሔር በር መቼም ክፍት አይሆንልንም፡፡ ሰይጣን ምንኛ ሐሰተኞችን አሰለጠነብን? ምን ያህል አይናችንን አሳወረን? ቃሉን በቀጥታ በድፍረት አለመስበክ አንድ ችግር ነው፣ በተቃራኒው ደግሞ ገንዘብን ራሱን እያሞጋገሱ መስበክ ሌላ ችግርና ውድቀት ነው፡፡

ሰዎች "ቃሉን በቀጥታ ነው የምትተረጉመው" ይሉኛል፡፡ የኔ መልስም፡ "እና፣ ላጣምመው ወይስ ልሸቃቅጠው?" የሚል ነው፡፡ The word means, what it says.

መጽሐፍ ቅዱስን ብሉይ ኪዳንና አዲስ ኪዳን ብለው የከፋፈሉት ሰዎች ቢሆኑም በትክክልም በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን መሃል ትልቅ ልዩነት አለ፡፡ ያ ልዩነትም ስለኛ ኃጢአት ወደ ምድር ስጋን ለብሶ የመጣው፣ መከራን የተቀበለው፣ የሞተውና በሶስተኛው ቀን ከሙታን የተነሳው የእግዚአብሔር ልጅ፣ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡
በብሉይ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር አብርሃምን፣ የእስራኤልን ሕዝብ፣ ኢዮብን፣ ሰለሞንን፣ በምድራዊ በረከትና ባለጠግነት መባረኩ ተጽፎአል፡፡ እስራኤል ፍልስጥኤማውያንን ድል ሲነሱ፣ ትንሹን ዳዊት፣ ንጉስ ሲያደርገው፣ ንጉሱ ሰለሞንን በዓለም ላይ ከርሱ በፊትም ሆነ ከርሱ በኋላ ታይቶ የማይታወቅ ጠቢብና ባለጠጋ ሲያደርገው፣ በአዲሱ ኪዳን ደግሞ የነገስታት ንጉስ፣ የዓለም መድኃኒት፣ የእግዚአብሔር ልጅ በግርግም ተወለደ፡፡ "ወንድሞች ሆይ፣ መጠራታችሁን ተመልከቱ፡፡ እንደ ሰው ጥበብ ጥበበኞች የሆኑ ብዙዎች፣ ኀያላን የሆኑ ብዙዎች፣ ባላባቶች የሆኑ ብዙዎች አልተጠሩም፡፡ *ነገር ግን እግዚአብሔር ጥበበኞችን እንዲያሳፍር የዓለምን ሞኝ ነገር መረጠ፡፡ ብርቱንም ነገር እንዲያሳፍር እግዚአብሔር የዓለምን ደካማ ነገር መረጠ፡፡ እግዚአብሔርም የሆነውን ነገር እንዲያጠፋ የዓለምን ምናንቴ ነገር የተናቀውንም ነገር ያልሆነውንም ነገር መረጠ፤ ሥጋን* የለበሰ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት እንዳይመካ፡፡ ነገር ግን፡ የሚመካ በእግዚአብሔር ይመካ ተብሎ እንደተጻፈው ይሆን ዘንድ፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበብና ጽድቅ፣ ቅድስናም፣ ቤዛነትም በተደረገልን በክርስቶስ ኢየሱስ የሆናችሁ ከእርሱ ነው፡፡" 1 ቆሮንቶስ 1፡26-31፡፡ በበአለ ሃምሳ ለክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ከሰማይ የፈሰሰውም፣ በመንፈስ ባለጠጋ የሚያደርገው ቅዱስ መንፈስ እንጂ በአለም ባለጠጋ የሚያደርገው ገንዘብ አልነበረም፡፡

"if you want to know what God thinks of money, just look at the people who got it." Dorothy Parker (writer and poet).
እግዚአብሔር ስለ ገንዘብ ምን እንደሚያስብ ማወቅ ከፈለግክ፣ ገንዘብ ያላቸውን ተመልከት፡፡

ማስታወሻ፡ ደሃ፣ ባለጠጋ፣ የሚሉትን መጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ በስፋት የተጠቀሱ ቃላት መኪና የሌለውንም፣ የሚበላው የሌለውንም አንድ ላይ ደሃ ብሎ ከሚፈርጀው ዘመኑ ለደሃና ለባለጠጋ(ሀብታም) ከሚሰጠው ትርጉም አንጻር መተርጎም ፍጹም አሳሳች ይሆናል፡፡

ምሳሌ 30፡8-9፡- ከንቱነትንና ሐሰተኛነትን ከእኔ አርቃቸው፡፡ ድኅነትንና ባለጠግነትን አትስጠኝ፡፡ ነገር ግን የሚያስፈልገኝን እንጀራ ስጠኝ፣ እንዳልጠግብ፣ እንዳልክድህም፡፡ እግዚአብሔርስ ማን ነው? እንዳልል፡፡ ድሃም እንዳልሆን እንዳልሰርቅም፣ በአምላኬም ስም በሐሰት እንዳልምል፡፡

አንድ ፈረንጅ በፌስቡክ "እኔ መኪና፣ ቪዲዮ ማጫወቻ፣ ኮምፒዩተር፣ ስልክና የመሳሰሉትን አለኝ፡፡ በአለም ደረጃ ስታይ በጣም ሀብታም ነኝ፣ በሀገሬ በአሜሪካ ደረጃ ደግሞ ደሃ ከሚባሉት ነው የምመደበው፡፡" አለኝ፡፡ በአንድ ሁሉም ዜጋ ሚሊዮነር በሆነበት ሀገር፣ አንድ ሰው በአስር ወይም በመቶ ሺ የሚቆጠር ብር ብቻ ቢኖረው፣ ይሄን ሰው ሀገሩም፣ ራሱም ደሃ ነህ ይለዋል፡፡ በእግዚአብሔር አይን ግን ደሃ፣ በልቶ የሚያድረውን የሌለውና የሚለብሰውን ያጣ ሰው ብቻ እንጂ ከቡድኑ ውስጥ ትንሽ ገንዘብ ያለው ሰው አይደለም፡፡

በእግዚአብሔር አይን ባለጠጋ ማለት፣ የጠገበ፣ ዛሬን አልፎ፣ ለነገ፣ ነገን አልፎ፣ ለአመት፣ ያከማቸ፣ ምቾትና ተድላን የሚሻ ማንኛውምና ሁሉም ሰው ማለት እንጂ ከነኛ መሃል ሚሊዮነርና ቢሊዮነር የሆነው፣ ጣሪያ የነካው ማለት አይደለም፡፡ በተረፈ እግዚአብሔር እንደ ፈቃዱ የሚኖርን፣ ቤተሰቡን ሰርቶ የሚያበላን ሰራተኛ ይወዳል፣ ይባርካል፡፡

መዝሙር 37፡25፡- ጎለመስሁ አረጀሁም፡፡ ጻድቅ ሲጣል፣ ዘሩም እህል ሲለምን አላየሁም፡፡

1 ጢሞቴዎስ 5፡8፡- ነገር ግን ለእርሱ ስለ ሆኑት ይልቁንም ስለ ቤተ ሰዎቹ የማያስብ ማንም ቢሆን፣ ሃይማኖትን የካደ ከማያምንም ሰው ይልቅ የሚከፋ ነው፡፡ (But if any provide not for his own, and specially for those of his own house, he hath denied the faith, and is worse than an infidel.)

እውነቱ ስለ ጥበብና ስለ እውቀት

ሁለት አይነት ጥበቦች አሉ፡፡ አንዱ፣ የሚዋሽበት፣የሚሰረቅበት፣ ክፉ ስራዎች የሚሰሩበት እርኩሱ የሰይጣን(የአለም) ጥበብ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ቀኝ ጉንጭ ሲመታ፣ የግራውን አዙሮ ለማስመታት የሚያስችል፣ ለመጠቀም ሳይሆን፣ ሰዎችን ለመጥቀም፣ የሚያኖር፣ ቅናትና ክርክር የሌለበት፣ ቅዱሱ የእግዚአብሔር ጥበብ ነው፡፡ የመጀመሪያውን ያለው፣ ሁለተኛውን ሊኖረው አይችለም፣ ሁለተኛውን ያለው፣ የመጀመሪያውን ሊኖረው አይችልም፡፡ የመጀመሪያውን ላለው፣ ሁለተኛው ሁሌ እንቆቅልሽ ነው፡፡ ሁለቱ በጣም ተቃራኒ ነገሮች ከመሆናቸው የተነሳ፣ አንዱን አዎንታዊ ካልን ሌላኛው የግድ አሉታዊ ነው፡፡ አንዱን ጥበብ ካልን፣ ሌላኛው ሞኝነት ነው፡፡

ጥበብ ወይም/እና እውቀት በተለይ በሀገራችን በጣም ሰዎች ከሚሳሳቱባቸው ርዕሶች መካከል ነው፡፡ እግዚአብሔር የሚመክረን የእግዚአብሔር ጥበብ የአለሙ ጥበብ እየመሰለን፣ እግዚአብሔር የሚያወግዘው ጥበብ እግዚአብሔር የሚመክረው ጥበብ እየመሰለን ብዙ ሰዎች ማስተዋል አልቻልንም፡፡ መጽሐፈ ምሳሌና መጽሐፈ መክብብ ዋና ትኩረታቸው ጥበብ ነው፡፡ እኛ ብዙ ያውቃሉ የምንላቸውን ሰዎች ጠቢባን፣ ምሁር፣ አዋቂ፣ እያልን እናሞጋግሳለን፣ መጽሐፍ ቅዱሳችን ግን የአለምን እውቀትና ጥበብ፣ ስንፍና፣ ሞኝነት(folly) ሲለው የአለምን ጥበብና እውቀት የሚከተሉትን ደግሞ፣ ማለትም እኛ የምናሞጋግሳቸውን ሰዎች፣ ሰነፍ፣ ሞኝ(fool) ይላቸዋል፡፡ በአንጻሩ የእግዚአብሔርን ጥበብ የሚከተሉትን ሰዎች ጠቢብ(wise) ይላቸዋል፡፡ የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው፡፡ ጥበብም እግዚአብሔርን ፈርቶ እግዚአብሔርን የሚያከብር ህይወት መኖር ነው፡፡ ለአባትና ለእናታቸው የሚታዘዙ በእግዚአብሔር ፊት ጠቢባን ተብለው የሚጠሩት እንደሆኑ ከመጽሐፈ ምሳሌ ምዕራፍ 1 እንረዳለን፡፡ ይሄም ማለት በእግዚአብሔር ፊት በሙሉ ልቡ ወላጆቹን የሚያከብርና የሚፈራ ልጅ ጠቢብ ሲሆን፣ ወላጆቻቸውን የሚያንቋሽሹ፣ የማይታዘዙ፣ እንደ ፈለጉ የሚናገሩትና ወላጆቻቸውን እንደማይረዷቸው ሞኞች የሚያዩትና ምክራቸውን የሚንቁት የፈረንጅ አይነት ልጆች ደግሞ ሞኞች ናቸው ማለት ነው፡፡

<u>የእግዚአብሔር ቃል ስለ እግዚአብሔር ጥበብ፡</u>

ምሳሌ 8፡ 1-14፡-

በውኑ ጥበብ አትጮህምን? ማስተዋልስ ድምፅዋን አትሰጥምን? በኮረብታ ላይ በመንገድ አጠገብ በጎዳና መካከል ትቆማለች፡፡ በበሩ አጠገብ በከተማይቱ መግቢያ ትጮኻለች፡፡ እናንተ ሰዎች፣ እናንተን እጠራለሁ፣ ድምጼም ወደ ሰዎች ልጆች ነው፡፡ እናንተ አላዋቂዎች፣ ብልሃትን አስተውሉ፡፡ እናንተም ሰነፎች ጥበብን በልባችሁ ያዙ፡፡ የከበረች ነገርን እናገራለሁና ስሙ፡፡ ከንፈሮቼም ቅን ነገርን ለመናገር ይከፈታሉ፡፡ አፌ እውነትን ይናገራልና፣ ከንፈሮቼም ክፋትን ይጸየፋሉ፡፡ የአፌ ቃላት ሁሉ ጽድቅ ናቸው፡፡ **ጠማማ ዘወርዋራም አይደሉም፡፡ እነርሱ በሚያስተውሉ ዘንድ የቀኑ ናቸው፣ እውነትንም ካገኙአት ሰዎች ጋር የተስማሙ ናቸው፡፡** ተግሣጼን እንጂ ብርን አትቀበሉ፣ ከምዝምዝ ወርቅም ይልቅ እውቀትን ተቀበሉ፡፡ጥበብ ከቀይ ዕንቁ ትበልጣለችና የከበረ ነገር ሁሉ አይተካከላትም፡፡ እኔ ጥበብ በብልሃት ተቀምጫለሁ፣ እውቀትንም ጥንቃቄንም አገኝቻለሁ፡፡ እግዚአብሔርን መፍራት ክፋትን ይጠላል፡፡ ትዕቢትንና እብሪትን ክፉንም መንገድ ጠማማውንም አፍ እጠላለሁ፡፡ምክርና መልካም ጥበብ የኔ ነው፡፡ ማስተዋል እኔ ነኝ፣ ብርታትም አለኝ፡፡

ምሳሌ 2፡1-10፡-

ልጄ ሆይ፣ ቃሌን ብትቀበል፣ ትዕዛዜንም በአንተ ዘንድ ሸሽገህ ብትይዛት፣ ጆሮህ ጥበብን እንዲያደምጥ ታደርጋለህ፣ ልብህንም ወደ ማስተዋል ታዘነብላለህ፡፡ ረቂቅ እውቀትን ብትጠራት፣ ለማስተዋልም ድምጽህን ብታነሳ፣ እርስዋንም እንደ ብር ብትፈልጋት፣ እርስዋንም እንደ ተቀበረ ገንዘብ ብትሻት፣ የዚያን ጊዜ እግዚአብሔርን መፍራት ታውቃለህ፣ የአምላክንም እውቀት ታገኛለህ፡፡ እግዚአብሔር ጥበብን ይሰጣልና፣ ከአፉም እውቀትና ማስተዋል ይወጣሉ፡፡ እርሱ ለቅኖች ደኅንነትን ያከማቻል፣ ያለ ነውር ለሚሄዱትም ጋሻ ነው፡፡ የፍርድን ጎዳና ይጠብቃል፤ የቅዱሳኑንም መንገድ ያጸናል፡፡ የዚያን ጊዜ ጽድቅንና ፍርድን ቅንነትንና መልካም መንገድን ሁሉ ታስተውላለህ፡፡ ጥበብ ወደ ልብህ ትገባለችና፣ እውቀትም ነፍስህን ደስ ታሰኛለችና፡፡

ምሳሌ 1፡7-8፡-
የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው፡፡ ሰነፎች ግን ጥበብንና ተግሳጽን ይንቃሉ፡፡ ልጄ ሆይ የአባትህን ምክር ስማ፣ የእናትህንም ሕግ አትተው፡፡ ለራስህ ሞገስ፣ ለአንገትህም ድሪ ይሆንሃልና፡፡

ምሳሌ 19፡20፡-
ምክርን ስማ፣ ተግሳጽንም ተቀበል በፍጻሜህ ጠቢብ ትሆን ዘንድ፡፡

ያዕ. 3፡17፡-
ላይኛይቱ ጥበብ ግን በመጀመሪያ ንጽሕት ናት፣ በኋላም ታራቂ፣ ገር፣ እሺ ባይ፣ ምህረትና በጎ ፍሬ የሞላት፣ *ጥርጥርና ግብዝነት የሌለባት ናት፡፡*

መክብብ 2፡26፡-
እርሱም ደስ ለሚያሰኘው ሰው ጥበብንና ዕውቀትን ደስታንም ይሰጠዋል፡፡

1 ጴጥሮስ 2፡2-3፡-
ጌታ ቸር መሆኑን ቀምሳችሁ እንደ ሆነ፣ ለመዳን በእርሱ እንድታድጉ አሁን እንደተወለዱ ህጻናት ተንኮል የሌለበትን የቃልን ወተት ተመኙ፡፡

1 ቆሮንቶስ 2፡12-14፡-
እኛ ግን ከእግዚአብሔር እንዲሁ የተሰጠንን እናውቅ ዘንድ ከእግዚአብሔር የሆነውን መንፈስ እንጂ የዓለምን መንፈስ አልተቀበልንም፡፡ መንፈሳዊውን ነገር ከመንፈሳዊው ነገር ጋር አስተያይተን መንፈስ በሚያስተምረን ቃል ይህን ደግሞ እንናገራለን እንጂ የሰው ጥበብ በሚያስተምረን ቃል አይደለም፡፡ ለፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት ነውና አይቀበለውም፡፡ በመንፈስም የሚመረመር ስለሆነ ሊያውቀው አይችልም፡፡

ምሳሌ፡ 4፡5-6፡-
ጥበብን አግኝ፣ ማስተዋልን አግኝ፡፡ አትርሳም፣ ከአፌም ቃል ፈቀቅ አትበል፡፡ አትተዋት፣ ትደግፍህማለች፤ ውደዳት፣ ትጠብቅህማለች፡፡

ቆላስያስ 2፡2-4፡- ልባቸው እንዲጽናና፣ በፍቅርም ተባብረው በማስተዋል ወደሚገኝበት ወደ መረዳት ባለ ጠግነት ሁሉ እንዲደርሱ የእግዚአብሔርንም ምሥጢር እርሱንም ክርስቶስን እንዲያውቁ እጋደላለሁ፡፡ የተሰወረ የጥበብና የእውቀት መዝገብ ሁሉ በእርሱ ነውና፡፡ ማንም በሚያባብል ቃል እንዳያስታችሁ ይህን እላለሁ፡፡

ሉቃስ 21፡15፡- ወደረኞቻችሁ ሁሉ ሊቃወሙና ሊከራከሩ የማይችሉትን አፍና ጥበብ እሰጣችኋለሁ፡፡

<u>የእግዚአብሔር ቃል ስለ አለማዊ ጥበብና እውቀት፡</u>

ዘፍጥረት 2፡16፡- እግዚአብሔር አምላክም ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው፡፡ ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ፡፡ ነገር ግን *መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፣* ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና፡፡
ዘፍጥረት 3፡6-7፡-

ሴቲቱም ዛፉ ለመብላት ያማረ እንደ ሆነ፣ ለዓይንም እንደሚያስጎመጅ፣ *ለጥበብም መልካም እንደሆነ አየች፡፡* ከፍሬውም ወሰደችና በላች፡፡ ለባልዋም ደግሞ ሰጠችው፡፡ እርሱም ከእርስዋ ጋር በላ፡፡

ዘፍጥረት 3፡22-23፡-

እግዚአብሔር አምላክም አለ፡- *እነሆ አዳም መልካምና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ፡፡* አሁንም እጁን እንዳይዘረጋ፣ ደግሞም ከሕይወት ዛፍ ወስዶ እንዳይበላ፣ ለዘላለምም ሕያው ሆኖ እንዳይኖር፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክ ከዔድን ገነት አስወጣው፣ የተገኘባትን መሬት ያርስ ዘንድ፡፡

1ቆሮ. 3፡18-20፡-

ማንም ራሱን አያታልል፡፡ ከእናንተ ማንም በዚች ዓለም ጥበበኛ የሆነ ቢመስለው ጥበበኛ ይሆን ዘንድ ሞኝ ይሁን፡፡ የዚህች ዓለም ጥበብ በእግዚአብሐር ፊት ሞኝነት ነውና፡፡ እርሱ ጥበበኞችን በተንኮላቸው የሚይዝ፣ ደግሞም፡ ጌታ የጥበበኞችን አሳብ ከንቱ እንደሆነ ያውቃል ተብሎ ተጽፎአልና፡፡

ያዕ. 3፡13-17፡-

ከእናንተ ጥበበኛና አስተዋይ ማን ነው? በመልካም አኗኗሩ ስራውን በጥበብ የዋህነት ያሳይ፡፡ ነገር ግን መራራ ቅንአትና አድመኛነት በልባችሁ ቢኖርባችሁ፣ አትመኩ በእውነት ላይም አትዋሹ፡፡ ይህ ጥበብ ከላይ የሚወርድ አይደለም፣ ***ነገር ግን የምድር ነው፡፡ የሲጋም ነው፣ የአጋንንትም ነው፡፡*** ቅንአትና አድመኛነት ባሉበት ስፍራ በዚያ ሁከትና ክፉ ስራ ሁሉ አሉና፡፡ ላይኛይቱ ጥበብ ግን መጀመሪያ ንጽህት ናት፣ በኋላም ታራቂ፣ ገር፣ እሺ ባይ ምሕረትና በጎ ፍሬ የሞላባት፣ **ጥርጥርና ግብዝነት የሌለባት ናት፡፡**

መክብብ 1፡16-18፡-

እኔ በልቤ፡ ከእኔ አስቀድመው በኢየሩሳሌም ላይ ከነበሩት ሁሉ ይልቅ ጥበብን አብዝቼ ጨመርሁ፤ ልቤም ብዙ ጥበብንና እውቀትን ተመለከተ ብዬ ተናገርሁ፡፡ ጥበብንና ዕውቀትን ሞኝነትንም አውቅ ዘንድ ልቤን ሰጠሁ፡፡ ይህም ደግሞ ነፋስን እንደ መከተል እንደ ሆነ አስተዋለሁ፡፡ በጥበብ መብዛት ትካዜ ይበዛልና፤ እውቀትንም የሚጨምር ኀዘንን ይጨምራልና፡፡ (17 And I gave my heart to know wisdom, and to know madness and folly: I perceived that this also is vexation of spirit).

መክብብ 10፡13፡-

የሞቱ ዝንቦች የተቀመመውን የዘይት ሽቱ ያገሙታል፤ እንዲሁም ትንሽ ስንፍና ጥበብንና ክብርን ያጠፋል፡፡ የጠቢብ ልብ በስተቀኙ ነው፣ የሰነፍ ልብ ግን በስተ ግራው ነው፡፡ ደግሞም ሰነፍ በመንገድ ሲመላለስ እርሱም ልብ ይጎድለዋል፣ የሚያስበውም ሁሉ ስንፍና ነው፡፡

ትንቢተ ኢሳይያስ 5፡21፡-

በዓይናቸው ጥበበኞች፣ በነፍሳቸውም አስተዋዮች ለሆኑ ወዮላቸው!

ኢሳይያስ 29፡ 13-14፡-

ጌታም ይህ ሕዝብ በአፉ ወደ እኔ ይቀርባልና፣ በከንፈሮቹም ያከብረኛልና፣ ልቡ ግን ከእኔ የራቀ ነውና፣ በሰዎች ሥርዓትና ትምህርት ብቻ ይፈራኛልና፡፡ ስለዚህ፣ እነሆ ድንቅ ነገርን በዚህ ሕዝብ መካከል፣ ድንቅ ነገርን ተአምራትንም፣ እንደገና አደርጋለሁ፡፡ የጥበበኞች ጥበብ ትጠፋለች፣ የአስተዋዮችም ማስተዋል ትሰወራለች፡፡

ኢሳይያስ 47፡10-11፡-

በክፋትሽ ታምነሻል፡፡ የሚያየኝ የለም ብለሻል፤ ጥበብሽና እውቀትሽ አታልለውሻል፣ በልብሽም፡ እኔ ነኝ ከእኔም በቀር ሌላ የለም ብለሻል፡፡ ስለዚህም ምክንያት ክፉ ነገር ይመጣብሻል፣ በምዋርትሽም እንዴት እንደምታርቂው አታውቂም፡፡ ጉዳት ይወድቅብሻል፣ ታስወግጂውም ዘንድ አይቻልሽም፤ የማታውቂያትም ጉስቁልና ድንገት ትመጣብሻለች፡፡

ኤርሚያስ 8፡8-9፡-

እናንተስ ጥበበኞች ነን የእግዚአብሔር ፍርድ ከእኛ ጋር ነው እንዴት ትላላችሁ? እነሆ፣ የጸሐፊ ብዕር ሐሰተኛ ነው፡፡ በሐሰትም አድርጎአል፡፡ ጥበበኞች አፍረዋል፣ ደንግጠውማል፤ ተማርከውማል፡፡ እነሆ የእግዚአብሔርን ቃል ጥለዋል፤ ምን አይነት ጥበብ አላቸው?

ማቴ. 11፡25፡-

በዚያን ጊዜ ኢየሱስ መልሶ እንዲህ አለ፡፡ አባት ሆይ፣ የሰማይና የምድር ጌታ፣ ይህን ከጥበበኞችና ከአስተዋዮች ሰውረህ ለሕፃናት ስለ ገለጥህላቸው አመሰግንሃለሁ፡፡

ሮሜ 1፡21-23፡-
ስለዚህም እግዚአብሔርን እያወቁ እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን ስላላከበሩትና ስላላመሰገኑት የሚያመካኙት አጡ፡፡ ነገር ግን በአሳባቸው ከንቱ ሆኑ የማያስተውለውም ልባቸው ጨለመ፡፡ ጥበበኞች ነን ሲሉ ደንቆሮ ሆኑ፡፡

ቆላስያስ 2፡8፡-
እንደ ክርስቶስ ትምህርት ሳይሆን፣ እንደ ሰው ወግና እንደ ዓለማዊ እንደ መጀመሪያ ትምህርት ባለ በፍልስፍና በከንቱም መታለል ማንም እንዳይማርካችሁ ተጠበቁ፡፡

1 ጢሞቴዎስ 6፡20-21፡-
ጢሞቴዎስ ሆይ፣ በውሸት እውቀት ከተባለ ለዓለም ከሚመች ከከንቱ መለፍለፍና መከራከር እየራቅህ፣ የተሰጠህን አደራ ጠብቅ፡፡ ይህ እውቀት አለን ብለው፣ አንዳንዶች ስለ እምነት ስተዋልና፡፡ ጸጋ ከአንተ ጋር ይሁን፡፡
20 O Timothy, keep that which is committed to thy trust, avoiding profane [and] vain babblings, and oppositions of *science* falsely so called:

ሕዝቅኤል 28፡- (ስለ ሳጥናኤል ጥበብ)

1 ቆሮንቶስ 1፡17-31፡-
ለማጥመቅ ክርስቶስ አልላከኝምና፣ ወንጌልን ልሰብክ እንጂ፡፡ የክርስቶስ መስቀል ከንቱ እንዳይሆን በቃል ጥበብ አይደለም፡፡ የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት፣ ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነውና፡፡ የጥበበኞችን ጥበብ አጠፋለሁ የአስተዋዮችንም ማስተዋል እጥላለሁ ተብሎ ተጽፎአልና፡፡ ጥበበኛ የት አለ? እግዚአብሔር የዚችን ዓለም ጥበብ ሞኝነት እንዲሆን አላደረገምን? በእግዚአብሔር ጥበብ ምክንያት ዓለም እግዚአብሔርን በጥበብዋ ስላላወቀች፣ በስብከት ሞኝነት የሚያምኑትን ሊያድን የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖአልና፡፡ መቼም አይሁድ ምልክትን ይለምናሉ፣ የግሪክ ሰዎችም ጥበብን ይሻሉ፡፡ እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን፡፡ ይህም ለአይሁድ ማሰናከያ፣ ለአሕዛብም ሞኝነት ነው፡፡ ለተጠሩት ግን፣ አይሁድም ቢሆኑ የግሪክ ሰዎችም ቢሆኑ፣ የእግዚአብሔር ኃይልና የእግዚአብሔር ጥበብ የሆነው ክርስቶስ ነው፡፡ ከሰው ይልቅ የእግዚአብሔር ሞኝነት ይጠበባልና፣ የእግዚአብሔር ድካም ከሰው ይልቅ ይበረታልና፡፡ ወንድሞች ሆይ፣ መጠራታችሁን ተመልከቱ፡፡ እንደ ሰው ጥበብ ጥበበኞች የሆኑ ብዙዎች፣ ኃያላን የሆኑ ብዙዎች፣ ባላባቶች የሆኑ ብዙዎች አልተጠሩም፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ጥበበኞችን እንዲያሳፍር የዓለምን ሞኝ ነገር መረጠ፡፡ ብርቱንም ነገር እንዲያሳፍር እግዚአብሔር የዓለምን ደካማ ነገር መረጠ፡፡ እግዚአብሔር የሆነውን ነገር እንዲያጠፋ የዓለምን ምናምንቴ ነገር የተናቀውንም ነገር ያልሆነውንም ነገር መረጠ፡፡ ሥጋን የለበሰ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት እንዳይመካ፡፡ ነገር ግን የሚመካ በእግዚአብሔር ይመካ ተብሎ እንደ ተጻፈው ይሆን ዘንድ፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበብና ጽድቅ ቅድስናም ቤዛነትም በተደረገልን በክርስቶስ ኢየሱስ የሆናችሁ ከእርሱ ነው፡፡

አንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ እንዳለው ሁሉ፣ እውቀት/ጥበብ እና ትምክህት፣ ባለጠግነትና ትምክህት የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው፡፡ አንዱን የሳንቲም ገጽታ አንስተህ ሌላውን መተው እንደማትችል ሁሉ፣ ጥበብንና ባለጠግነትን አንስተህ፣ ትምክህትን መተውም አትችልም፡፡ ራስህን እንደምትችል ማሞኘት እንጂ፡፡

ኢዮብ 5፡13፡-
ጠቢባንን በተንኮላቸው ይይዛቸዋል፣ የጠማሞችንም ምክር ይዘረዝራል፡፡

መክብብ 2፡15፡-
እኔም በልቤ፡ ለሰነፍ የሚደርሰው ለእኔም ይደርሳል፣ ለምን እጅግ ጠቢብ ሆንኩ? አልሁ፡፡ የዚያን ጊዜም በልቤ፡ ይህ ደግሞ ከንቱ ነው አልሁ፡፡

ሐዋርያት 17፡21፡-
የአቴና ሰዎች ሁሉና በዚያ የኖሩ እንግዶች አዲስ ነገርን ከመናገርና ከመስማት በቀር በሌላ ጉዳይ አይውሉም ነበርና፡፡

ዳንኤል 12፡4፡-
ዳንኤል ሆይ አንተ ግን እስከ ፍጻሜ ዘመን ድረስ ቃሉን ዝጋ፣ መጽሐፉንም አትም፡፡ *ብዙ ሰዎችም ይመረምራሉ፣ እውቀትም ይበዛል፡፡*

1 ጢሞቴዎስ 4፡1፡-
መንፈስ ግን በግልጥ፡- በኋለኞቹ ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንትን ትምህርት እያደመጡ፣ ሃይማኖትን ይክዳሉ ይላል፡፡ (Now the spirit speaketh expressly, that in the latter times some shall depart from the faith, giving heed to seducing spirits, and doctrines of devils.)

ሉቃስ 8፡16፡-
...ጌታውም ዓመጸኛውን መጋቢ በልባምነት ስላደረገ አመሰገነው የዚህ ዓለም ልጆች ለትውልዳቸው ከብርሃን ልጆች ይልቅ ልባሞች ናቸውና፡፡(for the children of this world are in their generation wiser than the children of light.)

ሉቃስ 18፡17፡-
እውነት እላችኋለሁ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደ ሕፃን የማይቀበላት ሁሉ ከቶ አይገባባትም፡፡

<u>እውቀት በሶስት መንገዶች እንደሚገኝ ሰማሁ፡፡</u>

1. **በማንበብ፣ በመስማት፣ በመማር፣ በማየት፣ በስሜት ህዋሳት፡፡**
   ይሄ አብዛኛውን ጊዜ፣ ያውቃሉ፣ ምሁራን ናቸው፣ አዋቂዎች ናቸው የተባሉ ፈላስፎች፣ የአለምን እውቀት በመረመረ አዕምሮአቸው የእግዚአብሔርን ቃል ሲተረጉሙ፣ በጣም ከመመራመር የተነሳ ስተው ሰዎችን የሚያስቱበት መንገድ ነው፡፡ ይሄ እውቀትም ብዙውን ጊዜ የእግዚአብሔር ሀሳብ ምን እንደሆነ ለማወቅ ሚደረግና ከሰው ጋር ለመከራከር፣ እንዲሁ እንደ ባዮሎጂ፣ ሳይኮሎጂ፣ ቲዮሎጂ፣ ቃሉን ለማብራራት መሞከር እንጂ በእውነቱ መኖር የሌለበት እውቀት ነው፡፡ ሮሜ 12፡2፡ "የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ፡፡" ይሄ የዕውቀት ማግኛ መንገድ መንፈሳውያንን ወደ ህይወት ይመራቸዋል፡፡ እምነትም ከመስማት ነውና፡፡ ተመራማሪዎች ግን ይጠፉበታል፡፡

2. **በትንቢት፣ በራዕይ፣ ወይም እንዲሁ እግዚአብሔርን ለፈለጉት፣ እግዚአብሔር ራሱ በመንፈሱ እንደፈቃዱ ለሚኖሩ ሰዎች የሚሰጠው እውቀትና ጥበብ፡፡** በአለም ጥበብ የተጠመዱ ሰዎች ይሄን መንፈሳዊ ጥበብ በአለማዊ አዕምሮአቸው መርምረው ለውዝግብና ለክርክር የተጋበዙበትና በጥበባቸው ያልደረሱበት ጥበብ ነው፡፡ 1 ቆሮንቶስ 9 2፡9-16፡

   "ነገር ግን፡ ዓይን ያላየችው ጆሮም ያልሰማው በሰውም ልብ ያልታሰበው እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀው ተብሎ እንደተጻፈ፣ እንዲህ እንናገራለን፡፡ መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር እንኳ ሳይቀር ሁሉን ይመረምራልና ለእኛ እግዚአብሔር በመንፈሱ በኩል ገለጠው፡፡ በእርሱ ውስጥ ካለው ከሰው መንፈስ በቀር ለሰው ያለውን የሚያውቅ ሰው ማን ነው? እንዲሁም ደግሞ ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር ለእግዚአብሔር ያለውን ማንም አያውቅም፡፡ እኛ ግን ከእግዚአብሔር እንዲያው የተሰጠንን እናውቅ ዘንድ ከእግዚአብሔር የሆነውን መንፈስ እንጂ የዓለምን መንፈስ አልተቀበልንም፡፡ መንፈሳዊውን ነገር ከመንፈሳዊው ነገር ጋር አስተያይተን መንፈስ በሚያስተምረን ቃል ይህን ደግሞ እንናገራለን እንጂ የሰው ጥበብ በሚያስተምረን ቃል አይደለም፡፡ ለፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔር ነገር ሞኝነት ነውና አይቀበለውም፡፡ በመንፈስም የሚመረመር ስለ ሆነ ሊያውቀው አይችልም፡፡ መንፈሳዊ ሰው ግን ሁሉን ይመረምራል ራሱ ግን በማንም አይመረመርም፡፡ እንዲያስተምረው የጌታን ልብ ማን አውቆት ነው? እኛ ግን የክርስቶስን ልብ አለን፡፡"

   ሉቃስ 12፡12፡- *መንፈስ ቅዱስ በዚያች ሰአት ልትናገሩ የሚገባችሁን ያስተምራችኋልና፡፡*
   1 ቆሮንቶስ 2፡4-5፡- እምነታችሁም በእግዚአብሔር ኃይል እንጂ በሰው ጥበብ እንዳይሆን፣ ቃሌም ስብከቴም መንፈስንና ኃይልን በመግለጥ ነበረ እንጂ፣ **በሚያባብል በጥበብ ቃል አልነበረም፡፡**

   ሰይጣን ከዘፍጥረት ጀምሮ ሁሌ በጥበቡ ሰዎችን በማባበል፣ ክፉን መልካም አስመስሎ በማቅረብ፣ ሰዎችን ያታልላል፡፡ መልካሙን በክፉ እየመረዘ፣ ሰዎችን ከእግዚአብሔር ያስርቃል፡፡ አንዳንድ ሰዎች እንደ ክርስቶስ ሰይጣንን ሊጋፈጡ ይፈልጋሉ፡፡ ነገር ግን ያ ሃይል ለሰው ስላልተሰጠ ሰዎች ይሸነፋሉ፡፡ አንዳንዶች እንደ አዳምና እንደ ሄዋን ለሰይጣን የሚያባብል ጥበብ ይወድቃሉ፡፡ አንዳንዶች እንደ መላእክቱ አለቃ እንደ ሚካኤል በጌታ ስም ይገስጹታል፡፡

3. **በልምድ/ በልምምድ፡፡**
   በልምድ ማለት ሰዎች ሲያደርጉት የሚገኝ፣ ሲወራ በመስማት፣ በማንበብ፣ ሳይሆን በመኖር፣ የሚገኝ እውቀት ማለት ነው፡፡ እንዲህ አይነቱ እውቀት፣ የሰማነውን፣ ያየነውን ነገር፣ የምናውቀውን ነገር የበለጠ ተጨባጭ በሆነ መንገድ ራሳችን ላይ ስናየው ነው ማለት ነው፡፡
   ያነበብነው ነገር እንለማመዳለን ሳይሆን የተለማመድነውን ነገር እናነባለን ወይም እንደ ሰለሞን እንጽፋለን፡፡

የሰለሞን መጽሐፍት በጥበቡና በባለ ጠግነቱ የደረሰበትን፣ ያየውን ነገር ነው በብዛት የጻፈልን፡፡ ያው የተጻፈው አንባቢ እንዲማርበት ስለሆነና የእግዚአብሔር ቃል ስለሆነ ግን የሰለሞን ሀሳብ ብቻ አይደለም፡፡ ትንቢቶች ጭምር አሉበት፡፡ እግዚአብሔር ሰለሞን በራሱ ላይ በተለማመደው ልምድ እያስተማረን ነው ባጭሩ፡፡ የሰለሞን መጽሐፍት በብዛት ሰለሞን እግዚአብሔር በሰጠው ጥበብ የጻፋቸው ሳይሆኑ የእግዚአብሔርን ጥበብ ለአለማዊ ጉዳይ በማዋሉ የተቀበለውን የመከራ እውቀት ነው የሚያስተምረን፡፡ እንደሱ እንዳንሆን፡፡ አንድ ሰው ስለ አንድ በሽታ ሲያወራ በተመሳሳይ በሽታ ታሞ የሚያውቅ ሰው ከሌላው ካልታመመው ይልቅ ይረዳል ተብሎ ይታመናል፡፡ እኔም በህይወቴ ላይ ስለ ተለማመድኩት ብዙ ሰለሞን የጻፋቸው ነገሮች እኔ የጻፍኳቸው ያህል ትርጉም ይሰጡኛል፡፡ ሰለሞን ስለ ጥበብና ስለ ባለጠግነት ከንቱነት ሲናገር፣ ተንድቶበት የማያውቅ፣ ወይ ላይገባው፣ ወይ በሌላ ሊተረጉመው፣ ወይ ችላ ሊለው፣ ወይ ቢገባውም መቀበል ሊያቅተው ይችላል፡፡ እንደኔ መከራውን ቀምሶ ያየ ግን ለራሱ ምንም ማድረግ ባይችል፣ ቢሰሙም ባይሰሙም ቀኑ ሳይመሽ ሌሎችን ያስጠነቅቃል፡፡ ላላየው፣ ገንዘብ መሰብሰብን በመከልከሉ እግዚአብሔር ሰው እንዲደሰት የማይፈልግ ይመስለዋል፡፡ ባለ ጠግነትን ቀምሶ ያየና እንደምትመር ያስተዋለ ግን እግዚአብሔር ምንኛ ስለ ወደደን ደጋግሞ እንዳስጠነቀቀን ይገባዋል፡፡ እውቀትና ገንዘብ ምን ያህል ጎጂ እንደሆኑ ቀምሰው መራራነቷን ያወቁ ምዕራባውያን ፓስተሮች፣ "እግዚአብሔር አስጠንቅቆን ነበር" "we were warned" ይላሉ፡፡

እውነቱ ስለ ቤተሰብ

Family is the base of the faith.

<u>ስለ ወንድና ሴት/ስለ ባልና ሚስት፡</u>

ቲቶ 2፡3-5፡-
እንዲሁም አሮጊቶች ሴቶች አካሄዳቸው ለቅዱስ አገልግሎት የሚገባ፣ የማያሙ፣ ለብዙ ወይን ጠጅ የማይገዙ፣ በጎ የሆነውን ነገር የሚያስተምሩ ይሁኑ፡፡ ቆነጃጅትም የእግዚአብሔር ቃል እንዳይሰደብ፣ ባሎቻቸውን የሚወዱ፣ ራሳቸውን የሚገዙ፣ ንጹሖች፣ በቤት የሚሠሩ፣ በጎዎች፣ ለባሎቻቸው የሚታዘዙ እንዲሆኑ ይምከሩአቸው፡፡ ጎበዞችም እንዲሁ ራሳቸውን እንዲገዙ ምከራቸው፡፡

1 ቆሮንቶስ 11፡3-16
ነገር ግን የወንድ ሁሉ ራስ ክርስቶስ፣ የሴትም ራስ ወንድ፣ የክርስቶስም ራስ እግዚአብሔር እንደ ሆነ ልታውቁ እወዳለሁ፡፡ ራሱን ተከናንቦ የሚጸልይ ወይም ትንቢት የሚናገር ወንድ ሁሉ ራሱን ያዋርዳል፡፡ ራስዋን ሳትሸፍን ግን የምትጸልይ ወይም ትንቢት የምትናገር ሴት ሁሉ ራስዋን ታዋርዳለች፡፡ እንደ ተላጨች ያህል ነውና፡፡ ሴትም ራስዋን ባትሸፍን ጠጉርዋን ትቆረጥ፡፡ ለሴት ግን ጠጉርዋን መቆረጥ ወይም መላጨት የሚያሳፍር ከሆነ ራስዋን ትሸፍን፡፡ ወንድ የእግዚአብሔር ምሳሌና ክብር ስለ ሆነ ራሱን መከናነብ አይገባውም፡፤ ሴት ግን የወንድ ክብር ናት፡፡ ሴት ከወንድ ናት እንጂ ወንድ ከሴት አይደለምና፡፡ ሴት ከወንድ ተፈጠረች እንጂ ወንድ ከሴት አልተፈጠረምና፡፡ ስለዚህ ሴት ከመላእክት የተነሣ በራስዋ ሥልጣን ሊኖራት ይገባል፡፡ ነገር ግን በጌታ ዘንድ ሴት ያለ ወንድ ወንድም ያለ ሴት አይሆንም፡፡ ሴት ከወንድ እንደ ሆነች እንዲሁ ወንድ ደግሞ በሴት ነውና፣ ሁሉም ከእግዚአብሔር ነው፡፡ በእናንተ በራሳችሁ መካከል ፍረዱ፡፡ ሴት ራስዋን ሳትሸፍን ወደ እግዚአብሔር ልትጸልይ ይገባታልን? ወንድ ጠጉሩን ቢያስረዝም ነውር እንዲሆንበት፣ ሴት ግን ጠጉርዋን ብታስረዝም ክብር እንዲሆንላት ተፈጥሮ እንኳ አያስተምራችሁምን? ጠጉርዋ መጎናጸፊያ ሊሆን ተሰጥቶአታልና፡፡ *ዳሩ ግን ማንም ሊከራከር ቢፈቅድ፣ እኛ ወይም የእግዚአብሔር አብያተ ክርስትያናት እንዲህ ያለ ልማድ የለንም፡፡*

1 ጢሞቴዎስ 2፡8-15
እንግዲህ ወንዶች በስፍራ ሁሉ አለ ቁጣና አለ ክፉ አሳብ የተቀደሱትን እጆች እያነሱ እንዲጸልዩ እፈቅዳለሁ፡፡ እንዲሁም ደግሞ ሴቶች በሚገባ ልብስ ከእፍረትና ራሳቸውን ከመግዛት ጋር ሰውነታቸውን ይሸልሙ፡፡ *እግዚአብሔርን እንፈራለን ለሚሉት ሴቶች እንደሚገባ፣* መልካም በማድረግ እንጂ በሽሩባና በወርቅ ወይም በዕንቁ ወይም ዋጋው እጅግ በከበረ ልብስ አይሸለሙ፡፡ ሴት በነገር ሁሉ እየተገዛች በዝግታ ትማር፡፡ ሴት ግን በዝግታ ትኑር እንጂ ልታስተምር ወይም በወንድ ላይ ልትሰለጥን አልፈቅድም፡፡አዳም ቀድሞ ተፈጥሮአልና፣ በኋላም ሔዋን ተፈጠረች፡፡ የተታለለም አዳም አይደለም፣ ሴቲቱ ግን ተታልላ በመተላለፍ ወደቀች፡፡ ነገር ግን በእምነትና በፍቅር በቅድስናም ራሳቸውን እየገዙ ቢኖሩ *በመውለድ ትድናለች፡፡*

1 ቆሮንቶስ 14፡34፡-
ሴቶች በማህበር ዝም ይበሉ፡፡ ሕግ ደግሞ እንደሚል እንዲገዙ እንጂ እንዲናገሩ አልተፈቀደላቸውምና፡፡ ለሴት በማህበር መካከል መናገር ነውር ነውና፣ ምንም ሊማሩ ቢወዱ በቤታቸው ባሎቻቸውን ይጠይቁ፡፡

ስለ ሴቶች ችሎታና ድክመት ሳይሆን ስለ ክርስቶስ ትእዛዝ ነው:: It is not about what women can or can't. It is about what Christ commanded and forbade.

1 ጢሞቴዎስ 5:5-6 ብቻዋንም ኖራ በእውነት ባልቴት የምትሆን በእግዚአብሔር ተስፋ ታደርጋለች:: ሌትና ቀንም በልመና፣ በጸሎትም ጸንታ ትኖራለች:: ቅምጥሊቱ ግን በሕይወትዋ ሳለች የሞተች ናት::

1 ጢሞቴዎስ 5:14-15:-
እንግዲህ ቆነጃጅት ሊያገቡ፣ ልጆችንም ሊወልዱ፣ ቤቶቻቸውንም ሊያስተዳድሩ፣ ተቃዋሚውም የሚሳደብበትን አንድን ምክንያት ስንኳ እንዳይሰጡ እፈቅዳለሁ:: ከአሁን በፊት አንዳንዶች ሰይጣንን እንዲከተሉ ፈቀቅ ብለዋልና::

1 ጢሞቴዎስ 3:1-6:-
ማንም ኤጲስ ቆጶስነትን ቢፈልግ መልካምን ሥራ ይመኛል የሚለው ቃል የታመነ ነው:: እንግዲህ ኤጲስ ቆጶስ እንዲህ ሊሆን ይገባዋል:: የማይነቀፍ፣ የአንዲት ሚስት ባል፣ ልከኛ፣ ራሱን የሚገዛ፣ እንደሚገባው የሚሰራ፣ እንግዳ ተቀባይ፣ ለማስተማር የሚበቃ፣ የማይሰክር፣ የማይጨቃጨቅ፣ ነገር ግን ገር የሆነ፣ የማይከራከር፣ ገንዘብን የማይወድ፣ ልጆቹን በጭምትነት ሁሉ እየገዛ የራሱን ቤት በመልካም የሚያስተዳድር:: ሰው ግን የራሱን ቤት እንዲያስተዳድር ባያውቅ፣ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስትያን እንዴት ይጠብቃታል:: በትዕቢት ተነፍቶ በዲያብሎስ ፍርድ እንዳይወድቅ፣ አዲስ ክርስትያን አይሁን::

<u>ስለ ትዳር:</u>

ማቴ 19:3-6:-
ፈሪሳውያንም ወደ እርሱ ቀረቡና ሲፈትኑት: ሰው በሆነው ምክንያት ሁሉ ሚስቱን ሊፈታ ተፈቅዶአልን? አሉት:: እርሱ ግን መልስ እንዲህ አለ:- ፈጣሪ በመጀመሪያ ወንድና ሴት አደረጋቸው፣ አለም: ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፣ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል፣ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ የሚለውን ቃል አላነበባችሁምን? ስለዚህ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ወደ ፊት ሁለት አይደሉም:: እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየውም::

ምሳሌ 12:4:-
ልባም ሴት ለባልዋ ዘውድ ናት:: አሳፋሪ ሴት ግን በአጥንቱ ውስጥ እንደ ቅንቅን ናት::

ምሳሌ 18:22:-
ሚስት ያገኘ በረከትን አገኘ፣ ከእግዚአብሔር ሞገስን ይቀበላል::

ምሳሌ 31:10:-
ልባም ሴት ማን ሊያገኛት ይችላል? ዋጋዋ ከቀይ ዕንቁ እጅግ ይበልጣል::

ኤፌሶን 5:22-33:-
ሚስቶች ሆይ፣ ለጌታ እንደምትገዙ ለባሎቻችሁ ተገዙ:: ክርስቶስ ደግሞ የቤተ ክርስትያን ራስ እንደ ሆነ፣ እርሱም አካሉን የሚያድን እንደ ሆነ ባል የሚስት ራስ ነውና:: ዳሩ ግን ቤተ ክርስትያን ለክርስቶስ እንደምትገዛ እንዲሁ ሚስቶች ደግሞ በሁሉ ለባሎቻቸው ይገዙ:: ባሎች ሆይ፣ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስትያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ:: በውኃ በመታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ:: እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተ ክርስትያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ:: እንዲሁ ባሎች ደግሞ እንደ ገዛ ሥጋቸው አድርገው የገዛ ሚስቶቻቸውን ሊወዷቸው ይገባቸዋል:: የገዛ ሚስቱን የሚወድ ራሱን ይወዳል:: ማንም የገዛ ሥጋውን የሚጠላ ከቶ የለምና፣ ነገር ግን የአካሉ ብልቶች ስለሆንን፣ ክርስቶስ ደግሞ ለቤተ ክርስትያን እንዳደረገላት፣ ይመግበዋል፣ ይንከባከበውማል:: ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል:: ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ:: ***ይህ ምሥጢር ታላቅ ነው፣ እኔ ግን ይህን ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተ ክርስትያን እላለሁ::*** *ሆኖም ከእናንተ ደግሞ እያንዳንዱ የገዛ ሚስቱን እንዲህ እንደ ራሱ አድርጎ ይውደዳት፣ ሚስቱም ባሏን ትፍራ::*

ቆላስያስ 3:18-19:-
ሚስቶች ሆይ በጌታ እንደሚገባ ለባሎቻችሁ ተገዙ:: ባሎች ሆይ፣ ሚስቶቻችሁን ውደዱ፣ መራራም አትሁኑባቸው::

1 ጴጥሮስ 3:1-7:-
እንዲሁም፣ እናንተ ሚስቶች ሆይ፣ ከባሎቻችሁ አንዳንዱ ለትምህርት የማይታዘዙ ቢኖሩ፣ በፍርሃት ያለውን ንጹሑን ኑሮአችሁን እየተመለከቱ ያለ ትምህርት በሚስቶቻቸው ኑሮ እንዲገኙ ተገዙላቸው:: ለእናንተም ጠጉርን በመሸረብና ወርቅን በማንጠልጠል ወይም ልብስን በመጎናጸፍ በውጭ የሆነ ሽልማት አይሁንላችሁ:: ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት ዋጋው እጅግ የከበረ የዋህና ዝግተኛ መንፈስ ያለውን የማይጠፋውን ልብስ ለብሶ የተሰወረ የልብ ሰው ይሁንላችሁ:: እንዲህ በቀድሞ ዘመን በእግዚአብሔር ተስፋ ያደረጉት ቅዱሳት ሴቶች ደግሞ ለባሎቻቸው

ሲገዙ ተሸልመው ነበርና፡፡ እንዲሁም ሣራ ለአብርሃም፡ ጌታ ብላ ታዘዘችለት፡፡ እናንተም ከሚያስደነግጥ ነገር አንዳች እንኳ ሳትፈሩ መልካም ብታደርጉ ልጆቿ ናችሁ፡፡ እንዲሁም እናንተ ባሎች ሆይ፣ ደካማ ፍጥረት ስለ ሆኑ ከሚስቶቻችሁ ጋር በማስተዋል አብራችሁ ኑሩ፣ ጸሎታችሁ እንዳይከለከል አብረው ደግሞ የሕይወትን ጸጋ እንደሚወርሱ አድርጋችሁ አክብሩአቸው፡፡

ማቴዎስ 19፡9፡-
እኔ ግን እላችኋለሁ፣ ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን ፈትቶ ሌላይቱን የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል፣ የተፈታችውንም የሚያገባ ያመነዝራል አላቸው፡፡

ዕብራውያን 13፡4፡-
መጋባት፣ በሁሉ ዘንድ ክቡር፣ መኝታውም ንጹህ ይሁን፡፡ ሴሰኞችንና አመንዝሮችን ግን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል፡፡

ትንቢተ ሚልክያስ 2፡
...14 እናንተም፡ ስለ ምንድን ነው? ብላችኋል፡፡ ሚስትህ ባልንጀራህና የቃል ኪዳንህ ሚስት ሆና ሳለች እርስዋን አታልለሃታልና እግዚአብሔር በአንተና በልጅነት ሚስትህ መካከል ምስክር ስለ ሆነ ነው፡፡ 15 እግዚአብሔር የሕይወትን መንፈስ አንድ አድርጎ ጠብቆልን የለምን? ስለዚህ መንፈሳችሁን ጠብቁ፣ ማንም የልጅነት ሚስቱን አያታልል፡፡ 16 መፋታትን እጠላለሁ፣ ይላል የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር፡፡ ልብሱንም በግፍ ሥራ የሚከድነውን ሰው እጠላለሁ፣ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፡፡ ስለዚህ እንዳታታልሉ መንፈሳችሁን ጠብቁ፡፡...

በዚህ በሰለጠነው ዘመን፣ ሴቶች ያውም በኩራት በቴሌቪዥን መስኮት ይሰብኩን ይገኛሉ፡፡ ማወቅ ያለብን ግን መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው ለሁሉም ትውልድ መሆኑን ነው፡፡ የሰዎች አስተሳሰብ ስለተቀየረና ሴቶች ከወንዶች እኩል ናቸው ስለተባለ የእግዚአብሔርን ቃል መከለስ አንችልም፡፡ እግዚአብሔርን ያመንነው ቃሉን ሰምተን ነው፡፡ በቃሉ የሚያምን ደግሞ ቃሉን ሳይሰርዝ፣ ሳይደልዝ፣ ሳይቀንስ፣ ሳይጨምርበት፣ እንዳለ ይቀበለዋል፡፡ ያልተመቸንን ቃል አውጥተን እየሰበክን፣ ያልተመቸንን እንደሌለ እየቆጠርን የምንኖረው ህይወት፣ እንደማያዋጣን ሁላችንም እናውቀዋለን፡፡ ከሁሉም በላይ የክርስቶስ ህይወት የተከፈለበትን "ክርስትያን" የሚል ስማችን (1 ጴጥ. 4፡16-17) ከኛ ላይ እንዲገፈፍ እናደርጋለን፡፡ "ያመነ ሁሉ በእርሱ እንዲጸድቅ በእናንተ ዘንድ የታወቀ ይሁን" (ሐዋርያት 13፡38-39) የሚለውን ቃል ቆርጠን አውጥተን መፈክራችን ብናደርግ ኪሳራው የራሳችን ነው፡፡ የአይሁድ ስርአት ስለነበረ ነው፣ ባህላችን ይለያያል እያልን በማምታታት እረስ በራሳችን ልንሞኝኝ እንችላለን፡፡ እግዚአብሔር ግን እግዚአብሔር ነው፡፡ ቃሉም ቃሉ ነው፡፡ የተጻፈውም ለሁላችንም ነው፡፡

Gotquestion.com የተባለ ዌብሳይት፣ ሴት ፓስተር ሰባኪ መሆን ትችላለች ወይ? የሚለውን ጥያቄ ሲመልስ እንዲህ ይላል፡
"ዛሬ ላይ ሴቶች ፓስተር ወይም ሰባኪ መሆን ይችላሉ ወይስ አይችሉም ከሚለው ርዕስ የበለጠ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ(እኔ፡ አውሮፓና አሜሪካ ውስጥ) አከራካሪ ጉዳይ የለም፡፡

ይሄን የክርክር ነጥብ እንደ ወንዶች ለሴቶች (men versus women) ክርክር አለመውሰድ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ "ሴቶች ፓስተር ወይም ሰባኪ ሆነው ማገልገል የለባቸውም፣ የእግዚአብሔር ቃል የሴቶች አገልግሎት እንዲኖር አይፈቅድም" ብለው የሚያምኑ ሴቶችና "ሴቶች ፓስተር ወይም ሰባኪ ሆነው ማገልገል ይችላሉ፣ የሴቶች አገልግሎት ችግር የለውም" ብለው የሚያምኑ ወንዶች ስላሉ፡፡ ይሄ የበላይነትና የበታችነት ጉዳይ ሳይሆን የእግዚአብሔር ቃል ትርጉም ጉዳይ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል ያውጃል፡- (1 ጢሞቴዎስ 2፡11-12)፡፡
ቤተ ክርስትያን ውስጥ እግዚአብሔር የተለያዩ የሥራ ድርሻዎችን ለወንዶችና ለሴቶች መረጠ፡፡ ይሄም የሰው ዘር የተፈጠረበት መንገድና ኃጢአት ወደ ዓለም የገባበት መንገድ ውጤት ነው፡፡ (1 ጢሞ. 2፡ 13-14)፡፡
በዚህ የሴቶች የስብከት አገልግሎት ላይ ብዙ ተቃውሞዎች ይነሳሉ፡፡ አንድ በጣም የሚታወቀውና የሚዘወተረው፡
ጳውሎስ ሴቶች እንዳያስተምሩ የከለከለው፣ በነኛው ክፍለዘመን የነበሩ ሴቶች በጣም መሃይም ስለነበሩ ነው ይላል፡፡ ነገር ግን 1 ጢሞቴዎስ 2፡11-14 ላይ አንድም፣ በተለይ ስለ ትምህርት ደረጃ (የተማረች መሆንና አለመሆን) አልተጻፈም፡፡ እውቀት የአገልጋይነት መመዘኛ ቢሆን ኖሮ፣ አብዛኞቹ የክርስቶስ ደቀመዛሙርት መስፈርቱን አያሟሉም ነበር፡፡
ሁለተኛውና ተደጋግሞ የሚነሳው ተቃውሞ፡
ጳውሎስ ወንዶችን እንዳያስተምሩ የከለከለው፣ የኤፌሶንን ሴቶች ብቻ ነው የሚል ነው፡፡ (1 ጢሞቴዎስ የተጻፈው በኤፌሶን ውስጥ የምትገኝ ቤተክርስትያን መጋቢ ለነበረው ለጢሞቴዎስ ነው፡፡) ኤፌሶን ያኔ አርቴሚስ በሚባል ጣኦቷ ትታወቅ ነበር፡፡ የዚያ ጣኦት አምልኮ መሪዎች(ስርአት አስፈጻሚዎች) ደግሞ ሴቶች ነበሩ፡፡ ስለዚህ ሀሳባቸው፡ ጳውሎስ የተቃወመው በሴቶች የሚመሩ የኤፌሶን ባህላዊ የጣኦት አምላኪዎችን ነው፣ ቤተ ክርስትያን ደግሞ ከዚያ መለየት ነበረባት የሚል ነው፡፡ ዳሩ ግን የመጀመሪያይቱ የጳውሎስ መልእክት ወደ ጢሞቴዎስ ላይ ስለ አርቲሜቲስም ሆነ የከለከለበት ምክንያት፣ የአርቲሜቲስ አምላኪዎች የነበሩበት ሁኔታ ስለመሆኑ፣ የሚናገር ክፍል የለም፡፡..."

የደርግ መንግስት በሴቶች ቀን ላይ ሴቶች ተሰብስበው የተለያዩ መፈክሮችን እያሰሙ እንዲሄዱ ያስደርግ ነበር አሉ፡፡ የእናቴ እናት የሆኑት ሴት አያቴም በገጠር ወጥተው መፈክር ከሚያሰሙት መሃል ነበሩ፡፡ ነገር ግን "እኛ ጭቁን ሴቶች..." ብሎ የሚጀምር መፈክር ሲሰሙ፣ አጠገባቸው ላሉት ሴቶች፣ "ኧረኔ ማንም አልጨቆነኝም" ብለው ነበር አሉ፡፡ አያቴ አልተጨቆንኩም ያሉት፣ እውነትም የእኩልነት መብታቸው ስለተከበረላቸው አልነበረም፡፡ ይልቅ፣ በነርሱ የገጠር መንደር፣ ገና የሴቶች መብት የሚሉት እንግዳ ፈሊጥ በወጉ መንደራቸውን ስላልዘለቀ ነው፡፡ ሰው ነገሮችን የሚተረጉመው አምኖ እንደተቀበለው ነው፡፡ አንድ ዘመናዊት ነኝ የምትል ሴት፣ እግዚአብሔር የሰጣትን ተፈጥሮ በሚጻረር መልኩ፣ እንደ ተጨቆነች ታስባለች፡፡ አንዳንዱ ደግሞ በእውነተኛ እስር ቤት ውስጥ ሆኖ በነጻነት ይዘምራል፡፡ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ላይ እየተረማመድን የምናስሰው ነጻነት፣ ከባድ ቀንበርን አስከትሎ ይገኛል፣ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሚኖር ግን በእስር ቤት ውስጥ

እንኳን ነጻ ነው፡፡ እንደ ተረገምነው ነው፡፡ ጤነኛ የምንለው ሰው የቱ ነው? ደሃ የምንለው ሰው የቱ ነው? ተጨቆነ የምንለው ሰው የቱ ነው? ደስተኛ ነው የምንለው ሰው የቱ ነው? የምንኖርባቸው ቦታዎችና ጊዜያት ለነዚህ ጥያቄዎች የተለያዩ መልሶች ይሰጡናል፡፡ ትክክለኛውና ብንቀበለው የሚያዋጣን መልስ ግን እውነትና ህያው የሆነው የእግዚአብሔር ቃል የሚሰጠን መልስ ነው፡፡

<u>ስለ ልጆች፡</u>

መዝሙር 127፡3-5፡-
እነሆ ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው፣ የሆድም ፍሬ የእርሱ ዋጋ ነው፡፡ በኃያል እጅ እንዳሉ ፍላጾች፣የጎልማሳነት ልጆች እንዲሁ ናቸው፡፡ ከእነርሱ ዘንድ ምኞቱን የሚፈጽም ብፁዕ ሰው ነው፡፡ ጠላቶቻቸውን በአደባባይ በተናገሩ ጊዜ እርሱ አያፍርም፡፡ (4 As arrows are in the hand of a mighty man; so are children of the youth.)

2 ጢሞቴዎስ 3፡15፡-11
ከሕጻንነትህም ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን፣ መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳን መጻሕፍት አውቀሃል፡፡

ማርቆስ 10፡13-16
እንዲዳስሳቸውም ሕጻናትን ወደ እርሱ አመጡ፡፡ ደቀ መዛሙርቱም ያመጡአቸውን ገሠጹአቸው፡፡ ኢየሱስ ግን አይቶ ተቆጣ፡፡ ሕጻናትን ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ ተዉ አትከልክሉአቸው፡፡ የእግዚአብሔር መንግስት እንደነዚህ ላሉት ናትና፡፡ እውነት እላችኋለሁ፡- የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደ ሕጻን የማይቀበላት ሁሉ ከቶ አይገባባትም አላቸው፡፡ አቀፋቸውም፣ እጁንም ጭኖ ባረካቸው፡፡

ዘዳግም 6፡6-7፡-
እኔም ዛሬ አንተን የማዝዘውን ይህን ቃል በልብህ ያዝ፡፡ ለልጆችህም አስተምረው፣ በቤትህም ስትቀመጥ፣ በመንገድም ስትሄድ፣ ስትተኛም፣ ስትነሣም ተጫወተው፡፡

ኤፌሶን 6፡1-4፣ ቆላስያስ 3፡20፡-
ልጆች ሆይ ለወላጆቻችሁ በጌታ ታዘዙ፣ ይህ የሚገባ ነውና፡፡ መልካም እንዲሆንልህ ዕድሜህም በምድር ላይ እንዲረዝም አባትህንና እናትህን አክብር፡፡ **እርስዋም የተስፋ ቃል ያላት ፊተኛይቱ ትእዛዝ ናት፡፡** እናንተም አባቶች ሆይ፣ ልጆቻችሁን በጌታ ምክርና በተግሳጽ አሳድጉአቸው እንጂ አታስቆጡአቸው፡፡
እግዚአብሔርን መፍራት የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ ነው፡፡ አባትና እናትን ማክበርም እግዚአብሔርን ከመፍራት ጋራ በቀጥታ ይገናኛል፡፡

ዘዳግም 6፡6-7፡-
እኔም ዛሬ አንተን የማዝዘውን ይህን ቃል በልብህ ያዝ፡፡ ለልጆችህም አስተምረው፡፡

ምሳሌ 1፡8-9፡-
ልጄ ሆይ፣ የአባትህን ምክር ስማ፣ የእናትህንም ሕግ አትተው፡፡ ለራስህ የሞገስ ዘውድ ለአንገትህም ድሪ ይሆንልሃልና፡፡

ምሳሌ 30፡17፡-
በአባትዋ የምታላግጥን የእናትዋንም ትእዛዝ የምትንቅን ዓይን የሸለቆ ቁራዎች ይጎጠጉጡአታል፣ አሞራዎችም ይበሉአታል፡፡

ምሳሌ 30፡11-12፡-
አባቱን የሚረግም፣ እናቱንም የማይባርክ ትውልድ አለ፡፡ ለራሱ ንጹሕ የሆነ የሚመስለው ከርኩስነቱ ያልጠራ ትውልድ አለ፡፡

ዘዳግም 11፡19፡-
ልጆቻችሁንም አስተምሯቸው፣ በቤትህም ስትቀመጥ፣ በመንገድም ስትሄድ፣ ስትተኛም ስትነሣም አጫውቱአቸው፡፡

ምሳሌ 23፡13-14፡-
ሕጻንን ከመቅጣት ቸል አትበል፣ በበትር ብትመታው አይሞትም፡፡ በበትር ትመታዋለህ፣ ነፍሱንም ትታደጋለህ፡፡

በበትር ትመታዋለህ፣ ነፍሱንም ትታደጋለህ፡፡ መረን ትለቀውና አቀማጥለህ ታሳድገዋለህ፣ ነፍሱ ትጠፋለች፡፡ አለምን ማትረፍ ወይስ ነፍስን ማትረፍ? ስጋዊውን አትረፍርፎ፣ በመንፈሳዊው መደህየት ወይስ ስጋ ጎድሎ ነፍስ ቢሞላ ይሻላል?

እውነቱ ስለ ቤተ ክርስትያን

1 ቆሮንቶስ 14፡
...26 እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፣ ምንድር ነው? በምትሰበሰቡበት ጊዜ ለእያንዳንዱ መዝሙር አለው፣ በልሳን መናገር አለው፣ መተርጎም አለው፡፡ *ሁሉ* **ለማነጽ ይሁን፡፡** በልሳን የሚናገር ቢኖር ሁለት ወይም ሶስት ሆነው በተራቸው ይናገሩ አንዱም ይተርጉም፡፡ የሚተረጉም ባይኖር ግን በማኅበር መካከል ዝም ይበልና ለራሱና ለእግዚአብሔር ይናገር፡፡ ነቢያትም ሁለት ሶስት ሆነው ይናገሩ ሌሎችም ይለዩአቸው፡፡ በዚያ ለሚቀመጥ ለሌላ ግን አንድ ነገር ቢገለጥለት ፊተኛው ዝም ይበል፡፡ ሁሉም እንዲማሩ ሁሉም እንዲመከሩ ሁላችሁ በእያንዳንዳችሁ ትንቢት ልትናገሩ ትችላላችሁ፡፡ የነቢያትም መናፍስት ለነቢያት ይገዛሉ፡፡ **እግዚአብሔርስ የሰላም አምላክ ነው እንጂ የሁከት አምላክ አይደለምና፡፡** በቅዱሳንም አብያተ ክርስትያናት ሁሉ እንዲህ ነው፡፡...36 ምን ነው? የእግዚአብሔር ቃል የወጣው ከናንተ ነውን? ወይስ ወደ እናንተ ብቻ ደርሶአልን? ማንም ነቢይ ወይም መንፈሳዊ የሆነ ቢመስለው ይህች የጻፍሁላችሁ የጌታ ትእዛዝ እንደ ሆነች ይወቅ፡፡ ማንም የማያውቅ ቢኖር ግን አይወቅ፡፡ ስለዚህ ወንድሞች ሆይ፣ ትንቢት ለመናገር በብርቱ ፈልጉ፣ በልሳኖች ከመናገርም አትከልክሉ፡፡ 40 **ነገር ግን ሁሉ በአግባብና በሥርአት ይሁን፡፡** (40 Let all things be done decently and in order.)

ትንቢተ ሕዝቅኤል 33፡30-32፡- አንተም የሰው ልጅ ሆይ፣ የሕዝብህ ልጆች በቅጥር አጠገብና በቤት ደጆች ውስጥ ስለ አንተ ይናገራሉ፣ እርስ በርሳቸውም፣ አንዱ ከአንዱ ጋር፡- እንሂድና እግዚአብሔር ያለው ቃል ምን እንደ ሆነ እንስማ ብለው ይናገራሉ፡፡ ሕዝብ እንደሚመጣ ወደ አንተ ይመጣሉ፣ እንደ ሕዝቤም በፊትህ ይቀመጣሉ፣ ቃልህንም ይሰማሉ ነገር ግን አያደርጉትም፡፡ ***በአፋቸው ብዙ ፍቅር ይገልጣሉ፣ ልባቸው ግን ስስታቸውን ትከተላለች፡፡*** *እነሆ፣ አንተ መልካም ድምጽ እንዳለው እንደሚወደድ መዝሙር ማለፊያም አድርጎ በገና እንደሚጫወት ሰው ሆነህላቸዋል፡፡ ቃልህንም ይሰማሉ ነገር ግን አያደርጉትም፡፡*

እውነቱ ስለ ፍቅር

1 ቆሮንቶስ 13፡- 1 በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብናገር፣ ፍቅር ግን ከሌለኝ እንደሚጮኽ ናስ ወይም እንደሚንሽዋሸው ጸናጽል ሆኜአለሁ፡፡ ትንቢትም ቢኖረኝ ምሥጢርንም ሁሉና እውቀትን ሁሉ ባውቅ፣ ተራሮችንም እስካፈልስ ድረስ እምነት ሁሉ ቢኖረኝ ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ፡፡ *ድሆችንም ልመግብ ያለኝን ሁሉ ባካፍል፣ ሥጋዬንም ለእሳት መቃጠል አሳልፌ ብሰጥ ፍቅር ግን ከሌለኝ ምንም አይጠቅመኝም፡፡ ፍቅር ይታገሳል፣ ቸርነትንም ያደርጋል፡፡ ፍቅር አይቀናም፣ ፍቅር አይመካም፣ አይታበይም፡፡ የማይገባውን አያደርግም፣ የራሱንም አይፈልግም፣ አይበሳጭም፣ በደልንም አይቆጥርም፡፡ ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ ዓመፃ ደስ አይለውም፡፡* ***ሁሉን ይታገሳል፣ ሁሉን ያምናል፣ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል፣ በሁሉ ይጸናል፡፡***...13 እንዲህም ከሆነ፣ እምነት፣ ተስፋ፣ ፍቅር፣ እነዚህ ሶስቱ ጸንተው ይኖራሉ፡፡ ከእነዚህም የሚበልጠው ፍቅር ነው፡፡

1 ዮሐንስ 4፡8፡-
ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን አያውቅም፣ እግዚአብሔር ፍቅር ነውና፡፡

1 ዮሐንስ 4፡20-21፡- ማንም፡- እግዚአብሔርን አወዳለሁ እያለ ወንድሙን ቢጠላ ሐሰተኛ ነው፡፡ ያየውን ወንድሙን የማይወድ ያላየውን እግዚአብሔርን ሊወደው እንዴት ይችላል? እግዚአብሔርንም የሚወድ ወንድሙን ደግሞ እንዲወድ ይህች ትዕዛዝ ከእርሱ አለችን፡፡

ዕብራውያን 13፡1-2፡-
የወንድማማቾች መዋደድ ይኑር፡፡ እንግዶችን መቀበል አትርሱ፡፡ በዚህ አንዳንዶች ሳያውቁ መላእክትን እንግድነት ተቀብለዋልና፡፡

1 ዮሐንስ 3፡14-24፡-
እኛ ወንድሞችን የምንወድ ስለ ሆንን ከሞት ወደ ህይወት እንደ ተሻገርን እናውቃለን፡፡ ወንድሙን የማይወድ በሞት ይኖራል፡፡ ወንድሙን የሚጠላ ሁሉ ነፍሰ ገዳይ ነው፣ ነፍሰ ገዳይም የሆነ ሁሉ የዘላለም ሕይወት በእርሱ እንዳይኖር ታውቃላችሁ፡፡...

መክብብ 4፡4-12፡-
ደግሞም የሰውን ድካምና የብልሃት ሥራውን ሁሉ ተመለከትሁ፡፡ በባልንጀራው ዘንድ ቅንአትን እንዲያስነሣ አየሁ፡፡ ይህም ደግሞ ከንቱ፣ ነፋስንም እንደ መከተል ነው፡፡ ሰነፍ እጆቹን ኮርትሞ ይቀመጣል፣ የገዛ ስጋውንም ይበላል፡፡ በድካምና ነፋስን በመከተል ከሁለት እጅ ሙሉ ይልቅ አንድ እጅ ሙሉ በእረፍት ይሻላል፡፡ እኔም ተመለስሁ፡፡ ከፀሐይ በታችም ከንቱን ነገር አየሁ፡፡ አንድ ሰው ብቻውን አለ፡፡ ሁለተኛም የለውም፡፡ ልጅም ሆነ ወንድም የለውም፡፡ ለድካሙ ግን መጨረሻ የለውም፣ ዓይኖቹም ከባለጠግነት አይጠግቡም፡፡ ለማን እደከማለሁ፣ ሰውነቴንስ መልካሙን ነገር ለምን እነፍጋታለሁ? ይላል፡፡ ይህም ደግሞ ከንቱ ነገር፣ ከፉም ጥረት ነው፡፡ ድካማቸው ዋጋ አለውና አንድ ከመሆን ሁለት መሆን ይሻላል፡፡ ቢወድቁ አንዱ ሁለተኛውን ያነሳዋልና፡፡ አንዱ ብቻውን ሆኖ በወደቀ ጊዜ ግን የሚያነሳው ሁለተኛ የለውምና ወዮለት፡፡ ሁለቱም በአንድነት ቢተኙ ይሞቃቸዋል፣ አንድ ብቻውን ግን እንዴት ይሞቀዋል? አንዱም አንዱን ቢያሸንፍ ሁለቱ በፊቱ ይቆማሉ፣ በሦስትም የተገመደ ገመድ ፈጥኖ አይበጠስም፡፡

ማቴዎስ 24፡12(ስለ መጨረሻው ዘመን)፡-...ከዓመጻም ብዛት የተነሳ የብዙ ሰዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች፡፡

ቤተሰብን የሚያስተሳስረው ደም ወይም ዘር ነው፡፡ ቤተ ክርስትያንም ቤተሰብ ነች፡፡ በቤተ ክርስትያን ቤተሰብነት ውስጥ ግን ማሰሪያና ቤተ ክርስትያኒቱን አንድ የሚያደርጋት፣ ሰዎችን የሚሰበስበው፣ ፍቅር ነው(ማለትም ያ የሚታገሰው፣ ቸርነትን የሚያደርገው፣ የማይቀናው፣ የማይመካው፣ የማይታበየው፣ የማይገባውን የማያደርገው፣ የራሴን ካልሰጣችሁኝ የማይለው፣ የማይበሳጨው፣ በደልን የማይቆጥረው፣ ከእውነት ጋር ደስ የሚለው እንጂ ስለ ዓመጻ ደስ የማይለው፣ ሁሉን የሚታገሰው፣ ሁሉን የሚያምነው፣ ሁሉን ተስፋ የሚያደርገውና በሁሉ የሚጸናው ፍቅር ነው፡፡) ቤተ ክርስትያን ሰዎች ክብርን፣ ወይም ገንዘብን ወይም የትኛውንም አይነት ስጋዊ ፍላጎታቸውን ለማሟላት የሚሄዱባት አለማዊት ስፍራ ሳትሆን፣ በፍቅር እንደሚያወራ ቤተሰብ፣ ሰዎች በፍቅር እግዚአብሔርን የሚያወድሱባት፣ የሚያመልኩባት፣ የሚዘምሩባት፣ የሚማማሩባት፣ በፍቅር የሚተናነጹባት፣ የሚገሳጸጹባት፣ ሁሉን መንፈሳዊ ነገር የሚያደርጉባት የጻዲቃን ጉባኤ ነች፡፡
ፍቅር ከሌለን ክርስቶስ በኛ መሃል አይኖርም፡፡ ክርስቶስ የሌለበት ቤተ ክርስትያን ደግሞ የለም፡፡ ፈላስፎች የሰውን ህልውና አላማ ይጠይቃሉ፡፡ መልሱም ፍቅር ነው፡፡ የየውሃት ፍቅር፡፡ የተፈጠርነውም፣ የምንኖረውም የምንሞተውም ስለ ፍቅር መሆን አለበት፡፡ የእግዚአብሔር ፍቅር፣ የባልንጀራ ፍቅር፡፡ ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን አያውቅም፣ እግዚአብሔር ፍቅር ነውና ይላልና ቃሉ፡፡
አንድ ያነበብኩት ጽሁፍ እንዲህ ይላል፡ people were created to be loved. Things were created to be used. The reason why the world is in chaos is because things are being loved and people are being used. (ሰዎች የተፈጠሩት እንድንወዳቸው ነበረ፡፡ ነገሮች(ቁሳቁሶች) የተፈጠሩት እንድንጠቀምባቸው ነበረ፡፡ ዓለም አሁን በምጥ ውስጥ ያለችው፣ ቁሳቁሶች እየተወደዱ፣ ሰዎች ደግሞ ለመጠቀሚያነት እየዋሉ ስላሉ ነው፡፡)

ማጠቃለያ

2 ጢሞቴዎስ 3፡1-10፡-
ነገር ግን በመጨረሻው ቀን የሚያስጨንቅ ዘመን እንደሚመጣ ይህን እወቅ፡፡ ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉና፣ ገንዘብን የሚወዱ፣ ትምክህተኞች፣ ትዕቢተኞች፣ ተሳዳቢዎች፣ ለወላጆቻቸው የማይታተዘዙ፣ የማያመሰግኑ፣ ቅድስና የሌላቸው፣ ዕርቅን የማይሰሙ፣ ሐሜተኞች፣ ራሳቸውን የማይገዙ፣ ጨካኞች፣ መልካም የሆነውን የማይወዱ፣ ከዳተኞች፣ ችኩሎች፣ በትዕቢት የተነፉ፣ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉ፡፡ **የአምልኮት መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል፡፡** ከእነዚህ ደግሞ ራቅ፡፡ ወደ ቤቶች ሾልከው እየገቡ፣ ኃጢአታቸው የተከመረባቸውን በልዩ ልዩ ምኞትንም የሚወሰዱትን ሁልጊዜም እየተማሩ እውነትን ወደ ማወቅ ሊደርሱ ከቶ የማይችሉትን ሞኞችን ሴቶች የሚማርኩ፣ ከእነዚህ ዘንድ ናቸውና፡፡ ኢያኔስና ኢያንበሬስም ሙሴን እንደ ተቃወሙት፣ እንዲሁ እነዚህ ደግሞ አእምሮአቸው የጠፋባቸው ስለ እምነትም የተጣሉ ሰዎች ሆነው፣ **እውነትን ይቃወማሉ፡፡** ዳሩ ግን የእነዚያ ሞኝነት ደግሞ ግልጥ እንደ ሆነ፣ ሞኝነታቸው ደግሞ ለሁሉ ይገለጣልና ከፊት ይልቅ አይቀናላቸውም፡፡ አንተ ግን ትምህርቴንና አካሄዴን፣ አሳቤንም እምነቴንም ትዕግስቴንም ፍቅሬንም መጽናቴንም ስደቴንም መከራዬንም ተከተልህ፡፡
(This know also, that in the last days perilous times shall come. For men shall be lovers of their own selves, covetous, boaster, proud, blasphemers, disobedient to parents, unthankful, unholy, without natural affection, trucebreakers, false accusers, incontinenent, fierce, despisers of those that are good, traitors, heady, highminded, lovers of pleasures more than lovers of God; *having a form of godliness, but denying the power thereof:* from such turn away. For of this sort are they which creep into houses, and lead captive silly women laden with sins, led away with divers lusts, Ever learning, and never able to come to the knowledge of the truth. Now as Jannes and Jambres withstood Moses, *so do*

these also resist the truth: men of corrupt minds, reprobate concerning the faith. But they shall proceed no further: for thou hast fully known my doctrine, manner of life, purpose, faith, longsuffering, charity, patience.

1 ቆሮንቶስ 14፡37-38፡-1
ማንም ነቢይ ወይም መንፈሳዊ የሆነ ቢመስለው ይህች የጻፍሁላችሁ የጌታ ትእዛዝ እንደ ሆነች ይወቅ፡፡ ማንም የማያውቅ ቢኖር ግን አይወቅ፡፡ (But if any man be ignorant, let him be ignorant.)

በተጨማሪ፡-
ማቴዎስ 10፡29-42፡-
...እንግዲህ አትፍሩ ከብዙ ድንቢጦች እናንተ ትበልጣላችሁ፡፡ ስለዚህ በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ፡፡ በሰው ፊትም የሚክደኝን ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እክደዋለሁ፡፡ በምድር ላይ ሰላምን ለማምጣት የመጣሁ አይምሰላችሁ፡፡ ሰይፍን እንጂ ሰላምን ለማምጣት አልመጣሁም፡፡...

ማቴዎስ 11፡15 13፡9፣ 9፡43፣ ማርቆስ 4፡9፣ 4፡23፣ 7፡16፣ ሉቃስ 8፡8፣ 14፡35 ራዕይ 13፡9፡-
የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ፡፡
ራዕይ 2፡7፣ 2፡11፣ 2፡17፣ 2፡29፣ 3፡6፣ 3፡13፣ 3፡22፡-
መንፈስ ለአብያተ ክርስትያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ፡፡

ክርስትናና ታሪክ

ጥያቄ የለውም፡፡ ሃይማኖት ውስጥ የተወሳሰቡ፣ የሚያጨቃጭቁ፣ የቱን ይዘን የቱን እንደምንጥል ግራ የሚያጋቡን፣ የትየለሌ ጉዳዮች አሉ፡፡ አንድ ልጅ አንዴ "አሁንስ ስለ ሃይማኖት ማሰብ ታከተኝ" ብሎአል፡፡ አዎ፣ ይታክታል፡፡ በርግጥ ከዚህ አንጻር ሲታይ ብዙ በአንድ ሃይማኖት ስር ተመሳሳይ ዶክትሪን የሚያራምዱ ሰዎች በአንድ ተቋም ስር መግባታቸው ቀርቶ፣ እያንዳንዱ ሰው በሀሳቡ ውስጥ የተለያዩ ተቋማት አለመመስረቱ ነው የሚገርመው፡፡ ስለዚህ ሳወራ ልጠቅሳቸው የምፈልገው ሶስት እውነትና ህያው የሆነው የእግዚአብሔር ቃል ጥቅሶችን መሰረት ያደረጉ ነጥቦች አሉ፡

1. ገላትያ 5፡19-21፡- *የሥጋ ስራም የተገለጠ ነው እርሱም ዝሙት፣ ርኩሰት፣ መዳራት፣ ጣኦትን ማምለክ፣ ምዋርት፣ ጥል፣* **ክርክር፣** *ቅንዓት፣ ቁጣ፣ አድመኛነት፣* ***መለያየት፣*** *መናፍቅነት፣ ምቀኝነት፣ መግደል፣ ስካር፣ ዘፋኝነት፣ ይህንም የሚመስል ነው፡፡ አስቀድሜም እንዳልሁ እንደዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም፡፡*
   መለያየት የሚለውን የአማርኛ ቃል እንግሊዘኛው መጽሐፍ ቅዱስ "heresy" ይለዋል፡፡ ይሄም ሀሳቡ ክርስትናን በየቦታው ከሚከፋፍሉ ትምህርቶች ጋር የተያያዘ መሆኑን ያሳየናል፡፡ በተለያዩ ተቋማት መከፋፈልም የስጋ ፍሬ እንጂ የመንፈስ እንዳልሆነ ያስገነዝበናል፡፡
2. እዚያው ገላትያ ምዕራፍ 15፣ ከፍ ብሎ ከቁጥር 17-18 ላይ፣ *"ሥጋ በመንፈስ ላይ፣ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ፡፡ ስለዚህም ምትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም፡፡ በመንፈስ ብትመሩ ግን ከሕግ በታች አይደላችሁም"* ይላል፡፡ ዝቅ ብሎ ከቁጥር 24-25 ላይ ደግሞ "የክርስቶስ ኢየሱስም የሆኑቱ *ሥጋን* ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ሰቀሉ፡፡ በመንፈስ ብንኖር በመንፈስ ደግሞ እንመላለስ፡፡" ይላል፡፡
   ከዚህ ቃል ደግሞ እውነተኛ ክርስትያኖች ስጋን ከክፉ መሻቱና ምኞቱ ጋር የሰቀሉ፣ እንደሆኑና ሕግና *ሥጋ* በነሱ ላይ ስልጣን እንደሌላቸው፣ የመንፈስ ፍሬንም እንደሚያደርጉ ይነግረናል፡፡ በአንጻሩ ስጋና መንፈስን በአንድ ላይ ማስኬድ እንደማይቻል ያስረዳናል፡፡ ስጋና መንፈስን አንድ ላይ ለማስኬድ ስናስብ፣ በሕግ በታች እንደሆንንና የምንወደውንም እንደማናደርግ ይናገራል፡፡ (ሮሜ 8፡13)፡፡
3. 1 ቆሮንቶስ 7-13፡- ነገር ግን እግዚአብሔር አስቀድሞ ከዘመናት በፊት ለክብራችን የወሰነውን፣ ተሰውሮም የነበረውን የእግዚአብሔርን ጥበብ በምሥጢር እንናገራለን፡፡ ከዚችም ዓለም ገዦች አንዱ እንኳ ይህን ጥበብ አላወቀም፡፡አውቀውስ ቢሆኑ የክብርን ጌታ ባልሰቀሉትም ነበር፡፡ *ነገር ግን፡- ዓይን ያላየችው፣ ጆሮም ያልሰማው በሰውም ልብ ያልታሰበው እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀው ተብሎ እንደተጻፈ፣ እንዲህ እንናገራለን፡፡ መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ስንኳ ሳይቀር ሁሉን ይመረምራልና ለእኛ እግዚአብሔር በመንፈሱ በኩል ገለጠው፡፡ በእርሱ ውስጥ ካለው ከሰው መንፈስ በቀር ለሰው ያለውን የሚያውቅ ሰው ማን ነው? እንዲሁም ደግሞ ከእግዚአብሔር የሆነውን መንፈስ እንጂ የዓለምን መንፈስ አልተቀበልንም፡፡ መንፈሳዊውን ነገር ከመንፈሳዊው ነገር ጋር አስተያይተን መንፈስ በሚያስተምረን ቃል ይህን ደግሞ እንናገራለን እንጂ የሰው ጥበብ በሚያስተምረን ቃል አይደለም፡፡*
   ሮሜ 8፡16፡- የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል፡፡

   ስለዚህ ይሄ ሁሉ ልዩነት የእግዚአብሔርን ቃል በአለም ሂሳብና በሎጂክ ባበደ አዕምሮአችን ለመተርጎም ስንሞክር የመጣና እውነተኛ ክርስትያን ያለመሆንና ስጋን ያለመተው ውጤት ነው ማለት ነው፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ሳይሆን የሰው ጥበብ ባስተማረን አስተሳሰብ መንፈሳዊውን ቃል ስንመረምር ሁሌም፣ ጥርጥር፣ ክርክርና መለያየቶች አይለዩንም፡፡(ሮሜ 12፡2)፡፡ ይሄም ከሃይማኖት እያራቅን፣ ትኩረታችንን ከክርስቶስ ወደ እምነት ተቋማችን መልሶ፣ ሃይማኖትን በጣም አከራካሪ፣ መቋጫ የሌለው ክርክር የሚያስነሳ ርዕስ አድርጎ፣ በእምነቱ ከመኖር ይልቅ አንብቦ፣ የበለጠ አሳማኝ ለመሆን በመሞከር አባዜ ውስጥ ከትቶ የሰይጣን መጠቀሚያ ያደርጋል፡፡ መንፈስ ግን ተከራክረን ሰውን የምናሳምንበትን እውቀት ሳይሆን በእምነት ጸንተን የምንኖርበትንና ወደ እውነት የምንመራበትንና የምንመራበትንም ጥበብ ነው የሚሰጠን፡፡ በአለም የታሰረ አዕምሮ ደግሞ ቃሉን አጣምሞ፣ ጠፍቶ ሌላውንም ያጠፋል፡፡

   የታሪክ ተመራማሪዎች ዘመናትን የጨለማ ዘመን፣ መካከለኛው ዘመን፣ የሰለጠነው ዘመን፣ ሬኔሳንስ፣ ሪፎርሜሽን… እያሉ በታሪክ ውስጥ ካላቸው አንደምታ አንጻር ይከፋፍላሉ፡፡ ታሪክ የሚያጠና ሰው ሁሉ በመቼት ላይ ተመስርቶ ነው፡፡ በተለያዩ ጊዜያትና ቦታዎች የተለያዩ ታሪኮች ተጽፈዋል፡፡ የእግዚአብሔርን ልጅ ስጋ ለብሶ ወደዚህ አለም መምጣት፣ መሰቃየት፣ መሞትና መነሳት ግን አለም ልታድበሰብስና ውሸት ልታስመስል ምንም ያህል ብትሞክር፣ እውነቱ ግን ዓለም በጣም አስፈላጊ፣ ድንቅ ከምትለው አጋጣሚ ሁሉ በላይ ልቆ እስከ መጨረሻው ይዘልቃል፡፡(ማቴዎስ 24፡14)፡፡

ሰዎች በታሪክ ውስጥ ለእውነቱ ያሳዩትን አቀባበል ዛሬ ላለን ክርስትያኖች የሚያስተምረን ነገር ካለ እንደሁ እስኪ እንመርምር፡፡

የመስፋፋትና የመሰደድ ዘመን

ጌታችንና መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅን ለማድረግ በመጥምቁ ዮሐንስ ከተጠመቀና ለአርባ ቀንና አርባ ሌሊት ከጾመና በዲያብሎስም ከተፈተነ በኋላ "ከዚያ ዘመን ጀምሮም ኢየሱስ፡- መንግስተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ እያለ ይሰብክ ጀመር፡፡"(ማቴዎስ 4፡17)፡፡ ሰዎች አጥማጆች የሚያደርጋቸውን ደቀ መዛሙርቱንም ጠራቸው፡፡ እነርሱም ሁሉን ትተው ተከተሉት፡፡ ኢየሱስ በምድር ላይ አገልግሎት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ በቅርቡ እንደሚመለስ ተናግሮ፣ መንፈስ ቅዱስንም ሊልክልንና ወደ አባቱ ሊመለስ ወደ ሰማይ እስካረገበት ጊዜ ድረስ አብረውት ነበሩ፡፡ ሲማሩ፣ ሲጠይቁት፣ የተለያዩ ተአምራቶችን ሲያደርግ አይተዋል፡፡ ተቆጥቷቸዋል፣ ዝቅ ብሎም እግራቸውን አጥቦላቸዋል፡፡ መከራን ሊቀበል ጊዜው እንደ ደረሰ ሲነግራቸውና ሁሉም ደቀ መዛሙርቱ እንደሚሰናከሉበት ሲነግራቸው፣ ጴጥሮስ፣ "ሁሉም በአንተ ቢሰናከሉ እኔ በአንተ አልሰናከልም" ያለው ክርስቶስን ሶስት ጊዜ የሚክደው ሆኖ ተገኘ፡፡ ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ ሲጠመቁና እግዚአብሔርም መንፈሱን ሲልክላቸው፣ እንደ ገና ተወለዱ፡፡ ከሃዲያን ሳይሆኑ እስከ መገደል በቃሉ ጸኑ፡፡ ጸጋው ከሃዲውን ታማኝ አደረገ፡፡ እንኳንስ በክርስቶስ ለመማርና፣ የቤተ ክርስትያን አሳዳጅ የነበረውን ሰው ጸጋው፣ በጥበብና በእግዚአብሔር እውቀት ሞላው፡፡ ጸጋው እንከናቸውን አስወግዶ ደቀ መዛሙርቱን የቃሉ እውነተኛና ጽኑ አገልጋዮች ሲያደርጋቸው፣ እግዚአብሔር ለገንዘብ ወዳድ አማኞች ቦታ እንደሌለው ደግሞ ከይሁዳና በሐዋርያት ስራ ምዕራፍ 5 ላይ ከተጠቀሰው የአናንያና የሰጲራ ታሪክ እንማራለን፡፡ ለሁለት ጌቶች መገዛት አይቻልም፡፡

"እግዚአብሔር ትዕግስተኛ፣ ኃይሉም ታላቅ ነው፣ በደለኛውንም፡- ንጹህ ነህ አይልም፡፡ እግዚአብሔር በወጀብና በዐውሎ ነፋስ ውስጥ መንገድ አለው፣ ደመናም የእግሩ ትቢያ ነው፡፡ ባሕሩንም ይገሥጻታል፣ ያደርቃትማል፣ ወንዞቹንም ሁሉ ያደርቃል፡፡ ባሳንና ቀርሜሎስም ላልተዋል፣ የሊባኖስም አበባ ጠውልጎአል፡፡ ተራሮችም ከሱ የተነሳ ታወኩ፣ ኮረብቶችም ቀለጡ፡፡ ምድርና ዓለም የሚኖሩበትም ሁሉ ከፊቱ ተናወጡ፡፡ በቁጣው ፊት የሚቆም ማን ነው? የቁጣውንም ትኩሳት ማን ይታገሳታል? መዓቱ እንደ እሳት ይፈስሳል፣ ከእርሱም የተነሳ ዓለቶች ተሰነጠቁ፡፡ እግዚአብሔር መልካም ነው፣ በመከራ ቀንም መሸሸጊያ ነው፡፡ በእርሱ የሚታመኑትንም ያውቃል፡፡" ናሆም 1፡3-7

በርግጥ በሐዋርያት ስራ ምዕራፍ 4 መጨረሻና ምዕራፍ 5 መጀመሪያ ላይ የተጻፈው ታሪክ፣ ቤተ ክርስትያን እንዴት መኖር እንዳለብን እንድንማርበት እንጂ እንዳመላችን እንድንሸቃቀጠውና እንድናጣምመው አይደለም የተጻፈልን፡፡ ሐዋርያት 4፡32-37፡ *"ያመኑትም ህዝብ አንድ ልብ አንዲትም ነፍስ ነበሩአቸው፡፡* ገንዘባቸውም ሁሉ በአንድነት ነበረ እንጂ ካለው አንድ ስንኳ የራሱ እንደ ሆነ ማንም አልተናገረም፡፡ ሐዋርያትም የጌታን ትንሳኤ በታላቅ ኃይል ይመሰክሩ ነበር፡፡ በሁሉም ታላቅ ጸጋ ነበረባቸው፡፡ በመካከላቸው አንድ ስንኳ ችግረኛ አልነበረምና፡፡ መሬት ወይም ቤት ያላቸው ሁሉ እየሸጡ የተሸጠውን ዋጋ ያመጡ ነበርና፡፡በሐዋርያትም እግር አጠገብ ያኖሩ ነበር፡፡ ማናቸውም እንደሚፈልግ መጠን ለእያንዳንዱ ያካፍሉት ነበር፡፡ ትውልዱም የቆጵሮስ ሰው የነበረ አንድ ሌዋዊ ዮሴፍ የሚሉት ነበረ፣ እርሱም በሐዋርያት በርናባስ ተባለ ትርጓሜውም የመጽናናት ልጅ ነው፡፡ እርሻም ነበረውና ሸጦ ገንዘቡን አምጥቶ ከሐዋርያት እግር አጠገብ አኖረው፡፡"

ዕብራውያን 13፡1-10፡- ...5 አካሄዳችሁ ገንዘብን ያለመውደድ ይሁን፣ *ያላችሁም ይብቃችሁ፡፡* እርሱ ራሱ፡- አልተውህም ከቶም አልለቅህም ብሎአልና፡፡ ስለዚህ በድፍረት፡- ጌታ ይረዳኛልና አልፈራም፡፡ ሰው ምን ያደርግላኛል? እንላለን፡፡ 7 ***የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩችሁን ዋናዎቻችሁን አስቡ፣ የኑሮአቸውንም ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሉአቸው፡፡*** *ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ዘላለምም ያው ነው፡፡ ልዩ ልዩ ዓይነት በሆነ በእንግዳ ትምህርት አትወሰዱ፡፡ ልባችሁ በጸጋ ቢጸና መልካም ነው እንጂ በመብል አይደለም፡፡ በዚህ የሚሰሩባት አልተጠቀሙምና፡፡ 10 መሠዊያ አለን፣ ከእርሱም ሊበሉ ድንኳኒቱን የሚያገለግሉ መብት የላቸውም፡፡ (ቁጥር 10 በጣም ቅኔነት ይስተዋልበታል)፡፡*

ይሁዳ፣ አናንያና ሰጲራ በገንዘብ ፍቅር ምክንያት ከሞቱ፣ ዛሬ ሰዎች ስለ ገንዘብ የሰው ስጋ ለመዘልዘል ወደ ኋላ በማይሉበትና ወንጌሉ እንደ ባንክ ደብተር መታሰብ በጀመረበትና ቤተ ክርስትያን ባንክ ቤት በመሰለችበት ዘመን ለገንዘብ ያለን ፍቅር ለምን አልፈጀንም ብለህ ልትጠይቀኝ ትችላለህ፡፡ ቃሉ እንዲህ ይላል፡ "እርሱ ግን መልሶ እንዲህ አላቸው፡- በመሽ ጊዜ፡- ሰማዩ ቀልቶአልና ብራ ይሆናል ትላላችሁ፡፡ ማለዳም፡- ሰማዩ ደምኖ ቀልቶአልና ዛሬ ይዘንባል ትላላችሁ፡፡ የሰማዩን ፊትማ መለየት ትችላላችሁ፡፡ የዘመኑንስ ምልክት መለየት አትችሉምን? ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክት ይሻል፣ ከነቢዩም ከዮናስ ምልክት በቀር ምልክት አይሰጠውም፡፡" ማቴ. 16፡4፡፡

2 ቆሮንቶስ ምዕራፍ 8ም ገንዘባችንን ምን ላይ ማዋል እንዳለብን ይናገራል፡፡ በዚህ ክፍል ቁጥር 9 ላይ "የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስ ቸር ስጦታ አውቃችኋልና፡፡ ሀብታም ሲሆን፣ እናንተ በእርሱ ድህነት ባለ ጠጎች ትሆኑ ዘንድ ስለ እናንተ ደሃ ሆነ፡፡" የሚለውን ጥቅስ የባለ ጠግነት

ትምህርት አስተማሪዎች፣ እነኛን በፊት ያነበብካቸውን በግልጽ የተጻፉ ጥቅሶች ለማፋለስ ይጠቀሙበታል፡፡ 2 ቆሮንቶስ 8 ሙሉውን ስናነብ ግን ጳውሎስ ባለ ጠግነትን መስበክ ፈልጎ ያንን ቃል ለቆሮንቶስ ሰዎች እንዳልጻፈ እንረዳለን፡፡ ምዕራፉ እንዳለ ስለ ፍቅር፣ ስለ መስጠትና ጎደሎን ስለመሙላት ነው፡፡ ቁጥር 8፡- ትእዛዝ እንደ ምሰጥ አልልም፣ ነገር ግን በሌሎች ትጋት በኩል የፍቅራችሁን እውነተኛነት ደግሞ ልመረምር እላለሁ፡፡

በርግጥ ቁጥር 15 ላይ "ብዙ ያከማቸ አላተረፈም፣ ጥቂትም ያከማቸ አላጎደለም፡፡" ይላል፡፡ ብዙ ገንዘብ ስላለን በእግዚአብሔር ፊት አንከበርም፣ ደሃ ስለሆንን በእግዚአብሔር ፊት አንናቅም፡፡ ክርስቶስ ደሃ የሆነው፣ የተናቀው፣ የተሰቃየውና የሞተው፣ እኛ በአለም ላይ እንድንከብርና ሀብታም እንድንሆን ሳይሆን ነፍሳችንን ሊያድን ነው፡፡ በክርስቶስ የዳንን ሁሉ ባለጠጋ ነን፡፡ የምንሰበስበው ገንዘብ ከሃይሞኖት ያርቀን እንደሆነ እንጂ ዋጋ የለውም፣ ትርፍም አይደለም፡፡(1 ጢሞ. 6፡10)፡፡ ትርፍ የሚሆነው፣ ለሌላቸው ያለስስት በፍቅር ብናካፍል ነው፡፡

ያ ጊዜ፣ ቤተ ክርስትያን ገንዘብን ክዳ ለእግዚአብሔር ብቻ መገዛት የቻለችበት ነበር፡፡ ለሁለት ጌቶች መገዛት እንደማንችል ይናገራል ቃሉ፡፡ ወይ ለእግዚአብሔር አሊያም የአዲስ ኪዳን ዘመን ጣኦት ለሆነው ለገንዘብ እንጂ፡፡ ያላቸውን ነገር ሁሉ ሸጠው፣ ባለ ጠጎች ምንም ከሌለው ጋር እኩል ይሆናሉ፡፡ ይሰራሉ፣ ሁሉም እንደሚፈልጉት መጠን ይከፋፈላሉ፡፡ ችግረኛም አልነበረም፡፡ ሰይጣን የተሸነፈበት ዘመን ነበረ፡፡ ከሁሉም የሚበልጠው ፍቅር ያሸነፈበት በአማኞች ልብ ላይ፣ እግዚአብሔር ብቻውን ከፍ ከፍ ያለበት፡፡

ሐዋርያት የሚነሳባቸውን ስደት በመንፈስ እርዳታ እየተቋቋሙ፣ ወንጌሉን መስበክ፣ ልጆችን ማፍራትና የክርስቶስን ቤተ ክርስትያን ማስፋፋት ጀመሩ፡፡ ክርስትያኖችም እየበዙ መጡ፡፡ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ክፍለ ዘመናት "ስለ አንተ ቀኑን ሙሉ እንገደላለን፣ እንደ ሚታረዱ በጎችም ተቆጠርን"(ሮሜ 8፡36) ተብሎ እንደ ተጻፈ ክርስትያኖች በተቀበሉት ወንጌል ጸንተው ተገደሉ፡፡ ነገር ግን የተቀበሉትን የእግዚአብሔር መንፈስ ወዳላመኑት እያስፋፉ፣ እያስተላለፉ፣ የክርስቶስን ቤተ ክርስትያን እያሳደጉ ነበር፡፡ አማኞች እየበዙ እየበዙ በመጡ ጊዜ "እንደ ክርስቶስ ትምህርት ሳይሆን፣ እንደ ሰው ወግና እንደ ዓለማዊ እንደ መጀመሪያ ትምህርት ባለ ፍልስፍና በከንቱም መታለል ማንም እንዳይማርካችሁ ተጠበቁ" የሚለው የጳውሎስ ምክር አልተለያቸውም ነበር፡፡

ቀስ በቀስ ወንጌሉ እየተሰራጨ መጣ፡፡ የክርስትያኖች መሰደድም እየቀነሰ መጣ፡፡ ማህበረሰቡ ክርስትናን እየተቀበለ ሲመጣ በክርስትያኖች ላይ የተደረገውን እገዳ ተነሳ፣ ክርስትና በሮማ ብሔራዊ ሃይማኖት እስከ መሆን ደረሰ፡፡

ከዚያም የግሪኮችን ፍልስፍና ያጠኑ ጠቢባን በአዲሱ ሃይማኖት ውስጥ የሃይማኖት መሪዎች እየሆኑ፣ የተለያዩ አከራካሪ ነጥቦችን እያነሱ፣ ለክርክር ሲጋበዙና ህዝቡን ለውዝግብ ሲያጋልጡት ነበር፡፡ የሮማ ቤተክርስትያንና ጳጳሷም መፋለሶችን ለማጥፋት ለሁሉም ቤተ-ክርስትያናት መሰረት የሆኑ ቀኖናዎችን ስታወጣ ነበር፡፡ በምዕራቡና በምስራቁ መካከል ልዩነቶች እየሰፉ በ11ኛው ክ.ዘ. ክርስትና በይፋ ለሁለት ተሰነጠቀ፡፡ የካቶሊክ ቤተ ክርስትያን ጳጳስ ከንጉሱ ጋር የሚነጻጸርና ያልተገደበ ስልጣን ሲሰጣቸው፣ ቤተ ክርስትያኒቱ ከስቃይ የሚያድን የተባለለትን ሀሰተኛ ወረቀት እስከ መሸጥ ደረሰች፡፡ በዚህ ጊዜ ክርክር የነበረው ከምስኪኑ ህዝቡ ይልቅ፣ ብዙ ገንዘብ ነክ፣ ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ጉዳዮችን በሚያስተዳድሩት የሃይማኖት መሪዎች መካከል ነበረ፡፡ በፍልስፍና ሲጠቁ የነበሩትም እነሱ ስለነበሩ፡፡ ከ11ኛው ክፍለ ዘመን የእግዚአብሔርን ቃል የበለጠ ግልጽ ለማድረግ፣ አዕምሮ ሊቀበለው በሚችለው መንገድ ለማብራራት እንዲቻል የሚደረገው ጥረት የሃይማኖት መሪዎቹን ለዓለማዊ አስተሳሰቦችና መተማመኖች አዕምሮአቸውን ከፈተ፡፡ የሃይማኖት መጽሐፍት ወደ ከተማ መውጣት መጀመራቸውንና የድሮ የግሪክ መጽሐፍት በብዙ ሰዎች እጅ መግባት መጀመራቸውን ተከትሎ ዩኒቨርሲቲዎች መስፋፋት ጀመሩ፡፡ ይኼ ፍልስፍና ሃይማኖትን በይፋ ተቀላቀሎ ነበር፡፡ እንዲህ እንዲህ እያለ ሬኔሳንስ መጣ፡፡ እንዲህ እንዲህ እያለ ማርቲን ሉተር ብቅ አለ፡፡

ከድጡ ወደ ማጡ

አይደለህም ሰዎች እንደሚሉት
አይደለህም ብዙዎች እንደሚናገሩት
አይደለህም ሁኔታ እንደሚያወራው
አይደለህም ሰነፍ እንደሚናገረው
ጌታዬ ቃልህ እንደ ሚልህ ነህ
እንደሚልህ ነህ ልክ እንደ ቃልህ፡፡
አይደለህም እናውቃለን ሚሉት እንዳሉት
አይደለህም ገንዘብን ሚከተሉት እንደሚናገሩት
ጌታዬ ቃልህ እንደሚልህ ነህ፡፡
እንደሚልህ ነህ፣ ልክ እንደ ቃልህ፡፡
አይደለህም ተቋምተኞች እንደሚሉት፣
አይደለህም ሰይጣን እንደከፋፈለን፣

ጌታዬ ቃልህ እንደሚልህ ነህ
እንደሚልህ ነህ፣ ልክ እንደ ቃልህ፡፡
በእውነት ለመረጠህ፣ ቅርብ ነህ፡፡
ቃልህ እንደሚልህ ነህ
በእውነት ለፈለገህ ትገለጣለህ፡፡
ጌታዬ ቃልህ እንደሚልህ ነህ
እንደሚልህ ነህ፣
በእውነት ለፈለገህ ትገልጠዋለህ፡፡

ህይወት ሁለት ጫፍ አላት፡፡ አንደኛው ጫፍ ሰዎች እግዚአብሔርን በመፍራት የሚኖሩበት፣ ሰዎች የሚተሳሰቡበትና በፍቅር የሚኖሩበት ነው፡፡ እብራዊ ህይወት(Hebraic life) ይባላል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ሰዎች ከራሳቸው በላይ የማያስቡበት፣ ስለሰዎች ምንም የማያስቡበት፣ ለጥቅማቸው ሰዎችን ከመግደል የማይመለሱበት፣ ፈሪሃ እግዚአብሔር የሌለበት፣ ህይወት ገንዘብ፣ ዝሙት የሆነበትና ምኞት የመጨረሻ የሰዎች የህይወት ግብ የሆነበት፣ ሰው በስሜቱ የሚነዳበት ህይወት ነው፡፡ ይሄ የራስ ወዳድነት ህይወት ደግሞ ሄለናዊ ህይወት(Hellenic life) ይባላል፡፡ ግሪኮችና ሮማውያን ክርስትና ከመስፋፋቱ በፊት ሲኖሩት የነበረውና ዛሬ ላይ አብዛኛው ዓለም እየኖረው ያለው ህይወት ነው፡፡ ይሄ ህይወት ስልጣኔና ባለጠግነትን ተከትሎ የሚመጣ ኑሮና የገንዘብና የአለማዊ ጥበብ ትርጉም መከፈቻና መዝጊያ ነው፡፡
አለማዊና መንፈሳዊ ህይወት ማለት ነው፡፡ ከክርስቶስ ወደ ምድር መምጣት ወዲህ አለም ቀስ በቀስ ከህብራዊ ህይወት ወደ ሄለናዊው በመሄድ አሁን ጫፍ ላይ ደርሳለች፡፡ በዘመናት መካከል አለም መንፈሳዊነትን ጥላ ሄለናዊነት ውስጥ ስትዳክር የለውጡ ምክንያት የሆኑ ሁኔታዎችና የለውጡ አራማጅ የሆኑ ታሪክ የማይረሳቸው ሰዎች አሉ፡፡ በዚህ ውስጥ እነጳውሎስ ለሰዎች ልብ የብርሃኑ አብሳሪዎች እንደነበሩ፣ ብርሃኑን ከሰው ልብ ውስጥ ያጠፉ የሃይማኖት ሰዎችም ደግሞ አሉ፡፡ በዘመናችን፣ በክርስቶስ ስም እንደሚነግዱት ነቢያት፡፡

አንድ ሰው በዓለም ጥበብ፣ ጠቢብ መሆን ጀመረ የሚባለው፣ ሃይማኖቱን ሲጠረጥር ነው፡፡ ክርስትናም ሆነ እስልምና ወይም የጣኦት አምልኮ፣ አንድ ሰው በአለም ጥበብ ሲለከፍ መጀመሪያ የሃይማኖቱን እውነተኛነት ጥያቄ ውስጥ ይከታል፡፡ ፕሌቶ "እነዚህ ጣኦታት፣ በዙብኝ፣ አንድ አምላክ ብቻ ነው ሊኖር የሚችለው" እንዳለው ማለት ነው፡፡ አንድ ክርስትያን በአለም እውቀት ሲለከፍ መጀመሪያ በስም ብቻ የሚያውቀው አምላክ ስለመኖሩ ይጠራጠራል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የሚጀምረው ከዘፍጥረት እንደሆነ፣ የአለም ጥበብም ስለ ፍጥረትና ስለ አፈጣጠር ከመጠየቅና እርግጠኛ ለመሆን ከመሞከር፣ ከመመርመር ነው የሚጀምረው፡፡ ከሚታዩት፣ እነባዮሎጂ፣ ፊዚክስ፣ ኬሚስትሪ ከሚያጠኗቸው፣ ከሚታዩት የእውቀት ዘርፎች አይደለም፡፡ ከማይደርስበት፣ ለመድረስ የተጋና ሲተጋ ዘመኑን ያባከነ እእምሮ ደግሞ ሊደርስበት የሚችለው፣ ሊያረጋግጠው የሚችለው አይከብደውም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን መርምሮ ሊደርስበት ሞክሮ ያቃተው አዕምሮ፣ ሌላውን መመርመር አያቅተውም፡፡ የማይቻለውን የሞከረ፣ የሚቻለው አያቅተውም፡፡ ችግሩ ከሃይማኖት ፈቀቅ ማለቱ ላይ ነው፡፡

ሉተር የካቶሊክ ቤተ ክርስትያን ከእውነቱ እንደ ራቀች አስተዋለ፡፡ ስህተት የሆነውን የካቶሊኮች ትምህርት በመተቸት፣ የጳጳሱን ስልጣን ተቃወመ፡፡ በአዲሱ የህትመት መሳሪያ የሉተርን መግለጫ አውሮፓ ተቀባበለች፡፡ ሉተር የዩኒቨርሲቲ ምሁራንን ለክርክር ጋበዘ፡፡ ትላልቅ ለውጦችን አደረገ፡፡

የነጻነት አቀንቃኝ የነበረው ማርቲን ሉተር "ጽድቅ በእምነት ብቻ" የሚለውን አዲስ ዶክትሪን ይዞ ሲመጣ ትልቁ ችግሩ በሮሜ 3፡28 "ሰው ያለ ሕግ ሥራ በእምነት እንዲጸድቅ እንቆጥራለንና" የሚለው ጥቅስ ላይ "ብቻ" የምትል ቃል መጨመሩ ነው፡፡ በእምነት ብቻ፡፡ ገንዘብ በመክፈል አይጸደቅም፣ በስራ አይጸደቅም፡፡ የሚጸደቀው በእምነት ብቻ ነው ከምትለው ሀሳብ ጀርባ የሃጢአትን ትርጉምና የጾምና የጸሎትን አስፈላጊነት ጥያቄ ውስጥ የሚከት አጥፊ ፍልስፍና አለ፡፡ ለዚህም ነው ፕሮቴስታንት ደካማ የጾም ባህል ያላት፡፡

የሉተር ትምህርት በዶክትሪን ደረጃ ከካቶሊኮቹ በጣም የተሻለ ነበር በርግጥ፡፡ የሉተር ትምህርት እዚህ ጋር ትክክል አልነበረም ከማለት ይልቅ ያልተሳካ ሙከራ፣ ያልተሳካ ሪፎርሜሽን ነበረ ማለቱ ይቀላል፡፡ ሰዎች ለአመጽና ለአለማዊ ፍላጎታቸው ማርኪያ ተጠቀሙበት፡፡ ከዚያ በኋላ ችግሮች፣ ነገሮችን ከድጡ ወደ ማጡ ወደሚባል አዲስ ምዕራፍ ነበር ያሸጋገሩት፡፡ በቀጣይ ዘመናት ሰዎች ለአለም ክፍት የሆነን አዲስ ሃይማኖት ማራመድ ጀመሩ፡፡ ካፒታሊስት አስተሳሰብና ህይወት ተንሰራፋ፡፡

ሪፎርሜሽን ህዝቡን ወደ ጽድቅ ሳይሆን በፊት ወዳልነበራቸው አመጸኛነትና ሰካራምነት ነበር የመራው፡፡ የማርቲን ሉተር ትምህርት ወደ መንፈሳዊነት ለመጠጋት የጠቀመ መታነፕ ሳይሆን፣ ስጋን ለመከተል ጥሩ ማሳበቢያ ነበር የሆነው፡፡ በሉተር የትውልድ ከተማ በዊተንበርግ

በተፈጠረው ቀውስ ማርቲን በጣም ተበሳጨ፡፡ "ሰካራሞች ሆነናል፣ በካቶሊክ ቤተ ክርስትያን ስር የተሻልን ክርስትያኖች ነበርን" እያለ በቤተ ክርስትያን ውስጥ ንግግር አደረገ፡፡ ከዚያ ነው ክረስትያን ነኝ የሚል ሰው፣ "እኔ አምኜአለሁ፣ ሃጢአቴ አይቆጠርብኝም" የሚልበት፣ ከጀርባው ሃጢአት ለማድረግ ነጻ ነኝ የሚል አይነት አዲስ እምነት የመጣው፡፡ እንደዚያ ከዚህ በኋላ ሃጢአት ማድረግ ትችላላችሁ እያለ ያስተማረ ሪፎርመር አልነበረም ሊሆን ይችላል፣ ግን ይሄ አዲስ ትምህርት እንዲህ ወዳለው አጥፊ አስተሳሰብ ነበር የመራው፡፡ የሪፎርሜሽን ትልቁ ችግር የሚያቀነቅናቸው ሀሳቦች እንከን ሳይሆን ሳይጠቅሳቸው አዳፍኖ ያለፋቸው ጠቃሚ ነጥቦች ናቸው፡፡ በካቶሊክ ቀሳውስት እንደ ተበዘበዘ ያሰበው ህዝብ በሉተር ትምህርት መረን ተለቀቀ፡፡

ሉተር የከፈተውን የጥፋት መንገድ መልሶ መዝጋት አልተቻለም፡፡ *"ይሄኛው ጥምቀትን አይቀበልም፣ ያኛው ቅዱስ ቁርባንን አይቀበልም፣ እንዲህና እንዲያ ይባላል፡፡ ቁጥር የሌላቸው ሃይማቶችና ቡድኖች አሉን፡፡ የሆነ ነገር ሲመኝና ህልም ሲያይ መንፈስ ቅዱስ ነው ያሳየኝ ይልና ነቢይ ካልሆንኩ ይላል፡፡"* በማለት በሪፎርሜሽኑ እንደ ተጸጸተ ገልጽዋል፡፡

ሉተር *"ገዢዎቹ፣ ከተሜዎቹ፣ ገበሬዎቹ፣ ሁሉም፣ ወንጌኑሉን ከኔም፣ ከቅዱስ ጳውሎስም የበለጠ እንደተረዱት ያስባሉ፡፡ አሁን፣ አስተዋዮች እንደሆኑና ከአስተማሪዎቻቸው የበለጠ እንዳወቁ ያስባሉ፣ ምን አይነት እምነት አላቸው?"* ሲልም ተናግሯል፡፡

እምነትና ስራ

ስናምን እንድናለን፣ ሃጢአታችን ሁሉ ይቅር ይባልልናል፡፡ ዮሐንስ 3፡16፡- "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና፡፡" ይላል፡፡ ማርቆስ 16፡16 ደግሞ "ያመነ የተጠመቀም ይድናል፡፡" ይላል፡፡ እምነት የክርስትና መሰረት ነው፡፡ ብዙ ሰዎች ከማመን በኋላ ሰላለው ነገር ይሳሳታሉ፡፡ አንዳንድ ሰዎች፣ ክርስቶስ የሞተው እኔ በምድር ላይ ዘና ብዬ እንድኖር ነው ይላሉ፡፡ እውነትም በስራና ህግን በማድረግ ሳይሆን በእምነት ብቻ የምንጸድቅ ከሆነ፣ ሃጢአት ታዲያ ምንድነው? በእምነት ብቻ የሚጸደቅ ከሆነ ለምን ይጾማል? ለምን ይጸለያል? ከሌሎች ቤተ ክርስትያናት ይልቅ የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስትያን በጣም ደካማ የጾም ባህል መያዟ ሉተርን ተከትለው የመጡ ትምህርቶች ውጤት ነው፡፡ በእምነት ብቻ የሚዳን ከሆነ የትኛውም የሚደረግን በጎ ስራ ሁሉ ከንቱ አያደርገውም? እውነት ነው፡፡ የሚዳነው በእምነት ብቻ ከሆነ የምንጾመውም ሆነ የምናደርገው ሌላ ነገር ከንቱ ነው፡፡ በእምነት መጽደቅ ዛሬም ዋነኛው ትምህርት ነው፡፡ ከዚያ ግን ስለ ሃጢአት የሚያብራራ ሰው የለም፡፡ በእምነት ትጸድቃለህ ብለን በአራት ነጥብ ስንዘጋው፣ አንድ እያልን ያለነው ነገር፣ ሃጢአት መስራት ችግር የለውም የሚል ነው፡፡ ለዚያም ነው የማርቲን ሉተር ዘመን ሰዎች ቁልቁል መሄድ የጀመሩት፡፡ ለዚያም ነው፣ በሃጢአት ውስጥ ስንዘፈቅ፣ የእግዚአብሔርን ፊት እንደመፈልና ንስሃ እንደ መግባት፣ እምነቴ አድኖኛል እያልን ራሳችንን የምናታልለው፡፡ እምነት አያድንም እያልኩኝ ነው ወይ? አይደለም፡፡ እምነት ሃጢአትን የማድረግ ፈቃድ እንዳልሰጠን ግን ቃሉን ሳናነብ እንኳን እንዲሁ ህሊናችን ያውቀዋል፡፡

ሁለት ትንቢታዊ ጥቅሶች:
2 ተሰሎንቄ 2፡9-12 "ይድኑ ዘንድ የእውነትን ፍቅር ስላልተቀበሉ ለሚጠፉ፣ የእርሱ መምጣት በተአምራት ሁሉና በምልክቶች በሐሰተኞች ድንቆችም በዓመጽም መታለል ሁሉ እንደ ሰይጣን አሠራር ነው፡፡ *ስለዚህም ምክንያት፣ በእውነት ያላመኑ ነገር ግን በዓመጽ ደስ ይላቸው የነበሩ ሁሉ ፍርድን እንዲቀበሉ፣ ሐሰትን ያምኑ ዘንድ እግዚአብሔር የስህተትን አሰራር ይልክባቸዋል፡፡"*

ምሳሌ 30፡12 "ለራሱ ንጹህ የሆነ የሚመስለው ከርኩስነቱ ያልጠራ ትውልድ አለ፡፡"

ዮሴፍ የሚባለው ጓደኛዬ 10ኛ ክፍል ላይ ስለ ት/ቤት ፓርቲ ጭፈራ ስናወራ "አንዳንድ ልጆች ከጨፈርኩ በኋላ ንስሃ እገባለሁ" ይላሉ አለኝ፡፡ ራሳቸውን ነው ሚያታልሉት አልኩት፡፡ አንዴ ደግሞ አንድ ልጅ በተኛበት ሞቶ ተገኝቶ ካንዲት ልጅ ጋር ስለሱ ስናወራ፣ "ከዚህ በኋላ ሁሌ ንስሃ ገብቼ ነው ምተኛው" አለችኝ፡፡ "ሞቼ ካደርኩስ? ብለሽ ነው?" ስላት አዎ አለችኝ፡፡ ቀን እንደፈለግሽ ስትሆኚ ውለሽ? ስላትም የሚያሳዝነው፣ "አዎ" አለችኝ፡፡ እነዚህ የትውልዳችን ንግግሮች ታዲያ ታሪካዊ አመጣጥ የላቸውም?

ካቶሊኮች በፍጹም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባልሆነ ዶክትሪን ደህንነትን በገንዘብ መግዛት እንደሚቻል ተናገሩ፡፡ ሉተር ደግሞ የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል በማጣመም መንጋውን ከድጡ ወደ ማጡ ከተተው፡፡

አንደኛ ነገር ሉተር ፈላስፋ ነበር፡፡ ሁለተኛ ነገር የሉተር ትምህርት በመለያየትና በክርክር ላይ የተመሰረተ ነበር፡፡ በመለያየትና በክርክር በመጣው ትምህርት ደግሞ ጥፋት እንጂ መንፈሳዊነት አይመጣም፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ ህዝብን የሚያጠፋና የሚያስት ትምህርት፣ ከእግዚአብሔር አይደለም፡፡

መዝሙር 127፥1፦ **እግዚአብሔር ቤትን ካልሠራ፣ ሠራተኞች በከንቱ ይደከማሉ፡፡ እግዚአብሔር ከተማን ካልጠበቀ፣ ጠባቂ በከንቱ ይተጋል፡፡**

ክርስቶስ ለጳውሎስ ያለ ምንም ትምህርት እውነተኛውን ትምህርት እንዲው ከገለጠለት፣ ለኛ ደግሞ አለምን ለመካድና በእውነቱ ብቻ ለመኖር እስከቆረጥን፣ እውነተኛውንና ወደ እውነት የሚመራውን መንገድና እውነተኛውን ቃሉን አይሰውርብንም፡፡
"ኢየሱስም ያመኑትን አይሁድ፦ እናንተ በቃሌ ብትኖሩ በእውነት ደቀ መዛሙርቴ ናችሁ፡፡ እውነትንም ታውቃላችሁ፣ እውነትም አርነት ያወጣችኋል አላቸው፡፡" (ዮሐንስ 8፥31-32)፡፡

እምነት የሃይማኖት(የክርስትና) መሰረት ነው፡፡ ያለ መሰረት የሚሰራን ቤት ግን ጎርፍ ያፈርሰዋል፡፡ ቤት መስራት ከመሰረት ይጀመራል፡፡ መሰረቱ ላይም የሚገነባ ነገር ይኖራል፡፡ ካመኑ በኋላ ደግሞ በቃሉ መኖር ያስፈልጋል፡፡

የሮሜ መልዕክት እምነትና ሃጢአትን እንዴት መረዳት እንዳለብን በስፋት ያስረዳናል፡፡ ከሮሜ 3 ጀምሮ ማንም ጻዲቅ እንደሌለና ሕግን በማድረግ ሳይሆን በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንደሚጸደቅ ይናገራል፡፡ እስከ ምዕራፍ 5 ድረስም ለአማኞች ስለ ተሰጠው ጸጋና መንፈስ ቅዱስ ይናገራል፡፡ ምዕራፍ 6 ደግሞ "እንግዲህ ምን እንላለን? ጸጋ እንዲበዛ በኃጢአት ጸንተን እንኑርን? አይደለም፡፡ ለኃጢአት የሞትን እኛ ወደ ፊት እንዴት አርገን በእርሱ እንኖራለን? ወይስ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን? እንግዲህ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሳ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ፣ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን፡፡ ሞቱንም በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን፡፡…10መሞትን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ለኃጢአት ሞቶአልና፡፡ በህይወት መኖርን ግን ለእግዚአብሔር ይኖራል፡፡…12እንግዲህ ለምኞቱ እንድትታዘዙ በሚሞት ሥጋችሁ ኃጢአት አይንገስ፡፡ 13ብልቶቻችሁንም የዓመጻ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለኃጢአት አታቅርቡ፣ ነገር ግን ከሙታን ተለይታችሁ በሕይወት እንደምትኖሩ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አቅርቡ፣ ብልቶቻችሁንም የጽድቅ የጦር እቃ አድርጋችሁ ለአግዚአብሔር አቅርቡ፡፡

ብዙ ሰዎች ዛሬም ክርስቶስ ይቅር ይለኛል በሚል ሰበብ በኃጢአት ውስጥ ይዘፈቃሉ፡፡ አንዳንዶች ኃጢአቴ አይቆጠርብኝም ይላሉ፡፡ አንዳንዶች እንደፈለጉ እየጨፈሩ፣ እየተዳሩ ውለው፣ ሊተኙ ሲሉ እግዚአብሔር ሆይ ይቅር በለኝ ይላሉ፡፡ አንዳንዶች እግዚአብሔር ይቅር እንደሚላቸው እያሰቡ እንደፈሉ ይሆናሉ፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔርን እናታልለው ዘንድ እግዚአብሔር ሰው አይደለም፡፡

እውነት ነው፡፡ በእምነት እንጂ በስራ አይዳንም፡፡ ምንም ያህል የሙሴን ህጎች ብናከብር በኢየሱስ ክርስቶስ እስካላመንን አንጸድቅም፡፡ ሰውም በህግ ገዢነት ከሃጢአት ነጻ መሆን እንዳልቻለ ሮሜ 3 ይናገራል፡፡ ክርስቶስ ግን ህግን በመፈጸም ከሃጢአት ቀንበር ነጻ አወጣን፡፡ አይሁዳውያን ከክርስቶስ በፊት፣ ህግን በማድረግ ለመጽደቅ ይሞክሩ ነበረ፡፡ ስጋ በህግ ስለምትገዛና ስጋ ጽድቅን ማድረግ ስላልተቻላት(ሮሜ 7፡19)፣ ጽድቅ ሆኖ የተቆጠረላቸውም እምነታቸው እንጂ ስራቸው አልነበረም፡፡ ለመጽደቅ የሚደረግ ጥረት ነበረ፡፡ ለመንጻት፡፡ ክርስቶስ ጽድቅን አድርጎ፣ ስለሃጢአታችንም ዋጋችንን ከፍሎ ሲሞትና ሲነሳ በኋላ ግን ህግን ሰበረ፡፡ በእርሱ ያመነም ከሃጢአቱ ሁሉ ይነጻል፡፡ ስናምን እንጸድቃለን፡፡ በእምነትና በጥምቀትም ከሃጢአት አገዛዝ ነጻ ወጥተን ቅዱስ መንፈሱን እንቀበላለን፡፡ አሁን የሚገዛን ህግ የለም፣ ሃጢአትን እየፈራን አንኖርም ማለት ግን ሃጢአትን እየሰራን እንደ ፈለግን እንኖራለን፣ እንደ ፈለግን እየኖርን ማታ እግዚአብሔር ሆይ ይቅር በለኝ እንላለን ማለት አይደለም፡፡(ሮሜ 6፡1)፡፡ ስናምን ጸደቅን፡፡ ለመጽደቅ ምንም ማድረግ አይጠበቅብንም፡፡ ጽድቅን ባደረገው በክርስቶስ ኢየሱስ ማመን ብቻ አጽድቆን ሃጢአታችንን ሁሉ ሽሮ ቅዱስ መንፈሱን አካፍሎናልና፡፡ በህግ የምንገዛ ሃጢአን ነበርን፣ ስናምን ግን በጸጋ የምንገዛ ጻድቃን ሆንን፡፡ ነጻን፡፡ እምነታችን ካነጻን ለመንጻት ሌላ ማድረግ የሚጠበቅብን ነገር የለም፡፡ በፊት ግን ንጹህ አልነበረም፡፡ ለመንጻት ብዙ ማድረግ ነበረብን፡፡ ያንን ግን ማድረግ አልቻልንም፡፡ ምክንያቱም በስጋችን የምንወደውን ሳይሆን የማንወደውን እናደርጋለንና፡፡ ስናምን ከሃጢአተኝነት ወደ ጻድቅነት ተሸጋገርን(ሮሜ 5፡1)፡፡ እንደ ገና ተወለድን፡፡ ስናምን ስጋችንን ከክርስቶስ ስጋ ጋር ሰቀልነው፡፡ አሁን በአዲስ በመንፈስ ኑሮ እንጂ በአሮጌው በህግ ኑሮ አንገዛም(ሮሜ 7፡6)፡፡ መንፈሳውያን እንጂ ስጋውያን ስላልሆንን ሃጢአት በእኛ ላይ አይሰለጥንም፡፡(ሮሜ 6፡22) ስለዚህ በሮሜ 8፡1-4 እንደ ተጠቀሰው በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት ኩነኔ የለባቸውም፡፡ በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት ሕግም ከሃጢአትና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶኛልና፡፡ ከስጋ የተነሳ ስለ ደከመ ለሕግ ያልተቻለውን፣ እግዚአብሔር የገዛ ልጁን በሃጢአተኛ ስጋ ምሳሌ በሃጢአትም ምክንያት ልኮ አድርጎአልና፡፡ እንደ መንፈስ ፈቃድ እንጂ እንደ ስጋ ፈቃድ በማንመላለስ በእኛ የሕግ ትእዛዝ ይፈጸም ዘንድ ሃጢአትን ኮነነ፡፡
ስለዚህ የሃጢአት ህግ አይገዛንም ማለት ስጋችንን በሰቀልነውና እንደ መንፈስ ፈቃድ እንጂ እንደ ስጋ ፈቃድ በማንመላለስ በእኛ የህግ ትእዛዝ ይፈጸም ዘንድ እንጂ እንደ ፈለግን መኖር እንድንችል ነው ማለት አይደለም፡፡ ነገር ግን ህጉን የምንፈጽመው ህግ ስለሆነ አይደለም፡፡ ህግ የስጋ ነው፣ ስጋ ደግሞ ሃጢአተኛ ነውና፡፡ ነገር ግን መንፈሳውያን እንጂ ስጋውያን ስላልሆንንና የእግዚአብሔርን መንፈስ ስለተቀበልንና በኛ ውስጥ ስለሚሰራ ነው፡፡

8፡5 እንደ ስጋ ፈቃድ የሚኖሩ የስጋን ነገር ያስባሉና፣ እንደ መንፈስ ፈቃድ የሚኖሩ ግን የመንፈስን ነገር ያስባሉ፡፡ ስለ ስጋ ማሰብ ሞት ነውና፣ ስለ መንፈስ ማሰብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው፡፡ ስለ ስጋ ማሰብ በእግዚአብሔር ዘንድ ጥል ነውና፡፡ ለእግዚአብሔር ሕግ አይገዛምና፣ መገዛትም ተስኖታል፡፡ በስጋ ያሉት እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኙት አይችሉም፡፡....14በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነኚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና፡፡...

ነገር ግን የተቀበልነውን መንፈስ ስለ ስጋ በማሰብ እንዳይገዛን፣ ጸጋውም እንዳይበዛልን ልናደርግ እንችላለን፡፡ ስጋና መንፈስ ይቀዋወማሉና፣(ገላትያ 5፡16-26) ለስጋችን ቦታ ከሰጠነው፣ ከመንፈስ ግዛት ስር ራሳችንን እያወጣን ነው ማለት ነው፡፡ ስለ ስጋ ስናስብ ራሳችንን ካወጣንበት ከህግ ግዛት ስር ራሳችንን እንከታለን፡፡ ያም የምንወደውን የማያስደርገን እና የማንወደውን የሚያስደርገን ይሄን ላድርግ ያንን ልተው እያልን ከራሳችን ጋር የምንሟገትበት ኩነኔ እንጂ ጽድቅ በሌለበት የሃጢአት ማዕበል ውስጥ ይከተናል፡፡ (1 ቆሮ. 3፡3) ራሳችንን ለስጋ ሀሳብ ባስገዛን መጠን የእግዚአብሔር መንፈስ እየራቀን እየራቀን ይሄዳል፡፡ የጾም ትርጉምም ይሄ ነው፡፡ ስጋችንን ስናዳክም መንፈሳችን ይበረታል፡፡

ሮሜ 12፡1፡- እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፣ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕያውና ቅዱስም መስዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፣ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው፡፡

አገልግሎት የሚጀምረው ሰውነታችንን ቅዱስ መስዋዕት አድርገን ከማቅረብ ነው፡፡ ከዚያ ቀጥሎ ነው ሌላው አገልግሎት፡፡ ጳውሎስ በርኅራኄ እለምናችኋለሁ ይለናል፡፡ ትንቢተ አሞጽ 5፡22-24፡- “የሚቃጠለውን መስዋዕታችሁና የእህሉን ቁርባናችሁን ብታቀርቡልኝም እንኳ አልቀበለውም፡፡ ለምስጋና መስዋዕት የምታቀርልኝን የሰቡትን እንስሶች አልመለከትም፡፡ የዝማሬህንም ጩኸት ከእኔ ዘንድ አርቅ፡፡ የመሰንቆህንም ዜማ አላዳምጥም፡፡ ነገር ግን ፍርድ እንደ ውሃ፣ ጽድቅም እንደማይደርቅ ፈሳሽ ይፍሰስ፡፡”

1 ቆሮንቶስ 6፡13-20፡- መብል ለሆድ ነው፣ ሆድም ለመብል ነው፡፡ እግዚአብሔር ግን ይህንም ያንም ያጠፋቸዋል፡፡ *ስጋ ግን ለጌታ ነው* እንጂ ለዝሙት አይደለም፡፡ ጌታም ለስጋ ነው፡፡ እግዚአብሔርም ጌታንም አስነሳ፣ እኛንም በሃይሉ ያስነሳናል፡፡ ስጋችሁ የክርስቶስ ብልቶች እንደ ሆነ አታውቁምን? እንግዲህ የክርስቶስን ብልቶች ወስጄ የጋለሞታ ብልቶች ላድርጋቸውን? አይገባም፡፡ ወይስ ከጋለሞታ ጋር የሚተባበር አንድ ስጋ እንዲሆን አታውቁምን? ሁለቱ አንድ ስጋ ይሆናሉ ተብሎአልና፡፡ ከጌታ ጋር የሚተባበር ግን አንድ መንፈስ ነው፡፡ ከዝሙት ሽሹ፡፡ ሰው የሚያደርገው ኃጢአት ሁሉ ከስጋ ውጭ ነው፡፡ ዝሙትን የሚሰራ ግን በገዛ ስጋው ላይ ሃጢአትን ይሰራል፡፡ ወይስ ስጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፡፡ ስለዚህ በስጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ፡፡

1 ቆሮንቶስ 3፡16-17፡- የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደ ሆናችሁ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን? ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እሱን ያፈርሰዋል፡፡ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነውና ያውም እናንተ ናችሁ፡፡

ስለዚህ በእምነት ብቻ መጽደቃችን አይደለም፡፡ ሮሜ 3፡31፡- “እንግዲህ ሕግን በእምነት እንሽራለንን? አይደለም፡፡ ሕግን እናጸናለን እንጂ፡፡” ይሄም ማለት ሕግን ሕግ ስለ ሆነ ልንፈጽመው እንተጋለን ማለት ሳይሆን ከሕግ እስራት አርነት ያወጣን ክርስቶስ፣ ሕግን የምንፈጽምበት መንፈሳዊ ሃይል ይሰጠናል፡፡ አማኞች ከሙሴ ዘመን የበለጠ በቅድስና ሊኖሩ ይገባቸዋል፡፡ ክርስቶስም በማቴዎስ ምዕራፍ አምስት ስለዚያ ይናገራል፡፡
ማቴዎስ 5፡20፡- እላችኋለሁና፡- ጽድቃችሁ ከጻፎችና ከፈሪሳውያን ጽድቅ ካልበለጠ፣ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም፡፡
ይሄ የሉተር ዘመን ሰዎች ያልገባቸው ነገር ነበረ፡፡ በርግጥ ሉተርን ጨምሮ ሌሎችም በአለም ፍልስፍና ተማርከው ስለ ነበር፣ “እምነት ብቻ እንጂ ስራ አያጸድቅም” ጥሩ መሰናከያ ቴክኒክ ነው፡፡

ያዕቆብ 2(ሙሉው)፡26፡- ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደ ሆነ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው፡፡

ዮሐንስ 14፡15፡- “ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ፡፡”

ማርቆስ 3፡35፡- የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ፣ እርሱ ወንድሜ ነው እህቴም እናቴም ነው አለ፡፡

1 ቆሮንቶስ 10፡1-12፡- ወንድሞች ሆይ ይህን ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ፡፡ አባቶቻችን ሁሉ ከደመና በታች ነበሩ ሁሉም በባሕር መካከል ተሻገሩ፡፡ ሁሉም ሙሴን ይተባበሩ ዘንድ በደመናና በባሕር ተጠመቁ፡፡ ሁሉም ያን መንፈሳዊ መብል በሉ ሁሉም ያን መንፈሳዊ መጠጥ ጠጡ፡፡ ይከተላቸው ከነበረው ከመንፈሳዊ ዓለት ጠጥተዋልና፣ ያም ዓለት ክርስቶስ ነበረ፡፡ እግዚአብሔር ግን ከእነርሱ በሚበዙት ደስ አላለውም፣ በምድረ በዳ ወድቀዋልና፡፡ እነዚህም ክፉ ነገር እንደ ተመኙ እኛ ደግሞ እንዳንመኝ ይህ ምሳሌ ሆነልን፡፡ ሕዝብም ሊበሉ ሊጠጡም

ተቀመጡ፡፡ ሊዘፍኑም ተነሱ ተብሎ እንደ ተጻፈ ከእነርሱ አንዳንዶቹ እንዳደረጉት ጣኦትን የምታመልኩ አትሁኑ፡፡ ከእነርሱም አንዳንዶቹ እንደ ሴሰኑ በአንድ ቀንም ሁለት እልፍ ከሦስት ሺህ እንደ ወደቁ አንሴስን፡፡ ከእነርሱም አንዳንዶቹ ጌታን እንደ ተፈታተኑት በእባቦቹም እንደ ጠፉ ጌታን አንፈታተን፡፡ ከእነርሱም አንዳንድዶቹ እንዳንጎራጎሩ በሚያጠፋውም እንደ ጠፉ አታንጎርጉሩ፡፡ ይህም ሁሉ እንደ ምሳሌ ሆነባቸው፣ **እኛንም የዘመናት መጨረሻ የደረሰብንን ሊገስጸን ተጻፈ፡፡ ስለዚህ እንደ ቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ፡፡**

1 ዮሐንስ 3፡6-9፡- በእርሱ የሚኖር ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም፡፡ ኃጢአትን የሚያደርግ ሁሉ አላየውም አላወቀውምም፡፡ **ልጆች ሆይ ማንም አያስታችሁ፡፡** እርሱ ጻድቅ እንደ ሆነ ጽድቅን የሚያደርግ ጻድቅ ነው፡፡ ኃጢአትን የሚያደርግ ከዲያብሎስ ነው፣ ዲያብሎስ ከመጀመሪያ ኃጢአትን ያደርጋልና፡፡ ስለዚህ የእግዚአብሔርን ስራ እንዲያፈርስ የእግዚአብሔር ቃል ተገለጠ፡፡ ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም፣ ዘሩ በእርሱ ይኖራልና፡፡ ከእግዚአብሔርም ተወልዶአልና ኃጢአትን ሊያደርግ አይችልም፡፡

ማቴዎስ 7፡21፡- በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፣ ጌታ ሆይ፣ ጌታ ሆይ፣ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም፡፡

2 ጴጥሮስ 1፡1-12፡- የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያና ሐዋርያ የሆነ ስምዖን ጴጥሮስ፣ በአምላካችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅ ካገኘነው ጋር የተካከለ *የክብር እምነትን ላገኙ፡፡* የመለኮቱ ኃይል በገዛ ክብሩና በበጎነቱ የጠራንን በማወቅ፣ ለሕይወትና እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚሆነውን ነገር ሁሉ ስለ ሰጠን በእግዚአብሔርና በጌታችን በኢየሱስ እውቀት ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ፡፡ ስለ ክፉ ምኞት በዓለም ካለው ጥፋት አምልጣችሁ ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች በተስፋ ቃል እንድትሆኑ በእነዚያ ክብርና በጎነት የተከበረና እጅግ ታላቅ የሆነ ተስፋን ሰጠን፡፡ስለዚህም ምክንያት ትጋትን ሁሉ እያሳያችሁ በእምነታችሁ በጎነትን ጨምሩ፡፡ በጎነትም እውቀትን፣ በእውቀትም ራስን መግዛት፣ ራስንም በመግዛት መጽናትን፣ በመጽናትም እግዚአብሔርን መምሰል፣ እግዚአብሔርንም በመምሰል፣ የወንድማማችን መዋደድ፣ በወንድማማችም መዋደድ ፍቅርን ጨምሩ፡፡ *እነዚህ ነገሮች ለእናንተ ሆነው ቢበዙ፣ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እውቀት ሥራ ፈቶችና ፍሬ ቢሶች እንዳትሆኑ ያደጉአችኋልና እነዚህ ነገሮች የሌሉት እውር ነውና፣ በቅርብም ያለውን ብቻ ያያል፣ የቀደመውንም ኃጢአቱን መንጻት ረስቶአል፡፡ ስለዚህ ወንድሞች ሆይ መጠራታችሁንና መመረጣችሁን ታጸኑ ዘንድ ከፊት ይልቅ ትጉ፡፡* **እነዚህን ብታደርጉ፣ ከቶ አትሰናከሉምና፡፡ እንዲሁ ወደ ዘላለሙ ወደ ጌታችንና መድኃኒታችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥት መግባት በሙላት ተሰጥቶአችኋልና፡፡...**
ይሄ ጥቅስ የእምነትንና የስራን ቁርኝት ያሳየናል፡፡
እምነት፡ የሃይማኖት መሰረት ነው ብለናል፡፡
በእምነት በጎነትን መጨመር፡ በሀሊና መልካም ነገርን ማድረግ፣ አንድ ክርስትያን የሚጠበቅበትን፣ እግዚአብሔር የሚወደውን ማድረግ፡፡ ቃሉን መማርን ያጠቃልላል፡፡
በበጎነት እውቀትን መጨመር፡ ያ እግዚአብሔርን ለማወቅና እንደ ፈቃዱ ለመኖር የምናደርገው ትጋት፣ እውነተኛ እውቀትን ይሰጠናል፡፡
በእውቀት ራስን መግዛትን መጨመር፡ ያ መንፈሳዊ እውቀት ደግሞ ስጋን የምንክድበትን፣ የሥጋን ምኞት የምንገልበትንና ራሳችንን የምንገዛበትን ሃይል ያበዛልናል፡፡
ራስን በመግዛት፣ መጽናትን መጨመር፡ ራሳችንን ገዝተን ስንቆይ ደግሞ ጽናቱ ይበዛልናል፡፡ ከኃጢአት ጋር ተለያይተናል፣ መንፈሳዊ ሆነናል ማለት ነው፡፡
በመጽናት፣ እግዚአብሔርን መምሰል፡ በእምነት፣ በበጎነት፣በእውቀት፣ ራስን በመግዛትና በጽናት ጻዲቃን ስንሆን ደግሞ የእግዚአብሔርን መንፈስ ተካፍለናል፣ የኢየሱስ ክርስቶስን ጻድቅ ስጋ ለብሰናል ማለት ነው፡፡ ሃጢአት በኛ ላይ ስልጣን የለውም፣ መንፈሳውያን ሆነናል ማለት ነው፡፡
እግዚአብሔርን በመምሰል የወንድማማች መዋደድ፣ በወንድማማች መዋደድ ፍቅር፡ የመጨረሻው የሃይማኖት አላማ፡፡ የጠራ የጸዳ፣ ከክፋት የራቀ፣ አዲስ መንፈሳዊ ማንነት፣ የቀኝ ጉንጭ ቢመታ፣ የግራውን መስጠት፣ ለባልንጀራ መልካም ማሰብ፣ ከራስ ይልቅ፣ ለሌሎች መኖር፣ ጾም አድሮ፣ ሌላውን ማብላት የሚያስችል፣ መንፈሳዊ ደረጃ ላይ መድረስ፡፡
ታዲያ እነዚህን የሚያደርጉ፣ ከቶ አይሰናከሉም፡፡
እነዚህ ሁሉ የእምነት ፍሬዎች ናቸው፡፡ አምኖም ቢሆን እነዚህን ነገሮች የሌሉት እውር ነውና፣ በቅርብም ያለውን ብቻ ያያል፣ የቀደመውንም ኃጢአቱን መንጻት ረስቶአል፡፡ የክርስትና ሃይማኖት የበጎ ስራ መጀመሪያና መሰረት እንጂ ጭካኔ የተሞላበት ሃጢአት መሸፈኛ አይደለችምና፡፡

ከሉተር በኋላ ህዘቡ ጭራቅ ሆነ፡፡ በአመጻኛነት ብቻ አላበቃም፡፡ በአውሮፓ፣ ሰማያዊ ጽድቅን በእምነት ተቀዳጀሁ ያለው ሀገሬው፣ የምድርን ጽድቅ ደግሞ ማሰስ ጀመረ፡፡ ካፒታሊስት አስተሳሰቦችን የሚደግፉ የሃይማኖት መሪዎች ተፈጠሩ፡፡ ህዝቡ የክፋት ስር በተባለው በገንዘብ ፍቅር አይኑ ታወረ፡፡
ህይወትን የሚያቀሉ መሳሪያዎች እየተፈጠሩ፣ ምድራዊ ጥበብ እየጠለቀ፣ ብዙ መጽሐፍት እየተጻፉ፣ እየተሰራጩ፣ እውቀት በአንድ ወቅት ለንጉሳውያን ቤተሰብ ይገደብ እንዳልነበረ፣ ተራው ህዝብ ማንበብና ማወቅ፣ መማር ሲጀምር፣ የለውጡ ፍጥነትም እንደዚያው ፈጣን ሆነ፡፡ ቀስ በቀስ፣ ሰዉ ከሃይማኖቱ ይልቅ ለእውቀቱ እያደላ መጣ፡፡

በኢንላይትመንት ዘመን ሳይንሳዊ ፈጠራዎች ተጠናክረው ሲቀጥሉ፣ በማህበረሰቡ ላይ የፈጣን ለውጥ ማሳየት ጀመሩ፡፡ የአሜሪካና የፈረንሳይ አብዮቶች፣ ቀጣይ ለሚመጡ ብዙ አመጾች ምክንያት ሊሆኑ፣ ወደ ዘመናዊ ዲሞክራሲ የሚደረገውን ጉዞ አስጀመሩት፡፡ በኢንላይትመንት ዘመን ነበር ሴኪዩላሪዝም የሚለው ሀሳብ የተጠነሰሰው፡፡ ከዚያ፣ ሳይንሳዊ አብዮት፣ 19ኛው ክ.ዘ.፣ 20ኛው ክ.ዘ. የሰውን ህይወት ቀስ በቀስ እየቀየሩት መጡ፡፡

ትንቢተ ሕዝቅኤል 33፡30-32፡- አንተም የሰው ልጅ ሆይ፣ የሕዝብህ ልጆች በቅጥር አጠገብና በቤት ደጆች ውስጥ ስለ አንተ ይናገራሉ፣ እርስ በርሳቸውም፣ አንዱ ከአንዱ ጋር፡- እንሂድና እግዚአብሔር ያለው ቃል ምን እንደ ሆነ እንስማ ብለው ይናገራሉ፡፡ ሕዝብ እንደሚመጣ ወደ አንተ ይመጣሉ፣ እንደ ሕዝቤም በፊትህ ይቀመጣሉ፣ ቃልህንም ይሰማሉ ነገር ግን አያደርጉትም፡፡ ***በአፋቸው ብዙ ፍቅር ይገልጣሉ፣ ልባቸው ግን ስስታቸውን ትከተላለች፡፡*** *እነሆ፣ አንተ መልካም ድምጽ እንዳለው እንደሚወደድ መዝሙር ማለፊያም አድርጎ በገና እንደሚጫወት ሰው ሆነህላቸዋል፡፡ ቃልህንም ይሰማሉ ነገር ግን አያደርጉትም፡፡*

ሬማና ሎጎስ የሚለው መጽሐፍ ደራሲ ፓስተር ተዘራ ያሬድ "ሙብል ለሆድ ነው፣ ሆድም ለሙብል ነው፣ እግዚአብሔር ግን ይህንም ያንም ያጠፋቸዋል" የሚለውን ቃል ጠቅሶ "እስኪጠፋ ግን ብላ" ሲል ሰምቼው በጣም ነበር የተሸማቀቀኩት፡፡ እነዚህን ሰዎች ጀሮ ሰጥቼ ባዳምጣቸው ብዙ ጆሮዎቼን የሚያስደፍኑኝ ነገሮችን እንደምሰማ አውቃለሁ፡፡ ለዚህ ነው በእግዚአብሔር ስም ገንዘብን ይሰብካሉ የምለው፡፡ ፓስተር ሜርሲ ደግሞ አንዴ ባለጠግነትን ስታሞጋግስ፣ የሀብታም ልጅ አሪፍ መኪና ምንም አይመስለውም፣ ገንዘብ ያለው ራዕይ አለው እያለች ደሃን ስታናንቅና ሀብታምን ስታሞጋግስና ብዙ "መጽሐፍ ቅዱስ አምብባ አታውቅም" የሚያስብሉ ነገሮችን ስታወራ በኤልሻዳይ ቲቪ ሰማኋት፡፡ የሴት ፓስተር? እኔን ያናደዱኝ ተመስጠው የሚያዳምጧት ተመልካቾቿና ጣቢያው ራሱ፣ የዚህ ዘመን የኢትዮጵያ ክርስትያን ምሳሌዎች ናቸው፡፡ ይሄ ትክክል እንዳልሆነ ለማስረዳት የሰይጣን ስም መጠቀስ አለበት ማለት ነው? ሴጣኒስቶች ናቸው በሴት ፓስተር(ፐሪስተስ) የሚመሩት፡፡ ይሄ ለቃሉ አለመታዘዝ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርን መሳደብ ነው፡፡ ይሄኮ ክርስትያን ነን በምንለው ብቻ የሚደረግ ነው፡፡ በእግዚአብሔር የማያምኑት ሙስሊሞች አያደርጉትም፣ ሌላውም አያደርገውም፡፡ ሮሜ 2፡24 "በእናንተ ሰበብ የእግዚአብሔር ስም በአሕዛብ መካከል ይሰደባልና" ይላል፡፡ ትምህርቷ ደግሞ ስህተት ባይሆንስ? ስለ ሴት አስተማሪነትና ስለ ባለ ጠግነት ቃሉ በግልጽ ባይናገርስ? አ ኢትዮጵያ ተመለሺ፡፡

አ ኢትዮጵያ አይኖችሽን ግለጪ፡፡ አ ኢትዮጵያ ሌሎች ቃሉን አንሰማ ብለው ጠፉ፡፡ አንቺ ግን ለቃሉ አለመታዘዝ ብቻ ሳይሆን ያልታዘዙት የት እንደ ደረሱ እያየሽ አቅጣጫሽን እነሱ ከሄዱበት መንገድ፣ እርምጃሽን በግልጽ ከሚታየውና ገደል ከሚከተው የእነሱ ዳና ካልለየሽና ነቅተሽ መንገድሽን ወደ እግዚአብሔር አቅጣጫ ካልቀየርሽ፣ እመኚኝ ኢትዮጵያ፣ ያንቺ ከነሱ ይብሳል፡፡ እመኚኝ ኢትዮጵያ፣ ያንቺ እንጦሮንጦስ ከነሱ ይልቅ ይፈጃል፡፡

ዘፈንን ስለ መፍቀድ ቤተ ክርስትያን ውስጥ የሚከራከሩትስ? እኔን የሚያናድደኝ፣ መከራከራቸው ሳይሆን በቲቪ ላይ መቅረባቸው ነው፡፡ ሰው ምን እንዲማር ነው? ዘፈንን ለማጽደቅ መጽሐፍ ቅዱስን ሲመረምሩ፣ አትከራከሩ ስለሚለው ብዙ ቦታ ላይ ስለ ተጠቀሰው ቃል አላነበቡም?

የሰብኮንሸስና የኮንሸስነስ አስተማሪዎቹስ? ክርስትናኮ የሰውን ሳይኮሎጂ የመመርመርና የመፈላሰፍ፣ በእውቀት የመምጠቅ ሃይማኖት አይደለም፡፡

2 ጢሞቴዎስ 4፡3፡- ሕይወት የሚገኝበትን ትምህርት የማይታገሱበት ዘመን ይመጣልና፡፡ ነገር ግን ጆሮቻቸውን የሚያሳክክ ስለ ሆነ እንደ ገዛ ምኞታቸው ለራሳቸው አስተማሪዎችን ያከማቻሉ፡፡

በቻናሉ ላይ ፈላስፋ ጋብዞ ሚከራከረው ጀግና ሐዋርያስ? ድንቄም ሐዋርያ! ሐዋርያትማ ከፈላስፎችና ከከንቱ ክርክር እንድንርቅ መከሩን፡፡ የዘመናችን ሐዋርያት ደግሞ ፈላስፋ ጋብዘው ሌክቸር ይሰጡናል፡፡ "ፍልስፍና ሰው እንደሚያስበው መሸሽ ያለበት ነገር አይደለም" ትላለች፡፡ ያን ቀን ስፈላሰፍ ብላ ያወራቻቸውን ነገሮች እዚህ ጋር መጥቀስ፣ ጸረ-ሐዋርያት ዘላለምን መተባበር ይሆንብኛል፡፡ እሱማ ምሁርነቱን ሊያሳየን ነው ሀሳቡ፡፡ ዋው የፈላስፋዋን አፍ አስዘጋት፣ ለብቻው አስተሳሰቧ ምን እንደ ሆነ ሊጠይቃት ሲችል፣ በቲቪ የህዝቡን አዕምሮ መመረዝ ለምን እንዳስፈለገው እኔ አልገባኝም፡፡ ክርስቶስ ከክርክር ራቁ ነው ያለን፡፡ መንፈሳዊ ነገር በክርክር አይሆንም፡፡ በአለም ፍልስፍና አይመረመርም፡፡ በክርክር ለራሳችን ከሃይማኖት ልንርቅ እንጂ ሰውን ወደ ሃይማኖት ልናመጣ አንችልም፡፡ የሪፎርሜሽን ጦስ ሲወርድ ሲዋረድ መጥቶ ይኸው አሳፋሪ አስተማሪዎችና ተማሪዎችን ያፈራበት፣ ሰዎች ለአለማዊ ጥማታቸው ቃሉን እየሸቀቀጡ የሚማማሩበት ጊዜ ላይ ደርሰናል፡፡

Can a man of money be a man of God too? የገንዘብ ሰው የእግዚአብሔር ሰው ጭምር ሊሆን ይችላልን? I sincerely doubt that. በዚህ ዘመን ግን የተቻለ ይመስላል፡፡ ባይቻልም ሰዎች፣ ተቀብለነዋል፡፡

አንድ ቀን ከእናቴ ጋር ተቀምጠን የአንዱን የሐሰተኛ ነቢይ ቻናል እያየን ነው፡፡ ቻናሉ Elohi TV፡፡ ሰውየው ለቲቪው ሳተላይት አመታዊ ክፍያ ብር ማሰባሰቢያ ጥሪ እያደረገ ነው፡፡ 5 ሚሊየን ብር ያስፈልጋል አለ፡፡ ለአስር ሰው ብናካፍል 500,000 ብር ነው፣ ለ20፣ ለ50፣ ለ100፣ 500፣ እያለ ገንዘቡ ብዙ እንዳልሆነ ሊያስረዳ ሞከረ፡፡ እኔንና እናቴን የገረመን ግን "ብሩን ባንክ ካስገባችሁ በኋላ ባንክ ስቴትመንታችሁን ይዛችሁ ኑ፣ በቴሌቪዥን ላይ ስንት ብር እንደሰጣችሁ ከነስማችሁ እናገራለሁ፣ እጸልይላችኋለሁ፣ እግዚአብሔር የተናገረኝን መልእክት

እነግራችኋለሁ፡፡” ለጆሮ አይከብድም? ይሄስ የበግ ለምድ የለበሰ ነጣቂ ተኩላ ብቻ ሳይሆን ለምዱን የገለጠ ነጣቂ ተኩላ ነው፡፡ ጌታ ሆይ ዓይኖቻችንን ግለጥልን፡፡ ከነዚህ የሰይጣን መልእክተኞች እጅ አውጣን፡፡ አይኖቻችንን ከአለም አንስተን ወደ አንተ ብቻ እንድናይ አምላኬ ሆይ እርዳን፡፡

እግዚአብሔር ሀሳባችንን ያውቃል፡፡ ምን እንደምንፈልግም ያውቃል፡፡ ሉተርን ተከትሎ የመጣው ጥፋት ልቡ ከእግዚአብሔር ጋር ያልነበረ ትውልድ የተቀበለው ሽልማት ነው፡፡ ዛሬ ላይ ደግሞ ልቡን በአለማዊና በስጋዊ ነገሮች የጠመደ ትውልድ ሐሰተኛ ነቢያት እየገረፉለት ነው፡፡ ለአለማዊ ነገሮች፣ ወደ እግዚአብሔር ስንጮህ እግዚአብሔር ሰምቶ ያዝንብናል፡፡ ለጽድቁና ለዘላለማዊው ሳይሆን ለሚጠፋው ያለን ትጋት ያስቆጣዋል፡፡ ከዚያም እግዚአብሔር የሚኮራብትን ኢዮብን ሰይጣን እንዲፈትነው እንደፈቀደ፣ በኛ በማይኮራብን፣ በእውነት ባላመንን ደግሞ ሐሰትን እናምን ዘንድ የሰይጣንን የስህተት አሰራርን ይልክብናል፡፡ እንድን ዘንድ የእውነትን ፍቅር ስላልተቀበልን በተአምራትና በዓመጽም መታለል ሁሉ እንደ ሰይጣን አሰራር እንታለላለን፡፡ (2 ተሰሎንቄ 2፡9-12)

አንባቢ ሆይ እንደኔው በአለም ፍልስፍና የተጠመድክ ሰው ሆነህ ማርቲን ሉተር ለምን ሁሉንም ዓለማዊ ነገር ትቶ ለመንፈስ የሚኖርበትን የገዳም ህይወት “ተስፋ ማጣትን ያየሁበት” አንዳለ ጥያቄ ሊሆንብህ ይችላል፡፡ ምክንያቱም፡ ሉተር ልቡ ፈቅዶ ሳይሆን ለቅድስት አና የገባውን ስእለት ለመፈጸም ሲል ብቻ ነበር ገዳም የገባው፡፡ በመንፈሳዊነት ሊደሰቱና፣ በጥማትና፣ በረሃብ፣ በስደትና፣ በግርፋት፣ በጉስቁልና ውስጥ፣ እግዚአብሔርን እያመሰገኑ በደስታ፣ እስር ቤት ውስጥ ለአመታት ቢታሰሩ እንኳን ጸንተው፣ በዝማሬ የሚኖሩት፣ እቃቸውን ሽጠው፣ ለድሆች ሰጥተው ገዳም የገቡት፣ ቁሳዊ መስፈርቱን ብቻ ያሟሉት ሳይሆኑ፣ በሀሳባቸውም ስጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር አብረው የሰቀሉት ናቸው፡፡ የተውት አለማዊ ህይወት፣ ከሩቅ የሚያስጎመጃቸው አይደሉም፡፡ ከተውነው አለማዊ ሀብታችን ጋር ያንን አለማዊ ነገር የሚመኘውን ስጋችንንም መተው፣ መስቀልና፣ መንፈሳዊ መሆን ያስፈልጋል፡፡ “የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግስት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የውሃት፣ ራስን መግዛት ነው፡፡” (ገላትያ 5፡22) ተብሎ እንደ ተጻፈ ስጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር የሰቀሉት ሰላምና ደስታን ሲያገኙ፣ ሌሎቹ ግን ያንን ሰላምና፣ ደስታ፣ ትዕግስት ሊያገኙ አይችሉም፡፡ መንፈሳውያን በእስር ቤት ውስጥም ቢሆን፣ ታጋሽና ደስተኛ ሲሆኑ፣ አለማውያን ግን በእስር ቤት፣ ወይም ለስጋ በማይመች እንደ ገዳም አይነት ስፍራ ይሰቃያሉ፡፡ የአለማውያንና የመንፈሳውያን የደስታ ወንዞች ከተለያዩ ምንጮች ሲቀዱ፣ “እኔ ምሰጣችሁ ሰላም ዓለም እንደሚሰጥ አይደለም” ተብሎ እንደ ተጻፈ መንፈሳዊው ምንጭ፣ ዘላለማዊ ሲሆን የዓለማዊው የደስታ ምንጭ ግን ከንቱና ጊዜያዊ ነው፡፡ መንፈሳዊው የደስታ ምንጭ መንፈሳዊ ሰው፣ ነፍሱን የሚያድንበት ሲሆን፣ ዓለማዊው የደስታ ምንጭ ደግሞ ዓለማዊ ሰው ነፍሱን የሚያጠፋበት ነው፡፡

ድንገት ያነበብኩት/WHO IS THE REAL CHRIST (እውነተኛው ክርስቶስ ማን ነው?)

በፔጊ ካናዳይ (Peggy kannaday)

ብዙ ክርስትያኖች ግባችንና አላማችን ክርስቶስን መምሰል እንደሆነ እንስማማለን፡፡ ግባችን መሰቀላችንን ተሸክመን ኢየሱስን፣ ወደ ክርስቶስ እድገትና ሙላት ማደግ እንደሆነ፡፡

በእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው እንድንሆን ተነግሮናል፡

1. ክርስቶስን እንድንመስል፡ ሮሜ 8፡29፡- “ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኩር ይሆን ዘንድ፣ አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወሰናቸልና፡፡”

2. ይቺን ዓለም እንዳንመስል፡ ሮሜ 12፡2፡- “የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ፡፡”

3. ራሳችንን ክደን መስቀላችንን እንድንሸከም፡ ማቴዎስ 16፡24-25፡- “በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አለ፡- እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር፣ ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ፡፡ ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታል፤ ስለ እኔ ግን ነፍሱን የሚያጠፋ ያገኛታል፡፡”

4. እንድናድግ ወይም ክርስቶስን በማወቅ ወደሚገኝ ሙላት እንድንመጣ፡ ኤፌሶን 4፡12-13፡- “ሁላችን የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት፣ ሙሉ ሰውም ወደ መሆን፣ የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ፣…”

እነኚህን መሰረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የማያውቅና የማይስማማባቸው ክርስትያን መኖሩን አላውቅም። ነገር ግን ማንኛውን ክርስቶስ እንድንከተል ነው እየተመራን ያለነው? ማንኛውን ክርስቶስስ ነው እያደግንበት ያለነው? በምን አይነት ክርስትና ነው የምናምነው? ወንጌላችን የቱ ነው? እውነተኛውን ክርስቶስ፣ ትክክለኛውን ክርስትናና እውነተኛውን ወንጌል ለማግኘት ወደ እግዚአብሔር ቃል መሄድ ይኖርብናል።

ክርስቶስ በአንዳንዶች፣ ትዕቢትን፣ ትምክህትን፣ ስስትን፣ ራስ ወዳድነትን እንደሚደግፍ ተደርጎ ተስሏል። ክርስቶስ በዋናነት ቁሳዊ ትርፋማነታችንን፣ ዓለማዊ ባለ ጠግነታችንንና በዚህ ምድር ላይ ደስተኛ መሆናችን እንደሚፈልግ ሲነገር ይሰማል። ነገር ግን፣ እውነተኛው ኢየሱስ፣ ከአለም ጋር መዋደድ፣ ከእግዚአብሔር ጋር መጣላት እንደሆነ ነው የተናገረው። እርሱ ትምክህት መፍረስን፣ ትዕቢትም ውድቀትን እንደሚያስከትሉ ያውቃል። እርሱ ዓለማዊ ባለ ጠግነትን መውደድና መመኘት የጣኦት አምልኮ እንደሆነ ያውቃል። ገንዘብን መደውድ የክፉት ሁሉ ሥር እንደሆነ ያውቃል። ዓለማዊ ደስታ፣ ሰውየውን በማፈራረስ የሚጠናቀቁ ሁኔታዎች ላይ የተመረኮዘ እንደሆነ ያውቀዋል። የዓለም ፍቅር፣ የዝሙት አይነት ነው። የክርስቶስ ፍቅር ግን፣ ሙሉ በሙሉ ራስን ያለመውደድና(unselfish) ራስን የመስጠት ነው። የእግዚአብሔርን መንግስትና ጽድቁን መጀመሪያ የመፈለግ ነው።

ክርስቶስ በሙሉ ልቡ የሚያስተምረውም ሆነ የሚሰብከው ፍቅርን ነው። ምክንያቱም እርሱ ፍቅር ነው። ነገር ግን ከተገበርነው በሁሉም የህይወታችን ክፍል የርሱን ልብ እየተከተልን እንድንኖር የሚያደርገን፣ እግዚአብሔርን ማዕከል ያደረገ ፍቅር ነው። እርሱ ለኛ የሚያስበው ሁሌ መልካም ነው። ነገር ግን የእርሱ ሀሳብ ሁሌ ቅጽበታዊ ደስታን የሚያመጣልን አይደለም። የእርሱ መንገድ ሁሌ ለከፍተኛውና ለመጨረሻው ጥቅማችን እንጂ ለጠፊውና ለአላፊው፣ የጠፊውና የአላፊው አለም ጥቅማችን አይደለም።

በአንዳንድ መዘውሮች ሌላ ወንጌልን እየሠማን እንገኛለን። በሰው ምኞትና በአታላይ መናፍስት የተሸቃቀጠ ወንጌል። የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ መጀመሪያ ፍቅር ሲሆን ይሄ ፍቅርም ራስ ወዳድ እንደመሆን፣ ክፉና የሚመካ አይደለም። የምትሰሙት መልእክት የመንፈስ ቅዱስን ፍሬ የሌለው ከሆነ፣ ከእግዚአብሔር እንዳልሆነ ወዲያው ታውቃላችሁ። ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ። ኢየሱስ ክርስቶስ የራሱ እውነተኛ እረኞች አሉት። እውነተኞቹ እረኞች እንደ ኢየሱስ ይሆናሉ። እነሱ መንጋውን መስዋእት በሚሆን ፍቅርና እንክብካቤ ይወድዳሉ። ክርስቶስ የሞተለትን መንጋ፣ አይጠቀሙም፣ አይበዘብዙምም።

እርሱ ብዙዎች እንዲጠብቁ እንደተማሩት አይደለም፡

1.) ኢየሱስ በዘመኑ፣ የተለየ ሰው አልነበረም። በምርጡ ሆስፒታል ውስጥ አልተወለደም። የተከበሩ ሰዎች በሚኖሩበት ከተማ ውስጥ አላደገም። ዝነኛ አልነበረም። የሰው አገልጋይ ከሆንክ ከመጽሐፍ ቅዱሱ ኢየሱስ ጋር ለመዋል አትፈልግም። መገኘቱ ንቀትን፣ ስደትንና እንግዳን አስከትሏል። አሁንም እየቀጠለ ይገኛል።

ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው። እናም ትምክህትን፣ ራስን ከፍ ከፍ ማድረግንና ራስ ወዳድነትን አያወቅም። የመጣው ለማገልገል እንጂ ለመገልገል አልነበረም። ከተናቁትና ከዝቅተኞች ጋር ይገኛል። የሰዎች ክብር በገነነበት ሳይሆን እሱ ብቻውን በከበረበት ይገኛል። ማቴዎስ 11:29፡- "ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ ከእኔም ተማሩ፣ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና፣ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ።"

2.) ኢየሱስ ዘመናዊውን ልብስ አልለበሰም። ተከታዮቹን ለማሟሟቅና እሱን ለመከተል እንዲፈልጉ የሚያምር የቤተ ክርስትያን ሕንጻ፣ ከትላልቅ ድምጽ ማጉያዎች፣ ምርጥ ሙዚቀኞችና ቀልብን የሚገዙትን ብዙ ነገሮች አልነበሩትም።

ኢየሱስ ራሱን ብቻ ነበረ። ምንም ማታለያ አልነበረውም። እሱ ከዓለም ጋር አልተመቻቸም። እኛም ልንመቻች አይገባንም። እሱ ሙሉ በሙሉ ስለ አባቱና ስለ ራሱ ሰዎች ፍቅርና ለመታዘዝ ሲል ወደ ዓለም መጣ። ስጋን ለብሶ የመስዋዕቱ በግ ለመሆን መጣ። ዓለምና የኃይማኖት መሪዎችም ጠሉት። እናም ሲጠብቁት የነበረው መሲህ ስላልነበረ ሰቀሉት። የንግስናን መስፈርት ስላላሟላላቸው የእግዚአብሔርን ልጅ አልተቀበሉትም።

ኢሳይያስ 53:3-4፡- የተናቀ ከሰውም የተጠላ፣ የሕማም ሰው ደዌንም የሚያውቅ ነው። ሰውም ፊቱን እንደሚሰውርበት የተናቀ ነው፣ እኛም አላከበርነውም። በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ። ሕማማችንንም ተሸከሞአል፤ እኛ ግን እንደ ተመታ በእግዚአብሔርም እንደ ተቀጸፈ ቆጠርነው።

3.) አንዳንዶች ኢየሱስ ዋጋችንን በመከራ፣ በድህነት፣ በሞትና በትንሳኤ ከከፈለልን፣ እኛ ከስቃይና ከሞት እንደተላቀቅን ያስተምራሉ። ኢየሱስ ግን እሱ የተጓዘበትን መንገድ እንድንከተል ይነግርናል። ከሱ ጋር ከተሰቃየን ከሱ ጋር እንደምንከበር ይነግረናል። የሰውን ወንጌል ሳይሆን እውነተኛውን የክረስቶስ ኢየሱስን ወንጌል እንደምታውቁ አረጋግጡ።

ሮሜ 8:17፡- ልጆች ከሆንን ወራሾች ደግሞ ነን፤ ማለት የእግዚአብሔር ወራሾች ነን፣ አብረንም ደግሞ እንድንከበር፣ መከራን ብንቀበል ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን።

አዎ፣ የእርሱ መስዋዕትነት፣ የእርሱን ዳናዎች ተከትለን እንድንሄድ ሃይሉን ሰጥቶናል። ዛሬ፣ ሌላውን ትተን፣ በጀርባችን ተንጋለን፣ ክርስቶስ የሰጠንን ትርፍ እንድናጣጥም የሚያስተምረን ወንጌል አለ። በዚህ በምድራዊ ህይወት፣ ደስታችንን እንድንከተልና እርካታችንን እንድንፈልግ የሚመክረን። እንዲህ አይነቱ ወንጌል፣ ዓለም አይቶ የማያውቀውን ስስታም፣ ራስ ወዳድ፣ ትዕቢተኛ፣ የሚመኩ፣ አመጸኞችና የማያፈሩ ክርስትያኖችን አምርትዋል።

እውነተኛና ህያው የሆነውን ክርስቶስ ኢየሱስን መካድ በጣም አደገኛ ነገር ነው። እርሱን ከካድን እርሱም እንደሚክደን በግልጽ ነግሮናል። ስጋዊው ክርስትያን፣ ሰውነቱን ወደ ቅዱሱ፣ ንጹሁ፣ ቸሩ፣ ጻድቁና ፍቅር የሆነውን ክርስቶስ ወደ መምሰል ከማደግ ይልቅ፣ ክርስቶስን ራሱን አስመስሎታል።

ከክርስቶስ ኢየሱስ ወንጌል የተለየ ዶክትሪን ያለው ወንጌል ነው እየተማርን ያለነው፡፡ እናም ካልተመለስንና ንስሃ ካልገባን፣ በጣም እንቀጣበታለን፡፡ ብዙ ቦታዎች ላይ ክርስትያኖች፣ ስጦታውን ከሚሰጠው ከእግዚአብሔር ይልቅ፣ እግዚአብሔር በሚሰጠው ስጦታ ላይ ትኩረታቸውን አድርገዋል፡፡

በዚህ በመጨረሻ ቀናት፣ ትኩረታችንን ወደ ክርስቶስ መመለስ ይገባናል፡፡ እርሱ ወደ ልባችን ገብቶ ከኛ ጋር ጥብቅ ግንኙት ሊመሰርት፣ በልባችን በር ላይ ቆሟል፡፡ እርሱ ብቻውን የክብር ንጉስ ነው፡፡ እርሱ ብቻውን ሊመለክና ሊወደድ ይገባዋል፡፡ እርሱ ብቻውን በህይወታችን፣ በቤታችን፣ ከፍ ከፍ ሊል ይገባዋል፡፡ እርሱ ድሮም፣ ዛሬም፣ እስከ ዘላለም፣ የነገስታት ንጉስ፣ የጌቶች ጌታ፣ የሃያላን ሃያል ነው፡፡

የምንናገረው፣ የምንለብሰው፣ የምናመልክበት መንገድ፣ የምንኖረው ህይወት ሁሉም ነገራችን ሰይጣናዊ እየሆነ ነው፡፡ ወደ እግዚአብሔር የመመለስ ጊዜ አልረፈደም ይሆናል፡፡ የሚረፍድበት ጊዜ ግን ሩቅ አይደለም፡፡

ከአንድ የፌስቡክ ጓደኛዬ ጋር ስለ ፍልስፍና እያወራን፣ መጠየቅና መመራመር ምን ችግር አለው ብሎ ጠየቀኝ፡፡ አንድ ቀለል ያለ የፍልስፍና ጥያቄ አንስቼለት፣ "ይሄ ጥያቄ ስህተት የለበትም፣ ትክክለኛ ጥያቄ ነው፣ ትክክል ያልሆነውና ትልቁ ስህተት፣ ይሄ ጥያቄ ወደ አእምሮህ መምጣቱ ነው፡፡" አልኩት፡፡

ይሄ መጽሐፍ አንባቢን ስለ ማሳመንና ትክክል ስለ መሆን አይደለም፡፡ ፈላስፎችኮ ያሳምናሉ፡፡ ትክክልም ናቸው፡፡ በጣም ብዙ ትክክል የሚያረጉኝ፣ አንባቢዬን ይሄም አለ እንዴ የሚያስብሉና ትክክለኛነቴን ሊያረጋግጡ የሚችሉ ግን አውቄ የማልጽፋቸው ማስረጃዎች አሉኝ፡፡ ነገር ግን ይሄ መጽሐፍ አንባቢዬ የምታውቃቸው ነገሮችና ስለ እውነቱ ያለህን አመለካከት ገምግመህ እውነቱን እንድታስተውልና በእውነቱ እንድትኖር የጻፍኩት እንጂ፣ በፊት የማታውቀውን አዲስ እውቀት እንዲኖርህና የትክክለኝነትና የማሳመን አባዜ ኖሮብኝ፣ አጉል ምርምር ውስጥ እንድትገባ አይደለም፡፡ እንደዚያ ከሆነማ ከፈላስፎች በምን እለያለሁ? አንዳንድ አሳማኝ ማስረጃዎችን፣ ነግሬህ ከማሳምንህ ሳታውቃቸውና ሳትሰማቸው ቢቀሩ ይሻላል፡፡ ማርቆስ 24፡24፡- ምን እንድትሰሙ ተጠበቁ፡፡

በዚህ ዘመን በቴክኖሎጂ ጦስ መልካሙም፣ ክፉውም ሚዳ ላይ ሆነና ነው እንጂ አንዲት ህጻን ልጅ ቢኖርህና መንገድ ላይ ስትሄድ አንድ ሌላ ህጻን ልጅ ድምጹን ከፍ አድርጎ አንድ አስጸያፊና ከዚያ ልጅ አፍ ስለ መውጣቱ የሚያጠራጥርህን ስድብ ሲሳደብ ብትሰማ፣ ቤት ገብተህ ለልጅህ "አሁን ወደ ቤት እየመጣሁ አንድ አንቺን የሚያክል ህጻን ልጅ እንዲህ እንዲህ ብሎ ሲሳደብ ሰማሁት፣ አንቺ ግን ያንን ቃል እንዳትዪ እሺ" ትላታለህ? ምን እንደምታረግ ልንገርህ፡፡ ልጁ እንደዚያ ሲል ከደነገጥክ በኋላ፣ ልጁ የልጅህ እኩያ መሆኑን አይተህ ልጅህ አጠገብህ ባለመሆኗና ይሄ ልጅ ያለውን ባለመስማቷ ደስ ይልሃል፡፡ ከዚያ በኋላም ልጅህ እንደዚያ አይነት ቃላትን ከምትሰማባቸው ሁኔታዎች ልታርቃት ትሞክራለህ እንጂ በማስጠንቀቅና በመምከር ስም፣ ያን ክፉ ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ የምትሰማው ካንተ አፍ ሲወጣ እንዲሆን አትፈልግም፡፡ አንዳንዴ ሰው ሊመክረንና ሊያስተምረን የሚነግረን ነገር ከመጥቀም ይልቅ በጣም ይጎዳናል፡፡ ስለ ማላውቀው ነገር ጉዳት አንድ ሰው ቢነግረኝ፣ መጀመሪያ ስለ ነገርየው ምንነት ካጣራሁ በኋላ ነው ጎጂነቱን የምቀበለው፡፡ ካወቅኩት በኋላ ጎጂውን ነገር ጎጂነቱን ላልቀበል እችላለሁ፡፡ ያ የመከረኝ ሰው ግን ባይመከረኝና ባይነግረኝ አይሻለውም ነበር? የልጅቷ አባት ባይመክራት አይሻለውም?

በተለይ የፍልስፍና ሀሳቦችን ከመተቀስና አዕምሮን ከመመረዝ ቢቀር ይሻላል፡፡ ሴትየዋ እንዲህ እንዲህ አለች ብልና ለማሳመን ብሞክር፣ የኦሾንና የፍሬድሪክ ኒቼን ፍልስፍና ብጠቃቅስ በፊት አስበህ የማታውቀውን ነገር፣ የነሱን ሰይጣናዊ ሀሳብ የምትሰማበት መንገድ ሆንኩኝ ማለት ነው፡፡ እኔ የራሴን ሀሳብ ለማጠናከር ሊሆን ይችላል የጠቀስኩት ግን ፍልስፍና ስለ መስማትና ስለ ማሰብ፣ ስለ ማሰላሰል እንጂ ስለምንሰጠው ማጠቃለያ አይደለም፡፡ በፊት እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ የሚል እምነት ነበረ፡፡ አሁን ግን ዝንጀሮነት አለ፡፡ በፊትም እግዚአብሔር ነው የፈጠረን ብለን ነው የምናምነው፡፡ የዝንጀሮውን ስንሰማ፣ ውሸት ነው እሱ፣ እግዚአብሔር ነው የፈጠረን እንላለን ግን እምነታችን ስለ ዝንጀሮው ከሰማን በፊትና በኋላ አንድ አይሆንም፡፡ ባንቀበለውም መስማታችን ብቻ ለውጥ ይፈጥርብናል፡፡ ይሄ ነው ፍልስፍና፡፡ ማሰብ፡፡ ማሰብ ጥርጣሬን ያመጣል፡፡ መጠርጠር፣ መጠየቅን፡፡ ጥያቄ ማብዛት እምነትን ይሸረሽራል፡፡

ፍልስፍና ሴትየዋ እንዳለችው ከጥያቄ ነው የሚጀምረው፡፡ የፍልስፍና ችግሩም ለጥያቄው የሚሰጠው መልስ ሳይሆን መጠየቁ ራሱ ነው፡፡ እንደ ህጻን የሚቀበለው፣ ስለ እግዚአብሔር ሲነገረው፣ ያምናል፡፡ ብልጣ ብልጡ ደግሞ ትንታኔ ይፈልጋል፡፡ ትንታኔን የሚያስፈልገን ደግሞ ጥርጣሬ ነው፡፡ ጥርጣሬ ደግሞ እንድንጠይቅ ያደርገናል፡፡ ጥያቄ ባበዛን ቁጥር ከሃይማኖት እየራቅን እንሄዳለን፡፡

ııኛ ክፍል ላይ ብዙ በተለይ ት/ቤት የምናሞጋግሳቸው እንደ አይዛክ ኒውተንና ዳ ቪንቺ ያሉ ታላላቅ የምንላቸው ሰዎች የሰይጣናዊ ማህበራት አባላት እንደነበሩ አነበብኩ፡፡ በተለይ ፈላስፋው ኒቼ ፍሪ ሜሰን መሆኑን ሳውቅ፣ ያ ሁሉ ምንም ትርጉም አልሰጥ ሲሉኝ የነበሩ አጉል ፍልስፍናዎች አላማቸው ይገባኝ ጀመር፡፡ አሁን ላይ ሳስበው፣ አላማቸው የሆነ እውነት ብለው ያመኑትን ነገር ለማስረዳት ሳይሆን ሆን ብለው፣ አጉል ጥያቄዎችን አዕምሮህ ውስጥ ለመፍጠርና ሁሉንም ነገር እንድትጠራጠር እንድትመራመር መሆኑንና ግባቸው ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻው አንባቢ በእግዚአብሔር ላይ ያለውን እምነት ለማጥፋት እንደሆነና እንደነበረ አሁን ሲገባኝ የጽሁፎቹ ርዕስ "አንባቢን ከእግዚአብሔር ጋር ማጣላት" መሆን ነበረበት እላለሁ፡፡ አለማስተዋሌንና ተው እየተባልኩ አዋቂ ልሁን ብዬ እነኛን መጽሐፎች ማንበቤን ሳስበው ያበሸቀኛል፡፡

ፊልም ሰይጣን እንድታይና እንድትሰማ የሚፈልገውን ነገር የምታይበትና የምትሰማበት የሰይጣን ዓለም እንደሆነ፣ የፍልስፍና መጽሐፍትም፣ ሰይጣን እንድታስብና እንድታሰላስል የሚፈልገውን ነገር ወደ አዕምሮህ የምትቀበልበት መሳሪያ ናቸው፡፡

በእውነት ስልጣኔ ምንድነው? The modern disease?

ስልጣኔ ምንድነው? በእውነት ልንፋጅለት የሚገባን ነገር ነው? እውነት በእግዚአብሔር ስም ገንዘብን የሚሰብኩ እንደ ቄስ ዶክተር ገመቺስ ያሉ ሰዎች "አውሮፓ ከክርስቶስ በፊት ስልጣኔን አታውቅም ነበር፣ ክርስቶስ አበራላት" እንደሚሉት ነው ወይስ የክርስቶስን ትዕዛዝ ያለመቀበል ውጤት? ስለዚህ ጉዳይ አውርተን ጨርሰናል፡፡ ያላወራነው ክርስቶስ ይጠቅማል ያለውን ነገር ገሸሽ ማድረግና አይጠቅምም ያለውን ነገር ደግሞ መከተል ትርፉና ኪሳራው ምን እንደ ሆነ ነው፡፡

ስልጣኔ ሲባል መጀመሪያ ላይ የሚመጣው ቴክኖሎጂ ነው፡፡ ሰዎች መጀመሪያ በትናንሽ እርሻ ላይ የሚሰሩና የእጅ ሰራተኞች ነበሩ፡፡ ትላልቅ ፋብሪካዎች ሲመጡ ምርታማነትና፣ ለፋብሪካዎች የሚያስፈልገው ግብአትም ስለ ጨመረ፣ ግብአቱን በበቂ ሁኔታ ማግኘት ስለነበረባቸው፣ ባለ ፋብሪካዎቹ ከደሃ ባለ መሬቶች ላይ መሬታቸውን በመንግስትም እርዳታ በትንሽ ዋጋ ገዝተው፣ ድሆቹን በራሳቸው መሬት ላይ በጥቂት ክፍያ ቀጥረው ማሰራት ጀመሩ፡፡ ጥቂቶች የትየለሌ ሃብት ሲሰበስቡ ተራው ህዝብ በተቃራኒው ብዙ እየሠራ ጥቂት የሚያገኝበትን ኑሮ መኖር ጀመረ፡፡ ፊዩዳሊዝም ነገሰ፡፡

አንድ ሰው የሬኔሳንስ ሰዎች እቅድ ምን ነበረ ወይም የሬኔሳንስ ዋና ግብ ምን ነበረ ብሎ ቢጠይቅ፣ መልሱ የሚሆነው፡ የሬኔሳንስ ግብ የዓለምን ህዝብ፣ ምክንያታዊ ማድረግና በእውቀት ማጥለቅለቅ ነበረ፡፡ የሬኔሳንስ ሰዎች ይሄን እቅድ ሲያወጡ፣ ምክንያት ሰውን ከሃይማኖት ሰውን እንደሚያርቅ አሳምረው ያውቁት ነበረ፡፡ እኛስ ይሄን ነገር አስተውለናል ወይ ብለን ራሳችንን ስንጠይቅ ከዚያም በላይ ግን ቃሉ በግልጽና በተደጋጋሚ ሲናገር አንብበናል፡፡ እግዚአብሔር የከለከለው አዕምሮን ነው፡፡ ሰይጣን የፈለገው አዕምሮን ነው፡፡ ሰውን ካስራብከው ማብላቱ አይከብድም፡፡ እዕምሮውን ካገኘ፣ እግዚአብሔር ላይ ማሳመጹ አይከብድም፡፡ እንድናይና እንድንሰማ፣ እንድናነብ የሚፈልገውን ነገር እንደፍላጎቱ ካደረግንለት፣ ሌላው ቀላል ይሆናል፡፡

የሬኔሳንስ ሰዎች ያቀዱት ማህበረሰብን በአስተሳሰብና በአኗኗር የመቀየር ውጥን እቅድ፣ በ19ኛው ምዕተአመት መጨረሻና በ20ኛው ምዕተአመት መጀመሪያ ነበር በከፍተኛ ደረጃና በዓለም አቀፍ ደረጃ መሳካት የጀመረው፡፡ ካርል ማርክስ በሶሻሊዝም በአንድ ሀገር ውስጥ የሚኖሩ ዜጎች ተመሳሳይ የኢኮኖሚ ደረጃ ሊኖራቸው ይገባል የሚል ፍልስፍና አመጣ፡፡

ኢትዮጵያውያን የስልጣኔ ከፋት ጥርት ብሎ እየታየን አይደለም፡፡ ዲሞክራሲና ነጻነት ምናምን እንላለን፡፡ ብዙ ሚስጥሮች አሉ፡፡ ዶናልድ ትራምፕ ከመመረጡ በፊት እንደሚመረጥ ይታወቅ ነበረ፣ የአሜሪካ ዲሞክራሲ ውሸት ነው ይባላል፡፡ የአሜሪካ ዲሞክራሲ እውነት ቢሆንስ ዲሞክራሲ ምን ያረግልኛል? ስልጣን የህዝብ እንጂ የግለሰቦች ስላልሆነ? ማነው እንደዚያ ያለው? አሜሪካ? ጆርጅ ዋሺንግተን? የሲቪክ መጽሐፍ?

በፊት በፊት ሀገር የሚያስተዳድሩት ንጉሶች ነበሩ፤ ህዝቡ ለንጉሱ ከመገዛት ሌላ የሚያስበው ነገር አልነበረውም፡፡ ፖለቲካ የንጉሳውያኖቹ ብቻ ነበር፡፡ እነሱ እዚያ ለስልጣን ስንት ደባ ይሰራሉ፡፡ ህዝቡ ግን ምንም ድርሻ አልነበረውም፡፡ በፊት በፊት ዴሞክራሲ(በግሪክ ብቻ) ጭላንጭል ነበረ፡፡ አሜሪካ ከታላቋ ብሪቴን ቅኝ ግዛት ተዋግታ ነጻ ስትወጣ በጦርነቱ ላይ ከፍተኛ የመሪነት ብቃት ያሳየ የጦር ጀነራል ነበረ፡፡ ጆርጅ ዋሺንግተን ይባላል፡፡ የነጻዋ ምድር የመጀመሪያ ፕሬዝዳንት፡፡ ጦርነቱ ሲጠናቀቅ ህዝቡ ንጉስ እንዲሆነው ተማጸነ፡፡ ጆርጅ ዋሺንግተንን ብትሆን ምን እንደምታረግ አስበው፡፡ ህዝቡ፣ እስከ እለተሞትህ የሀገራችን ፈላጭ ቆራጭ ሁንልን ቢለው፣ ዋሺንግተን አሻፈረኝ ብሎ በፕሬዝዳንትነት ለ8 አመት አገልግሎ ለመተካት ተስማማ፡፡ አሜሪካ፣ ዛሬም ድረስ አለም እንደ ሞዴል የሚወስደውን ህገ መንግስት አወጣች፡፡ ስልጣን የህዝብ ነው ተባለ፡፡ ህዝብ የፈለገውን ይሾማል፣ የጠላውን ይሽራል፡፡ ህዝቡ በፖለቲካው ውስጥ ቀጥተኛ ተሳታፊ ሆነ፡፡

“አንድም ድምጽ ዋጋ አላት” አይደል ከነአባባሉ፡፡ አሜሪካ ለዜጎቿ የመሾምና የመሻር መብት ብቻ አይደለም የሰጠችው፡፡ ዛሬ ዲሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብት የምንላቸውን መብቶች ሁሉ እንጂ፡፡ ሰላማዊ ሰልፍ የመውጣት መብት፣ የፈለጉትን የመጻፍ መብት፣ እንደ ፈለጉ የማውራት መብት…ብዙ መብቶች፡፡ የአሜሪካን ዲሞክራሲ ፈጥኖም ሆነ ዘግይቶ፣ ወደ ሌላ ሀገራት ተዛመተ፡፡

ናሽናሊዝም፣ የሀገር ፍቅር ብለው ተደራጅተው መጨፋጨፍ፣ እየተለመደ መጣ፡፡ ለዲሞክራሲ የተደረገው ትግል በጣም ደም ያፋሰሰ ነበር፡፡ በዲሞክራሲ ውስጥ የመጀመሪያው መብት የማመጽ መብት ነው፡፡ መንግስት ለማውረድ ስራ ማቆም፣ ሰላማዊ ይሉታል፣ ሰላማዊ ሰልፍ መውጣት፣… የዲሞክራሲ የመጀመሪያው ግብ ህዝብን በመንግስትና በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ላይ ማሳመጽ ነው፡፡

ሮሜ 13፥1-6፡- ነፍስ ሁሉ በበላይ ላሉት ባለ ሥልጣኖች ይገዛ፡፡ ከእግዚአብሔር ካልተገኘ በቀር ሥልጣን የለምና፡፡ ያሉትም ባለ ሥልጣኖች በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው፡፡ ስለዚህ ባለ ሥልጣንን የሚቃወም የእግዚአብሔርን ሥርአት ይቃወማል፡፡ የሚቃወሙትም በራሳቸው ላይ ፍርድን ይቀበላሉ፡፡ ገዢዎች ለክፉ አድራጊዎች እንጂ መልካም ለሚያደርጉ የሚያስፈሩ አይደሉምና፡፡ ባለ ሥልጣንን እንዳትፈራ ትወዳለህን? መልካሙን አድርግ ከእርሱም ምስጋና ይሆንልሃል፡፡ ለመልካም ነገር ለአንተ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና፡፡ በከንቱ ግን ሰይፍ አይታጠቅምና ክፉ ብታደርግ ፍራ፡፡ ቁጣውንም ለማሳየት ክፉ አድራጊውን የሚበቀል የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና፡፡ ስለዚህ ስለ ቁጣው ብቻ አይደለም ነገር ግን ስለ ሕሊና ደግሞ መገዛት ግድ ነው፡፡ ስለዚህ ደግሞ ትገብራላችሁና፡፡ **በዚህ ነገር የሚተጉ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸውና፡፡**

1 ጴጥሮስ 2፥13-25 *ስለ ጌታ ብላችሁ* ለሰው ሥርአት ሁሉ ተገዙ፡፡ ለንጉሥም ቢሆን፣ ከሁሉ በላይ ነውና፡፡ ለመኳንንትም ቢሆን፣ ክፉ የሚያደርጉትን ለመቅጣት በጎም የሚያደርጉትን ለማመስግ ከእርሱ ተልከዋልና ተገዙ፡፡ በጎ እያደረጋችሁ የማያውቁትን ሞኞች ዝም ታሰኙ ዘንድ እንዲህ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነውና፡፡ አርነት ወጥታችሁ እንደ እግዚአብሔር ባሪያዊች ሁኑ እንጂ ያ አርነት ለክፋት መሸፈኛ እንዲሆን አታድርጉ፡፡ ሁሉን አክብሩ፣ ወንድሞችን ውደዱ፣ እግዚአብሔርን ፍሩ፣ ንጉሥን አክብሩ፡፡ ሎሌዎች ሆይ፣ ለበጎዎችና ለገሮች ጌቶቻችሁ ብቻ ሳይሆን ለጠማሞች ደግሞ በፍርሃት ሁሉ ተገዙ፡፡ በግፍ መከራን የሚቀበል ሰው እግዚአብሔርን እያሰበ ኃዘንን ቢታገሥ ምስጋና ይገባዋልና፡፡ ኃጢአት አድርጋችሁ ስትጎሰሙ፣ ብትታገሡ፣ ምን ክብር አለበት? ነገር ግን መልካም አድርጋችሁ መከራን ስትቀበሉ ብትታገሡ፣ ይህ ነገር በእግዚአብሔር ዘንድ ምስጋና ይገባዋል፡፡ የተጠራችሁት ለዚህ ነውና፡፡ ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለ እናንተ መከራን ተቀብሎአልና፡፡እርሱም ኃጢአት አላደረገም፣ ተንኮልም በአፉ አልተገኘበትም፡፡ ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም፡፡ መከራን ሲቀበል አልዛተም፣ ነገር ግን በጽድቅ ለሚፈርደው ራሱን አሳልፎ ሰጠ፡፡ ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር፣ እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ፡፡ በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ፡፡ እንደ በጎችም ትቅበዘበዙ ነበርና፣ አሁን ግን ወደ ነፍሳችሁ እረኛና ጠባቂ ተመልሳችኋል፡፡

በስመ ዲሞክራሲ፣ ሰው የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ጥሶ መንግስቱን ቁም ስቅል ማሳየትና መጨፋጨፍ ቀጠለ፡፡

በሀገራችን፣ ሃይለስላሴ ዩኒቨርሲቲ ከፈቱ፡፡ የአውሮፓን ፖለቲካ ምድራቸው ላይ ሲንቀሳቀስ ማየት የፈለጉና ደሃው ገበሬ መብቱ እየተበዘበዘ የመሰላቸው ወጣት ተማሪዎች፣ አመጹ፡፡ ሃይለ ስላሴም በፖሊሶቻቸው፣ አስገደሏቸው፡፡ ተማሪዎቹ መሬት ላራሹ እንዲሆን እንጂ ለመንግስታዊ ዲክራሲ አላመጹም ይሆናል፡፡ ግን ማን አምጹ አላቸው? የማመጽ መብት እንዳላቸው ማን ነገራቸው? ተምረው የተለያዩ ሀገራትን ተሞክሮዎች ማንበባቸው ብቻ ሳይሆን የሌላ ሀገር ታሪክ ባያነቡም መማር ብቻውን ራሱ አማጺ ያደርጋል፡፡ ይሄን ለማረጋገጥ የተማረና ያልተማረ ሰው ወስዶ ማየት ነው፡፡ የተማረ ሰው ጥቅምና ጉዳቱን ያስባል፡፡ የተማረው ለመብቱ ይታገላል፡፡ ያልተማረ ሰው ጥቅምና ጉዳቱን አያስብም፡፡ አይንተገተግም፡፡

ከዚያ ደርግ ስልጣኑን ከጃንሆይ ተረከበ፡፡ ደርጉ ዲክራሲያዊ አልነበረም፡፡ ከላይ የኤርትራ ጦርነት፣ ከውስጥ፣ ኢህአፓ፣ የቦረቦሩት ደርግ፣ ጨፍጫፊ ሆኖ አረፈው፡፡ ይሄ ሁሉ ግድያ ወጣቱ ዝም ብሎ ቢገዛ ይመጣ ነበረ ወይ? ለምን አላመጽክም፣ ለምን አርፈህ እራትህን በልተህ ተኛህ፣ ብሎ የሚገድል መንግስት የለም፡፡ “ለነጻነት የሚደረግ ትግል፣ በህይወት ጣፋጩ ትግል ነው” የሚባል ፍልስፍና አለ፡፡ “ታስረህ ከመኖር፣ ታግለህ መሞት ይሻላል”፡፡ በንደነዚህ በጣም ጥበብ የታከለባቸው የሚመስሉ፣ ግን ባዶ በሆኑ አባባሎች ነው የሀገር ወጣት የሚታለለው፡፡ የሀገር ፍቅር ይባላል፡፡ ሀገር ከሲኦል እንደሚያስጥል፡፡ ሀገር ከነፍስህና አንተን በማጣት ከሚሰቃየው ቤተሰብህ እንዴት እንደሚበልጥብህ እኔ አላውቅም፡፡ ሀገሬ የሚባል ነገር የለም፡፡ ሀገር የመንግስት ነው፡፡ ትገዛለህ፣ ትታዘዛለህ፡፡ ለመንግስት መታዘዝ ብቻ ሳይሆን ትታመናለህ፡፡ ሀገርህን ስለምትወድ አይደለም፡፡ ቃሉ ለባለ ስልጣናት ተገዙ ስለሚል፡፡ ካመጽክም ሞትህን ታፈጥናለህ፡፡ በሌሊት አብዮቱን የሚቃወም ነገር ግርግዳ ላይ እለጥፋለሁ፣ የደርግ ወታደር እገላለሁ፣ የምትል ከሆነ ግን ሞትህን በራስህ ላይ አወጅክ፡፡ የዚያ ሁሉ የኢህአፓ አባል ሞት ምን አተረፈ? ለምን ዝም ብለን ቃሉ በሮሜ 13 ላይ እንደሚለው እንደተባልነው፣ እንደታዘዝነው መኖር አንችልም? በስመ ዲሞክራሲ በወያኔ ጦርነት ስንት ወጣት አለቀ? በቅርቡ በማስተር ፕላን ስም ወደ 500 የኦሮሞ ወጣት ተጨፈጨፈ አሉ፡፡ በመላው ሀገሪቱ አመጽ ነበረ፡፡ ማስተር ፕላኑ ተሰርቶ 500 ሰው መሞቱ ቢቀር አይሻልም? እዚህም እዚያም ረብሻ፣ አመጽ፡፡ ይሄ የስጋዊነት ፍሬ ነው፡፡ቲቶ 3፥1-2፡፡ ቃሉን ገሸሽ ስናረግ፣ ቃሉ ገሸሽ የሚያረገን ጊዜ ይመጣል፡፡ “ተው ቃሉ የሚለው እንዲህ ነው” ብለው ወጣቶችን የመከሩ ቤተ-ክርስትያናት የትኞቹ ናቸው? በርግጥ አንድ ፓስተር የማስተር ፕላኑን አመጽ ሲደግፍ በቪኦኤ ሰምቼአለሁ፡፡

የሀገር ፍቅር፣ ናሽናሊዝም፣ የሚባሉ ነገሮች ሰይጣን አላማውን ለማሳካትና ህዝቡን በገዢዎቹ ላይ እንዲያምጽ የፈጠረው ዘዴ ነው፡፡ እግዚአብሔር ግን ሀገራችሁን ውደዱ ሳይሆን ቤተሰባችሁን፣ ባልንጀሮቻችሁን ውደዱ ነው የሚለው፡፡ ራሳችንን እንደምንወድ ባልንጀራችንን እንድንወድ ያዘንና፣ ለመንግስታት እንድንገዛ ብቻ እንጂ ሀገራችን ብለን እግዚአብሔር ያስቀመጠው ባለ ስልጣን ላይ እንድናምጽ አይደለም፡፡

ለምን ዝም ብለን እንደ ተባልነው አንኖርም? ምክንያቱም ከልጅነታችን ጀምሮ መብት የህዝብ ነው እያሉ አስተማሩን፡፡ ወሬው ተንቀረቀረ፡፡ ዲሞክራሲን ማስፈን ተባለ፡፡ እግዚአብሔር ያልሰጠንን መብት ውሸታሞች ሰጡን፡፡ ባይሰጡንም የኛ እንደ ሆነ ነገሩን፡፡ ነገሩ ደግሞ እንዲሁ በቀላሉ የሚሰፍን ነገር አይደለም፡፡ ባህል ነው፡፡ ለማሰፈን በመነጋገር ማመን፣ ሽንፈትን መቀበል ያስፈልጋል፡፡ ያ ደግሞ የተማሩ ሰዎች የሚያደርጉት ነገር ነው፡፡ እኛ ደግሞ አልተማርንም፡፡ ሳንማር፣ የሌለንን ባህል ፈለግን፡፡ መንግስታችንም የማያውቀውን ባህል ሊተገብር ፈቃደኛ መሆን አልቻለም፡፡ ታዲያ ለምን ስልጣኑን አሳልፎ ይሰጣል? ሰጥቶ ለራሱ ደግሞ የት ሊሄድ? ሙስና፣ ሰው ገደልክ ሲባል፣ ሊሰደድ ወይስ በፈቃዱ እስር ቤት ሊጣል? ይሄ ነው የብዙ አፍሪካ ሀገራት መሪዎች ችግር፡፡ የማይፈጸም ቃል ይገባሉ፣ ትውልዱን፣ ስለ ዴሞክራሲና ስለ መብት አስተምረው፣ የገቡለትን ቃል ሳይፈጽሙ ሲቀሩ ህዝቡ ያምጻል፡፡ ሲያምጽ ይጨፈጨፋል፣ ጦርነት ይነሳል፣ ብዙ ሰው ይሞታል፡፡ አንድ አማጺ ቡድን በበለጸጉ ሀገራት ድጋፍ ለማግኘት ዲሞክራሲያዊ ነኝ ማለት አለበት፡፡ ዲሞክራሲያዊ ነኝ ሲል እነአሜሪካም፣ ህዝቡም ይደግፉታል፡፡ ስልጣኑን ሲጨብጥ፣ ይከብደዋል፣ ጦርነት ይነሳል፡፡ በየጊዜው ጦርነት ነው፡፡ በዚህ ሁሉ ውስጥ ሁሉም የህይወትን መንገድ፣ ያነባል፣ ያነባል፣ ግን የአለም ምኞት ቃሉን ያንቃል፡፡ አያስተውልም፡፡ አይኑ ትርፍ በሌለው በአለም ምኞት ተጋርዷልና፡፡

ዲሞክራሲን ለማስፈን የሚደረገው ትግል በጣም ደም አፋሳሽ ከመሆኑ የተነሳ ዲሞክራሲው ቢቀርስ ያስብላል፡፡ ዲሞክራሲ ብዬ መሞት አልፈልግም፡፡ ለምን ልሙት ለማይተገበር ነገር፡፡ እሺ ዲሞክራሲ ስራ ላይ ዋለ እንበል፡፡ እውነት ዲሞክራሲ ጥሩ ነገር ነው እንዴ? የተገበሩት ምን አተረፉ?

ከዲሞክራሲ በፊት ሊበራሊዝም የሚሉት ነገር አለ፡፡ በርግጥ ተቆራርጠው የተቆራረጡ ሁለት ቃላት አይደሉም፡፡ ሊበራል ዲሞክራሲ የሚባል ነገርም አለ፡፡ ነገር አዳፍነን አጠቃለን ስናየው፣ ዲሞክራሲ በቡድን የህዝብ መብት ላይ ሲያተኩር፣ ሊበራሊዝም ደግሞ የግል ላይ ያተኩራል፡፡ የማውራት ነጻነት፣ የመናገር ነጻነት፣ የህትመት ነጻነት የሚባሉት ናቸው ሊበራሊዝም ስር የሚካተቱት፡፡ ታዲያ ነጻ የሚለው ቃል ፖለቲካዊ ብቻ አይደለም፡፡ ማህበራዊም ነው፡፡ በፖለቲካው መንግስት ላይ እንደፈለግክ ታላግጣለህ፣ ትቃወማለህ፡፡ ሃይ የሚልህም የሚያስርህም የለም፡፡ ስለማህበራዊውም እንደፈለግክ ትጽፋለህ፣ እንደ ፈለግክ ታወራለህ፡፡ በሚዲያ ላይ የፈለግከውን ሃይማኖት ብትሳደብና ህዝብ ቢነሳብህ እንኳን መንግስት ከለላ ይሆንሃል፡፡ እንደ ፈለግክ ትቀልዳለህ፡፡ በሊበራሊዝም ትውልድ ታበላሻለህ፣ በዲሞክራሲ ብልሽቱን ታጸድቃለህ፡፡ በሊበራሊዝም ጥቂት ሰዎች ሰፊ ማህበረሰብን ያበላሻሉ፡፡
አንድ ዱሪዬ፣ አስጸያፊ ቃላትን የሚናገር ልጅ፣ ጸባየኛ የሆኑ ልጆች ጓደኛ ለመሆን ይፈልጋል፡፡ ይሄን የተረዱት ልጆች ልጁ ዱሪዬ እንደሆነ ስለሚያውቁ ያርቁታል፡፡ ምክንያቱም “የጓደኛህን ስም ንገረኝ፣ ማንነትህን ልንገርህ” የምትባለዋ ፈሊጥ ትርጉም ለነዚህ ልጆች ብትክክል ገብቶአቸዋል፡፡ ይሄን ልጅ ጓደኛቸው ቢያረጉ ያበላሻቸዋል፡፡ አብረው መዋል ከጀመሩ እሱ ደጋግሞ የሚጠቀማቸውን አስጸያፊ ቃላት ሊለማመዱ ነው ማለት ነው፡፡ በዚያ ላይ ይሄን ልጅ ጓደኛቸው ቢያደርጉ፣ ወላጆቻቸው፣ የሠፈር ሰው አንድ ላይ ካዩአቸው ጥሩ ስለማይመጣና ስለሚቆጡአቸው ይሄን ልጅ አይቀርቡትም፡፡ ስለዚህ ቢያንስ ይሄ ልጅ ማህበረሰቡ የሚያገለው ስለሚሆን ከህብረተሰቡ ለመቀላቀል፣ ጸባዩን ለማሻሻል ይሞክራል፡፡ ሊበራሊዝም ደግሞ ለጸባየኛውም፣ ለዱሪዬውም እንደፈለጉ የማውራት፣ እንደፈለጉ የመጻፍ መብት ይሰጣቸዋል፡፡ መንፈሳዊ ቻናል መክፈት የፈለገም፣ ዝሙትን የሚያሰራጭ ቻናል መክፈት፣ ፊልም መስራት የሚፈልግም፣ ወይም መጽሐፍ ማሳተም የሚፈልግም፣ እንደ ደርግ እግዚአብሔር የለም ይሄን ማሳተም አትችልም፣ ወይም ይሄ ብልግና ነው ማሳየት አትችልም ብሎ የሚከለክል መንግስት የለም፡፡ በየሰፈሩ አንዳንድ ዱሪዬ አለ እንበል፡፡ በጣም ጸባየኛ ሰዎች በበዙበትና ጥቂት ዱሪዬዎች ባሉበት፣ በምሳሌያችን መሰረት፣ መንፈሳዊ የህትመት ውጤቶች፣ ቻናሎች እንጂ፣ የዱሪዬነት ነገሮች አይኖሩም፡፡ አንድ ዱሪዬ እድሉን አግኝቶ ማሳተም፣ ቻናል መክፈት፣ ፊልም መስራት ቢችል ግን ሰፊውን ማህበረሰብ፣ በቀላሉ ያበላሸዋል፡፡ ያን ዱሪዬ ልጅ ለነዚያ ልጆች ጓደኛ ቢሆን፣ አብረው ሊሄዱ ነው፣ ሊያወሩ ነው፣ አንድ ላይ ሰው ሊያያቸው ነው… በቲቪ ሲመጣ ግን ጓደኛቸው መሆን አይጠበቅበትን፡፡ በመጽሐፍ ሲመጣ ግን ወላጆቻቸው አብረው አያዩአቸውም፡፡ የሚለውንና የሚያረገውን ማየት ብቻ ነው፡፡ እንኳን ማኅበረሰባቸውንና ቤተሰባቸውን፣ እነዚህ ጓደኞች እርስ በራስ ቢተፋፈሩ እንኳን፣ ብቻቸውን በነጻነት፣ የዚህን ዱሪዬ ክፉ ስራዎች ማየትና መስማት ይችላሉ፡፡ ከጊዜ በኋላ፣ አንዱ ዱሪዬ ሁለት ወይ ሶስት ልጆች ብቻ ሳይሆን መላውን ማህበረሰብ የራሱ ቤተሰብ ያደርጋል፡፡ በፊት አስጸያፊ ሲባል የነበረው ቃል ትርጉሙ ወደ ጥሩ ነገር የተቀየረ እስኪመስል ሰዎች ከአረፍተነገራቸው የማያወጡት ቃል ይሆናል፡፡ ሁሉም ዱሪዬ ይሆናል ማለት ነው፡፡

ዴሞክራሲ ደግሞ በሊበራሊዝም ስም በዱሪዬነት የተበከለ ማህበረሰብ በጋራ በፊት ሳይበላሽ ያወጣውን ህግ ከዱሪዬነቱ ጋር በሚጣጣም መንገድ የሚያሻሽልበት ስርአት ነው፡፡ ለምሳሌ በፊት ከጋብቻ ውጪ መተኛት፣ ዝሙት ወይም ማመንዘር በህግ የሚያስቀጣ ከሆነ፣ በሊበራሊዝም አበሳ፣ ከጊዜ በኋላ ከጋብቻ ውጪ መተኛት በማህበረሰቡ ነውር የሌለው ነገር ይሆንና ሰዎች ሰላማዊ ሰልፍ ይወጣሉ፣ ቅስቀሳ ይደረጋል፣ ዴሞክራሲም አደል፣ ነጻነትም አይደል፣ የበላይ ድምጽ ያሸንፋልም አይደል፣ ብዙው ድምጽ በሊበራሊዝም ጦስ ስለተበላሸና ዱሪዬ ሆኖ ከጋብቻ ውጪ መተኛትን ስለሚደግፍ ህጉ ይሻራል ማለት ነው፡፡ በሊበራሊዝም ጥቂቶች ብዙሃንን ብልግና ይሰብካሉ፡፡ በዴሞክራሲ ብዙሃን ብልግናን ያጸድቃሉ፡፡ “ኢትዮጵያ፣ ጓደኞችሽን ንገሪኝ፣ ምንነትሽን ልንገርሽ፡፡ ትውልድሽን ሆሊውድ እየወረሰው አይደለምን?”

ዲክታተርሺፕ ወይም አምባገነን ስርአት ይባላል፡፡ ዘመን አመጣሽ ብሂል ነው፡፡ ይሄን ቃል ለመንግስታት ክፋት ይጠቀሙበታል፡፡ ነገር ግን ዲክታተርነት የመንግስት ክፉነት ሳይሆን የህዝቡ ክፉነት ውጤት ነው፡፡ አለም፣ መንግስትን መገልበጥ ትችላለህ ስላለህ፣ መንግስት መገልበጥ ትችላለህ ማለት አይደለም፡፡ እግዚአብሔር ከሚለውና አለም ከሚለው የቱ ይበልጣል? በመንግስት ላይ ስታምጽ ለራስህ ትቀጣበታለህ፡፡ ከመንግስት ጋር ጥል የሚነሳው ሃይማኖት ላይ ብቻ ነው፡፡ እግዚአብሔርን አታምልክ ሲልህ እሺ ብለህ አትተውም፡፡ ሌላውን ግን እንደ ፈለገ ያድርግ፡፡ መንግስት ተገለበጠ፣ ቆየ ለውጥ የለውም፡፡ ለውጡ የሚጨፈጨፉ ሰዎች መኖራቸው ነው፡፡ ዲሞክራሲ ቢመጣ ለውጥ የለውም፡፡ እድሜህ ላይ አንድ ደቂቃ አይጨምርልህም፡፡ ፖለቲካ ከንቱ ነው፡፡ ዝም ብለህ ለምን ኑሮህን አትኖርም? ቤተሰብህን ለምን አታስተዳድርም፡፡ ለምን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ትጥሳለህ? የፖለቲካ ትርፉ፣ ብክነት ነው፡፡ የሀገር ፍቅር ነው? ገሃነም የሚከት የሀገር ፍቅር ጥንቅር ይበል፡፡ ከሀገርህ የበለጠ ለቤተሰብህ ታስፈልጋለህ፡፡ ለሀገርህ እንዲያውም ምንም አትፈይድም፡፡ ቤተሰብህን መቀለብ ከቻልክና ልጆችህን ለሀገራችሁ

ህይወታችሁን አባክኑ ከሚል ከንቱ ትምህርት ፈሪሃ እግዚአብሔርንና ለባለ ስልጣናት እየተገዙ መኖርን እያስተማርክ ብታሳድግ ከዚያ በላይ ምን አለ? የሚያምጽ ቅጣቱን ይቀበላታል፡፡ በዚህም ሆነ በዚያ፡፡

እውነተኛ ክርስትያን በመንግስት ስራ ውስጥ አይገባም፡፡ መንግስት የፈለገውን እንደፈለገ ያድርግ፡፡ እውነተኛ ክርስትያን እኔ የዚህ አለም ዜጋ አይደለሁም ብሎ ነው ሚያስበው፡፡ ስለተዘጋጀለት ዘላለማዊ ክብር ነው ሚያስበው፡፡ መንግስት የፈለገውን ያድርግ፡፡ ግድ የለውም፡፡ ከፈለገም የክርስትያን ሃይማኖትን ያግድ፡፡ ይፈቀድ ወይም መታገድ የለበትም ተብሎ ሰልፍ አይወጣም፡፡ እግዚአብሔርን ማምለክም አያቆምም፡፡ ያገዱት ሊገሉት ቢመጡ አይታገላቸውም፡፡ ስለ እውነተኛው እውነት ከመገደል የበለጠ ጣፋጭ ነገር ምናለ? እውነተኛ ክርስትያን ስለነፍሱና ስለሌሎች ነፍሶች እንጂ ስለ አለም ግድ የለውም፡፡ ስለ አለም ከንቱ ወሬ በመስማት የሚያጠፋው ጊዜም የለውም፡፡

ዛሬ ላይ ኢትዮጵያ ውስጥ እንደ ፈረንጅ ኮሜዲያኖች ሃይማኖት ላይ እንደፈለጉ መቀለድ አለመቻሉ ትልቅ እጥረት ተደርጎ ይነሳል፡፡ እኛስ የሰው ጥርስ ለመቁጠር እግዚአብሔር ላይ መቀለድ አማረን፡፡ ብንቀልድም እግዚአብሔርን አንጎዳውም፡፡ እሱ የቀለደብን እለት ግን የሚስቁ ጥርሶች ሳይሆኑ የሚያለቅሱ ነፍሶች ናቸው የሚኖሩት፡፡ ዋይ ዋይ...

አሜሪካኖች ድሮ በጦርነት ምናምን ጊዜ እግዚአብሔር ከአሜሪካ ጎን ነው የሚሉት ነገር ነበራቸው፡፡ እግዚአብሔር ከኛ ጋር ነው ማለት የሚችል ሀገር ቢኖር እንኳን እስራኤል ብቻ ነች፡፡ ክርስትና ይቆረቆረው የነበረው አብረሃም ሊንከን ታዲያ ሲናገር "እግዚአብሔር ከኛ ጋር መሆኑን ሳይሆን እኛ ከእግዚአብሔር ጋር መሆናችንን ነው ራሳችንን መጠየቅ ያለብን" ይላል፡፡ ክርስትናን በቸርች ውስጥ ብቻ በማጠር ታዲያ አሜሪካን የቀደመ አልነበረም፡፡ ሴኪላሪዝምን ለማስፈን ተዋከቡ፣ ተዋከቡ፡፡

እግዚአብሔር እስራኤላውያን ሳይመርጡት መረጣቸው፡፡ እያጉረመረሙ ቀይ ባህርን ለሁለት ከፍሎ አሻገራቸውና ጠላታቸውን ፈረኦንን አሳፈረ፡፡ እግዚአብሔር ላልመረጡትና ላጉረመረሙበት፣ እንዲሁም ከዚህ ሁሉ እርዳታው በኋላ ጣኦትን ላመለኩበት ህዝብ ይሄን ሁሉ ካደረገ፣ እኛ ብንመርጠውና በእውነት ብንፈልገው ደግሞ ከዚህ በላይ አያደርግልንምን?

የዳርዊን ቲዮሪ ህዝቡን፣ የእግዚአብሔርንና የመንፈስን ህልውና፣ ከህይወት በኋላ ህይወትን አስካደው፡፡ ዘመናዊ የእርግዝና መከላከያዎች ተጨምረው የዝሙት ነውርነት አከተመ፡፡ ዝሙት ነገሰ፡፡ መፋታት በጣም የተለመደ ነገር ሆነ፡፡ ቀደምት የሃይማኖት መሪዎች፣ ስለ መኻታ፡ "ባልና ሚስት ድንግላውያን መሆን አለባቸው፣ ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው፡፡ ሁሉም ግንኙነት ጽንስን የሚከላከል መሆን የለበትም፡፡ ጽንስን የሚከላከሉ ባልና ሚስት ትዳርን ሽፋን አድርገው ያመነዝራሉ የሚል ነበር አቋማቸው፡፡" በ20ኛው ክ.ዘ. ግን ውርጃና እርግዝናን መከላከል ፋሽን ሲሆኑ፣ ዝሙት አደጋነቱ ኤችአይቪን ለመሳሰሉ በሽታዎች እንጂ መንፈሳዊ ውድቀቱ ተረሳ፡፡ እስከ ዛሬ ግን ቃሉ ይነበባል፡፡

የዴሞክራሲና የነጻነት ግቡ ሰዎችን ከእግዚአብሔር አገዛዝ ስር ማውጣት ነው፡፡ ቀስ በቀስ ክርስትናን ካቀጨጩ በኋላ አሁን በካናዳ የጥላቻ ንግግር ህግ(Hate speech law) አጽድቀዋል፡፡ ይሄም ሰው በተሰበሰበበት ስለ ክርስትና እየጠፋ ነው፣ ወደ እግዚአብሔር እንመለስንና መንግስታት በክርስትና ላይ እያደረሱ ያሉትን ጭቆና የሚቃወሙ ንግግሮችን የሚያግድና እንደዚህ በሚያደርጉ ክርስትያኖችና የሐይማኖት መሪዎች ላይ እርምጃን የሚወስድ ጸረ ክርስትና የሆነ ህግ ነው፡፡ ምንም ቢሆን አሁንም በምዕራባውያን ሀገራት የክርስትያን ባህል ጠፍቶ አልጠፋም፡፡ ሰው ባይሄድባቸውም፣ ቤተ ክርስትያናት አሉ፡፡ በአሜሪካ ምንም እንኳን ባይኖርበት ዛሬ ላይ ከ75% በላይ የህዝብ ቁጥር ክርስትያን ነኝ ይላል፡፡ ስለዚህ ይሄ ህግ ክርስትናን የማጥፋቱ ዘመቻ አንድ አካል ነው፡፡ በካናዳ ማርክ ሃርንግ የተባሉ ፓስተር የሌላ ሃይማኖት መጽሐፍ በትምህርት ቤት ውስጥ መከፋፈሉን ተቃውሙ፡፡ ያ መጽሐፍ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚከፋፈል ከሆነ ቢያንስ መጽሐፍ ቅዱስንም ማከፋፈል መፈቀድ አለበት አሉ፡፡ ይሄም ከፍተኛ ውዝግብን በማስነሳት ፓስተሩ በካናዳ የጥላቻ ንግግር ህግ ተከሰሱ፡፡ ቀላል ቅጣትም ተላለፈባቸው፡፡ በምዕራቡ አለም ሰው ክርስትናውን ባልጣለበት ዘመን ከመሬት ተነስተው የሃይማኖት ነጻነትን አመጡ፡፡ በነጻነት ስም ስራቸውን ሰርተው፣ ይኸው አሁን ክርስትያኖች ያ ሁሉ ታሪክ ተቀያይሮ፣ በግልባጩ ለሃይመኖት ነጻነት የሚታገሉበትና ክርስትያኖች የሚሰደዱበት ጊዜ እየመጣ ነው፡፡ በአሜሪካ ይሄ የጥላቻ ንግግር ህግ ያልጸደቀው ሁለት ሴናተሮች ስለ ተቃወሙት ብቻ ነው፡፡ በአለም ላይ መሰራጨቱና ወደ ከፋ ስደት መመራቱ፣ የጊዜ ጉዳይ ነው፡፡ ጥያቄው "ስለ ክርስቶ ስ የሚሰደድ ሰው ይኖራል ወይ?" የሚል ነው፡፡

እኔ ስለ ራሴ ሳስበው ይገርመኛል፡፡ ትምህርት ቤት እሄዳለሁ፣ እገባለሁ፣ አጠናለሁ፣ ቤት ውስጥ አንዳንድ ስራዎችን እሰራለሁ፣ ፌስቡክ እጠቀማለሁ፣ ፊልም አያለሁ፣ አነባለሁ፣ ቲቪ አያለሁ፡፡ ይሄ በዚህን ጊዜ የብዙዎቻችን ህይወት ነው፡፡ ሐዋርያት 17፡21፡ "የአቴና ሰዎች ሁሉና በዚያ የኖሩ እንግዶች አዲስ ነገርን ከመናገርና ከመስማት በቀር በሌላ ነገር አይውሉምና፡፡" ይላል፡፡ በየቀኑ ትምህርት ቤት እየሄድን አዲስ ነገር እናውቃለን፡፡ በዚህ ዘመን በየቀኑ ይሄ ዋና ስራ ሆኗል፡፡ አዲስ ነገር መናገርና መስማት፡፡
ስራ ያላቸው ደግሞ፣ ይነሳሉ፣ ቢሮ ይሄዳሉ፣ ይጽፋሉ፣ ኮምፒተር ላይ ሲያፈጡ ይውላሉ፣ ይሰበሰባሉ፣ ምናምን፡፡ እና ስራ ይሉታል፡፡ ስራ ላይ ነኝ ይባላል፡፡ እየተቀመጡ መዋል ምንድነው ስራነቱ? ስለ ውሎህ አስበው፡፡ በተለይ መኪና ባላቸው ይብሳል፡፡ ገንዘብ ስላስገኘህ ስራ አያስብለውምኮ፡፡ ተቀምጠህ ውለህ ገንዘብ ስላገኘህበት፣ መኪና ስለነዛህበትኮ ስራ ነው ማለት አይደለም፡፡ የጉልበት ስራዎችን እንዳሉ ማሽኖች እየተረከቡ ስለሆነ የሰው ልጅ ሰርቶ ሳይሆን አስቦ ለመብላት ተገዷል፡፡ ሰውኮ እንዲያውም ስራ ስለሌለው ነው የሚያስበው፡፡ ማሰብማ ቢሮ መሄድ ትተህ ዝም ብለህ ቤትህ ብትቀመጥም ታስባለህ፡፡ ሰዎች ልማት ይሉታል፡፡ አሁን ደግሞ የጉልበት(እውነተኛ) ስራዎችን ሁሉ ለሮቦቶች የሚያስረክብ እቅድ ተግባራዊ ሊደረግ ነው፡፡ ያኔ ሰዎች ምንም ስራ አይሰሩም፣ ዝም ብለው ይኖራሉ፣ መንግስት ይዶግማቸዋል፡፡ የቴክኖሎጂ ጉዞ ሰዎችን ስራ ፈት አድርጎ ተፈጥሮአዊ ያልሆነ፣ ተዘፍዝፎ የሚውል ማህበረሰብን መፍጠር ነው፡፡

መክብብ 5፡18፦ እነሆ እኔ ያየሁት መልካምና የተዋበ ነገር ሰው እግአብሔር ሰው በሕይወቱ ዘመን ሁሉ ይበላና ይጠጣ ዘንድ፣ ከፀሐይ በታች በሚደክምበት ድካም ሁሉ ደስ ይለው ዘንድ ነው፡፡ ይህ እድል ፈንታው ነውና፡፡

2 ተሰሎንቄ 3፡10፡- ሊሰራ የማይወድ አይብላ ብለን አዘናችሁ ነበርና፡፡

85% የሀገራችን ህዝብ ገበሬ ነው፡፡ እና ምንድነው ችግሩ? ባደጉት ሀገራት ገበሬው 5% ብቻ ነው፡፡ እሱንም በትራክተር ነው የሚታረሰው፡፡ አለም በስራ ፈቶችና በሰነፎች እየተሞላች ነው፡፡ ጥሮ ግሮ በልቶ እግዚአብሔርን አመስግኖ በሰላም ማደር ምንድነው ክፋቱ?
"በጠቅላላ ግን የአገሩ ጥቅም፣ እርሻን የሚወድድ ንጉስ ቢኖር ነው፡፡" መክብብ 5፡9፡፡
ደሃ በመሆናችን ምን ተጎዳን? ሌላው አለም የደረሰበት ቦታ አለመድረሳችንን ጉዳት እንለዋለን፡፡ እነሱ የት ደረሱ? እነሱ የት ደርሰው ነው እኛ እነሱ ጋር መድረስ የምንፈልገው?

ስለ መናገር መብት የምናወራው፣ መናገርን የሚከለክል አካል ሲኖር ነው፡፡ መናገር የምንፈልገው ግን ከንቱ ወሬያችንን መስማት የሚፈልግ ከንቱ ሰው ሲኖር ነው፡፡ ከዚህ አለም ጉዳይ የሌለው ትውልድ ቢኖር፣ ከዚያ ትውልድ ስሙኝ ስሙኝ የሚል ሰው አይወጣም፡፡ ጉዳዩን ከእግዚአሔር ጋር ብቻ ያደረገና አለምን የተወ ትውልድ ቢኖር ግጭትና ፍጅት ባልኖረ ነበር፡፡

የሰው ጥበብ ከንቱ ብቻ ሳይሆን አደገኛ ነው፡፡ ሰይጣን ህጻናትን ከሰው ነጥሎ፣ በኤሌክትሮኒክስና በመጫወቻ ከቦ ነፍሳቸውን ያጠምዳል፡፡ ተዘፍዝፈው መዋል፣ ውፍረት፣ አለመንቀሳቀስ ሁሉ የሰይጣን ስራ ነው፡፡ ከዚህ ሁሉ ራስንና ህጻናትን ማራቅ ጥበብ ነው፡፡

ት/ቤት 11ኛ ክፍል ስማር ማለትም ይሄን መጽሐፍ መጻፍ በጀመርኩበት አመት 2008 ዓ.ም. የሲቪክ አስተማሪ ፕረዘንቴሽን እንድናቀርብ በቡድን ርዕስ አካለፈለን፡፡ Government bodies, knowledge and reading የመሳሰሉ ርዕሶች ነበሩ የተከፋፈሉት፡፡ እኔ እጣዬ የሆነው the significance of knowledge ነበረ፡፡ የትምህርት ጥቅም፡፡ ሰፋ አድርጌ ነበር የጻፍኩት፡፡ ስለ ቃላቱ፣ ሲግኒፊካንስና ኖውሌጅ ማብራሪያ ሰጠሁ፡፡ እውቀት የሚገኝባቸውን መንገዶች አብራራሁ፡፡ መምህሩ ደስተኛ አልነበረም፡፡ እሱ የፈለገው ርዕስ አከፋፍሎ፣ እኛ ለስሙ ትንሽ አብራርተን ፖርሽኑ አልቆ፣ ነጥብ ይዞልን ለመውጣት ነበር፡፡ እኔ ግን ካለ ርዕሴ ገብቼ አራዘምኩበት፡፡ መጀመሪያ ላይ "ናትናኤል ጊዜ" አለኝ፡፡ ትንሽ ቆይቶ ወደ ሲግኒፊካንስ አፍ ኖውሌጅ ግባ አለኝ፡፡ የሚገርመው ስለ እውቀት ጥቅም ትንሽ ነበር የጻፍኩት፡፡ ገንዘብ ለማግኘት፣ ጥሩ ስራ ለማግኘት፣ ምናምን ብዬ ጠቅሼአለሁ፡፡ ሌላው ደግሞ ከሌላ ቦታ የሰማሁት "to make the world a better place to live in" ብዬ የጻፍኩት ነው፡፡ ሜክ ኤ ቤተር ፕሌስ? ስለዚህኛው ደስተኛ አልነበርኩም፡፡ ይሄን አባባል ብዙ ጊዜ የምሰማው ፊልም ላይ ነው፡፡ እውቀት አዎ ህይወትን፣ ያቀላል፣ መኪና ይፈጥራል፣ አካላዊ እንቅስቃሴን ይገድባል፣ ስራን አጥፍቶ የመዝናኛ ጊዜን ያበዛል፡፡ ባጠቃላይ ያሰንፋል፡፡ እውቀት ግን ደስተኛ ሳይሆን ህይወትን አሰቃቂ ነው የሚያደርጋት፡፡ እኛስ መኪናና ፎቃቸውን አይተን ህይታቸውን ለመኖር እንቋምጣለን፡፡ እነሱ ግን መፈጠራቸውን ይጠላሉ፡፡
እኔ ከጓደኞቼ የበለጠ ብዙ አውቃለሁ የምለው ሰውዬ፣ ምንም አያውቁም የምላቸውን ጓደኞቼን ሳይ እነሱን በሆንኩ እላለሁ፡፡ አለምን የተሻለች ቦታ ማድረግ ይበሉ እንጂ የተመሰቃቀለ ህይወት ነው የሚመሩት፡፡ ለዚያ ነው demerits of knowledge የሚል ርዕስ ፕረዘንቴሽኔ ላይ ቀጥዬ የጻፍኩት፡፡ እውቀት ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናልና የሚያመዝነው መረሳት የለበትም፡፡ እውቀት እንድንመረምር ያደርገናል፡፡ ብዙ መመርመር ደግሞ ለዲፕሬሽን ወይም ለጭንቀት ይዳርጋል፡፡ ስለዚህ ይሄ የእውቀት መጥፎ ጎኑ ነው፡፡ ማወቁ በቀረብኝ ያስብላል፡፡(መክብብ 2፡15) በሀገራችንም ባይሆን ብዙ ሰዎች በዲፕሬሽን ይጠቃሉ፡፡ ነገር ግን ከመሰቃየትና ህይወታቸውን እንደ መጥላታቸው መንስኤው ምን እንደ ሆነ አይረዱትም፡፡ በፕረዘንቴሽኔ ላይ ያልተማሩ ሰዎች ከተማሩት ይልቅ ደስተኛ ናቸው ብዬ ጽፌ ነበር፡፡ አስተማሪው ግን አቅርቤ ሳልጨርስ አቋረጠኝ፡፡

ያ ብቻ አይደለም፡፡ ከዚያ ወዲህ ባነበብኩት መጽሐፍ ላይ ይሄ አለምን የተሻለች ቦታ ማድረግ የሚሉት አባባል የኢሉሚናቲዎች መፈክር እንደሆነ አወቅኩ፡፡ ለዚያ ነው በፊልሙ ላይ የምሰማው ማለት ነው፡፡ ይሄ የሰይጣናውያን ስብከት የሰይጣን ብቻ ሳይሆን የሁላችንም ሆኗል፡፡ የተሻለ ህይወት እንፈልጋለን፣ ልማት፣ ቴክኖሎጂ፣ ሀብት ማካበት፣ ይህች አለም ያላትን ውድ፣ ብዙ ገንዘብ የሚያወጣውንና ደስታን ያስገኝልናል ብለን የምናስበውን ነገር ሁሉ መመኘት ብቻ ሳይሆን ሚሊየኖች ይሄን ፍለጋ እንደወጡ ቀርተዋል፣ ለዚህ ሲሉ ተጨፋጭፈዋል፣ ተፋልመዋል፣ ወድቀዋል፡፡ ይሄ የሰይጣናውያን ስብከት የሁላችንም ሆኗል፡፡ የፓስተሮቻችንም፡፡ ቢዝነሳችን እንዲያድግ፣ ሀገራችን እንድትለማ ቀን ተሌት ይጸልዩናል፣ ራዕይንም ያዩልናል፡፡ ነገር ግን ምንም ያህል አለም ላይ ያለ እያንዳንዱ ፓስተርና ቄስ ስለ ሀብታምነት ቢሰብክ፣ የተሻለ ህይወት በራዕይ ቢያይልን፣ ምንም እንኳን የሰይጣን ተልእኮ እኛ የምንኖርለትና የምንሞትለት የህይወታችን ግብ ቢሆን፣ ምንም እንኳን እኛ የዚህን አለም ሀብት እንጠቀም ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ብለን ብናስብ፣ እግዚአብሔርና ሰይጣን ለኛ ያላቸው አላማ፣ እንኳንስ አንድ ሊሆንና ሊመሳሰል፣ እንኳንስ ሊቀራረብ፣ ላይቃረን አይችልም፡፡ የሚያስፈልገን የአለምን ሀብት አሟጦ መጠቀም ሳይሆን፣ እምነታችንን ከሚያቀጭጩ ነገሮች መራቅ ነው፡፡ የአለም ብልጭልጭ ደግሞ መቀመቅ ነው የሚከተው፡፡ ከተባለ አይቀር ደግሞ እነሱ የተሻለ አለም የሚሉት ውሸት ነው፡፡ የተሻለ አለም የተሻለ ህይወት ሊሰጠን አይደል የሚገባው? የተሻለ ህይወት ደግሞ ደስተኛ ሆኖ መኖር ማለት አይደል? የእግዚአብሔር ቃል በዮሐንስ 14፡27 "ሰላምን እተውላችኋለሁ፣ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ፣ እኔ የምሰጣችሁ ሰላም ዓለም እንደሚሰጥ አይደለም" ይላል፡፡

CYC በተባለ የኦርቶዶክሶች ቻናል፣ በአንድ The Well በተሰኘ ሾው ላይ ቄሱ "MONEY PROMISES WHAT GOD PROVIDES" በሚል ርዕስ ስለ ገንዘብ አደገኛነት ሲያስተምር ነበረ፡፡ ገንዘብ ደስታን፣ ጤናን፣ ሰላምን፣ ደህንነትን፣ ክብርን ቃል ይገባልናል፡፡ ታዲያ ዛሬ ላይ ህይወታቸውን የምንመኘው ምዕራባውያን፣ በገንዘባቸው ከላይ የተጠቀሱትን ነገሮች አግኝተዋልን? ገንዘብ ደስታን አይገዛም እንላለን፡፡ ገንዘብ እንዲኖረን ግን አንጠላም፡፡ ገንዘብኮ ደስታ ባይሰጥም ለጊዜው ደስታን ይሰጣል፡፡ አዲስ ጫማ ሲገዛልኝ ለአንድ ሳምንትም ይሁን ለአንድ ቀን ደስ ይለኛል፡፡ አንድ ሰው መኪና ሲገዛ ደስ ይለዋል፡፡ መኪናውን ማጣት ግን ለዚያ ሰው ሞት ነው፡፡ አንዴ በመኪና ሲሸከረከር ታይቶ፣ እግረኛ መሆን ሞት ነው፡፡ ገንዘብን የመውደድ ወይም ለገንዘብ የመገዛት ትርጉምም ይሄው ነው፡፡ የግድ ለገንዘብ ብለህ ሰው መግደል

የለብህም፡፡ መኪና የገዛው ከአመት በኋላ መኪና ስላለው ደስ አይለውም፣ ግን ማጣትን ማሰብ ደግሞ ያስፈራል፡፡ ቢያጣው የሚያዝንበት ሀብቱ ብዙ ያልሆነና ትንሽ ነገር ሲያገኝ የሚደሰተው ደሃ ግን ደስተኛ ነው፡፡ ዛሬ በልቶ ስላደረ ደስ የሚለው ከሆነ ደስተኛ ነው፡፡ ሀብታሙ ግን ዛሬ በልቶ ስላደረ ደስ አይለውም፡፡ በልቶ ስላደረ እግዚአብሔርን አያመሰግንም፡፡ መደሰት ሊናፍቀውም ይችላል፡፡ ገንዘብ ለጥቂት ጊዜ ደስታን፣ ለረጅም ጊዜ ደግሞ መከራን ወደ ህይወታችን ይጋብዛል፡፡

በመንፈሳዊው ይቅርና በአለማዊው እንኳን ሁሉም ነገር ስለ ስሜቱ እንጂ ስለ መዝገቡ ብዛት አይደለም፡፡ "It is not about how much you have. It is about how you feel with what you got". በትንሽ ነገር አትደሰት፣ ትልቅ አልም ይላሉ፡፡ በትንሽ ነገር መደሰት ምንድነው ችግሩ? ከዚህ በላይ ጥበብ የታለ? ሰዎች ገንዘብን የሚያሳድዱት ደስታን ይሰጣል ብለው ስለሚያስቡ ነው፡፡ አንባቢዬ ተሳስተሃል እኔ ገንዘብን የማሳድደው ደስታን ፍለጋ አይደለም ልትለኝ ትችላለህ፡፡ እንደዚያ ባይሆን ግን ያለህን ሁሉ ለደሃ አከፋፍለህ የተንደላቀቀና የተደላደለ ህይወትን ማሯሯጥ ትተህ ሃብትህን ታርዘህ ከመዋል የሚከላከልህና ተርበህ እንዳታድር የሚያደርግህ ብቻ ታደርገው ነበር፡፡ ሰዎች ደስታን ለማግኘት፣ ገንዘብን ይከተላሉ፡፡ ነገር ግን ገንዘባቸውን ከምረው ደስተኛ አያረጋቸውም፡፡ ስለዚህ ደሃው ከሃብታሙ ይልቅ ደስተኛ ከሆነ፣ ደሃ መሆን ይሻላል ማለት ነው፡፡ ካለህ የገንዘብ ብዛት ጋር ስታወዳድረው ስሜትህ እንዴት ነው? ደስተኛ ነህ? ሀዘንተኛ ነህ? ደሃ የነበረ ሀብታም ከሆንክ የድህነትህን ዘመናትና የባለጠግነት ዘመናት ደስታህን አወዳድር፡፡ ባለጠግነትን የተመኘህበትን ጊዜና ሳትመኝ ባለህ አመስግነህ ብትኖር የሚኖረውን ልዩነት አስብ፡፡
መክብብ 5፡10፣ 1 ጢሞቴዎስ 6፡7፡፡

ምሳሌ 30፡8፡- ከንቱነትንና ሐሰተኛነትን ከእኔ አርቃቸው፡፡ ድህነትንና ባለጠግነትን አትስጠኝ፡፡ ነገር ግን የሚያስፈልገኝን እንጀራ ስጠኝ፡፡ እንዳልጠግብም እንዳልክድህም፡፡ እግዚአብሔርስ ማን ነው? እንዳልል፡፡ ድሀም እንዳልሆን እንዳልሰርቅም፣ በአምላኬም ስም በሐሰት እንዳልምል፡፡

በአሜሪካ ከ40-50% መነሻቸው ቃል ኪዳን የሆነ ባልና ሚስት፣ ፍቺ መዳረሻቸው ይሆናል፡፡ እንደፈለጉ መጋባትና መፋታት አያስደስትም ወይ? ነጻነት ስላላቸው ነውኮ፣ እንደኛ የሚያስር ባህል ስለሌላቸው ነው ልትለኝ ይሆናል፡፡ ጥያቄው አንዴ ካገቡ ለምን በትዳራቸው ተደስተው መኖር አይችሉም? እንደ ከረሜላ ተማጥጠው ለምን ይተፋፋሉ? እናትና አባቴ ሳይፋቱ ለምን ኖሩ? የአሜሪካ ባልና ሚስትስ ይሄ ለምን አቃታቸው? እነሱ የተማሩ አይደሉ? አዋቂ አይደሉ? የራሳቸው ቢቀር እንዴት እያወቁ ልጆቻቸውን ያንከራትታሉ? በአሜሪካና በኢትዮጵያ ባለ ትዳሮች መሃል ያለው ልዩነት በርግጠኝነት የዜግነት ብቻ አይደለም፡፡ ከኋላው ብዙ ነገሮች አሉ፡፡ እንዲሁ እንደ ቀልድ የሚለያዩት ባልና ሚስት ልጅ ለብዙ ስቃይ ይዳረጋል፡፡ ይሄ ጉዳይ ለብዙዎቻችን ይሄን መጽሐፍ ለምናነብ ሰዎች ቀምሰነው ስለማናውቅ ቀላል ሊመስለን ወይም ክብደቱ ላይታየን ይችላል፡፡ በአሜሪካ 40ና 50 ፐርሰንት ትዳር በፍቺ ይቋጫል ማለት፣ የእናትና አባቱን ተለያይቶ፣ የተለያየ ቤት ውስጥ መኖር፣ ሌላ ማግባት፣ ሳይቀምስ የሚያድግ ልጅ በጣም ጥቂት ነው ማለት ነው፡፡ እናትና አባቱ ሲለያዩ ከማን ጋር መኖር ትፈልጋለህ የሚባል ማለት ነው፡፡

1. የአባትና እናታቸውን መለያየት የሚጋፈጡትን ልጆች ብዛት አስብ፡፡
2. ያለ ትዳር የሚወለደውን ልጅ ብዛት አስብ፡፡
3. ሳይፋቱ ደግሞ ጤናማ ቤተሰብ የሚመሩ ምዕራባውያን ምን ያህል እንደሚሆኑ ገምት፡፡
   ከዚህ ሶስት ነጥቦች ተነስተህ በምዕራቡ አለም ቤተሰብ የሚባል ነገር ቅርፊቱና ውሃው እንጂ፣ አስኳሉ በቦታው እንደሌለ ትረዳለህ፡፡

2008 ዓ.ም. 11ኛ ክፍል ስማር፣ ፌስቡክ ላይ የፈረንጆችን ሳይኮሎጂ፣ አስተሳሰብ፣ ፖለቲካ፣ የማወቅ ጉጉት ስለነበረብኝ ዝም ብዬ የዜና አውታሮችን እነቢቢሲን፣ ሲኤንኤንን ላይክ አደርግ ነበር፡፡ ስለፈረንጆቹ የማጠናው ከሚሰጡት ኮሜንች ነበር፡፡ ታዲያ አንዴ አንድ ላይክ ያረግኩትና ስሙን የማላስታውሰው ሚዲያ "ኦንላይን እየተቀረጹ የተደረጉ አስደንጋጭ የራስ ማጥፋቶች" በሚል ርዕስ አንድ ሊንክ ሼር ያረጋል፡፡ በዚህ ፖስት ላይ የተሰጡትን ኮሜንቶች ሳነብ ምን ባገኝ ጥሩ ነው? አንድ የፈረንጅ ስም ነው፡፡ "I am 13, but I wanna commit a suicide" "13 አመቴ ነው ግን እራሴን ማጥፋት እፈልጋለሁ" ይላል፡፡ ስለዚህ ጉዳይ ለማረጋገጥ እንደገና ጉግል ሳረግ ደግሞ፣ አንዷት የ12 አመት ልጅ በፌስቡክ ቀጥታ ስርጭት 15000 ሰው እያየ እራሷን እንዳጠፋች ዜናውን አነበብኩ፡፡ እንዲህ አይነት ብዙ ዜናዎች ይሰማሉ ማለት ነው፡፡ ይህቺ ልጅ እራሷን ያጠፋችው በወላጆቿ ምክንያት ላይሆን ይችላል፡፡ ግን እባክህ ኢትዮጵያ ውስጥ በ12 አመቱ እራሱን ለማጥፋት የሚያስብ ልጅ ካወቅክ አስተዋውቀኝ፡፡ እነሱ የ12 አመት ልጅ እራሷን የምታጠፋበትን አለም የተሻለ አለም ነው ይሉናል፡፡ ያ አለም ግን እነሱ በውሸት የተሻለ አለም የሚሉት አስቀያሚ አለም ብቻ ሳይሆን እኛ የምንቋምጥለት፣ ሲጋና ነፍሳችንን የምናባክንለት፣ ብዙዎች በበረሃ ህይወታቸውን የሚሰዉለት፣ ብዙዎች ለወታደር ጠብመንጃ እራት የሚሆኑለት ከንቱ አለም ነው፣ ወንድም አለም፡፡

እኔ በ12 አመቴ ሳድግ ቪላ ቤት ነው ወይስ ግራውንድ ፕላስ የሆነ ቤት ውስጥ ነው የምኖረው? የሚለው ነበር የሚያሳስበኝ፡፡ ምን አይነት መኪና ነው የምይዘው ብዬ ነበር የምጨነቀው፡፡ ምን አይነት አስቀያሚ ህይወት ቢኖረው ነው ሰው በ13 አመቱ እራሱን ስለ ማጥፋት የሚያስበው?

"ሰላምን እተውላችኋለሁ፣ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ፡፡ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጥ አይደለም፡፡ ልባችሁ አይታወክ አይፍራም፡፡" የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ፡፡

የእግዚአብሔር ቃል "መንፈስ ለአብያተ ክርስትያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ" ይላል፡፡ የእግዚአብሔር ቃል በኤፌሶን 5፣ ከ22 ጀምሮ ባልና ሚስት እንዴት መኖር እንዳለባቸው ከክርስቶስና ከቤተ ክርስትያን ጋር አያይዞ ሲገልጽ በቁጥር 32 "ይህ ምስጢር ታላቅ ነው፣ እኔ ግን

ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተ ክርስትያን እላለሁ" ይላል፡፡ በ 1 ቆሮንቶስ 11፡16 ደግሞ "ዳሩ ግን ማንም ሊከራከር ቢፈቅድ፣ እኛ ወይም የእግዚአብሔር አብያተ ክርስትያናት እንዲህ ያለ ልማድ የለንም፡፡"
የእግዚአብሔር ቃል ስለ ወንድና ስለ ሴት ምን እንደሚል አይተናል፡፡ ሴት ሰውን ከብቸኝነቱ ለመገላገል እንደ መምጣቷ በረከት ነች፡፡ የተሳሳተችው እሷ በመሆኗና ለሰው ውድቀት ምክንያት በመሆኗ ደግሞ እርግማን ነች፡፡ ለዚህ መፍትሄው 1 ጢሞቴዎስ 2 ውስጥ ተቀምጦልናል፡፡

ዘመኑ ሴትና ወንድ እኩል ናቸው የሚል ትምህርት ይዞ መጣ፡፡ ሴቶች ልጆች ቃሉ እንደሚለው በቤተሰባቸውም ሆነ በአብያተ ክርስትያናት በዝግታ እንዲኖሩ የሚመከራቸው ሰው የለም፡፡ ትምህርት ቤት ካሪኩለሙ ለሙብታችሁ ታገሉ ይላቸዋል፣ ከወንድ ጋር እኩል ናችሁ ይላቸዋል፣ ሚዲያውም ይሄን ሰይጣናዊ ወሬ ያናፍሳል፡፡ በአለም ፍልስፍና የሚነዱት ቤተሰቦቻችንም ይሄኑ እየመከሩ እየዘከሩ ልጆቻቸውን ያሳድጋሉ፡፡ ወንድ የሚሰራውን ሴት መስራት ትችላለች፣ ሴት የምትሰራውን ወንድ ቢሰራ ነውር የለውም፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ታላቅ ምስጢር ቢለውም ቤተ ክርስትያንም ይሄን ከመስበክ ይልቅ ሴቶች አስተማሪዎችን ማብዛት መረጠች፡፡ ቃሉን አጣሞ ከዘመኑ ጋር ማስኬድ የሚፈልግ በዛ፡፡

በፊት ሴት ለባሏ እንድትታዘዝ፣ ቃሉ ላይ እንዳለው እንድትኖር ተደርጋ ስትመከር፣ አሁን ይኸው እንደምናየው ነው፡፡ እኩል ነሽ ነው፡፡
በፊት ሴት ቤት ወስጥ የምትሰራና ልጆች የምታሳድግ፣ ባል የውጪ ስራ የሚሰራ ሲሆን፣ አሁን ሚስት ካሻት መከረኛውን ወሊድ መከላለያ ወስዳ የፈለገችውን ያህል ትወልዳለች፡፡ ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው የሚለው ቃል እዚህ ጋር ቦታ አይሰጠውም፡፡ የልጅ ቁጥር ይመደባል፡፡ ለምን? ገንዘብ ለመቆጠብ፣ ልጆች ሆድ ውስጥ ይገደላሉ፡፡ በዚህ ብቻ ከሚመጣብን እርግማን ወዴት እንደምናመልጥ እኔ አላወቅም፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ብዙ ልጆች በረከት እንደሆኑ ይናገራል፡፡ እኛ ግን ብዙ ልጆችን እንደ እርግማን አድርገናል፡፡ ኢሳይያስ 5፡20 ለዚህ መልስ አለው፡፡ አሁን ትዳር ቢዝነስ ነው፡፡ ለዜግነት ተብሎ መጋባት፣ ገንዘብ ለመውረስ ማግባት... የእግዚአብሔር ቃል የቤቱ ራስ ወንድ ነው ይላል፡፡

እኔ መማር በሚባለው ነገር አላምንም፡፡ መማርን ይሁን ብንል እራሱ ግን የሴቶች መማር፣ አንድን ትዳር ትዳር ሳይሆን የክርክር መድረክ ያደርገዋል፡፡ ሚስት ባሏ ለሚላት ነገር ተገዢ መሆን አለባት፡፡
በዚህ ሁሉ ውስጥ አብያተ ክርስትያናት ከዘመኑ፣ ከሚዲያው፣ ከፊልሙ ጋር ከፖለቲካው ጋር እራሳቸውን እያጣጣሙና እያዘመኑ ሲሄዱ፣ ዮሐንስ ራዕይ በተደጋጋሚ መንፈስ ለአብያተ ክርስትያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ ይላል፡፡
ትምህርት ወይም እውቀት የማይነካው ነገር የለም፡፡ አዕምሮአችን ተለወጠ ማለት፣ ሁሉም ነገር ተለወጠ ማለት ነው፡፡ የሆነ ነገር ሲለወጥ በአዕምሮአችን ነው መለወጡን የምንገነዘበው፡፡ አዕምሮ እራሱ ሲለወጥ ደግሞ ሁሉም ነገር ይለወጣል፡፡ ትምህርት አደገኛ ነገር ነው፡፡

ሌላው ቤተሰብ የሚበጠብጠው ቴክኖሎጂ ነው፡፡ ቲቪ፣ ኢንተርኔት የመሳሰሉ ቴክኖሎጂዎች፣ ትኩረታችንን ከቤተሰባችንና ባካባቢያችን ባሉ ሰዎች ላይ እንዳናደርግ ሰይጣን የፈጠራቸው ነገሮች ናቸው፡፡ ማታ ማታ ተቀምጠን ቲቪ ላይ ስናፈጥ እንውላለን፡፡ ቲቪው የአለም ወሬ ሲያንቀረቁር እኛ ዝም ብለን እናዳምጠዋለን፡፡ በአለም ላይ ከሰው ጋር ማውራት አለ፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ማውራት አለ፡፡ ጸሎት ደግሞ አለ፡፡ እኛ እናወራለን እግዚአብሔር ይሰማል፡፡ በየቀኑ ማታ ማታ ቤተሰብ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ቤተሰባዊ ፍቅርን መካፈል ሲቻል ላም አለኝ በሰማይ የሆነ ወሬ ሲጠጡ መዋል፣ ቤተሰባዊ ፍቅርን ያሻክራል፡፡ እኛ የማያስፈልገን ወሬ፣ ትኩረታችንን ከቲቪው ላይ ነቅለን ወደ ቤተሰባችን እንዳንመልስ ምርጥ ምርጥ ሰዎች ዩኒቨርሲቲ ገብተው የኛን ትኩረት የሚስቡበትን መንገድ ይሰለጥናሉ፡፡ ጋዜጠኞች ይባላሉ፡፡ ባለህበት ከተማ እንኳን የሆነ ሰው ከሞተ ወይም የሆነ ነገር ከተፈጠረ፣ ወሬውን ከጎረቤትህ እንዳትሰማ ሚዲያዎች ፈጥነው ከጆሮህ ያደርሱታል፡፡ ታዲያ መስማት ያለብህን ከቲቪ ከሰማህ ለምን ብለህ ከጎረቤትህ ጋር ታወራለህ? ቤስት ፍሬንድህ ማን ነው ብልህ አንድ የሰው ስም እንደምትጠቅስልኝ እርግጠኛ ነኝ፡፡ ነገር ግን ስልክህን እይ፣ ካንተ የማይለይ፣ መስማት ያለብህን የሚያሰማህ፣ ከሰው ጋር የሚያገናኝህ፣ ማወቅ ያለብህን የሚያሳውቅህ፣ የሚያጫውትህ፣ የሚያዝናናህ፣ ብዙ ሰዎች እንዲያውቁ የማትፈልጋቸውን ነገሮች ጭምር በነጻነት እንድታደርግ የሚያደርግህ ሚስጥረኛህ፣ ብዙ ጊዜ የምታጠፋበት ነገር፣ ከምርጥ ጓደኛ ቀርቶ ከሚስትህ፣ ከወላጆችህና ከቤተሰብህ አይበልጥብህም?

ችግሩ ቴክኖሎጂ ሰው መሆን አለመቻሉ ነው፡፡ ቴክኖሎጂ ህይወታችንን ለማቅለል ሳይሆን ህይወታችንን ፍቅር የሌለበት፣ መተሳሰብ የሌለበት፣ ለማድረግና ከማህበራዊ ህይወት እኛን ለማራቅ የተፈጠረ ነገር ነው፡፡ ፍቅር ከሌለን ባዶ እንደሆንን የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል፡፡ ቴክኖሎጂ ስለሌለ እንደ ከተማው ስላልተስፋፋ ነው በገጠር ከፍተኛ የመተሳሰብ ነገር የምናስተውለው፡፡ ሁሉም ነገር እምነታችን ላይ ተጽእኖ አለው፡፡ ቴክኖሎጂ ዋና ግቡ፣ ሰዎችን ማበላሸት ነው፡፡ ለሃጢአት ቅርብ ማድረግ ነው፡፡ 2 ዮሐንስ 1፡12

በፊት ቤት የማይቀመጥ፣ የሚዞር ልጅ ነበር ዱሪዬ የሚባለው፡፡ አሁን ግን ቲቪና ፊልም ከመጡ በኋላ ቤትን አደገኛ ስፍራ ሲያደርገው፣ ማህበረሰቡን በጠቅላላ በአንጼ ዱሪዬ የማድረግ ሃይል አለው፡፡ ሃይማኖት ለይስሙላ የሆነበት ጊዜ ላይ ነን፡፡ ሰይጣን ቤታችን ውስጥ አስቀምጠን ቸርች የፈለግነውን ብለን ብንገባ ዋጋ የለውም፡፡ ስንጸልይ ውለን፣ እኔም ፓስተሬም ፊልም ስር የምንገለት ከሆነ እምነት ዋጋ አላጣም? ፊልሞችና ቴክኖሎጂ፣ በፍጥነት ማህበረሰባችንን ወደ ማይገመት አዘቅት እየከተቱት ይገኛሉ፡፡

አንዳንድ ሰዎች ስለ ገንዘብና ስለ ቴክኖሎጂ ሲነሳ ወንጌልን ለማስፋፋት ይጠቅማል ይላሉ፡፡ መጀመሪያ ነገር እግዚአብሔር ወንጌልን ለማሰራጨት ገንዘብን(የሰይጣንን እቃ) ተጠቀሙ አላለንም፡፡ ሁለተኛው፣ ሲጀመር እንዲህ የምንለው ሃይማኖትን ሁለተኛ ላይ ስላስቀመጥን ነው፡፡ አንደኛችን የሰይጣን ስለሆነ ነው፡፡ እናት ምንም ልጇ ክፉ ቢሆን ለሰው፣ ያለውን መልካም ጎን ፈልፍላ፣ ጨማምራበት ትናገራለች እንጂ ስለክፋቱ ምንም አትልም፡፡ ምክንያቱም ልጇን ቆርጣ አትጥለውም፡፡ እኛም የሰይጣንን መሳሪያዎች ቆርጠን ለመጣል ፈቃደኞች

ስላልሆንን መልካም ጎን የምንለውን ነገር አፈላልገን ትልቁንና ልንሸፍነው የማንችለውን መርዝ ልንሸፍንና ልንለብጥ እንሞክራለን፡፡ ክርስቶስም አይንና እጅ ጠቃሚ ስላልሆኑ አይደለም የሚያሰናክሉን ከሆነ ቆርጠን እንድንጥላቸውና አይንና እጃችንን አጥተን የእግዚአብሔርን መንግስት ብንቀላቀል እንደሚሻለን የነገረን፡፡

የቴክኖሎጂ ግቡ ሰይጣናዊ ማህበረሰብ መፍጠር ነው፡፡ የመጣውም ከድሮ ከጣኦት አምላኪዎች ከግብጽ፣ ግሪክ፣ ሜሶፖታሚያን የመሳሰሉ ስልጣኔዎች ነው፡፡ ኬሚስትሪ የሚለው ቃል ውስጥ ኬሚ የሚለው ቃል የድሮ የመድሃኒት ጣኦት ስም ነው፡፡ አቲና ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ላይም እንደተጠቀሰው የግሪኮች የጥበብ ጣኦት ነች፡፡ የ ቴክኖሎጂ ግቡም ሰዎችን በሃጢአት ውስጥ መዝፈቅ ብቻ ነው፡፡

እየኖርንባት ያለችው አለም የመጨረሻው ክፋት፣ ውድድር ነው፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ እንዳለው አለም አሸናፊዎች እንጂ ተሸናፊዎች የማይኖሩባት እየሆነች ነው፡፡ ለኔ ግን ይህቺ አለም አሸናፊ የሌለባት የውድድር መድረክ ነች፡፡ አሸናፊ የሚባሉት መቼም ሀብታሞቹና ዝነኞቹ ናቸው፡፡ እነሱ ደስተኛ ካልሆኑና እንደ ሮብን ዊሊያምስ ያሉት እራሳቸውን ካጠፉ፣ አሸናፊው ማን ነው ታዲያ፡፡ የፊልምና የዘፋኞች፣ የመዝሙርም ይሁን፣ የቲቪ ችግር ይሄ ነው፡፡ ትኩረትህን ከአካባቢህ ወደማታውቃቸውና ወደማያውቁህ ሰዎች እንድታደርግ ያደርጉሃል፡፡ እነኛ በቲቪ ላይ የሚታዩ ሰዎች ደግሞ ሁሉም ቤት ስለሚታዩ ታዋቂ ይሆናሉ፡፡ ይሄም ታዋቂ ሆኖ በቲቪ ላይ እየታዩ የመዋል ፍላጎትን በሰው ውስጥ ይጭራል፡፡ የህይወት ግብህ ዝና ይሆናል፡፡ አንድ ዘፋኝ ታዋቂ ሲሆን ስለ ሰውየው አይደለም ጉዳዩ፡፡ እንደሱ የመሆን ጥማት የሚጠናወተው የህዝብ ብዛት እንጂ፡፡ ህይወት ቲቪና ስልክ በሆነችበት አለም፣ ዝነኛ ካልሆንክ የኖርክ አይመስልህም፡፡ የጎረቤትህን ስም የማታውቅና የፊልም ተዋናዮችን ታሪክ አብጠርጥረህ የምታውቅ ከሆነ፣ ጓደኛ ከሌለህና ዘፋኞችን በጣም የምትወድ ከሆነ ህይወትህ ቲቪ ውስጥ ነው ማለት ነው፡፡ እየኖርክ እንዲመስልህ ደግሞ የቲቪው ስክሪን ላይ መንቀሳቀስ አለብህ፡፡

እንደ አሜሪካ ባሉ ሀገራት ዝነኝነት የህይወታቸው ግብ ነው፡፡ በእንደኛ አይነት ሀገራት ግን ቀስ በቀስ እየተሰራጨ ያለ ነገር ነው፡፡ በፊት ቲቪ ላይ ለመቅረብ በሀገር ደረጃ ነበር ፉክክሩ፡፡ አሁን ደግሞ ፌስቡክ ጨዋታውን ወደ ሰፈርና ወደ ከተማ በማውረድ ዝነኝነትን የእለት ተእለት ህይወታችን ክፍል አድርጎታል፡፡ ለፎቶ ብዙ ላይክ ለማግኘት የሚለቀቁ ፎቶዎች፣ እራስን ከሌሎች ጋር ማወዳደር፣ በጣም አደገኛ ጨዋታ ነው፡፡ እንዲህ አይነት ነገሮች ማህበራዊ ህይወትን ለማኮላሸት የተፈጠሩ ነገሮች ናቸው፡፡ ሰውን ያለ መጥገብን፣ ብዙ የመፈለግንና በስጋዊ ፍላጎቶች ተነድቶ መጥፋትን የሚያስከትሉ ነገሮች ናቸው፡፡ ከጓደኞቻችን ጋር እራሳችንን እንድናነጻጽር ሲያረጉን ውድድር ውስጥ ይከቱናል፡፡ በሌላ በኩል ሰፊ ጊዜ እነዚህ ቴክኖሎጂዎች ላይ ስናጠፋ እውነተኛውን ፍቅር ያለበትን ህይወት ይቀንሳሉ፡፡ የብቸኝነትንና ሰዎችን የመጥላትን ህይወት ያለማምዱናል፡፡

በመንፈሳዊውም፣ ቻናል መክፈት፣ መዝሙር በሲዲ ማውጣት፣ የመሳሰሉት ነገሮች በዋነኝነት እግዚአብሔርን ለማክበር ሳይሆን ለዝና የሚደረጉ ነገሮች እንደሆኑ በአምስት ጣቴ እፈርማለሁ፡፡ በርግጥ ቴክኖሎጂ የሚያመጣውን ዝና የእግዚአብሔር በረከት አድርገው ሲናገሩ፣ ከነቢያቱም፣ ከዘማሪዎችም ሰምቼአለሁ፡፡ መጨረሻው ግን መሰናከል ነው፡፡ ዋው ድምጹ እንዴት ያምራል?
ለምን በማይክ ይዘመራል? በማይክ ሲዘመር ሰው ስለሚነቃቃ? ደስ ስለሚል? እግዚአብሔርስ? እግዚአብሔር ከሱ ይልቅ ዘማሪዎች ላይ ትኩረት ማረጋችን ደስ ይለዋል? ቲቪ ላይ ለመውጣት ወይም ዝነኛ ለመሆን ለምናደርገው ተጋድሎ፣ የምንጠቀመው የእግዚአብሔርን ስም ሲሆን ክፋቱ ይብሳል፡፡ አንድ ሰው ዝነኛ በመሆኑ የሚከተለው ግርማ ሞገስ፣ ሌላውን እንዳለ ይዞት ይጠፋል፡፡

እኔ በዚህ ቃና ቲቪ ቀኑን ሙሉ በሚንቆረቆርበት ዘመን፣ እራቱን የተቃጠለ ወጥ ለመብላት የሚገደደው ባል ሳይሆን፣ ቃና ላይ ስታፈጥ ቤቷን የምትረሳው ሚስት ሳትሆን በቃና ዘመን የሚወለዱና የሚያድጉ ህጻናት ናቸው የሚያሳዝኑኝ፡፡ ቤቱ ትኩረቱን ሁሉ ቃና ላይ ሲያደርግ፣ የሚገባውን ፍቅር ሳያገኝ የሚያድገው ልጅ፣ ዘመኑን ሙሉ ምንም የማያጠፋው የወላጆቹን ፍቅር ማጣት አብሮት ያድጋል፡፡ ብዙ ወላጆች ሰራተኞች ከሆኑና ከልጆቻቸው ጋር የሚገናኙት ማታ ከሆነና ማታ ደግሞ እስከ 5 ሰአት ቃናን የሚያዩ ከሆነ ህጻኑ ወላጅ አልባ ሆነ ማለትም አይደል? ወጥቶ ከእኩዮቹ ጋር ከመጫወት ይልቅ መጀመሪያ የሚማረው ነገር ቲቪ ላይ ሲያፈጡ መዋልን ሲሆንናም፣ በጣም ያነሰ ማህበራዊ ህይወት ይኖረዋል፡፡ ከሰው ጋር በፍቅር መኖር ሲከብደው ይኖራል፡፡ ከሁሉም የሚያስፈራኝ ደግሞ ቃና ገና መጀመሪያ ብቻ መሆን መቻሉ ነው፡፡ ከድራማዎቹና ከዘፈኖቹ ህጻናት የሚለቅሙት ሀሳብ ደግሞ ነገሮችን የከፋ ያረጋሉ፡፡ በሀገራችን እየበዙ ያሉት ከንቱ የቴሌቪዥን ቻናሎችም ሳይረሱ፡፡

ልማት ማለት እኮ ብዙ ትምህርት ቤቶች፣ ብዙ ናይት ክለቦች፣ ብዙ በልተው የጠገቡ፣ ከምግብ የሚገኝን ደስታ ቀምሰው የጨረሱ፣ ስልክ ያላቸው ሰዎች፣ ኢንተርኔት የሚጠቀሙ ሰዎች፣ ፊልም ሲያዩ የሚውሉ ሰዎች፣ የሚፋቱ ባልና ሚስቶች፣ በምኞት ምክንያት የሚያስቡትን ያጡና እግዚአብሔርን የሚገዳደሩ ሰዎች ሲበዙ ማለትኮ ነው፡፡ እናም የእግዚአብሔርን ቃል እመን፣ ምንም በጎ ነገር የለውም፡፡

የጥላሁን ጉግሳ ስህተት በአዲስ አመት

“በእግዚአብሔር ጥበብ ምክንያት ዓለም እግዚአብሔርን በጥበብዋ ስላላወቀች፣ በስብከት ሞኝነት የሚምኑትን ሊያድን የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖአልና፡፡” 1 ቆሮንቶስ 1፡21

ጥላሁን ጉግሳ ሲጄ ቲቪ ላይ በ2009 አዲስ አመትን በማስመልከት በነበረው ልዩ ዝግጅት ተጋብዞ ቃለ መጠይቅ ተደረገለት፡፡ ቃለ መጠይቁ ባብዛኛው የሚያጠነጥነው አርትንና ቤተ ክርስትያንን በማጣመር ላይ ነው፡፡ ቃለ መጠይቁ ጥሩ ማስተማርያ መንገድ ስለመሰለኝ፣ የዚህ መጽሐፍ ግብአት እንዲሆን ለማድረግ ብዬ ፕሮግራሙ ሲደገም ቃለ መጠይቁን በስልኬ የድምጽ መቅጃ ቀዳሁት፡፡

ሲጄ ቲቪ፡- መጀመሪያ ወንጌልና አርትን እንዴት አንድ ላይ ማጣመር ይቻላል? ምክንያቱም ብዙ ሰዎች፣ ትወና፣ አርት ሚባለውን ነገር የሚያዩት ከአለማዊ ነገር ጋር ነው፡፡ ከመዝናናት ጋር፣ ከተለያዩ ነገሮች ጋር ነው፡፡ ግን ብዙ መንፈሳዊ ነገሮች በአርት ይሰራሉ፡፡ ጥበብ ራሱ ከቤተ ክርስትያን ነው የመጣው፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር የጥበብ አምላክ ስለሆነ፡፡ እሱን እንዴት ታያለህ?

እኔ፡- እግዚአብሔር የጥበብ አምላክ ነው፡፡ ጥበብ ደግሞ ለሁለት ይከፈላል፡፡ የብርሃን ጥበብና የጨለማ ጥበብ፡፡ የእግዚአብሔር ጥበብና የሰይጣን ጥበብ፡፡ እግዚአብሔር እነአዳምን የከለከለውና ሰይጣን እነአዳምን ያታለለበት ጥበብም ጥበብ ነው፡፡ ያ ክፉው ጥበብ ግን የእግዚአብሔር(godly) ጥበብ አይደለም፡፡

ጥላሁን ጉግሳ፡- አጠቃቀሙ ላይ ነው ትልቁ ነገር፡፡ ማንኛውም ነገር፣ አጠቃቀሙ ላይ ነው፡፡ ይሄ ሳውንድ ሲስተም ባጋጣሚ ተገዝቶ ለናይት ክለብ ሊሆን ይችላል፡፡ ይሄ ሳውንድ ሲስተም እዚህ መጥቶ ደግሞ ለአምልኮ ሊሆን ይችላል፡፡ (ህዝብ ያጨበጭባል)፡፡ አርት በዋናነት የቤተ ክርስትያን ንብረት ነው፣ በንብረትነት ደረጃ፡፡(ጭብጨባ)፡፡ ለምሳሌ በአዲሳባ ዩኒቨርሲቲ በአርት ዲፓርትመንት ውስጥ ወይም በዚህ በትያትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ውስጥ ከሚሰጡት ኮርሶች አንዱ ሂስትሪ ኦፍ ቲያትር የሚል አለ፡፡ ሂስትሪ ኦፍ ቲያትርን በምናጠናበት ጊዜ፣ የትያትር መጀመሪያው፣ መነሻው ቤተ ክርስትያን ነው ነው የሚለው፡፡ ምክንያቱም አንድ ትያትር ለመስራት አስፈላጊ የሚባሉ ነገሮች አሉ፡፡ እነዚያ ነገሮች ደግሞ ተሟልተው ለመጀመሪያ ጊዜ የታዩት ቤተ-ክርስትያን ውስጥ ነው፡፡ ስለዚህ አርት መጀመሪያውም፣ መነሻውም፣ መፍለቂያውም ቤተ ክርስያን ነው፡፡ አክቹዋሊ አርት ብቻ አይደለም፡፡ ማንኛውም በዚህ አለም ውስጥ ያሉ ነገሮች መነሻቸው መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡ ስለ መከላከያ ሰራዊት ብንወስድ መነሻው መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡ ስለ ሳይንስ ጥበብ ብንወስድ መነሻው መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡ ስለ ህዝብ አስተዳደር ብንወስድ ከነሙሴ የሚጀምር መነሻው መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡ የሁሉ ነገር መሰረትና መነሻ መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡(ጭብጨባ)፡፡ አርትም መነሻው ቤተ ክርስትያን ነው፡፡ ከዚያ እያደገ መጥቶ ለተለያየ አገልግሎት ውሏል፡፡ ስለዚህ አሁንም ከወንጌል ጋራ የሚኖራቸው አንድነትና ልዩነት፣ እንዳጠቃቀሙና እንደምንጠቀምበት ቦታ፣ እንደምንጠቀምበት ሁኔታ ይለያያል እንጂ አርት የቤተ ክርስትያን ንብረት ነው፡፡ ስለዚህ እኔ አርት ችግር አለው ብዬ አላስብም፡፡(ጭብጨባ)፡፡

እኔ፡- መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ስለ ትያትር የሚናገር ቦታ የለም አይደል ግን? ከስብከት፣ ከመዝሙር፣ ከትንቢት፣ ከልሳን ጎን ጳውሎስ ድራማን አልጻፈም አይደል? በርግጥ አስፈላጊ የሚባሉ ነገሮች ተሟልተውም ይሁን ሳይሟሉ፣ ግሪኮች ከጥንት ጀምሮ ትያትረኞች ነበሩ፡፡ ቤተ ክርስትያን ውስጥ ትያትር ይሰራ ስለ ነበረ አርት መነሻው ቤተ ክርስትያን ነው? በርግጥ እውነቱ የአርት መነሻ ጥንታዊ የግሪክ ስልጣኔ ነው፡፡ እንዲያውም አሪስቶትልን "የትያትር አባት" ይሉታል፡፡ የድሮ ቤተ ክርስትያን ጽድቅን በገንዘብ ብላ ታስተዋውቅ ስለነበረ ያን መቀበል አለብን ማለት ነው እንዴ? ድሮ ስለነበረ ትክክል ነበሩ ማለት አይደለም፡፡ የጥንት ቤተ ክርስትያን ትምህርት ቤቶችንና ዩኒቨርሲቲዎችን ፍጹም የእግዚአብሔርን ቃል በሚቃረን መልኩ ስላስጀመረች፣ ትምህርት የቤተ ክርስትያን ነው ማለት አንችልም፡፡ ምክንያቱም ቤተ ክርስትያን ማለት ክርስቶስ ነው፣ ክርስቶስ የኔ ነው ያላለውን ነገር ደግሞ በድሮ አስታከን የክርስቶስ ማድረግ አንችልም፡፡ ክርስቶስ የሕይወት መንገድ እንጂ ወደ ጥፋት የምናመራበት መንገድ አይደለምና፡፡

ሲጄ ቲቪ፡- ከዚህ ጋር አያይዤ አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ፡፡ በዚሁ በመንፈሳዊ አርት አንድ ስብስብ ነበራችሁ፡፡ አርት ሚኒስትሪ ማለት ነው፡፡ በሱ በጣም ብዙ ገጠሮች፣ የተለያዩ ሞባይል ኤሪያዎች በመሄድ በጣም ወንጌል ሰብከችኋል፡፡ ወንጌልን በመናገር ሳይሆን፣ ድራማ በማሳየት ብቻ በጣም ብዙ ሰዎች ጌታን እንዳገኙ መረጃው አለኝ፡፡ ስለሱ ስብስብና ምን ያህል ጌታ ይጠቀምበት እንደነበር ስለሱ እስቲ፡፡

ጥላሁን ጉግሳ፡- በጣም ትልቅ ስራ የሰራ ሚኒስትሪ ነው ይሄ ሚኒስትሪ፡፡ አሁንም አለ፡፡ እያገለገሉ ነው፡፡ እያገለገሉ ብል ይሻለኛል አሁን፡፡ ምክንያቱም እኔ ብዙ ጊዜ እዚህ አልኖርም፡፡ ስለዚህ በመጣሁ ጊዜ ያሉኝን ስራዎች ቶሎ ጨርሼ መመለስ ስለማስብ...በበርካታ የኢትዮጵያ ክፍሎች እያንዳንዱ ከተማ አንዴም ሁለቴም ሶስቴም አራቴም በመመላለስ ወንጌል ለመስራት ተሞክሯል ብዬ አስባለሁ፡፡ በዚህም በሙቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ወደ ጌታ እንደመጡ አውቃለሁ፡፡(ጭብጨባ)፡፡ ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን፡፡ እና ለኔ በጣም ኢፌክቲቭ መንገድ ነው ድራማ፡፡ እና የተለያዩ የአርት ስራዎች፡፡ ዝማሬውም አርት ነው፡፡ እና ድራማ በጣም ኢፌክቲቭ መንገድ ነው ወንጌልን ለመመስከር፣ ወንጌልን ለመስበክ፣ በተግባርም ያየሁት ነገር ስለሆነ በጣም ኢፌክቲቭ ነው ብዬ አስባለሁ፡፡ አሁን ይሄ ነገር በአርት ሚኒስትሪ ብቻ ሳይሆን ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት ነገር ነው፡፡ ግን ባብዛኛው ብዙ ቦታዎች ላይ ይሄንን አገልግሎት ወንጌልን እንደሚመሰክር አገልግሎት ያለመቀበል ችግሮች ይታያሉ፡፡ ኢቭን በቤተ ክርስትያን፡፡ ስለዚህ ይሄ አስተሳሰብ መቀየር ያለበት ይመስለኛል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ለምሳሌ አመታዊ በአላችንን ስለምናከብር እባካችሁ መጥታችሁ ትያትር ስሩልን ወይም ድራማ አቅርቡልን ብለው የሚጠሩን ቤተ ክርስትያኖች ነበሩ፡፡ እኔ ደግሞ ከመጀመሪያው ጥሪዬ በድራማ ወንጌልን መስበክ እንጂ አመታዊ በአል ላይ ለክብረ በአል የሚሆን ድራማ ሰርቼም አላቅም የለኝም ነው የምለው፡፡(ጭብጨባ)፡፡ አሁንም ወደፊትም የኔ ኮሊንግ ይሄ ነው፡፡(ጭብጨባ)፡፡ አሁን ላይ ላላ ብዬ ፣ ለዘብ ብዬ ሊሆን ይችላል፡፡ አሁን ላይ ወደ ስራዬና ወደ ሌላ ነገር ዘምበል ብዬ ሊሆን ይችላል፡፡ ግን የኔ ዴስቲኒ አይደለም፡፡ የኔ ዴስቲኒ እስከመጨረሻው ኢየሱስ ክርስቶስን በመላው አለም መስበክ ነው፡፡...

እኔ፡- ከመጀሪያው እውነት ያልሆነ እውነት እውነት አይደለም፡፡ አርት የእግዚአብሔር አይደለም፡፡ አራት ነጥብ፡፡ ዝማሬ አርት ከሆነ ዳዊት አርቲስት ነው ማለት ነው፡፡ እንዲህ ብለን እግዚአብሔር እንደ ልቤ ያለውን ሰው ከማንም መናጢ ሴጣኒስት ባንቀላቅለው ጥሩ ነው፡፡ መስበክምኮ ጥበብ ይፈልጋል በአለማዊው አይን ስናሰላው፡፡ ርሄቶሪክ ብለን በቀደመው ምዕራፍ አንስተነዋል፡፡ የአንደበተ ርቱእነት ሳይንስ፡፡

መዝሙር እንደ ዘፈን ሁሉ አርት ስለሆነ፣ እነጥላሁን ጉግሳ መቶ ሺህ ሰው ስለ ጠሩ ግን አርትን አናጸድቅም፡፡ ቢሊየኖችን አጥፍቶ እናውቃለንና፡፡ ድራማ ለመስራት፣ ለመተወን፣ ስክሪፕት ለመጻፍ፣ ዳይሬክተር ለመሆን፣ የአለም ጥበብ ያስፈልጋል፡፡ ብዙ ማወቅ ይጠይቃል፡፡ መዝሙር ለመጻፍ ግን የአለም ጥበብ አያስፈልግም፡፡ ወንጌልን ለመስበክ ግን የአለም እውቀት አያስፈልግም፡፡ ትንቢት መናገር የአለም እውቀት አያስፈልግም፡፡ እነዚህ የእግዚአብሔር ጥበብና ጸጋ የሚሰጣቸው አገልግሎቶች ናቸው፡፡ ድራማ የሚያሰራ የሰይጣን እንጂ ደግሞ የእግዚአብሔር ጥበብ የለም፡፡ በድራማ ሰውን እንጂ እግዚአብሔርን ልናገለግል አንችልም፡፡ ድራማ የእግዚአብሔር አይደለም፡፡

ክርስትናና አርት አብረው የሚሄዱ ነገሮች አይደሉም፡፡ አርት ሎጂክ ነው፡፡ አርት ስጋዊ ነው፡፡ በታሪክና በቦታ ስናነጻጽረው፣ ፈረንጆች እንደአሁኑ አርትና ጥበብ ሳይበዛ፣ በፊት የተሻሉ ክርስትያኖች ነበሩ፡፡ የአለም ጥበብ ሲበዛ፣ ክርስትና እየጠፋ መጣ፡፡ በሞኝነት የሚያመልኩ ጊዜ የተሻሉ ክርስትያኖች ነበሩ፡፡ እያወቁ እያወቁ ሲሄዱ ግን ከእግዚአብሔር እየራቁ መጡ፡፡ ሰይጣን አዳምንና ሔዋንን ያሳሳተው ለምን ሆኖ? እግዚአብሔር ከዚህ አለም ጥበብ ራቁ ያለን ከሃይማኖት ስለሚያሰናክለን አይደል?
በቦታ ደግሞ፣ ዛሬ ላይ እኛ ኢትዮጵያውያን ከፈረንጆች ይልቅ በክርስትና ብርቱዎች ነን፡፡ በአርት፣ በትምህርት፣ በእውቀት ደግሞ የመጨረሻ ዝቅተኛ ነን፡፡ እንዳያያዛችን አርታችንም፣ እውቀታችንም፣ ኢኮኖሚያችንም እያደገ ሲሄድ፣ ሃይማኖትን እየተውን እየተውን ቀሪውን አለም መቀላቀላችን አይቀሬ ነው፡፡ ቃሉም ያንን ነው የሚለው፡፡ ከታሪክም ያንን ነው የምንማረው፡፡ ሁለቱንም ማቻቻል እንችላለን ብለን ራሳችንን ማሞኘት ደግሞ ያው ሞኝነት ነው፡፡ የሚሆነው እግዚአብሔር እንዳለው ነው፡፡ ኢትዮጵያን ለብቻ ሁለቱንም የሚያስችላት አዲስ ቃል ደግሞ አይኖርም፡፡ እንመርጣለን፣ ወደ መረጥንበትም እንሮጣለን፡፡

ሲጄ ቲቪ፡- በዚህ አጋጣሚ ይሄንን ፕሮግራም በሲጄ ቲቪ በጣም ብዙ ሰዎች ያዩታልና ቤተ ክርስትያኖች እዚያው ቤተ ክርስትያን ውስጥ የሚያድጉ እንደ ኳየር ከልጅነታቸው ጀምሮ ቤተ ክርስትያን ውስጥ እያደጉ እዚያው ለሚያገለግሉ ወጣቶች ይሄንን አፖርቹኒቲ ቢሰጡ፡፡ ምክንያቱም ልክ እንደ ዝማሬ፣ እንደ ስብከት ሁሉ ድራማም ወይም አርትም በእኩል መንገድ ወንጌልን ለማድረስ ምክንያቱም የሁላችንም ዋናው አላማ ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ማድረስ ነውና ቤተ ክርስትያኖች ለሚያሳድጓቸው ወጣቶች፣ ቲኔጀሮች እድሉን እንዲሰጡ መልእክት እንድታስተላልፍ፡፡

ጥላሁን ጉግሳ፡- እንግዲህ በውጭው አለም ይሄ አገልግሎት ባብዛኛው በተግባር እየተቀየረ ብዙዎች እየተጠቀሙበት ነው፡፡ ይሄ አሁን እኛም ሀገር መለመድ መቻል አለበት፡፡ ዘመን እየዘመነ ሲሄድ ከዘመኑ ጋራ እየዘመነ ሚሄድ ምንድነው ብሎ እያንዳንዱ ቤተ ክርስትያን ሊያይ ሊያጤን ይገባዋል፡፡ ምናልባት በቤተ ክርስትያን ደረጃ ሊከብድ ይችል ይሆናል፡፡ በያንዳንዱ ቤተ ክርስትያን እንደዚህ አይነት ነገር እየሰሩ ማቅረቡ በራሱ አስቸጋሪ ቢሆንም ግን አት ሊስት ለዚህ አይነት አገልግሎት በር መዝጋት አይገባትም ቤተ ክርስትያን፡፡ ቤተ ክርስትያን ይሄንን አገልግሎት ኢንከሬጅ ልታረግ ይገባላታል፡፡(ጭብጨባ)፡፡ ምክንያቱም ቅድም እንዳልኩት ይሄ የቤተ ክርስትያን ንብረት ነውና የቤተ ክርስትያን ንብረት ተዋጅቶ ወደ ቤቷ ሲመለስ ቤተ ክርስትያን በር መዝጋት የለባትም፡፡ ይሄንን አገልግሎት መቀበል ይገባል ብዬ አስባለሁ፡፡ እፈልጋለሁ፡፡ ወደ ፊትም በዚህ ጉዳይ ላይ ብዙ እሰራለሁ ብዬ አምናለሁ፡፡

እኔ፡- በውጭ ሀገራት በአርት አደገኛነት የነቁና በአግባቡ ጉዳቱ የገባቸው ፓስተሮች የአርትን ፍቅር ከወጣቶች ልብ ውስጥ ለማጥፋት ሲሞክሩና እየተቸገሩ እንደሆነ የሚገልጹ ጽሁፎችን አንብቤአለሁ፡፡ ከዘመኑ ጋር እየዘመኑ መሄድ ደግሞ ትርፉ ኪሳራ ነው፡፡ ቃሉ በኤፌሶን 5፡16፡- ቀኖቹ ክፉዎች ናቸውና ዘመኑን ዋጁ ነው እንጂ የሚለው ከቀኖቹ ክፋት ጋር አብራችሁ ተሞላለጩ አይደለም፡፡ የዘመን ዘመንማ በዚህ ከቀጠልን ኢትዮጵያውያን ሴቶች እራቁታቸውን በቴሌቪዥን መስኮታችን ብቅ የሚሉበት ዘመን ሩቅ አይደለም፡፡ ኬቲ ፔሪ የፓስተር ልጅ ነች፡፡ ዘማሪም ነበረች፡፡ በሀገራችንም ዘማሪዎች ዘፋኝ ሲሆኑ አይተናል፡፡ የነጥላሁን ትያትረኛ ክርስትያኖች ነገ እነኛን የውጪዎቹን አክተሮች ላለመሆናቸው ምንም አይነት መተማመኛ የለም፡፡ ሁሉም ክፉት መጀመሪያ በሃይማኖት ስም ጀምሮ ነው ወዳገጠጠ ወዳፈጠጠ እርኩሰት የሚሸጋገረው፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል ጥሰው ፍልስፍናን ለሃይማኖት ይጠቅማል ብለው ሃይማኖትን በፍልስፍና መተንተን ጀመሩ፡፡ ትምህርት ቤቶችን ከፈቱ፡፡ ቃሉ እንደሚለው አብረው የሚሄዱ አይደሉምና ሰዎች ሃይማኖትን ለማስረዳት ይጠቅማል ያሉት ትምህርት ይኸው ዛሬ ሃይማኖትን እያጠፋ ይገኛል፡፡ ጥላሁን ጉግሳ እንደሚለው ከሆነ አርትንም ወንጌልን መስበኪያ ብለው ይሆናል የአለም ጥበብ ጥማታቸውን ለማርካት ሃይማኖት ውስጥ የቀላቀሉት፡፡ ይኸው ዛሬ፣ ያኔ ለሃይማኖት ተብሎ የተጀመረው የትያትር ጥበብ፣ ዛሬ የሰይጣን መሳሪያ፣ የሰይጣን ቃል አቀባይ፣ ሰዎች ሳይሰለቹ በሰይጣን የሚሰበኩበትና የሰይጣንን ዶክትሪን የሚያደምጡበት(1 ጢሞ. 4፡1-2) መጥፊያቸው ሆኗል፡፡ ከመጀመሪያው አርት የማን ነበረና?

ቤተ ክርስትያን ወጣቶች ተሰጥኦዋቸውን ዲስከቨር የሚያደርጉበት ቦታ አይደለችም፡፡ ነገር ግን ቤተ ክርስትያን ውስጥ እየሆነ ያለው ይሄ ነው፡፡ ቸርች ታሰለጥንና ለዘፋኝነት አሳልፋ ትሰጣለች፡፡ ይሄ ከቤተ ክርስትያን ወጥቶ ዘፋኝ የመሆን ነገር ሲጀመር መድረክ ላይ የሚወጣው ለዝና እንደ ሆነ ያሳያል፡፡ ብቻ ይከብዳል፡፡

ቤቶች ምን አይነት ድራማ ነው? የይቤ አራድነት ይመቻል፣ የበዜ ሞኝነት ያስቃል፣ የዘሩ ቆጥቋጣነት ያስቃል፣ የእከ ሞኝነትና እኔን ነው ማለት ቢሰለችም ያስቃል፣ የማፊ ዘመናዊት ሴትነትና ለፊልምና ለዝና ያላት ጉጉት፣ የህጻን ሴት ልጆችን አዕምሮ ይቀርጻል...፡፡ ወደ አባትየው ወደ ዘሩ እንደ ህጻን ልጅ መሆን፣ ወደ ህጻኗ ርስቴ እንደ ትልቅ ሰው ማሰብና መናገር፣ ወደ ቤታቸው የሀሳብ የበላይነት፣ ፍጹም ኢትዮያዊና ክርስትያናዊ ያልሆኑ ሰይጣናዊ የድራማው ስብከቶች ውስጥ ደግሞ ሳንዘልቅ እንለፈው፡፡ መጀመሪያ ነገር ትያትር፣ ልቦለድ፣ ድራማ የሚሉት ምንትስ የሰይጣን ነው፡፡ መንፈሳዊ ድራማ ራሱ የሰይጣን ነው፡፡ ሰዎች በፊልም ብዙ በጎ ሀሳቦች ይተላለፋሉ ይላሉ፡፡ የጥላሁን ቤቶች ድራማ ስለ ውሃ እጥረት፣ ስለመብራት ሀሳቦችን ያነሳሉ፡፡ አስተማሪ ነው ይባላል፡፡ ነገር ግን ፊልሞች የሚያስተምሩት እነጥላሁንም እንደሚሉት፣ “ማስተላለፍ የፈለግነው...” ብለው እንደሚናገሩት አይነት መልእክት ሳይሆን ተደጋግሞ የሚታየው ነገር ነው፡፡ ቤቶች ላይ እነዘሩ የሚያወሩት

ነገር ሳይሆን፣ የይቤ ገጸ ባህርይ፣ አነጋገሩ፣ ዱሪዬነቱ እንጂ በጎ ነገሩ ሰው አይዘልቅም፡፡ ያሳዝናል፡፡ ከአንድ ሙሉ ፊልም ምንም አትማርም፡፡ ከፊልም የምትማረው ብዙ ፊልሞች ላይ የሚደጋገሙ ነገሮችን ነው፡፡ መላላስ፣ ዝሙት፣ ቋንቋ፣ ግድያ፣ ጭፈራ፣ ወላጆችን አለማክበር፣ ሲናደዱ እቃ መሰባበር፣ እንጂ በጎ ነገሮች ሰውን አይዘልቁም፡፡ እንደዚያ ቢሆንማ እስካሁን አለም ባልተበላሸች፡፡ ሁሌ ፊልሞች ላይ ቤተ ክርስትያን ካለ ቀልድ ነው፣ ፌዝ ነው፡፡ ያን ነው ሳትወድ በግድ አዳፕት እያደረግክ ምትሄደው፡፡ ከቤቶች አይነቶቹ አስቂኝና ተከታታይ የሆኑትን ደግሞ እያስተማረ ያዝናናል ይላሉ፣ የምትማረው ግን ፌዘኝነትን ነው፡፡ የአማርኛ ፊልሞች ፌዘኝነትን፣ ጨፋሪነትን፣ ዝሙትን ነው ትውልዱን ያስተማሩት፡፡ ፊልሞች የአሜሪካ ባህል ወደ መላው አለም እንዲሰራጭ ከፍተኛ አስተዋጽኦን አበርክተዋል፡፡ ካለባበስ እስካነጋገር፣ በሁሉም ዘርፍ፡፡ ፊልም ላይ የሚፋቱ ሰዎችን ደጋግመህ ስታይ የፍቺ ክብደት ይቀንስብሃል፡፡ የማህበረሰቡን አስተሳሰብ ይቀይረዋል፡፡

አንድ ሰው የሆኑ ሰዎች ልጁን ያግቱበትና ልጁን ለማስመለስ፣ 20 ሰው ይገላል፡፡ ይሄ ፊልም የአባትን ፍቅር ነው የሚያስተምረው ማለት ነው? ሰው ሲጨፈጨፍ ደስ ይልሃል፡፡ ያ ነው ትምህርቱ፡፡ በብልሃት የተጣመመ እውነት፣ የተጭበረበረ ዓለምን እንድታይ ነው የሚያደርጉት፡፡

እውነቱ፣ እውነተኛ አርቲስት ነገሮችን በጥበብ የሚመለከት፣ ትናንሽ ነገሮችን እንኳን በትኩረት የሚያይ በኢሳይያስ 5፡21 ላይ የተጠቀሰው አይነት ሰው መሆኑ ነው፡፡ ነገሮችን በጥልቀት የሚያስተውል ሰው ሙያው ባይሆንም፣ በሙያው አርቲስት ነው፡፡ ታዲያ ትንሹም ትልቁም አርት፣ የበለጠ የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን ልብ ሊገዛ አይችሉም፡፡ በአርት የሰውን ቀልብ መሳብ እንጂ የእግዚአብሔርን ትኩረት መሳብ አንችልም፡፡ እግዚአብሔር የብልጣ ብልጦች ሳይሆን የሞኞች አምላክ ነውና፡፡ እግዚአብሔር የሰውን ትኩረት የሚፈልጉ ሰዎች አምላክ አይደለም፡፡ መንፈሳዊም ሆነ አለማዊ፣ ሜል ጊብሰን የሰራው የስቅለት ፊልምም ቢሆን ሰዎችን ዋው የሚያስብል እንጂ እግዚአብሔርን አይደለም፡፡ የእግዚአብሔር ቃል "ማንም ራሱን አያታልል፡፡ ከእናንተ ማንም በዚች ዓለም ጥበበኛ የሆነ ቢመስለው ጥበበኛ ይሆን ዘንድ ሞኝ ይሁን፡፡"(1 ቆሮ. 3፡18) ነው የሚለው፡፡

መዝሙር ስንዘምር፣ በዚህ ዘመን መዝሙርም እንደ ዘፈን፣ ዝናን፣ ልታይ ልታይ ባይነትን፣ ብዙ አለማዊ ነገሮችን ይዞ መጣ እንጂ እየዘመርን ብቻ ነው፡፡ ስንሰብክም አለማዊነት በውስጣችን እስካሌለ እየተሰባበክን ብቻ ነው፡፡ ትያትር የሚሉትን ነገር ስንሰራ ግን ብዙ ነገር አለው፡፡ ስብከትና ዝማሬ፣ ትንቢትና መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያሉ ሌሎች አገልግሎቶች ውስጥ መንፈስ አለ፡፡ ስብከት ትምህርት ነው፡፡ ዝማሬ ምስጋናና መስዋዕትም ነው፡፡ ትንቢት መተናነፕ ነው፡፡ ትያትር ግን ምንድነው? አክቲንግ ነው፡፡ ጥሩ ሰው መስሎ መጫወት፣ መጥፎ ሰው ሆኖ መጫወት፣ ክርስቶስን መስሎ መጫወት... በፊልም ወይም በትያትር ውስጥ መልእክት ለማስተላለፍም እንበለው፣ ጥሩ ሰው ሆነን ስንጫወት ጥሩ ሰው ሆነን ሳይሆን መስለን እየተጫትን ነው፡፡ መጥፎ ሰው ሆነን ስንጫወት መጥፎ ሰው ሆነን ሳይሆን፣ መጥፎ ሰው መስለን እየተጫወትን ነው፡፡ ለክርስትና የምንቆረቆር ሆነን ስንጫወት ሆነን ሳይሆን መስለን እየተጫወትን ነው፡፡ እያስመሰልን ነው፡፡ እግዚአብሔር ደግሞ በመምሰልና በማስመሰል ተማማሩ አላለንም፡፡ ፓሽን ኦፍ ዘ ክራይስት የሚለው ፊልም ላይ ሰውየው ሚስማር ሲቸነከርበት አይተው ሰዎች ያለቅሳሉ፡፡ ክርስቶስ የተቀበለውን መከራ እየተቀበለ ያለ ሲያስመስል ግን ክርስቶስ ደስ ይለዋል እንዴ? እነሜል ጊብሰን ወንጌልን ለመስበክ ነው እንዴ የስቅለቱን ፊልም የሰሩት? መጠበብ ፈልገው ብቻ ነው፡፡ ከሌላ የታሪክ ፊልም የሚለይበት ነገር የለውም፡፡ ከንደ ስፓርታከስ አይነት ፊልሞች የሚለይበት ነገር የለውም፡፡ የ1977ቱ የክርስቶስ ከልደት እስከ እርጋት የሚያሳየው ፊልም ላይ ክርስቶስን ሆኖ የተወነው ሮበርት ፓወል የሚባለው ተዋናይ ደግሞ ሰዎች በቤተ ክርስትያንና በየቦታው ፎቶውን እየሰቀሉ ሲያመልኩ እኔን ማምለክ ትታችሁ እውነተኛውን ክርስቶስ አምልኩ ብሎ ሲማጸን ነበረ፡፡

ሁለት አይነት ማስመሰል አለ፡፡ አንደኛው ከላይ እንተጠቀሰው ትያትር፣ ድራማ ውስጥ ያለው ሰዎች ሆን ብለው በጥበብ ስም የሚሰሩት ማስመሰል ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የፈሪሳውያንና የብዙ የዚህ ዘመን ክርስትያኖች ማስመሰል ነው፡፡ ከልብ ሳይሆን ለማህበራዊ ፍጆታ የሚውል ክርስትና፡፡ ከሰፈር ጀምሮ፣ ተንበርክከው እያለቀሱ እየጸለዩ በካሜራ ተቀርጸው አደባባይ ላይ በትነው፣ ዝናዬ አንተው ነህ እስከሚሉት፡፡ መዝሙሮቻችንን ብዙ መውቀስ ይቻላል፡፡ ነገር ግን በግልጽ ሰዎች ሳያውቁት ሳይሆን ሃይማኖት ግድ ስላልሰጣቸው የሚያደርጉትን ነገር ማውራት ለምን? ቤተ ክርስትያን ሌላ ቦታ የማናሳየውን ስርአት አልበኝነት በሽፋን የምናካሂድበት ቦታ አይደለችም፡፡
ባጠቃላይ በየትኛውም ዘርፍ፣ ክርስትና ዝነኛ ሰዎችን አይፈልግም፡፡ እነጳውሎስ ግን ሰው ሃይማኖቱን እንዲከተል ምክንያት ሆኑ እንጂ ሰው ሃይማኖቱ ግድ ሳይለው በዝነኝነትና በአለማዊነት አባዜ እንዲሰናከል ምክንያት አልሆኑም፡፡ Christianity doesn't need a celebrity. ክርስትና ዝነኞችን አትፈልግም፡፡ ወደ ዝና መወጣጫ መሰላል የሚያደርጓትም ቅጣታቸውን ይቀበላሉ፡፡ የእውነተኛ ክርስትዮኖች ሴሌብሪቲ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ እውነተኛ ክርስትያኖች ታዋቂ ለመሆን ሃይማኖትን ሽፋን የሚያደርጉ ሰዎችን መምሰል የሚፈልጉ፣ ለዝና ብቻ፣ መድረክ ላይና በየሰዉ ቤት ቲቪ ላይ፣ ነጭ ሱፍ ለብሰው፣ እየተጀነኑ ለመንንግለል ሐሰተኛ ነቢያትንና አስተማሪዎችን መምሰል የሚፈልጉ ሳይሆኑ የተማሪዎቹን እግር ያጠበው፣ ዝቅ ዝቅ ማለትን ያስተማረው፣ ክብርን መጠማትን ሳይሆን ሰውን ማክበርን ያስተማረው ኢየሱስን መምሰል ይፈልጋሉ፡፡ መሆን የሚፈልጉት ባካባቢያቸው እግዚአብሔርን በሙሉ ልቡ እንደሚወደው፣ በመውጣት በመግባቱ እግዚአብሔርን የማያሳዝንና ለመንደሩ አርአያ የሚሆነውን ሰው ነው እንጂ አንድ ዘማሪ ነኝ የሚል በቲቪ ላይ ታይቶ ሰዎች አጀብ ያሉለትን ሰው አይደለም፡፡ አጃቢ ፍለጋ አይደለም፡፡

በቤተ ክርስትያን ውስጥ ለማስተማር እየተባለ ዘመኑ ወደ ፈሰሰበት ለመፍሰስ የሚሰራ ትያትርና ፊልም፣ ሆሊውድ፣ ቤተ ክርስትያን ውስጥ ከሚሰራው ኮሜዲ ፊልም አይተናነስም፡፡ ሲጀመር አርት የተባለ ነገር የሰይጣን ነው፡፡ የውጪ ፊልም ላይ ኦ ማይ ጋድ፣ ጂስ፣ ጂሰስ፣ ጂሰስ ክራይስት፣ ሲሉና ይሄ ነገር በሁሉም ፊልም ላይ ሲደጋገም እነዚህ ፈረንጆች አግዚአብሔርን ያውቃሉ ለካ፣ እንዲያውም ከኛ የበለጠ ሁሌ አይደል እንዴ የሚሉት? እል ነበረ፡፡ ነገር ግን ያ የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ አትጥራ የሚለውን የእግዚአብሔር ህግ የመጣስና ክርስትናን ከቀልድ በላይ ትርጉም የሌለው፣ አድርገው የማቅረብ አላማቸው አካል ነው፡፡
ትንቢተ ኢሳይያስ 52፡5፡ "ወገኔ በከንቱ ተወስዶአልና አሁን ከዚህ ምናለኝ? ይላል እግዚአብሔር፡፡ የሚገዙአቸው ይጮኻሉ፣ ይላል እግዚአብሔር፣ ስሜም ቀኑን ሁሉ ይሰደባል፡፡" ይላል፡፡

በተለይ ትያትር እያሉ በሃይማኖት ላይ መቀለድ አያዋጣም፡፡ አንድ ሰው ሌላ ሰው የጻፈውን ምንም አይነት ትርጉም ያለው ጽሁፍ አንብቦ ሲተውን በጣም ተለማምዶ ተውኖ በሰው ለመደነቅ ከመፈለግ ሌላ ሊያስበው የሚችለው ነገር አይኖርም፡፡

አርት፣ አንድ ማህበረሰብ በአለም የተወሰደበት ደረጃ መለኪያ ነው፡፡ ባለጠግነት በበዛበትና ምግብ በተተረፈረፈበት ሰው በልቶ በማደር ስለማይረካ በምግቡ ላይ አርት እየሠራ፣ ለአይንና ለምላስ የሚያረካ አድርጎ ለማቅረብ ይጣጣራል፡፡ ማህበራዊ ውድቀት ባለበት በሰው ህይወት ውስጥ የሰዎችን ቦታ ለመሸፈን የፊልም ተዋናዮችና ዘፋኞች፣ የቪዲዮ ጌሞች ይተካሉ፡፡ የአርት ጥልቀትም በንደዚህ አይነት ነገሮች ላይ ይመሰረታል፡፡

ይሄ ዘመን ፌዘኛና አዝማሪ የሚሞጋገሱበትና ጥሮ ግሮ የሚሰራው ገበሬ የሚናቅበት ነው፡፡ ሰው አስቀን ጥርስና ብር ስለ ቆጠርንኮ ፌዘኝነት ወደ ስራነት አይለወጥም፡፡ አሁን የምናረገው ያ ነው? ልጆቻችንን ፌዘኛ ኮሜዲያኖች እንዲሆኑ እናበረታታቸው?

አንድ The shape of things የተሰኘ ፊልም ላይ “Moralists have no place in an art gallery” የሚል ጽሁፍ አየሁኝ፡፡ እናም በጣም ትክክል ነው ብዬ አሰባለሁ፡፡ በዚህ ዘመን አለም ያፈነገጠችው ሁሉም ሰው አርቲስት እየሆነ ስለመጣ ነው፡፡ አርት የአለምን ገጽታ አሳምሮ(እሴት ጨምሮበት) ለሰዎች ማሳየት ማለት ነው፡፡ እውነተኛ አርት ሃይማኖትን አሳምራ ለሰዎች ታሳያለች እንጂ ሃይማኖት የላትም፡፡ አርት ሞራሊስትነትን ለሰዎች ታሳያለች እንጂ ሞራሊስት አይደለችም፡፡ አርት አንድ ነገር ላይ ቀብቶ ማሳመር ማለት ነው፡፡ ከብረት የተሰራ የእጅ ሰአት ላይ ወርቅ ቀብተን ስናሳምረው፣ አርት ነው፡፡ መንፈሳዊ ሀሳባችንን አሳምረን በድራማ መልክ ስናቀርበው አርት ነው፡፡ በጥበብ ስንሰርቅ አርት ነው፡፡ አርት መልካሙንም ክፉውንም፣ የቱንም፣ ቀብቶ ማሳመር ነው፡፡ ታዲያ አርትን ለተለያየ ነገር ስንጠቀመው፣ የብልጭልጭና በጥበብ የተሰራ ነገር አፍቃሪ ሆነን እናርፋለን፡፡ በጥበብ የተሰሩ ድራማዎችን በጥበብ የተካነ ንግግር ስናዳምጥ ኖረን፣ ህይወት የሚገኝበት ግን በአርት ዝባዝንኪ ያልተሸሞነሞነው፣ ሞኝነት የሚመስለው መንፈሳዊ ስብከት ያስጠላናል፣ ከማዳመጥና በስብከቱ ከመታነጽ ይልቅ፣ መተቸት፣ መናቅ ይወርሰናል፡፡ በመጨረሻም በምክንያታዊነትና በአመንክዮ፣ አዕምሮን በሚገዛ በአለማዊ ጥበብ ሳይሆን፣ በመንፈስ የሚመረመረውን እውነት እንክዳለን፡፡ አንድ ቀን ክርስትያኖች በሃይማኖት ውስጥ ሲጠቀሟት የነበረችው አርት እውነተኛ ምንነቷን እየገለጠች፣ እየገለጠች፣ ዛሬ ላይ ወደ እውነተኛ ማንነቷ እየተጠጋች ነው፡፡ አርት ዋነኛ የሰይጣን መሳሪያ ነች፡፡

እውነት(ክርስትና) ውብ ነች፡፡ የሚያሳምራትና አስውቦ የሚያቀርባት አትፈልግም፡፡ ነገር ግን ልንቀባባትና ልናሰማምራት ስንሞክር፣ እያስዋብናት ሳይሆን እየደበቅናት ነው፡፡ ልናሳምራትና ልናስውባት የምንሞክረው፣ ለአይናችንና ለጆሮአችን ስላለትመቸችን ነው፡፡ ብርሃኑ ካልበራልንና ለማብራት የራሳችንን ዓለማዊ መንገድ ስንጠቀም፣ ችግራችን የውስጥ አይናችን እውርነት ነው ማለት ነው፡፡ የእግዚአብሔር ቃል እንደ ምግብ ቢሆን፣ እንደ አለማዊው ምግብ አይደለም፡፡ የአለማዊው ምግብ ጨው ካነሰው፣ ጨው ጨምረህ ታጣፍጠዋለህ፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ግን ሙሉ ነው፣ ካልጣፈጠህ፣ ጨው አትጨምርበትም፡፡ ካልጣፈጠህ፣ ምላስህ ችግር አለበት ማለት ነው፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ላይ ማጣፈጫ እንጨምር ስንል፣ ቃሉ የሚጨምርብን ነገር ይኖራል፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል አውጥተን እንጣል ብንል፣ አውጥቶ ይጥለናል፡፡

አንድ BETV(Bible Exploration TV) የሚባል የቴሌቪዥን ቻናል ላይ ያለ ሰውዬ እንዲህ አለ፡
“በባቢሎን ት/ቤት እንማራለን፣ የባቢሎንን ፖለቲካ ውስጥ እንገባለን፣ የባቢሎንን ዜና እናዳምጣለን፣ የባቢሎንን ፊልም እናያለን፣ የባቢሎንን ዘፈን እናዳጣለን፣ የባቢሎንን መጽሐፍት እናነባለን፣ የባቢሎንን ስብከት እናዳምጣለን፣ ከዚያ ቀስ በቀስ እንደ ባቢሎን ማሰብ እንጀምራለን፣ ከዚያ እንደ ባቢሎን ማውራት እንጀምራለን፣ ከዚያ ቀስ በቀስ እንደ ባቢሎን መኖር እንጀምራለን፣ ከዚያ እንደ ባቢሎን ማምለክ እንጀምራለን፣ ከዚያ እንደ ባቢሎን ማመን እንጀምራለን፡፡” ክርስቶስ ግን ከመጀመሪያው ለመኖሩም፣ ለንባቡም፣ ለማየቱም፣ ሳንደርስ “ምን እንድትሰሙ ተጠበቁ” ይለናል፡፡ (ማርቆስ 4፡24) ጆሮአችን ውስጥ ክፋትን ሊጨምሩ ከሚችሉ ሁኔታዎች እንድንርቅ ይናገረናል፡፡
እንደ ባቢሎን እንኖራለን፣ እንደ ባቢሎን እናመልካለን፡ በምንኖረው በባቢሎን መንገድ የእግዚአብሔርን ቃል አጣመው የሚያስተምሩ፣ ብልጥግና ጥሩ ነው፣ ት/ት ጥሩ ነው እያሉ በእግዚአብሔር ስም ትንቢትን ከሰይጣን የሚቀበሉና ቤተ ክርስትያንን የሚያፈርስ ትምህርት የሚያስተምሩ አስተማሪዎችን እናከማቻለን፡፡ 2 ጢሞ. 4፡3፡፡

ምሳሌና መክብብ

ሰው ብረት አይደለም፣ ቶሎ ይሰበራል፤ ሰው ብረት አይደለም፣ ዝገት አይበላውም፡፡ የሚሰብረውን፣ ከማያዝገው፣ የሚጠቅመውን ከሚጎዳው፣ የማይጠቅመውን ከማይጎዳው፣ የሚያኖረውን ከሚገለው ለይቶ የሚያውቅ አስተዋይ፣ እርሱ ጠቢብ ነው፡፡
The stronger you are, the more easily you can get broken. The higher you are, the more damaged you can get, when you fall.

ጎበዝ ተማሪ የሚኮነው፣ በማንበብ፣ በመመርመር፣ ችግሮችን በመገንዘብና በመፍታት አይደል? ት/ቤት ስንማር፣ ት/ትን እንወደዋለን እንዴ?
ት/ት ወይም ክፍል ውስጥ ገብተን በየአመቱ 1ኛ፣ 2ኛ፣ 3ኛ እያልን የምንማረው ት/ት ለአዕምሮአችን ባእድ አካል ነው፡፡ ተፈጥሮአዊ አይደለም፡፡ ሰዎች ማወቅ አለብህ፣ ት/ቤት መግባት አለብህ ስላሉን ወደ አዕምሮአችን የምንጨምረው ነገር ነው፡፡ ከሀያ አመት በኋላ

የምናገኘውን ሽልማት፣ቅንጡ ህይወት እያሰብን ነው፣ ዛሬ አእምሮአችንን የምናደማው፡፡ ትምህርትን የራሱ አድርጎ፣ ራሱን አስገዝቶ በጥሩ ነጥብ የሚያልፍ ሰው፣ በአለም ላይ ከፍተኛ ተስፋን የጣለ ሰው ነው፡፡ በአለም ላይ ከፍተኛ ተስፋን የማይጥልና፣ አወቅኩ አላወቅኩ፣ ሀብታም ሆንኩ፣ ደሃ ለውጥ የለውም ብሎ የሚያስብ ሰው፣ በከንቱ ነገር አእምሮውን ሊያጨናንቅና ሊወሳሰብ አይችልም፡፡ ይጠቅመኛል፣ ነገ ያበላኛል፣ ያኖረኛል፣ ብሎ ማመን ያስፈልጋል፡፡ አዋቂ ምሁር ስትሆን፣ ከሌላው እንደምትሻል ማወቅ ብቻ ሳይሆን ማመን ያስፈልጋል፣ አስጨናቂውን ትምህርት ወደ አእምሮህ ለመሳብና አእምሮህ ውስጥ ለማስቀመጥ፡፡   አርቲፊሻል እግር ለተፈጥሮአዊው ሰውነት ባእድ አካል ነው፡፡ ባእድ አካል ወደ ሰውነቱ እንዲገባ የተደረገ ሰው ያመዋል፡፡ እንደራስ አካል አይሆንም፡፡ ግን ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ነው፡፡ እየተዋሃደው፣ እየተለማመደው ይሄዳል፡፡ ወደ ትምህርትና አዕምሮአችን ስንመጣ፣ አዕምሮአችን እግሩ እንደተቆረጠ ሰው ባዶ ቦታ የለውም፡፡ እግሩ የተቆረጠ፣ ያው በተቆረጠው ቦታ ነው አርቲፊሻሉና ጠቃሚው እግር የሚገባለት፡፡ ኩላሊቱን የታመመውም አንደዚያው የበፊቱ ወጥቶ ጠቃሚው ይገባል፡፡ ለእውቀትና ለአዕመሮ ግን ይሄ ምሳሌ አይሰራም፡፡ ጠቃሚው እውቀት፣ በባዶ ቦታ ወይም፣ ሌላ ነገር አውጥተን አይደለም የሚገባው፡፡

ትምህርት ስንማር ወይም አዲስ እውቀትን ስንቀበል፣ ያ የምንማረው ነገር ለአዕምሮአችን አዲስ እስከሆነ ድረስ ባእድ ነው፡፡ ታዲያ አዕምሮአችን፣ ለፈተናም ይሁን ለምን፣ አዕምሮአችንን ዘልቆ እንዲገባን ለምንፈልገው ባእድ እውቀት ቦታ የለውም፡፡ አዕምሮአችን ሁሌ ሙሉ ነው፡፡ የማይሞላ ሙሉ፡፡ አንድ ሰው ብዙ ስለሚያውቅ፣ አዕምሮው ሞላ ከዚህ በላይ ማወቅ አይችልም፣ አዕምሮው ሞልቷል የሚባል ነገር የለም፡፡ እንዲያውም ብዙ የሚያውቁት የበለጠ ለማወቅ ሲጣጣሩ እናያለን፡፡ አንድ ሰው ደግሞ ስላልተማረ ወይም መሃይም ስለሆነ ወይም ማንበብና መጻፍ ስለማይችል ደግሞ ብዙ ማወቅ ይችላል፣ ብዙ ክፍት ቦታ አለው ማለት አይደለም፡፡ አዕምሮአችን የማይሞላ፣ ግን ሙሉ ነው፡፡ ሙሉ ነው ግን ይሰፋል፡፡ ይለጠጣል፡፡አንድ ዘንቢል አይነት፣ እንደ ብር ላስቲክ ከሚለጠጥ ነገር የተሰራ ቅርጫት አለ እንበል፡፡ ቅርጫቱ ደግሞ በቁመት ከእስከሪብቶ ጋር እኩል የሆኑ እንጨቶች ተጠቅጥቀውበት ሞልቷል እንበል፡፡ የቅርጫቱ ቁመትና የሁሉም እንጨቶች ቁመት እኩል ነው እንበል፡፡ ቅርጫቱን አዕምሮ፣ እንጨቶቹን፣ አውቀቶች፣ ትዝታዎች፣ የሂሳብ ቀመሮች፣ የሰው ስሞች፣ አዕምሮ ውስጥ ያሉ ዳታና ዶኩሜንቶች ናቸው እንበል፡፡ የእንጨቶቹ ስፋት እንደየዶኩሜንቶቹ ስፋትና ጥልቀት ይለያያል፡፡ ለምሳሌ የአንድ ሰው ስም በጣም ለመያዝም ብዙ ስለማይከብድ በጣም ቀጭን ይሆናል፡፡ በቅርጫቱ ውስጥ ትንሽ ቦታ ቢይዝ ነው ማለት ነው፡፡ አንድ ሙሉውን የምናስታውሰው ፊልም ወይም በቃላችን የሸመደድነው ጽሁፍ ደግሞ በጣም ሰፊና ብዙ ቦታ ይይዛል፡፡ ቦታውን ያጣብባል ወይም ይሞላዋል ማለት ነው፡፡ አንድ የምናውቀው ነገር፣ የአዕምሮአችን አካል ነው፡፡ ሌላ የማናውቀውን ነገር በአዕምሮአችን ለመያዝ ወይም ለመረዳት ስንሞክር ደግሞ አዲስ እንጨት በሙሉው ቅርጫት ላይ ለመጨመር እየሞከርን ነው፡፡ የሆነ ነገር ለመያዝ ወይም ለመረዳት ስንሞክር አዕምሮአችንን ባእድ አካል እንዲያስተናግድ እያስገደድነው ብቻ ሳይሆን በሌለው ቦታ ላይ ነው እያስገደድነው ያለነው፡፡ አዕምሮአችን ሙሉ ነው ማለት ቦታ የለውም ማለት ነው፡፡ ይለጠጣል ማለት ደግሞ ቦታ ይኖረዋል ማለት ነው፡፡ ቅርጫቱ የሚለጠጥ ነገር ነው ብያለሁ፡፡ አዕምሮ ደግሞ ተለጥጦ አያልቅም ብያለሁ፡፡ ነገር ግን ዝም ብለን ማስገባት የፈለግነውን እንጨት ወደታች ስንገፋ፣ እንጨቶቹ ይገፋፉና ቅርጫቱን ገፍተው ይለጥጡታል፡፡ ከዚያ ይገባል፡፡ የሚገባው እንጨት በጣም ሰፊ ከሆነ፣ መላላጥ፣ በጣም መጨናነቅ በቅርጫቱ ውስጥ መፈጠሩ አይቀርም፡፡ ነገር ግን አዕምሮ ላይ እንደ እንጨቱ እውቀቱን እንደ እጅ ወደ አዕምሮ የሚገፋው አካል ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ መያዝ የፈለግነው የሰው ስም ከሆነ እንጨቱ በጣም ቀጭን ስለሚሆን ወደ አዕምሮአችን ውስጥ ለማስባት ብዙ ግፊት አይፈልግም፡፡ ቆይ ግን ብዙ መሸምደድ ሰንፈልግ፣ ለፈተና ብዙ ውስብስብና ረጃጅም እውቀቶችን ወደ እዕምሮአችን ለማስገባት ስንል ምንድነው ወደ ውስጥ የሚገፋልንና ሙሉውን አዕምሮአችንን በግድ አጣበን እነኛን ሰፋፊ እንጨቶች እንድንቀበል የሚያደርገን? ምንድነው እጅ ሆኖ የሚገፋልን? አዕምሮአችን ራሱ ነው፡፡ ሰው የነገረን የሰው ስም፣ ስም ለማስታወስ ብዙም አስቸጋሪ ባይሆንም ግን ፍላጎታችን ይወስነዋል፡፡ አዕምሮአችን ያንን ስም ማወቁ በሚጠቅመው መጠን ነው ያ ስም በአዕምሮአችን ውስጥ የሚቀመጠው፡፡ ፍላጎቱ ከሌለ የሰው ስምም ይረሳል፡፡ ፍላጎቱ(እጁ) ካለ ብዙ እውቀት ወደ አዕምሮ ይገባል፡፡ ግን በጣም ከባባድ እውቀቶችን ባዶ ቦታ በሌለው አዕሮአችን ላይ በግድ እንድንጭን የሚያደርገን እጅ ከየት ነው የሚመጣው፡፡ አንድ አለም የፈጠረልን እውነት አለ፡፡ እውቀት ጥሩ ነው፡፡ ሰውን ሰው የሚያረገው ትምህርት ነው ይባላል፡፡ ይሄን እየሰማህ ታድጋለህ፡፡ ዶክተር ስለመሆን እየሰማህ ታድጋለህ፡፡ ማህበረሰቡ አዕምሮህ ላይ የሚፈጥረው ተጽእኖ ትምህርትን ሳትወድ በግድ ፍላጎቱን እንዲኖርህ ያደርግሃል፡፡ አ አር ኤስ እንደመጠጣት ነው፡፡ ስለወደድከው ሳይሆን ስለሚጠቅም ነው የምትጠጣው፡፡ ታዲያ ይሄ በአዕምሮአችን አንድ ጎን ማህበረሰቡ የተፈጠረው የማወቅ፣ አውቆ አንደኛ የመውጣት ፍላጎት፣ ትምህርትን በመዶሻ እንደመምታት ወደ አዕምሮአችን ይከተዋል፡፡ እውነተኛው አዕምሮ እውቀትን አይወደውም፡፡ እውቀት ለአዕምሮ ባእድ ነው፡፡ ማህበረሰቡ በአዕምሮ አንድ ክፍል የፈጠረው አስተሳሰብ ደግሞ እውቀት ጥሩ ነው ይላል፡፡ ሰው መሆን ከፈለግክ አጥና ይላል፡፡ በአዕምሮአችን ባእዱንና ግዙፉን እውቀት ለመቀበል ያለመፈለግና ሙሉ የመሆንና ለማወቅ የመፈለግ አርቲፊሻል ፍላጎት መሃል የሚፈጠረው ግፊትና ውጥረት፣ ከተማሪዎች አፍ የማይወርደው ከበደኝ የምትለዋል ቃል ይፈጥራል፡፡ ብዙ እውቀት በቀላሉ አይገባንም፡፡ ፍላገጎታችንና አዕምሮአችን ይታገላሉ፡፡ አንዳንዴ እንዲሁ ስናጠና ያልገባን የፈተና ሰሞን ስናጠናው ይገባናል፡፡ ፈተናውን ማለፍ የሚፈልገው የአዕምሮ ክፍል በግድ እውቀቱን ወደ አዕምሮአችን ይጭነዋል፡፡ በፊት ብዙም ፍላጎቱን ስላልነበረን ነው፡፡ ፈተናውን የማለፍ ፍላጎታችን ደግሞ እውቀቱን በሃይል ወደ አዕምሮአችን እንድንጨምረው ያደርገንና ብዙ ጊዜ አጥንተን ያልገባን፣ በጥቂት ቀናት ውስጥ ይገባናል፡፡ የዚህ ጊዜ የሚፈጠረውን ነገር ቴንሽን ይሉታል፡፡ ቴንሽን አይገልጸውም፡፡ አዕምሮአችንን ደም እያስተፋነው ነው፡፡ ልንቀበል ከሚገባን በላይ እየተቀበልን አዕምሮአችንን እናጨናንቀዋለን፡፡ አጨናንቀን አጨናንቀን አዕምሮአችንን ለውጥረት   እንዳርገዋለን፡፡ በእንጨቶቹ ምሳሌ፣ ቅርጫቱ እንደሁ ተለጥጦ ስለማያልቅ እውቀቱ መግባቱ አይቀርም፡፡ ግን ከፍተኛ ፍሪክሽን ይፈጠራል፡፡ አዕምሮአችን ይላላጣል፡፡ እንደ አርቲፊሻሉ እግር አዕምሮአችን ላይ ከባድና ባዕድ ነገር በጫንበት፣ የሚከብድ ነገር በግድ በሰጠነው መጠን እየተላላጠ ይሄዳል፡፡ የፈተና ሰሞን አዕምሮ ይዝላል፡፡ ከፈተና በኋላ የሆነ ሸክም ከላይህ ላይ ሲወርድ የሚሰማህ ስሜት አለ፡፡ ከዚያ በኋላ ቀስ በቀስ እንደዚያ አዕምሮአችንን አላልጦ የገባው እውቀት እየተዋሃደ እየተለማመደ፣ ስማችንን የማወቅ ያህል ቀላል ነገር ይሆናል፡፡ 8ኛ ክፍል ላይ አዕምሮዬን ያደማ ሂሳብ፣ ዛሬ ምኔም አይደለም፡፡ ምክንያቱም ተዋህዶኛል፡፡ አሁን ሌላ ከሱ በላይ የሆነ እውቀት ለማስጋባት አዕምሮዬን እያደማሁ ብሆን ነው፡፡

ነገር ግን እወቀትን ሳናቆራርጥ ወደ አዕምሮአችን እያፈስስን አዕምሮአችንን እያሰፋን እያሰፋን ስንሄድ በፊት እየጠላን በግድ የምንቀበለው እውቀት ሱስ እየሆነብን ይመጣል፡፡ እውቀት መጨረሻ የለውም፡፡ አንድ ነገር ስናውቅ አንድ ሌላ ነገር እንድናውቅ ይጋብዘናል፡፡ ብዙ እያወቅን ስንሄድ ብዙ ጥያቄዎችን መጠየቅ እንጀምራለን፡፡ በተከታታይ እውቀትን እየተመገበ ያደገው አዕምሮአችን ደግሞ መልስ ይሻል፡፡ ከዚያ አግኝ የነበረው አዕምሮአችን መልስ የሚሻ ጠያቂ የእውቀት ሱሰኛ ሆኖ ያርፈዋል፡፡ መመርመር የአዕምሮአችን አዲሱ ስራ ይሆናል፡፡ አዕምሮአችን በፊት ደም ሲተፋ እንዳልነበረ፣ እውቀትን ይጠማል፡፡ እውቀት ለአዕምሮ እንደ ሲጋራ ወይም የመጠጥ ሱስ ነው፡፡ መጀመሪያ አይመችም፡፡ ከተመቸ ግን ማቆሚያ የለውም፡፡ እንደ ስፖርት ነው፡፡ መጀመሪያ ስትራፖ ያስይዛል፣ እየቆየ ሲሄድ ደስ ይላል፡፡ ከሲጋራ ሱስ እንዴትም ተብሎ ነጻ መውጣት ይቻላል፡፡ አንዴ አስፍቶ አሳቢ፣ እውቀትን ፈላጊ የሆነን አዕምሮ ግን መልሶ ከዚያ ምርምር ነጻ ማውጣት አይቻልም፡፡ እውቀት ደግሞ መከራ አለው፡፡ (ኢሳይያስ 5፡21) አለም አውቀትን መፈለግ መልካም ነው ትላለች፡፡ አለም ውሸታም ነች፡፡

ብዙ እውቀትን ከተከተልክና ካወቅክ በኋላ፣ አንድ ቀን፣ ከአንድ ቀን በኋላ፣ የጭንቀት ትርጉም ይለወጥብሃል፣ የሃዘን ትርጉም ይለወጥብሃል፡፡ የደስታ ትርጉም ይቀየርብሃል፣ ለሃዘን የነበረህ አመላከት ይቀየራል፡፡ ትልቅ የምትለው ነገር ትንሽ፣ ትንሽ የምትለው ነገር ትልቅ ይሆኑብሃል፡፡ ይጠቅመኛል ስትለው የነበረው ገንዘብ አንሶ፣ ጥቅመ ቢስ መስሎ፣ አይጠቅመኝም ስትለው የነበረው ከሰው ጋር በፍቅር መኖር፣ በጣም አስፈላጊ ነገር ይሆኑብሃል፡፡ ነገሮች በአንድ ሌሊት ሲገለባበጡ፣ አዋቂ ነኝ የምትለው ሰው፣ በምክንያት የምታምነው ሰው፣ ራስህን ማብራራት ይሳንሃል፡፡ እንደኔ እድለኛ ከሆንክ በምክንያት ሳይሆን በእውነት ወደተጻፈው ካነበብካቸው መጽሐፍት ሁሉ ከተለየውና ሌሎች መጽሐፍትና ደራሲዎች እውነቷን ሊሸሽጉ ሲጣጣሩ፣ እውነት በግልጽ ከተገለጸችበት የእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ማብራሪያን ታገኛለህ፣ በሞኝነትህ ትቆጫለህ፡፡

ሰው ሀሳቡ፣ ይሰብረዋል፣ ገንዘቡ፣ ትምክህቱ፣ እውቀቱ ያጠፋዋል፣ ሰው፣ ማጣቱ፣ መሃይምነቱ፣ ዝቅ ዝቅ ማለቱ፣ ዝገት እንዲበላው አያደርጉትም፡፡

የአዕምሮ መለኪያ የተሰጠን ዳሽ ላይ ትክክለኛ መልስ መሙላት መቻል ወይም ምክንያታዊ መልስ መስጠት ወይም ረጅም የሂሳብ ቀመርን ያለ ስህተት መፍታት፣ ጥያቄና መልስ ሳይሆን ከነዚህ ነገሮች ራስን አርቆ ወደ እውነቱ መቅረብና እውነቱን በሞኝነት መቀበል መቻል ነው፡፡

 መጽሐፈ መክብብ "ከንቱ የከንቱ ከንቱ" በሚለው ቃል ይታወቃል፡፡ በዘመናችን ብዙ ክርስትያኖች ይሄን ያውቃሉ፡፡ እግዚአብሔር አጽንኦት የሰጠበትን ይሄን ቃል ግን ትኩረት የሰጠበት ሰው ያለ አይመስልም፡፡ መጽሐፈ መክብብ ሲጀምር እንዲህ ይላል፡- "በኢየሩሳሌም የነገሰ የሰባኪው የዳዊት ልጅ ቃል፡፡ ሰባኪው፡- ከንቱ፣ ከንቱ፣ የከንቱ ከንቱ ሁሉ ከንቱ ነው ይላል፡፡" (Vanity of vanities, saith the preacher, vanity of vanities; all is vanity). በአንድ አረፍተ ነገር ውስጥ አንድ ቃል 5ቴ ሲደጋገም፣ ቆም ብለን ለማስተዋል መሞከር አለብን፡፡

ሃብታሙም ይሞታል፣ ደሃውም ይሞታል ሲባል በጣም የሞኝ አባባል ይመስለኝ ነበር፡፡ ሀብታሙ የፈለገውን አርጎ፣ ተደስቶ ይሞታል፣ ደሃው ተንከራቶ ይሞታል እል ነበር፡፡ አሁን ደስታ እግዚአብሔር የሚሰጠው እንጂ በገንዘብ የሚገኝ ነገር እንዳልሆነ፣ ደስታ በውስጣዊ ማንነታችን እንጂ በብልጭልጭ የምናገኘው ነገር እንዳልሆነ በራሴ ላይ ሳየው ግን ገንዘብ ከከንቱነት ያለፈ፣ አለም እንደሚለው አይነት ትርጉም እንደ ሌለው ገባኝ፡፡ ሀብታም ነኝ ማለቴ አይደለም፡፡ ነገር ግን ይህቺን አለም ጠቅልለው ቢሸጡልህ፣ በአለም ላይ ቁጥር አንድ ዝነኛ ከሚባለው ሰው የበለጠ ዝናን ቢያጎናጽፉህ ደስታን መልሰህ እንደማታያት የምትረዳበት ነጥብ አለ፡፡ መጽሐፈ መክብብን ሳነብ ምነው ቀድሜ ባነበብኩት አልኩኝ፡፡ ለነገሩ ቀድሜ ባነበው፣ አሁን ተጎድቼ እንደገባኝ ላይገባኝ ይችላል፡፡

መጽሐፈ መክብብ፣ ሰዎች ከዚህች አለም የሚፈልጉትን ነገር ሁሉ የቀመሰ ሰው የጻፈው መጽሐፍ ነው፡፡ መጽሐፈ መክብብ የዚህ አለም ነገር ከንቱ ነው፣ ስትሞት ትተኸው ትሄዳለህ፣ ብቻ አይደለም እያለን ያለው፡፡ አዎ የከንቱ አንድ ትርጉም የሚያልፍ ነገር ማለት ነው፡፡ እንደ ገና ግን ከንቱ ማለት የሚያልፍ ነገር ማለት ብቻ ሳይሆን ዋጋ የሌለው ነገር ማለትም ነው፡፡ (vanity)፡፡ የአለምን ነገር መከተል ነፋስን እንደ መከተል ከንቱ እንደ ሆነ ይነግረናል፡፡

አዕምሮአችን ሁሌም ይሰራል፡፡ ደሃው በልቶ የሚያድረው ያሳስበዋል፡፡ እግዚአብሔር የእለት እንጀራውን እንዲሰጠው ይለምናል፡፡ ካገኘም ደስ ብሎት እግዚአብሔርን አመስግኖ ያድራል፡፡ ስለዚህ በደሃ አዕምሮ ምግብ በጣም ትልቅ ነገር ነው፡፡ እድሜ ልክ አጥግቦና ምግብ አማርጦ መብላት የሚያስችል፣ የተቀመጠ ገንዘብ ሲኖርና አቅርቦ ለመብላት እንኳን መቸገር ሳያስፈልግ ሲቀርና፣ ያንን የሚያደርግ ሰራተኛ ሲኖር፣ ምግብ የሚያሳስብ ነገር አይሆንም፡፡ ደሃው ቆፍሮ፣ ላቡን ጠብ አርጎ የእለት ጉርሱን ሲያገኝ የቤተሰቡን ቀለብ በመሸፈኑ ከመደሰት ሌላ ብዙ የሚያስበው ነገር አይኖርም፡፡ ነገር ግን ስራው አንድ የሚያምር ትልቅ ቢሮ ውስጥ ተቀምጦ ሰዎችን አዝዞ፣ ወይም ሲጽፉ ውለው ወይም ሲያወሩ ውለው ብዙ ገንዘብ ማግኘት ሲሆን ብዙ የሚያሳስቡ ነገሮች ይኖራሉ፡፡ ራስን ከሰዎች ጋር ማወዳደር፣ ደረጃን ከፍ ለማድረግ መጨነቅ፣ የሚለብሱት፣ የሚነዱት፣ የሚኖሩበት ሁሉ ያሳስባል፡፡ ምቾት ብቻ ሳይሆን ስኬታማ ለመሆን(ስኬት ከተባለ) በጣም መማርና ማሰብ ማስፈለጉ ብዙ ነገሮች እንዲያሳስቡ ያደርጋል፡፡ በርግጥ ስለብዙ ነገር ለማሰብና ለመጨነቅ፣ ብዙ መማርና ብዙ ማሰብ፣ ያልተማረ የትም አይደርስም መባል አያስፈልግም፡፡
የዘመናዊ ስልጣኔ ጀማሪዎች የሚባሉትን እንደ ሶቅራጠስ ያሉ ፈላስፎችን ያመረተው፣ ክላሲካል ተብሎ ሚታወቀው፣ ጥንታዊት ግሪክ ከፍተኛ የስልጣኔ ደረጃ ላይ የደረሰችበት ዘመን፣ ጦርነት ያልነበረበት፣ ከበቂ በላይ ምግብ የተመረተበትና ጎተራ የሞላበት፣ ህዝቡ በተድላ ሲኖር የነበረበት ዘመን ነው፡፡ ሰዎች ሆዳቸው ሲሞላና የሚያሳስባቸው እውነተኛ ችግር ሲያጡ፣ አካባቢያቸውን መመራመር ይጀምራሉ፡፡ አንድ ፊልም ላይ እናት የሌለው ልጅ እናቴን በምናቤ ፈጥሬ አብራኝ እንዳለች አስባለሁ እንዳለው፣ አዕምሮአችን የሚያሳስበው ተጨባጭ ነገር ሲያጣ ለራሱ እንቆቅልሾችንና ውስብስብ ጥያቄዎችን ፈጥሮ ራሱን ያስጨንቃል፡፡ የሚያሳስበው እውነተኛ ነገር የሌለው አዕምሮ እግዚአብሔርን እስከ መፈታተን ይደርሳል፡፡ ታዲያ ይሄ ምቾት የሚያመጣው ቁስል፣ አካላዊ ችግር ከሚያመጣው በጣም ይብሳል፡፡

በመክብብ 5፡19-20 ላይ እንደ ተጻፈው "እግዚአብሔር ለሰው ሁሉ ባለጠግነትንና ሀብትን መስጠቱ፣ ከእርስዋም ይበላና እድል ፈንታውን ይወስድ ዘንድ በድካሙም ደስ ይለው ዘንድ ማሠልጠኑ፣ ይህ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው፡፡ እግዚአብሔር ደስታን ስለ ሰጠው እርሱ የሕይወቱን ዘመን እጅግ አያስብም፡፡" ሰው ወደ ምድር ከወደቀ ጀምሮ፣ ሰርቶ መብላት እጣፈንታው ብቻ ሳይሆን ስጦታው ሆኗል፡፡ ተፈጥሮው ነው፡፡ እግዚአብሔር ሰው የሚያምር ነገር አይቶ፣ የገንዘቡን ብዛት አይቶ፣ ጣፋጭ ምግብ በልቶ፣ በስካር፣ በዝሙት፣ በአዕምሮው ልህቀት፣ በክፉ ስራ ደስ እንዲለው ሳይሆን፣ በድካሙ ደስ እንዲለው ነው ትዕዛዙም፣ ፈቃዱም፡፡ የላቡን ዋጋ ሲበላ፡፡ ሰው የሚሰራው ለምግብ ብቻ አይደለም፡፡ ሰው እድሜ ልኩን የሚያኖረው ምግብ ቢኖረው እንኳን መስራት አለበት፡፡ ምክንያቱም ስራ ተፈጥሮው ነው፡፡ "ሊሰራ የማይወድ አይብላ" ይላልና ቃሉ፡፡
ሸክላ፣ ሰሪውን ለምን እንዲህ አደረግከኝ፣ ለምን እንዲህ አላደረግከኝም፣ አንተ ማን ነህ ብሎ ሰሪውን ሊጠይቀው አይችልም፡፡ አንደዚያው ደግሞ ምቾትና ሀብት ባመጡት መዘዝ የማይገባቸውን ጥያቄ እየጠየቁ ፈጣሪያቸውን የሚመረምሩና የሚፈታተኑ ሰዎች፣ እንደ ሸክላው ሁሉ ፍጡራን እንደመሆናቸው፣ ሰሪያቸው እንደ ወደደ እንደ ፈቃዱ ያደርጋቸዋል፡፡

መክብብ 1፡14፡- I have seen all the works that are done under the sun; and, behold, all is vanity and *vexation of spirit.* መክብብ 1፡17-18፣ 2፡22-25፣ 4፡5፣ 4፡8፣ 5፡8-20፣ 7፡2-4፣ 7፡23-25(7፡25፡- I applied mine own heart to know, and to search, and to seek out wisdom, *and the reason of things,* and to know the wickedness of folly, even of foolishness and madness:) ፣ 7፡29፣ 8፡9፣ 8፡15-17፣ 12፡12፡፡

መጽሐፈ ምሳሌ 1፡1፡- የእስራኤል ንጉሥ የዳዊት ልጅ የሰለሞን ምሳሌዎች፡፡

ምሳሌ(proverb) የሚለው ቃል የእብራይስኛ ቀጥተኛ ትርጉም ማነጻጸር(comparison) ማለት ነው፡፡ በእውነትም ደግሞ በዚህ መጽሐፍ ጠቢብና ሰነፍ... ይነጻጸራሉ፡፡ ነገር ግን ቃሉ ሰፋ ላሉ ሀዘንንና ጸጸትን ለሚገልጹ ምሳሌያዊ ንግግሮችም ውሏል፡፡ በምሳሌ መጽሐፍ ውስጥ ምሳሌ የሚለው ቃል ቀጥተኛ፣ እውነተኛና ክብደት ያላቸው ሀሳቦችን ለመግለጽ ገብቶአል፡፡
በሰለሞን የምሳሌ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱ ምሳሌዎች አጭርና ግልጽ ንግግሮች ሲሆኑ ጊዜ የማይገድበውን እውነትና ጥበብን ይገልጻሉ፡፡

መጽሐፈ ምሳሌ በመክብብ ከንቱና ስንፍና የተባሉትን ነገሮች(ገንዘብ፣ ጥበብና እውቀት)(መክብብ 1፡17) ስለሚከተሉና የእግዚአብሔርን በጎ ጥበብና ማስተዋልን ስለሚከተሉ ሰዎች ይናገራል፡፡ የመጀመሪያዎቹን(አለምን የሚከተሉትን) ሰነፍ፣ ሞኝ፣ ይላቸዋል፡፡ የእግዚአብሔርን ጥበብ የሚከተሉትን ደግሞ፣ ጠቢብ፡፡ ብዙ ሰዎች መጽሐፈ ምሳሌን በትክክል አይረዱም፡፡ አለማዊ ት/ቤት ሄዶ መማርን እግዚአብሔር እንደሚደግፍ አርገው መናገር ሲፈልጉ ከመጽሐፈ ምሳሌ ይጠቅሳሉ፡፡ በትክክል ስናየው ግን ተቃራኒው ነው ትክክል፡፡

ምሳሌ 1፡7፡ "የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው፡፡ ሰነፎች ግን ጥበብንና ተግሳጽን ይንቃሉ፡፡"

አንድ ሰው አዋቂ ነኝ ብሎ ማሰብ ሲጀምር የመጀመሪያው ነገር ራሱን በጣም ያከብራል፡፡ ራሱን በጣም ያደንቃል፡፡ ራሱን ከፍ ከፍ ያደርጋል፡፡ ሰዎችን ይንቃል፡፡ ቃሉ በምሳሌ 18፡12 "ሰው ሳይወድቅ በፊት ልቡ ከፍ ከፍ ይላል፣ ትሕትናም ክብረትን ትቀድማለች፡፡" ይላል፡፡ እንደኔ፡፡
ብዙ የማወቅ ትልቁ ችግር ሁሌ አንተ ትክክል እንደ ሆንክ ማሰብህ ላይ ነው፡፡ ንቀት በልብህ ውስጥ ይሰርጻል፡፡ እንደዚያ እንደምታስብ አታምንም ግን እኔ ብቻ ነኝ ትክክል ትላለህ፡፡ ጠቢብ ነኝ ብለህ፣ ልብህ ይነፋል፡፡

ቀጥሎ ቁጥር 8-9 "ልጄ ሆይ፣ የአባትህን ምክር ስማ፣ የእናትህን ሕግ አትተው፡፡ ለራስህ የሞገስ ዘውድ ለአንገትህም ድሪ ይሆንልሃል፡፡"
የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው ማለት ቀጣዩ ጥበብ ደግሞ ከንቱውን የአለምን ጥበብ ማግበስበስ ነው ማለት አይደለም፡፡ የጥበብ መሰረት እግዚአብሔርን መፍራት ነው ማለት እንጂ፡፡ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው የመጀመሪያ ባህርይ ደግሞ አባትና እናቱን በሙሉ ልብ ማክበር፣ መታዘዝ፣ ምክራቸውን መስማት ነው፡፡ እናትና አባትህን ታከብራለህ ወይ? ብዙ ያወቅክ ሲመስልህ አባትና እናትህ የማይረዱህ መሃይሞች ይመስሉሃል፡፡ መቼም አይረዱኝም ትላለህ፡፡ ምክራቸው እቃ እቃ ጨዋታ ይመስልሃል፡፡ ልትከራከራቸው ይቃጣሃል፡፡ ትንቃቸዋለህ፡፡ ስትታዘዝ በግድ ነው የምትሰራው፡፡ ቃሉ መታዘዝ መስዋዕት ከማቅረብ ይበልጣል ይላል፡፡ የአቤልንና የቃየንን መስዋዕት አስታውስ፡፡ መማርን አደገኛ የሚያደርገው ይሄ ነው፡፡ የተማረ ሰው ወላጆቹ ሞኝ ላይመስሉት አይችልም፡፡ ባይመስሉትም በልቡ አያከብራቸውም፡፡ ለዚህ ነው እግዚአብሔር ከአለም ጥበብ እንድንርቅ የሚያዘን፡፡ ትእዛዙን ከመጠበቅ ስለሚያጎድለን፡፡

ምሳሌ 30፡17 "በአባቷ የምታላግጥን የእናቷንም ትእዛዝ የምትንቅን ዓይን የሸለቆ ቁራዎች ይጎጠጉጡአታል፣ አሞራዎችም ይበሉአታል፡፡" ይላል፡፡ ስለ ምንናረገው ነገር ብቻ አይደለም፡፡ ስለ ምናስበውም ጭምር እንጂ፡፡ ወላጆችህን ምን ያህል ታከብራለህ? ፈረንጆች ወላጆቻቸውን ምን ያህል ያከብራሉ? በኢትዮጵያ ገጠር አካባቢዎችስ? ፈረንጆችን እኛ ጠቢባን፣ አዋቂዎች እንላቸዋለን፡፡ ነገር ግን ወላጆቻቸውን አያከብሩም፡፡ የእግዚአብሔር ቃል የአባትን ምክር መስማትና የእናትን ሕግ አለመተው ጥበብ ነው ይለናል፡፡ ሰነፎች ግን ጥበብንና ተግሳጽን ይንቃሉ ይላል፡፡ ሰነፍ የሚለውን ቃል እንግሊዘኛው መጽሐፍ ቅዱስ fool(ሞኝ) ይለዋል፡፡ ስለዚህ በእግዚአብሔር አይን ፈረንጆች ሰነፎች ወይም ፉሎች ወይም ሞኞች ናቸው ማለት ነው፡፡ የአባቱን ትእዛዝ ሳያንገራግር የሚያደርገው ገጠሬው፣ ወላጆቹን በሙሉ ልቡ የሚያከብረው ደግሞ እኛ ብንንቀውም በእግዚአብሔር ፊት፣ እሱ ነው ጠቢብ፡፡ እኛ በገጠሬውና በፈረንጁ መሃል ያለን፣ እንደ ፈረንጁ ያልሰለጠንን፣ እንደ

ገጠሬውም ያልገጠርነው፣ የገጠሬው ያህል ወላጆቻችንን የማናከብረው፣ በወላጆቻችን ላይ ሀይለ ቃል ለመናገር የማንደፍረው፣ ግን የፈረንጅ ባህል የሚያስጎመጀን ደግሞ፣ ወደ ጥፋት የምናመራ ተቅበዝባዦች ነን።

ምሳሌ 1፡ "10 ልጄ ሆይ፣ ሃጢአተኞች ቢያባብሉህ እሺ አትበል። 11 ደምን ለማፍሰስ ለእኛ ጋር ና እናድባ፣ ለንጹሕም ያለ ምክንያት ወጥመድን እንሸምቅበት ቢሉ።

12 በሕይወታቸው ሳሉ እንደ ሲኦል ሆነን እንዋጣቸው፣ በሙሉም ወደ ጉድጓድ እንደሚወቀድቁ ይሁኑ። መልካሙን ሀብት ሁሉ እናገኛለን፣ ከምርኮውም ቤታችንን እንሞላለን። ዕጣህን ከእኛ ጋር ጣል። የሁላችንም አንድ ከረጢት ይሁን ቢሉ። ልጄ ሆይ፣ ከእነርሱ ጋር አትሂድ፣ ከጎዳናቸውም እግርህን ፈቀቅ አድርግ። እግሮቻቸው ወደ ክፉት ይሮጣሉና፣ ደም ለማፍሰስም ይፈጥናሉና። መርበብ በወፎች አይን ፊት በከንቱ ትተከላለችና።

18 እነርሱም በደማቸው ላይ ያደባሉ፣ በነፍሳቸውም ላይ ይሸምቃሉ። 19 እንዲሁ ይህ መንገድ ትርፍን ለማግኘት የሚሳሳ ሁሉ ነው። የባለቤቱን ነፍስ ይነጥቃል። (so are the ways of everyone that is greedy of gain; which taketh away the life of the owners thereof.)

እናንተ አላዋቂዎች እስከ መቼ አላዋቂነትን ትወዳላችሁ? ፌዘኞችም ፌዝን ይፈቅዳሉ? ሰነፎችም እውቀትን ይጠላሉ? ወደ ዘለፋዬ ተመለሱ እነሆ መንፈሴን አፈስስላችኋለሁ። ቃሌንም አስተምራችኋለሁ።

በጠራሁ ጊዜ እምቢ ስላላችሁ፣ እጄንም በዘረጋሁ ጊዜ ማንም ስላላስተዋለ፣ ምክሬን ሁሉ ግን ቸል ስላላችሁ፣ ዘለፋዬንም ስላልፈቀዳችሁ። እኔም ስለዚህ በጥፋታችሁ እስቃለሁ። ጥፋታችሁም በመጣ ጊዜ አላግጥባችኋለሁ። ድንጋጤ እንደ ጎርፍ በደረሰባችሁ ጊዜ፣ ጥፋታችሁም እንደ ዐውሎ ነፋስ በመጣ ጊዜ፣ ጭንቅና መከራ በወረደባችሁ ጊዜ። የዚያን ጊዜ ይጠሩኛል፣ እኔ ግን አልመልስም። ተግተው ይሹኛል፣ ነገር ግን አያገኙኝም። እውቀትን ጠልተዋልና፣ እግዚአብሔርንም መፍራት አልመረጡምና። ምክሬንም አልፈቀዱምና፣ ዘለፋዬንም ሁሉ ንቀዋልና። ስለዚህ የመንገዳቸውን ፍሬ ይበላሉ፣ ከራሳቸውም ምክር ይጠግባሉ። አላዋቂዎችን ከጥበብ መራቅ ይገላቸዋልና፣ ሰነፎችንም ቸልተኛ መሆን ያጠፋቸዋልና። የሚሰማኝ ግን በእርጋታ ይቀመጣል፣ ከመከራም ስጋት ያርፋል።"

ይሄ ክፍል ስለ ሲኦል አይደለም። በህይወት ሳሉ ስለሚያጋጥም ሲኦል እንጂ። እምቢ እምቢ፣ ቃሉ ቸል ቸል ከተባለ በኋላ፣ እግዚአብሔር መንፈሱን የሚመልስበት ጊዜ አለ፣ ጸሎታችንን የማይሰማበት ጊዜ አለ። በገሃነም ውስጥ ንስሃ መግባትና መዳን የለም። ያ በምድር ላይም አለ ነው የሚለው ቃሉ። በርግጥም ደግሞ አለ።

ራስህን ላይ፣ ጣሪያ ላይ ትሰቅላለህ፣ ከዚያ ውድቀት ድንገት ሲመጣ፣ ራስህን ላይ ጣሪያ ላይ የሰቀልከው ሰውዬ፣ ራስህን ታች፣ ከወለሉ በታች ታየዋለህ፣ ማህበረሰቡ ውስጥ ራስህን የምታይበት መንገድና የምትሆነው፣ ሆድና ጀርባ ይሆናሉ። ዳቦ እየጠበቅክ ድንጋይ ይቀርብልሃል። መጀመሪያ ይሄማ እኔ አይደለሁም ብለህ ነገሮችን ለማስተካከል፣ ራስህን እንደገና ለማስከበር በጣም ታስባለህ፣ ትጥራለህ። የበለጠ ባሰብክና በጣርክ፣ ቁጥር ነገሮች የባሰውን እየከፉ፣ እየከፉ ይመጣሉ።

እኔ 10ኛ ክፍል በጣም አስከፊ ጊዜ ሳሳልፍ፣ በሰዎች ላይ ነበር ሳላክክ የነበረው። ልጆች እንዲህ አረጉኝ ምናምን። ነገር ግን እየተቀጣሁ ነበር። ለዚህ አለም ጥበብና እውቀት ልቤን ከፍቼ ነበር። ለሞኝነት ልቤን ከፍቼ ነበር። የአለምን ከንቱነት መፈለግ ደግሞ ከእግዚአብሔር መንፈስ ሰውን ይዞ ይጠፋል። ሰለሞን እግዚአብሔርን አልካደም። ነገር ግን የእግዚአብሔርን ጥበብ ለአለማዊነት ስለተጠቀመ ይዞት ሄደ። የአለም ጥበብ ደግሞ የአለም ጥበብ ነው። የእግዚአብሔር ጥበብና የአለም ጥበብ ሁለት ተጻራሪ ነገሮች ናቸው። ሁለቱን አንድ ላይ ማስኬድ የሚባል ነገር የለም። እግዚአብሔር የሞኞች አምላክ ነው። እግዚአብሔር እንደ ህጻናት በሞኝነት የሚያምኑት አምላክ ነው። ይሄ የኔ ታሪክ አጋጣሚም አይደለም። ለመረጥኩት መንገድ የተቀበልኩት ሽልማት ነው። ይሄ የኔ ታሪክ አጋጣሚ አይደለም ምክንያቱም፣ ኢንተርኔት ላይ እንደኔው፣ ከሚኖሩበት ከተማ ሲወጡ፣ ሰላማቸው የሚመለስላቸው የመሰላቸው፣ በጣም እኔ እንደማስበውና እኔ እንደ ተሰቃየሁት የተሰቃዩ፣ በሙዚቃ ብሶታቸውን የሚገልጹ፣ በጣም እኔን እስኪመስሉኝ ተመሳሳይ ታሪክ ያላቸው ብዙ ሰዎችን ታሪክ አንብቤአለሁ። አንድ ፈረንጅ ወጣት(ቲኔጀር) የጻፈችውን እንግሊዘኛ ግጥም አንባቢዬን ላካፍልህ፡

What do you call it when all you feel is pain?
When your loved ones look at you and all you feel is shame?
When you're tired of playing this game?
When you know your life is meaningless and you're the only one to blame?
What do you call it when the hurt is in your soul?
When you smile and laugh but you know it's all a show?
When you feel you've hit your all time low?
When nothing makes you happy and the darkness around you grows?
What do you call it when you feel so alone?

When you look back in your life and every choice you made now seems wrong?
When the wait to die seems too long?

ኳየር እሄድ የነበረ ጊዜ፣ አንድ ቀን የኳየር ቤታችን ልጆች አልመጡም ነበርና አራት ልጆች ብቻ ነበርን የሄድነው፡፡ ፈይሳ እየመራን ነበር፡፡ ከአራታችን አንዱ ልጅ፣ ስለ ኳየር ሲያወራ፣ "እኔ ይሄ ኳየር፣ ትራክ የያዘው ዲስክ ይመስለኛል" ሲል እኔ ሳቅኩኝ፡፡ ያን ቀን ፈይሳ እኔን ያየበትን አስተያየት አስታውሰዋለሁ፡፡ አይቶኝ ፈገግ አለ፡፡ ጥቂት ስለነበርን ፈታ ብዬ ስለነበረና በነጻነት ስለ ሳቅኩኝ ነው ፈይሳ በግርምት ፈገግ ብሎ ያየኝ፡፡ ዌልካም ናቲ አይነት አስተያየት፡፡ በመፍታታቴ የመደሰት አስተያየት፡፡ ምን ያደርጋል፣ ያ ነጻነት፣ ጊዜያዊና ቅጽበታዊ ነበረ፡፡ እንደዚያው ባስቀጥለው ምኞቴ ነበር፡፡ ከሁሉም ጋር በሰላም መኖር እችል ነር፡፡ ነገር ግን በዚህ ዓለም ላይ የማይቻሉ የሚመስሉ ነገሮች እየተቻሉ እንደመጡት ሁሉ፣ ቀላል፣ ኢምንት የሆኑ ነገሮች በፍጹም የማይቻሉም ሆነዋል፡፡ ምን ያህል በህይወቴ ተጫውቻለሁ? ራሱን የሚወቅስ ሊኖር ይችላል፣ ልወቅሰው የምንችለው ሰው ያለ ሊመስል ይችላል፣ እውነታው ግን እኔው ነኝ በእጄና በሌላ ሰው እጅ ራሴን የገረፍኩትና የተሰቃየሁት፡፡ **I am the only one to blame.**

ምሳሌ 15፡13 "ደስ ያለው ልብ ፊትን ያበራል፤ በልብ ኀዘን ግን ነፍስ ትሰበራለች፡፡"

ምሳሌ 12፡25 "ሰውን የልቡ ኀዘን ያዋርደዋል፡፡ መልካም ቃል ግን ደስ ያሰኘዋል፡፡" ይላል፡፡
ውርደት(stoop) ማለት የሚጠበቁበት ቦታ አለመገኘት፣ ወይም የማይጠበቁበት ቦታ ላይ መገኘት ማለት ነው፡፡ አላሙዲን ገንዘብ ሲለምን እንደ ማግኘት፡፡ ውርደት ነው አይደል የሚሰማው? ልዩነቱ፣ እኔ እያልኩ ያለሁት መንፈሳዊ ነው፡፡

በልጅነቴ ነፍስ ሲባል፣ ድው ድው የሚለው የልብ ትርታዬ ነፍሴ ይመስለኝ ነበር፡፡ ለስጋዊና ለአለማዊ ነገር መኳተን፣ ባለ ጠግነትን መከተል፣ ሁሉን ለመብለጥ ዝነኛ ለመሆን፣ በሰው ለመከበር የሚደረግ ጥረት፣ የአለምን እውቀት መከተል፣ ለዚህ አለም ጥበብ ልብን መክፈት፣ ዝሙት፣ ሱስ...፡፡ ሰው ከስጋ ከመንፈስና ከነፍስ ነው የተፈጠረው፡፡ ስጋ ሰው በህይወት እስካለ አብሮት ያለ ነገር ነው፡፡ ነገር ግን ስጋን ስንክደው፣ ስንንቀውና የእግዚአብሔርን ጥበብ ስንከተል፣ ወደ መንፈስ እንጠጋለን፡፡ መንፈሳችን ይገለጣል፡፡ ፍሬውንም ማየት እንጀምራለን፡፡ ነፍስም ታርፋለች፣ ሀሴት ታረጋለች፡፡ ሰላምም ይሆንላታል፡፡ (ዮሐ. 27፡14)፡፡ ልባችንን ለአለማዊ ነገሮች ስናተጋውና ስጋችንን ስንከተል ደግሞ፣ ያ ነፍስን በስጋ ውስጥ ለማግኘት የሚደረግ አሰሳ ነው፡፡ ነፍሳችንን እንፈልጋለን፣ እንፈልጋለን፣ እንፈልጋለን፣ አንዳንዶች፣ ነፍሳቸውን እየፈለጉ፣ እየፈለጉ፣ ማለትም በሃጢአት ውስጥ ተዘፍቀው እያሉ፣ ነፍሳቸውን ሳያገኙ፣ መንገድ ላይ የህይወትን ቃል ሰምተው ፊታቸውን ወደ እግዚአብሔር ይመልሳሉ፡፡ ስጋቸውን ትተውም ወደ መንፈስን መፈለግ ይጀምራሉ፡፡ ስጋቸውን ይክዳሉ፡፡ በመጨረሻም እግዚአብሔር ወዳዘጋጀላቸው ክብር ይገባሉ፡፡ አንዳንዶች በአለም ተጠምደው ስጋቸውን ሲከተሉ፣ ነፍሳቸውን ሳያገኙዋት ይሞታሉ፡፡ ለነዚህ ደግሞ ገሃነም ይጠብቃቸዋል፡፡ አንዳንዶች ደግሞ ነፍሳቸውን ሲፈልጉ ሲፈልጉ፣ አንዳንዶች፣ ነፍሳቸውን በ12 አመታቸው ያገኙዋትል፡፡ አንዳንዶች በ13 አመታቸው ያገነኙዋታል፡፡ አንዳንዶች በ16 አመታቸው ያገኟታል፣ አንዳንዶች አርጅተውም ያገኙዋታል፡፡ በነፍሳቸው ላይ ይሸምቃሉ፡፡ አንዴ ነፍስህን ካገኘህ በኋላ ሁሉም ነገር ረፍዷል፡፡ ቃሉ "*ጥበብ በጎዳና ትጮሃለች፣ በአደባባይም ድምጽዋን ከፍ ታረጋለች፡፡ በአደባባይ ትጣራለች፡፡ በከተማይቱ መግቢያ በር ቃልን ትናገራለች፡፡*" ይላል፡፡ ጥሪውን ላልተቀበሉትና ጆሮ ዳባ ልበስ ላሉት ከዚያ በኋላ ህይወት ትለዋወጣለች፡፡ ህይወትህ ከእጅህ ትወጣለች፡፡ 10ኛ ክፍል ጭንቀት ሲይዘኝ፣ መጽሐፍ ቅዱስም አላነብም፣ ባነብም ነፍስ ለኔ እንቆቅልሽ፣ ምንም የማይገባኝ ነገር ነበረ፡፡ ከዚያ ወዲህ ግን መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ ሳልጀምር ነበር "ነፍሴ ተሰቃየች" ማለት የጀመርኩት፡፡ ነፍስን አንዴ ካገኘሃት በኋላ እረፍት የለም፡፡ እርካታ የለም፡፡ ደስታ የለም፡፡ አዲስ ማንነት ነው፡፡ ነፍስህን በራስህ ራስህ ላይ ትቀሰቅሳታለህ፡፡ ነፍስህ እረፍት አትሰጥህም፡፡ ታሰቃይሃለች፡፡

ነፍስ ባልተገኘበት አለም፣ ስለ ምትበላው፣ ስለምትለብሰው ነገር ትጨነቃለህ፣ ስለ አለም ትጨነቃለህ፣ ግን ይሄ መኖርን እንድትወደው እንጂ፣ ያንን ነገር ማግኘት የሚያስደስትህ ስለሚመስልህ መኖርን እንድትጠላው አያደርግህም፡፡ ተስፋህ አልሞተም፡፡ ግን የሚጠፋውን ነው ተስፋ ያደግከው፡፡ የሚገልህን ነው ተስፋ ያደረግከው፡፡ ከዚያ በመንገድ ላይ ነፍስህን ስታገኛት ግን የህይወትህ ጸሃይ ተመልሳ ላትወጣ፣ ስትገባ ሸኝት ታደርግላታለህ፡፡ ቁልቁል ስትወርድ ራስህን ትታዘባለህ፡፡ የምትንቃቸው ሰዎች ሲንቁህ አይተህ ልብህ ለሁለት የተፈለቀቀ ይመስልሃል፡፡ ገሃነምን በምድር ላይ ትለማመዳለህ፡፡ ሰው ያስጠላሃል፣ ስለ ሰው መልካም ነገር ማሰብ ይከብድሃል፡፡ ገጣሚው እንዳለውም፣ ሁሉም ነገር ውድቀት እንደሆነ፣ አንድም ትክክል እያደረግክ ያለኸው ነገር እንደሌለ ታስባለህ፡፡ መልካም፣ የሚያስደስት ነገር ለማሰብ ትሞክራለህ ግን ያቅትሃል፡፡ የልብህ ንዳድ፣ ለሰዎች ይታያቸዋል፣ ዝቅ ዝቅ እያልክ፣ በቁምህ እየሞትክ፣ ችግሩ ራስህ እንደ ሆንክ እስከትረዳ ድረስ ሰዎችን ትወቅሳለህ፡፡

ምሳሌ 26፡13፡- "ታካች ሰው፡- አንበሳ በመንገድ አለ፣ አንበሳ በጎዳና አለ ይላል፡፡" መኖር ከታከተው ሰው የበለጠ ታካች የለም፡፡ አዲስ ጸባይ ታመጣለህ፡፡ መንገድ ላይ የሚመጡብህን ሰዎች ፈርተህ ከቤት መውጣት ያስጠላሃል(ያስፈራሃል)፡፡ ሰውን መሸሽ ስትጀምር ነፍሳቸውን ያላገኙ ጓደኞችህ ምንድነው ሰው ይበላሃል እንዴ? ይሉሃል፡፡

ስለ ሚሰማህ ስሜት፣ ስለ ብዙ ጥልቅ ነገሮች ማውራት ትጀምራለህ፡፡ ጓደኞችህን ታሰለቻለህ፣ ታስጨንቃቸዋለህ፣ ትወሳሰብባቸዋለህ፡፡ ከመቼ ጀምሮ ነው እንዲህ ማውራት የጀመርከው ይሉሃል፡፡ ምሳሌ 18፡2፡- "ሰነፍ የጥበብን ነገር አይወድድም፡፡ በልቡ ያለውን መግለጥ ብቻ ይወድዳል እንጂ፡፡" ይላል፡፡ ብዙ ጊዜ በተደጋጋሚ ከ10ኛ ክፍል በኋላ ማዕበል እንደመታኝና ሌላ ሰው እንዳረገኝ፣ የበፊቱ ህይወቴ እንደሚናፍቀኝ ለማውቃቸው ሰዎች ከመለፍለፌ የተነሳ "በቃ 10ኛ ክፍል ላንተ ትልቅ ነገረ ነው አይደል?" ይሉኛል፡፡ መናገር የሌለብኝ እንደሆነና በልቤ ይዤው ልሰቃይበት የሚገባኝ ነገር እንደሆነ እያወቅኩና መናገር እንደሚጎዳኝ እያወቅኩ ነው የምለፈልፈው፡፡ በጣም ይገርመኛል፡፡ ታዲያ ሳወራ ሰው አጨናንቃለሁ፡፡ አንዳንዴ እያወራሁ እምባ ይተናነቀኛል፡፡

በአንጻሩ አስተሳሰብህ ይቀየራል፡፡ የምታስበው ነገር ሁሉ ከልብህ፣ ከነፍስህ ይሆናል፡፡ የዚህ አለም ትርጉም ይገባሃል፡፡ ሰው ሁሉ የሚሮጠው፣ ለመብለጥ፣ ለክብርና የበላይ ለመሆን እንደሆነ እድሜ ዘመንህን አስበህ የማታውቀው ነገር ይገለጥልሃል፡፡ ተቀባይነት ለማግኘት ትጥራለህ፡፡ ነገር ግን በማታስበው ጊዜ የነበረህንም ነገር እያወቅክ፣ እያሰብክበት፣ የምታስበው ወደ ላይ፣ የምትሄደው ወደ ታች ይሆናል፡፡ በኮንሸንስነስ ቋንቋ፣ በፊት ሰብኮንሸንስሊ የምትኖረውን ማህበራዊ ህይወት ኮንሸንስሊ ማጤን ትጀምራለህ፡፡ ታዲያ ስለ ማህበራዊ ህይወትህ ማሰብ ስትጀምር ባለ መቶ እግርነቱ እንደተነገረው መቶ እግር ትል ተጠላልፈህ ትወድቃለህ፡፡ ማሰብ ስትጀምር ከበፊቱ የምታሻሽለው የመሰለህ ህይወትህ፣ ሲወርድ፣ ሲወርድ፣ ኮንሸስሊ፣ ነቅተህ ትታዘበዋለህ፡፡ እንዲህ ሳይበራልህና ሳታውቅ ማህበራዊ ህይወትህ ቢወድቅ ማደንዘዣ ተወግቶ፣ ሳያውቁና ሳይነቁ ተቀዶ እንደ መሰፋት ነው፡፡ ይሄ ኮንሸስ ውድቀት ደግሞ እያንዳንዷ ወደ ታች የምትደረግ እንቅስቃሴ እየተሰማችህ፣ ያለምንም ማደንዘዣ፣ እንዲያውም የበለጠ እንዲያምህና ስቃዩ እንዲብስብህ የተወጋኸው ነገር ያለ እስኪመስል ድረስ እያንዳንዷን የግንባር ቋጠሮ፣ የአይን ጥንካሬ፣ የሰዎች ጭካኔ፣ ልቡ እንደሚተረተር ሰው እየተሰማህ ትሰቀያለህ፡፡ ሰዎች ያላሰቡት ነገር እንኳን በአንተ አዕምሮ ውስጥ እየተፈጠረ መንፈስህን ይሸረካክተዋል፡፡ ራስህን ትጠላለህ፡፡

አንድ ፈረንጅ የፌስቡክ ጓደኛዬ እንዲህ ብላ ፖስት አረገች፡፡ “If the wounds on my heart and the bruises on my soul were translated on my skin, you wouldn’t recognize me anymore.” “ልቤ ላይ ያሉት ቁስሎችና ነፍሴ ላይ ያሉት ብልልዞች ቆዳዬ ላይ ቢገለበጡ፣ ማን እንደሆንኩ አትለዩኝም ነበር፡፡”

አስረኛ ክፍል ለነሄለን “ለአንድ ቀን ማደንዘዣ ተወግቼ ራሴን ስቼ፣ ከዚህ አለም ጣጣ ለአንድ ቀን አርፌ ውዬ ባድር ደስ ይለኛል” ማለቴ ትዝ ይለኛል፡፡ በጣም ህይወት መራኝ ስለነበረ እንደዚያ እንዳልኩ እንዳልገባቸው ግን እርግጠኛ ነኝ፡፡

አንዳንዴ ሰዎች ሲያወሩ፣ ነገሮችን አጠናና አንዱ አንዱ ላይ የሆነ እየሸረበ ያለው ነገር እንዳለ ወይም መጥፎ ነገር እንዳለ አስብና ባለ ቤቱ ከነቃ ብዬ ሳስብ፣ እሱ አይገባውም፡፡ በጭራሽ አይጠረጥርም፡፡ ቢጠረጥርና ቢያስብ ግን የሚናደደው እሱ ነው፡፡ አንዳንዴ ደግሞ ሰዎች የሚያስከፉ ነገሮችን ጥሩ ጎናቸውን ፈልፍለው ፈልገው ሲያወሩ ይገርመኛል፡፡ አንዳንዴ ጥሩ ያልሆነ ነገር ጥሩነቱ ሲታያቸውና ፖዘቲቭነትን በውስጣቸው ሳይ አንዳንዴ “እኔም እንደ እናንተ ባስብ ደስ ይለኝ ነበር” እላቸውና እግዚአብሔር አስተሳሰባቸውን የሚጠብቅበት መንገድ ይገርመኛል፡፡ አንዳንዱ ብዙ ጥሩ ነገር ኖሮት፣ የሌለ መጥፎ ነገር ይታየዋል፡፡ አንዳንዱ ብዙ መጥፎ ነገር ኖሮት ያ መጥፎ ነገር መልካም መስሎ ይታየዋል፡፡ ደስታና እርካታ እግዚአብሔር በውስጣችን የሚያስቀምጣቸው ነገሮች ናቸው እንጂ በዚህ አለም ውስጥ ፈልገን የምናገኛቸው ነገሮች አይደሉም፡፡

የምታደርጋቸው ነገሮች ጥልቀት ይኖራቸዋል፡፡ የምትናገራቸው ነገሮች ሰዎችን ያስገርማሉ፡፡ ቀልዶችህ ያስቃሉ፡፡ ራሴን ማካበድ አይሁንብኝና፣ በየቀኑ የምትላቸውን ነገሮች ብትጽፍኮ መጽሐፍ ይወጣዋል ተብዬ አውቃለሁ፡፡ የምትሰራው ነገር ሁሉ ያምርልሃል፡፡ ለዚህ ነው የፈረንጅ ስራዎች በጣም ጥልቀት የሚታይባቸው፡፡ ከዘፈናቸው ጀምሮ ነፍስን ይገዛሉ፡፡ ነፍስን ለማግኘት የሚደረገውን አሰሳም ያጥዋጥፉታል፡፡ ነገር ግን ጸሃይዋ ገብታለች፡፡ በዚህ ምክንያት በሚገኘው የአዕምሮ ልህቀት የሚገኘው ክብርም ሆነ ገንዘብ የደስታን ጸሃይ ወደ ህይወት አይመልስም፡፡ ብዙ የሆሊውድ አርቲስቶች ዝናቸውን ማጣጣም ሲሳናቸው ተስተውሏል፡፡ ሁሉም ዝነኛ መሆን ይፈልጋል፣ ዝነኛ ካልሆኑ ደስተኛ መሆን የማይችሉና ህይወት ትርጉም እንደሌላት ያስባሉ፡፡ ክብር ይጠማቸዋል፡፡ ዝነኛ የሆኑት   ቲቪ ላይ ታይተው ሰው ለፊርማቸው ስማቸውን እየጠራ ሲለምናቸው ያልማሉ፡፡ ለዚያም የሞት ሽረት ትግል ያደርጋሉ፡፡ ከዚያ ጥቂቶች ይሳካላቸዋል፡፡ መጀመሪያ ደስ ይላቸዋል፡፡ ህልማቸው ተሳክቶ እንዴት ደስ አይላቸውም? ማንም ሁለቴ ደግሞ የማያያቸውን ጊዜ እያስታወሱ፣ አሸናፊነት ይሰማቸዋል፡፡ ስንት ሚሊየን ሰው እንደነሱ ለመሆን እንደሚፈልግ እያሰቡ ደስ ይላቸዋል፡፡ ድሮ እንደ ሌላው የፈለጉበት ቦታ በፈለጉበት ሰአት ደርሰው የሚመለሱበት ጊዜ ሊናፍቃቸው ግን ብዙ አይቆይም፡፡ የበፊቱ ህይወታቸው ይናፍቃቸዋል፡፡ ብዙዎቹ ዝነኛ ከመሆናቸው በፊት ከነበረው የበለጠ ደስታ የራቀው ህይወትን ለመምራት ይገደዳሉ፡፡ አንዳንዶቹ ራሳቸውን እስከ ማጥፋት ይደርሳሉ፡፡ ሁሌም የሚያስጨንቅ ስሜት ይከተላቸዋል፡፡ የገንዘብ ብዛት፣ ዝነኝነት፣ አደንዛዥ ዕፅ የማያባርረው ስሜት፡፡ ስለዚህ ቲቪ ላይ ያለውም ቲቪውን የሚያየውም ልዩነት አይኖራቸውም፡፡ ሁሉም ግን ቲቪዋ ላይ መንቀሳቀስ ይፈልጋል፡፡

ፌዝና ቀልድ የግልህ ይሆናሉ፣ ቀልዶችህ ማሳቅ ብቻ ሳይሆን ሌሎችን ያስቀናሉ፡፡ በዕውቀቱ ስዩም እንደገጠመው ግን፡

“ቧልትን ከፈገግታ
ሣቅን ከፌዝ ጋራ
ባ’ንድ ላይ ቀይጠን
አቅልመን በጥብጠን
በሐዘን ባሕር ላይ፣ ብናንቆረቁርም
ባሕሩ ሰፊ ነው፣ መልኩን አይቀይርም፡፡”

“በሳቅ ደግሞ ልብ ያዝናል፣ የደስታም ፍጻሜ ልቅሶ ነው፡፡” ምሳሌ 14፡13 (Even in laughter, the heart is sorrowful; and of that mirth [is] heaviness.)

Intelligence and suffering ብዬ ጉግል ላይ ሰርች ሳረግ "Pain and suffering are always inevitable for a large intelligence and a deep heart. The really great men must, I think have great sadness on earth." የሚል ጽሁፍ አነበብኩኝ፡፡ "ህመምና ጭንቀት ከትልቅ የማሰብ ችሎታና ከጥልቅ ልብ፣ መለየት የማይቻሉ ነገሮች ናቸው፡፡ ትልልቅ የምንላቸው ሰዎች በዚህች አለም ላይ ትልልቅ ሀዘንተኞች ናቸው ብዬ አስባለሁ፡፡"

በ20ኛው ክ.ዘ. ዝናቸው ከገነነው ደራሲዎች መሃል ግንባር ቀደሙ የነበረው፣ አሜሪካዊው ደራሲ፣ ኤርነስት ሄሚንግዌይ አባባሎች መካከል፡

"Happiness in the intelligent people is the rarest thing I know." (ትልቅ የማሰብ ችሎታ ያላቸው ሰዎች ውስጥ ደስታ፣ ከማውቃቸው ነገሮች ለማግኘት በጣም የሚከብደው ነው፡፡)

"All thinking men are atheists." (ሁሉም (በጣም) የሚያስቡ ሰዎች ሃይማኖት የለሽ ናቸው፡፡)
ይሄን ሙሉ በሙሉ መቀበል ባይቻልም፣ ከዘመናትና ከሀገራት አንጻር ስናየው አስተሳሰባችን ባደገ መጠን ከእግዚአብሔር እየራቅን እንደምንሄድ ማየት እንችላለን፡፡ (ሉቃስ 8፡16)፡፡ ለዚያ ነው የእግዚአብሔር ቃል ከአለም እውቀት እንድንርቅ በተደጋጋሚ የሚያስጠነቅቀን፡፡ የምዕራባውያን የሁሉም ውድቀት ስር መሰረት መጀመሪያው እውቀት ነው፡፡ ከእውቀት ቀጥሎ ገንዘብ አለ፡፡ ገንዘብ ደግሞ የክፋት ሁሉ ስር ነው ይላል ቃሉ፡፡ የእግዚአብሔር ጥበብና የሰው ጥበብ አብረው አይሄዱም፡፡ ይሄ ገብቶት ሳይሆን አይቀርም ደራሲው እንደዚያ ያለው፡፡፡

"You can't get away from yourself by moving from one place to another." (ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ፣ አድራሻህን በመቀያየር ከራስህ መራቅ አትችልም፡፡)
ይሄ እያወራን ያለነው ጭንቀትና መከራ ከውጪ ሰዎች፣ የምንኖርበት ቦታ፣ ጓደኞቻችን፣ በአካባቢያችን ያሉ ሰዎች ያመጡብን ነገር ይመስለናል፡፡ ይሄ አባባል ከኔ ጋር በጣም ይስማማል፡፡

ኤሚኔም የመጀመሪያውን አልበም ለቆ የጠበቀውን ተቀባይነት ሲያጣ ራሱን ለማጥፋት ሞክሯል፡፡ ከዚያ የታዋቂ ሰዎችን የህይወት ተሞክሮ የሚያቀርቡ እንደ የኢቢሲው "ወጣቶች" አይነት ፕሮግራሞች፣ ተስፋ አለመቁረጥ ዋናው አስፈላጊው ነገር ነው እያሉ፣ ወጣቶችን ለዝና ጥማትና እንደ ኤሚኔም ታዋቂ ካልሆንኩ ልሙት አይነት ሀሳብን ይቀርጻሉ፡፡

ለዚህ ነው ይህቺ አለም አሸናፊ የሌለባት የውድድር መድረክ ናት ያልኩት፡፡ ውድድሩን የሚያሸንፉት እናገኛለን ብለው የሚያስቡትን ሽልማት አያገኙም፡፡ ቢያገኙም ባያገኙም ደግሞ የዚህ አለም አሸናፊነት ሽልማት ውድቀት ነው፡፡ ይህቺን አለም የናቁና ከውድድሩ ራሳቸውን ያገለሉና የራሳቸውን ክብር ጥለው ለእግዚአብሔር ክብር የሚኖሩ፣ አለም ግን የሚንቃቸው ግን፣ እነሱ አሸናፊዎች ናቸው፡፡ በመጨረሻም ሽልማታቸውን ይቀበላሉ፡፡ ከፍ ከፍም ይላሉ፡፡
ማቴዎስ 23፡12፡- ራሱን ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ይዋረዳል፣ ራሱንም የሚያዋርድ ሁሉ ከፍ ይላል፡፡
መዝሙር 37፡39-40፡- የጻድቃን መድኃኒታቸው ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው፤ በመከራቸውም ጊዜ መጠጊያቸው እርሱ ነው፡፡ እግዚአብሔር ይረዳቸዋል፣ ያድናቸዋልም፣ ከኃጢአተኞችም እጅ ያወጣቸዋል፣ ያድናቸዋል፣ በእርሱ ታምነዋልና፡፡

በፊት ደስተኛ የነበርኩት ሰዎች ያከብሩኝ ስለነበረ አይደለም፡፡ የተሰበርኩትም ሰዎች ስለ ናቁኝ አይደለም፡፡ አስተሳሰቤ ነው የሰበረኝ፡፡

አንድ ቀን አንድ ሰው፣ እግዚአብሔር ለምን ባለ ጠጋ እንዳልሆን ይፈልጋል? ብሎ ጠየቀኝ፡፡ ምክንያቱም እሱ ሞት እስኪናፍቀን ድረስ ህይወታችንን እንድንጠላ አይፈልግም፡፡ እግዚአብሔር የሚፈልገው እንደ ተፈጥሮአችን እሱንም የሚያስደስት፣ ነፍሳችንም ሀሴት የምታደርግበት ህይወት እንድንኖር ነው፡፡ እኛ ለምንድነው ለማይጠቅመንና ከውሃ ውስጥ ወጥታ መኖር እንደምትፈልግ አሳ፣ ፍጹም በሚጎዳን በባለጠግነት ሀሳብ በጣም ታምነን የተጠመድነው? ምሳሌ 14፡12፡- ለሰው ቅን የምትመስል መንገድ አለች ፍጻሜዋ ግን የሞት መንገድ ነው፡፡

ሃያላን ናቸው የሚፈሩ፡፡ ገንዘብ አላቸው እንዲታፈሩ፡፡ ተዋኒ ናቸው እንዳይነኩ፡፡ አሳማኝ ናቸው እንዳይጠየቁ፡፡ ብልሆች ናቸው እንዳይታለሉ፡፡ ያስጎመጃሉ ከውጭ ሲታዩ፡፡ ከውስጥ ግን ጦር ሜዳ ናቸው፡፡ ከራሳቸው ጋር የሚዋጉ፣ የተሰባበሩ፡፡ ብዙ ማሳመን ቢችሉም፣ ብዙ ነገር ቢያውቁም ቅሉ፣ የብዙ ውዝግብ፣ የብዙ ግራ መጋባት ቅርጫትም ናቸው፣ የማያዋጣውን መንገድ የመረጡ፡፡ አወቅን ሲሉ የተሞኙ፡፡ ከእግዚአብሔር ጋራ የተጣሉ፡፡ በመረጡት ገንዘብ፣ ዓለማዊ ጥበብ የተወጉ፡፡

ይሄ አለምን ከመከተል የሚመጣ ስቃይና እውቀት የሰዎችን አንጻራዊነት እንድትረዳ ያደርግሃል፡፡ በገሃነማዊ የህይወትህ ክፍል ማንም ሊረዳህ እንዳልቻለ ትረዳለህ፡፡ አንዳንዶች የስቃይህ ምክንያት እነሱ እስኪመስሉህ ገሃነምህ ላይ የተጨመሩ እሳት ይሆኑብሃል፡፡ ከሁሉም በላይ፣ ኤርሚያስ 17፡9፡ "የሰው ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኮለኛ እጅግም ክፉ ነው፡፡ ማንስ ያውቀዋል?" ይላል፡፡ ከምንም በላይ አዕምሮህ የሰዎችን ክፋትና ተንኮል ቆዳቸውን ዘልቆ ማየት ይጀምራል፡፡ ቃሉ እንደ ህጻናት ሁኑ ሲልኮ ህጻናት ሰው ቢላዋ ይዞ ሊያርዳቸው ቢመጣ እንኳን መጫወቻ እንዳመጣላቸው ሁሉ ከመደሰት ሌላ፣ ክፋት ስለ ማያስቡና ያን ያህል የዋህነት ስላላቸው ነውኮ፡፡ ክፉ ሰው ግን ሰው ስጦታ ከጀርባው ደብቆ ሰርፕራይዝ ሊያደርገው ሲል ሽጉጥ ይመስለዋል፡፡ ይመስለዋል ብቻ ሳይሆን ሰዎች ሲያደቡበትም ከመጀመሪያው ከመሬት ተነስቶ ተጠራጣሪ፣ ሰውን የማመን ችግር ስላለበትና በጎ ነገር ስለ ማያስብ የሰዎችን ሸር በቀላሉ ይጠራጠራል፣ ይረዳል፡፡ እኔ መጀመሪያ የሰዎችን ተንኮል ከአይናቸው እንዲሁ ሳውቅና እንዳሰብኩት ሲሆን ደስ ይለኝ ነበር፡፡ የሰውን ጭንቅላት በሳይኮሎጂ ማንበብ የሚሉት አይነት ነገር ነው፡፡ ቃላትን አጠናለሁ፣ ሰው ድሮ ያለውን ካሁኑ ጋር እያገናኘሁ ትርጉም እፈልግለታለሁ፡፡ ከኔ ጋር ማውራት ከባድ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ

ግምቴ ትክክል የሆነ ቢሆንና አልፎ አልፎ ብቻ ስለ ሰዎች ክፋት የምሳሳት ቢሆንም ግን በተደረገልኝ ጥሩ ነገር ከመደሰት ይልቅ ባልተደረገብኝ፣ ሰው ባላቀደው ወይም ሳያስበው የሚሰራውን ክፋት እያሰላሰልኩ መዋሌና ንዴቴ እያሳሰበኝ መጣ፡፡ የሌለ ነገር ፈጣጥሬ ሳወራ ብዙ ሰው ኮምፕሌክሳም ነህ ብሎኛል፡፡ ስለ ሰው ክፋት የማላስብብበት፣ ዝም ብዬ ሰው ሁሉ ክፉ ቢሆን የማይገደኝና ዝም ብዬ ደስተኛ ሆኜ ብዙ ሳላስብ እኖርና የአድር የነበረበት ጊዜያት ናፈቀኝ፡፡ ሰው ሁሌም ክፉ ነው፡፡ በመጥፎ ጊዜ ጓደኛን ተስፋ ማድረግ አይቻልም ይሆናል፡፡ ስለ ጓደኞችህ ክፋት ማወቅና እንደማይወዱህ ማሰብና ለራሳቸው እንኳን በውል ያላሰቡትን ሴራቸውን ማወቅ ግን ጥቅም የለውም፡፡ ቢጎዳ እንጂ፡፡ ሰዎች ሁሌም ክፉ ናቸው፡፡ በጎ በጎውን ማሰብ አለመቻል ግን ፍቅረ ቢስነት ነው፡፡

የአዲስ ኪዳንና የብሉይ ኪዳን ልዩነት ይሄ ነው፡፡ በአዲስ ኪዳን አለምን ከደህ፣ ስጋህን ገለህ፣ ካመንክ፣ መንፈሱ ባንተ ውስጥ ይሰራል፡፡ ከሃጢአት ጋር ትግል የለም፡፡ ገንዘብንና እውቀትን ስትከተል ግን እምነትህ ዋጋ የለውም፡፡

ኢየሱስማ ክርስቶስማ
ወይ እኔን ወይ ገንዘብን
ምረጡ ነው ያለን
ከሁለት አንዱን ካልመረጥን
ዋጋ ያጣል እምነታችን፡፡

ምሳሌ 15፡11-15 "ሲኦልና ጥፋት በእግዚአብሔር ፊት የታወቁ ናቸው፡፡ ይልቁንም የሰዎች ልብ የታወቀ ነው፡፡ ፌዘኛ ሰው የሚዘልፈውን አይወድድም፡፡ ወደ ጠቢባንም አይሄድም፡፡ *ደስ ያለው ልብ ፊትን ያበራል፡፡ በልብ ኀዘን ግን ነፍስ ትሰበራለች፡፡* የአዋቂ ልብ እውቀትን ይፈልጋል፡፡ የሰነፎች አፍ ግን በስንፍና ይሰማራል፡፡ ልቡ የሚያዝን ሰው ዘመኑ ሁሉ የከፋች ናት፡፡ የልብ ደስታ ግን ሁል ጊዜ እንደ ግብዣ ነው፡፡"

17፡22 "ደስ ያላት ልብ መልካም መድሃኒት ናት፡፡ ያዘነች ነፍስ ግን እጥንትን ታደርቃለች፡፡

እውነት ነው፡፡ ደስተኛ ልብ ኖሮኝም አይቼዋለሁ፣ ነፍሴ አዝና አጥንቴ ደርቆም አውቀዋለሁ፡፡

18፡14 "የሰው ነፍስ ህመሙን ይታገሳል፡፡ የተቀጠቀጠን መንፈስ ግን ማን ያጠነክረዋል?" (The spirit of a man will sustain his infirmity; but a wounded spirit who can bear?)

19:29 "ለሚያፌዙ ሰዎች ፍርድ ተዘጋጅታለች፣ ለሰነፎችም ጀርባ በትር፡፡"

ከጠቢቡ ሰለሞን እስከ ፕሌቶ፣ ከማርቲን ሉተር፣ እስከ አዶልፍ ሂትለር፣ ከጆርጅ ዋሺንግተን እስከ አብርሃም ሊንከን፣ ከቤትሆቨን እስከ ሚካኤላንጄሎ፣ ከቻርለስ ዲከንስ እስከ ቻርለስ ዳርዊን፣ ከዊንስተን ቸርቺል እስከ አይዛክ ኒውተን አለም ላይ ትልልቅ ስራ የሰሩና ምሁር የምንላቸው ሰዎች፣ ነፍሳቸው መከራ ውስጥ ውላ የምታድር ሰዎች ናቸው፡፡

በዚህ ዘመን ብዙ ሰለሞኖች አሉን፡፡ ባለ ጠጎችና አዋቂዎች፡፡ ስንፍናን የተከተሉ፡፡ እናም ብዙዎች ለጀርባቸው በትርን እየተቀበሉ፣ መንፈሳቸው እየተቀጠቀጠ፣ ነፍሳቸው አዝና አጥንታቸው እየደረቀ፣ ነፍሳቸው ተሰብሯ፣ በነፍሳቸው ላይ የሸመቁ፣ የገዛ ነፍሳቸውን የነጠቁ፣ በህይወት ሳሉ ሲኦል ውስጥ እንደ ገቡ የሆኑ ብዙ ሰዎች አሉን፡፡ ይሄ ዘመን ዲፕሬሽን ይለዋል፡፡ የኦሉተር ዘመን እንግሊዘኛ ደግሞ 'melancholia' (ሜላንኮሊያ)፡፡ በአለምና ባደጉት ሀገራት ምን ያህል ሰዎች በዲፕሬሽን እንደሚያዙ ለማወቅ ጉግል አርጌ ያገኘሁት መልስ አላሳመነኝም፡፡ ውሸታሞች ናቸው፡፡ አንደኛ ነገር እንዲህ አይነት ነገር በቀላሉ ሊታወቅ አይችልም፡፡ ሁለተኛ ነገር ደግሞ ባደጉት ሀገራት ዲፕሬሽን እንደ ተንሰራፋ ግልጽ ነው፡፡ ሶስተኛ፣ መንግስታት ችግሩን ማጋለጥ አይፈልጉም፡፡ ችግሩን እንዳለና ትኩረት እንደሚያሻው ባመኑ ቁጥር ስለ መፍትሄው ደግሞ ማውራትና መወያየት ስለሚኖርባቸው፣ መፍትሄው ደግሞ የበለጠ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ከአለም ከንቱ ባለ ጠግነትና እውቀት ራስን መቆጠብ ስለ ሆነና ያ ደግሞ የነሱ አላማ፣ ሰውን በውሸት ማታለል ስለሆነ አድበስብሰው ሊያልፉት ይሞክራሉ፡፡ ሰይጣን ውሸታም፣ የውሸት አባት ነው፡፡

ሂላሪና ትራምፕ ሲከራከሩና ቅስቀሳ ሲያደርጉ፣ የሚናገሩት ሁሉም ነገር ሰው እንዲመርጣቸው ለቅስቀሳ ብቻ መሆኑ ይታወቃል፡፡ አንዳንዴ የሚያወሩት ነገር ሰው ለመቀስቀስ ብቻ እንጂ ከልባቸው እያሉት እንዳልሆነ በጣም ያስታውቃል፡፡ ሁሉም ነገር የታሰበበትና የታቀደበት ይሆንና ሁሉም ነገር እውነተኛ ስሜት ያጣል፡፡ ሳቃቸው፣ ሰው አጨባበጣቸው፣ የሆነ የውሸት መሆኑ ያስጠላል፡፡ አንድን ነገር፣ መልካምም ቢሆን በጣም አስበንበት ባደረግን ቁጥር ነገሩ ውሸት እየሆነ ይሄዳል፡፡ እንዲሁ ከልባችን መንጭቶ ሳይሆን በአዕምሮአችን ትርፍና ጉዳቱን አስልተን የምናረገው ነገር ውሸት ነው፡፡ ለምሳሌ ሰው ስለ እኔ መልካምነት እንዲያወራ፣ ደግ ነው ብሎ እንዲያስብ ፈልጌ ምጽዋት ብሰጥ፣ ወይም ሌላ ነገር ባደርግ ያ በእግዚአብሔር ዘንድ ነውር ነው፡፡

በአሜሪካ በ2014 ብቻ 42000 ሰዎች ራሳቸውን አጥፍተዋል ይላል፡፡ በየሶስት ደቂቃው አንድ አሜሪካዊ ራሱን ያጠፋል፡፡ ስንት ሰው ራሱን ለማጥፋት ሞክሮ እንዳልተሳካለት፣ ስንቱ ሀሳቡን እንዳለውና ግን እንደሚፈራ ስታስብ፣ ስንቱ በህይወቱ ደስተኛ እንደሆነ ስታስብ የእግዚአብሔር ቃል እውነትና ህያው እንደሆነ ይገባሃል፡፡ የሰው ህግ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው፡፡ እግዚአብሔርም ለቃሉ ታማኝ ነው፡፡

የሰይጣን ህግ ደግሞ ሰውን ከእግአብሔር ፈቃድ ማጉደል ነው፡፡ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሚኖሩት ግን ጸጋው ከነሱ ጋር ይሆናል ሁሉንም ያስችላቸዋል፡፡ ማቴ 19፡26፡፡

ለጭንቀቴ ራሴን በጥበብ ፍቅር ውስጥ መከተቴን ምክንያት አድርጌ አቀርባለሁ፡፡ ከትምህርቴ ውጪ ወደ 80 የሚጠጉ መጽሐፍትን አንብቤአለሁ፡፡ የሚቀርቡኝ ሰዎች አንተ ያነበብካቸውን መጽሐፍት ባነብ እንዳንተ አልሆንም ይሉኛል፡፡ አንዳንዶቹ ያንተን ያህል አልጨነቅም ይሉኛል፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ ያንተን ያህል አልመራመርም ይሉኛል፡፡ እውነት ነው ያነበብኩትን ወይም ያወቅኩትን ነገር በጥልቀት የመመርመር ጸባይ አለኝ፡፡ ጓደኛዬ አቡሽ ተመራማሪነትህ ተፈጥሮ ነው እንጂ ማንበብህ አይደለም ይለኛል፡፡ ይሄ ነገር እኔም ራሴን ስጠይቅ የነበረ ሲሆን ልቀበለው አልፈልግም ነበር፡፡ እውነት ሊሆን ይችላል፡፡ የማንበብ የማንበብ ብዙ መቶ መጽሐፍት አንብበው ብዙም የእውቀት ብዛት የማያሳዩ ሰዎች ይኖራሉ፡፡ በዚያ ላይ ከቤት የሚሉኝ ነገር አለ፡፡ እኔም የማስበው፡፡ በልጅነቴም ብዙ የማሰላስል፣ ነገሮችን ቀለል አድርጌ እንደሌላ ልጆች የማልኖር ልጅ ነበርኩኝ፡፡ በዚያ ላይ፣ ከሞሉ እኩዮቼ፣ እኔን ብቻ ምን አንባቢ ተመራማሪ አደረገኝ? ንባብ አብረን የጀመርነው ጓደኛዬ አሊ ራሱኮ ደህና ነው፣ አብሮኝ ጀመረ፣ ተመችቶት ነበር ግን እሱ አቆመ፣ እኔ ለምን በጥልቀት ቀጠልኩበት? ጥበብን አፍቃሪ ሆኜ ተወልጄ ሊሆን አይችልም? ብዙ አላነበብኩም ግን ከሚገባኝ በላይ አንብቤአለሁ፡፡
አንድ ቀን፣ ያኔ 10 አመት ቢሆነኝ ነው፣ ጎረቤት፣ እነ ኦዳ ቤት አቡካዶ ይሸጡ ነበርና ሄጄ የሳሎናቸውን በር አንኳኳሁኝ፡፡ ኦዳ ከፈተልኝ፡፡ “አቡካዶ አለ ወይ?” አልኩት፡፡ አለ አለኝ፡፡ በብር ስንት ነው አልኩት፡፡ ሁለት አለኝ፡፡ አትመርቅልኝም? አልኩት፡፡ እመርቅልሃለሁ አለኝ፡፡ በቃ ምርቃቷን ብቻ ስጠኝ አልኩት፡፡ አባረረኝ ይባላል፡፡ ይሄን ይሄን ሳስብ ይሄን ነገር ተወልጄበት እንደሆነ እንድጠረጥር እገፋፋለሁ፡፡
የኔስ ይሁን፡፡ ዛሬ ዛሬ ላይ ማንም ምንም ሳይላቸው፣ ማንበብ ይቅርና ማንበብ ጥሩ ነው ሳይባሉ የሶስት አመት ህጻናት የአዋቂ ሰው ንግግር ይናገሩና ሰውን ያስገርማሉ፡፡ አንድ ድራማ ላይ ያለች አዋቂዎቹን ተዋንያን የምታስንቀው ህጻን ተዋናይ፣ ሆሊውድ ፊልሞች ላይ የሚታዩት ህጻናት፣ የሚያስደምሙ፣ ትልቅ ሰዎችን የሚያስገርሙ ነገሮችን የሚሰሩ ህጻናት ስለተማሩት አይደለም፡፡ ህጻን ተዋናዮቹ ስላነበቡ ወይም እንዴት ማስመሰል እንደሚችሉ ስላጠኑ አይደለም በትክክል አፍ ያልፈቱ ህጻናት ሰውን አፍ የሚያስከፍቱት፡፡ ተፈጥሮ ነው፡፡ በጣም የሚሰራ ጭንቅላት ይዘው ይወለዳሉ፡፡

ድራማው ላይ ያለችውን ህጻን ለአባቴ “ትላልቆቹን ተዋናዮች ታስንቃለች” ብዬ ስነግረው “የስምንተኛው ሺ(የመጨረሻው ዘመን) ምልክት ነው” አለኝ፡፡ እንዴት? ስለው “አንድ ፍካሬ ኢየሱስ የሚል መጽሐፍ ላይ በመጨረሻው ዘመን የሚናገሩ ውሾች ይወለዳሉ ይላል” አለኝ፡፡ ትንቢቱ ፊልም ላይ እንደሚታየው አይነት፣ ውሾች የሚያወሩ መስሎኝ እየተገረምኩኝ “ከዚህ ጋር ምን አገናኘው ታዲያ?” አልኩት፡፡ “ውሾቹ ውሻ ሳይሆኑ ህጻናት ናቸው ይላሉ፣ በልጅነታቸው እንደ ትልቅ ሰው የሚያስቡ ህጻናት ማለት ነው” አለኝ፡፡ ያው መጽሐፍ፣ በመጨረሻው ዘመን ሴችና ሕጻናት ፈራጅ ይሆናሉ እንደሚልም አባቴ ነግሮኛል፡፡ ሕጻናት ፈራጆች ይሆናሉ ማለት፣ ፍርድ ቤት ውስጥ ተቀምጠው ፍርድ ይሰጣሉ ማለት አይደለም፡፡ ይልቅ ሕጻናት፣ ወላጆቻቸው ላይ ይሰለጥናሉ ማለት ነው፡፡
ስማርት ሆኖ መወለድ፣ ከማህበረሰቡ የልብ ትርታ የመነጨ ይመስለኛል፡፡ ገሃነምና መንግስተ ሰማያት አሉ፡፡ ወደ ሰራህለት ትሄዳለህ፡፡ የጸሎትህን ታገኛለህ፡፡ የምትጸልየውን ነገር የማወቅ ፋንታ ያንተ ነው፡፡ የሚያኖርህን ነገር ከፈለግክ ታገኘዋለህ፣ የሚያጠፋህን ነገር ከለመንክ ታገኘዋለህ፡፡ እንደ ሃሰተኛ ነቢያት ነው፡፡ የማህበረሰቡ ፍላጎት የሚፈጥራቸው አጭበርባሪ መናፍስት ናቸው፡፡ የሰዎች ምኞት የሚፈጥራቸው ሰዎች ናቸው፡፡ ሰው መስማት የሚፈልገውን ነገር ይነግሩታል፡፡ ስለ ገንዘብ፣ ስለ እውቀት…ሰው እግዚአብሔር ሰጠኝ ብሎ ያመሰግናል፡፡ ሲጠፋ ታዲያ ጣቱን ወደ እግዚአብሔር እንዳይቀስር፡፡ የእግዚአብሔርና እውነተኛ ቃል ትቶ የሠው ምኞት የፈጠራቸውን፣ ለስጋው በሚመች መንገድ ከእግዚአብሔር በተቃራኒ እግዚአብሔር እንዲህ አለ፣ የሚሉትን ሰዎች ያደመጠው ለራሱ ነውና፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌላት መጽሐፍት ውስጥ ብዙ ነገሮችን በምሳሌ እንደ ተናገረ ተጽፎአል፡፡ ከነዚህም በማቴዎስ 13 ላይ የተጠቀሰው የዘሮቹ ታሪክ አንዱ ነው፡፡
ክርስቶስ ይሄን ምሳሌ ለደቀ መዛሙርቱ ሲናገር በ9-15 “የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ፡፡ ደቀ መዛሙርቱም ቀርበው፡- ስለ ምን በምሳሌ ትነግራቸዋለህ? አሉት፡፡ እርሱም መልሶ እንዲህ አላቸው፡- ለእናንተ የመንግሥተ ሰማያትን ምስጢር ማወቅ ተሰጥቶአችኋል፣ ለእነርሱ ግን አልተሰጣቸውም፡፡ ላለው ይሰጠዋልና ይበዛለትማል፡፡ ከሌለው ግን ያለው እንኳ ይወሰድበታል፡፡ ስለዚህ እያዩ ስለማያዩ እየሰሙም ስለማያስተውሉ በምሳሌ እነግራቸዋለሁ፡፡ መስማትማ ትሰማላችሁና አታስተውሉም፣ ማየትማ ታያላችሁና አትመለከቱም፡፡ በዓይናቸው እንዳያዩ፣ በጆሮአቸውም እንዳይሰሙ፣ በልባቸውም እንዳያስተውሉ፣ ተመልሰውም እንዳልፈውሳቸው የዚህ ህዝብ ልብ ደንድኖአልና ጆሮአቸውም ደንቁሮአል ዓይናቸውንም ጨፍነዋል የሚል የኢሳይያስ ትንቢት በነሱ ይፈጸማል፡፡

እግዚአብሔር ይሄን ምሳሌ ብዙ ሰዎች እንደ ማያስተውሉት ይነግረናል፡፡

ይሄ ምሳሌ፣ ስለ አማኞች ነው፡፡ ስለ አማኞች አይነት፡፡

1. “የመንግስትን ቃል ሰምቶ በማያስተውል ሁሉ፣ ክፉው ይመጣል፣ በልቡ የተዘራውንም ይነጥቃል፡፡ በመንገድ ዳር የተዘራው ይህ ነው፡፡”

በመንገድ ዳር የሚወድቀውና ወፎች የሚወስዱት ፍሬ(አማኝ)፣ በብዛት የዚህን ትውልድ ኣማኝ ይወክላል፡፡ ከጨቅላነቱ ጀምሮ በአለማዊ እውቀትና ጥበብ ያበደ፣ ከጨቅላነቱ ጀምሮ በጣም አስጸያፊ ግድያ፣ ዝሙት፣ ፌዝ፣ ሁሉም የስጋዊነት ፈሬዎች የሚተዋቁባቸውንና ተንኮልና ክፋት መልካም ተደርገው የሚቀርቡባቸውን ፊልሞች እየጠጣ፣ የሚያድገውና የሚኖረው አማኝ ነው፡፡ በከንቱ ፖለቲካ፣ የዝነኝነት ጥማት፣ በአፍቅሮተ ንዋይ የታወረ አማኝ ነው፡፡ ሉቃስ 6፡43፡- “ክፉ ፍሬ የሚያደረግ መልካም ዛፍ የለምና፣ እንዲሁም መልካም ፍሬ የሚያደርግ ክፉ ዛፍ የለም፡፡”

ዕብራውያን 6፡4-8፡- “አንድ ጊዜ ብርሃን የበራላቸውን፣ ሰማያዊውንም ስጦታ የቀመሱትን ከመንፈስ ቅዱስም ተካፋዮች ሆነው የነበሩትን መልካሙንም የእግዚአብሔርን ቃልና ሊመጣ ያለውን የዓለም ኃይል የቀመሱትን፣ በኋላም የካዱትን እንደገና ለንስሐ እነርሱን ማደስ የማይቻል ነው፡፡ ለራሳቸው የእግዚአብሔርን ልጅ ይሰቅሉታልና ያዋርዱትማልና፡፡ ብዙ ጊዜ በእርሷ ላይ የሚወርደውን ዝናብ የምትጠጣ መሬት፣ ለሚወርሲአትም ደግሞ የምትጠቅምን አትክልት የምታበቅል፣ ከእግዚአብሔር በረከትን ታገኛለችና፡፡ እሾህና ኩርንችትን ግን ብታወጣ፣ የተጣለች ናት ለመርገምም ትቀርባለች፣ መጨረሻዋም መቃጠል ነው፡፡”

2. “በጭንጫ ላይ የተዘራውም ይህ ቃሉን ሰምቶ ወዲያው በደስታ የሚቀበለው ነው፡፡ ነገር ግን ለጊዜው ነው እንጂ በእርሱ ሥር የለውም፣ በቃሉ ምክንያትም መከራ ወይም ስደት በሆነ ጊዜ ወዲያው ይሰናከላል፡፡”

   እነኚህ ደግሞ ቃሉን በልባቸው ሳይሆን በምላሳቸው የሚቀበሉት ናቸው፡፡ እነኚህ፣ ሐሰተኞች መምህራን ማመን ሚሊዬነር ያደርጋል ሲሏቸው ገንዘብ ፍለጋ የሚቀበሉት ናቸው፡፡ እነኚህ እምነትን ቢዝነስ ያደረጉት ናቸው፡፡ እውነቱ ገብቶአቸው ሳይሆን ምኞት ጠርቶአቸው ስለ ሆነ የመጡት፣ መከራ ወይም ስደት፣ ለነኚህ ከውላቸው ውጪ ነው፡፡

3. “በእሾህ መካከል የተዘራውም ይህ ቃሉን የሚሰማ ነው፣ የዚህም ዓለም አሳብና የባለጠግነት መታለል ቃሉን ያንቃል፣ የማያፈራም ይሆናል፡፡”

   አብዛኞቹን የሀገራችን አማኞች፣ ይሄ ፍሬ ይወክላል፡፡ ቃሉን የሚሰማ ነው፡፡ ነገር ግን የባለጠግነትና የብልጭልጭ ትምህርት ያታልለዋል፡፡ ቃሉንም ያንቃል፡፡ ፍሬ የማያፈራም ይሆናል፡፡

4. “በመልካም መሬት ላይ የተዘራውም ይህ ቃሉን ሰምቶ የሚያስተውል ነው፡፡ እርሱም ፍሬ ያፈራል፡፡ አንዱም መቶ አንዱም ስድሳ አንዱም ሠላሳ ያደርጋል፡፡”
   እነኚህ ደግሞ ክርስቶስ ወደ አባቱ ሲመለስ የላከለልን መንፈስ የሚመራቸውና የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ የሚጠብቁ መንፈሳውያን ናቸው፡፡

ቴክኖሎጂ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው ብለው የሚያምኑ ሰዎች አሉ፡፡ ቴክኖሎጂ የእግዚአብሔር ስጦታ ቢሆን ቴክኖሎጂ የተባለ ነገር ላይ ሁሉ ስድስት ስድሳ ስድስትን ጨምሮ የሰይጣን ምልክቶች እነኚህ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ላይ ባይታተም ነበር፡፡ ሰዎች እንደ ቲቪ፣ ኢንተርኔት ያሉ ቴክኖሎጂዎች ትውልዱን መቀመቅ እየከተቱ መሆኑን ትተው፣ የእግዚአሔርን ወንጌል በቀላሉ ለማዳረስ ይጠቅማል ይላሉ፡፡ ከሪፎርሜሽንና ከዳርዊን የሰውና የአለም አፈጣጠር ቲዮሪ ቀጥሎ በክርስትና ላይ ትልቁን ጥላ ያጠላል ተብሎ የሚገመተው የማይክሮቺፕ(በስጋ ውስጥ የሚቀበርና እንደ ሚሞሪ አይነት አርቲፊሻል እውቀትን የሚሰጥና ለሌላም ነገር የሚውል) ቴክኖሎጂ ሲመጣም እግዚአብሔርን የበለጠ ለማወቅ ይረዳል እንል ይሆናል፡፡

አንድ የኦርቶዶክስ ቄስ በቲቪ ኢንተርኔት እንደ ፋርማሲ ነው ሲሉ ሰማሁ፡፡ እንደ ፋርማሲ ነው ሁሉም አይጠቅምህም፣ የሚጠቅምህን መርጠህ ትጠቀማለህ እንጂ ሁሉንም ልጠቀም ካልክ ልትጎዳም ትችላለህ፡፡ ጥላሁን ጉግሳም እንደ አጠቃቀማችን ነው ነበር ያለው፡፡ ገንዘብም እንዳጠቃቀማችን ነው፡፡ እውቀትም እንደ አጠቃቀማችን ነው፡፡ ችግሩ እኛ በአለም ላይ መጨከን ስላልፈለግን እንጂ ክርስቶስ እንዳጠቃቀማችሁ ነው አላለንም፡፡ እግዚአብሔር ያለው፡ “ለዓለም ስለ ማሰናከያ፣ ማሰናከያ ሳይመጣ አይቀርምና፣ ነገር ግን በእርሱ ጠንቅ ማሰናከያ ለሚመጣበት ለዚያ ሰው ወዮለት፡፡ እጅህ ወይም እግርህ ብታሰናክልህ፣ ቆርጠህ ከአንተ ጣላት፡፡ ሁለት እጅ ወይም ሁለት እግር ኖሮህ ወደ ዘለአለም እሳት ከምትጣል አንካሳ ወይም ጉንድሽ ሆነህ ወደ ህይወት መግባት ይሻልሃል፡፡…” (ማቴ. 18፡7-9)
አውቀው ለመንጋው፣ ቴክኖሎጂ፣ ዴሞክራሲ፣ አርት፣ ትምህርት፣ ገንዘብ… እያሉት ከስክሪኑ በስተጀርባ ማሰናከያ የሚያዘጋጁ፣ ከሰይጣን ጋር ያበሩና የተባበሩት ሰዎች ወዮላቸው(woe unto them) ይላል ቃሉ፡፡ ክርስቶስ እጅህ ወይም እግርህ ብታሰናክልህ አውጥተህ ጣላት ሲል ጥፋትን የሚያስበው፣ ወይም የሚሰናከለው አዕምሮ እንጂ ያለ አዕምሮ ምንም የሆኑት እጅና አይን እንዳልሆኑ አጥቶት አይደለም፡፡ በእጃችን ወይም በአይናችን ብንሰናከልም፣ ንስሃ ከመግባት ይልቅ አይናችንን ጎልጉሎ ማውጣት መፍትሄ ነው ብሎም አይደለም፡፡ ምሳሌ ነው፡፡ ከራሳችን ይልቅ እግዚአብሔር ምን ያህል ደካማ ፍጥረታት እንደ ሆንን ያውቀዋል፡፡ እግዚአብሔር ሃጢአትን ለማድረግ ምክንያት ሊሆን ከሚችል ወይም ከሚያሰናክል ከየትኛውም አይነት ነገር እንድንርቅ፣ ተጣብቆን ካለ እንድንላቀቀው፣ ሱስ ሆኖብን ካለ እንድናቆመው፣ የሰውነታችን ብልት ሆኖ ቢሆን እንኳን ቆርጠን እንድንጥለው ነው በምሳሌ የሚመክረን፡፡ ክርስቶስ እጅ ወይም ዓይን ምን ያህል እንደሚጠቅሙ አጥቶት አይደለም፡፡ በሚጠቅም ነገር ተሰናክሎ ከመንግስቱ ከመጉደል፣ እጅ ወይም አይንን ቆርጦ ጥሎ መንግስቱን መውረስ ይሻላል፡፡ በገንዘብ ድሆችን መርዳትን ጨምሮ ብዙ ጠቃሚ ነገሮች ሊደረጉ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ገንዘብ አከማችቶ ከመንግስቱ ከመጉደልና ወደ ዘላለማዊ እሳት ከመጣል፣ ገንዘቡ ቢቀር ይሻላል፡፡ “በምድር መዝገብን አትሰብስቡ፣ ብልና ትልም በማያጠፉት፣ሌቦችም ቆፍረው በማይሰርቁት በሰማይ ሰብስቡ፣ መዝገብህ ባለበት ልብህ በዚያ ይሆናልና” (ማቴ. 6፡20) የሚለው ቃል የክርስቶስ ምክር ብቻ ሳይሆን እንደ ፈቃዱ ሊኖሩ ለሚሹት ትዕዛዝም እንደ ሆነ ማቴዎስ 6ን ሙሉውን ስናነነብ ይገባናል፡፡ እውቀትም፣ ስልክም ኢንተርኔትም ጥቅም ይኖራቸዋል፣ ግን ያሰናክላሉ፡፡ በሚጠቅም ነገር ተሰናክሎ ከመንግስቱ ከመጉደል ደግሞ፣ የሚጠቅምን ነገር አጥቶ መንግስቱን መውረስ ይሻላል፡፡

ምን ያህል ጓኞች ነው ያለህ? ከሰፈርህ ሰዎች ጋር ያለህ ግንኙነት እንዴት ነው? ቡና ትጠራራላችሁ? የጎረቤቶችህ ቤት ትሄዳለህ? ሠርግ ቤት መሄድ ያስደስትሃል? ስለ ለቅሶ ቤት ምን ታስባለህ? ቤት ውስጥ ብቻህን መቀመጥ ያስደስትሃል? ከጓኞችህ ጋር ወጥተህ መጫወት ያስደስትሃል ወይስ ፊልም እያየህ መዋልን ትመርጣለህ?

ፍቅር፣ ዘመኑ ዝሙትን ፍቅር ብሎ ከሚገልጽልን የተለየ ትርጉም አለው፡፡ ይሄ ፍቅር ቀኑን ሙሉ ሙቶ ጊዜ አይ ላቭ ዩ ሲባባሉ ውለው በነጋታው ተሰዳድበው፣ ተጫጨኸው የሚለያዩበት አይነት የውሸት ፍቅር አይደለም፡፡ ፍቅር ለሰዎች ያለን አመለካከት መመዘኛ ነው፡፡ እግዚአብሔር ፍቅር የሚለው ፍቅር፣ በዚህ ዘመን መተሳሰብ የምንለው አይነት ሲሆን መተሳሰብም በትክክል አይገልጸውም፡፡ ፍቅርን ከጊዜ አንጻር ስናየው(ማቴ. 24፡12) እየቀነሰ፣ እየቀነሰ፣ ሰዎች የብቸኝነት ህይወትን እየመረጡ፣ ሰዎችን ከህይታቸው እያስወጡ ያሉበት ጊዜ ላይ ነን፡፡ እኔ በኖርኩባቸው አጭር አመታት በህይወቴ ውስጥ ይሄን ታዝቤአለሁ፡፡ ሰዎች ያላቸው መተሳሰብና ፍቅር፣ ወደ ምቀኝነት እየተቀየረ ነው፡፡ እኔ በጊዜያት መካከል፣ ለሰዎች ያለኝ አመለካከት እየተበላሸ፣ እየተበላሸ፣ እንደዚያው ከሰው ጋር ያለኝ ቅርበትም እየቀነሰ እየቀሰ ብቸኛ እስከ መሆን ደርሻለሁ፡፡ ከሰዎች ጋር የነበረህን ህይወት ወደ ኋላ ተመልሰህ አስብ፡፡ ወላጆችህን ጠይቃቸው፡፡ እየተሻሻለ ነው ወይስ እየቀነሰና እየተበላሸ ነው የመጣው? ከቦታ አንጻር ስናየው ደግሞ፣ በፈረንጆች ጋር ካለው ፍቅር(መተሳሰብ) ይልቅ ኢትዮጵያ ውስጥ ፍቅር አለ፡፡ ሰዎች በደስታና በሃዘን ይደጋገፋሉ፣ ሰፈርተኞች በጣም ይቀራረባሉ፡፡ አዲሳባ ከቦታ ቦታ ሊለያይ ቢችልም አዲሳባ ላይ ካለው ፍቅር ይልቅ እኔ ተወልጄ ባደግኩበት መቱ የበለጠ ፍቅር አለ፡፡ ከመቱ ይልቅ ደግሞ ከመቱ በሚያንሱ ከተሞችና ገጠሮች ፍቅር አለ፡፡ ማህበራዊ ትስስር ማለት ነው፡፡

እኔ መቱ ውስጥ እድሜ ልኬን ኖሬ ሰዎችን ካወቅኩት በላይ፣ የወረዳ ልጆች መቱ መጥተው በአመት ከተማዋን ሲወርሱና መኖሪያ ቤታቸው ሲያደርጉም ታዝቤአለሁ፡፡ ይሄ ነገር በጣም ይገርመኝ ነበር፡፡ ግን እነሱ እንደዚያ የሆኑት ከመጡበት ቦታ ይዘው የመጡት ሰፊ ልብና ብዙ ፍቅር ስላላቸው ነው፡፡ እነሱ የመጡት ሰዎች በጣም ከሚቀራረቡበት ቦታ ስለሆነ ነው፣ ፍቅር የሚያንስበትን ቦታ በቀላሉ የሚያሸንፉት፡፡ በጣም እየገጠረ በሄደ ቁጥር የበለጠ የሰዎች ፍቅር ሰውን እያስደመመ ይሄዳል፡፡
ታዲያ የዚህ ምክንያቱ ምንድነው? ሰዎች እየዘመኑና እየከተሙ ሲመጡ ለምን ይፈራራሉ? ይራራቃሉ? ፈረንጆች ለምን ከጎረቤታቸው ጋር አይቀራረቡም? በገጠር፣ በከተማ ያለው ቴክኖሎጂ በብዛት የለም፡፡ ሰዎች ይቀራረባሉ፡፡ በከተማ ግን ለመዝናናትም ይሁን ለመሳቅ ሰዎች የማያስፈልጉባቸው ብዙ ቴክኖሎጂዎች አሉ፡፡ ቲቪውን ስትቀያይር ጊዜው ይከንፋል፡፡ ጌም እየተጫወትክ እንቅልፍ ይዞህ ይሄዳል፡፡ ፌስቡክ ካለ ሰው ለምንህ? በከተማና በገጠር መሃል ያለው አንድ ልዩነት አንዱ ቴክኖሎጂ የመጠቀም ባህል ነው፡፡ ከህጻንነቱ ጀምሮ ኤሌክትሮኒክስ ጭንቅላቱ ውስጥ ሲንጫጫና ሲፈራረቅ የሚያድግ ሰው ከማህበረሰቡ ጋር የመቀላቀል ችግር የህይወቱ አካል ይሆናል፡፡ ከሰው ጋር መሆን ይረብሸዋል፡፡ በገጠሩ ግን ያን ያህል ሰዎች አይራራቁም፣ ሰዎች ይቀራረባሉ፣ ደስተኞች ናቸው፡፡ ቴክኖሎጂ የመጀመሪያ ግቡ፣ ፍቅርን ከሰዎች ልብ ውስጥ መምጠጥ ነው፡፡ ፍቅር የሌለው ሰው ደግሞ እንደ ስሜቱ፣ በቁሙ የሞተ ነው፡፡ ዮሐ. 13፡34፣ 1 ቆሮ. 16፡14፣ 1ዮሐ. 4፡21፣ 1ጴጥ. 4፡8፣ 1 ቆሮ. 13፡13፣ ኤፌ. 4፡2፣ ሮሜ. 12፡10፣ ሮሜ 13፡8፡- “እርስ በርሳችሁ ከመዋደድ በቀር ለማንም እዳ አይኑርባችሁ፣ ሌላውን የሚወድ ሕግን ፈጽሞታልና፡፡”

ታላቅ ወንድሜ በህጻንነቱ ነው አሉ፡ እናቴ ሽሮ ወጥ ሰርታ ትሰጠዋለች፡፡ አልበላም ብሎ ያለቅሳል፡፡ ከዚያ እናቴ እሱን ራሱን ወጥ፣ ፈትፍታ ጎረቤት ታደርስና የጎረቤታችን ሴትዮ “አቡቲ ናና ምንቸታብሽ(የተፈጨ ስጋ፣ ወጥ) ብላ” ትለዋለች፡፡ ከዚያ ሄዶ ግጥም አድርጎ ከአተር የተሰራ ምንቸታብሹን ይበላና እናቴ “ዛሬ ምሳህን ምንድነው የበላኸው?” ስትለው “ምንቸታብሽ” ይላታል፡፡

የእግዚአብሔር ቃል እንደ ህጻናት እንድንሆን ያዘናል፡፡(ማቴ. 18፡20)፡፡ ያም ማለት፣ ከጥርጣሬ ነጻ መሆን፣ እንደ ህጻን ሞኝ መሆን ማለት ነው፡፡ “እውነት እላችኋለሁ፡፡ የእግዚአብሔርን መንግስት እንደ ሕጻን የማይቀበላት ሁሉ ከቶ አይገባባትም”(ማር. 10፡15) ሲል እንደ ህጻን ማለትኮ የእግዚአብሔርን መንግስት ሳይጠራጠር እንደ ህጻን የማይቀበላት ማለት ነው፡፡ የእግዚአብሔርን መንግስት እንደ ህጻን እንዳንቀበል ከሚያደርጉን ነገሮች ዋነኛው፣ ትምህርት ነው፡፡ ሰው ከዝንጀሮ ነው የመጣው፣ አለም ቢግ ባንግ ቲዮሪ፣ 3፥6 ቢሊየን አመት ሲሉ፣ የእግዚአብሔርን ህልውና መጠራጠር ያስጀምሩናል፡፡ በፊት በፊት እውቀት ከመብዛቱ በፊት እንኳን የእግዚአብሔርን ህልውና ጥያቄ ውስጥ ለመክተት የተፈበረከ ተረት፣ ለመጀመሪያ ጊዜ መሬት ነች በሰማይ ዙሪያ ምትሽከረከረው ያለውን ሰውዬ እግዚአብሔርን ተሳደበ ብለው ገድለውታል፡፡ ሰው የእግዚአብሔርን ህልውና መጠራጠር ወይም እንደ ህጻን መቀበል ማቆም የጀመረው ግን በቻርለስ ዳርዊን ስለ ዝንጀሮ ሲሰማ በ19ኛው ክ.ዘ. አይደለም፡፡ መጀመሪያ ህዝቡን በእውቀትና በፍልስፍና፣ በምርምር፣ በምክንያታዊነትና በአመንክዮ ሞሉት፡፡ ሁሉን መመርመር ሲጀምሩ ብዙ ነገር እያወቁ መጡ፡፡ ሁሉንም ነገር ይጠይቃሉ፣ መልስ ይሻሉ፡፡ የመማር ትርጉም ይሄ አይደል? ስለ እግዚአብሔርም ይጠይቃሉ፡፡ የተማሩትን እውነት እውነትነት ይጠራጠራሉ፡፡ እግዚአብሔር ሰማይ ላይ ነው ይባላል፡፡ ይሄ ሰማይ ዝም ብሎ ባዶ ቦታ ቢሆንስ ማለት ይጀምራሉ፣ በጥያቄዎች የተጠመዱት የዚህች አለም ጠቢባን፡፡ ስለ እግዚአብሔር ነገር ሊያሳምናቸው፣ የሚችል ሰባኪ አይኖርም፡፡ እንዴት አወቅክ ብለው ጥያቄያቸውን በጥያቄ ሊቋጩ ይችላሉ፡፡ ተጠራጣሪ፣ የተጨባጭ መልስ ፈላጊ የሆነው ህዝብ፣ አንድ አዋቂ ነው የሚለው ሳይንቲስት፣ ይሄን ተጠራጣሪ ህዝብ ያሳምናል፣ ይቀበለዋል የሚለውን ማሳመኛ ሀሳቦች ዘርዝሮ ከሰማይና ከምድር እንዲሁም ከሰው አፈጣጠር ጋር ለሚያነሳቸው እንደ ህጻን መቀበል ያለመቻል ጥያቄዎች መልስ ይዞ ብቅ አለ፡፡ በፊት መጽሐፍ ቅዱስ የአንድ መንግስት ህገ መንግስት ሆኖ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ፍልስፍና ሃይማኖት ውስጥ ገባ፡፡ ፈላስፎች በእግዚአብሔር ቃል ላይ መፈላሰፍ ጀመሩ፡፡(ሮሜ 12፡2)፡፡ በፍልስፍና የተጠቁ የሃይማኖት ትምህርት ቤቶች ተከፈቱ፡፡ ከጊዜ በኋላ ፍልስፍና ትምህርት ቤቶቹን ወረሰ፡፡ ፍልስፍና ከሃይማኖት ይልቅ አስፈላጊ ሆነ፡፡ ከጊዜ በኋላ ሴኪዩላሪዝም መንግስትንና ሃይማኖትን፣ ትምህርት ቤቶችንና ሃይማኖትን መለያየት ጀመረ፡፡ ከዚያ ዳርዊን መጣና ሰውን ዝንጀሮ ነህ አለው፡፡ ከጊዜ በኋላ እግዚአብሔር የለም የሚሉ እንደ ሶሻሊዝም አይነት የመንግስት ስርአቶች መጡ፡፡ ተማሪዎች ዝንጀሮ እንደሆኑ ይሰበኩ ጀመር፡፡ ይሄም እግዚአብሔር የለም ማለት ነው፡፡ ሰው በአለም ለሚኖርበት ዘመን፣ ለ80 አመት የሚያቅድበት ጊዜ መጣ፡፡ ከሰማንያ በኋላ ምንም የለማ፡፡ አሁን ደግሞ በዚህ ጊዜ ሰዎች እግዚአብሔር የለም አይሉም፡፡ ነገር ግን በእግዚአብሔር አያምኑም፡፡ አሁን ሰዎች ፊታቸውን ወደ ጨለማው ገዢ እያዘነበሉ ነው፡፡ የክርስትያኖች ብዛት ከአመት ወደ አመት እየቀነሰ ሲመጣ የሌሎች ሃይማኖቶች ደግሞ በእጥፍ እየጨመረ ይገኛል፡፡ ጊዜው እየከፋ ነው የመጣው፡፡ ከመልካሙ ጫፍ፣ ወደ ወደ ከፉው ጨፍ የሚደረገው የዘመናት ጉዞ ሞተር ደግሞ ገንዘብ(ምኞት) ነው፡፡

የሰው ክፋት ብዙ እያወቀ እያወቀ፣ ሲሄድ ነው እየጨመረ የሚሄደው፡፡
1 ቆሮንቶስ 1፡18 “የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት፣ ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነውና፡፡” ይላል፡፡ ሁሉም መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ታሪኮች፣ በታሪክነት ደረጃም ሆነ በአስተማሪነት ደረጃ፣ እንደ ህጻን ካልሆነ ለመቀበልና ለማመን የሚያዳግቱ ናቸው፡፡ የሁሉ ነገር አፈጣጠር፣ የአዳምና የሔዋን ታሪክ፣ የአቤልና የቃየነ ታሪክ፣ የአብረሃምና የሳራ ታሪክ፣ የያዕቆብና የዔሳው ታሪክ፣ የዮሴፍ፣ የሙሴ፣ የዳዊት፣ የሰለሞን፣ የዳንኤል፣ የዮናስ፣ የአዳኛችን የኢየሱስ ክርስቶስ፣ የይሁዳ፣ የጳውሎስ… የሁሉም፡፡   እንደ ህጻን ለሚቀበሉት ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነው፡፡ እንደ ህጻን መቀበል ሲባል እንደ ህጻን መሆን፣ እንደ ህጻን ልሁን ስላልን ወይም በጸሎት የምናገኘው ነገር ሳይሆን ከምድራዊ ጥበብና እውቀት እራሳችንን በመጠበቅ ነው፡፡ መጀመሪያ፣ ጸሎት በእምነት እንጂ እምነት በጸሎት አይደለም፡፡ ጥርጣሬ ደግሞ እምነትን ያጠፋል፡፡ ሳናምን የምንጸልየውን ጸሎት ደግሞ እግዚአብሔር አይሰማልንም፡፡ ስለዚህ እውቀት እምነታችንን አጠፋው ማለት ነው፡፡

እውቀት የእግዚአብሔርን መንግስት እንደ ህጻናት እንዳንቀበል ብቻ አይደለም የሚያደርገን፣ ከምንም በላይ ፍቅርን ያሳጣናል፡፡ እውቀት ያለው ሰው ምንም አይነት ማህበረሰብ ውስጥ ቢኖር ልቡ መሞቱ አይቀርም፡፡ ጊዜና ቦታ አይገድበውም፡፡ እንደኔ በጣም ፍቅር የሞላበት ህይወት፣ ልብን ለአለም ጥበብና እውቀት ከመክፈት የተነሳ ፍቅርን ማጣት አለ፡፡ የእውቀት ጥማቴ ልቤን ሲሸረሽረው፣ አስተዳደጌ ምንም ሊረዳኝ አልቻለም፡፡ ወዳጅ የሆነ ልብ ባላቸው ሰዎች ብከበብም የቀዘቀዘው ልቤ የሞቀ አቀባበል ሊያደርጉለት የተዘጋጁ ልቦች እንዳያቀልጡት ፈራ፡፡ ዘመንም አይገድበውም፡፡ ዛሬ እውቀት ከመብዛቱ የተነሳ ፍቅር ቀዝቅዛለች፡፡ እውቀት ባልበዛበት፣ አዋቂ ባልነበረበት ዘመን አዋቂ የነበረው ሰው እንኳን ግን ፍቅርን አጥቷል፡፡
በመጨረሻው ዘመን ፍቅር ትቀዘቅዛለች/ በመጨረሻው ዘመን እውቀት ትበዛለች፡፡

አንዳንዴ አንዳንድ ሰዎች በጣም ክፉ እንደሆኑ አስብና ሳገኛቸውና በጣም እኔን ለመቅረብ ጉጉ ሆነውና የነሱ ያህል ጉጉ መሆን ሲያቅተኝና በተቀራኒው እኔ ልቀርባቸው የማልፈልግ ስሆንና ተቃራኒው ሲከሰት፣ በጣም በራሴ አፍራለሁ፡፡ assumption፣ imagination፣ expectation፣ suspicion የሚባሉት ነገሮች ከመጠን በላይ ጎጂ ናቸው፡፡ በጣም ተጠራጣሪ ያደርጋሉ፡፡ እንዲህ አስቦ ነው እንዲህ ያደረገው፣ እንደዚህ ይሆናል፣ እንደዚህ ቢሆንኮ እንዲህ አይሆንም ነበር.. ልቦለድ ማንበብ ከሁሉም በላይ ለዚህ ነገር ያጋልጣል፡፡ የሌለ ነገር በአዕምሮ ውስጥ መፍጠር ነው፡፡ አዕምሮ ደግሞ ያንን ይለማመድና በእውነተኛው አለም ውስጥ የራሱን እሳቤዎች ይፈጥራል፡፡ ይሄም ማህበራዊና ግላዊ ህይወትን ይጎዳል፡፡ ይሄን የሚያመጣው ደግሞ ብዙ ማሰብ ነው፡፡ ስለ ፍቅር 1 ቆሮንቶስ 13፡7 “ሁሉን ይታገሳል፣ ሁሉን ያምናል፣ ሁሉን ተስፋ የደርጋል፣ በሁሉ ይጸናል፡፡” ይላል፡፡
አንድ ቀን አንድ ጓደኛዬ ብዙ ጊዜ እገሌ አይመቸኝም፣ እገሌ አይመቸኝም፣ እገሊት አትመቸኝም ብዬ ልጆችን ሳጣጥል፣ አንተን ግን ማነው ሚመችህ? ብሎኛል፡፡ ሰው ሁሉ ክፉ ነው፡፡ ስለ ሰው ክፋት እንከን እየፈለገ የሚያወራ ሰው ደግሞ ከሰው ሁሉ በላይ ክፉ ነው፡፡ ይሄም ብዙ የመብሰልሰል ውጤት ነው፡፡ ሰውን መውደድን ያከብዳል፡፡ ለዚህ ነው እግዚአብሔር ብዙ እንድናውቅ ያልፈለገው፡፡ ምክንያቱም እውቀትን መከተል፣ አዳምና ሔዋንን መከተል ነው፡፡ በነሱ ምክንያት ሁላችንም ወድቀነናል፡፡ እራሳችንን አውቀናል፡፡ በዚያ በነሱ ምክንያት ራስን ማወቅ ላይ የዓለምን እውቀት መከተል ግን፣ ከነሱ ጋር ማበርና እነሱን መተባበር ነው፡፡ በእግዚአብሔር ላይ ማመጽ ነው፡፡

ልብ ለአለም እውቀትና ጥበብ ሲወድቅና ብልጥግና ሲበዛ፣ ፍቅር ለመጥፋት አፍታ እንደማይፈጅበት ለመረዳት በአጭር ጊዜ ውስጥ ካደጉት ከንደነ ህንድና ቻይና አይነት ሀገሮች መረዳት እንችላለን፡፡

አንዴ በፌስቡክ አንድ ብዙ በሚሊየን የሚቆጠሩ ተከታዮች ያሉት የህንዶች ፔጅ “NOBODY CARES UNLESS YOU ARE BEAUTIFUL, POPULAR OR DEAD” የሚል ጽሁፍ ፖስት አረገ፡፡ “ቆንጆ ካልሆንክ፣ ዝነኛ ካልሆንክ ወይም ካልሞትክ በስተቀር ማንም ስላንተ ግድ አይለውም፡፡”
ከዚያ እኔ ኮሜንት ሰጠሁበት(በእንግሊዘኛ ነው የጻፍኩት)፡
“ያ በሀገሮቻችሁ ነው፡፡ በኔ ሀገር መንደሩ በሙሉ ስለናንተ ግድ ይለዋል፡፡ ስትሞቱ ብቻ ሳይሆን ስትወለዱም ጭምር፡፡ የሰፈር ሰዎች የተወለደውን ልጅና እናቱን ለመመረቅ ይመጣሉ፡፡ ከፍተኛ ማህበራዊ ህይወት ነው ያለው፡፡ ሠርግ ለሳምንት ያህል ይከበራል፡፡ ሁሉም ሰው ደስ ይለዋል፡፡ ትክክል ነው፣ ስትሞቱ ደግሞ ሁሉም ሰው ይደነግጣል፡፡ የሁሉም ሰው ፊት በእምባ ይታጠባል፡፡ እውነቱን ለመናገር እንደማነበው፣ እንደምሰማው፣ እንደማያቸው ፊልሞች፣ ፌስቡክ ላይ እንደሚለቀቁ እንዲህ አይነት ፖስቶች ከሆነ፣ በናንተ ሀገራት ውስጥ ከመኖር በኔ ሀገር መሞት ይሻላል፡፡ ሀገሬ ኢትዮጵያ ነች፡፡ ምንም የለንም ግን ፍቅር አለን፡፡ ችግሩ የኔ ሀገር ሰዎች የናንተ አድጓል የሚባል አለም ምን ያህል አስከፊ እንደሆነ አለማወቃቸው ነው፡፡ የናንተ ነገር በጣም ይስባቸዋል፡፡ እንደናንተ መሆን ይፈልጋሉ፡፡”
አንዱ “I guess I should move to your country soon. Very very soon.” ብሎ ሪፕላይ አረገልኝ፡፡ ሌላኛው ደግሞ “too much desire in materialistic pleasure in the modern world has killed all the happiness”፡፡

አያይም አይናችን
አይሰማም ጆሮአችን
ደንዝዞኣል አምሮአችን
አምጾአል ስጋችን፡፡
በእግዚአብሔር ላይ ታምጾ
አይታወቅም ሲተርፍ ታይቶ
ኪሳራ ነው ሁሌ ትርፉ
ውድቀት ነው ሽልማቱ፡፡

በእግዚአብሔር ላይ ታምጾ
አይታወቅም ሲተርፍ ታይቶ
ኪሳራ ነው ሁሌ ትርፉ
መከራ ነው ሽልማቱ፡፡

ሌላው ፍቅር የሚያሳጣው የገንዘብ ፍቅር ነው፡፡ በቃኝ የማያስብለው የገንዘብ ፍቅር፣ በስራ ስም ሌላው ቢቀር የራሳችንን ልጆች ማሳደግና ቤተሰባችንን መምራት እንዳለብን ያስረሳናል፡፡ ወጪና ገቢን በአግባቡ ለመቆጣጠርና በተቻለ መጠን ገንዘብን ለመቆጠብ ሲባል ሰውን ማራቅ የሚመጣ ከሆነ ፍቅራችን እየቀነሰ ነው ማለት ነው፡፡ አለም ቆጥብ፣ ቆጥብ ወደ ባንክ እሩጥ ትላለች፡፡ እግዚአብሔር ደግሞ ደሃውን እርዳበት፣ ሥርግ ደግስበት፣ አትሰስት፣ ጠፊ ነው፣ ስትሰጥ፣ ከላይ የማይጠፋ መዝገብ እየተሰበሰበልህ ነው ይላል፡፡ ገንዘብን ለፍቅር እንጂ ለስስት አታውለው፡፡ ይሄ አለም ጠፊ ነው፣ ስንት አመት ለምትኖረው ነው? ይላል፡፡

ክርስቶስ ኢየሱስ በምድር ላይ በተመላለሰ ጊዜ፣ አስተማሪ ነበረ፡፡ በቃና ዘ ገሊላ ከሥርግ ቤቱ የወይን ጠጅ ሲያልቅ ክርስቶስ ስድስት ጋን ውሃ ወደ ወይን ጠጅ መቀየሩ የተጻፈውኮ ስለ ተአምራቱ ብቻ አይደለም፡፡ ክርስቶስ እንደኛ የድግስ ተቃዋሚ ቢሆንኮ እንደ አስተማሪነቱ፣ ቤተ መንግስቱ ውስጥ እንዳደረገው፣ ሥርግ ምን ያደርጋል? ብራችሁን አትቆጥቡም፣ እስካሁን የተጠጣው ራሱ አልበዛም? በገሰጻቸው ነበር፡፡ የአልአዛር ሞት ታሪክኮ ለተአምራቱ ብቻ አይደለም የተጻፈልን፡፡ እኛ እግዚአብሔር ያለው ሆነ፣ ማልቀስ አያስፈልግም እንደምንለው አጉል ፍልስፍና ሳይሆን በዮሐንስ ፲፩:32-33 “ማሪያምም ኢየሱስ ወዳለበት መጥታ ባየችው ጊዜ በእግሩ ላይ ወድቃ፡- ጌታ ሆይ፣ አንተ በዚህ ኖረህ ብትሆን ወንድሜ ባልሞተም ነበር አለችው፡፡ ኢየሱስም እርስዋ ስታለቅስ ከእርስዋም ጋር የመጡት አይሁድ ሲያለቅሱ አይቶ በመንፈሱ አዘነ በራሱም ታወከ፣ ወዴት አኖራችሁት? አለም፡፡ እነርሱም ጌታ ሆይ፣ መጥተህ እይ አሉት፡፡ ኢየሱስም እምባውን አፈሰሰ፡፡” ተብሎ እንደተጻፈልን ሳይሆን ያለቀሱትን በገሰጻቸው ነበር፡፡ እርሱ ግን የፍቅር አምላክ ነው፡፡ ሩህሩህ ልብም ነበረው፡፡

ፍቅርን የሚያጠፋ ነገር ይጥፋ፣ ፍቅርን የሚቀንስ ነገር ይጥፋ፣ ፍቅርን የሚያጎድል ነገር ይጥፋ፣ ፍቅርን የማይጨምር ነገር ይጥፋ፡፡

አንድ ልጅ ተወለደ፣ ት/ቤት ይገባል፣ ፊደል ይቆጥራል፡፡ እውቀትን መቃረም ይጀምራል፡፡ አንድ የአምስት ወይም የስድስት አመት ህጻን፣ ጠዋት ቁርሱን በልቶ ትምህርት ቤት ይሄዳል፡፡ ከዚያ ከወላጆቹ ጋር የሚገናኘው ማታ ነው፡፡ ማታ የቤት ስራ ያሰሩታል፣ ቲቪ አለ፣ ፊልም አለ እንደዚያ እንደዚያ እያለ ራሱን እያወቀ ይመጣል፡፡ ትምህርት ቤት መሄድ፣ ከትምህርት ቤት መግባት፣ መደንዘዝ፡፡ 4ኛ ክፍል ላይ ሳይንስ ስለ ጾታ ያስተምራል፡፡ ስለ ፒዩበርቲ፡፡ ይሄ ትምህርት አንድ ሰው ስለሚገጥመው እድገቶች ያስተምራል፡፡ አስተማሪው ሲያስተምር ተማሪዎች ያፍራሉ፡፡ አስተማሪው ሳይንስ የሚያሳፍር ነገር የለውም ይላቸዋል፡፡ በዚህ ዘመን ወላጆች ስለ እንደዚህ አይነት ጉዳዮች ከልጆቻቸው ጋር በግል ጽ እንዲመካከሩ ይመከራል፡፡ ተፈጥሮአዊ ነገር ነው፣ የሚያሳፍር ነገር የለውም… ተፈጥሮአዊ ነገር ከሆነ ታዲያ ሰዎች ለምን ያፍራሉ? ዘመናዊ ስላልሆኑ ነው? እንዲህ አይነት ጉዳዮች ድሮ ተፈጥሮአዊ አልነበሩም? ስለ ጾታዊ ነገሮቻችን በግልጽ ማውራት ምንም መንፈሳዊ ፋይዳ የለውም፡፡ ግዴታ እስካልሆነ ድረስ፡፡ አዳምና ሄዋን ያቺን የእውቀት ፍሬ ሲበሉ ራቁት እንደሆኑ አውቀው ተፋፈሩ፡፡ የመጀመሪያው ሃጢአት፡፡ ማወቃቸውና መተፋፈራቸው በሰሩት ሃጢአት ምክንያት ነው፡፡ መተዋወቃቸው ክፉ ነው፡፡ መተፋፈራቸው ግን መልካም ነው፡፡ ህጻናት አዳምና ሄዋን ከፍሬዋ በፊት እንደነበሩት ናቸው፡፡ ሲያድጉ መተዋወቅና መተፋፈር ይጀምራሉ፡፡ አዳምና ሄዋን ያፈሩት ሃጢአት ሊታፈርበት የሚገባ ነገር ስለሆነ ነው፡፡ ህጻናትም እርኩሰት በሃይል በሚደገፍበት ሁኔታ ውስጥ እያደጉ እንኳን ሲያድጉና ወጣት እየሆኑ ሲመጡ ሃፍረት ይሰማቸዋል፡፡ አዲስ በሚያስተናግዷቸው ስሜቶች ያፍራሉ፡፡ ታዲያ የ4ኛ ክፍል የሳይንስ ካሪኩለም፣ ወደዚህ እድሜ እየተጠጉ ያሉትን ልጆች በመምህራን በኩል፣ የህይወት አንድ አካል ነው፣ የሚያሳፍር ነገር የለውም፣ አትፈሩ ይላቸዋል፡፡ ተማሪዎችም ይሄ የህይወት ክፍል ነው፣ ተፈጥሮ ነው፣ ብለው ለሚሰማቸው ስሜት መልስ ለመስጠት አያፍሩም፡፡ ይሄ እድሜ ፋየር ኤጅ ይባላል ይባላሉ፡፡ ከቤተሰብ ጋር በግልጽ ማውራት የሚሉት የዘመናችን ፈሊጥ ደግሞ ልጆችን መረን እንደ መልቀቅ ነው፡፡ ወላጅ ልጆች ለዚህ እድሜ ሲደርሱ ወንበር መዞ፣ የራሱን የዚያን እድሜ ታሪክ መተረክና ስለ ተፈጥሮአዊነቱ መናገር ሳይሆን ያለበት፣ ህጉን ማጥበቅ ነው፡፡ ልጆቹን በአይነቁራኛ መከታተል፡፡ እንዲጾሙና እንዲጸልዩ መምከር፡፡

ከዚያ ኢቮሊሽን ቲዮሪ፣ ሆሞ ሳፒየንስ ምናምን፡፡ እንደዚያ ነው ልጆቻችንን ማሳደግ የምንፈልገው? ውሸት እያስተማርን? ዝንጀሮ ናችሁ፣ እግዚአብሔርና ትእዛዛቱ የሉም እያልን? ከእግዚአብሔር መንግስት የሚያጎድል ትምህርት ቢቀርባቸው አይሻልም? እንደ እግዚአብሔር ቃል እያሳደግን ፍሬን የሚያፈሩ እንዲሆኑ ብናደርግ አይሻልም?

ዩኒቨርሲቲ ወጣቶችን በሃጢአት ውስጥ ለመዝፈቅ ሰይጣን የፈጠረው ዘዴ ነው፡፡ አንድ ሰው በቤተሰቡ፣ በዘመዶቹና በሚያውቁት ሰዎች ተከቦ እንጂ መኖርና ማርጀት ያለበት፣ ማንም አያውቀኝም፣ እንደፈለግኩ እኖራለሁ በሚልበት አይደለም፡፡ በዚህ ዘመን ግን ለልጆች ዩኒቨርሲቲ የሚገቡበትን ጊዜ ሲያልሙ ነው የሚኖሩት፡፡ ምክንያቱም ነጻ ሆነው እንደፈለጉ ይሆናሉ፡፡ ልጃገረድ እንዴት ማንም በማያውቃት ሀገር እንዲሁ ትተዋለችም ይሄም ውድቀት ነው፡፡ በዚያ ላይ በየዩኒቨርሲቲው አቅራቢያ ጭፈራ ቤቶችና የቢራ ፋብሪካዎች እየተከፈቱ ነው፡፡

መተዋወቅና መፈላለግ፣ ሰይጣን አዳምና ሔዋንን ካሳሳተ በኋላ የመጣ ነገር ነው፡፡ የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም፡፡ ስለዚህም ሃጢአት ነው፡፡ ራቁት እንደሆንን መተዋወቃቅ አልነበረብንም፡፡ ልንተፋፈርበት ግን ይገባናል፡፡ አለማፈር ወይም ልቅ ሆኖ ሳያፍሩ ስለንደዚህ አይነት ጉዳይ ማውራት ግን አዳምና ሔዋንን መተባበር ነው፡፡ ራቁት ሳያፍሩ እየተገላለጡ መሄድም እንደዚያው ከአዳምና ከሔዋን ጋር ማበር ሲሆን

አመጻ ነው፡፡ ጳውሎስ ብትችሉ እንደኔ ብቻችሁን ሁኑ፣ በፍትወት ከመቃጠል ግን አግቡ ይላል፡፡ መተዋወቅና መተኛት የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም፡፡ ነገር ግን ሰው ስለማይቻለው ብቻ ነው እግዚአብሔር ጋብቻን ለሰው የመሰረተው፡፡ ከጋብቻ ውጪ የሚደረግ ዝሙትና ማመንዘር ግን አሁንም አመፃ ሲሆን ትልቅ ሃጢአት ነው፡፡ ጋብቻ ደግሞ በቀጥታ ከዘፍጥረትና ከክርስቶስና ከቤተ ክርስትያን ጋር እንደሚገናኝ ቃሉ ይናገራል፡፡

ት/ቤት ግን ኮንዶም ስለመጠቀምና ስለ ወሊድ መቆጣጠሪያ እንጂ ስለ ትዳር የሚያስተምር ክፍል የለም፡፡ በአለም ጥበብ፣ ትዳር ሞኝነት ነው፡፡ ለሚድኑት ግን እግዚአብሔር በጥበብ የመሰረተው ትልቅ ሚስጥር ያለበት ተቋም ነው፡፡

ት/ቤት የማንግራቸውና ሎጂክ ወይም አመንክዮ ሊያብራሯቸው የማይችሏቸው ብዙ ነገሮች አሉ፡፡ ለምሳሌ እግዚአብሔርና መንፈሳዊ ነገሮች፡፡ ሰው ት/ቤት ገብቶ በምክንያትና በምክንያት ላይ ብቻ የተመሰረቱ ቲዮሪዎችን ለአመታት ሲማርና አዕምሮው በምክንያታዊነት በማሰብ ሲሰለጥን፣ ሁሉንም ነገር ወዶም ባይሆን በምክንያት ሚዛን ላይ ማስቀመጥ ይጀምራል፡፡ ታዲያ እነዚህን በምክንያታዊነት ሊደርስባቸው የማይችላቸውን ነገሮች መርምሮ መርምሮ፣ ሊያረጋግጥ እንደማይችል ወይም እንደማይቻል ሲረዳ ምክንያት የሌለውን፣ ከአእምሮ በላይ የሆነውን ይሄን ነገር፣ ሞኝነት አድርጎ ማሰብ ይጀምራል፡፡ ትልቁ ነገር ትንሽ፣ ትንሹ ነገር ትልቅ ይሆንበታል፡፡ ያ ነው ህጻናትን ት/ቤት የማስገባትና ምሁራን የማድረግ አደጋ፡፡
የአንደኛ ክፍል ሳይስ ትምህርት የሰው መሰረታዊ ፍላጎቶች ምግብ፣ ልብስና ቤት ናቸው ይላል፡፡ ጠቢብ ወላጅ ግን ከምግብ፣ ከልብስና ከቤት በላይ የእግዚአብሔር መንፈስ እንደሚያስፈልግ ልጆቹን ያስተምራል፡፡

ትምህርት ቤት፣ የሰው መንፈስ የሚገደልበት ቦታ ነው፡፡ ነፍስ ባልተጠራችበት በአለም ዝባዝንኪ ውስጥ የምትሰምጥበትና እንድትጠፋ የምትበረታታበት፣ ስጋዊነት በሰው ውስጥ እንዲነግስ ከህጻንነት ጀምሮ የሚኮተኮቱበት ስፍራ ነው፡፡

ትምህርት ቤት ይሉታል ስሙን አሳምረው
ወይ ትምህርት ቤት ድንቄም ትምህርት ቤት
ወይ ከርቸሌ፣ የዘመኑ እስር ቤት፡፡
እንዲህ ያዜማል ያላስተዋለ
የትምህርትን ጉዳት ልብ ያላለ፡
"ተማር ልጄ፣ ተማር ልጄ
ወገን ዘመድ ሀብት የለኝ ከእጄ
ያልተማረ ሰው ቀኑ ጨለማ ነው"
ብሎ ያዜማል ያላስተዋለ፣
የሰይጣንን ምርት ጉዳት ልብ ያላለ፡፡

"ጢሞቴዎስ ሆይ እውቀት ከተባለ ለዓለም ከሚመች ከከንቱ መለፍለፍና መከራከር እየራቅህ፣ የተሰጠህን አደራ ጠብቅ፡፡" 1 ጢሞቴዎስ 6፡20፡፡

ወሬው ሁሉ ኢኮኖሚ፣ የሀገር ፍቅር፣ ዴሞክራሲ በሆነበት ዘመን ሰይጣን ገንዘብ ከቤተሰብ፣ ከሃይማኖት፣ ከፍቅር እንደሚበልጥ ሲሰብከን ይውላል፡፡ እድገት ልማት ስንል ትውልድ እያመለጠ ነው፡፡ እግዚአብሔር ጠቃሚ ያለው ጎጂ፣ ጎጂ ያለው ደግሞ ጠቃሚ ሊሆኑ ከቶ አይችሉም፡፡ ከኢኮኖሚ በላይ ፍቅር አስፈላጊያችን እንደ ሆነና ኢኮኖሚ ከንቱ እንደሆነ ልንነቃ ይገባል፡፡ አንባቢ ሆይ ኢኮኖሚና ፍቅርን ምን አገናኛቸው ብለህ ይሆናል፡፡ ነገር ግን አንዱ ሲያድግ ሌላኛው የሚጠፉ ነገሮች እንደሆኑ ነው ያለን የሀገራትና የታሪክ መረጃ እንዲሁም የእግዚአብሔር ቃል እንደ ማስረጃ የሚያመለክቱት፡፡

ሰይጣን ቴክኖሎጂን ለሁለት ነገሮች ይጠቀምበታል፡፡ መጀመሪያ ሰዎችን አራርቆ፣ ፍቅርን ያቀዘቅዝበታል፡፡ ሁለተኛ የጥፋት ዶክትሪኑን ያራምድበታል፡፡ ሰው ይሄን ነገር ተው ተባብሎ እንዳይገሳጸጽ እንኳን ሁሉም በግል ስለሆነ፣ ሰው የሚጠፋበት መንገድ በገፍ የተዘረጋለትና የሚጓዝበት በግሉ ስለሆነና ለሁሉም ስለሆነ ሁሉም ተያይዞ ይጠፋል እንጂ የሚመለስ ሰው አይኖርም፡፡

You want to resist it, avoid it. ልንቋቋመው ከፈለግን፣ እንተወው፡፡ ሰዎች ሰይጣን ሲወጣ ለማየት ቴሌቪዥናቸው ላይ ሲያፈጡ ይውላሉ፡፡ ዋናው ሰይጣን ቴሌቪዥናቸው እንደ ሆነ ያልገባቸው ሰዎች፡፡ እውነተኛው ሰይጣን በቲቪ ኢንተርቪው ሚደረግለት ሰይጣን ሳይሆን ስንቱ በረሃብ በሚሰቃይበት ሀገር ገንዘብ አውጥተን የገዛነውና ቤታችን ውስጥ ያስቀመጥነው ቲቪው ራሱ ነው፣ ስልካችን ነው፣ ትምህርት ነው፡፡ ከዚያ የሚያወጣን ነቢይ ደግሞ የለም፡፡ ሰይጣን ወደ ሲኦል ይዞ ትውልድን ወደ ገደል እያገባበት ያለውን የሰይጣን ምላስ የሆነውን ቴክኖሎጂ ሁሉ እምቢ ብለን ፊታችንን ወደ እግዚአብሔር መመለስ አለብን፡፡ ሰይጣን ከእውነቱ ሊያርቀን፣ በክርስቶስ ስም አጋንንትን ማውጣት ብቻ ሳይሆን ክርስቶስ ነኝ ብሎ የሚያሳስትበት ጊዜ ይመጣል፡፡ ቤታችን ሲጸዳ በሽታውም አይኖርም፡፡ የሚያሰናክለንን ሁሉ ከቤታችን፣ ከሰውነታችን ውስጥ አስወጥተን ጤናማውንና የህይወት መንገድ የሆነውን ስንከተልም እየተቀላቀለ የሚረብሸን የኤሌክትሮኒክስ ጫጫታ አይኖርም፡፡

እንዴት መልካሙን ክፉ እንዲመስለን ማድረግ እንደሚችሉ ያውቁበታል፡፡ እንዴት ክፉውን ነገር መልካም እንደሆነ አድርገን እንድናስብ ማድረግ እንደሚችሉ ያውቁበታል፡፡

እንደ አንድ ሰው ሲታሰብ ይከብዳል፡፡ እንደ ብዙ ሰዎች ሀሳብ ሲታሰብ፣ በተለይ ክርስቶስ እንደ መሰረታትና ሐዋርያት እንዳስተላለፉልን ቤተ ክርስትያን ሲታሰብ ግን ሁሉም ነገር ይቻላል፡፡

ጥያቄዬ ልጆቻችን ስለ አለም ትምህርት ቤት እንደሚሰሙት እየሰሙ እንዲያድጉ ነው ወይ የምንፈልገው? የሚል ነው፡፡ ስለ ክርስትና ፊልም እንደሚያስተምረው እየተረዱ እንዲያድጉ ነው ወይ የምንፈልገው? ነው፡፡ ስለ አለም ፌስቡክ እንደሚለው እየተረዱ እንዲያድጉ ነው ወይ? ስለ አለም ከትምህርት ቤት፣ ከፊልምና ከኢንተርኔት እንዲረዱ ነው የምንፈልገው ወይስ ከእግዚአብሔር ቃል ብቻ? የኛ ሞኝነት በኛ ላይ ይቁም እንላለን ወይስ ወደ ልጆቻችን እናስተላልፈዋለን? ቀላል አይደለም፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር እንኳንስ የመረጡትን፣ የመረጣቸውንም አላሳፈረም፡፡ ማድረግ ያለብን ቀጣዩን ትውልድ በቴክኖሎጂ ማደንዘዝ ወይም ለዚህ አለም ከንቱ ትምህርትና ገንዘብ ማመቻቸት ሳይሆን የአለምን ጥበብና ገንዘብ የናቀ፣ ጥበቡም መዝገቡም ከሰማይና ሰማይ ላይ የሆነ እግዚአብሔርን የሚፈራ ትውልድ ማፍራት ነው፡፡ ለቀጣዩ ትውልድ መታነካ ነው ወይስ መሰናከያ ነው መሆን የምንፈልገው?
እንደ አቴና ሰዎች አዲስ ነገር ከማወቅ በቀር በሌላ ጉዳይ የማይውሉ(የሐ/ስራ 17፡21) ልጆች ወይስ እንደ ጢሞቴዎስ ከሕጻንነታቸው ጀምረው ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን፣ መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡ የሚችሉትን ቅዱሳን መጻሕፍት የሚያውቁ(2 ጢሞ.3፡15) ልጆች?

ያኔ ማታ መብራት ይጠፉ ያልነበረ ቢሆን፣ ቲቪ ላይ ስናፈጥ፣ አባትና እናቴ እነኛን ደስ ደስ የሚሉ፣ የድሮ ትዝታዎቻቸውን ባላካፈሉንና ቤታችን በቤተሰባዊ ስሜት ባልተሞላ ነበር፡፡ ያኔ የመብራት ሃይል ሰራተኞችን በጣም እንድንራገም ያደረገን ቢሆንም፣ ገመና ድራማ ላይመሰረት መብራቴ፣ ሳምሶን ታደሰን በጥፊ ስትመታው፣ እንኳንም መብራቱ ድርግም አለ፡፡ ምክንያቱም እንደዚያ ባይሆን በህይወቴ የማልረሳው ገጠመኝ ቀርቶ ያን ቀን የነበረው ታሪክ ሌላ ይሆን ነበር፡፡ እንኳንም ከልጆች ጋር ጭቃ ውስጥ ሸርተቴ ተጫወትኩና ወድቄ ልብሴ ጭቃ በጭቃ ሆነ፣ እንኳንም [የህጻንነት] ትዝታዬ በፊልም ላይ የማያቸው አዝናኝ ግድያዎች፣ የቶም ኤንድ ጄሪ ካርቱኖችና ቴሌቪዥን ላይ የሚታዩ ብዙ ሌላ ነገሮች አልሆኑ፡፡ እንኳንም እኔ ስወለድ ቲቪ አልነበረን፣ እንኳንም፣ እስከ 1999 ድረስ ዲቪዲ አልተገዛልን፣ እንኳንም 9ኛ ክፍል እስከገባ ከቤት ዲሽ አንገዛም አሉኝ፡፡ ካላወቅክ መኖር አትችልም መባል በሌለበት፣ ስልክ በሌለበት፣ ኢንተርኔት በሌለበት፣ ቲቪ በሌለበት፣ ኮምፒዩተር በሌለበት፣ ቴክኖሎጂ በሌለበት ቦታና ጊዜ ተወልጄ ብኖርና ብሞት ደስታዬ ነበረ፡፡ ምክንያቱም እንደዚያ ቢሆን ቢያንስ ሀዘንተኛ፣ ጭንቀታም፣ ተጠራጣሪ፣ ፍቅር የሌለውና ገንዘብና ምቾት ወዳድ ሰው ሳይሆን፣ ሩህሩህ፣ ሰው የሚወድ፣ ፍቅር የሞላው፣ እግዚአብሔር የሚወደው አይነት ሰው እሆን ነበር፡፡

The most expensive present you can ever give to your children is, teaching them the true and the uncorrupted word of God.
በጣም ውዱ ለልጅህ ልትሰጥ የምትችለው ስጦታ፣ የሚጠፉ ሰዎች ያልሸቃቀጡትን እውነተኛውን የእግዚአብሔር ቃል ማስተማር ነው፡፡ ነፍሳቸውን መታደግ፡፡ "ሰው ዓለምን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋል?" ይላልና ቃሉ፡፡

የእግዚአብሔር ቃል ስለ ንስሃና ስለ እግዚአብሔር ይቅር ባይነት

"በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው፡፡" 1 ዮሐንስ 1፡9፡፡

"እንግዲህ ከጌታ ፊት የመጽናናት ዘመን እንድትመጣላችሁ አስቀድሞም ለእናንተ የመረጠውን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲልክላችሁ፣ ኃጢአታችሁ ይደመሰስ ዘንድ ንስሐ ግቡ ተመለሱም፡፡" የሐዋርያት ሥራ 3፡19-20፡፡

"ኑና እንወቃቀስ ይላል እግዘአብሔር ፡፡ ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን እንደ አመዳይ ትነጻለች፡፡ እንደ ደምም ብተቀላ እንደ ባዘቶ ትጠራለች፡፡" ኢሳያስ 1፡ 18

"በዚያ ጊዜ፡- እነሆ በመጽሐፍ ጥቅልል ስለ እኔ እንደ ተጻፈ፣ አምላኬ ሆይ፣ ፈቃድህን ላደርግ መጥቼአለሁ አልሁ ይላል፡፡ በዚህ ላይ፡- መሥዋዕትን አልወደድህም በእርሱም ደስ አላለህም ብሎ፣ እነዚህም እንደ ሕግ የሚቀርቡ ናቸው፡፡ ቀጥሎ፡ እነሆ አምላኬ ሆይ፣ ፈቃድህን ላደርግ መጥቼአለሁ ብሎአል፡፡ ሁለተኛውንም ሊያቆም የፊተኛውን ይሽራል፡፡ በዚህም ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋ አንድ ጊዜ ፈጽሞ በማቅረብ ተቀድሰናል፡፡ ሊቀ ካህናትም ሁሉ ዕለት ዕለት እያገለገለ ኃጢአትን ሊያስወግዱ ከቶ የማይችሉትን እነዚያን መስዋዕቶች ብዙ ጊዜ እያቀረበ ቆሞአል፡፡እርሱ ግን ስለ ኃጢአት አንድን መሥዋዕት ለዘላለም አቅርቦ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀመጠ፡፡ ጠላቶቹም የእግሩ መርገጫ እስኪደረጉ ድረስ ወደ ፊት ይጠብቃል፡፡ አንድ ጊዜ በማቅረብ የሚቀደሱትን የዘላለም ፍጹማን አድርጎአቸዋልና፡፡ መንፈስ ቅዱስም ደግሞ ስለዚህ ይመሰክርልናል፡፡ ከዚያ ወራት በኋላ ከእነርሱ ጋር የምገባው ኪዳን ይህ ነው ይላል ጌታ፡፡ **በልባቸው ሕጌን አኖራለሁ በልቡናቸውም እጽፈዋለሁ ብሎ ከተናገረ በኋላ፣ ኃጢአታቸውንና ዓመጻቸውን ደግሜ አላስብም ይላል፡፡ የእነዚህም ስርየት ባለበት ዘንድ፣ ከዚህ ወዲህ ስለ ኃጢአት ማቅረብ የለም፡፡** እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፣ በመረቀልን በአዲስና በሕያው መንገድ ወደ ቅድስት በኢየሱስ ደም በመጋረጃው ማለት በሥጋው በኩል እንድንገባ ድፍረት ስላለን፣ **በእግዘአብሔርም ቤት ላይ የሆነ ታላቅ ካህን ስላለን፣** ከክፉ ሕሊና ለመንጻት ልባችንን ተረጭተን፣ ሰውነታችንንም በጥሩ ውሃ ታጥበን በተረዳንበት እምነት በቅን ልብ እንቅረብ፡፡ የተስፋን ቃል የሰጠው የታመነ ነውና እንዳይነቃነቅ የተስፋችንን ምስክርነት እንጠብቅ፡፡ ለፍቅርና ለመልካምም ሥራ እንድንነቃቃ እርስ በርሳችን እንተያይ፡፡ በአንዳንዶችም ዘንድ ልማድ እንደ ሆነው፣ መሰብሰባችንን አንተው፡፡ እርስ በርሳችን እንመካከር እንጂ፣ *ይልቁንም ቀኑ ሲቀርብ እያያችሁ አብልጣችሁ ይህን*

ሊደርጉ፡፡ የእውነትን እውቀት ከተቀበልን በኋላ ወደን ኃጢአት ብናደርግ ከእንግዲህ ወዲህ ስለ ኃጢአት መስዋዕት አይቀርልንምና፡፡ የሚያስፈራ ግን የፍርድ መጠበቅ ተቃዋሚዎችንም ሊበላ ያለው የእሳት ብርታት አለ፡፡ የሙሴን ሕግ የናቀ ሰው ሁለት ወይም ሦስት ቢመሰክሩበት ያለ ርኅራኄ ይሞታል፡፡ የእግዚአብሔርን ልጅ የረገጠ ያንንም የተቀደሰበትን የኪዳኑን ደም እንደ ርኩስ ነገር የቆጠረ የጸጋውንም መንፈስ ያክፋፋ፣ እንዴት ይልቅ የሚብስ ቅጣት የሚገባው ይመስላችኋል? በቀል የእኔ ነው፣ እኔ ብድራትን እመልሳለሁ ያለውን እናውቃለንና፡፡ ደግሞም ጌታ በሕዝቡ ይፈርዳል፡፡ በሕያው እግዚአብሔር እጅ መውደቅ የሚያስፈራ ነው፡፡ ነገር ግን ግማሽ በነቀፋና በጭንቅ እንደ መጫወቻ ስለ ሆናችሁ ግማሽም እንዲህ ካሉት ጋር ስለ ተካፈላችሁ፣ ብርሃን ከበራላችሁ በኋላ መከራ በሆነበት በትልቅ ተጋድሎ የጸናችሁበትን የቀደመውን ዘመን አስቡ፡፡ የሚበልጥና ለዘወትር የሚኖር ገንዘብ በሰማይ ራሳችሁ እንዳላችሁ አውቃችሁ፣ በእስራቴ ራራችሁልኝ፡፡የገንዘባችሁንም ንጥቂያ በደስታ ተቀበላችሁ፡፡ እንግዲህ ታላቅ ብድራት ያለውን ድፍረታችሁን አትጣሉ፡፡ የእግዚአብሔርን ፈቃድ አድርጋችሁ የተሰጣችሁን የተስፋ ቃል እንድታገኙ መጽናት ያስፈልጋችኋልና፡፡ ገና በጣም ጥቂት ጊዜ ነው፣ ሊመጣ ያለውም ይመጣል አይዘገይምም፡፡ ጻድቅ ግን በእምነት ይኖራል ወደ ኋላም ቢያፈገፍግ፣ ነፍሴ በእርሱ ደስ አይላትም፡፡ **እኛ ግን ነፍሳቸውን ሊያድኑ ከሚያምኑቱ ነን እንጂ ወደ ጥፋት ከሚያፈገፍጉ አይደለንም፡፡"** ዕብራውያን 10፡7-39

ማጠቃለያ

"የሚሰማኝ ግን በእርጋታ ይቀመጣል፣ ከመከራም ሥጋት ያርፋል፡፡" ምሳሌ 1፡33

ይሄ ትውልድ በዚህ ጊዜ ቸል ቢል፣ ዕረፍትና መዳን ለኢትዮጵያ ከሌላ ትውልድ ይሆንላታል፡፡ ይሄ ትውልድ ግን ይጠፋል፡፡ ደግሞስ ይሄን የአሁኑን የኢትዮጵያ ትውልድ እግዚአብሔር በአርበኞች በኩል በታላቅ ደም መፋሰስ ሁለቴ ከፈረንጅ ስልጣኔ ያስጣላትና ያስመለጣት፣ በምክንያት እንደሆነ ማን ያውቃል?

ሰው በምኞቱና በአታላይ መናፍስት ተመርቶ ካየው ራዕይ ይልቅ ዳዊት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የጻፈው የእግዚአብሔር ትንቢት እንደሚፈጸም አምናለሁ፡፡

በእውነት አሳድገን ጌታ ሆይ በፍቅር
በከንቱ መታበያችን ይቅር
በእውነት አሳድገን ጌታ ሆይ በፍቅር
በክርስትናችን እድሜ ቆጥረን
በልምምዳችን ኮርተን
በትህትና መማሩ ቀረና
እድገታችን ቆመ ታበይንና...

"ለአንዳንዶች እንደሚመስላቸው ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም፡፡ ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል፡፡" (2 ጴጥሮስ 3፡9) ጌታ እየታገሡን ነው፡፡

...ዓይን ያላየችው ጆሮም ያልሰማው በሰውም ልብ ያልታሰበው **እግዚአብሔር ለሚወዱት** ያዘጋጀው...
...Eye hath not seen, nor ear heard, neither have entered into the heart of man, the things which God hath prepared **for them that love him.**

የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ!

- ተፈፀመ -

ውድ አንባቢ፣ የዚህን መጽሐፍ ሀሳብ በትክክል እንድትረዳ፣ እኔ የዚህ መጽሐፍ ጸሀፊ፣ ይሄን መጽሐፍ እንደገና እንድታነበው በትህትና እጋብዝሃለሁ፡፡

ምዕራፍ አራት፡ በውሸት የተሞላ ሕይወት…

Back cove

“ሕዝቤ እውቀትን ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቶአል፡፡…” ትንቢተ ሆሴዕ 4፡6፡፡ ይሄን መጽሐፍ የጻፍኩት፣ እኔ ያጣሁትን እውቀት ይሄኛውና የሚመጣው ትውልድ እንዳያጣና የማይናወጠው፣ የሚጠቅመው እውቀት የትኛው እንሆነ እንዲለይ ነው፡፡

አንባቢ ሆይ ይህ መጽሐፍ የተጻፈው የማታውቀውን አዲስ ነገር እንድታውቅ አይደለም፡፡ የምታውቀውን ነገር እንድታነብም አይደለም፡፡ እውነትን እንድትለያት፣ እንድትመረምራትና እንድታስተውላት፣ አስተውለህም እንድትኖራት ብቻ እንጂ፡፡

ሎጂክ መጥፎ ነገር ነው፡፡
ይሄን መጽሐፍ የጻፍኩት የእግዚአብሔር መለኮታዊ ሃይል ገልጦልኝ ነው ብዬ ለማለት አልደፍርም፡፡
ይሄን መጽሐፍ በሎጂክ ነው የጻፍኩት፡፡
የኔን ሎጂክ ትክክልና እውነት የሚያደርገው ግን፣ የእግዚአብሔርን ቃል ከኖርኩትና ካየሁት የህይወት ተሞክሮዬና አለም ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ከነበራት ግንኙነት ታሪክ ጋር በማዋዛት የሎጂክን ክፋት ስለሚያብራራ ነው፡፡ እኔ የምቃወመውና ክፉነቱን ላጋልጥ የሞከርኩት ሎጂክም፣ እግዚአብሔር ሽሹት ያለው ሎጂክ፣ ራሱ ነው፡፡ My logic is right because it proves logic is wrong.